101

ገመዱ

ከሰለሞን ለማ



ጎሚ

(ልቦለድ)

መጻሕፍት ከአልማዝ የሚበልጡ ስጦታዎች ናቸው።
Books Are Gifts More Precious Than Jewels
ሰለሞን ለማ
ስጦታውን ያበረከቱት/Donated By

አበበ አበሸረ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
፲፱፻፹፬

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
KURAZ PUBLISHING AGNECY

ስልክ } 11 27 19
Tel

ፖ.ሣ.ቁ } 30933
P.O.Box

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Addis Ababa
Ethiopia

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

የሽፋን ሥዕል ሉቃስ አማረ

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ

ምዕራፍ አንድ

ክረምትና አዲስ አበባ አልሀ የተጋቡ ይመስላል ፡ የሌተቱን የአለትሀም ፡ ግብግብ ። ሐምሌና ነሐሴን ሙሉ አዲስ አበባን የሙጥኝ ብሎ የከረመው ዝናብ መስከረም ሲጠባም አገረሽበትና አዲስ ገቢ ክረምት መስሎ ቁጭ አለ ። መጀመሪያ የአዲስ አበባን ሰማይ በስስ የጉም ሻሽ ይጋርደዋል ፡ ቀጥሎ የደመና ሸማ ያከናንበዋል ። ከሸማው በላይ ነጭ የጥጥ ክምር መስል ደመና ይቆልልበትና አዲስ አበባንና ፀሐይን ያኮራርፋቸዋል ። የደመናው ሸማና ጥጡ መ ልካቸው እየ[illegible]ጠ አዲስ አ[illegible] የጨለመች ፀደይ ማየት ሲሳነው የዝናቡን ሲምባ ከላዩ ይለቅባታል ። ሁለትና ሦስት ሰዓት አከታትሎ ይደበድባታል ። እየፎከረ ፡ ከበሮውን እየደለቀ ፡ መድፉን እየተኮሰ ፡ ርችቱን እያንበገበገ ፡ "ጉድ ነው የዘንድሮ ክረምት" እስኪባል ድረስ ።

እኝኝ ሲል የዋለው ዝናብ የልቡን አድርሶ ዘወር ሲል ፡ ረጭ ብሎ የቆየው የአዲስ አበባ ሕይወት ነፍስ ዘርቶ መላወስ ይጀምራል። አራት ኪሎ ደመና በዞረ ፡ ባከፋና በዘነመ ቁጥር ቀዝቀዝ ትላለች ። ፀሐይ የደስ ደስ ብርሃኗን ስትፈነጥቅ ከየጉሬው የሚወጣው ሕይወት የትርዒት መድረክ ያደርጋታል ። የመንገድ ዳር ትርዒት ፡ ተመልካቹ ተዋናይ መልሶም ተመልካች የሚሆንበት ልዩ ትርዒት ።

ሠራተኛው ወደ ምሳው ሲሠማራ የጀመረው ዶፍ ዝናብ ፡ አራት ኪሎን አጠገበና ዘወር ሲል በየታዛው ተጠልሎ የነበረው ሁሉ ከተደበቀበት ወጣና መንገዱን ሞላው ። እና የነበረው

የትርዒት መድረክ በተመልካቾችም በተዋንያንም ተሞላ ። አራት ኪሎ መልሳ ነፍስ ዘራች ። ገና ወደ ምሳው የሚሔደው ከምሳው ወደ መሥሪያ ቤቱ የሚመለሰው ፡ ወደ ትምህርት ቤት ፡ ወደ ሆስፒታል ፡ ወደ ፍርድ ቤት የሚገሠግሠው ፡ ጠጥቶ ጠግቦ ወይም ተምሮ የሚወጣው ፡ ገና ሊጠጣ የሚጣደፈው ፡ ዘመድ ጥየቃ የሚሮጠው ፡ የዕለት ጉርሱን ለመያዝ የሚባክነው ፡ እግሩ እያደረሰበት ውሎ እቤቱ ለመመለስ የሚንከራተተው ፡ ለንግድ የተሠማራው ፡ ወፈፌው ፡ የለየለቱ ዕብድ ፡ ደንደስ መችው … ሁሉም በየፈናው ወዲያ ወዲህ ይርመሰመሳል ፡ ከዝናቡ ጋር የድብብቆሽ ጨዋታ ይጫወት ይመስል ። አሮጊት ፡ ሽማግሌ ፡ ወጣት፡ ሴት ፡ ወንድ ፡ ትንንሽ ልጆች ሁሉም አራት ኪሎን አድምቀዋታል ። ሁሉም ይርመሰመሳል በግራም በቀኝም ።

በየመንገዱ ዳር ዳር አልፈው አልፈው የሚታዩት ትንንሽ ሐይቆች መልሰው በሚያንጸባርቁት የፀሐይ ጨረር የአላፊ አግዳሚውን ዐይን እየወጉ አስቸግረዋል ። የሌላው ችግር የሚያስታቸው ጉረምሳ ባለመኪናዎች ወደ መንገዱ ዳር መኪናቸውን ያሽከረክሩና እትንንሾቹ ሐይቆች ውስጥ ገብተው ፈትለክ ይላሉ ፡ እየገለፈጡ ። ልብሱ በውሃ የራሰበት ፡ በጭቃ የተበላሸበት ሁሉ የሚችለውን ስድብ በሚችለው ቋንቋ ያወርድባቸዋል ። “ቡልሽት ፡ ሜርድ ፡ ቅማላም ፡ ባፋንኩሎ ፡ ጋጣራው …” ብዙ ዐይነት ስድብ ። እነሱም ዝም ብለው እየገለፈጡ ይበራሉ ፡ ሌላ ትንሽ ሐይቅ እስከሚያገኙ ድረስ ።

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፊት ለፊት አንዲት ልጅ እግር ሴት ፡ ሕፃን ልጅ ታቅፋ ትጮኻለች እጇን እያወናጨፈች ።

“ምን ሆንሻል ?” አላት ለእርዳታ ከደረሱላትና ከከበቡአት ሰዎች አንዱ ። አሁንም ትጮኻለች እጇን እያወናጨፈች ።

“ምን ሆንሻል ?” አላት ያው ሰው ድምፁን ከፍ አደረገና ።

“ጉድ ሠራችኝ … ጉድ ሠራችኝ” አለች እንባዋን ዱብዱብ እያደረገች ። “ማንናት … ማንናት” አለ አንዱ አረጋዊ ፡

“አላውቃትም … አላውቃትም ። ጉድ ሠራችኝ … ጉድ ሠራችኝ” ማልቀሷን ቀጠለች ።

“ምኗ የማትረባዋ ናት ! አትናገሪም እንጂ ሲጠይቁሽ” አሉና ተቆጡ አረጋዊው ።

“አንዲት ሴት ይህንን ልጅ ይዛ መጣችና ፡ ስለ በለስ ብለሽ ይህንን ልጅ ያዥልኝ ፡ የአራት ዓመት ልጄን አስከትዬ ነበር ፡ ከኋላ ከኋላዬ ጠፋብኝ ፡ ጠፋብኝ ስለ በለስ ይህንን ልጅ ያዥልኝ … ብር ብዬ ልፈልገው” ስትለኝ ጊዜ አዝኜ ተቀበልኳት ። ይኸው የውሃ ሽታ ሆና ቀረች” ለቅሶዋን ቀጠለች ።

“በየት በኩል ነው የሔደችው” አሉ አንዱ ነገሩ የገረመው ።

“በዚህ ታች ነው … የሮጠችው ። በዚህ ነው የሮጠችው …”

“መልኳን ታውቂዋለሽ ?”

“ታየኋት አትጠፋኝም ፡ አትጠፋኝም” አለች እንባዋን እየጠራረገች ። የተሰበሰበው ሁሉ አዘነላት ፡

“እንደ ፈረደብሽ ወሰደሽ አሳድጊያ !” እያለ ያችን ልጇን ጥላ የሮጠችውን ደሞ ረገማት ።

ቦት ጫማ ያደረገ ፡ ከተጣጠፈ ጥቁር ካፖርት በላይ አረንጓዴ ጥለት ያላት ነጠላ የደረበ አጭር ሰው ከቴረስት ሆቴል በስተጀርባ ብቅ አለና እየተደናበረ መንገዱን አቋርጦ ጠርዙ ላይ ቆመ ። ጥቂት ብርሌ ጠጅ ቀማምሷል ። መንገዱ ጠርዝ ላይ ቆሞ ግራና ቀኝ ተመለከተና አፋሽገ ። ደሞ ግራና ቀኙን ተመለከተና ወደ ሐውልቱ አቅጣጫ ገሥገሥ አቀርቅሮ ብቻውን እያወራ ። አላፊ አግዳሚው ሁሉ ወሬውን እየሰማ “ዕብድ ነው ጤነኛ ?” እያለ ለጉድ ይመለከተዋል ። ብቻውን እያወራ ቀጠለ መንገዱን ። “እንደው መከረ እጥቻ ልቀር ፡ ከእንግዲህ ምን ልጨምር ነው በዚህ ዕድሜ ላይ ? ጉድ ነው የጉድ ጉድ ! አሁን እንዴት ነው ዐይኗን የማየው ፡ ባል ተገኝቶ ተሞቶአልአ ! ታማኝ ተገኝቶ ተሞቶአልአ !” አለ በሚያሳዝን ድምፅ ። እጆቹን ከጀርባው አነባብሮ ራሳ እንደሚሸኝ ለቀስተኛ ቀስ

ብሎ መራመዱን ቀጠለ "ኧረ… አንቺ እመ ብርሃን በቃህ በይኝ ! በቃህ በይኝ እባክሽ ፡ የዛሬ ወር አህዮቹን በጅብ አስበልቼ ገባሁ ፡ ዛሬ ደሞ የዚያችን ምስኪን የዋህ ሴት ገንዘብ ጠጥቼበት ስገባ ምን ይባላል ? ባል ተገኝቷልአ ! ቁም ነገረኛ ተገኝቶ ተሞቶአልአ ! እስቲ ቢቀርብኝ ባልጠጣ ፡ ገደል ሲገቡ አይቶ ገደል የሚገባ ሰው አለ እንዴ ? ሰው እንዴት ራሱን ያጠፋል ! ኧረ እንዴት ብዬ ነው ዐይኗን የማየው ? እጇን እጇን ስታይ ምን ልሰጣት ነው አሁን ! ወይስ ቀባሬ ዘረፈኝ ብየ ልዋሻት ! … ኧረ እመብርሃን በቃህ በይኝ ! ሰው ጠጅ ጠጣ ብየ … የሚስቱን ገንዘብ አጥፍቼ … አደራዋን በልቼ … ጠጥቼበት ስገባ ምን ይባላል ! … ጓደኔን በጨው አጥቤ ልገባ ?… አላረገውም … አላረገውም ። … አሁን ያች ሚስኪን ሴት … ፍልጥ አንሥታ ፡ ግንባሬን ብትፈልጠው ይፈረድባታል ? ማንም አይፈርድባትም ፡ አላስገባም ብላ ከደጅ ብትመልሰኝ … እኔንም እንደ አህዮቹ ጅብ ቢበላኝ አሁን ጨካኝ ብሎ ማን … ማን ይወቅሳታል ? ማንም አይወቅሳትም ! ባል ተገኝቶ ተሞቶአልአ … ታማኝ ተገኝቶ ተሞቶአልአ … ኧረ እመብርሃን በቃህ በይኝ … ጉበኞቹማ ሻሽ ገዝተው ፡ ሽቶ ገዝተው ‘በይ ይመርብሽ’ ብለው ለሚስቶቻቸው ይሰጣሉ … አቦ ሰው እንዴት ራሱን ያንገበግባል … ኧረ …" እያለ ሔደ ፡ አተርትሮ ራሱን እየወቀሰ ፡ እያፋሸገ ፡ ወደ ሾላ …

ሁለት በዕድሜ ጠና ያሉ ጓደኛሞች ቆመው የአራት ኪሎን ሕንፃዎች እያደነቁ ያወራሉ ። ሁለቱም ከዘራ ይዘዋል ፡ ሁለቱም ባርኔጣ ደፍተዋል ። ልብ ብሎ ለተመለከታቸው ሁለቱም ዘመናዊ ሽማግሌዎች ናቸው ። አዲስ አበባን ለብዙ ጊዜ ተለይተዋት ኖረው የመጡ ይመስላሉ ። "ይኸውልህ" አሉ አንደኛው በከዘራቸው ጫፍ ወደ ትምህርት ሚኒስቴር ሕንፃ እየመለከቱ ። "የ53ቱ ግርግር ጊዜ ትልቁ የመድፍ ጥይት ያረፈው እዚያ ላይ ነው ። ግንበኛውም መሐንዲሱም ተሰባስቦ ሕንፃውን ይሠራ ነበር ። ታዲያ ተየት መጣ ሳይባል መኻላቸው ዐርፎ እንዴ ድብልቅልቁን አያወጣውም መሰለህ ። እዚያ መሬት ቁና ሆነች ፡ አቧራው ጨሰልህ ። ትንሽ

ቆየት አለና አንዱ ድሞ እየተምዘገዘገ መጥቶ እዚያው አትራቢያ ናጋና ምድራቱን እናወጣት" የነበረችውን ሜዳ ወይ ሌላ አቅጣጫ እያመለከቱ "ይታያሃል ··· እንዚያ ሜማ ጠራጊዎች ያሉበት" ፡ "አዎ" አለ ጓደኞቻቸው ራሳቸውን እየነቀነቁ ። "ያኸውልህ እዚያ ላይ ነበርኩ እኔ ፡ ከላይ ከማርያም እየገመገምኩ ስመጣልህ አንድዬ ሲያባርቅብኝ ጊዜ ቁጭ አልኩ ጥግ ያዝኩና ፡ መቸስ ሰው ይሯሯጣል ፡ መግቢያ መውጫ አጥቶ ተቸግሮአል ፡ እኔ አደፈጥኩልሀና ዝም አልኩ ።"

"ነው እኮ ግራገዝማች" አሉና አቋረጡአቸው ጓደኞቻቸው ፡ ቀጠሉ "ጥይት ይተኮስ የለም ፡ ··· መድኃኒቱ ቁጭ ማለት ነው ። በቃ ። እንግዲህ አቅጣጫው አይታወቅም ፡ ከየትም ሊመጣ ይችላል፡ ሁኔታው እስኪረጋጋ ዝም ብሎ ማድፈጥ ነው ። አለያማ የተባራሪ እራት መሆን ነው" አሉ በእርግጠኝነት አነጋገር ። ሁለቱ ጓደኛሞች እየተሣሣቁ ቀጠሉ ጉብኝታቸውን ፡ ለብዙ ጊዜ ተለይተዋት የቆዩትን አዲስ አበባን ።

"ከታች ··· ከታች ያግኙት ··· ከታች ያግኙት" ይላሉ ነጠላቸውን እየጐተቱ የሚሮጡት ባልቴት ። ምጥ የያዛትን ሴት ተሸክመው ታክሲ ፍለጋ የሚሮጡትን ሰዎች ከኋላ ኋላ እየተከተሉ። ወዲያው ቀብራራው ንጉሤ ከተፍ አለ ። የፊት ጥርሶቹ ሁሉም ረግፈዋል ። ምላሱን በጥርሶቹ ቀዳዳ አሾልኮ ዐይኑን ሲያፈጥ ያስፈራል ። ቁመቱ ረዥም ነው ። ሰውነቱ ግዙፍ። ሲሔድ እየዘለለና ዐይኑን እያጉረጠረጠ ነው ።

"ቀብራራው ን ጉ ሤ" አለ በተረከዙ እየነጠረና ንጉሤ የሚሉትን ሆሄያት እየረገጠ ።

"አንበሳ ገዳይ ፡ ዝሆን ገዳይ ፡ ቀጭኔ ገዳይ ወንዱ የእሳቱ ላንቃ" ቆመ ዐይኑን እያጉረጠረጠ ፡ ደሞ መንጠር ጀመረ ፡ "አንበሳ ገዳይ ··· አይጥም ገዳይ" አለና የኮረኮሩትን ያህል ሣቀ ። ቀብራራው ንጉሤ ሳያብድ አብጅለሁ እያለ በጉልበቱ የሚጠጣ ፡ በጉልበቱ

የሚበላ ፡ በጉልበቱ የሚኖር ወደል ዱርዬ ነው ። ወንዱን ቤቱን የሚነጥቅ ፡ ሲለፈልፍ ሰው ሁሉ ትኩር ብሎ ይመለከተዋል ። ደስ ይለዋል ፡ ኩራት ይሰማዋል ። ሴቶች ድምፁን ሲሰሙ ከሩቅ ይሸሹታል ፡ ደስ ይለዋል ። ይታሰራል ፡ ይፈታል ፡ ደስ ይለዋል ።

"የዶሮ ሌባ … የዶሮ ሌባ" ይላሉ ትናንሽ ልጆች አጉንብሰው በዘንጋቸው ድጋፍ እየተጉተቱ የሚራመዱትን ደካማ ሽማግሌ እየተከተሉ ። ሽማግሌው ብርድ ልብስም ካፖርትም የማይሉት ባለብዙ መጣፊያ ድሪቶአቸውን ትከሻቸው ላይ ጣል አድርገው መሬት ለመሬት እየጉተቱ አቀርቅረው ዘንጋቸውን ተደግፈው ይንጓተታሉ ። የአራት ኪሎ ውሪዎች የሽማግሌ ውን ድሪቶ ከኋላ እየጉተቱ "የዶሮ ሌባ … የዶሮ ሌባ" ይላሉ እየሣቁ ። ደሞ እየሮጡ ይበታተናሉ ። ሽማግሌው ዘንጋቸውን የግድ ያነሡና በሌላ ጉልበት ካልተማታሁ ይላሉ ፡ ይናደዳሉ ፡ የዚህ ጊዜ ልጆቹ ይበረታሉ "የዶሮ ሌባ … የዶሮ ሌባ" እያሉ ይሮጣሉ ፡ ይሮጣሉ ፡ ይበታተናሉ፡ ደሞ ይሰበሰቡና እየጉተቱ ይሰድቡአቸዋል ፡ ሽማግሌው በበሽቁ ቁጥር ልጆቹ ይበልጥ ደስ ይላቸዋል ። ልባቸው እስኪፈርስ እየሮጡ ይሥቃሉ ። "የልጅ ነገር … አይ የልጅ ጨዋታ" ይላቸዋል ያለፈ ያገደመው ።

"አየሽልኝ እነዚህን ባለጌዎች … ሽማግሌውን እኮ እየሙቱ ነው የሚሮጡት … ሲያስጠሉ" አለች ከጓደኛዋ ጋር ሆና ታክሲ የምትጠብቀው ኮረዳ ፡ ፊቷን ቅጭም አድርጋ ዐይኖቿ ከልጆቹ ጋር አብረው እየሮጡ ።

"እንሱን ተያቸው እባክሽ … የጀመርሽውን ጨርሽልኝ እስቲርዬ" ለመነቻት ጓደኛዋ ።

"እናቴ ትሙት ሲያስጠሉ" አለችና ጀመረች ፡ አቋርጣው የነበረውን ጨዋታዋን ።

"ምን ላይ ነበር ያቆምኩልሽ … አዎን ያችን ጉርዷን ፡ አዲሷን ጉርድ ቀሚሴን ለብሼ … አንቺ አታውቂውም ያክስቴ ልጅ

ከውጭ የላከልኝን ጫማና ቦርሳ አድርጌ ቂው ቂው እያልኩ እሔዳለሁ ። መቸስ ጫማውና ጉርዱ ሲስማሙኝ ልነግርሽ አልችልም ። በተለይ እለ አይደለም ውሃ ሰማያዊ ማላበሻ ሸሚዝ ካለሽ ልነግርሽ አልችልም … 'ፕስ' ነው የምትይው ። እና ይኸውልሽ ብቻየን ነኝ በሲ.ሲ ገብረ ማርያም ወደላይ ስወጣ ከፊቴ ቀድመኝና መኪናውን አቁሞ በሩን ከፈተልኝ ። 'ማነው' ብየ ስመለከት እሱ ነው ። ደሞ እኮ የፊተኛዋን መኪና ሽጦ ሉክስ የሆነች መኪና ገዝቶአል ፣ ተናደድኩኝና ቀርቅሬው ዝም ብዬ አለፍኩኝ ። ቀስ እያለ እየተከተለኝ 'እስቴር ! እስቴር !' እያለ ይጠራኝ ጀመር ። ቅርቅር አደረኩትና መንገዬን ቀጠልኩ ፣ ፊቱ እሳት ሲመስል ይታየኛል ። እየበረረ አለፈኝና ሔደ ። 'እሰይ ተገላገልኩ' ስል እላይ መኪናውን አቁሞ በእግሩ ለምን አይመጣልሽም ። የማደርገው ጥፍት አለኝ ፣ ከፊት ለፊቴ እየመጣ ሊደርስብኝ ትንሽ ሲቀረው ለምን … አንድ ታክሲ መጥታ ከጐኔ አትገተርልሽም ፣ ፒያሳ 50 አልኩና ጥልቅ አልኩ ።”

“እሽ ከዚያስ” አለች ጓደኛዋ ወሬው ጥሟት ።

“ታክሲው ውስጥ ከኋላ ተቀመጥኩና ዞር ብዬ እጄን እያወዛወዝኩ 'ቻው' አልኩት ፣ የባሰውን አይቃጠልልሽም ፣ እናቴ ትሙት ሽጉጥ ቢኖረው ኖሮ ተኩሶ ይገድለኝ ነበር ። ከዚያማ ጸጉሩን እየነጨ እየሮጠ ወደመኪናው ሔደ ። ፒያሳ ደርሼ ለታክሲው ሳንቲሙን ከፍዬ ቀና ስል ከጐኔ ቆሞአል ። ከው አልኩ ። 'የኔ እመቤት እንደ እምዬ ማርያም እንድሰግድልሽ ከፈለግሽ ማርያም ጐን ቤት እሠራና ቁጭ በይ ! እንደምነሽ የእኔ እመቤት' አለና እጄን ዘረጋ ሰላምታ ሊሰጠኝ ። ወደኋላየ አንድ እርምጃ ፈንጠር ብዬ ልሸሸው ስል ጆኒዬ ፣ አንቺ አታውቂውም የአጎቴ ልጅ አለ ፣ አዲሷን መኪናውን እያሽከረከረ ብቅ አይልልሽም 'ጆኒ! ጆኒ' አልኩት መንገዱ መኻል ገብቼ … አቆመልኝና ገብቼ ኸው …”

“ከዚያስ አለች” ጓደኛዋ በውስጧ እየሣቀች ።

ወዲያው ሁለት ጐረምሶች “እስቴር ቡፋ ፣ እስቴር ቡፋ”

አሉና አለፉ ፡ ወደ ሁለቱ ሴቶች እየተመለከቱ ።

“አስቴር እንቺን ነው ? ያውቁሻል እንዴ ?” ጠየቀቻት ጓደኛዋ።

“ተያቸው አባክሽ ፎጋሪዎች ናቸው ...” አለች ንዴቷ እንዳይታወቅባት የኀፍረትና ብስጭት ቅልቅል ያቀላውን ፊቷን ከጓደኛዋ እየደበቀች። ጊዜ አላጠፋችም አንድ ታክሲ ውስጥ ገባችና ከነፈች ወደ ፒያሳ ።

አንድ ወንድና አንድ ሴት ከስድስት ኪሎ አቅጣጫ እየወረዱ መጡና አራት ኪሎ ጆሊ ባር ሲደርሱ ቆሙ ። ቆመው ጥቂት አወሩ ። ወደ ቀኛቸው ታጥፈው የፒያሳን መንገድ ቀስ እያሉ ተያያዙት ። ሁለቱም አረማመዳቸው ፡ ወጋቸው ፡ አለባበሳቸውና ፈገግታቸው ያስቀናል ። ቁመታቸው እኩል ነው ፡ መካከለኛ የሚባለው ዐይነት ቁመት ። ወንዱ ከሴቷ በዕድሜ ጠና ያለ ነው ፡ ወደ ሀርባ ዓመት ይጠጋዋል ። ሴቷ ወጣት ናት ። ቢበዛ ከሐያ አምስት አትበልጥም ። ያወሩ ያወሩና ፈገግ ይላሉ ። የሁለቱም ፈገግታ ደስ ይላል ። አዲስ ጀማሪ ፍቅረኛሞች ናቸው ።

ተያይተው አይጣገቡም ። ምሳ አብረው ይበላሉ ፡ በየቀኑ ከሥራ በኋላ ይገናኛሉ ፡ በዕረፍት ቀናት አብረው ይውላሉ ያመሻሉ። ግን አይጣገቡም። ከተዋወቁ ሁለት ወር ሆናአቸዋል ፡ ሁለቱንም ወር ሁሉ አብረው ናቸው ። ፈገግታ ይመጋገባሉ ፡ ፍቅሩን ይሰጣታል ፡ ፍቅሯን ትሰጠዋለች ፡ ልብ ለልብ ተገናኝተዋል ። አይጠጋገቡም ፡ ምሳ አብረው በልተው ወደ መሥሪያ ቤታቸው እየሔዱ ነው ። ይሄዱ ይሔዱና ቆም ብለው ጥቂት ያወራሉ ፡ ሁለቱም ፈገግ ይላሉ ፡ እንደገና መንገዳቸውን ይቀጥላሉ።

አብረው እስካሉ ድረስ በዓለም ላይ ከሁለቱ በቀር ሌላ ያለ መስሎ አይታያቸውም ፡ መንገዱ ሁሉ የተፈጠረው ለሁለቱ ብቻ ይመስላቸዋል ። ደስ ይላሉ ፡ ያሳዝናሉ ፡ አዲስ ፍቅረኛሞች ፡ ፍቅራቸውን አጥብቀው የጀመሩ የሚያስቀኑ ፍጡሮች ። በዚህች

ሁለት ወር ብዙ አስበዋል ፡ ትዳርን ፡ ቤትን ፡ ልጅን እንዶተው ተመካከረዋል ። ተግባብተው ተስማምተው ጨርሰዋል ።

ሁለቱን ፍቅረኛሞች አንድ ሰው ራቅ ብሎ ይከተላቸዋል ። ሲቆሙ እሱም ይቆማል ፡ መንገድ ሲጀምሩ እሱም ይጀምራል ፡ ፊቱ ያስፈራራል ፡ ብቻውን ያወራል ፡ ይቅበጠበጣል ፡ ፍቅረኛሞቹ ቆም ብለው ገጽ ለገጽ እየተያዩ ፈገግ ሲሉ የእሱ ፊት ፍም ይመስልና ያስፈራል፡ ጥርሱን ነክሶ እንደሚናደፍ እባብ አንገቱን ይመዝና ቆም ይላል ። ኪሱን ቶሎ ቶሎ ይዳብሳል ፡ ፈጠን ፈጠን እያለ ይራመድና ቆም ይላል ፡ በሐሳብ ይዋዥቃል ፡ ሐሳብ ውስጥ ገብቶ ሲዋዥቅ ያልበዋል ፡ መሐረቡን ያወጣና ፊቱን ይጠራርጋል ፡ ቀኝ እጁን ከኮቱ ኪስ ያስገባና ፈጠን ፈጠን እያለ ይገሠግሣል ። ሁለት ዐይነት ዓለም ። ፍቅር ፡ ፈገግታ ፡ ተስፋ ፡ አንድነት በአንድ በኩል ፡ ቁጣ ፡ አስፈሪ ፊት ፡ ተናዳፊ ሐሳብ በሌላ በኩል ። ምስቅልቅል ሕይወት ፡ አስከፊ ሕይወት ። ከእጅ እንዳመለጠ ሸክላ ለአፍታ አመድ የሚሆን የውሻሽት ሕይወት ። ኤጭ !

ሰውየው ያንን አስከፊና የሚያስፈራራ ፊቱን የበለጠ የሚያስፈራራ አደረገና እየሮጠ ተጠጋቸው ። ከኮት ኪሱ ሽጉጡን መዘዘ ፡ አነጣጠረና ልጅቱን ራሷ ላይ ሁለት ጊዜ አከታትሎ መታት ። ድፍት አለች ፡ በቃ ። ወደ ሰውየው አዞረና አንድ ጊዜ ተኩሶ መታው። ግን ሰውየው ሮጠ ። እየተከታተለ አከታትሎ ተኮሰበት ። የአራት ኪሎ ግርግር ረጭ አለና በሐዘን ተዋጠ ። ለአፍታ ብዙ ሰው ተሰባሰበ ። በፊቷ የተደፋችውን ያችን ጉብል እየተመለከተ ሁሉም አዘነ። ሁሉም ለግድያው ምክንያት ሊሆን ይችላል የሚለውን ሰነዘረ ። የብዙዎቹ ግምት ትክክል ነበር ።

ከሁለት ወራት በፊት ገዳይና ሟች ፍቅረኛሞች ነበሩ ። አይግባቡም፡ ገዳይ ይበድላታል ፡ ሁልጊዜ ያሳዝናታል ፡ እንደ ፍቅረኛ ሳይሆን እንደ ገረድ ሊመለከታት ይዳዳዋል ። በአባቱ ሀብት ስለሚኮራ ያሻኝን ላድርግሽ ይላታል ። እሷ አርቆ አስተዋይ ናት ፡ ረጋ ያለች የበሰለች ናት ። ላስቀናሽ ሲላት አትቀናም ። ትወደዋለች ፡

ግን ጥሩ ፍቅረኛ ሊሆናት አልቻለም ። ባጣ ቆይኝ አያረጋት ። ብዙ ጊዜ ታገባው ብዙ ጊዜ መከራው ሊመለስላት አልቻለም ። አንድ ቀን ቁጭ ብለው እያለቀሰች ነገረችው "በል እንግዲህ አንተ እኔን ታራክሰኛለህ ፡ ታመናጭቀኛለህ ፡ ሲፈልግህም የት ዐውቅሻለሁ ትለኛለህ ፡ ትመለሳለህ ብዬ ብዙ ጠብቄሃለሁ ፡ እንደማታዋጣኝ ስለማምን የዕድሌን እሞክራለሁ ፡ አንተም ይቅናህ" ብላው ተሰናበተችው ። ከነበሩበት የእሱ ጓደኛ ቤት ተናዳ ስትወጣ እግሮቹን አጣጥፎ እየማቀ ተመለከታት ። በሩ ላይ ስትደርስ "ደህና ዋል" አለችና ገሠገሠች ። አልተመለሰችም ። ብዙም ጊዜ አልቆየች ጥሩ ሰው ገጠማት የሚያገንላት ፡ በእውነት የሚወዳት ፡ የሚንከባከባት ፍቅረኛ ። ያሳለፈችውን የውሸት ፍቅር ዘመን እያማረረች ከአዲሱ ፍቅረኛዋ ጋር ሁለት ወራት ቆየች ። ግን ጥሩ ፍቅር አይዘልቅም ?

አራት ኪሎ ልዩ ልዩ ትርዒቶች የሚታዩባት ውብና ግልጽ መድረክ ናት ። አሥቂኝ ፡ አሳዛኝ ፡ አስደናቂ ፡ ትርዒት የሚታይባት ነጻ መድረክ ። የሚያሥቅ የሚያሳዝን ፡ የማያበሽቅ ትርዒትም ይታይባታል ። ግን ይኸም ራሱ ያበሽቃል ። የሕይወት ልዩ ልዩ ቀለማት ይታዩባታል ፡ ተቸግሮ የሚያለቅስ ፡ ተቸግሮ የሚዘፍን ፡ ጠግቦ የሚደባደብ ፡ ጠግቦ የሚለምን ሁሉም በያይነቱ ። እያንዳንዱን ትርዒት በተናጠል ሲመለከቱት ፡ በጽሞና ሲከታተሉት ሥራን ያስረሳል ፡ ያዝናጋል … ደስ እያለ ። አጠቃላዩን ትርዒት መመልከቱ ደግሞ የራሱን ደማቅ ኅብር ፈጥሮ የበለጠ ያረካል ። እያንዳንዱ የተናጠል ትርዒት ፡ ዕብደቱ ፡ ቅብጠቱ ፡ ቅጥፈቱ ፡ ደስታው ፡ ሁካታው ስካሩ ሲገጣጠሙ በአንድ ኦርኬስትራ ውስጥ የተለያዩ የሙዚቃ መሣሪያዎች በተናጠል የሚያወጡት የተለያየ ድምፅ ተዋሕዶ የሚፈጥረውን ዓይነት ቃና ይፈጥርና የደስታን ስሜት ያጭራል ፡ የሕሊና ምግብ ሆኖ ያረካል ። አዲስ አበባ ፡ አራት ኪሎ መስከረም 21 ቀን 1964 ልክ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ።

ታክሲዋ መንገዱ ዳር የቋጠረውን ውሃ አፈናጥራ ረጨችና

ሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ ፊት ለፊት ቆመች ። ሦስት ሰዎች ተከታትለው ወረዱ ። ከፊት ካለው የታክሲዋ መቀመጫ የወረዱት ረዥም ወፍራም ሰው ናቸው ። ከቀይ ዳማ ፊታቸው ላይ የሚንቦገቦገው ወዝና የተስተካከለ አቋማቸው ድሎት ያልተለያቸው መሆኑን ይመሰክራል ። ዕድሜያቸውን ሸፍኖ ወጣት አስመስሏቸዋል ። መኻል አናታቸው ላይ ደርሶ የቆመው በራቸው አጠርና ሰፋ ካለው ፊታቸው ጋር ተዳምሮ ግርማ ሞገስ አላብሷቸዋል ። ሁለትና ሦስት እርምጃ በተራመዱ ቁጥር በራቸውን ያልባቸዋል ። ነጭ መሐረብ ከግራ እጃቸው አይለይም ። ራመድ ራመድ ይሉና በግራ እጃቸው ከግንባራቸው ጀምረው እስከ መኻል አናታቸው ይጠርጋሉ ። ጥቂት እርምጃዎች ይራመዱና መልሰው መጥረግ ይጀምራሉ ። ከአረማመዳቸውና በፊታቸው ላይ ከሚታየው ኩስታሬ የተናደዱ መሆኑን መገመት ይቻላል ። ለምን ተደፈርኩ ብለው የሚቆጡ ፤ በትንሹ በትልቁ የሚናደዱ፤ እያንዳንዷን ጥቃቅን ጥቃት ከክብራቸው መደፈር ጋር የሚያያይዙ ፤ እልከኛና ጠማማ ሰው ናቸው ። ጥቃት አይወዱም ። በሌላ በኩል ደግሞ ጠንካራ ፤ ርኅሩኅና ይሉኝታ የሚያጠቃቸው ናቸው ። “ተመቀደም ይሻላል ማስቀደም ፤ ገላጋይ አያጣም በኋላ ያለደም” ይላሉ ተደፈርኩ ፤ ተጠቃሁ የሚል ቅሬታ ሲያድርባቸው ። በብዙ አካባቢዎች የአውራጃ ገዥ ሆነው ሠርተዋል ። ብዙ ሰው ያውቃቸዋል ። ብዙ ሰው ያውቃሉ ። ወንዲራድ በሻህ ይባላሉ ። በጡረታ ለመገለል የቀራቸው አንድ ዓመት ብቻ ነው ።

ሁለተኛው አለቃ መዘምር ናቸው ። የወንዲራድ የነፍስ አባት። በዕድሜ ከወንዲራድ ያንሳሉ በሀሥር ዓመት ። ወንዲራድ ግን እንቱ ይሏቸዋል ። የነፍስ አባታቸው ብቻም ሳይሆኑ የቅርብ አማካሪያቸውና አጽናኛቸው ናቸው ። ወንዲራድ ሲሥቁ አለቃ መዘምርም ይሥቃሉ ። ሲከፋቸው ይከፋሉ ፤ ሲያዝኑም ያዝናሉ ። “የዘመድ ቁስ እየፈታ ያለቅስ አይደል ከነተረቱ” ይሏቸዋል የወንዲራድ ባለቤት ወይዘሮ ተዋበች ፤ መርጊያ ከቤተሰቡ ጋር

አብረው ሲጨንቁ አብረው ሲያዝኑ አብረው ሲደሰቱ እየተመለከቱ።

ሦስተኛው የወንዲራድ አሽከር ናቸው ። በዕድሜ ከጌታቸው አይተናነሱም ። በወንዲራድ ቤት መኖር ከጀመሩ ከዓሥር ዓመት በላይ ይሆናቸዋል ። ቀድሞ ነዋሪነታቸው በገጠር ነበር ። የወንዲራድን መሬት እያረሱና ምርቱን እየተቆጣጠሩ ወደ አዲስ አበባ የሚያመጡ የወንዲራድ አሽከር ። የኋላ ኋላ ግን በገጠር መኖር አስጠላቸው ። ሁለት ሚስቶች አግብተው ሁለቱም ሞቱባቸው ። አገሬው ይኸ "ገፊ" እያለ ሲያስቸግራቸው ጊዜ ወንዲራድን መጥተው አስቸገሩ ። "ታዲያ ምን ከፍቶኝ ቤቱ ቤትህ ነው ሲገኝ ትበላለህ ፡ ሲታጣ ቤተሰቤን መስለህ ትኖራለህ ። እንደውም እኔን ሆነህ ቤተሰቤን ትጠብቃለህ ፡ ቤቱን አስከባሪ ትሆናለህ ፡ እዚሁ ሆነህ ታግዛቸዋለህ አይዞህ አትጨነቅ" ብለው በአሽከርነት አስገቡአቸው ። ገበየሁ አጥናፍ በዕድሜ እየገፉ ቢሔዱም የጉረምሳ ያህል ጉልበት ያላቸው ልባቸው የማይሸነፍ ብርቱ ሰው ናቸው ። ቤት አጥብቀው ይወዳሉ ።

ወንዲራድ ከመንገዱ ዳር ቆመው በከዘራቸው መንገዱን እየቆረቆሩ ግራና ቀኝ የሚመላለሱት መኪናዎች አልፈው መንገዱን እስከሚለቁላቸው ድረስ ይጠብቃሉ ። ከበራቸው ዙሪያ ችምችም ብሎ ያደገው ጸጉራቸው እንደመቆም ብሏል ። በመሐረባቸው በራቸውን አሻሹና ወደኋላ ዘወር አሉ ።

"ካፖርት ስጠኝ ! ካፖርት ስጠኝ" አሉ ። ገበየሁ እየሮጡ ተጠጉና ካፖርቱን ሰጡአቸው ።

"ከዘራውን ተቀበሏቸው ተቀበሏቸው" አሉ አለቃ የራሳቸውን ላይ ጥምጥም እያስተካከሉ ። ቀጠሉ ።

"ጌታዬ እንግዲህ ቻል ያድርጉት ፡ በገረገራው ጊዮርጊስ ይገዝዎታለሁ ቻል ያድርጉት ። ስንቱን ክፉና ደግ አሳልፈው ለትንሽ ነገር እንዲህ ሲሆኑ አገርስ ምን ይላል ? በተሰቀለው ይገዝዎታለሁ ! ረጋ ይበሉ ! በሽታ ላይ ይወድቃሉ !" አሉ አለቃ በጭራቸው አየሩን

እየደበደቡ ። ወንዲራድ ቀና ብለው ተመለከቱአቸው ። ንዴታቸው አሁንም ግልጽ ሆና ከፊታቸው ላይ ይነበባል ። ትንፋሻቸው ይገፋተራል ። ገበየሁ አንድ ጊዜ ወንዲራድን አንድ ጊዜ አለቃን እያፈራረቁ ይመለከታሉ ። ተናግረው ጌታቸውን ለማጽናናት ወይ ለማጀገን ቢፈልጉም የሚናገሩት ጠፍቶባቸው ተጨንቀዋል ። ወንዲራድ ከፒያሳና ከአራት ኪሎ እየጐረፈ በፊታቸው የሚያልፈውን መኪና ግራና ቀኝ ተዘዋውረው ቃኙና ወደ አለቃ ዞረው ከግር እስከ ራሳቸው ተመለከቱአቸው ። አለቃ የወንድዬራድ አመለካከት የከፋት እንዳልሆነ ገብቶአቸዋል ። "ምን ላድርግ አለቃ" የሚል የጭንቀት መልእክት መሰሎ ታያቸው ።

"የለም የለም ፡ የኢዮብን ትዕግሥት ይስጥዎ ! ረጋ ብለው በደልዎን ፡ መደፈርዎን በጨዋ ደንብ ማስረዳት እንጂ እንዲህ ዐይነት ንዴት ምን ያደርጋል! ራስዎን በሽታ ላይ ይጥላሉ አልኩዎ" አሉ አለቃ ድምፃቸውን ከፍና ዝቅ እያደረጉ ።

"ደግሞ እኮ የስኳር በሽታ ንዴት አይወድ ፡ ሐኪሞቹም መክረዋቸዋል እኮ ፡ ኧረ እንደው አስተዳደራቸውን ቢያዩ ምን ይሉ ነበር አለቃ" አሉ ገበየሁ ድምፃቸው ቁርጥ ቁርጥ እያለ ።

"ስሙኝ አለቃ ያን ጉረምሳ ከቤቴ እንዲወጣ ያድርጉልኝ ። ለዚህ ሁሉ የዳረገኝ እሱ ነው ። ቤቴን ሊበትን ፡ ትዳሬን ሊያፈርስ ፡ ስሜንና ክብሬን ሊያጐድፍ የተላከ ሰው ነው ። ዛሬውኑ ያስወጡልኝ። እኔ ከሷ ጋር እንዳልቀያየም ብዬ እንጂ እስከዛሬም አስወጥቸው ነበር ። አለቃ ሌላ የምልዎት የለም ። ዛሬውኑ ከቤቴ ወጥቶልኝ እንዲያድር —" የወንዲራድ ንዴት ከፊታቸው ላይ በግልጽ ይነበባል። መንገዱን ማቋረጥ ጀመሩ ።

"ጉድ እኮ ነው" አሉ ገበየሁ ወንዲራድ ያቀረቡት ሐሳብ ውስጥ ውስጡን ደስ እያላቸው "ጉድ እኮ ነው አለቃ ፡ ሜትና መጽሐፍ ጉያው ውስጥ ሸጉጦ ነው እኮ የሚውለው ። ታዲያ ይኸን ጤነኛ ነው የሚል ሰው አለ ? ይኸው ታየሁት ጀምሮ ተብብቱ ውስጥ መጽሐፍ ሸጉጦ ነው የማየው ። ያውም እኮ ስንት ቅዱስ

መጽሐፍ ሞልቶ ምናምኑን ሁሉ እኮ ነው ይዞ የሚዞረው ። ውነትም እማኑኤል! ቀድሞውንም ዐውቀው ነው ዛማኤል ያሉት ስሙን ። እሷም ታዲያ የእሱን ወረሰችና እንደሱው መጽሐፍ እንጠልጥላ ነው የምትውለው ፤ ምናለ በሉኝ እሱው ነው ታባት ከናቷ ወጣ እንድትወጣ ፤ ተከብረው የኖሩትን ያገር ሽማግሌ መሣቂያ ፤ ያገር መሣቂያ እንድታደርግ የሚመክራት እሱው ነው ። ‘ታሀይ የዋለች ጊደር ፈስ ተምራ መጣች’ አሉ ። እውነታቸውን ነው” እሳቸውም እንደጌታቸው ተናደዱ ።

ወንዲራድ ዘወር አሉና ገበየሁን ተመለከቷቸው ። “ደግ ብለሃል” ዐይነት አመለካከት ። ገበየሁ ደስ አላቸው ።

“ጌታየ ያሉት ነገር … የልጁ ነገር መቸስ ቀስ ብሎ የሚደርስ ጉዳይ ነው ። መቸስ መማርና ማወቅ ፤ የጨዋ ልጅ መሆን ለመቼ ነው? ለዚህ ለዚህ አይደለም እንዴ? ዋናው ነገር አሁን የመጣንበትን ጉዳይ ዳር አድርሰን መመለሱ ነው ። በጨዋ ደንብ ስምዎንና ክብርዎን ጠብቀው ማስረዳት ነው ያለብዎ ። ንዴቱን ተወት ያድርጉ ። ሰው ጉድ ይላል ፤ ራሱን ለሰዳቢ አሳልፎ የሚሰጥ ጅል ብቻ ነው ። ረጋ ይበሉ ። የልጁንም ጉዳይ ከሆነ እንደርስበታለን። መቸስ ሲያውደለድል ውሎ ጮማ መቁረጥ ጠጅ መጠጣት እስጠላኝ ካለ ምን ይደረጋል ፤ ‘ዕውር ሲቀናጣ ዘንጉን ወርውሮ ፍለጋ ይሒዳል’ ይባላል እኮ ፤ እምቢ ታለማ ይወጣታል ክብር ካልወደደለት …”

“እሱ ግዴለም አለቃ … ያለቀ ጉዳይ ነው” አቋረጧቸው ወንድራድ ፤ “ዋናው ሰኞን አለመሆን ነው እንጂ ሌላውማ ምን ቁምነገር አለው? ። ነገሩ እኮ ያለቀ ጉዳይ ነው ። ጧት እኮ ዋናው ኃላፊ ጋ ሔጄ ተነጋግረናል ፤ ቀደም ብሎ ያለቀ ነው ። ደሞም ጉዳዩን፡ ባጫወትኩዎት መሠረት ወሰንየለህ የራሱ ጉዳይ አድርጎ ስለሚከታተለው ያለቀ የደቀቀ ጉዳይ ነው” አሉና ፈጠን ፈጠኝ በማለት ተራመዱ ።

“እሰይ! እሰይ! ወሰንየለህ ተያዘው እማ አልቋልአ … ኧረ ይሞ

ለራስዎት ጉዳይ እርስዎስ መች አነሱና ።”

ወንድራድ ሁለተኛ ማቢያ ገብተው ከበረንዳው ላይ ቆሙና በየክፍሎቹ በር አናት ላይ የተጻፉትን ምልክቶች ማንበብ ጀመሩ ። “አዎ አዎ ያው” አሉ “የወንጀል ምርመራ ክፍል” የሚለውን እንዳነበቡ ። ካፖርታቸውን አወለቁና ከከዘራቸው ጋር ለገበየሁ ሰጡአቸው ። ወንዲራድ “ወንጀል ምርመራ” ወደሚለው ክፍል አመሩ ። ሻለቃ ባሻ አላምረው ወንዲራድን ሲመለከታቸው ድንግጥ አለ ። ያውቃቸዋል ። የት እንደሚያውቃቸው ግን ግራ ገባው ።

“ይቀመጡ ይቀመጡ” አለ ወንበሩን በእጁ እያመለከታቸው ። ወንዲራድ ተቀመጡና “እእ…” ብለው ጉሮሮአቸውን ጠራረጉ ። ገበየሁና አለቃ በሩ ላይ ቆመው ወደ ውስጥ ይመለከታሉ ። አላምረው መጻፊያ ብዕሩንና ወረቀቱን ከፊት ለፊቱ አድርጎ ፤

“ምን ልታዘዝ” አለ ።

“በደል ደርሶብኛል … ትልቅ በደል ደርሶብኛል ፤ ይኸንኑ ወደ ሕግ ለማቅረብና ወንጀለኛው ተይዞ እንዲመረመርልኝ ነው ። ወንዲራድ በሻህ እባላለሁ” ወደኋላቸው ተለጠጡና በረዥሙ ተነፈሱ ። አለቃ መዘምርና ገበየሁ በረንዳው ላይ ቆመው ከሁለት ወጣት ፖሊሶች ጋር እየተሟሟቁ ያወራሉ ። ወንዲራድ ደረሰብኝ የሚሉትን በደል በዝርዝር ያስረዳሉ ። ሻለቃ ባሻ አላምረው “ይቀጥሉ” እያለ ይጽፋል ።

“እሽከሮቼ እንኳ እንዴት ተደፈርን እንግደል ብለው ነበር ፤ እኔ ነኝ ‘አይሆንም ያልኩት ፤ ሕግ ባለበት ቦታ በሕግ እንፋረዳለን እንጂ ሕግ እያወቅን ከሕግ አንተላለፍም’ ብዬ የከለከልኩ እኔ ነኝ ።” አሉ ወንዲራድ ከአፋቸው የሚያወጡአቸውን ቃላት በእርግጠኝነትና በልበሙሉነት ስሜት ጫን እያሉ ። አላምረው ጽፎ ጽፎ ቀና ባለ ቁጥር ፈገግ ይላል ። ጽፎ እንደ ጨረሰ ግራ ተጋብቶ ዐይን ዐይናቸውን ይመለከታቸው ጀመር ። ወዲያው ከፊት ለፊቱ ጠረጴዛው ላይ ያለችው ስልክ ጮኸች ።

“አቤት” አለ አላምረው ። “ዐውቄያለሁ ፡ ዐውቄያለሁ ምን ልታዘዝ ፡ አዎ … አዎ… አሁን ከእኔ ጋር ናቸው ። ክሳቸውን እያቀረቡ ነው ፡ … አዎ ጨርሰዋል … እሺ … እሺ ግዴየለም … ግዴየለም እፈጽማለሁ” ስልኩን ዘጋ ።

ለጥቂት ሰከንዶች አቀርቅሮ ቀና አለ ። ፊቱ ከቀድሞው የተለወጠ ገጽታ ይነበብበታል ። አዕምሮው ውስጥ የተደነቀረው ሐሳብ ቀድሞ የነበረውን ፈገግታና የደስ ደስ ስሜት አሟጦ ወሰደበት ።

“ስለ እርስዎ ጉዳይ ነበር የተደወለልኝ” ቀና ብሎ በመስኮቱ ባሻገር ተመለከተና መለስ አለ ። የፊቱ ገጽታ ያው ነው ።

“አዎ ገባኝ … እኮ… ታዲያ አሁን ሰውየው ተይዞ ይመርመር ልኛ ፡ ጌታዬ ” ከመቀመጫቸው ተነሡና ቆሙ ። ትልቅ የዕፎይታ ስሜት ሰውነታቸውን ሲወራቸው ተሰማቸው ። አሊቃና ገበየሁ ከበሩ ውጭ ቆመው ክፍሉ ውስጥ የሚደረገውን ሁሉ ይከታተላሉ ።

“ቁጭ ይበሉ … ቁጭ ይበሉ” አላቸው አላምረው ።

“የሰውየው ስም ማን ይባላል ?” ጠየቃቸው ።

“የየቱ ሰው … ስም” አሉ ወንዲራድ ፈጠን ብለው ።

ልጄን ደፈረ ያሉት ሰው !”

“እሃ … ቆይ … ገበየሁ ገበየሁ” ተጣሩ ። ገበየሁ ካፖርትና ከዘራ ይዘው መጡና ከወንዲራድ ኋላ ቆሙ ።

“ና ከፊት ሁን ምን ከጀርባ ይዞራል–” ተቆጡ ወንዲራድ ።

“ማነው ስሙ ያ ደፋር ማን ብሎ ነበር የነገረን ወሰንየለህ ።”

“ዓለማየሁ … ዓለማየሁ ድምበሩ ነው የሚባለው” አሉ ገበየሁ ።

“የሚሠራበት መሥሪያ ቤትስ” ጠየቀ አላምረው ። ወንዲራድ ገበየሁን ቀና ብለው ተመለከቷቸው ።

“አዎ… አዋሽ ባለሥልጣን … የለም የለም አዋሽ ሸለቆ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ነው የሚሠራ ።” መለሱ ገበየሁ ቀኝ እጃቸውን እያወናጨፉ ።

"እሺ ፔርሶናል ሰውየው አሁኑኑ ተይዞ ይመጣል ፡ እናንተ እዚሁ ትጠብቃላችሁ" የጻፈበትን ወረቀት ሰብስቦ አሳምሮ ወደ ሌላው ክፍል ሔደ ።

"ይኸው ነው ጌታዬ ፡ ረጋ ብሎ ማስረዳት ነው ዋናው ፡ ኮራሁብዎ ፡ በእውነት ኮራሁብዎ 'ወደ መንግሥተ ሰማያት የምታደርስ ምግባርን ለመሥራት መከራን ታግሦ መቀበል ነው' ይላል እኮ መጽሐፉ ። ደግሞም ይስሙኝ ችግር ደረሰ ብለው አይማረሩ ። በዚህች ዓለም ላይ የሚያለቅሱ ሰዎች የተመሰገኑ ናቸው ። እስመ እሙንቱ ይትፌሥሑ' ብሏቸዋል ። ደስ ይላቸዋል ተብለዋል ። በእውነት ምክሬን በመቀበልዎ ደስ ብሎኛል ። አሁን የሁለቱ ፖሊሶች አካሔድ ይዘውት ሊመጡ አይደለም እንዴ?" አሉ አለቃ ካባቸውን እያስተካከሉ ።

"አዎ ሊያመጡት ነው የሔዱት ፡ ብቻ ቅድም ያልኩዎትን ነገር እንዳይረሱ ። ለዚህ ሁሉ ያበቃኝ እሱ ነው ብየዎታለሁ ። እንዴ እኔስ ምን በወጣኝ ባጐረስኩ ጣቴን እነክሳለሁ እንዴ? ይኸው ድፍን ዓመት ቀለብኩ …አይበቃኝም ። ኧረ በደሌ ምንድን ነው? ልጄን አበላሽቶብኛል ከቤቴ ይውጣልኝ ብየዎታለሁ ። ኋላ ባለቤቴ ጋር እንዳያጣላኝ ። 'የተማርኩ ነኝ' … ይላል ። የእሱስ ትምህርት ይቅር…" አሉና ብድግ አሉ ወንዲራድ ።

ከትናንት ምሽት ጀምሮ ሲተናነቃቸው የነበረው እልህ እንደ ጤዛ ቀስ በቀስ እየረገፈ ጠፋላቸው ። በውስጣቸው የነበረው የበቀል ስሜት ቀስ በቀስ እየለቀቃቸው ሔደ ። ታላቅ የዕፎይታ ስሜት ተሰማቸው ።

"መጣ…መጣ" አሉ ገበየሁ ሁለቱ ፖሊሶች አስከትለውት የመጡትን አንድ ወጣት እየተመለከቱ ። ጎለማሳው ደምበሩ ነጭ ሱሪ ታጥቆ ከላይ ቡናማ ቀለም ያለው ጃኬት ደርቦአል ። አሳጥሮ የተቆረጠው ጸጉሩ ፊቱን የበለጠ ጉልቶ እንዲታይ አድርጎታል ። ጉንጩ ከወትሮው ይልቅ ደንቦጭ ያለ ሆኖ ይታያል ። ረጋ ብሎ ነው የሚራመደው ፡ የኩራት አረማመድ ።

“በገረገራው ጊዮርጊዮስ ይገርምዎታለሁ···· ምንም ነገር እንዳይናገሩ ፡ ሕግ ፊት የቀረበ ወንጀለኛ ወጥመድ ውስጥ የገባች ዐይጥ ማለት ነው ፡ እርስዎ ምንም እንዳይናገሩ…” አለቃ ወንዲራድን ተማጠኑአቸው ። ወንዲራድ ቀደም ሲል ገሸሽ ብሎላቸው የነበረው የእልህና የበቀል ስሜት መልሶ እንደዛር ሲሰፍርባቸው መልካቸው ሁሉ ቅይርይር አለ ። ዓለማየሁ በአንዱ ፖሊስ እየተመራ ከፊት ለፊታቸው ዐልፎ ወደ ወንጀል ምርመራ ክፍል ሲገባ ከእግር እስከ ራሱ ተመለከቱትና አንገታቸውን ነቀነቁ ።

“ካልጠፋ እህል ጓያ ሸመታ … ምነው ይኸን ሳላይ ገለኸኝ በነበር” አሉ አሁንም አንገታቸውን እያነቃነቁ ። ዓለማየሁ ወንዲራድን ሲመለከት ድንግጥ አለ ። የመጣበትን ጉዳይ ቢያውቀውም ወንዲራድ ይኖራሉ ብሎ አልጠረጠረም ነበር ። በአክብሮት አንገቱን አቀርቅሮ በፊታቸው ሲያልፍ ይኸ ነው ብሎ ሊገልጸው የማይችል እንዳች ነገር ሰውነቱን ሁሉ ወረረው ። ውሉ የጠፋ ሐሳብ አዕምሮውን በጠበጠው ። ለልዩ ልዩ ጉዳዮች ሁለተኛ ጣቢያን አጣበው የተመለከታቸው ሰዎች ሁሉ እሱን ለማየት የመጡ መስሎ ተሰማው ። ድንጋጤ ፡ ፍርሃት ፡ ይሉኝታ እንደ ዝንብ ወረሩት ።

“እዚህ ተቀመጥ እዚህ ተቀመጥ” አለ አላምረው ወደ ወንበሩ በእጁ እየመለከተ ። “ጌታዬ ሊገቡ ይችላሉ ሌሎቻችሁ ውጭ ቆዩ” ወንበሩን አስተካከለና ተደላድሎ ቁጭ አለ ።

ዓለማየሁ ከፊት ለፊቱ ወንዲራድ ሲቀመጡ ግራ ተጋባ ። የኃፍረት ፡ የድንጋጤ ፡ የመሸበር ፡ የመገረም ድብልቅልቅ ሐሳብ መላ ሰውነቱን ወረረው ። ሲጃራ አውጥቶ ለማጨስ እጁን ጃኬቱ ኪስ ከተተና መልሶ ሐሳቡን ለወጠ ። እጆቹን ከደረቱ ላይ አነባብሮ መሬት መሬት እያየ ዝም አለ ።

“እሺ…ዓለማየሁ ተከሰህ የመጣህበትን ጉዳይ ታውቃለህ?” አለ አላምረው የግራ እጁን ግንባሩ ላይ ተክሎ ።

“የለም አላወቅሁም ፡ ያመጡኝ ፖሊሶች ‘ሁለተኛ ጣቢያ

ትፈልጋለህ' አሉኝ ። ለምን ጉዳይ እንደሆነ ጠይቄያቸው ነበር ፡ ግን 'እዚያው ይነግርሃል' ብለው ነው ያመጡኝ ።"

"እሽ …ሐረገወይን ወንዲራድን ታውቃታለህ?"

ዓለማየሁ ካቀረቀረበት ቀና አለ ። አዕምሮውን አስጨንቆት የነበረው ድብልቅልቅ ሐሳብ በአንድ አፍታ ብትንትኑ ወጣና አንድ ነገር ላይ ብቻ አተኮረለት ። ችግር ሊደርስበት እንደሚችል ቢገምትም በዚህ መልክ ፖሊስ ጣቢያ ተከስሼ እቀርባለሁ የሚል ግምት አልነበረውም ። የእሱ ጥርጣሬ ሌላ ነበር ።

'ነገሮች መልካቸውን እየለወጡ መጡ ማለት ነው' ብሎ አሰበ በልቡ ።

"አዎ እንተዋወቃለን" አለ ፍርጥም ብሎ ።

"ስትተዋወቁ ስንት ዓመታችሁ?"

"አንድ አምስት ዓመት ይሆነናል … አዎ ልክ አምስት ዓመታችን ነው ።"

አላምረው በግራ እጁ መዳፍ ግራ ጉንጩን አስደግፎ ዓለማየሁን ትክ ብሎ እየተመለከተ ለጥቂት ሰከንዶች ዝም አለና ፡

"እሽ ዓለማየሁ … የተከሰስክበት ጉዳይ የአቶ ወንዲራድን ልጅ ሐረገወይን ወንዲራድን ደፍረሃል ፡ ክብረንጽሕናዋን ገሥሃል በመባል ነው ፡ ታምናለህ አታምንም" አለ ከመቀመጫው እየተነሣ፡ ዓለማየሁ ቀና አለና ፈገግ አለ ፡ የመገረም ፈገግታ ።

"ደሞ ይገለፍጣል እኮ እያፍርም ወይ ድፍረት" አሉ ገበየሁ ከውጭ ቆመው ወደ አለቃ ጆሮ ጠጋ አሉና ፡ "የሌባ ዐይነደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ' እያለ ነገሩ ይገርማል እኮ !"

አለቃ መልስ ለመስጠትም አልፈለጉ ። ወንዲራድ በደም ፍላት ተነሥተው አንድ ነገር ያደርጋሉ ብለው ሐሳባቸው ሁሉ ወንዲራድ ላይ ነው ።

"አልደፈርኩም ሐሰት ነው ፡ የተከሰስኩት በዚህ ከሆነ ልጅቷን አልደፈርኩም ሐሰት ነው ሐሰት" ዓለማየሁ ፊቱ ልውጥ

አለ ። እንደ በጋ ሰማይ የጠሩትንና ከሩቅ የሚጣሩትን ዐይኖቹን ቀይ ድር አደረባቸው ። ብስጭት ውስጡ ገብቶ "ተነሥ!… ተነሥ!" እያለ ሲኮረኩረው ተሰማው ። ግን አፈነው ። ወንዲራድ ግን ሊቆጣጠሩት አልቻሉም ብድግ አሉ ።

"ምስክር አለኝ …ምስክር አለኝ … አገር ይመሰክራል ፡ ከቤት ወጥታ የማታውቀውን ልጅ አቤቱ ለማሳደሩ አገር ይመሰክርልኛል። ልጄን በጉልበት ደፍሯል ፡ እኔን አባቷን አዋርዷል ፡ ልጄን ደፍሯል እፋረደዋለሁ ።"

"ውሸት… ውሸት ነው… ሐሰት… ሐሰት ነው…" የሚል የሴት ድምፅ ተሰማ ከውጭ ። ሁሉም ድንግጥ አሉ ። ሐረገወይን ወንዲራድ ከበር የቆመውን ሁሉ እየገፈተረች ገባችና በአባቷና በዓለማየሁ መካከል ቆመች ።

"ምን ሥርዓት …ምን ሥርዓት" ይላል አንድ ፖሊስ ከውጭ ።

"ሐ…ሰት…ሐ…ሰት" አለች ቁርጥቁርጥ ባለ ድምፅ ሲቃ እየተናነቃት ። "ስማ… ስማ… ተደፈረች የምባለው እኔ ነኝ ። ውሸት ነው… ውሸት … የጭቦ ምስክር ነው… ውሸት .. ውሸት…" አለች እንባዋ እየፈሰሰ ። ሁሉም ግራ ተጋባና ዝም አለ ። ወንዲራድ ወደ ውጭ ወጡና የአሊቃን እጅ እየጐተቱ ወደ አንድ ጥግ ይዘዋቸው ሔዱ። "እባክዎን ይችን ዕብድ ይውሰዱልኝ ፡ እንዲህ አድርጋ ታዋርደኝ አሊቃ ፡ ሁለት ጊዜ አዋረደችኝ እኮ! ምነው ምነው እናንተስ ዝም ትላላችሁ? ገና ስትመጣ ስታዩ ሲሊዋን አንቃችሁ አትመልሱልኝም ነበር ። ምነው አሊቃ ምንነው ተከብሬ በኖርኩበት አገር በእስተርጅና ስዋረድ ዝም ትላላችሁ ፡ ስዋረድ ዝም ብላችሁ ታዩኛላችሁ" አሉ በመሐረባቸው አናታቸውን እየጠረጉ ።

አሊቃ መዘምር ክው አሉ "ተየት መጣች ሳትባል እኮ ነው ያዋረደችን ። ምን እርስዎን ብቻ ሁላችንንም አዋረደች እንጂ … በስመአብ …በስመአብ… ሹልክ ብላ መጥታ እንዲህ ጉድ ትሥራን፡ አላየናት ሆኖ እንጂ ከእኛው ኋላ ቁማ ስታዳምጥ አይደለ እንዴ

የቆየችው ። ድንገት እኮ ነው ገፍትራኝ የገባችው ፣ እኔ ደሞ መች እሷ መሰለችኝ ። የሚገፋኝ ፖሊሱ መስሎኝ እኮ ነው ዘወር ብዬ ያሳለፍኳት ። በሉ አሁንም ግቡ እሷን ተቆጥቼ እወስዳለሁ በገረገራው ·· በገረገራው" አሉ ካባቸውን እያስተካከሉ ። ሁለቱም ተመልሰው ወደ ወንጀል ምርመራ ክፍል አመሩ ። አሳምረው አቀርቅሮ ይጽፋል ። ዓለማየሁ አቀርቅሮ መሬት መሬት ያያል ። ሐረገወይን ወገቧን በሁለት እጆቿ ጥብቅ አድርጋ ይዛ ቆማለች ። በጧት ተነሥታ አስተካክላና አሳምራ ያበጠረችው ጸጉሯ ምስቅልቅል ብሏል ። ያ ድንቡሽቡሽ ፊቷ በንዴት እሳት ወላፈን ተገርፎ የተቃጠለ መስሏል ። ዓለማየሁ ቀና ብሎ ተመለከታት ። በሁለቱ ጉንጮቿ አቋርጠው ወደታች የሚፈሱትን የእንባ ዘለላዎች ተመለከተ ። ብድግ አለ ድንገት ። ከሱሪው ኪስ መሐረብ አወጣና እቅፍ አድርጎ እንባዋን ጠረገላት ።

"አንቺ ···ዝም በይ··· ምን አስለቀሰሽ ··· በቃ··· በቃ··· ልክ አይደለሽም በቃ ···ሒጂ ወደቤትሽ ··· ሒጂ" መልሶ ቁጭ አለ ። ከኪሱ ሲጃራ አውጥቶ አቀጣጠለ ።

"እይ የዛሬ ዘመን ልጅ! ጉድ ዘመን ልጅ አባቱን ባደባባይ የሚያሳፍርበት ዘመን! እይ ስምንተኛው ሺህ" አሊቃ በመረረና ተስፋ በመቁረጥ ስሜት አንገታቸውን ነቀነቁ ። "እይ ስምንተኛው ሺህ! ያስነኳት ነገር አለ ፣ አላንዳች ነገር እንዲህ አትሆንም ። ዐውቃት የለም እንዴ ልጅቷን···የለም የለም···ያስነካት አንድ ነገር አለ" አሉ አጠገባቸው ወደቆሙት ፖሊሶች አፈጠጡና "··· ነው እኮ ልጆቼ! አንድ ነገር አስነክቷት ነው" አሉ ። ገበየሁ አሊቃን ትኩር ብለው ይመለከቷቸዋል ፣ "ትክክል ነዎት አሊቃ" እያሉ በልባቸው። አሊቃ የተናገሩትን የሰሙት ፖሊሶች ይሥቃሉ ለብቻቸው ።

"እይ መምሩ እንዴት እንዲህ ይላሉ" አሏቸው አንዱ ፖሊስ ።

"እንዴታ የእኔ ልጅ" አሉ የጭራቸውን ጸጉር በጣታቸው እያበጠሩ ።

"አንድ ነገር አስነክቷታል ፣ አላንዳች ነገር እንዲህ አትሆንም ሲሉ ነው የሳቅነው" አለ ፖሊሱ አሁንም እየሣቀ ።

"እዎ ብያለሁ ፣ ያለ አንዳች ነገር እንዲህ አልሆነችም ፣ ይኸ ምን ያሥቃል?"

"ንጽሕናዋን ያፈረ አላላችሁም እንዴ ቅድም?"

"እንዴት ፣ እንዴታ … መጠርጠሩስ !"

"እይ መምሩ ታዲያ የነካት ነገር ጠፍቶዎት ነው እኛን የሚጠይቁን ፤ ብዙ የሚያውቁት እርስዎ አባታችን ይኸ ጠፍቶዎ ነው? 'ያፈራት' አላችሁ… ታዲያ ከእሱ ወዲያ ምን ያስነካት ብለው ነው የሚገረሙት መምሩ…" ፖሊሱ ሣቀ ልክ የከረከሩት ያህል ።

"እይ የልጅ ነገር አሁን በእኔ መቀለዱ ነው?" አለቃ ቆጣ አሉ ።

"አላምረው የሚጽፈውን ጽፎ ጨረሰና ቀና አለ ። አለቃ የሐረገወይንን እጅ እየጐተቱ ወደ ውጭ ይዘዋት ወጡ ። ወንዲራድ አላምረው ቀና ሲል ምን ሊናገር ይሆን ብለው በጉጉት ይጠብቃሉ ። ዓለማየሁ አሁንም እንዳቀረቀረ ነው ።

"እሺ ለማንኛውም አቶ ወንዲራድ ያሉዎትን መረጃዎች ያመጣሉ ። ዓለማየሁ ጉዳዩ እስከሚጣራ ድረስ እስር ቤት ትገባለህ ። አቶ ወንዲራድ ምስክሮችዎን ነገ ሊያመጡ ይችላሉ ፤ በእኛ በኩል የሚጣራውን እኛ እናጣራለን ። እሺ ወደ ውጭ እንውጣ" ወረቀቶቹን ሰብስቦ ቀድሞ ወጣ አላምረው ። ወንዲራድ ተከተሉት ። በራቸው ላይ ያለውን ላብ በመሐረባቸው እያራረቁና ካፖርታቸውን መልበስ ጀመሩ ። ከዘራቸውን ተቀበሉና በቀኝ እጃቸው ይዘው በኩራት ተጀንነው ቆሙ ።

"ማነህ እሱን እስር ቤት አስገባ" አለ አላምረው አንዱን እጁን ወደ ዓለማየሁ ፣ አንዱን እጁን ወደ አንድ ፖሊስ እያመለከተ ። ዓለማየሁ በዐይኑ አካባቢውን ማተረና ወደኋላው ዘወር ሲል ሐረገወይንን አየ ። አለቃ ያደባብሷታል ። እሷም ቀና ብላ

ተመለከተችው ። ዐይኖቿ እንባ አቅርረዋል ። ብር አለችና ወደ እሱ ሮጠች ። እቅፍ አደረገችውና አለቀሰች ።

“እያዬሽ …ምንም የምሆነው የለም ፤ አታልቅሽ …እባክሽ አታልቅሽ” አላት እጇን ከወገቡ ላይ እያላቀቀ ።

“ወደዚህ ና ወደዚህ” አለ አንድ ፖሊስ ዓለማየሁን እየተጣራ። ዓለማየሁ ሮጥ አለ ፤ ወደ አንዱ ቢሮ ሔደ ። በሩ ላይ እንደ ደረሰ ዘወር አለና ሐረገወይንን ተመለከታት ። “እያዬሽ” አለ ለስለስ ባለ ድምፅ ፤ እጁን አርገበገበላት ። ሐረገወይን አካባቢዋን ገላመጠችና እንባዋን እየጠራረገች ፈጠን ፈጠን እያለች ወጣች ወደ ውጭ … በቁጣ አረማመድ ። አባቷ በዐይናቸው ተከተሏት ። የአጥሩን በር እንዳለፈች ከዐይናቸው ተሰወረችባቸው ። በራቸው ከማላብ ዐልፎ ውሃ የሚያመነጭ መስሏል ። በከዘራቸው የኮሪደሩን ወለል ደበደቡ።

“የአህያ ባል ከጅብ አያስጥል ፤ እካች…” አሉና በረዥሙ ተነፈሱ። “እካች” የሚለው ቃል ከአፋቸው ሲወጣ የመረራቸው መሆኑ ተሰማቸው ። በውስጣቸው የሚደለቀው የድል ነጋሪት በፊታቸው ላይ የደስታ መረቡን ዘርግቶ የእፎይታ ስሜት ወረራቸው ። ዓለማየሁ ወደገባበት ክፍል ዐይናቸውን ወርወር አድርገው መለሱና “እ…ህ” አሉ በረዥሙ ። ደሞ ቀጥ ብለው ቆሙና አሻግረው መመልከት ጀመሩ ። በድርሰቱና በተዋንያኑ ችሎታ እጅግ የረካ የቲያትር ተመልካች በትርዒቱ ፍጻሜ ከመቀመጫው ብድግ ብሎ የደመቀ ጭብጨባ እያሰማ ፤ እየጮኸ ተዋንያኑን ሲሰናበት ፤ የደስታ እንባ እየተናነቀው ከኋላ ሆኖ እንደሚመለከት የተዋጣለት ጀማሪ ጸሐፊ ተውኔት ፤ እሳቸውም ጅምራቸው በመሳካቱ በውስጣቸው የሚደለቀው የደስታ ነጋሪት “ፎክር ፎክር” የሚል ስሜት አሳደረባቸው ። ዓይናቸውንና ሐሳባቸውን ከላኩበት የራቀ ቦታ ሰብሰብ አደረጉና አለቃንና አሽከራቸውን ገበየሁን ዞር ብለው ገልመጥ አደረጓቸው ። ጠደፍ ጠደፍ እያሉ ወጡ፣ ከዘራቸውን እያወዛወዙ ፤ አለቃና ገበየሁ ተከተሉአቸው ።

ገበየሁ ሮጥ ሮጥ አሉና ፡ "አለቃ አለቃ ስሙኝ ፡ እኒህን ሰው በሽታ ላይ የጣላቸው ሌላ እኮ አይደለም ፡ የዚህ ሁሉ ጉድ ጠንሳሽ እኮ ያ ዕብድ ሰካራም ነው ።" እንደምንም ብለው ይኸን ዛማኔል የሚባል ሰው ከቤታቸው ያስወጡላቸው ... ይገላግሉአቸው እባክዎ" አሉ። አለቃ ዘወርም ብለው አልተመለከቱአቸው ። ገሥገሡ ወንዲራድን እየተከተሉ ።

ምዕራፍ ሁለት

ዓለማየሁ በኪሱ ውስጥ የነበረውን አንድ መቶ አምስት ብር ለፖሊሱ ሲያስረክበው ፖሊሱ መዘገበና አስቀመጠ ። ቀበቶውንም አውልቆ ሰጠ ። በመጀመሪያ "ገንዘብህንና ቀበቶህን እዚህ አስረክበህ ነው የምትገባው" ሲባል የጥርጣሬ ስሜት አድሮበት ነበር ። ፖሊሱ ጉዳዩን በዝርዝር ካስረዳው በኋላ ግን ፣ ገንዘቡን ለማስረከብና ቀበቶውን ለማውለቅ ተስማማ ። ደሴ ወይዘሮ ስሂን ትምህርት ቤት የዐሥረኛ ክፍል ተማሪ በነበረበት ወቅት አንዱ ሰው ደብድበው ታስረው ፖሊስ ጣቢያ እየተመላለሰ ጠይቋቸዋል ። በቃ። ከዚያ በፊትም ሆነ በኋላ የፖሊስ ጣቢያን በር ረግጦ አያውቅም ። ለመታሰር የመጀመሪያ ጊዜው ነው ። የማያውቀውን አዲስ ሕይወት ፣ የእስር ቤት ሕይወት ለማየት በመብቃቱ ደስ አለው ። ከሁለት ዓመት በፊት ከዩኒቨርስቲ ለመመረቅ ዝግጅት ያደርግ በነበረበት ወቅት አንድ የሶሲዮሎጂ ተማሪ ጓደኛው ለባችለር ዲግሪ ማሟያ ያዘጋጀውንና ያነበበለትን በእስር ቤት ሕይወት ላይ ያተኮረ ጥናታዊ ጽሑፍ አስታወሰ ። የጓደኛው ጥናታዊ ጽሑፍ ባተኮረባቸው ጉዳዮች እጅግ ተመስጦ ነበር ። ዛሬ ይህንን ሕይወት በዐይኑ ለማየትና ለመቅመስ ዕድሉ ስላጋጠመው ተደሰተ። ወደ እስር ቤት ሳይሆን ወደ ቤተመጻሕፍት እንደሚገባ ሰው ራሱን አፅናና ። አንድ ባለመቶ ብርና አንድ ባለአምስት ብር ኖት ፣ እንዲሁም ቀበቶውን አስረክቦ ወደ ውጭ ወጣ ። ከበሩ ላይ የሚጠብቀው ፖሊስ "ተከተለኝ" አለና ከፊት ከፊቱ መራመድ ያዘ።

"ማነህ? ማነህ? ተመለስ ተመለስ" አለ ብሩን የተረከበው ፖሊስ።

"እኔን ነው?" አለ አለማየሁ ።

"አዎ… አንድ ጊዜ አንድ ጊዜ ይቅርታ" አለው ፖሊሱ ።

ዓለማየሁ ተመልሶ ወደ ነበረበት ክፍል ሔደ ። 'ምን ነገር ተፈጠረ' ብሎ ገርሞታል ።

"ይቅርታ ወንድሜ ፡ ልብስና ፍራሽ የሚያመጣልህ ዘመድ ካለ ስልኩን ንገረኝና እደውልልሃለሁ ። በተረፈ እስረኞቹ የሻማ ብለው ገንዘብ አምጣ ስለሚሉህ ይህችን አምስት ብርህን ይዘሃት ግባ ። የሚጠይቁህ እንኳ አንድ ብር ነው ። ዝርዝር ስለሌለኝ ነው አምስቱን የሰጠሁህ ፡ በተረፈ ከእኔ ጋር ያለህ አንድ መቶ ብር ብቻ ነው" አለ አምስት ብሩን የያዘውን እጁን ወደ ዓለማየሁ እየዘረጋ ። ዓለማየሁ ብሩን ተቀበለና አመሰገነው ። ለጥቂት ጊዜ አቀርቅሮ ቆየና "የልብሱና የፍራሹ ግን ግዴለም ይቆይ… ነገ ታስመጣልኛለህ ። ለዛሬው ይኼ አይበቃም እንዴ" አለ የጃኬቱን ኮሌታ ይዞ እየጐተተ። ኮሌታውን የጐተተው ጃኬት የሌሊት ብርድ ልብስም ሆነ ፍራሽ ሊሆን እንደማይችል ያውቃል ። ፍራሽ ካነጠፈ ብርድ ልብስ ደርቦ ከተኛ ግን የእስር ቤቱ ሕይወት ትዝታ የሚፈጥር የተለየ ሕይወት ሊሆን አይችልም ብሎ ፈራ ።

"ምን ቸገረኝ እንደ ፍላጐትህ " አለ ፖሊሱ ወደ ውጭ ለመውጣት እየተዘጋጀ ።

"እሺ …ተከተለኝ" አለው ሌላው ፖሊስ ዓለማየሁን ። እየተከታተሉ ወደ ማሰሪያዎቹ ክፍሎች ሔዱ ። ፖሊሱ በብረት መዝጊያው ላይ በትልቁ "የወንዶች" የሚል ጽሑፍ ወደ አለበት ክፍል ሔደና የበሩን ቁልፍ መክፈት ጀመረ ። ከክፍሉ ውስጥ ጫጫታ ይሰማል ። ዓለማየሁ የሚገባበትን ክፍል አረጋግጦ ሲያይና ከውስጡ ያለውን ሁካታ ሲሰማ አዲስ የእስር ቤት ሕይወት አያለሁ ብሎ የተጽናናው አእምሮው ተሸበረ ። "እሺ ግባ" አለ ፖሊሱ በሩን ገርበብ አድርጐ ከፈተና ። ዓለማየሁ ከመግባቱ ፖሊሱ በሩን ዘጋና መቆለፍ ጀመረ ። የዓለማየሁ አዲስ ሕይወት ተጀመረ ። በክፍሉ ውስጥ እግሩን እንዳሳረፈ እስረኞቹ አጨበጨቡለት ። በቂ ብርሃን ስለሌለ በውስጡ ያለውን ለመለየት አልቻለም ። ጭብጨባው ለእሱ

መሆኑ አልገባውም ። ድንግዝግዝ ብሎት እንደተገተረ ቀረ ። ወዲያው የሚያጥወለውል ግም ሽታ መጣና አወደው። ሊያስመልሰው ቃጣው ፤ ሲጋራ አወጣና አቀጣጠለ ።

“ወይ አረንጓዴ ሳሎን እንኳን በደህና መጡ ። ከእስረኞቹ አለቃ ትዕዛዝ እስከሚደርስዎ ድረስ እዚያው የቆሙበት ቁጭ ይበሉ” አንቧረቀበት ከፊት ለፊቱ ያለ አንድ ድምፅ ። ዓለማየሁ ሲጋራውን እያቦነነ ቁጭ አለ ።

“እሽ…ጸጥታ…ጸጥታ” አለ የእስረኞች አለቃ ። “አዲሱ ባልደረባችን እንኳን በደህና መጡ ። በታሰሩበት ጉዳይ ፍርድ ቤት ቀርበው እስከ ሚፈረድብዎ ወይም እስከሚፈረድልዎ ድረስ የሚተዳደሩት በዚህች ክፍል የእስረኞች ሕግ ነው ። እኔ የእስረኞች አለቃ ነኝ ፤ እዚህ የሚመለከቷቸው ። ከአሁን ጀምሮም የእርስዎም አለቃ ነኝ ያስሙኛል ?” ጮኸ ዓለማየሁ ለሱ መሆኑ አልገባውም ። ሽታው አንጀቱን ረብሾት ይተናነቀዋል ።

“እርስዎን እኮ ነው አዲሱ እስረኛ ፤ የእስረኞች አለቃ የሚለውን ይሰማሉ … ሄይ ኮር” አለ የመጀመሪያው ድምፅ ። ‘ይችን ይወዳል’ አለ ዓለማየሁ በልቡ ። ሁኔታው ገርሞት ።

“እኔን ነው እንዴ የምትናገሩ? ይቅርታ ፤ እኔን ስላልመሰለኝ ነው … እየዳመጥኩ ነው” አለ ማቅ እየተናነቀው ።

“የእስረኞቹ አለቃ ቀጥል” ብሎ ጮኸ የመጀመሪያው ሰውየ።

“እኬ…እኬ እቀጥላለሁ አስተዋዋቂ ። አስረሳችሁኝ እኮ ምን ላይ ነው የቆምኩት …”

“ሸማግሌው ተደናበሩ አለ ያ ጋዜጠኛ ያደናብረውና” ብሎ ጮኸ አንድ ወፍራም ድምፅ ያለው እጥግ የተቀመጠ ሰው ።

“አንተ ወፈፌ ዝም አትልም ፤ ያን የለመድከውን የቃሪያ ጥፊ ትቀምሳለህ…” ተቆጣ አስተዋዋቂው ።

“በረፈረፉ በአፍ ተደፉ … በረፈረፉ በአፍ ተደፉ…” ይጮኻል ወፈፌው ።

“በለው በጥፊ በለው”

“ፏ.”

“ይገመቱ”

“ፏ.”

ጭጭ አለ ወፈፈው ። የእስረኞች አለቃ ጸጥታ መስፈኑን ካረጋገጠ በኋላ ገለጻውን ጀመረ ። “እሺ አዲስ እስረኞችን ፡ እንኳን በደህና መጡ ብለንዎታል ። በዚች ክፍል ሕግ መሠረት እያንዳንዱ አዲስ እስረኛ እንግዳችን ነው ። ሁላችንም ራሳችንን እናስተዋውቀዋለን ። እሱም ራሱን ያስተዋውቀናል ። ያስተዋውቃል ስልዎ የተወለደበትን ፡ ያደገበትን ሁሉ ይዘረዝራል ማለት ሳይሆን ፡ የታሰረበትን ምክንያት ብቻ በአጭሩ ይገልጻል ማለቴ ነው። እዚህ ክፍል ያሉት ከሁሉን እስረኞች ራሳቸውን ካስተዋወቁዎት በኋላ በመጨረሻ ራስዎን ያስተዋውቃሉ። አዲስ እስረኛ እስከሚመጣ ድረስም እንግዳችን ሆነው ይቀመጣሉ ። አዲስ እስረኛ ከመጣ እርስዎ ነባር እስረኛ ይሆናሉ ። እንግድነትዎ ያከትማል ማለት ነው ···ገባዎት ···”

“አዎ ገብቶኛል” አለ ዓለማየሁ ። ነገሩ ሁሉ ደስ ብሎታል ። ከእስር ቤት ወጥቶ የእስር ቤቱን ሕይወት ለጓደኞቹ ለማውራት ችኩሏል ። አዲስ ሲጃራ አወጣና አቀጣጠለ ። ሌሎቹ ሱሰኛ እስረኞች በእሱ ሲጃራ ማጨስ ቀንተዋል ። ዓለማየሁን ሊለምኑት ፈልገዋል ። ግን የእስረኞች አለቃ ከእንግዳ እስረኛ ለመናችሁ ብሎ የቃሪያ ጥፊ ያዝብናል ብለው ፈርተው ዝም አሉ ።

የእስረኞች አለቃ በዙሪያው የተቀመጡትን እስረኞች በየተራ ተመለከታቸው ። አንዳንዶቹ ያንቀላፋሉ ፡ አንዳንዶቹ በሐሳብ ማጥ ውስጥ ገብተው ይዳክራሉ ፡ አንዱ ጸጉሩን ይፎክታል ። የእስረኞቹ አለቃ እስረኞቹን በየተራ ሲመለከት አንድ ጊዜ ፈገግ ፡ አንድ ጊዜ ኮስተር አንድ ጊዜ ቆጣ እያለ ነው ። ከሚያንቀላፉት በቀር ሌሎቹ አፍጠው ይመለከቱታል ።

“እሺ ከመንዜው እንጀምራለን ። መንዜው ··· ራስህን አስተዋውቅ··· አሳጥረህ የታሰርክበትን ምክንያት ለእንግዳው እስረኛ አውራ” አለ በትዕዛዛዊ ድምፅ ።

"እንግዲህ የአዲስ አበባ ሰው ሲታሰር ሲፈታ ይውላልና እኔ ታሪኬን ለድፍን ዓለም ሳወራ ልከርምልህ ነው? ቃሌን እንደ ሰጥቻለሁ ሁለተኛ ስለፈለፍ አልናገርም ፡ እንዴ ትዕግስትም ድንበር አለው እኮ ። ሀሞቴ ለፋፌ አረከኝ እንዴ! አልናገርም አልኩህ ፡ ሁለተኛ አልናገርም ቃሌን እንደ ሰጥቻለሁ አልኩህ" እየተቆጣ መልስ ሰጠ መንዜው ።

"አትናገርም ማለት ነው?" አምባረቀበት የእስረኞቹ አለቃ ።

"እም! አልናገርም አልኩህ ። አሁንማ መቀለጃ አረከኝ እኮ! ያንተ ሳንቲም ይቅርብኝ ተወው…ጥንቅር ይበል ። ደሞስ እስረኛ በመጣ ቁጥር ስታስለፈልፈን ታሪካችንን ሁሉ በውቀኸዋል ፡ ከፈለክ ራስህ ተናገር ፡ የሁሉንም ራስህ ተናገር ይመርብህ ተናገር ።"

"እሽ እኔ የአንተን አስተዋውቃለሁ ። ሌሎቻችሁ ራሳችሁን ታስተዋውቃላችሁ ፡ እሽ"

ዓለማየሁ የክፍሉን ሽታ ለምዶት የአንጀቱ መረበሽ ጋብ ብሎለታል ። ሐሳቡ ከሐረገወይን ጋር ነው ፡ "ከቤተሰቦቿ ጋር ትጣላ ይሆን? በብስጭት መኪና ይገጫት ይሆን? እነዚያ አርከሶች አንድ ነገር ያደረጓት ይሆን?" የተለያየ መልክ ያለው ጭንቀት አዕምሮውን ረበሸው ። የንንለት የእስር ቤት ሕይወት ለአፍታ ሰለቸው።

"ጸጥታ …መንዜውን ለእንግዶችን አስተዋውቃለሁ ገም በሉ" አለ የእስረኞቹ አለቃ ። "መንዜው የዚህ ክፍል አባል ከሆነ ዛሬ አምስተኛ ቀኑ ነው ። የታሰረው በግድያ ወንጀል ነው ። ታሪኩ እንዲህ ነው ። ከሐያ ዓመት በፊት አባቱ ከአንድ ሰው ጋር በመሬት ሙግት ገጥመው ብዙ ዓመት ከተከራከሩ በኋላ ጠላታቸውን ይረቱታል ። እሱም አዲስ አበባ ድረስ መጥቶ ይግባኝ ይልና ከሞላሌ ድረስ አስጠርቶ ይሟግታቸዋል ። እዚህ አዲስ አበባም የመንዜው አባት ጠላታቸውን ይረቱና ደስ ብሎአቸው ወደ ሀገራቸው ይመለሳሉ ። መሬታቸውን ማረስ ይጀምራሉ ። ልክ በረቱት በሁለተኛው ወር ያ ጠላታቸው መንገድ ላይ ይጠብቅና በጥይት ወይንስባቸውን ያወልቀዋል ።"

"ማም… የማም ውላጅ" መንዜው ብድግ አለ "ደሞ በጥይት ገደላቸው ማለት እንስሀና የምን ስድብ ነው አንተ ፡ የአንተ አይነገጃ ይውለቅ ፡ ማም የማም ውላጅ…."

"በቃ በቃ መንዜው ያስተካክልልሃል" አለ የእስረኞች አስተዋዋቂ ። የእስረኞች አለቃ ከትከት ብሎ ሣቀና ታሪኩን ካቆመበት ቀጠለ ።

"አባቴ ሞቴ… መንዜው አልቅሶ ቀበረ ። ያን ጊዜ ሕፃን ልጅ ነበር ‥"

"እስተካክል የምን ሕፃን ! ዐሥራ ሰበት ዓመቴ ነበር ።"

"እሽ አሥራ ሰባት ዓመቴ ነበር ። አባቴን የገደሉት ሰው ተከሰሱና ፍርድቤት ቀርበው የሐያ ዓመት እስራት ተፈረደባቸው ። መንዜው ሐያ ዓመት ሙሉ ቀኗን ስትቆጥር ትቆይና ሰውየው የሚፈቱበትን ቀን አስልቶ ወደ ደብረ ብርሃን ይመጣል ። ደብረ ብርሃን አራት ቀን እንዳደረ የአባቴ ገዳይ ተፈተው በመንገድ ሱክ ሱክ እያሉ ሲሔዱ ያያቸዋል ። መንዜው 'ይችን ይወዳል…' ይልና ባዘጋጀው ጩቤ ዘክዝኮ አምልጦ ወደ አዲስ አበባ ይሸሻል ። ሦስት ቀን አላደረም ጋማውን ተይዞ እዚህ እኛ ጋ ነው እልሃለሁ' አይደለም እንዴ መንዜው?"

"አዎ ትክክል ነው ፡ አሳምረኸዋል ፡ ተንግዲህ በእኔ ፋንታ አንተን ወክያለሁ ፡ በቃ ወክየሃለሁ" አለ መንዜው እየሣቀ ። የእስረኞች አለቃ መንዜው ዝም እንዲል አስጠንቀቀውና "እሽ ቀጥሎ ማን ይሁን" በዙሪያው ያሉትን እስረኞች ተመለከተ ። "በቃ በቃ ጆሬ ቀጥል"አለ ። ጆሬ ቀጠን ያለ ልጅ እግር ነው ።ከእስረኞቹ ሁሉ በዕድሜ ትንሹ እሱ ነው ። ተራው ስለ ደረሰው ጉሮሮውን ጠራረገና ጀመረ ራሱን ማስተዋወቁን ፡

"የእኔ እኳ ዝም ብሎ ነው ። በምንተፋ ነው የታሰርኩት ። እምና ሦስት ሆነን ስድስት ቁጥር አውቶቡስ ላይ ነበር የምንሠራው፣ ሁለት ወርም ሳንሠራ ተነቃብንና ወደ ሦስት ቁጥር ተዛወርን። እዛም ላይ ችግር ስላጋጠመን ወደ ዘጠኝ ቁጥር ተሸጋገርን ።

ጥሩ ገበያ ነበረን ፤ ግን ምን ያደርጋል ጥቂት ወራት እንደሠራን እኔ ተያዝኩ ። ያውም እኮ አውቶቡሱ እዚህ ማቢያ ድረስ አምጥቶ ነው አስረክቦኝ የሔደው ። በአውቶቡሱ ውስጥ የነበረው ሰው ሁሉ ያቀመሰኝ እርግጫ ይብቃ ነበር ። ግን ምን ታደርገዋለህ እጅ ከፍንጅ ስለሆነ ወደዚህ መጣሁ ከእንግዲህ በእኔ በኩል ዘጠኝ ቁጥር አክትሞለታል ማለት ነው ። አይበቃም?... ባጭሩ ይኸው ነው ።”

“ጥሩ በጣም ጥሩ ግን ይቀጥል ? እሽ ወፈፌው ተናገርና ይውጣልህ ... ቀጥል ።”

“እኔን ዝም ብለው ነው ያሰሩኝ ። ለምን ጠጣህ ለምን ሰከርክ ብለው በምቀኝነት” አለ ወፈፌው ራሱን እያከከ ፤ “እስኪ በራሴ ገንዘብ በጠጣሁ ምን አደረኳቸው ፤ ትንሽ እለማምንና ገንዘቧ ጠርቀም ስትል ባሻዬ ጠጅ ቤት እሔድና እጠጣለሁ ። እዚያም ባሻዬ ቤት ሰው አይጨክንብኝም እጠጣለሁ ፤ ጠጥቼ እደሰታለሁ ። በቃ ። ታዲያ ለምን ጠጣህ ? ለምን ሰከርክ ? ብሎ ሰው ማሰር አለ እንዴ ? ‘በረፈረፉ በአፍ ተደፉ’ አለ አያ ወልዴ ! ምንም ሳላደርግ መታሰር አለ እንዴ ? ይኸው ነው እንግዲ የእኔ ታሪክ ።”

“አትዋሽ እውነቱን ተናገር ! ያችን እምትወዳትን ጥሬ ትቀምሳለህ” አስፈራራው የእስረኞቹ አለቃ ።

“በቃ ይኸው ነው እውነቱ ። እርግጥ ባሻዬ ቤት ጠጥቼ ወጣሁና ቁልቁል ወደ ጉልት ስሔድ ሦስት ሴቶች ከፊት ለፊቴ ሲመጡ አየኋቸው ። እኔ ፈጽሞ አላሰብኩትም ነበር ። ቀና ብዬ በየተራ ስመለከታቸው አንዷ ደስ አለችኝ ፤ ውድድ አደረኳት ። በጣም ውድድ አደረኳት ። ተዚያማ... ተንደረደርኩና እቅፍ አድርጌ ስስም ፤ ስስም ፤ ስስም ። ከወደጀርባዬ በኩል ቀፈፈኝ ፤ አንድ ጊዜ ሳም አደረኩና ዞር ስል ሁለት ፖሊሶች ጨምድደው ይዘውኛል ። በናታችሁ የመጨረሻ አንዴ ልሳም ብላቸው እየጐተቱ አመጡኝ ። አይ ጭካኔ ! በቃ ይኸው ነው አለቃ ...” ።

“እውነቱን ተናገር ብየሃለሁ አንተ ወፈፌ”

“አለቃ አላበዛኸውም ፤ እውነቱን ነገርኩህ ፤ ከዚህ ወዲያ

የሥላሴን ጽላት ሰረቅሁ ወይስ የአራት ኪሎን ባንክ ዘረፍኩ ልበልህ ወይስ እንደ መንዜው ወንድ ወቶኝ ሰው በጩቤ ዘከዘኩ ልበልህ"

"እሽ በቃህ አትለፍልፍልብኝ ፡"

"አለቃ አንድ ጊዜ ፡ አንድ ጊዜ ፣ በናታችሁ ፍቀዱልኝ ! ሁላችሁም ፍቀዱልኝ !"

"ምንድነው የሚፈቀድልህ ?" የእስረኞቹ አለቃ ተቆጣ ። ወፈፌው ከተቀመጠበት ተነሣ ።

"በናታችሁ ፡ በናታችሁ ፡ እንደ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በአንድ እግሬ ቆሜ ሰባት ዓመት እጸልይላችኋለሁ እንድትፈቱ ። አንድ አፍታ ፍቀዱልኝ… ልጩህ አንድ ጊዜ ልጩህ … ፍቀዱልኝ" ተማፀናቸው በክፍሉ ውስጥ ያሉትን እስረኞች ሁሉ ። ዓለማየሁ ሣቁን መቆጣጠር አልቻለም ።

"አይሆንም ተቀመጥ ፡ አይሆንም ተቀመጥ… ወፈፌ" ጮሁበት።

"እሽ ዐሥራ አራት ዓመት ላድርግላችሁ"

"አይሆንም ተቀመጥ …"

"እሺ ሐያ ዓመት ላድርግላችሁ"

"ሲናገሩህ አትሰማም አንተ ወፈፌ ?"

"ከሐያ ዓመት በላይስ አንድ ቀንም አልጨምርላችሁ እዚሁ በስብላችሁ ቅሩ" አለና ተቀመጠ ።

"በጥሬ በለው ፡ አትምሰው አንድ ጊዜ ።"

"ጪ."

"ድገመው"

"ጪ."

የእስረኞች አለቃ በቁጣ ማስጠንቀቂያ ሰጠና እስረኞች ራሳቸውን ሲያስተዋውቁ አጠር አድርገው እንዲናገሩ ፡ ትርፍ ቃል

እንዳይጨምሩ አሳሰበ ። ከወፈፌው በኋላ ሰባት እስረኞች በየተራ እየተነሡ ራሳቸውን አስተዋወቁ ። ግማሾቹ ዓይነ አፋሮች ናቸው ። አለቃው ባስጠነቀቀው መሠረት አጠር አጠር እያደረጉ ተናገሩና ቁጭ አሉ ።

"እሺ አሁን ተራው የእንግዳችን ነው ፣ ሌሎቹን እንደ ሰሙት ሁሉ አጠር አድርገው ራስዎን ያስተዋውቁ" አለ የእስረኞች አለቃ ወደ ዓለማየሁ እጁን እየጠነቆለ ።

ዓለማየሁ የሚናገረው ጠፋው ፣ ተምታታበት ። ሌሎች እስረኞች ራሳቸውን ሲያስተዋውቁ እሱ መናገር የነበረበትን ማሰብ ነበረበት ። ይህንን ስላላደረገ ተናደደ ።

"የእኔ እንኳ ገና የሚጣራ ጉዳይ ነው ፤ በሐሰት ነው ተወንጅየ እንድታሰር የተደረገው" አለ እየፈራ እየቸረ ።

"እኮ ሐሰትም ቢሆን ምን ተብለው ነው የተወነጀሉት ?" የሚያወላውል ጥያቄ ሆነበት ። ልናገር አልናገር እያለ ለጥቂት ጊዜ ከራሱ ጋር ተሟገተ ።

"እንዲት ልጅ ደፍረሃል ተብየ ነው የተከሰስኩት"

ድንገት ከአፉ የወጣው ቃል ራሱንም ገርሞት አፉን ያዘ ። በዚህ መልክ ሊያቀርበው አልነበረም ፍላጎቱ ፤ የፈሰሰ ውሃ አይታፈስም ። ዝም አለ የእስረኞች አለቃ የሚለውን ለመስማት ።

"ታዲያ ይህ ያሸልማል እንጂ እስር ቤት ያስገባል እንዴ !" አለ የእስረኞች አለቃ ።

"እንኳን የደፈረው እኔስ ሳምኩ ተብየ ታስሬ የለም" ብስጭት አለ ወፈፌው ።

የእስረኞች አለቃ የማስተዋወቁ ሥነ ሥርዓት ማለቁን አስታወቀና በእስረኛ ደንብ መሠረት የሻማ አንድ ብር እንዲከፍል ዓለማየሁን ጠየቀ ። ዓለማየሁ ከኪሱ ያለችውን አምስት ብር አውጥቶ ሰጠ ። አብዛኞቹ እስረኞች አራት ብሩ አይመለስ ሲሉ

ወፈፌውና መንዜው ያመለሰለት ብለው ድርቅ አሉ ። አራት ብሩ ተመልሶለት ከሌሎቹ እስረኞች ጋር ተቀላቅሎ እንዲቀመጥ ተፈቀደለት ።

ዓለማየሁ የእስር ቤቱን ሽታ እየለመደው መጣ ። ካልጠጣሁ እያሉ ሲተናነቁት የነበሩት በምሳ ሰዓት የበላው ቅቅልና የጠጣው ኮካኮላ ተረጋጉለት ።

"ወደ እኛ ተቀላቀል" ብሎ የእስረኞቹ አለቃ ትዕዛዝ እንዳስተላለፈለት ከወፈፌው ወይንም ከመንዜው ጐን ለመቀመጥ አስቦ ነበር። ወዲያው ሐሳቡን ለወጠ ። ሌሎቹን እስረኞች ተራምዶ መሔዱን በአንድ በኩል አልወደደውም ። የድፍረት መስሎ ታየው። በሌላ በኩል መንዜውና ወፈፌው የተቀመጡበት የእስር ቤቷ ክፍል ጥግ ሙቀት እንደሚረብሸው ገመተና ከበሩ አካባቢ ላለመራቅ ወሰነ ። እስረኛው ሁሉ እርስ በርሱ እያወራ ፡ እየተራበሸ እየተኮማመከ ሲሳሳቅ ዓለማየሁ ከራሱ ጋር ትግል ጀመረ ። ሐሳቡ ሁሉ ሐረገወይን ጋር ሆነ ። ስለ ሐረገወይን ሁኔታ ጥቂት ካሰበ በኋላ ወደ ሚልክያስ ተሸጋገረ ። "ሰው እንዴት ሰውን በገንዘብ ለመግዛት ይሞክራል ?" ብሎ እንጀቱ አረረ ። ስለ ወሰንየለህም አሰበ ፡ የባሰውን ተናደደ ።

የእስር ቤቱ በር ቁልፍ ሲንኳኳ ዓለማየሁ ከነበረበት የሐሳብ ባህር ውስጥ ወጣና በር በሩን መመልከት ጀመረ ። በሩ ገርበብ ብሎ ተከፈተና አንድ ሰው ወደ ውስጥ ገባ ። ዓለማየሁ ሰውየውን ሲመለከተው ድንግጥ አለ ። ይተዋወቃሉ ፡ ዩኒቨርስቲ ተማሪ በነበረበት ጊዜ ያውቀዋል ። የተመረቁትም አንድ ላይ ነው ። ሰውዬው ቡላ ቀለም ያለው ኮትና ሱሪ ሱፍ ለብሷል ። ከበሩ ላይ ቆመና የቀኝ እጁን መዳፍ ግንባሩ ላይ ተክሎ እንደ ወታደራዊ ሰላምታ ዓይነት አደረገና በጨለማው ክፍል ውስጥ ያለውን ለመመልከት ሞከረ ። ዓለማየሁ "ሲሳይ" ብሎ ሊጠራው ፈለገና ፈራ ።

ወዲያው የእስረኞች አስተዋዋቂ "እንኳን ደህና መጡ" በማለት ተቀበለው ። ማስተዋወቁ ቀጠለ ። እንግዳው እስረኛም ራሱን አስተዋወቀና በሩ ጥግ ቁጭ አለ ። ብዙም ሳይቆይ ሌላ እስረኛ መጣ ፡ ሽምግል ያሉ ሰው ናቸው ። አጐንብሰው ገቡና ተቀመጡ "እንደምን ዋላችሁ ልጆቼ ፡" እያሉ ። የታሰሩት አሮጊት ሚስታቸውን ደብድበው ነው ። "ነገር ገብቶኝ ነበር ። እንደው አንድ ነገር ስትናገረኝ ጊዜ ብልጭ አለብኝ ፡ ከጐኔ ባገኘሁት የቤት መቀርቀሪያ ክፉኛ ነው የመታኋት" እያሉ ይጸጸታሉ ። እርሳቸውም ራሳቸውን አስተዋወቁና ቁጭ አሉ ።

"ሲሳይ ሲሳይ" ተጣራ ዓለማየሁ ። ሲሳይ ግራና ቀኙን ተመለከተና "እኔን ነው" አለ በተደናገረ ድምፅ ።

"ዓለማየሁ ነኝ ና ወደዚህ ።"

ዓለማየሁና ሲሳይ ተሳሳሙ ። ሁለቱም ይሥቃሉ ። የተገናኙበት ሁኔታ ደንቋቸው ሽማግሌውን ከዳር አድርገው ጐን ለጐን ተቀመጡ ። "አይ አጅሬ" "አይ አጅሬ" መባባል ጀመሩ ።

"አይ ሲሳይ ድሮም እኮ ተደባዳቢ ነህ ። ደሞ ምን አድርጎ ብለህ ነው አለቃህን የምትደበድበው ። ደሞ እንደ ጀግንነት ቆጥረህ ታወራዋለህ እስር ቤት ውስጥ ። እኔ እምልህ በምን ተጋጭታችሁ ነው ድብድብ የደረሳችሁት ?"

"እባክሽ ብዙ ነው ታሪኩ" ··· ሲሳይ በቅርብ የሚያውቃቸውን ወንዶች ሁሉ አንቺ እያለ ነው የሚያናግረው ።

"ባጭሩ ስትናገረውማ ሰምቻለሁ ፡ አሁን የምጠይቅህ እኮ ዝርዝሩን እንድትነግረኝ ነው ሲሳይ··· በምን ተጋጫችሁ ።"

"ዝርዝሩ ብዙ ነው አልኩሽ ። ግን ባጭሩ ንገረኝ ካልሽኝ እነግርሻለሁ ። ምን ታደርጊዋለሽ ! እኔን እዚህ ጨለማ ቤት ወርውሮ ይኸን ጊዜ እሱ ይንቀባረራል ። ጋደኛም ሺት ··· ሰው በስንቱ ይቃጠላል ። ሙች ! በጣም እኮ ነው የሚያበሽቅ ። የሰው አንጀት ይገርመኛል የዳቦ መጋገሪያ ሸክላ እኮ ነው ። ስንቱ

ያጠብሰዋል ፡ ስንቱ ያቃጥለዋል ፡ ስንቱ ያንገበግበዋል ፡ ግን ንቅንቅ አይልም ይገርመኛል …”

“አሁን አሊቃህ እዚህ ስለሌለ መናደድ የለብህም ፡ እዚህ የምታያቸው ሰዎች የየራሳቸው ታሪክ ያላቸው የየራሳቸውን ክፉና ደግ ሠርተው የተሰባሰቡ ሰዎች ናቸው ። አንደ ሰማሃቸው ሲናገሩ ደስ የሚሉ የሚያዝናኑ ሰዎች ናቸው ። ይህን ያለህበትን ቦታ እንደእኔ የምትወደው ከሆነ አዲስ ሕይወት የሚቀመስበት ቦታ ነው፡ እንደ ሳናቶሪየም ልትቆጥረው ትችላለህ ሳይሰማህ ለመውጣት ከፈለግህ ። እኔ የምልህ ሰውየውን እርሳውና ፡ የተናደድክበትን ጉዳይ ቸል በለውና ታሪኩን ንገረኝ ነው ። ሲሳይ ቻል አድርገው ።”

“ዓለማየሁ ምን መሰለሽ ? ሐሳብሽ ይገባኛል ፡ ግን የሚያናድድሽ ነገር ፡ የሚያቃጥልሽ ነገር እኮ ትዝታው ተከትሎሽ የትም ስለሚሔድ በእውን ልትርቂው አትችይም ። ገባሽ ? ከሁሉም በላይ ደግሞ የሚቃጠል አንጀትሽን ቆርጠሽ ልትወረውሪው አትችይም ። ትሸክመሽው ነው የምትዞሪው ፡ እና በየዞርሽበት ትቃጠያለሽ ማለት ነው ፡ የተቃጠለ አንጀትሽን አውልቀሽ እስካልጣልሽ ድረስ። የትም ሒጂ የት ትቃጠያለሽ ማለት ነው ። እና በአጭሩ ውስጥሽ እያረረ ላይ ላዩን ልጣቅ ብትይ ራስን ማጽናናት ሳይሆን ራስን ማታለል ነው ። ራስን ማታለል ደግሞ ከወንጀሎች ሁሉ የከፋ ወንጀል ይመስለኛል ። ስለዚህ ነው የምናደደው ገባሽ ?”

“ይገባኛል ሲሳይ ። የምትለው ይገባኛል ግን አልደግፍህም ። ማለቴ ሐሳብህን አልደግፍም ። ሰው በዚህች ዓለም ላይ በሚቆይበት በስንዝር በሚቆጠር ዕድሜ ውስጥ እጅግ የተለያዩና የሚቃረኑ ሁኔታዎች ይገጥሙታል ። በእርግጥ እያንዳንዱን ሰው በተናጠል ወስደህ በሕይወቱ ውስጥ የገጠመውን መከራ ፡ ያየውን ሥቃይ ያሳለፈውን የደስታ ሕይወት መርምረህ ለመሆኑ ስንት ዓመት ኖሮ ሞተ ብለህ ብትጠይቅ ለማመን ያስቸግርሃል ። ዕድሜውና ያሳለፋቸው እጅግ የበዙና የተለያዩ ነገሮች አይመጣጠኑልህም ። ‘በዚህች አጭር ዕድሜ ነው ይህንን ሁሉ ያደረገው ? በዚህች አጭር ዕድሜ

ነው ይህ ሁሉ የደረሰበት ? ይህ ሁሉ የተፈራረቀበት ?" ብለህ ትገረማለህ ። አየህ በሕይወታችን ውስጥ እንደዋዛ የምናሳልፋት እያንዳንዷ ሰኮንድ ዋጋ አላት ። ብዙዎቻችን ግን እንንቃቃለን ። በአጭሩ ምን ለማለት ነው የምፈልገው ፡ ሰው ይደሰታል ፡ ይናደዳል፡ ያለቅሳል ፡ ይቦርቃል ። በዚህ እንስማማለን አይደለም ።

"ይኸ በዳቦ መጋገሪያ የመሰልከው እንጆታችን ይኸንን ሁሉ ያስተናግዳል ። አንድ ጊዜ ተናድጃለሁ ፡ አንድ ጊዜ ተበሳጭቻለሁ ብሎ ዳግመኛ አልደሰትም ፡ አልዝናናም አይልም ማለቱ ነው ። እና አንተም ካሊቃህ ጋር ተጣላህ ቅድም ፡ ይህ የሕይወትህ አንድ ክፍል ነው ፡ በተወሰና ጊዜና ቦታ የተፈጸመ ። ምናልባትም ቢሮአችሁ ውስጥ ። አሁን ደግሞ ያለኸው ሌላ ቦታ ነው ። በሌላ የሕይወትህ ክፍል ውስጥ ነው ። እና እርሳውና ተደሰት ነው የምልህ ። አዕምሮህ እኮ የአንተ ነው እንጂ የሌላ ሰው አይደለም ። እና እዘዘው ነው የምልህ ።"

ዓለማየሁ ጓደኛውን ሲሳይን ለማጽናናት ብዙ ምስቅልቅል ሐሳብ ውስጥ ለመግባት አልፈለገም ። የእሱ ጭንቀት ከጓደኛው ጭንቀት እንደማያንስ ያውቃል ። ይሁንና በዚህ ዓይነቱ ውይይት ጊዜውን ለማሳለፍና ጭንቀቱን ለመርሳት ስለ ፈለገ ጥሞታል ። የሲሳይን ታስሮ መምጣት ለእርሱ ማጽናኛ ታስቦ የተደረገ አድርጎ ቆጠረው።

የእስር ቤቱ ሰዎች ግማሹ ያንቀላፋል ። ግማሹ ያወራል ። ከአዲሶቹ እስረኞች በተሰበሰበው ሳንቲም ሲጋራ ተገዝቶ እስረኛው ሁሉ ያጨሳል ። ክፍሏ በጢስ ተጨናንቃለች ። መንዜው 'አላጨስም' ብሎ በማንገራገሩ ወፈፌው ጢሱን እያንቧለቀበት ተጣልተው ከተደባደቡ ወዲህ ክፍሏ ሰላም ሰፍኖባታል ። የእስረኞቹ አለቃ የመንዜውን እግር ተንተርሶ ያንቀላፋል ።

"ይገባኛል… ይገባኛል" አለ ሲሳይ ጥቂት አሰብ ካደረገ በኋላ፡ "ምን መሰለሽ አሌክስ ? አንድ ጊዜ ካዘንሽ ሁልጊዜም

ታገኛለሽ ማለቴ አይደለም ። ተደስችም ፡ ምንም በደ ያ የተከፋሽ በት ሁኔታ ቀንና ሌሊት እየመጣ ያባንንሻል ፡ ያፈታትንሻል ፡ ያስጨንቅሻል ። ልትረሺው ስትፈልጊ እምቢ ይልሻል ። አዕምሮሽ እሺ ብሎ ወደሌላ አቅጣጫ አይንዝልሽም ። ሰው ሁሉ ያስጠላሻል ። ለዚህ ነው በስጨትጨት ያልኩብሽ ።”

“እሺ አሁን ይኸንን እርሳውና ከአለቃህ የተጣላህበትን ጉዳይ እስኪ አውራኝ ሲሳይ ?”

“ነገሩ ምን መሰለሽ ፡ አንድ ትዕዛዝ መጣ ። አለቃዬ ያንን ወደ እኔ ይመራዋል ። በእውነት እልሻለሁ ተጨንቄ ተጠብቤ ሠራሁት ። በሥራው ረካሁበት ። መጨረሻ ለአለቃየ ወስጄ አስረከብኩት ። በእርግጥ ከመቀመጫው ተነሥቶ ተቀበለኝ ። ይህ ደስ ብሎኛል ። ይህንን ያደርግ ማለቴ ግን አይደለም ። እና ስለ ሥራው አስረዳሁት። ራሱን ነቅንቀና ‘የለም ይህንን እንዲህ አድርገው’ አለኝ ። አስረዳሁት ፡ ‘የለም እንዲህ አድርገው’ አለኝ ። ‘ይኸ ከሆነ ይሳሳታል ትክክል አይሆንም’ ። አጥቦ አጥቦ ጭቃ አለልሽ አይደለም ። እንደሱ ይሆናል ብዬ ለማስረዳት ሞከርኩ ። ነገሩ በጣም ሰፊ ነው ። ግን በአጭር ምሳሌ ብገልጽልሽ ደስ ይለኛል ። … ሁለትና ሁለት ሲደመር አራት ብዬ ሠራሁ ። ይኸ ትክክል ነው አይደለም ? እሱ አየና አምስት አድርገው አለኝ ። የለም ሁለትና ሁለት አምስት ሆኖ አያውቅም አልኩ ። ‘ነግሬሃለሁ አድርግ’ አለኝ። ‘እኔ አላደርግም። ከፈለግህ ራስህ አድርገው’ አልኩት ። ተቆጣልሽና ከመቀመጫው ተነሣ ። ‘ስማ እኔ አለቃህ እኮነኝ’ አለኝ ‘ዐውቃለሁ አለቃዬ ነህ’ አልኩት ። ‘ታዲያ የማዝህን አትሠራም ?’ ፡ ‘የምታዝኝን እሠራለሁ ይህንን ሁለትና ሁለትን አምስት በል ያልከኝን ግን አላደርግም’ አልኩት ። ‘ለምን’ አለ ፊቱ ሁሉ ልውጥውጥ ብሎ ። ‘መቼስ ሁለትና ሁለት አራት መሆኑን እያወቅሁ አምስት ለማለት ሕሊናዬ አይፈቅድልኝም ፡ ራሴን አታልዬ ስጨነቅ አላደርግም ፡ አንተም ሁለትና ሁለት አራት መሆኑን ታውቃለህ ። ግን የአንተ ሕሊና የሚፈቅድልህ ከሆነ አራትን ሰርዘህ አምስት በለው’ አልኩና

ወረቀቱን ሰጥቻቸው ልወጣ በሩ ጋር ስደርስ 'ውጣ እኮ አላልኩህም' አለኝ ። … 'ዶክተር' አልኩና ተመለስኩ ። 'ሦስት ደቂቃ ሰጥቼሃለሁ በሦስት ደቂቃ ውስጥ ሠርተህ ባታመጣ አንተን አያድርገኝ' አለና ወረቀቱን ፊቴ ላይ ወረወረው ። ብልጭ አለብኝ … በቃ… ብልጭ አለብኝ አልኩሽ ።"

"እና ደበደብከው ?"

"ወይ እስኪጠላ ነዋ ! ማን ምን ታደርጊዋለሽ ሚኒስትሩ የቅርብ ዘመዱ ናቸው ። እያዋከቡ አመጡኝ" አለና ኪሱን መዳበስ ጀመረ ።

ወረፈው ተነሣበትና ጮኸ ። እስር ቤቱን አንድ ጊዜ በጠበጠው ። ጆሮዎቹን ግራና ቀኝ በሁለቱ መዳፎቹ ሸፍኖ ኡኡታውን አቀለጠው ። አከታተለና ጮኸ ።

"ልማዱን ስጠው ፡ አቅምሰው አንድ ጊዜ በለው" አለ የእስረኞቹ አለቃ ።

"ፏ."

"ድገመው"

"ፏ."

ወረፈው ለጥቂት ጊዜ ዝም ብሎ ቆየና "እሺ አንድ ሲጃራ ስጡኝ እዩ … እዩ … ገና ገና እንተሳሰብሃለን … የሻማ እያልክ የምትሰበስበውን ሁሉ የት እንደምታስገባው እንተሳሰብሃለን ።

ሒድና ፒያሳ ሞኝህን ብላ ፡ በእንተ ቤት አራዳ መሆንህ ነው ። አጋሰስ … አሁን አንድ ሲጃራ ስጠኝ" የእስረኞች አለቃ ላይ አፈጠጠበት ።

"አንተ ወረፈ አታርፍም" አለ አለቃ ።

"አላርፍም ባላርፍ ምን ታደርገኛለህ"

"ያን የለመድከውን ጥፊ ትቀምሳለህ"

"አሁንስ አበዛኸው ማን አባቱ ነው የሚመታኝ? እስኪ ወንዱ ንክች አድርጉኝ" ወደ መንዜው ጠጋ አለና ቱግ አለ ። መንዜውን ገላመጠው ። መንዜው ወፈፌው ቢሰድበውም ይወደዋል ፤ ያዝንለታል ።

"እንዴ! አሁንስ እንደኛውን ወንፈት አረጋችሁት እኮ ጠፍጥፋችሁ ልትገሉት አይደል እንዴ ፤ ኧረ በሕግ ተዳኙ! እንዴ ተወንድ ልጅ በጥፊ ይመታል ። ሕግ ይዳኛችሁ ።" ጮኸ መንዜው ። ወፈፌው አጓኸ ሰላቴን ይበ አለው ። እጅጌውን ሰበሰበና እጁን ለቦክስ አዘጋጅቶ ተነሣ ። ሁሉም ትኩር ብለው ይመለከቱታል ። ዓለማየሁ ከኪሱ አንድ ሲጋራ አወጣና በቀኝ እጁ ሦስት ጣቶች የሲጃራውን ሜፍ ያዘ ፤

"አለቃ ሲጃራ ልስጠው?" አለ ።

"ስጠው ··· ስጠው"

ሲጃራውን ለወፈፌው ወረወረለት ።

"ጉሽ ··· የተማረ ሰው ያስታውቃል ፤ በል በነካ እጅህ ደግሞ ክብሪት ስጠኝ"

ዓለማየሁ ማት አለና ክብሪት ወረወረለት ። የእስር ቤቱ ረብሻ ጋብ አለና ሁሉም የየግሉን ጭውውት ጀመረ ። ዓለማየሁ ወደ ሲሳይ ዞር አለ ፤ ያቋረጡትን ጨዋታ ለመቀጠል ። የቆመበት ጠፍቶት ጥቂት አሰበና ፤

"በጣም ባለጌ ነህ ፤ በእውነት በጣም ባለጌ ነህ ፤ ይቅርታ አድርግልኝ ። ትሕትናና ደግነት ማንንም ሲገድል አይቼ አላውቅም። መታገሥ ነበረብህ ። አንተ እኮ ገና ሁለት ዓመትህ ነው ሥራ ከጀመርክ ። ሁለት ዓመት ደግሞ ቢሮክራሲውን ለመጋፋት ቀርቶ ውስጡን ለማወቅ እንኳ አይበቃህም" ። ዛሬ አሳሰረህ ፤ ነገ ደግሞ ከሥራህ ሊያባርርህ ይችላል ። እኔ ይኸንን ዐይንን ጨፍኖ ከግንብ ጋር እንደ መጋጨት ነው የምቆጥረው ። አየህ ከግንብ ጋር ብትጋጭ ደግሞ ኳስ አይደለህም ፤ ነጥረህ አትመለስም ። እዚያው ላይ ትቀራለህ ።"

“አቋሽ ሸለቆ ባለሥልጣን የሚብረቀረቅበት ኮርስ ስትቶሽል መሰል አሉ ፡ ነገርሽ ሁሉ የባሕታዊ ዐይነት ሆነብኝ” አለ ሲሳይ በሽርደዳ ዐይነት አነጋገር ። “የእኔን በዚሁ እንተወውና እስኪ ደግሞ ወደ አንቺ ታሪክ እንግባ” አለና ሲጋራ ጋበዘው ። ሁለቱም አቀጣጥለው ማጨስ ጀመሩ ።

“አሌክስ አንቺስ ደግሞ ማንን ደብድበሽ ይሆን? ወይስ ለተንዳሆ እርሻ ሠራተኛ ልትመለምዪ ነው የመጣሽው ?”

“እኔ እንኳ እንደ አንተ ዘልየ ቀንድ የምነክስ የጅብ ችኩል አይደለሁም”

“የለም በቁም ነገር ነው የምጠይቅሽ ፡ እውነቱን ነው ።

ሳይሽ እኮ በጣም ነው የደነገጥኩት ፡ በምን ጣጣ ወደዚህ መጣሽ አለየ ?”

ዓለማየሁ የእስር ቤቱን ጣራ አንጋጦ ተመለከተ ። ለጥቂት ጊዜ በሐሳብ ኩሬ ውስጥ ሲንቦጫረቅ ቆየና ጉንበስ አለ ። ከሲጋራው አከታትሎ ሳበና ፡ “ኡ ··ሁ” አለ ትልቅ ሸክም እንደ ወረደለት ሰው ።

“የእኔ ችግር እንኳ ትንሽ ኮምፕሊክስ ማለቴ ውስብስብ ነው ። ግን በትዕግሥትና በጥበብ ሊፈታ የሚችል ። ሐረገወይንን ታውቃት የለም እንዴ?” አለ ወደ ሲሳይ ዞር ብሎ ። ሲሳይ ድንግጥ አለና ከመቀመጫው ብድግ አለ ።

“ታዲያ እሷ ምን ሆነች” አለው በተጣደፈ አነጋገር ።

“የለም ፡ እሷስ ምንም አልሆነች ። የእሷ አባት ናቸው ከሰው እዚህ ያሳሰሩኝ ። ከጀመርኩት መቼስ ላውራህ አዳምጠኝ ፡ ጊዜ ማሳለፊያ ይሆነናል ። ሐረገወይን እና እኔ በጓደኝነት አምስት ዓመት አሳልፈናል ። በእርግጥ ቤተሰቦቿ ይህንን አያውቁም ። ከቤተሰቦቿ መካከል የእኛን ጓደኝነት የሚያውቅ ዛማኑኤል የሚባለው የአክስቷ ልጅ ብቻ ነው ።

“ምን ይሆናል መሰለህ ትናንትና ትንሽ ወንድሜ ከአባዲና

ፖሊስ ኮሌጅ ይመረቅ ስለ ነበር እሱና ጓደኞቹ ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ግብዣ አድረገው ጠሩን ። እያንዳንዱ ተመራቂ ሦስት ሦስት ዘመዱን የጠራ ነበር ። እኔ፣ ሐረገወይንና አንድ አክስት አለችኝ ሦስት ሆነን ተያይዘን ሔድን ። በእርግጥ ግብዣው የሚያመች አልመሰለኝም ነበር ። ሐረገወይንን ስጠራት እሷም የጊዜው ጉዳይ አሳስቧት ነበር ። 'የለም በጊዜ ነው የሚያልቀው' ብለው ነግረውኛል ። 'በዐሥራ ሁለት ተጀምሮ በሁለት ሰዓት ያልቃል' ብለውኛል አልኳት ። በዚሁ ተስማምታ መጣች ። እኔም በዚያው ሰዓት ተጀምሮ ያልቃል ። በጊዜ ወደ ቤቷ እሸኛታለሁ የሚል ግምት ነበረኝ ። ግን አልሆነም ። በዐሥራ ሁለት ሰዓት የተባለው በስንት ይጀምርልሃል ፤ በሁለት ሰዓት ልክ በሁለት ሰዓት ፤ ምንም ማድረግ አልቻልንም ። እሷም ወንድሜን ለማስደሰት ብላ ጥላ ለመሔድ አልፈለገችም ። ግብዣ ከተጀመረ ደግሞ ታውቃለህ ጋባዡ ይበዛል፣ ቆዩ የሚለው ይበዛል። ግን መምሸቱን ስናውቅ በአራት ሰዓት ተኩል ላይ ቤቷ ደወለችና የአክስቷን ልጅ አስጠርታ ሁኔታውን አስረዳችው ።

"ሰባት ሰዓት ሆነ ምን እንደማደርግ ጨነቀኝ ። ታክሲ ፈለግን፣ ልናገኝ አልቻልንም ። ቤቷ ደግሞ ላም በረት ነው ። ጨነቀን ምን እንደምናደርግ ። ምርጫ ስናጣ የእኔ ቤት ቅርብ ስለሆነ አራት ሆነን እኔ ቤት ሔድንንና አደርን ።

"በእውነት አዳርም አይደል ስንጨነቅ አደርን ። ቤት ስልክ ደውላ የአክስቷን ልጅ ስታናገረው ፤ አባቷ ሲናደዱ ማምሸታቸውን ፤ በየቦታው ስልክ ሲደውሉ ማምሸታቸውን እኔንም በመጠርጠር ቢፎከሩ መቆየታቸውን ነግሮአታል ። ምንም ማድረግ አልቻልንም ፤ የጭንቀት ሌሊት አነጋን ። የእኔን አልጋ ለእሷና ለአክስቷ ለቅቄ እኔና ወንድሜ ሶፋ ላይ አደርን ። በሌሊት ተነሥታ ወደ ቤቷ ሔደች ። መሥሪያ ቤቷ ገብታ ደወለችልኝ ። ቤቷ ደርሳ መምጣቷን ፤ አባቷ በሌሊት ወጥተው መሔዳቸው እንደ ተነገራት አወራችኝ ። 'በይ ደህና ዋይ' ብዬ ስልኩን ዘጋሁ ።

"ወደ ስድስት ሰዓት ገደማ ያ ያክስቷ ልጅ ደደውልልኝና ፡ 'አባቷ እየተሯሯጡ ነው ። ከወሰንየለህ ጋር ሆነው ሲዞሩ ነው የዋሉት በየባለሥልጣኑ ቤት ፡ ከቢሮህ ውጣና አንድ ቦታ ተደበቅ ቢሮህን ለቀህ ውጣ' አለኝ ። ለጊዜው ትንሽ አስደነገጠኝ ። ግን ለመጥፋት አልፈለግሁም ። 'የመጣው ይምጣ' ብዬ ቢሮዬ ቁጭ አልኩ ። ወደ ዐሥር ሰዓት አካባቢ ፖሊሶች መጥተው 'ትፈለጋለህ' አሉኝ ። ነገሩ ስለገባኝ ምንም ሳልናገር ሰተት ብዬ ወጣሁላቸው ። እዚህ ስደርስ አባትዬው እሳት ሆነው 'ልጄን በጉልበት ደፍሯል ይታሰርልኝ' አሉ ታሰርኩ ።እዚህም መጥቼ ብቸኛ አልሆንኩም ፡ አንተን የመሰለ ጓደኛዬን አገኘሁ ።" የእፎይታ ትንፋሽ ተነፈሰ ።

ሲሳይን ማግኘቱን ቢወደውም ፡ ችላ ብሎት ከነበረው ጭንቀት ውስጥ መልሶ እንዲገባ ስላደረገው በስጨት አለ ። ኪሱን ዳበሰ ሲጋራ ለማውጣት ፡ ግን አልነበረውም ። ከሲሳይ ወሰደና አቀጣጠለ። እያከታተለ ሳበለት ። የሲጋራው ጢስ ቀለበት እየሠራ ጥቂት ይንዝና ብትንትን ይላል ። እያከታተለ ሳበለት ። ጢሱ ያችን ክፍል ሞላት ። 'ጭንቀት እንደዚህ ጢስ በኖ በአፍታ የሚጠፋ ቢሆን እንዴት ጥሩ ነበር' አለ በልቡ ። የራሱ ሲጋራ ጢስ አፈነውና ዐይኖቹን ማሻሸት ያዘ ።

የእስረኞች አለቃ መንጌው ጋር የሞቀ ጭውውት ይዟል ። ጆፌና ወፈፌው ይጨቃጨቃሉ ። አንዳንዶቹ እንደ ማሽላ ብሉአቸዋል ። የአንዱን እስረኛ እግር ተንተርሰው የተኛው ታጣቂ የሰፈር ሌባ የተሰጣ ብርድ ልብስ ሰርቆ ሊያመልጥ ሲል ፡ ሰፈርተኛው ደርሶ ክፉኛ ስለ ደበደበው ቁስሉ እያደር እየተሰማው ተንጋሎ ያቃስታል ፡ የሚያዝንለት ሰው ግን የለም ፡ ዝም ብሎ ያቃስታል ። ወፈፌው ጆፌ ጋር ሲጨቃጨቅ ቆየና ብድግ አለ ። መለፍለፍ ጀመረ ።

"እስኪ ወንድ ንክች አድርገኝ ፡ ምቀኛ … ምቀኛ ሁሉ … ሲጋራ ስጡኝ እምቢ ፡ ልጠጣባት እምቢ ፡ ልሰብህ እምቢ … በጥፊ ብቻ መማታት ‥ የየት አገር ጎኸ ነህ እባክህ? እስረኛ መሆንህን

አረሳኸው እንዴ? ወይስ ይኸ ቤት ተስማምቶሃል፡ እኔን ይብድበህ እዚሁ ታስሮ መከረም ትፈልጋለህ?… ምቀኛ … ያ ፖሊስ ለምን ሳምክ ብሎ በምቀኝነት አሳሰረኝ ‥ እስኪ ምን አገባው? ፡ የእሱን ሚስት አልሳምኩበት” ክትክት ብሎ ሣቀ ። ቀጠለ ደሞ “እውነትም ምቀኛ ፡ ብቻ የተማረ ሰው አይጥፋ! አይደለም … እንዴ ወንድም? ‥ … አንተ …. አንተ ቅድም ሲጋራ የሰጠኸኝ… ልክ አይደለሁም ‥ የተማረ ሰው አይጥፋ …” ወደ እነ ዓለማየሁ ሔደና ከፊት ለፊታቸው ቆመ ። ጉንበስ ብሎ ተመለከታቸው … “ብቻ የተማረ ሰው አይጥፋ ‥ አንድ ሲጃራ… ወይ ቁር ካለ ስጡኝ እስኪ …’ ሲሳይ ማት አለና ሲጃራ አውጥቶ ሰጠው ።

ወፈፌው እየፈነደቀ ተቀበለ ፡ ሲጃራውን አቀጣጠለና “ብቻ የተማረ ሰው አይጥፋ” እያለ ወደ ቦታው ተመለሰ ። ተንጋሎ የሚያቃስተው ሰው አንገቱን ቀና አደረገና ፡ “ወፈፌው በእራዳ ጊዮርጊስ ይገዛሃለሁ… እባክህ… እባክህ አትበጥብጠኝ ልተኛበት እባክህ ተለመንኝ‥ ዐርፌ ልተኛበት …” ለመነው ።

“ባላርፍ ምን ታደርገኛለህ?”

“እይ … ምን አደርግሃለሁ … እባክህ እባክህ !”

“እኔ የማሰጣውም ብርድ ልብስ የለኝ… ይህን የለበስኩትን ድሪቶ እቀማሃለሁ ብትለኝም ደሞ በጄ አልልህ … ምቀኛ ዝም ብለህ አቃስት” ከሲጃራው አከታትሎ ማገለትና ያቺን የጨለመች ክፍል በጢስ ሞላት ።

“የምልሽ አሉ” አለ ሲሳይ ወፈፌውን ሲከታተል ቆየና ፡ “የሚገርመኝ ነገር እኮ ነው የነገርሽኝ ። ማይሯን መቃወማቸው እኬ። ማን እንቺን ሲያሳስሩ የእሷንም ስሜት እንካለሁ ፡ እስቀይማታለሁ ብለው አያስቡም እንዴ? ደግሞስ መጀመሪያ መጠየቅ የነበረ ባት እሷ አይደለችም እንዴ? እሷ ብትቃወምሽ መክሰስ ያባት ነው ። ደሞስ ቅድም ስታወሪልኝ የእንቺንና የእሷን ጓደኝነት የሚያውቀው የአክስቷ ልጅ ብቻ ነው ። ቤተሰቦቿ አያውቁም ብለሽኝ ነበር ። እንቺንና የምትሠሪበት መሥሪያ ቤትሽን በምን ዐወቁና አባቷ

ሊያስይዙሽ ቻሉ?"

"ለዚህ ኮ ነው ቅድም ውስብስብ ነው ያልኩህ ።"

"ቢሆንም ንገረኝኮ ኢንተረስቲንግ ታሪክ ነው ። አየሽ ለእኛም ለጀማሪዎች ትምህርት የሚቀሰምበት ይሆናል" ሲሳይ ተደላድሎ ተቀመጠ ።

"ተወኝ እባክህ ከችግር ውስጥ መውጣት እንጂ ችግር ውስጥ መግባት ቀላል ነው ። እና እኔን የሚያሳስበኝ ያለፈው ሳይሆን ወደ ፊት እንዴት? የሚለው ነው ። ቃላት ቢጠራቀሙ ባስኬት አይሞሉም ነው የሚባለው ፡ ለዛሬው በዚህ ይብቃህ …" ትክዝ ብሎ ሲጋራውን መሳብ ጀመረ ።

"እሴ ይኸውልሽ በገዛ ሎጂክሽ ተረታሽ ፡ ብዙም ሳትፈናፈኝ ተረታሽ ።"

"በምንድነው የተረታሁት" ዓለማየሁ ግርም አለው ።

"ቅድም እኔን ምን ስትይ ነበር ፡ መናደድህን ትተህ ታሪኩን አውጋኝ ስትይኝ አልነበር ። 'ብስጭትና ጥቃት እየተከታተለ ያቆስልሻል' ስልሽ 'ለሁሉም ቦታ ቦታ አለው' ብለሽ ስታራክሽ አልነበረም ። ይኸው በእንቺም ደረሰ ። የደረሰብሽ ጥቃት ትዝታው ሲነግብሽ ምን ታደርጊዋለሽ … ብቻ ተረትሻል ።"

"መረታት አይደለም ፡ ደሞ እኔኮ አልተናደድኩም ። ጥሩ ጥሩ ወግ እያመጣን እንድንደሰት ብዬ እንጂ መናደድ አይደለም ። ስማ ደሞ በዚህ ክፍል ሕግ መሠረት ቅድም እንደ ተነገረህ የታሰርነበትን ጉዳይ ባጭሩ እንጂ ዓመት ስትተርክ አትቆይም እኮ" ብሎት ፈገግ አለ ።

"የለም እሱን ተወት አድርጊውና ቁምነገሩን አውጊኝ ። በጣም ነው ኢንተረስት ያደረብኝ… ሲረየስሊ…"

"የለም ምን መሰለህ ሲሳይ ስጀምርልህ ውስብስብ ነው ያልኩህ እኔም ሙሉ በሙሉ የነገሩን ምስጢር ስላልደረስኩበት ነው። ለእኔም ያስቸግረኛል ። ነገሩን ቀስ በቀስ ስከታተለው

ቆይቻለሁ ። ስለዚህም ዐውቀዋለሁ ማለት ይቻላል ። ግን የማውቀው ምስጢሩን ሙሉውን ይሁን በከፊል እርግጠኛ አይደለሁም ። ያም ሆነ ይህ ጉዳዩ ምን መሰለህ… በእርግጥ ከየት እንደምጀምርም ይቸግረኛል … እጅግ የተቆራረጠ ታሪክ በመሆኑ መቀጣጠሉ ያስቸግረኛል ። ትናንት እሷ እኔ ቤት ማደሯ ሰበብ ሆነ እንጂ አንድ ነገር ሲደገስልን እንደኖረ ዐውቃለሁ ። … ይኸውልህ እኔ ከዩኒቨርስቲ ስመረቅ እሷም የ12ኛ ክፍል ትምህርቷን አጠናቀቀች። ሁለታችንም እኩል ሥራ ያዝን ። አባቴ አንድ የሚያውቁት አዲስ አበባን የሚያምስ በእውነት ባሕሪውን ለመግለጽ የሚያስቸግረኝ ሰው አለ ። ባሕሪውንም ብቻ ሳይሆን ሥራውን ይኸ ነው ብሎ ለመግለጽ ያስቸግረኛል ። ባለሥልጣን የተባለን ሁሉ ያውቃል ፡ ትልልቆቹን ነጋዴ ፡ አስመጪና ላኪውን ፡ ባለኩባንያውን ሁሉ ያውቃል ። ሴቱን ሁሉ ያውቃል ። ይደልላል ፡ ጉዳይ ይፈጽማል ፡ ሥራ ያስይዛል ፡ ያጋባል፡ ያፋታል ፡ እጅግ የሚገርምህ እስስት ሰው ነው ። የሐረ አባት ይኸን ሰው ያውቁታል ፡ ማወቅ ብቻ ሳይሆን ያመልኩታል ፡ ያላቸውን ሁሉ ይቀበላሉ ፡ እንደ ፈለገ ነው የሚያሽከረክራቸው ። ሐረ የ12ኛ ክፍል ትምህርቷን እንደ ጨረሰች በማትሪክ ዩኒቨርስቲ ያስገባ የሚችል ነጥብ ስላላመጣች አባቷ ‘ሥራ ፈልጊ ላስገባሽ’ አሏት ። ለእኔ አማከረችኝ ‘በጣም ጥሩ ነው ፡ ሥራ ከተገኘልሽ መሥራትሽን እደግፈዋለሁ ፡ ማታ ማታ እየተማርሽም ውጤትሽን ለማሻሻል መጣር አለብሽ’ አልኳት ፡ በዚሁ ተስማማን ። ከዚያ አባትዬው ይኸን ወስንየለህ የሚባለውን አቀጣሪ ለልጄ ሥራ ፈልግልኝ ይሉታል ። ‘ምን ችግር አለ ወርቅ ሥራ ነው የማስይዛት በእኔ ይተዉት’ ይላቸዋል ። ይወስድና ሰፈሪያን ኩባንያ ያስቀጥራታል ። ይኸን ሁላችንም የደገፍነው ጥሩ ሥራ ነው ። እሷን ሥራ ያስገባልህና አንድ አስመጭና ላኪ ጓደኛ አለው ፡ ሚልኪያስ የሚባል ለእሱ ወስዶ ያስተዋውቃታል ። አቶ ሚልኪያስ በገንዘብ ልቡ ያበጠ ነው ፡ አላስወጣ አላስገባ ብሎ ያስቸግራታል ።

"ያ አቃጣሪ ጥሩ ሚስት አገኘሁልህ እያለ ከሚልኪያስ የደላላነቱን ገንዘብ ይቀበላል ማለት ነው ። በዚህ ብቻ አላበቃም ወሰንየለህ ለአባትየው ይሄድና 'እህትህን ዳርልኝ እያለ አንድ ሰው አስቸግሮኛል ፡ ምን ይመስሎታል' ብሎ ይሰብካቸዋል። እፁ ስትጠየቅ አሻፈረኝ ትላለች ። ይኸን ነገር ለእኔ ሳትነግረኝ ይብቃኝ ትቆይና ፡ አባቷም ሆነ እነዚያ ሰዎች ሲያስቸግሯት ለእኔ ትነግረኛለች ። ከባድ ጉዳይ መስሎ ስላልታየኝ ብዙም አላስጨነቀኝ ፡ 'ተይ እባክሽ ምን አባቱ ይሆናል" ስል እከረማለሁ ። የእነሱ ሐሳብ ምን ነበር ልጅቷን በገንዘብና በጌጣጌጥ አታለው እሺ ካስባሉ በኋላ ወደ ቤተሰቧ ሽማግሌ ለመላክ ነበር ። እፁ ግን ድርቅ አለችባቸው ። በልዩ ልዩ መልክ ተፈታተኗት 'እምቢ' አለቻቸው ።

ተስፋ ሲቆርጡ ሽማግሌ ይልካሉ ። እናት እፁ ትጠየቅ ሲሉ አባት ከኛ ፈቃድ የት ልትደርስ ይሉና እሺ ይላሉ ። አቶ ወሰንየለህ ሚልኪያስ የላከው ነው እያለ ለአባቷ ልዩ ልዩ ስጦታ ይወስድላቸዋል ። አንዴ ሰማሁት አሁን በቅርቡ እንኳን ለቅዱስ ዮሐንስ ብሎ አንድ ካፖርት ስጦታ ልኮላቸዋል አሉ ። እየሀ ሰውየው የተሰፋ ልዩ ልዩ ልብሶች ከውጭ እያስመጣ ሀገር ውስጥ የሚያከፋፍል ኩባንያ ባለቤት ነው ። ይገርምሃል እኮ! ደሞ ሰውየውን አይቸዋለሁ አባቷ እኮ ይሆናል ። ብቻ ነገሩን አንዛዛሁብህ መሰለኝ" ዞር አለ ወደ ሲሳይ ።

"የለም የለም አልበዛም ፡ እኔ እንደውም ሥጋቴ እንዳታሳጥርብኝ ነው" አለው ።

"እሽ… ካልሰለቸህ ምን ቸገረኝ ፡ እና ሚልኪያስና ወሰንየለህ ልጅቷ እማትበገር ስትሆንባቸው ጊዜ መውጫ መግቢያ ያሳጧታል፡ እፁን ብቻም ሳይሆን እኔንም በምስጢር ይከታተሉኛል ። ከሥራ ወጥታ ወደ ትምህርት ቤት ፡ ከትምህርት ቤት ወጥታ ወደ ሥራ ስትሄድ ይከታተሏታል ። ያንን መናጢ ሒሳብ ሁለት ጊዜ ስለወደቀች ማትሪክ ለሦስተኛ ጊዜ ለመውሰድ ካቴድራል ነበር የምትማረው ። እኔና እፁ ደሞ በየቀኑ እንገናኛለን ፡ ከትምህርት ቤት

ስትወጣ ጠብቂ አውቶቡስ አሳፍሬአት ነው የምመለሰው ። በዊክ ኤንድ እንገናኛለን፣ ምሳም አብረን እንበላለን ። ይህንን ሁሉ ሲከታተሉን ቆይተዋል ። ይኸ ወሰንየለህ የሚባለውን ሰውዬ እንደ ሁለት ጊዜ ከእኛም ሥራ አስኪያጅ ጋር ምሳ ሲበላ አይቸዋለሁ ። ... አሁን እንደሚመስለኝ እስከ አሁን ያልሞከሩትን ጉልበት ለመሞከር ወስነዋል ። የባሬውም መታሰሬ ከዚሁ ጋር የተያያዘ ሳይሆን አይቀርም ። ይኸው ነው ሲሱ የእኔ ኮምፕሌክስ ታሪክ" አለና አንገቱን ደፋ ።

“አሌክስ በእውነት አሳዘንሽኝ ። ቅድም እኔን ከግንብ ጋር በጭፍን እየተጋጨሁ ነው አልሺኝ እንጂ ከብረት አጥር ጋር ግብግብ የገጠምሽስ አንቺ ነሽ ። አሳዘንሺኝ ። የእኔማ ምን አላት ብለሽ! ቢጠና ከሥራ እባረራለሁ ፣ ሌላ ሥራ ፈልጌ እገባለሁ ። በእውነት አሳዘንሽኝ ። ቆንጆ ልጅ ወደሽ ችግር ውስጥ በመግባትሽ አሳዘንሺኝ፣ የሐረገወይን አባትም ቆንጆ ልጅ ወልደው ችግር ውስጥ ስለገቡ አሳዘኑኝ ፣ እሷም ቆንጆ ሁና ተፈጥራ ችግር ውስጥ ስለገባች አሳዘነችኝ ። በእውነት ሁላችሁም ታሳዝናለችሁ ። እኔ እምልሽ አሁን አንቺ ምንድን ነው ሐሳብሽ ወጥመድ ውስጥ እኮ አልፈዲ አስገብተውሻል ማለት ነው ። በዚህ ዐይነት ።”

“የለም ወጥመድ ውስጥ አልገባሁም ፣ አትሳሳት ፣ መቸስ ምን ቢሆን ፍቅርን በገንዘብ መግዛት አይቻልም ። ሐረገወይን እንደማትከዳኝም ሀውቃለሁ ። ስማ እኔን እንዳሳሰሩ እሷንም እኮ አስረው የፈለጋቸውን ሊያደርጓት ይችላሉ ፣ ግን የበለጠ ትጠላቸዋለች እንጂ አታፈቅራቸውም ። እኔ ወጥመድ ውስጥ ገባሁ እል የነበረው የእሷም ልብ ከሌላ ጋር ሆኖ እኔ ብወዳት ነበር ። ወጥመድ ውስጥ የገቡት የእኔ ጠላቶች እንጂ እኔ አይደለሁም ። እውነቱን ልንገርህ እኔ ነፍጠኛ አይደለሁም ፣ እልከኛም አይደለሁም ። ጅል አይደለሁም ። እሷ እኔን የምትወድ መሆኑን እርግጠኛ ባልሆን ኖሮ እስከዚህም አልደርስ ነበር ። የምትወደኝ ፣ የማትከዳኝ መሆኑን ስለማውቅ ግን የፈለገው ቢመጣ ወደ ኋላ አላፈገፍግም ። የብረት

አጥሩ የእሷ እና እኔ ፍቅር ነው ። ፍቅራችን እስካለ ድረስ ይህ የብረት አጥር አይደፈርም ፣ ፍቅራችን ከፈረሰ አጥሩም ተደረመሰ ማለት ነው ። ገባህ? የሁለታችን ፍቅር እስካለ ድረስ ጣልቃ ሊገቡ የሚነሡ ሁሉ ከብረቱ አጥር ጋር እየተጋጩ ይወድቃሉ እንጂ አያሳካላቸውም ። ይህንን ስናገር ከልቤ ነው ። ባጭሩ እኔ እዚህ ብታሰር ፣ ወህኒም ብወርድ የእሷ ፍቅር ከልቤ አይጠፋም ፣ እሷም ምንም ይድረስባት ምን እኔ ከልቧ አልጠፋም ፣ ይህንን ማንም ሊፍቀው አይችልም ።

“ይህንን ነው የብረት አጥር የምለው ። በተረፈ ግን ችግሩ ቀላል እንዳልሆነ ይሰማኛል ፣ በብልሃትና በጥበብ ከያዝነውም ምንም እንደማንሆን ዐውቃለሁ ። አየህ ቀን ለምን እንደ ጨለመ ካላወቅህ በጨለማ ውስጥ መጓዝ አትችልም ። ማለቴ የችግሩን መንስዔ ምክንያቱን በሚገባና በዝርዝር ማወቅ ይኖርብሃል ። ለችግሩ መፍትሔ ለመሻት በቅድሚያ ፕሮብሌሙን አፕሪሺየት ማድረግ ይኖርብሃል” አለ ዓለማየሁ ከልብ በመነጨ የእርግጠኝነት ስሜት ፣ በልቡ የበቀል ስሜት እየተቀጣጠለ ።

“እሱክስ አንድ የማይንቅልሽ ነገር አለ ፣ ችግርን በትዕግሥትና በጥበብ መከታተል የምትይውን ነገር ። ግን ይኸም ቢሆን እኮ ችግር ውስጥ መልሶ እንደሚከት ማወቅ ይኖርብሻል ። ከኅብረተሰቡ ጋር በምትቀላቀይበትና የማኅበራዊ ሕይወት ተጋሪ በምትሆኚበት ወቅት እርግብ መሆን ብዙም አያዛልቅም ። ሁልጊዜም ቆቅ መሆን አለብሽ ። እንደ አራስ ነብር ሰውነትሽን ሁሉ አስቆጥተሽ መብትሽን ለማስከበር ራዲ መሆን አለብሽ ። ነገሮችን ፣ ችግሮችን ማጥናትና የሚፈቱበትን ሁኔታ መተንተን ትምህርት ቤት ውስጥ የምንገለገልበትን ያህል በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ የሚያወላዳን መስሎ አይታየኝም ። ‘ለምን?’ በይኝ ። አየሽ ይህች ዓለማችን የብዙ ምስቅልቅል ሁኔታዎች ጐተራ እንደ መሆኗ ሰዎች ሁሉ የመልካቸውን ያህል ባይሆንም ጠባያቸው የተለያየ ነው ። ግን አንድ የሚያደርጋቸው ራሱ ማኅበራዊ ሕይወት የፈጠረው ያለመተማ

መን፡ የእሽክርና የጌታ ፡ የማጣትና የማግኘት ፡ የመብለጥና የመበለጥ፡ የማጥቃትና የመጠቃት ፡ ሥነልቡና የፈጠረው 'ሳልቀደም ልቅደም' የሚሉት ጣጣ አለ ። እየሽ ጠላትሽ ሊያጠቃሽ ሲሯሯጥ አንቺ ትዕግሥት ፡ ስልት የምትይ ከሆነ ፋታ ትሰጭዋለሽ ፡ እጅሽን ሳትሰንዝሪ ትወድቂያለሽ ፡ ጠላትሽ በአንቺ ላይ ይነግሳል ። ይህ ደግሞ የሞት ሞት ነው ። ስለዚህ ቶሎ እርምጃ መውሰድ አለብሽ፡ እንደእኔ ሐሳብ ከሆነ ማድረግ ያለብሽ ይኸን ነው ።"

"እስኪ በአንተ ሐሳብ እኔ ምን ማድረግ አለብኝ ትላለህ?"

"ጥሩ ጥያቄ ነው ፡ ማድረግ ያለብሽ አንድ ቀላል ነገር ነው ። ምን መሰለሽ ዛሬ ያሳሰሩሽ ሰዎች ነገ ትወደኛለች ፡ እወዳታለሁ በመኻላችን የብረት አጥር አለ የምትያትን ልጅ አፍነው ከወሰዱብሽ ነገሩ ሁሉ ያከትማል ። እስብተሽ እስብተሽ ለአራጅ መስጠት ይሆንብሻል ። ያን ጊዜ ከፉኛ ትቃጠያለሽ ፡ የምትይው እውነተኛ ፍቅር በመካከላችሁ ኖሮ ልጅቱ ከጠላቶችሽ አምልጣ ወደ አንቺ ብትመጣም ነገሩ አይጥምሽም ፡ ውራጅ ሳልባጅ እንደመልበስ ይቆጠራል ። ቂምሽ ደግሞ ያን ጊዜ የከፋ ይሆናል ። ጠላቶቹን አጥፍቼ ልጥፋ ወደ ሚል የጥፋት ውሳኔ ታዘነብያለሽ ። ለዚህ እኔ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነኝ ። ትዕግሥት እንደምታጠብቂ ዐውቃለሁ ፡ ዛሬ ብቻ ሳይሆን ትምህርት ቤትም ሆነን ዐውቅሻለሁ ። ግን ይኽ አያዛልቅሽም ። ስሚ ምንም ቢሆን እኮ በአድዋና በማይጨው ፡ የተፋለሙት ሰዎች ደም አለብሽ…"

"የምትናገረው አልገባኝም ። ትዕግሥት ይቅርብህ ነው የምትለኝ ትዕግሥቱስ አልቆ ምንድን ነው የምሆነው?" አቋረጠው ዓለማየሁ ።

"እስጨርሽኝ አሌ ፡ ወደ ነጥቡ ልመጣ ነው ። መቸስ እዚህ ፖሊስ ጣቢያ ታስረሽ አትኖሪም ትፈቻለሽ ፡ እስከ ምትፈቺ ድረስ ጠላቶችሽ ጽጌረዳሽን ካልቆረጡብሽም ዕድለኛ ነሽ ። ምን ታደርጊያለሽ ከዚህ ቤት እንደ ወጣሽ ሐረገወይንን ጠልፈሽ ወደ ቤትሽ…"

"አላደርገውም ፡ አላደርገውም ሲሳይ" ተቆጣ ፡ ዓለማየሁ

"ፈጽሞ አላደርገውም ፤ ስማ ስርቀህ የምትወስደው ነገር እኮ የራስህ ያልሆነውን ነው ። እንዴት የራሴን ንብረት እሰርቃለሁ ። ጠለፋ እኮ ስርቆት ነው ። እና እንዴት ሐረገወይንን እሰርቃለሁ …"

"እሴ አሁንስ ሞኝ ሆንሽብኝ በጣም ፤ ስሚ 'እየፈጩ ጥሬ ለምን ትሆኝብኛለሽ ። ሐረገወይን የእንቺ ንብረት ብትሆንማ ለመታሰርም ባልበቃሽ ነበር ። እርግጥ ነው ጠለፋ ስርቆት ነው ሊባል ይችላል ። ትክክል ነሽ ። የሚሰረቀውም የራስ ንብረት አይደለም ። በዚህ እስማማለሁ ። እየሽ ሐረገወይን ከእንቺ ጋር ነች። አባቷ ግን ከእንቺ ጋር አይደሉም ። እንቺ ሐረገወይን የእኔ ናት ስትይ ፤ አባቷ ደግሞ የለም የእኔ ናት ይሉሻል ። እየሽ ኮንፍሊክቱ እዚህ ላይ ነው ። ስለዚህም የምትሰርቂው ነገር የራስሽን ሳይሆን የገርል ፍሬንድሽ አባት ንብረት መሆኑ ነው ። በዚህ ስርቆት ፤ የምትሳሳልሽ ሐረገወይን የማትቀየምና የማትቃወም ከሆነ 'ንብረቴ ናት' ለሚሏት አባቷ ማዘን የለብሽም …"

"የለም… የለም… አዝናለሁ እንጂ ለምን አላዝንም ፤ እየህ አባቷ ለጊዜው እኔን ቢቃወሙም ዞሮ ዞሮ የእሷ አባት ናቸው ። ዛሬ ምናልባትም በገንዘብ ተታለው ይሆናል ፤ ዛሬ ምናልባት በዘር በደም በእጥኟት አምነው ከሰውም ሰው ይመርጡ ይሆናል ፤ በመምረጣቸውም ልጃቸውን ማስከፋታቸውን ልብ ላይሉት ይችሉ ይሆናል ። ግን አባቷ ናቸው ። ምንም ቢሆን ሰው ናቸውና በትናንቱ ስሕተታቸው ዛሬ ፤ በዛሬው ስሕተታቸው ነገ ይጸጸታሉ የሚል እምነት አለኝ ። ስለዚህም እሷን ጠልፌ ከአባቷ ጋር ላቆራርጥ አልፈልግም ። ደግሞም እኮ የሰዎች ግፊት እዚህ አደረሰን እንጂ እሷ እና እኔ ዛሬ ወይም ነገ የመጋባት ዓላማ የለንም ። ትምህርቷን ለመቀጠል ትፈልጋለች ። እኔም እፈልጋለሁ ። እናም የመጀመሪያው ምርጫችን አዕምሮዋ ሳይረበሽ ትምህርቷን እንድትከታተል ፤ ይህ ካልሆነ ለማግባት የማትፈልገውን ሰው እንድታገባ እንዳትገደድ ነው ።

"በእውነቱ ልንገርህ አባቷ ዛሬ ስላሳሰሩኝ እኔ ቂም አልይዝባ

ቸውም ። ሁለታችን የሁለት ዘመን ትውልዶች ነን ። እርሳቸውም አንድ ሐቅ አላቸው ፤ ልጃቸውን ለፈለገኝ እዳራለሁ የሚል ሐቅ ። እኔ ደግሞ ሌላ ሐቅ አለኝ ። ሐረገወይንም የእኔን መሰል ሐቅ አላት ። ግጭቱ በእርሳቸውና በእኛ መካከል ይከሰት እንጂ ነገሩ እኮ የሁለት ዘመናት ግጭት ነው ፤ የአሮጌና የአዲስ ዘመን ግጭት ። እና አንተም እንደምታምንበት አሮጌው እየሞተ አዲሱ እያበበ ነው የሚሄደው። እኛ እንደምናሸንፍ ይገባኛል ፤ ግን 'የሚሞት ሽማግሌ' እያርገምህ እንደሚባለው ፤ በጥበብ ፤ በትዕግሥት እንጂ በእልህ ልናደርገው አናስብም ። ዞሮ ዞሮ አባቴ ናቸው ብየሃለሁ ። እኔ በምፈጽመው ጥፋት ከአባቴ ጋር ላቀያይማቸውና አባት አልባ ላደርጋት አልፈለግም ። አንተ የምትለው ነገር እጅግ በጣም ቀላል ጉዳይ ነው ። ምናልባትም እኔ እሷን ብጠልፍ ፤በዓለም ውስጥ ቀላሉ ጠለፋ ሊሆን ይችል ይሆናል ። ለምንድነው እንዲህ የምልህ በቀላሉ ቤቱ ወይንም ቢሮየ ቁጭ ብየ 'ሐሬ እንግዲህ አባትሽ እምቢ ስላሉ ምርጫ የለንምና ከዛሬ ጀምሮ ጠልፌሻለሁ በዚህ ሰዓት ቤቴ እንድትመጪ' ብላት እንደምትመጣ ስለማውቅ ነው ። ግን በዚህ መንገድ ትዳራችን ትዳር እንደማይሆን ፤ ሁለታችንም እናውቃለን ። በሌላ በኩል ደግሞ ይኸ የምትለው ጠለፋ ሰው ሁሉ እንደ ጀግንነት ያወራዋል እንጂ ለእኔ የደካሞች ሥራ ነው ። እና አላደርገውም ሲሳይ ።"

"እኔ መቸስ ···የወንድምነት ምክሬን ነው የለገሥኩሽ ፤ መቀበል ወይም አለመቀበል የራስሽ ፋንታ ነው ። እንደኔ ቢሆን ግን እውነቱን ልንገርሽ ፤ ሁለቱንም ደፍቻቸው የመጣው ይመጣል እንጂ እንዲህ ስጠቃ ዝም ብዬ አልመለከትም ።"

"ይኸማ ሞኝነት ነው ሲሳይ ። ሁለቱንም ደፍተሃቸው ምን ለመሆን ትፈልጋለህ? የምትወዳትን ልጅ እኮ ከዚያ በኋላ ልታገኛት ወይንም ልታገባት አትችልም ፤ ይኸ በእውነቱ ዐዋቂ ሰው የሚሠራው ቀርቶ የሚያስበውም መስሎ አይታየኝም ።"

ሲሳይ የመናደድ ምልክት አሳየ ። ውይይቱ ቢጥመውም

ከዓለማየሁ ጋር እንደማይግባቡ ስላወቀ ነገሩን ወደሌላ አቅጣጫ ለማዞር ፈለገ ። ከኪሱ ሲጋራ አወጣና ለዓለማየሁ ጋበዘው ፤ አቀጣጠለለትና ሁለቱም ማጨስ ጀመሩ ።

ወዲያውኑ የእስር ቤቱ በር ተከፈተና ፤ "ዓለማየሁ ድንበሩ ፤ ዓለማየሁ ድንበሩ" የሚል ድምፅ ተሰማ ። ዓለማየሁ ሲጋራውን መሬት ላይ ጥሎ ደፈጠጠና "አቤት" ብሎ ተነሣ ። "ሰዎች ይፈልጉሃል ውጣ" አለ ከውጭ በሩን ከፍቶ የቆመው ፖሊስ ።

ዓለማየሁ ወደ ውጭ ወጣና ወደ ዋናው በር አሸጋግሮ ተመለከተ። ሐረገወይን ፤ ወንድሙ ምክትል መቶ አለቃ ስንታየሁ ፤ የዓለማየሁ አክስት ወይዘሮ አስካለና የሐረገወይን አክስት ልጅ ዛማኑኤል በተርታ ቆመው ተመለከታቸው ። ሐረገወይንና ዛማኑኤል ዕቃ ይዘዋል ።

ሐረገወይን ፡ ዓለማየሁ ወደ እስር ቤት እንዲገባ ሲታዘዝ እንባዋን እያፈሰሰችና እየሮጠች በታክሲ ተሳፍራ ወደ ዓለማየሁ ቤት ሔደች ። ቤት ውስጥ የዓለማየሁ ወንድም ምክትል መቶ አለቃ ስንታየሁንና የዓለማየሁን የቤት ሠራተኛ አገኘቻቸው ። የዓለማየሁን መታሰር ለመናገር ፈራች ። መርዶ እንደሚያረዳ ሰው ዐይነት ከበዳት ። ወደ ማድቤት ገባችና የዓለማየሁን ሠራተኛ ጠራቻት፤ አልነገረቻትም ። "እስኪ ለእራት የሚሆን ምግብ ቶሎ አዘጋጂ" ብላ አዘዘቻትና ተመልሳ ወደ ሳሎን ሔደች ። መቶ አለቃ ስንታየሁ መጽሐፍ ያነባል ።

"ታዲያስ ሐሪ ምነው ሥራ የለም እንዴ ዛሬ?" አላት ።

"አይ … አለ አንድ ችግር ገጥሞኝ ነው የመጣሁት ።"

"ምነው? ምን ሆንሽ" አለና መጽሐፉን ወርውሮ ተነሣ ። ሐረገወይን የባሰ ደነገጠች ፤ ጭንቀት ያንገላታት ጀመር ። ስትፈራ ስትጨነቅ ቆየችና ወደ መሬት አቀርቅራ

"የለም ዓለማየሁ ታስሮ ነው" አለች ።

በቤቱ ለጥቂት ጊዜ ጸጥታ ሰፈነ ። ሐረገወይን ስንታየሁ ምን

ይናገር ይሆን ብላ በጉጉት በመጠበቅ አፍ አፉን ትመለከተዋለች ። "ለምን ታሰረ" ቢላት የምትሰጠው ምክንያት ጠፍቷት ተጨነቀች። ሁለቱም ተፋጠው ለጥቂት ጊዜ ቆዩና ።

"የት ነው የታሰረው" አላት ለስለስ ባለ ድምፅ ።
"ሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ ነው"
"ምነው በጠብ ነው ወይስ በሌላ ?"
"አይ ቀላል ነው ፡ ቀላል ጉዳይ ነው"
"ንገሪኝ ምንድን ነው ?"
"በእኔ ምክንያት መሰለኝ"

ስንታየሁ ቆዝሞ ለጥቂት ጊዜ ቆየና ፡ "እሺ እንሒዳለን" አለ። ልብሱን ሊቀይር ወደ መኝታ ክፍሉ ገባ ። ትናንት የነበረው ደስታ ውሎ ሳያድር ወደ ሐዘን ተለወጠበት ። ለአፍታ እያሉ ክፉና ደግ ሐሳቦች ተፈራረቁበት ።

ልብሱን ቀይሮ እንደወጣ ከባድ የራስ ምታት አጣደፈው ። "ስንታየሁ እንዲህ ብናደርግ አይሻልም" አለች ሐረገወይን ። "ምን እናድርግ ሐረ"

"እራት እየተሠራለት ነው ፡እሱ እስከሚደርስ ድረስ አንተ ለአክስትህ ሔደህ ብትነግራቸው እኔ ደግሞ ትንሽ ፍራሽ እዚህ ስለሌለ መርካቶ ሔጄ ገዝቼ ልምጣ ።"

"ጥሩ… ጥሩ ሐሳብ ነው ። አክስቴ ቤት ስልክ ስለሌለ ሔጄ ልነግራት እችላለሁ ፡ … ብቻ ባንነግራትም ምንም አይደል ።"

"የለም የለም በኋላ ከሚቆጨን ብንነግራቸው ምንም አይደለም!"

"ለመሆኑ እንቺ ማን ነገረሽ ቢሮሽ አልነበርሽም እንዴ?"

"አዎ ቢሮ ነበርኩ ። ወንድሜ ዛማኑኤል ደወለልኝና 'ሊያሳስሩት ሰዎች እየፈለጉት ነው ፡ ለዓለማየሁም ደውየለታለሁ ፡ ከቢሮው ወጥቶ ሌላ ቦታ እንዲደብቅ' አለኝ ። ወዲያውኑ ለዓለማየሁ ደወልኩለትና አነጋገርኩት ። 'ለምን ታዲያ አትወጣና ሌላ ቦታ

አትደበቅም' ብለው 'ማዴለሽም አትሆኚ ምንም አይደርስብንም' አለኝና ስልኩን ዘጋ ። ከሰዓት በኋላ መልሼ ስደውል አንድ ሰው 'ሁለት ፖሊሶች አሁን መጥተው ይዘውት ሔዱ' አለኝ ወዲያውኑ ታክሲ ኮንትራት ይዤ ሁለተኛ ጣቢያ ስሔድ ወደ እስር ቤት ሲወስዱት አገኘሁት" አለችና ማልቀስ ጀመረች ። ስንታየሁ ተቆጣት ፣ ማልቀሷን አስተዋት ።

ለዛማኑኤል ስልክ ደውላ ወደ መርካቶ ሔዳ በንፋስ የሚሞላ ተጣጣፊ ፍራሽ ገዝታ ተመለሰች ። ከየቦታው ተሰባስበው አራት ሆነው ወደ ሁለተኛ ጣቢያ ሔዱ ።

ዓለማየሁ አራቱንም ከሩቅ ሲመለከታቸው የደስታም የሐዘንም ስሜት ተፈራረቁበት ፣ ታስሮ ጠያቂ የለሽ ምስኪን ባለመሆኑ ደስ አለው ። እሱ በመታሰሩ ሌሎቹ እሱን ሲጠይቁ መምጣታቸውና መድከማቸው ደግሞ አሳሰበው ፣ ከፋው ። እርግጥ ዘመድ ለዚህ ለዚህማ ካልሆነ ለመቼ ይሆናል ? የቸገረን ለአጉል ነገር እየዋለ ፣ 'ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ' አለ በልቡ ።

“እሺ ጠጋ ብላችሁ ልታነጋግሩት ትችላላችሁ” አለ ፖሊሱ ወደ አራቱ ሰዎች ጣቱን እያመለከተ ። ዓለማየሁ የእስረኞቹን ክፍሎች አነስተኛ አጥር ተደግፎ ጠበቃቸው ። ወደእሱ እየቀረቡ መጡ ። ሐረገወይን ትመራለች ፣ ዐይኖቿ ላይ ያቀረሩት እንባዎች ለመውረድ እየተዘጋጁ ዓይኖቿን ጭጋግ የጋረደው ሰማይ አስመስለውታል ። ወይዘሮ አስካለና ምክትል መቶ አለቃ ስንታየሁ ትክዝ ብለዋል ። ዛማኑኤል እስረኛ የሚጠይቅም አይመስልም ፣ ይሥቃል። ዓለማየሁ ሁሉንም በየተራ ተመለከታቸው ፣ ፈገግታ አልተለየውም። ሁሉንም ጨበጣቸውና ሐረገወይንን እቅፍ አድርጎ እንባዎቿን ጠራረገላት ።

“ዝም ብላችሁ እኮ ነው የለፋችሁት ፣ አያስፈልግም ነበር” አላቸው ፣ ድምፁ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ።

“እየ እኛ ምን እንሆናለን ብለህ ፣ አንተ የታሰርከው እያለህ

ለእኛ ታስባለህ?" አሉ አክስቱ እንባቸውን እየጠራረጉ ።

"እማትዬ ፡ ይተው ለቅሶ ምንም አይጠቅመውም ፡ ወንጀለኛ አይደለም ፡ ይፈታል አይዞዎት" አለ ዛማኑኤል ፈገግ እያለ ።

የወይዘሮ አስካለን ትከሻ ጨብጦ አደረገና ደሞ ወደ ዓለማየሁ ዞረ ።

"ዓሌ አይዞህ የሕይወትን ጣፋጭ ጐኗን ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ጊዜ መራራዋን መቅመስ ጥሩ ነው ። ራሱ ሕይወት ስለሆነ ያበረታል እኮ ! እውነቱን ነው እኔም እንደ ዓመት ከ14 ቀን ቀምሼታለሁ ። መራራ ሲበዛ ደግሞ ይጣፍጣል ፡ የሚመረው ሕይወት ሁልጊዜ ስትጣፍጥ ብቻ ነው ፡ አይዞህ ምንም አትሆንም ። በርታ ዘመድ ሆነን በትዕዛዝ ልናስፈታህ ባንችልም ፡ በሐሳብ ግን ሁልጊዜም ካንተ ጋር ነን ።" የያዛቸውን ሁለት መጻሕፍት አጠጣና ሰጠው ። "አሜሪቆቾች ቢሆኑህ ብዬ ነው ፡ ሰሞኑን የወጡ ናቸው" አለ አሁንም ፈገግ እያለ።

"እመሰግናለሁ ዛማኑኤል ፡ እኔ አልተጨነቅሁም አይዟችሁ ፡ ብቻ ይችን ልጅ ተቆጡልኝ ። ቅድም እዚህ ያደረገችው ሁሉ ደስ አላለኝም ። ሁሉንም ነገር ቀስ ብለን እንደርስበታለን ፡ መቸኮል ጥሩ አይደለም ። ዛማኑኤል እንግዲህ የሐረግን ነገር ለአንተ ጥየዋለሁ ፡ እባክህ ተቆጣት ። አልሟሟም እኔ" አለ ዓለማየሁ ጠያቂዎቹ እንዳያስቡ ፈገግ እያለ ።

"በቃ በቃ ተመለስ ወደ…ክፍልህ" አለ ፖሊሱ ሮጦ ።

"እባክህ… ሦስት ደቂቃ… ሦስት ደቂቃ…" ለመነችው ሐረገወይን ።

"ቶሎ በሉ እሺ ቶሎ በሉ" አለ ፖሊሱ ሁኔታቸውን ከሩቅ ሆኖ እየተከታተለ ።

"በቃ እንሒድ ፍራሹን ጋቢውንና ሳህኑን ስጡት ። አይዞህ በርታ አንተም ፡ ጧት ቁርስ ይዤልህ እመጣለሁ በቃ" አለ መቶአለቃ ሌሎቹን ሲያዳምጥና ሐሳብ ባሕር ውስጥ ገብቶ ሲዋኝ ከቆየ በኋላ ። ሐረገወይን እጆቿን ዓለማየሁ ትከሻ ላይ ጣል

እያረገችና ትክ ብላ ተመለከተችው ። አልከሳም ፡ አልጠቆረም ፡ ያው የምታውቀው ዓለማየሁ ነው ።

“ቁንጫ አለው እዩል ክፍሉ” አለች ዐይኖቿን ዐይኖቹ ላይ ተክላ ። ዓለማየሁ ፈገግ እያለ ራሱን ነቀነቀ የለውም ለማለት ። እንዳያከፋት ፡ እንዳትጨነቅበት ።

“በጧት ቁርስ አመጣለሁ ፡ ቅያሪ ልብስም ያስፈልግሃል” አለችና ወደ ጆሮው ጠጋ አለች ። “እኔ እንግዲህ በቃኝ አባት አለኝ ብዬ ቤት አለኝ ብዬ እነሱ ጋር አልሔድም ፡ ከዛሬ ጀምሮ አንተ ቤት ነው የማድረው ይኸን እወቀው” አለችው ።

ዓለማየሁ የሐረገወይንን እጆች ከትከሻው ላይ አላቀቀና ፡

“እንዳትጣሊኝ… ፡ ሐረ እንዳትጣሊኝ ፡ ነግሬ…ሻለሁ እቀ… የምሻለሁ ። ልክ… አይደለሽም ። ልክ… አይደለሽም ፡ ብየሻለሁ ” አለ ቃሉ ቁርጥ ቁርጥ እያለበትና ጭንቀት እያንገላታው ። መታሰሩ አሁን የበለጠ ቆጨው ።

“ምንድን ነው ሐረ” እያለ ጠጋ አለ ዛማኑኤል ።

“ዛማኑኤል እባክህ ተቆጣልኝ ። ‘ቤቴ አልሔድም’ ነው የምትለኝ ፡ ይህች ልጅ ከቤተሰቦቿ ጋር ተቆራርጣ ትቀራለች… እባክህ ተቆጣልኝ ።”

“እሱማ አይሆንም ፡ ግዴለህም ዓሌ ለእኔ ተወው አሁኑን ይዣት ነው የምሔደው” ዛማኑኤል ሐረገወይንን እቅፍ አደረጋት ። አሁንም ታለቅሳለች ። ዓለማየሁ ከእነሱ ጋር ቆይቶ የበለጠ ለመጨነቅ አልፈለገም ። “ዛማኑኤል እንግዲህ አደራህን ! በሉ በቃ ደህና እደሩ ፡ ደህና እደሩ” አለ ።

መቶአለቃ ሰንታዬሁ ከኪሱ ሁለት ባለ ዊንስተን ሲጃራና ሦስት ክብሪት አውጥቶ ወደ ጠባቂው ፖሊስ ሔደ ። ለፖሊሱ አሳየውና መልሶ ለዓለማየሁ ሰጠው ። ሌሎችም የያዙትን እያስፈተሹ ሰጡት ። “ደህና እደር” ተባብለው ተሰነባበቱ ።

ዓለማየሁ ፍራሹን ፣ የሳህን እንጀራውን ፣ ሲጃራውንና ዛማንኤል የሰጠውን መጻሕፍት ተሸክሞ ወደ ክፍሉ አመራ ። ፖሊሱ በሩን ከፍቶ አስገባውና ከጀርባው በሩን ቆለፈ ። አንዷ ባኮ ሲጃራ ወዲያውን አለቀች ።

ምሽቱ ላይ የእስር ቤቷ በር ተከፈተ ። "ግባ ግባ ወዮልህ ግባ ብየሃለሁ" ይላል ፖሊሱ ።

"ቀስ ብዬ ተንቀባርሬ ነው የምገባው… ቀስ ብዬ ተንቀባርሬ ነው የምገባ" ይላል የሚታሰረው ሰው በቀብራራ አነጋገር ። ፖሊሱ በሩን ከፈት አድርጎለት እንደገባ "የእሳቱ ላንቃ ፣ ወንዱ የእሳቱ ላንቃ ፣ ፈትበል ወስላታ… ሁሉ" አለና ሽማግሌውን እስረኛ በእርግጫ መታቸው ።

"ቀብራራው ንጉሤ ይኸን እስር ቤት አልበረጉ አያረከው አያደልም እንዴ?" አለ ወፈፌው ጥጉን ይዞ የዓለማየሁን ሲጋራ እያቦነነ ። ያች ጠባብ የእስር ቤት ክፍል ተረበሸች ። ቀብራራው ሰውን ሁሉ እያረጋገጠ አለፈና ጥግ የተቀመጠውን ሰው ጉትቶ አስነሣና ቁጭ አለ ። ሁሉም ስለሚያውቀው ፈራው ። ጫጫታና ሁካታ ንግግባት የሞላው እስር ቤት ረጭ አለች ።

ምዕራፍ ሦስት

ሐረገወይን ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ በዐይኗ አልዞረም ። ስታስብ ስትጨነቅ ፡ ስትቃዥ አደረች ። ዕንቅልፍ እንዲወስዳት ያላደረገችው ጥረት አልነበረም ። ግን እምቢ አላት ። እንቅልፍ አልወስድ ሲል ተንጋሎ ቁጥር መቁጠር ጥሩ ነው ሲባል ትሰማ ነበር። አራት ጊዜ ከአንድ እስከ መቶ ቀስ እያለች ቆጠረች ፡ ግን አልሆንላትም ። በአዕምሮዋ ውስጥ ያለውን ለመርሳትና ለማሸለብ የተለያዩ ሐሳቦችን አፈለቀች ። የልጅነት ጊዜዋን አስታወሰች ፡ የትምህርት ቤት ጓደኞቿን ፡ የወላጆች ቀን እሷና ጓደኞቿ በትምህርት ቤት የሚያደርጉትን ፡ ወደ ትምህርት ቤት ሲሔዱ ሸሁ ሱቅ ፓስቴ ገዝተው እየተከፋፈሉ የሚበሉትን… ሌሎች ሌሎችንም ጥሩ ጥሩ ትዝታዎቿን እያሰበች ጭንቀቷን ለመርሳት ሞከረች ። ግን አልሆንላትም ።

በጭንቀት ያሳለፈችው ሌሊት የግድ ነጋላት ። አልጋዋ ላይ እንደ ተንጋለለች ሰዓቷን ተመለከተች ። ልክ አሥራሁለት ሰዓት ይላል ከንጋቱ ። ፒጃማዋን እንደ ለበሰች ተነሣች ። የመኝታ ክፍሏን መብራት አበራችና መስኮቷን ከፈተች ። ከመኝታ ቤቷ መስኮት ፊት ለፊት የሚታዩት የወጥቤት ሠራተኞች መኝታ ክፍልና የማዕድ ቤቱ በሮች እንደተዘጉ ናቸው ። መለስ ብላ ቁምሳጥኗን ከፈተች ። ከቁምሳጥኑ መዝጊያ ላይ ከተለጠፈው መስተዋት ጋር ተፋጠጠች ። አንዲት ውብ ልጅ ከመስተዋቱ ውስጥ ሆና ተመለከተቻት ። ዐይኗ እንደ ከዋክብት ያበራል ፡ ጸጉሯ በጀርባዋ በኩል ወርዶ ትከሻዋ ላይ ያርፍና ግራና ቀኝ በአንገቷና በትከሻዋ መካከል ሾልኮ በደረቷ ላይ ከተተከሉት ጡቶቿ ላይ ዘፍ ብሏል ። ሰልከክ ያለው አፍንጫዋ ከዐይኖቿ የሚፈልቀውን ብርሃን መልሶ እያስተጋባ ደምቆ ከፊቷ መኻል ጉብ ብሏል ።

ትናንት ከሰዓት በኋላ ከዐይኖቿ የሚወርደውን እንባ እያስተናገዱ ቁልቁል ሲያንከባልሉ የነበሩት ጉንጮቿ የእንባ መስመር ሰርተዋል ። ጸጉሯን በጣቶቿ አበጠረችና በጀርባዋ በኩል ነሰነሰችው ። በጉንጮቿ ላይ ያሉትን የእንባ መስመሮች ጠረገችና መልሳ ወደ መስኮቷ ተጠጋች ። ከፊት ለፊት የሚታዩት በሮች አሁንም እንደተዘጉ ናቸው ። ብርዱ ይጋረፋል ። ጥቂት ተመለከተችና መታጠቢያ ቤት ገብታ በሩን ከውስጥ ዘጋች ።

ዓለማየሁን ጠይቃ እንደተመለሰች ከዛማኑኤል ጋር እየተጨቃጨቁ ነው ቤቷ የገባችው ። ገና ትምህርት “ሀ” ብላ ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ ዛሬ ድረስ በምትተኛበት አልጋዋ ላይ ለማደር አልፈለገችም ነበር ። ይሁንና ዛማኑኤል አልፈቀደላትም ። ተቆጣት። ሌላ ምርጫ አልነበራትም እሱኑ ተከትላ መጣች ። ከእስር ቤት ዓለማየሁን ጠይቀው እንደወጡ ስንታየሁ ራት ጋብዞአቸው ስለነበር ቤቷ እንደደረሰች ቀጥታ ወደ መኝታ ክፍሏ ነው የገባችው። እንደ ገባች ልብሷን አወላለቀችና ፒጃማዋን ለብሳ ተኛች ፡ ሽፍንፍን ብላ ። ግራና ቀኝ ስትገላበጥ ቆየችና ብዙም ሳትቆይ ተነሣች ። ራስጌዋ ካለችው ኮሞዲኖ ላይ ካስቀመጠቻቸው መጻሕፍት መካከል አንዱን አንሥታ ማንበብ ጀመረች ። ጥቂት ገጾች አነበበችና መጽሐፏን ካነሳችበት መለሰቻት ። ዐይኗን መጽሐፏ ላይ ተክላ ብዙ ገጾች ገልብጣለች ። ግን ያነበበችው ስለምን መሆኑን አታስታውስም ። መልሳ ጥቅልል አለችና ተኛች ። ጥቂት ቆይታ መቁጠር ጀመረች ። ለብዙ ጊዜ ስትቆጥር ቆየችና ጉልበቶቿን አጣጥፋ ፊቷን ወደ ግድግዳው አዙራ ተኛች ። የፈለገችው እንቅልፍ ሊወስዳት አልቻለም ። ተነሣች ። ጋቢዋን ደረበችና መኝታ ክፍሏ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ማለት ጀመረች ። ሲደክማት አልጋዋ ጫፍ ላይ ዐረፍ አለች ። ሌላ መጽሐፍ አነሣች ። እጇ እንዳመጣላት አንዱን ገጽ ገለጥ አደረገችና ማንበብ ጀመረች ።

“ሐሳብ መጨረሻ የለውም ። ቁምነገሩ መኖር ነው ፡ የኑሮን ጣዕም ማወቅ ። ሐሳብ የፈጠረው ግብ ካልደረሱ ውጤቱ ያው ነው ፡

ምሬትና ብስጭት” ብላ አነበበች ። “ኢጭ” አለችና መጽሐፉን ወረወረችው ።

መስኮቷን ከፍታ ወደ ውጭ ተመለከተች ። የሚሰማ ነገር የለም ። ሁሉም ተኝቷል ። ዘነበች ፡ ዘነበች” አለችና ተጣራች ። መልስ አላገኘችም ። የመኝታ ቤቷን በር ከፍታ ወደ ዛማኑኤል መኝታ ክፍል ሔደች ። ገና በሩ ላይ ስትደርስ ሲያንኰራፋ ተሰማት ። ተናደደችና ተመለሰች ፡ መስኮቷንና በሯን ዘግታ ተኛች ። የምትፈልገውን እንቅልፍ ልታገኝ አልቻለችም ። ጥቂት ቆይታ ቅዠት ጀመራት ።

መጀመሪያ ጥቅጥቅ ያለ ደመና በእሳት ሲቃጠል ታያት ፡ ከዚያ ከሚቃጠለው ደመና መኻል አንድ ግዙፍ ሰው የሚመስል ነገር ብቅ አለና አስደነገጣት ። የሰው መሰሉ ፍጡር አፍንጫ ከመሬት ሊነሣ የሚያሽከበክብ ጃምቦ ጄት አይሮፕላን መስሎ ታያት ። ጆሮዎቹ ሰፋፊ ሜዳ መስለው በግራና በቀኝ ተለጥፈዋል ። ከላይ እንደ አህያ ጆሮ ቀጥ ይሉና ከታች ጉልበቱ ድረስ ይደርሳሉ ። አፉ የጣናን ሐይቅ ያህል ይሰፋል ። በግራ ጐኑ የታጠቀው ጐራዴ ርዝማኔው የአክሱምን ሐውልት የሚበልጥ መሰላት ። ሲራመድ መሬት ሲጢጢጥ ትላለች ። ወደ እርሷ ሲቀርብ ድምጿ እንደማይ ሰማ ሆና ጥቅልል ብላ ተኛች ።

“አንቺ··· አንቺ ሐረገወይን” አለ ልክ የመብረቅ ያህል ጮሆ። ዝም አለች ። ተሸፋፈነችና ጸጥ ።

“አትሰማም ! አንቺ ባለጌ አትሰሚም··· ተነሽ !ለመሆኑስ ከእኔ ለማምለጥ ትሻለሽን? ዓመት ብትሮጪ እንዴ ተራምጄ እደርስብሻለሁ ፡ ተኝተሽ እንዳልሰማ ብትሆኚ እፍ ብዬ እነሳሻለሁ ··· ፡ እህሳ አትነሽም?” አላት ያ ግዙፍ ነገር ጨረቃ ጨረቃ የሚያካክሉ ዐይኖቹን እያንቦገቦገ ።

“እ···ሽ··· እ···ሽ··· እነሣለሁ” አለችና ተነሥታ እግሩ ሥር ተንበርክካ መለመን ጀመረች ። አሻቅባ ስትመለከተው ፊቱን ማየት

አቃታት ። ከእግሩ ሥር ሆና ወደላይ አንጋጣ ስትመለከት ካደረገዉ ሰፊ ቦት ጫማ በላይ ማየት አቃታት ።

“ተነሽና ራቅ ብለሽ ቁሚ” አላት ።

“እ…ሽ… እ…ሽ…” ከፊቱ ራቅ አለችና ቆመች ። ርቃ አቋሙን ሁሉ ስትመለከተው እጅግ አስፈራት ። እንባዋን ዱብ ዱብ ማድረግ ጀመረች ።

“አስቀድሞ ነበር አልሞ መደቆስ… ስማሽ የእኔ እህት ፡ አስቀድሞ ነበር…አሁን ልቅሶሽ ለምን ሊበጅ ፡ ከማን ሊያስጥል?”

“ምን አደረ…ኩዎ! ምን…ም አላደረኩዎ… እባክዎ ይማሩኝ”

“ኩኩኩኩኩ” አለና ሣቀ ። ሲሥቅ የክረምትን ነጎድጓድ ያህል ያስፈራራል ።

“ንሺ አንቱ አልሽኝ ደግሞ ፡ ደግ ብለሻል ፡ መግዘፌን አይተሽ፡ አንቱ አልሽኝ ፡ በ7 ዓመት ትበልጪኛለሽ እኮ …አንተ በይኝ… አንተ በይኝ ቁጣዬን አታምጪብኝ”

“እ…ሽ ፡… እ…ሽ” አለች ሁለቱንም እጆቿን አፏ ላይ ለጥፋ።

“ለመሆኑ ታውቂኛለሽ? ማን መባሌን ታውቂያለሽ?”

“ኧረ አላውቅም ፡ ፈጽሞ አላውቅም”

“ደግ… ሰይፈ ነጎድጓድ እባላለሁ ፡ ፍርዱ አይላዳይ ፡ ቅጣቱ አዳባይ ፡ ምርቃኑ ሲሳይ ፡ ሰይፈ ነጎድጓድ እባላለሁ ። ስቆጣ መሬቷ ትረግዳለች ፡ ሰይፌን ስመዝ ትርበደበዳለች ፡ ስስንዝር እንዳልነበር ትሆናለች ፡ አሁንሳ ከልብ ዐውቅሺኝ”

“አዎን እያ ሰይፈ ነጎድጓድ ዐውቅሁህ ፡ ቁጣህን አታምጣብኝ”

“ኩኩኩኩኩ ፡ ቁጣህን አታምጣብኝ አልሺ ”

“አዎ… ማረኝ ሰይፈ ነጎድጓድ… ማረኝ”

"ዝም ብለሽ የምጠይቅሽን መልሺ ። አንድ ስጠይቅሽ አንድ ሁለት ስጠይቅሽ ሁለት መልሺ …ቁጣየ እንዲበርድልሽ"

"እሺ እመልሳለሁ"

"ለምንሳ አባትሽን ካድሽ አንቺ ከንዲ"

"በፍጹም በፍጹም ሰይፈ ንጉድጓድ !"

"ለጉረምሳ ፡ ካድሽው አባትሽን… በጉረምሳ ለውጥሽው?"

"ፍጹም ፍጹም ሰይፈ ንጉድጓድ ፡ አባቴን በማንም አልለውጥም ሐሰት ሐሰት በማንም አልለውጠውም"

"እኔንም ካድሽኝ" አለና ጉራዴውን መዘዘ ፡ የሚያንቦገቡግ ጉራዴውን ።

"ውይ… ውይ… ሰይፈ ንጉድጓድ" አለችና ተንበረከከች ። ከፊት ለፊቷ ያለውን መሬት በጉራዴው እንዴ አቀመሰው ። የአባይን ሸለቆ ያህል ተሰነጠቀ ።

"ው…ይ ው…ይ ሰይፈ ንጉድጓድ አባክህን ምሕረትህን"

ከጉኗ ዞረና ያልተሰነጠቀውን መሬት በጉራዴው አቀመሰው ። ሌላ ሸለቆ ፡ ከኋላዋ ዞረና ጉራዴውን ሰነዘረ ፡ ሌላ የአባይ ዐይነት ሸለቆ ፡ በአራተኛው ማዕዘን ዞረና ጉራዴውን ሰነዘረ ሌላ ሸለቆ ።

"ውይ… ውይ… ምነው ሰይፈ ንጉድጓድ? ምነው ሰይፈ ንጉድጓድ? ብቸኛ እኮ አደረከኝ ፡ ከዓለም እኮ ለያየኸኝ ፡ እረ ምሕረትህን"

"…ከ·ከ·ከከ·ከከከ" አለና ሸለቆው ውስጥ ሽንቱን ሸናበት ። በአንድ ጊዜ በአራቱም ማዕዘን ሞላ ።

"ውይ… ውይ… ሰይፈ ንጉድጓድ ውይ… ውይ… ሰይፈ ንጉድጓድ"

"አሁንሳ ትክጃለሽ… በይ ተናገሪ"

"እሺ… እሺ… ጉሬዴህን አፎቱ ውስጥ ክተተው ፡ እውነቱን እነግርሃለሁ ክተተው… ክተተው ሰይፈ ንጉድጓድ"

"ተናገሪያ ፡ ተናገሪያ" ጕራዴውን ወደ አፎቱ መለሰው ።

"በይ ተናገሪያ እውነቱን" አለና ዐይኑን አንቦገቦገባት ።

"እሽ አባቴን እወደዋለሁ ፡ ከእርሱ ሌላ አባት የለኝም ፡ በአባትነቱ እሱን ማንም ሊተካልኝ የሚችል የለም ፡ በአባትነቱ በማንም አልለውጠውም ። ፈጽሞ አልለውጠውም ። ሰይፈ ነጐድጓድ ጐረምሳ ያልከው እኮ አባቴ አይደለም ። አየህ እሱን ደሞ አባቴ አይተካልኝም ፡ አየህ ሰይፈ ነጐድጓድ…"

"ምን አልሽ" አለና ጕራዴውን መዘዘ ። አስተካከለና በራሷ ትክክል ሲሰነዝርባት "ዋ…ይ" አለችና ነቃች ። በቃ ከዚያ በኋላ አልተኛችም ።

በመታጠቢያው ቤት ውስጥ ቆይታ ወጣች ። ፊቷ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ያበራል ። የብስጭት እንባ ሲወርድበት ያደረው ጉንጯ በውሃ ተወልውሎ ያንፀባርቃል ፡ እንደ ወጣች ቀጥታ ወደ መስኮቱ ሔደችና አሻግራ ተመለከተች ። ፊት ለፊት የሚታዩት ሦስት በሮች እንደተዘጉ ናቸው ። መለስ አለችና ወደ ዛማኑኤል መኝታ ክፍል ሮጠች ።አሁንም ያንኮራፋል ። ወደ መኝታ ክፍሏ ተመልሳ ቁም ሳጥኗን ከፍታ ከመስታወቱ ጋር ጨዋታ ጀመረች ። ከመስተዋቱ ውስጥ ሆና ፊት ለፊት አትኩራ የምትመለከታትን ውብ ሴት መልክ አደነቀች ፡ እንደ መሽኮርመም አለችና ዐይኗን መለስ አደረገች ። ከቁም ሳጥኑ ውስጥ ካሉት መሳቢያዎች አንዱን ሳበችና ከውስጡ ያሉትን ወረቀቶች ማገላበጥ ጀመረች ። ዐይኗ አንድ ደብዳቤ ላይ አረፈ ። ከሌሎች ወረቀቶች መኻል መዛ አወጣችው ። ዓለማየሁ ለብሔራዊ የዩኒቨርስቲ ሰርቪስ ጐሙጐፋ ዐርባምንጭ በመምህርነት ሲሔድ የጻፈላት የመጀመሪያ ደብዳቤው ናት ።

"የምወድሽና የማፈቅርሽ ምንጊዜም ከዐይኔ የማትሰወሪው ፡ እህቴ ወይዘሪት ሐረገወይን ወንዲራድ ፡ እንባ እየተናነቀን ከተሰነባበትንበት ዕለት ጀምሮ እስካሁን እንደምን ሰንብተሻል ። እውቶቡስ

ተራ ስንሰነባበት በአውቶቡሱ መስኮት ብቅ ብዬ ‘ቻው ሐረየ’ ብየ እጇን ሳርገበግብልሽ ከፊትሽ ላይ ይነበብ የነበረው የሐዘን ስሜት ዛሬም ድረስ ከፊቴ ገጭ እያለ ያስቸግረኛል ። ሐረ ሰው መቻስ ትልቁ ሞት መጥቶ ዳግም እንዳይመለስ አድርጎ እስከ ወሰደው ድረስ እየተለያየ መገናኘቱ ያለ ነው ። ለዐሥር ወራት ዕድሜ ነው እዚህ የምቆየው ። ለዚያውም በየሲሚስተሩ መጨረሻ ስለምመጣ እንገናኛለን ።

“ሐረ አውቶቡሳችን ዐርባ ምንጭ ደርሶ ውረዱ ስንባል ፈጽሞ አላመንኩም ነበር ። ከሰው ሁሉ መጨረሻ የወረድኩት እኔ ነኝ ። የወረዳ ከተማ እንጂ በውነት ዐርባምንጭ አልመሰለኝም ነበር ። ከአዲስ አበባ ስነሣ በሐሳቤ የሳልኩት ዐርባምንጭና እውነተኛው አርባ ምንጭ ፈጽሞ አልገናኝ ብለውኝ ምን ትቀልዳላችሁ ዐርባ ምንጭ ይኸ ነው እንዴ? እያልኩ ሰውን ሁሉ አሥቄያለሁ ። ግን አሁን ይገርምሻል በጣም እየወደድኩት ነው ። ከተማው ለሁለት የተከፈለ ነው ። ዐይንን እጅግ የሚማርክ የተፈጥሮ ውበት የታደለ ሀገር ነው ። ማታ ማታ በቀለ ሞላ ቡና ቤት ሆነን ኮካኮላችንን እየተጎነጨን ዙሪያውን ስንመለከት መንፈሳችን ይታደሳል ። ቀን ቀን ሲያቃጥል ከሚውለው የፀሐይ ሐሩር ተላቀን ግራና ቀኝ ካሉት ኃይቆች የሚነፍሰውን ንጹሕ አየር እየተመገብንና አሻግረን የነጭ ሳርን ብሔራዊ ፓርክ እየቃኘን የሕይወትን ግሩም ጣዕም እያጣጣምን እናመሻለን ። ሐረዬ እዚህ ቦታ ሆኜ ቁልቁል ጥቅጥቅ ያለውን ደንና በግራና በቀኝ ያሉትን የአባያና ጫሞ ኃይቆች ስመለከት እቆይና ምነው ሐረዬ እዚህ ኖራ በነበር እላለሁ ። መቼም አንድ ቀን ይህንን ውብ ተፈጥሮ በግድ መጎብኘት ይኖርብሻል ።

“ይህንን በጥቂቱ ካወሳሁልሽ ወደ ቁም ነገሩ ልመለስ ፡ ሐረ በሚቀጥለው ዓመት ማትሪክ ወሳጅ እንደሆንሽ ታውቂያለሽ ፡ ስለዚህም ከአሁኑ ጀምሮ ከፍተኛ ዝግጅት ማድረግ ይኖርብሻል ፡ በዚህ አንቺን እህቴን ባምንብሽም የወንድምነት ምክሬን ግን መለገስ ይኖርብኛል ። ሐረዬ እኔ ከዩኒቨርሲቲ ስወጣ አንቺ መግባት

አለብሽ ። አደራሽን በርቺ ። ሀገሩን የበለጠ ስለምደውና ለአንቺ የሚጸፉ ጥሩ ጥሩ ነገሮች ሳገኝ በሰፊው አወጋሻለሁ ፡ እስከዚያው ሰላምና ጤና ከአንቺ ጋር ይሁኑ ።

ያንቺው ዓለማየሁ ድንበሩ ።”

አንብባ እንደ ጨረሰች አጣጥፋ መልሳ ከነበረበት አስቀመጠችው ። ዓለማየሁ ዓርባ ምንጭ በቆየባቸው ዐሥር ወራት ውስጥ የጻፋቸውን ዐሥራ ስድስት ደብዳቤዎች አጣጥፋ አስቀምጣቸዋለች። ለጥቂት ጊዜ ስታስብ ቆየችና ወደ መስኮቱ አመራች ። ዘነበች ከማዕድ ቤት ወጥታ ወደ መኝታ ቤቷ ስትገባ አየቻት ። ከባድ ዝናብ ይጥላል ፡ የሚያስደነግጥ ጉርምርምታ ይሰማል ።

“ዘነበች ፡ ዘነበች” ብላ ተጣራች ።

ዘነበች ዞር ብላ ተመለከተችና ፈገግታ የሞላው ሰላምታ አቀረበችላት ። ዘነበች ሐረገወይን ስትጠራት እንድታጫውታት መሆኑ ይገባታል ። እሷም መጫወት ትወዳለች ። ግን ‘ሥራ ፈትሽ ወሬ ታወሪያለሽ?’ ይሉኛል ብላ በጣም ትፈራለች ። ሐረገወይን ደግሞ ከዘነበች ጋር መጫወትን ትወዳለች። ሐሳቧን ጭንቀቷን የምታስረሳት መካሪዋና ምስጢረኛዋ ናት ።

ዘነበች የሐያ ስምንት ዓመት ሴት ናት ። ወሎ ጉባላፍቶ ውስጥ ተወልዳ አደገችና በ15 ዓመቷ ተዳረች ። ከባሏ ጋር ስድስት ወር ቆየችና ጠፍታ ቤተሰቦቿ ዘንድ ሔደች ። አባቷ ጨቅጭቀው መልሰው ለባሏ ሰጧት ። እንደ ምንም ተቸግራ አንድ ዓመት ቆየችና ተመልሳ ወደ ቤተሰቦቿ ኮበለለች ። በልጅነት ዕድሜዋ ትዳር ፈጽሞ ሊጥማት አልቻለም ። በዐሥራ አምስት ዓመቷ ያገኛት ጐረምሳም በትንሽ ትልቁ ‘ውሃ ቀጠነ’ ብሎ ይቆጣታል ፡ መልስ ስትመልስለት ይደበድባታል ። ስልችት አላትና ኮበለለች ። በዚህ ወቅት አባቷ ብዙም ሊያስገድዷት አልፈለጉም ። ሽማግሌ ልከው አፋቷትና አባት እናቷ ቤት ቁጭ አለች ።

'ላግባ' የሚል ብዙ ወንድ መጣ ። ያልተላከ የመንደር ሽማግሌ አልነበረም ፡ ዘነበች አሻፈረኝ አለች ። የመጀመሪያ ባሏ አራጋው ወንዱን ሁሉ እንድትጠላ አደረጋት ። አባትና እናቷ የሽማግሌ ግፊት ሲበዛባቸው ተቆጧት ፡ ጨቀጨቋት ። ሦስት ዓመት ከቤተሰቦቿ ጋር ተቀመጠችና ኮብልላ ወደ ደሴ ሔደች ። ደሴ ወይዘሮ ሙሉ መጠጥ ቤት በወጥቤት ሠራተኛነት ስታገለግል ቆየች ።እዚያም አልተስማማት ። "አዲስ አበባ ዘመድ አለኝ እዚያው ሔጄ ዕድሌን እሞክራለሁ" ስትል ከነበረች የሥራ ጓደኛዋ ጋር ወደ አዲስ አበባ መጣች ።

አቶ ወንዲራድ ቤት ሦስተኛዋ ነው በቤት ሠራተኛነት ተቀጥራ ስትሠራ ። አንድ ዓመት ከስድስት ወር ሆኖአታል ። ዘነበች ጠይም ናት ፡ ቆንጆ ጠይም ። ግንባሯ ላይ የተነቀሰችው የመስቀል ምልክት ቀረብ ብሎ ካላዩት በስተቀር ከሩቅ አይለይም ። ቅባትና ማበጠሪያ አይቶ የማያውቀው ጸጉሯ አንድ ቀን ወግ ቢደርሰው ድንቡሽቡሽ ካለው መልኳ ጋር ተዳምሮ የብዙ ወንዶችን ልብ ያሸፍታል ። በሻሽ ተጠፍሮ የሚውለው ጸጉሯም ቢሆን መልኳን አልደበቀውም ። የማይመስላትን ነገር ስትሰማ "ተብየም አላቅ" አለች እትዬ ቸሬ" ትላለች ፈገግ እያለች ። ፈገግ ስትል ደግሞ ጥርሶቿ የተለየ ውበት ይሰጧታል ።

"አንቺ ዘነበች ደንቆሮ አትሰሚም" ደገመችና ተጣራች ሐረገወይን ። ሲጨንቅ ያደረውን አዕምሮዋን ለማዝናናት የፈለገች ትመስላለች ፡ ጭንቀቷን ለመርሳት ።

ዘነበች በሩን ገርበብ አድርጋ ፡ "ፈለግሽኝ እትዬ" አለች ፈገግታዋን እያሳየቻት ።

"ማቢ ደንባራ ፡ ዛሬ ደግሞ ብሎ ብሎ ጆሮሽም ደነቆረ ።"

"ተብየም አላቅ…ሰምቸሻለሁ እኮ እሳት ላቀጣጥል ብዬ እንጂ ስትጣሪማ ሰምቸሻለሁ ሙች ሰምቸሻለሁ ።"

"በይ ቁጭ በይና እምነግርሽ ጉዳይ አለ"

“ኧረ አቦ ሥራ አለኝ ልሒድበት”

“ቁጭ በይ ብየሻለሁ እማጫውትሽ ጉዳይ አለ”

“እንደው ልታጃጅይኝ ነው እይ አሁን ምን ቁም ነገር ልትነግሪኝ ነው?” ዘነበች ቁጭ አለች ከሐረገወይን ፊት ለፊት ። የቀሚሷን ጫፍ ሰብሰብ አደረገችና ጠቅልላ በጭኗና በወንበሩ ሥር ከተተችው።

“በያ ንገሪኝ” አለች እጆቿን ጡቶቿ ላይ አደራርባ ።

“ይኸን ሰሞን ደግሞ ፍዝዝ ብለሽብኛል ፣ አራጋው ትዝ አለሽ መሰለኝ ?”

“ዐውቄብሻለሁ አቦ ልታጃጅይኝ መሆኑን በፊቱንም ዐውቄዋለሁ። ታዲያ በጧቱ ምን ቁም ነገር ልታወሪኝ !”

“አራጋው አዲስ አበባ መጥቶ እየፈለገሽ ነው ማለትን ሰምቻለሁ ከዚህ ግቢ ትወጪና አፍኖ ነው እዚያው ወልድያሽ የሚወስድሽ ተጠንቀቂ ፣ ነግሬሻለሁ ተጠንቀቂ” አለች ቀልድ መሆኑ እንዳይታወቅባት ሣቋን አፍና አድርጋ ።

“ድንቄም እቴ! እንኳን አዲስ አበባን ደሴንም በቅጡ አያውቀው ።” ዘነበች የራሷ እንጋገር አሣቃት ። ከት ብላ ሣቀች ። “አቦ እትዬ ንገሪኝና ልሒድበት ፣ ልታጃጂይኝ መሆኑን ዐውቄብሻለሁ ። በይ ልጂ ሥራየን ልሥራበት” ተነሣች ከመቀመጫዋ ።

“ቁጭ በይ” ሐረገወይን ገላመጠቻት ። ዘነበች ቁጭ አለች ።

“ስሚ ዘነበች ፣ እውነቱን እኮ ነው የምነግርሽ ፣ አቤት መቼስ ይታየኛል ፣ አራጋው ‘አንቺን እወስዳለሁ’ ብሎ እዚህ ቤት ሲመጣ አቶ ገበየሁ ደግሞ አትወስድም ብለው ሲደባደቡ አቤት …ይታየኛል” አለች አሁንም ሣቋን እያፈነች ።

“አይ እትዬ አሁንስ አሣቅሽኝ ! ገበየሁ ደሞ ምንቤት ናቸውና ነው ድብድብ እሚደርሱት” ኮስተር አለች ።

“እንዴ አንቺ ደሞ ልትደብቂ ነው እንዴ ?”

"በእኔ ሞት ንገሪኝ ምኑን ነው የምደብቀው ? አይሰማ የለው የሰው ጆሮ ! አፈር ስሆን ንገሪኝ ። እትዬ...በእኔ ሞት ንገሪኝ" ተነሣች ከመቀመጫዋ ።

"እንዴ ምኑን እነግርሻለሁ ፣ አገር የሚያውቀውን ፣ እሳቸው ሚስቴ ናት ነው የሚሉት"

"ተብየም አላቅ!" እንደ መሽኮርመም አደረጋትና ፊቷ ፍም መሰለ ። ፈገግ እያለች ተቀመጠች ።

"ይኸውልሽ እልቅስ ካነሳሽው አንድ ነገር ላውራሽ"

"የእንቺንና የእሳቸውን ታሪክ ነው የምትነግሪኝ?"

"እቦ አታጃጂይኝ ዝም ብለሽ አዳምጭኝ አልኩሽ" እጇን አወራጨች በቁጣ ፣ ጐንበስ አለችና የቀሚሷን ጫፍ ያዘች ። የተንጠለጠለች ክር አግኝታ በጠሰችና ቀና አለች ።

"ይኸውልሽ ያ ኩሩሩ ተሰማ...ተዚህ ቤት እሱን የነቀለኝን ታቦት መቸም እዘክረዋለሁ ።" ጉልበቶቿን በሁለት እጇቿ ጥብቅ አድርጋ ይዛ የኮረኮሯትን ያህል ሣቀች ።

"ምን አደረገኝ ልትይ ነው ደሞ እሱ ?"

"ምን ሆነልሽ...አንድ ቀን የጌቶችን ሸሚዝ ሳሎን ሆኖ ይተኩሳል ፣ እኔ ደግሞ ቤት እወለውላለሁ ። ሲተኩስ ቆየና 'ዘኒ' አለኝ ። ዝም አልኩት ። እንደው ውቃቢየም ሁሉ አይወደው ። ሙች እውነቴን ነው ፣ ጉረኛ ! ደሞ ቁመት ተገኘና በዚያች እኮ ሲሽከረከርባት አያፍርም...ዝም ስለው ጊዜ መተኮሱን አቆመና ፣ 'አንቺ ሲጠሩሽ አትሰሚም እንዴ?' አለና ተቆጣ ። እኔ እህትሽ ዝም። ቆየ ቆየና 'ዘነበች አንቺን እኮ ነው...ዘነበች' አለ ። መቸስ ተናዶ እሳት ሆኖአል ። 'ምን ፈለግህ' አልኩና ጮኩበት ። 'ሒጂና ሲጃራ ግዥና አምጪልኝ' አለኝ ኪሱን እየዳበሰ ። ንድድ አለኝና 'አንተ ደሞ የወዴት አገር ጌታ ነህ ። መተኮስህን አቁምና ሒደህ ገዝተህ አቡንን። መላክ ካማረህ ደሞ ገረድ ቅጠርና ላካት' ብየው መወልወሌን ቀጠልኩ ። 'ነይ ግዥና አምጪ ብያለሁ ኋላ ጉድ

ይፈላል’ አለና በዚያች ድብልብል ቁመቱ ወገቡን ይዞ ይውረገረግ ጀመረ ። እንደው እኮ ይገርምሻል ! ‘ጉረኛ የአሽከር ጉረኛ እማያቁህ አገር ሒድና አጉዛ እንጥፉልኝ በል ጉረኛ፡ ቱ…’ አልኩት ። ‘እንቺ ጅል ወሎዬ አትመጭም’ እያለኝም መሰለሽ ። እንደው ብልጭ ሲልብኝ ጊዜ ተንደረደርኩና በመወልወያው ግንባሩን አልኩት…”

“ታዲያ ዝም አለሽ?” አቋረጠቻት ሐረገወይን ።

“ልንገርሽ አደል ፡ ቡጢ ተያያዝን መችስ ጉልበቱ አያድርስ ነው ። እንደው ጅብ ነው አያድርስብሽ ፡ እትዮ ሙች ። ዘረጠጠና እሶፋው ላይ ጣለኝ ። ‘ልብ አድርግ ፡ ልብ አድርግ ትመታኝና ጉድ ይፈላል ልብ አድርግ’ እያልኩ ጮኩኝ እየተፈረጋገጥኩ ።” አቆመችና የኮረኮሯትን ያህል ሳቀች ። ቀጠለች ካቆመችበት “እቶ ተሰማ ሆዬ መማታቱን ተወና ጉንጩን ሳም አረገኝ ። ግራ ግብት እንዳለኝ ከንፈሬ ላይ እየጠመጠምልሽም! በምን ጉልበቴ ላላቀው። ዝም ብዬ እፈራገጣለሁ ። በዚሁ ሊያበቃልሽ ነው እንዴ ጉድ እኮ ነው… ቀሚሴን ገለበና እርቃኔን እያስቀረኝም መሰለሽ ። ኡ ኡ ብዬ ጮኩኝ ።”

“ታዲያ ለቀቀሽ ?”

“ምን ይለቀኛል እንደ ተናንቅን እቶ ገበየሁ ብቅ አሉ ። ጉዱ እዚህ ላይ አይደለም !! አቦ ዝም ብለሽ አድምጭኝ ፡ ገበየሁ ‘ምንድን ነው ? ምንድነው ?’ አሉ ዱላቸውን ቀስረው ። ‘ትሳደባለች ይች ጅል’ አለና ተላዬ ላይ ተነግልኝ ።

“ሲጀራ ታልገዛሽ ብሎ ይደበድበኛል ይኽ ጉረኛ” አልኳቸው።

‘እንተን ብሎ ሲጀራ እጫሽ ፡ ወጠጤ ፡ የምታደርገውን ሁሉ እኮ አይቻለሁ ወሽከሬ’ አሉት ። ‘እርስዎን የተናገረዎት የለም ፡ ዐርፈው ተቀመጡ’ አለና አፈጠጠባቸው ። ‘ባላርፍ ምን ታደርገኛለህ ፡ እስቲ ንገረኝ ምን ታደርገኛለህ’ አሉ ዱላቸውን እያዘጋጁ ፡ መልካቸው መቸስ ልውጥውጥ አለ ፡ እንዳው ዘለው እሚውጡት መሰለኝ ። ያም ባለጌ ነው ‘በቴስታ ነው ዐይንጋጃህን እማወልቀው።’

አይላቸውም መሰለሽ ። እንደው አላቅሙ ደፋር እኮ ነው እትየ ሙች ። ተይኝ መቸም ፡ በዚያ በዱላ ተርክክሰው ተርክክሰው ተውት ። ኩርምት አለና ቁጭ አለ ። እዛው እተቀመጠበት ወገብ ወገቡን አቦነኑት ። እኔ እንጀቴ ቅቤ ጠጣ ። ደሞ መቸም አልችል አይል ፡ ተንበርክኮ ሲሽማቀቅ ሳየው ጊዜ በደሉን ሁሉ ረሳሁለትና እንጀቴ ስፍስፍ አለለት ። ‘ለውሽማህ አግዘህ ነው የምትደበድበኝ’ አላቸው ። ‘እዎ ውሽማየ ናት ምን ትሆን ! ሁለተኛ ቀና ብለህ ብታያት አሳራለሃለሁ’ አሉትና ሙልቅ አሉ ።”

ሐረገወይን ከዚህ ቀደም ሰምታው የማታውቀው በመሆኑ ግርም እያላት መልሶም እያሣቃት ፡

“ይኸውልሽ ሰምቻለሁ ነው የምልሽ ። እሳቸውማ ብዙ ነው የሚያወሩት ውነት እሳቸው ምንሽም አይደሉ?” አለቻት ። የሐረገወይን አባባል በቀልድ መልክ ቢቀርብም የምትጠረጥረው ነገርም ነበራት ። እንደቀልድ የጀመረችው ነገር ምስጢር ይዘክዝካል ብላ አሰበችና ልትቀጥልበት ወሰነች።

“ምነው እትዬ ? ታልጠፋ ወንድ ከእሳቸው ጋር ትጠረጥሪኝ ። ምነው እባክሽ…በቆሽማዳ ሽማግሌ ትጠረጥሪኝ ስንት ሎጋ ሞልቶ። ለነገሩማ እሳቸውም ወገኛ ናቸው እኮ ! ሞዛዛ የሽማግሌ… ሞዛዛ።” ብድግ አለች ። “እኔስ ታዘብኩሽ ! ሙች ታዘብኩሽ ! ምንስ ማድቤት ብልኮሰኮስ ውይ በስማም…” አለች ወደ በሩ እየገሠገሠች።

“አንቺ ተመለሽ ነው የምልሽ ሙች ተመለሽ”

“ቢቃሽ እኮ አጃጃልሽኝ እስታሁን … ደሞ ሥራ አለብኝ እባክሽ ልሒድ” ገና እኮ ቡና አላፈላሁም ፡ እትዬ ሙች ጌቶች ከተነሡ ይቆጡ የለም እንዴ ።”

“ድርቢ የለችም እንዴ ? እሷ ታፍላ አንቺ ነይ ቁጭ በይ”

“እይ እትዬ ሰው አግኝተሽ ሙተሻል ፡ ተይኝ መቸም አስተዳደራቸው ፡ ምን ምኑን ቢገፉት ነው እቴ ! በስማም በስማም፡

ቤቱን አበለሻሽተውት አደል እንዴ ያደሩት ! በስማም በስማም ፡ እኒ እንደው ተነገሬ ሁሉ የቤት ሰካራም ፡ ሽቶ እሚቀባ ወንድ ፡ ሞዛዛ ሽማግሌ ያስጠላኛል ። ውይ እትዬ” አለች እጆቿን በመገረም ራሷ ላይ ጭና ።

በሩ ድንገት ብርግድ አለና ተከፈተ ። ሁለቱም የመደንገጥ ያህል በርግገው ፊታቸውን አዞሩ ። ዛማኑኤል ነው ።

“ምን እያደረጋችሁ ነው ? ደህና አደራችሁ ።”...ከሐረገወይን አልጋ ጠርዝ ላይ ሔዶ ተቀመጠ ። ዘነበች ገልመጥ አድርጋ ተመለከተችው ፤ እንደ መሽኮርመም አደረጋትና በሩን ገፍታ ወጣች።

“ተብየም አላቅ ፤ ደህና ስታሥቀኝ ቆየች ። ጭንቀቴን ሁሉ አስለቀቀችልኝ” አለች ሐረገወይን እየተንጠራራች ።

“ጥሩ ነው ጥሩ መቀለጃ አግኝተሻል … እሱን ተይውና ወደቁም ነገሩ እንሒድ” በውስጡ ያለውን ምስጢር የምታውቅበት መስሎት ድንግጥ አለ ።

ሐረገወይን ሌሊቱን እንዴት እንዳሳለፈች ፡ በዝርዝር አወራችለት። ዛማኑኤል አንገቱን ደፍቶ አዳመጣት ። ስለ ሰይፈ ነጐድጓድ ስታወራው የጭንቀቷ ልክ ምን ያህል እንደሆነ ለመገመት አላዳገተውም ። እሱም እንደሷ እንቅልፍ ሳይወስደው ሲባንንና ሲቃዥ ባያድርም ፡ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን አልጋው ላይ ተንጋሎ የእሷን ችግር ሲያወጣና ሲያወርድ ቆይቷል ።

ዛማኑኤል አንድም ገጽ ይሁን ሁለት ሳያነብ ተኝቶ የሚያውቅበት ዕለት የለም ። የትናንት አዳሩ ግን ከወትሮው የተለየ ነበር ። ሐረገወይን ጋር ራት በልተው ፡ እየተጨቃጨቁ ፡ እየተቆጣት እየመከራት ቤት ከገቡ በኋላ ለጥቂት ጊዜ ከእርሷ ጋር ቆይቶ ቀጥታ ወደ አልጋው ሔዶ ተኛ ። የማንበብ ፍላጐትም አልነበረውም ። የሐረገወይን ጭንቀት የእርሱም ጭንቀት ነው ። ከጥቂት ወራት ወዲህ አቶ ወንዲራድ ለእሱ ያላቸው አስተያየት ሁሉ ስለተለወጠ ፡ ባለፉ ባገደሙ ቁጥር ፊታቸውን የሚያጠቁሩበት መሆኑ ፡ ቀድሞ

እርሱ ካልቀረበ ራት የማይበላላቸው ሰው ከጥቂት ወራት ወዲህ መኝታ ቤታቸውን ቆልፈው ብቻቸውን መብላት መጀመራቸው አሳስቦታል ። የእሱ ጭንቀት አንድ አይደለም ። ድርብ ነው ። አንድ ለሐረገወይን አንድ ለራሱ ። በእርግጥ ከአቶ ወንዲራድ ቤት ወጥቶ የትም ሔዶ ለማደር እንደሚችል ያውቃል ፡ ብዙ ጓደኞች አሉት ፡ የሚወዱት የሚያደንቁት ብዙ ወዳጆች አፍርቷል ። ግን ከወንዲራድና ከአክስቱ ከወይዘሮ ተዋበች ጋር ተቀያይሞ ከቤት መውጣቱን አልወደደውም ። ይህ ሐሳብ ሌትም ቀንም ይረብሸዋል ። ግን ችግሩን ለማንም አላወራም ። "ዐዋቂ ሰው ችግሩን ራሱ ይፈታል" የሚል ግትር ሐሳብ አለው ። ሲያዳምጣት ቆየና ካቀረቀረበት ቀና ብሎ ፊት ፊቷን ተመለከተ። አልተጕሳቆለችም ፡ የውስጧ ብስጭትና ሕመም ፊቷ ላይ አይታይም ። ዘወትር የሚያውቃት የሚኮራባት ውድ እህቱ ሐረገወይን አሁንም ውበቷ ያው ልቅም ያለ ነው ። ደስ አለው ።

"እና ዛሬ ምን ልታደርጊ አስበሻል ?" አለ ሲፈራ ሲቸር ቆየና።

"እኔ እንጃ ግራ ገብቶኛል ። ግን ··· አሁን ወደ ሠንጋ ተራ እሔዳለሁ ፡ እሱ ቤት ሔጄ ሻይ አፍልቼ ቁርስ ልወስድለት ነው ያሰብኩት ።...ምን እሱስ ምን ፋይዳ ይኖረዋል ብለህ ነው። ሻይ ብወስድለት ቁርስ ምን ፋይዳ አለው ብለህ ነው..." ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ ይላል ።

"የለም መጀመሪያ መሥሪያ ቤትሽ ሒጅና አስፈቅደሽ ብትወጪ ይሻላል ፡ ከዚያ ያልሽውን ማድረግ ትችያለሽ ። በተረፈ ግን ፡ እኔ ብዙ መጨነቅ ያለብሽ አይመስለኝም ። አየሽ ሐሬ ለዚህች ዘላለማዊ ላልሆነች ሕይወትሽ ደስታን ልትነፍጊያት አይገባም ። እውነቱን ነው የምልሽ ተጨንቀሽ ራስሽን ከመጉዳት በቀር የምታደርጊው ፡ ዓለማየሁን የሚጠቅም አንድም ነገር ይኖራል ብዬ አላስብም ። እኔ ጋሼ ወንዲራድን እንደ ምንም ብሎ ማግባባት የሚያስፈልግ መስሎ ነው የሚታየኝ..."

ተወኝ እባክህ …" ፈንጠር ብላ ከመቀመጫዋ ላይ ተነሣች ፡

"ስሚኝ ሐረ ትልቅሽ ነኝ እኮ ከፋም ለማም ከአንቺ የተሻለ ብዙ ነገር ዐውቃለሁ ፡ የምነግርሽን ብትሰሚኝ የሚሻል ይመስለኛል።"

"እና ለምን ነው የምትለኝ ? እያወቅህ አበባን ለምን ነው የምትለኝ ?"

"አላልኩሽም ፡ ለምን አላልኩም ፡ እትዬ ለአለቃ ትንገሬቸው። አለቃ ጋሼ ወንዲራድን እንደምንም ብለው ለማግባባት ይሞክሩ የሚታየኝ ይኸው ነው …"

"እየ ሞኝ ነህ ለካ ! ምን ልዩነት አላቸውና ነው ለአለቃ የምንነግረው ። ዋናው ማን ነውና ተወኝ እባክህ !"

ወደ ቁምሳጥኑ ሔዳ ልብስ ማውረድ ጀመረች ። ፒጃማዋን አውልቃ የዕለት ልብሷን መልበስ ጀመረች ። ዛማኑኤል በትካዜ እያሰበ ዓይኖቹን ከመስኮቱ በሻገር ልኮ የሚወርደውን ዶፍ ዝናብ ይመለከታል ።

"እና ለማንኛውም አሁን ቀጥታ ወደ መሥሪያ ቤትሽ ሒጂና አስፈቅደሽ ውጪ ። ደሞ አንድ ነገር ጠምጥመው በሥራሽ ላይ እንቅፋት ሊፈጥሩ ይችላሉ ።"

"እንዴ እሱማ የእኛም ሥራ አስኪያጅ እኮ የሰውየው ጓደኛ ነው ።"

"ሒደሽ በቅድሚያ አስፈቅጅና ከዚያ እንደሚሆን እንደሚሆን አድርጊ ። አብሬሽ መሔድ ነበረብኝ ። ግን ከሰው ጋር ቀጠሮ ስላለኝ በጣም አዝናለሁ ።"

ቀጠሮ አልነበረውም ፡ "ቀጠሮ አለብኝ" ብሎ ሲናገር ፡ የልቡን ፈልፍላ ውሸትነቱን ታውቃለች ብሎ ደንግጥ አለ ። ወንዲራድ ትናንት በንዴት ወዲያ ወዲህ ሲሉ በየቦታው ስልክ ሲደውሉ ፡ ከአለቃ ጋር ሲወያዩ የእሱን ስም በክፉ ሲያነሡ ሰምቶአል ። ከዚያ ወዲህ ከፍቶታል ። እንደ ልቡ የሚናገር ደፋር

ቢሆንም የአክስቱን ባል ወንዲራድን ክፉ ተናገሩኝ ብሎ ማስቀየም አይፈልግም ። አሁንም ከእሷ ጋር ውሎ መታየትን አልፈለገም ። ቀጠሮ አለብኝ ብሎ ዋሻት ። ልቡ ግን አልተቀበለውም ። ከራሱ ጋር ትልቅ ግብ ግብ ገጥሞ "ዋሽ" የሚለው ሐሳብ አየለበት ።

ዘነበች እንጀራ ፈርፍራ ሻይ አፍልታ የሐረገወይንን ቁርስ ይዛ በሩን ቀስ ብላ ከፈተችና ገባች ። ዛማኑኤል አልጋው ጠርዝ ላይ ተቀምጦ ስታየው አንድ ዐይነት ስሜት ሰውነቷን ወረረው ፤ የማፈር፣ የመደሰትና የመሳቀቅ ቅልቅል ስሜት ። የያዘችውን ከትንሿ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠችና ዞር አለች ። ሐረገወይን የቁምሳጥኑን መስተዋት እያየች ጸጉሯን ታበጥራለች ።

"እትዬ ቁርስ መጥቷል" አለች ድምጿን ከፍ አድርጋ ።

"በቃ አስቀምጪውና ሒጂ ··· ዘነብ"

ዘነበች ግራና ቀኝ ተመለከተችና ዛማኑኤልን ገልመጥ አደረገችው ።

"እዚሁ ላይ ልጨምርልህ ወይስ ለብቻህ ላምጣልህ ?"

በዐይንና በራሱ የሆነ ምልክት ሰጣትና ወጣች ወደ ማዕድ ቤቷ።

"ስማሽ ሐረ ለማንኛውም ትዕግሥት ያስፈልጋል ፤ አየሽ ፈረንጆች ፤ ትዕግሥት በሕይወት ውስጥ የማናቸውም ስናይ ነገር አዋላጅ ናት ይላሉ ። እና አደራሽን ··· ለማንኛውም ደህና ዋይ" አለ ዛማኑኤል ወደ በሩ እያመራ ።

ሐረገወይን ቁርሷን በልታ ወደ መሥሪያ ቤቷ ሔደች ። ለቅርብ አለቃዋ ችግር ያለባት መሆኑን ነግራ ፈቃድ እንዲሰጣት ጠየቀች ። አለቃዋ ፈቃዱን ለመስጠት ቢስማማም አጣዳፊ ሥራ ስለነበር ወዲያው ሊፈቅድላት አልቻለም ። ሐረገወይን እጅግ ተማረረች ፤ "ወደ መሥሪያ ቤትሽ ሒጂ" የሚለውን ምክር የለገሳትንም ዛማኑኤልን ረገመችው ። ሥራውን አልፈልግም ብላ ለመልቀቅ ካልፈለገች በቀር የግድ መቆየት ነበረባት ። እንደ ችኮላዋ

ሥራውን ቶሎ መጨረስ አልሆንላትም ። ሐሳቧ ብትንትን እያለባት ቶሎ ጨርሳ ወደ ቸኮለችበት ቦታ ለመሔድ አልቻለችም ።

ሥራዋን እንደ ምንም ብላ ጨረሰችና ወደ አለቃዋ ቢሮ ለመሔድ ስትጣደፍ የቢሮዋ ስልክ ጮኸ ። ወደ ስልኩ ሮጥ አለችና እጇን ከሰነዘረች በኋላ ፡ እንዳች ነገር ያስደነገጣት ይመስል የዘረጋችውን እጇን ሰብሰብ አደረገችው ። አለቃዋ ከሆነ ሥራውን ጨርሳ እየሔደች ነበር ። ስልኩን ባታነሣ አለቃዋ ሊቆጣት አይችልም ። እዚያው ቢሮው ውስጥ ያገኛታል ። ሌላ ከሆነ ግን ጥቂት ሰኮንዶችም ቢሆን ሊያደናቅፏት ነው ። ለዚሁ ነበር ስልኩን ለማንሣት የዘረጋችውን እጅ መልሳ ሰብሰብ ያደረገችው ። ስልኩ ይጮኻል ። ተወችውና ወደ አለቃዋ ቢሮ ሔደች ። የተሰጣትን ሥራ የጨረሰች መሆኑን አስረድታ ወደ ውጭ ስትወጣ ፡ ተላላኪው "ሐረገወይን ፡ ሐረገወይን ስልክ ፡ ስልክ" አላት ። ዓለማየሁን ፡ ምቶ አለቃ ስንታየሁን ፡ ዛማኑኤልን እያሰበች ሮጣ ስልኩን አነሣች።

"ሃሎ ! ሃሎ !"

"ሐረገወይን ነሽ"

"አዎን ማን ልበል"

"ትናንት እኮ ሰምቼ በእውነት በጣም ነው ያዘንኩት ..."

"ይቅርታ ማን ልበል ?"

"ይኸውልሽ ሐረገወይን ፡ እንቺ እኮ ዝም ብለሽ ነው ራስሽን የምታስቸግሪ ፡ በጌትነት መኖርን እንዴት ሰው ይጠላል ... እውነቱን ነው ። ማንም የማያገኘውን ዕድል ስትገፈትሪ ምን ይባላል ? ..."

"ይቅርታ ማን ልበል ..."

"አሁን እዚያው ቢሮሽ ነኝ አይደለም ፡ እስኪ መጥቼ በግንባር እንጫወታለን ። እመጣለሁ ጠብቂኝ ..."

“ማን ልበል ይቅርታ ፡ ማን ልበል አላወቅሁህም ?”

“እኔ ነኝ ፡ እኔ ወሰንየለህ ነኝ”

ስልኩን ጆሮው ላይ ዘጋችበት ። የባሰውን ብስጭትጭት አለች። ጸጉሯን ለመንጩት አሰበች ። እንጀቷ ውሃ እንደሚርከፈከፍበት የከሰል ፍም “ችስስ” ሲልና ሲጨስ ተሰማት ። ችላ የማትወጣው ፈተና የገጠማት መሰሎ ታያት።

ታክሲ ይዛ ወደ ሠንጋ ተራ አመራች ። ዓለማየሁ ቤት ስትደርስ ሠራተኛዋን ብቻ አገኘች ። መቶ አለቃ ስንታየሁን አገኛለሁ ብላ አስባ ነበር ። ሠራተኛዋ በጧት ምግብ አዘጋጅታ ልብስና ቁርስ ይዞ ወደ ሁለተኛ ጣቢያ እንደሔደ ነገረቻት ። ቤቱ ውስጥ ለመቆየት አልፈለገችም ። ወደ ጣቢያ ለመሔድ ሠራተኛዋን “ደኅና ዋይ” ሳትላት ወጣች ።

ሁለተኛ ጣቢያ ስትደርስ ያች ግቢ በሰዎች ተሞልታ አገኘቻት። ከየት እንደምትጀምር ግራ ገባት ። ወደ ወንጀል ምርመራ ክፍል ሔደች ። ሻለቃ ባሻ አላምረው በሰዎች ተከቦ አጉንብሶ ይጽፋል ። በሩ ላይ ጥቂት ቆመችና ተመለከተች ። የምታደርገው ስታጣ እስር ቤቶቹን ወደ ሚጠብቀው ፖሊስ አመራች ። ትናንት ዓለማየሁን የጠራላት ፖሊስ ባለመሆኑ ቅር ተሰኛች ። ጠጋ ብላ አነጋገረችው ።

“የለም ጧት ሰው መጥቶ አነጋግሮት ምግብ ሰጥቶ ሔዷል ። አሁን አይቻልም” አላት ። ለመነችው አልሆነላትም ። ከሰዓት በኋላ እንድትመለስ ነገራትና ትቷት ሔደ ። ለጥቂት ደቂቃዎች ተክዛ ቆየችና ወደ ሻለቃ ባሻ ቢሮ ተመለሰች ። የነበረው ሰው ጥቂት ቀነስ ብሏል ። አንዲት ጉስቁልቁል ያለች ሴት ከአላምረው ፊት ለፊት ቆማ ታለቅሳለች ።

“ምን ላድርግ ጌታዬ ፡ ለራሴ የሰው ጥገኛ ነኝ ። ከሰው ቤት ነው ተቀጥሬ እምሠራ ፡ ‘በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ’ ሆኖብኝ ነው ፡ ምን ላርግ ጌታዬ ፡ ቸግሮኝ ነው ፡ ግራ ቢገባኝ ነው ፡ ራሴን

ያልቻልኩ መጠጊያ የሌለኝ ሆኖ እንጂ ጨክኜስ አይደለም ፡ በጭራሽ … በጭራሽ ጨክኜስ አይደለም …” ትላለች እንባ እየተናነቃት ።

ሐረገወይን የሴትዮዋን ሁኔታ ስታይ አዘነችላት ። ከጐኗ ቆሞ አፉን ከፍቶ ነገሩን ይከታተል የነበረውን ሰው ትከሻውን ነካ አደረገችና “ጋሼ ምን ሆና ነው ?” አለችው በማዘንና በመቆርቆር አነጋገር ። ሰውየው መልስም አልሰጣት ። አፉን እንደ ከፈተ ፈዞ የሴትዮዋን ሁኔታ ይመለከታል ። ሐረገወይን ሰውየው እንዳልሰማት ዐወቀችና ዝም አለች ። ወደ ምታለቅሰው ሴት ተመለከተች ። “ምን ላድርግ ጌታዬ” እያለች ታለቅሳለች ። ከበሩ ላይ የተሰበሰበው ሁሉ ይረግማታል ፡ “የት አባቷ ይች ጨካኝ” ይላል ሰው ። ሐረገወይን ግራ ገባት ። ከተሰበሰቡት መኻል ለሴትዮዋ የምታዝን እሷ ብቻ መሆኗ ገረማት ። ወደ አንዲት ባልቴት ጠጋ አለች ።

“እማማ ምን ሆና ነው ?” አለች ድምጿን ከፍ አድርጋ ። እኒህም እንደ ሰውየው ሰምተው ዝም ይሉኝ ይሆን ? የሚል ሥጋት አድሮባት ። ሴትዮዋ ሐረገወይንን ትክ ብለው ተመለከቷትና ፡

“ልጇን ፡ የወለደችውን ልጇን ጥላ ነው የእኔ ቆንጆ” አሉ አፋቸውን ወደ እሷ እያሞጠሞጡ ።

“ውይ ምን ውስጥ ጥላው ጦንዝ ውስጥ ?” አለች ራሷን ይዛ ።

“እጅራት … ወንዝስ ውስጥ አልጣለችውም ። መቼስ የእናት አንጀት አይደለ ፡ እየሽ አልጨከነችም ልትገለው ፡ እንደ ዕድሉ ይደግ ትልና ለአንዷ ምስኪን አስታቅፋት ጠፋች ፡ ይኸው የልጁ አምላክ በማግሥቱ አሲያዛት ። አይ ቁልቢ ገብርኤል እንዳው እንደዬት ታረገኝ ይሆን ?” አሉ አንጋጠው ወደ ሰማይ ።

ሐረገወይን ገርሞአት ትኩር ብላ ትመለከታቸዋለች ። መልሰው አፋቸውን ወደ እሷ አሞጠሞጡና ፡

“የእኔ ቆንጆ ተዚህ መዓት ይጠብቅሽ ፡ አሜን በይ የእናት ምርቃን ጥሩ ነው ። ይኸውልሽ ይች ሴት የሰው ቤት ተቀጣሪ ናት ።

አላትሟ ስትዛለል ከረመችና ፡ እይው በገዛ እጇ ኀጢአት ውስጥ ገባች" አሉና ወደ ኋላቸው ዞር ብለው የተሰባሰቡትን ሰዎች ተመለከቱና "አያ ጐሽሜ አያ ጐሽሜ" ብለው ተጣሩ ።

ቀጭን ረዥም ጢማም ሰው ፡ "ፈለግሽኝ ? ፈለግሽኝ እንዴ ?" እያሉ ተጠጉ ። ባልቴቷ የጐሽሜን ትከሻ ጨብጥ አደረጉና ፡ "እየው ምናለች በለኝ ያች ትናንት ወስቢታል ተሸክመን የወሰድናት ሴትም ምናለች በለኝ ልጇን ጉድጓድ ውስጥ ባትከተው ! ድፍን አራት ኪሎ እስኪስቅብኝ ተሸክሜ ወሲቢታል አድርሼ ምናለች በለኝ ጉድጓድ ውስጥ ያልከተተችው እንደሁ …"

"በስማብ በይ … በስማብ በይ" እያሉ ሸሹ ሽማግሌው ።

ሰው ሁሉ ሔዶ የሻለቃ ባሻ አላምረው ቢሮ ጸጥታ ሲሰፍንበት ሐረገወይን ጐንበስ ብላ ሰላምታ ሰጠችና ገባች ። አላምረው እንዳያት ወዲያውኑ ዐወቃት ። ሰላምታ ካቀረበላት በኋላ የምትቀመጥበትን ወንበር በጣቱ አመለከታት ። ከፊት ለፊቱ ተቀመጠች ። የምትናገረው ጠፍቷት እንዴ ጣራውን ፡ እንዴ በር በሩን ፡ እንዴ አላምረውን በየተራ ተመለከተችና አቀርቅራ ዝም አለች ። አላምረው የተቸገረች መሆኑ ገብቶታል ። ብዙ እንድትጨነቅና እንድታስብ አልፈለገም ፡ መግቢያ ቀዳዳ ሊከፍትላት ፈለገ ።

"አባትሽ … ጊምቢ አውራጃ ገዢ ነበሩ አይደል ?" አላት ድምፁን ከፍና ዝቅ እያደረገ ።

"አዎ እዚያም ሠርቷል" ብላ መለሰች ቅር እያላት ።

"አባትሽ በጣም ኃይለኛ ሰው ናቸው ። እኔ በደንብ ነው የማውቃቸው ፡ ጊምቢ ነበርኩ ፡ ዐውቃቸዋለሁ ፡ በጣም ኃይለኛ ሰው ናቸው ።"

ሐረገወይን የምትመልሰው አልነበራትም ። ከፋት አላት ። የአላምረው ጨዋታ እሷ የምትፈልገውን እንድትተነፍስ በር ለመክፈት ነበር ። ግን ሳያውቀው አስከፋት ። የሚናገረው የሚያስከፋት መሆኑን ቢያውቅ ባቆመው ነበር ። ግን አያውቅም።

"ጢ.ትም መጥተው ነበር ፣ ብዙ ብዙ ብለው ነው የሔዱት እ … ሆ ;ኃይለኛ ሰው ናቸው … 'ለምን ተደፍሬ' ነው የሳቸው ነገር ። ከሁለት ሰዎች ጋር መጥተው ነበር ፣ 'ተደፍሬአለሁ ፣ እስከ መጨረሻው አልለቅም …"

"ታዲያ ለምን እኔንስ አያሳስረኝም ?" አቋረጠችውና ተነሣች። "እውጭ አደረች የተባልኩት እኔ ነኝ ። ታዲያ ለምን እኔን አያሳስረኝም ? እዎ ለምን አያሳስረኝም ። ምንም ያላደረገ ሰው እንዴት ታስራላችሁ ? ምን አደረገ ? ። እኔንም እሰሩኝ እሰሩኝ" ሻለቃ ባሻ ድንግጥ አለ ። ለጊዜው የሚናገረው ተምታታበት ።

"ረጋ በይ ፣ ረጋ በይ … ቁጭ በይ" አለ እሱም ተነሥቶ ።

"የለም እኔንም እሰረኝ ፣ እውነት ከሆነ እኔንም እሰረኝ ።"

"እንቺማ ምን አድርገሽ እናስርሻለን ፣ አይዞሽ አናስርሽም ።"

"ያስደፈርኩት እኔ ነኝ ፣ እኔን ነው የሚያውቀው ፣ የማያውቀውን ሰው ከማሳሰር እኔን አያሳስርም ።"

"የለም አናስርሽም … ብናስርሽም እኮ እሱ ጋር አትገናኙ ። የሴት ክፍል ለብቻው አለን …" አለ ፈገግ እያለ ። ፈገግታው ሐረገወይንን አላስደሰታትም ። እሷን ለማጽናናት ያለው ነበር ፣ ግን አስከፋት ። እሱም ወዲያው ገባው ።

"ስማኝ የእኔ እህት አንድ ምክር ልንገርሽ ። በእውነቱ በእኔ ብትቀየሚ ፣ በእኔ ብታዝኚ እኔ ላይ ብትጮሂ ዋጋ የለውም ። እኔም ችግር ሆኖብኝ እንጂ አንድ ሰዓት አላስረውም ነበር ። እውነቱን ልንገርሽ ከዐቅሜ በላይ ሆኖብኝ ነው ። ይህ ምስጢር ነው የምነግርሽ ልብ አድርጊ ። ዋናው ቁልፉ አባትሽ ዘንድ ያለ መሆኑን ማወቅ አለብሽ ። ጢ.ትም መጥተው ፎክረው ነው የሔዱት ። አንድ ነገር ልንገርሽ ፣ ትናንት መረጃዩን አመጣለሁ ብለው ነው የሔዱት አላመጡም ። ወደ ፍርድ ቤት በቶሎ ይመራልን እያሉ እየፎከሩ ነው የወጡት ። እኛ ምንም መረጃ ስለሌለን ወደ ፍርድ ቤት መምራት ያስቸግረናል ። ግን አሁንም ምስጢር ልንገርሽ ወደ ፍርድ ቤት ምራ

ተብዬ ታዝገርለሁ ። ምንም ማድረግ አልችልም ። የታዘዝኩትን እፈጽማለሁ ። ፍርድ ቤት ሔደው የሚያደርጉትን ደግሞ እኛ አናውቅም ። ሌላ ተአምር ሊፈጥሩ ይችላሉ ። እውነቱን ልንገርሽ ታቅሜ በላይ ባይሆንብኝ ትናንትናውኑ ነበር ወደ ቤቴ የምሸኘው ። እና ቁልፉ አባትሽ ጋ ነው ። ልጁን የምታዝኚለት ከሆነ ነገርኩሽ ። የጋባሽ መሰለኝ ። አባትሽን ተማፀኚ ነው የምልሽ” አለና ከመቀመጫው ተነሣ ። ሐረገወይን አንገቷን እንደ ደፋች ቆየችና አላምረው መናገር ማቆሙን ስታውቅ ቀና አለች ። ቆሞ ስታየው እሷም ከመቀመጫዋ ተነሣች ።

ትክዝ ብላ ቆየችና “እሽ አንድ ነገር አድርግልኝ” አለችው ምርር ባለ ድምፅ ።

“ምን ? ምን ?” አለ “ምን ልትጠይቀኝ ነው” የሚል ጉጉት እያጣደፈው ።

“አስጠራልኝና አነጋግሬው ልሒድ”

“እሻ ··· እሱ ቀላል ነው ··· ነይ” ብሎ ወደ በረንዳው ወጣ ። ተከተለችው ።

ከየአካባቢው ተሰባስቦ በአዲስ አበባ ሰማይ ላይ ተቆልሎ የነበረው ደመና የተነደፈ ጥጥ ይመስል የነበረው መልኩ ቀስ በቀስ እየጠቆረ ፡ እየጠቆረ ··· ጥቅርሻ መሰለና ነፋስና ውሽንፍር የቀላቀለ ዝናብ መውረድ ጀመረ ። በአካባቢው ይሰማ የነበረው ሁካታና ይታይ የነበረው ትርምስ ጸጥ አለና የሚሰማው የቆርቆሮ ጩኸት ብቻ ሆነ ። ጥቂት ቆየና ነፋሱ እየበረታ ሔደ ። በአካባቢው ያሉ ዛፎች ከወዲያ ወዲህ ይወዛወዛሉ ። ለጥ ይሉና ወደቁ ሲባል መልሰው ቀጥ ይላሉ ። እንደገና ወደ አንድ ወገን ያዘነብሉና ቅጠላቸውን አረጋግፈው እፎይ ይላሉ ።

ከትላልቆቹ ዛፎች ሥር ያሉት የሚያማምሩ አበቦቹ ከዛፎቹ ጋር አብረው ተጨንቀዋል ። ውሽንፍሩና ነፋሱ መግቢያ ሲያሳጣቸው ዛፎቹን የሙጥኝ ብለው አስጠጉን እያሉ የሚማፀኑ ይመስላል።

ረጃጅሞቹ ባለብዙ ቅርንጫፍ ዛፎች ሲሸበሩ እንሱም ይሸበራሉ ። ነፋሱ እየሎባቸው ዛፎቹ ተንገዳግዶ እንደሚወድቅ ሰነሩም አንገታቸውን ዝቅ ሲያደርጉ አበቦቹ ለውሽንፍሩና ለንፋሱ ይጋለጡና ራቁቱን ዝናብ ላይ እንደ ቆመ ሕፃን ልጅ ይንቀጠቀጣሉ ። ዛፎቹ ቀጥ ብለው ሲቆሙላቸው እፎይ ይላሉ ። አበቦቹ የጥቢንና የበጋን የጧት ፀሐይ አላስቀምስም ብለው በሚያስቸግሩአቸው ረጃጅም ዛፎች ቂም እንዳልያዙ ሁሉ ከክረምቱ ውሽንፍር ሲያድኗቸው ቂማቸውን ይረሱና ደስ ይላቸዋል ።

አስደንጋጭ ጉርምርምታና መብረቅ ተሰማና ለግማሽ ሰዓት ያህል እሩችግር የነበረው ዝናብ በረድ አለ ፡ ዝግ እያለም ጭራሽ አቆመ ። እንቁራሪቶች በዝናቡ መቆም የተደሰቱ ይመስል እየተቀባ በሉ ዕልልታቸውን አስነኩት ። ሐረገወይን የዝናቡን ፡ የዛፎቹንና የአበቦቹን ሁኔታ ስትመለከት ቆየችና የጆሮን ታንቡር ለመብሳት የሚቃጣው የቆርቆሮ ሁካታ አቁሞ ሰው መደማመጥ ሲችል ፡

“ለመሆኑ ፍርድ ቤት የሚቀርበው መቼ ነው ?” ጠየቀችው አላምረውን ።

“ነገ ያው እሑድ ስለሆነ አይሠሩም ፡ ሰኞ ካልሆነም ማክሰኞ ይቀርባል”

“በእኛ በኩል ምን ዝግጅት ማድረግ ይኖርብናል ፡ ማመልከቻ መጻፍ ያስፈልገን ይሆን ?”

“አይመስለኝም ፡ ካስፈለገም ፍርድ ቤቱ ለክሱ መልስ እንድትሰጡ ቀጠሮ ይሰጣችኋል ...” ብዙም መናገር አልፈለገም ። የእስር ቤቱን ጠባቂ ፖሊስ ጠራና ከዓለማየሁ ጋር እንዲያገናኛት አዞ ወደ ቢሮው ተመለሰ ።

ዓለማየሁ ገና “ሰው ይፈልግሃል” ተብሎ ሲነገረው ሐረገወይን መሆኗ ገባው ። የእስር ቤቱን በር ወጣ እንዳለ አሻግሮ ተመለከተና ፈገግ አለ ። ሣቅ የሚቃጣው ፈገግታ እያሳየ ተጠጋት ። ሐረገወይን የዓለማየሁ ፈገግታ ከደስታ የመነጨ አልመሰላትም ።

'ውስጡን እያረረ ላይ ላዩን ይሥቃል' እንደሚባለው ማሽላ መስሎ ታያት ። ፈገግታውን በፈገግታ ለመመለስ አልፈለገችም ። ዐይኗን ከዐይኑ ላይ ሳትነቅል ትኩር ብላ እየተመለከተችው እሷም ወደ እሱ ተጠጋች ። ከትናንቱ የበለጠ ከስቶ ፤ የበለጠ ጠቁሮ ታያት ። ዓለማየሁ ግን ለውጥ አልነበረውም ። ትናንት ለብሶት የነበረውን ልብስ ለውጦ ሌላ ጃኬትና ሱሪ ለብሶአል ። በላዩ ላይ ጋቢ ደርቦአል ።

የእጅ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ሁለቱም እንደ ተፋፈረ ሰው ለጥቂት ደቂቃ ዝም አሉ ።

"መሥሪያ ቤቴ ሔጄ እኮ ነው የዘገየሁት ··· ስንታየሁ ቁርስ እመጣልህ ?" ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ጠየቀችው ።

"እኔም ጠርጥሬአለሁ ፤ ከዛማኑኤል ጋር ወደ ቤትሽ መሔድሽን ስንታየሁ ነገረኝ ። እንደ ተናገርሽው ቤትሽ ሳትገቢ ቤተሰብ ታስቀይሚያለሽ ብዬ ሳስብ ነው ያደርኩት ። ግን እንዴት ነው ሰላም ነው አይደለም ?" ትከሻዋን ያዝ አደረገና ጉንጯን ደበስበስ አደረገው ።

"ምን ይሆናል ብለህ ነው ? ምንም አልሆንኩም" አለች ፤ የተናገረችው ከልቧ አልነበረም ። ስትናገር በምትናገረው ቃል የምትጠራጠር መሆኑ ይታወቅባታል ።

"እሱን ነው እኔም ያልኩሽ ። አየሽ ይህ በጣም ቀላል ነገር ነው፤ እኛ የማኅበራዊ ሕይወትን ውጣ ውረድ ገና ባለመቅመሳችን ትንሿ ነገር ሁሉ የማይወጡት ተራራ ትመስለናለች እንጂ ፤ በእውነት የእኔ መታሰር ብዙም ሊያስጨንቅሽ አይገባም ። ይልቁንስ የበለጠ ችግር እንዳይፈጠር መጠንቀቁ ነው ዋናው ነገር" አላት። እሷን ለማጽናናት የተናገረው እንጂ ሐሳቡን ሙሉ በሙሉ የሚያምንበት አልነበረም ። ግን ሐረገወይንን ማበረታታት አለበት ። መቆጣት ፤ መምከር አለበት ። እንኳን መታሰር ከዚህ የከፋ ችግር ቢደርስበትም ችግሩን እያቃለለ ምንም አይደለም ከማለት አይቆጠብም ።

"እንደው እኮ ተቻኩየ ዝም ብየ ነው የመጣሁት ፡ ተቻኩየ እኮ ነው ባዶ እጄን የመጣሁት እየ የእኔ ነገር" ትክዝ አለች ።

"ሐሪ የሚያስፈልጉኝን ነገሮች ሁሉ ስንታየሁ አምጥቶልኛል። ምንም እንዳታስቢ ፡ ይልቁንስ ስንታየሁ ምደባችንን የምንሰማው ዛሬ ነው ብሎኛል ፡ ምናልባት ከማይፈልገው ቦታ ከደረሰው መናደዱ ስለማይቀር ፡ እኔ ቤት ሔደሽ ጠብቂውና ከተናደደ አጽናኚው ፡ ደስ ካለውም የደስታው ተካፋይ ሁኚ ። እሽ ሐሪ ። ማታ መምጣት አያስፈልጋችሁም ። እንደውም ቤት የመጣውን ሁሉ አልበላሁትም ። የሌሎችም ሰዎች እንዲሁ ስለሚመጣ አንድ ላይ ነው የምንበላውና መቸገር አያስፈልግም ። አክስቴም ማታ እንዳትመጣ ስንታየሁ ነግሮኛል … በቃ ሒጂ ነገም እንዳትመጭ እውነቴን ነው እንጣላለን እንዳትመጭ ፡ በቃ ሒጂ ቻው …"

"ምን አስቸኮለህ" አቋረጠችው ።

"መቸኮል አይደለም ሐሪ … ምን ታደርጊያለሽ ብዬ ነው ። በቃ ሒጂ" አለ እጇን ለሰላምታ እየዘረጋላት ።

ዓለማየሁ ከሐረገወይን ጋር ቁጭ ብሎ ብዙ ለማውራት አስቦ ነበር ፡ ከእስር ቤቷ ክፍል ሲወጣ ። ግን አንድ ሐሳብ መጣና አስደነገጠው ። አባቷ መረጃዎቹን ነገ ይዤ እመጣለሁ ሲሉ ሰምቶ ስለነበር ፡ ድንገት ከመጡ ከእርሱ ጋር እንዲያዩዋት አልፈለገም ።

"ፖሊሱን አሁን አነጋግሬው ነበር ፡ ምናለኝ … ሰኞ ወይንም ማክሰኞ ፍርድ ቤት እናቀርበዋለን ብሎኛል ። እዚያ እንግዲህ የሚሉትን ደግሞ እንሰማለን" አለች ። ፖሊሱ ምስጢር ነው ብሎ የነገራትን ግን ለመንገር አልፈለገችም ። የፖሊሱን ምስጢር ለመጠበቅ አልነበረም ፡ ዓለማየሁን ብዙ ልታሳስበው አልፈለገችም።

"መቼ ነው እንዲህ ያለሽ ?"

"ቅድም እኮ ገብቼ አነጋገርኩት ፡ ሰኞ ወይም ማክሰኞ እናቀርበዋለን ብሎኛል ።"

"ኦኬ ሐረ ፡ ከቻልሽ ሰኞ ጧት ብቅ በይ ቻው" በማድ እጇን ጨብጦ ወደ እስር ቤቱ አመራ ። ሐረገወይን በዐይኗ ሸኘችውና በሩ ሲዘጋ ዞር ብላ መንገዷን ቀጠለች ።

ዓለማየሁ ገብቶ ከሲሳይ ጐን ቁጭ አለ ። "ቀረብህ እባክህ መንዜው በሣቅ ገደለን ። ከቀብራራው ጋር ተጣልተው በሣት ሊገለን ነበር" አለው ሲሳይ ።

"ስሙ ስሙ አንድ ታሪክ ላውራላችሁ፡ መቸስ አንድ ጊዜ የእናንተ መቀለጃ ሆኛለሁ" አለ መንዜው ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

"አንፈልግም ዝጋ ፡ ተፈለግህ መንዝ ውረድና ተረት አውራ" አለ ወፈፌው ከተዘረፈጠበት ተነሥቶ ።

"ዝም በል ፡ ዝም በል ያውራበት" አሉና ሎሁበት ሌሎቹ ።

"መንዜው ··· አውራ ተፈቅዶልሃል ?" የእስረኞቹ አለቃ በትዕዛዛዊ ድምፅ ተናገረ ። መንዜው ጉሮሮውን ጠራረገና ቀጠለ ።

"እየው ፡ እኔ መቸስ እብድና ሰካራም ዱሮም አይሆነኝ ። ምን ያረጋል ሕግ እኩል እዚህ አስቀመጠን እይ እንተማ አትቀልድብኝም ነበር ። ምን ታረግ እንተማ! ወንድ የዋለበት መች ውለህ ታቅና። አንቡላ እያንቃረርክ ሴት አባረህ ትቀማና እወንዶቹ ጋር እኩል ትታውራለህ ምን ታረግ ። እንዳርጌ ይሙት! የያዘ ይዞኝ እንጂ ፈስህን ነበር እማስረጭህ ።" ብድግ አለ ከመቀመጫው ።

"እስቲ ተወው ምናባቱ ሊሆን ፡ የእሳቱን ላንቃ አያውቀውም ልቀቀው አሳየዋለሁ።" ብድግ አለ ቀብራራው ንጉሤ ።

የእስረኞች አለቃ ሁለቱንም ተቆጣና አስቀመጣቸው ። መንዜው የጀመረውን እንዲጨርስ ተፈቀደለት ። መንዜው ደረት ሣቅ ሣቀና ቀጠለ ።

"ምነውሳ የልጅ ጨዋታ አደረጋችሁብኝ ? የአንድ ሰው ታሪክ እኮ ነው እምነግራችሁ ። መቸስ የእኔ አገር ሰው እንደ እናንተ በቅጥፈት ፡ በስርቆት አይያዝም ። ምንድነው እምትሉት ጆሬ

ምንድነው እምትሉት?" ወደ ጆሬ ዞረና ተመለከተ ። ጆሬ ሐሳብ ማጥ ውስጥ ገብቶ ጥርግ ብሏል ። "አዎ ሞጨለፈ ነው እምትሉት ፡ በጥፊ ይሞጭልፋችሁና ። የእኔ አገር ሰው ቢታሰርም የወንድነት ሥራ ሠርቶ ነው ። እልሁን ተወጥቶ አይባይቶ ነው ። አንጀቱን አርሶ ነው ። እንደው እኮ ይገርመኛል እኔ አሁን ፡ ሲቀመልእኩ ምስክሬ ነው ፡ ሁለት ጀምበር አድራለሁ ብየም አላሰብኩ ። የአባቱን ደመኛ ዐፈር ድቤ አግብቶ ነበር አሳቤ ፡ ተልጅነቴ ጀምሮ ። ኤዲያ ደመኛዬን ገድዬ ወዲያው ለመሞት ነበር አቆራረጤ ። ይኸው ነው ። ይኸን ያህል ጀምበር እያለሁ ብየ አላሰብኩም ። እቦ ነገሬን ሁሉ አስረሳችሁኝ ። በይህ በቀብራራው የተነማ አይል እንዴ ላውራላ ችሁ ያልኩት ··· አዎ ! አዎ !

"በነገር የተነማ ነው ። የእኛ አገር ሰው ነገረኛ አሽሙር አይወድም ብዬ ነው የጀመርኩት ። አገራችን አንድ ሰው ነበር ዘውዱ ይሉታል። ጅግና ነበር የጅግና ጅግና ። አዳ መልኩ እንደ እኔ ጉረድረድ ያለ ነው ። ምን ይሆንላችሁአል ፡ አንድ እንደዚህ ዘብናና እንደ ንጉሤ ያለ ሰው ተወዲህ ከእናንተ አገር ለሥራ ወደ እኛ ይመጣል ። ወንደላጤ ነው ፡ ትዳር አልመሠረተም ። እዲያ በየቦታው ይወስልት ኖሯል ። የዘውዱ ሚስት ልጅ እግር ናት··· እንደው እንደ ባሏ አይደለችም ። ቆንጆ ናት ። ባልና ሚስት ተያይዘው ገበያ ይውሉና ሲመለሱ ያ ባለጌ ትኩር ብሎ ይመለከታታል ፡ ዘውዱ ነገሩ አላምርህ ይለውና ባለጅንፎ ዱላውን መዞ ሰውዬው ላይ ያፈጥበታል ። ያ ባለጌ ሊመለስ ነው ። ዝም ብሎ ይመለከታታል ። 'ቆይ ቀንህን ጠብቅ' ብሎ እቤቱ ይገባል ዘውዱ ። አዲያ ሲወጣ ሲገባ ያየዋል ። እንደው ቁመናውን አላምሮ ይንጐባለላል ። እንደው··· ነገሩን ላሳጥርላችሁ እና አንድ ቀን ምን ይሆናል··· ሁለቱም ሠርግ ይጠሩና አንድ ቤት ይሔዳሉ ። ዘውዱ ተሚስቱ ጋር ሆኖ ጉን ለጉን ቁጭ ብለው ይበላል ፡ ይጠጣል ። ያ ባለጌ ባሻገር ቁጭ ብሎ እየጠጣ ይንጐማለላል ። ዘውዱ በጥርጣሬ ዝም ብሎ ይመለከተዋል ። መቼም አዞብት የለም ፡ ያ ሰውየ ዐይኑ አላርፍ ብሎ

የሰው ሚስት መመልከት ፤ ብርጭቆውን ባነሳ በጣለ ቁጥር እተ ባለጌ የሰው ሚስት መገልመጥ ። ዘውዱም ደሙ እየፈላ ያ ሰውዬውም ዐይኑ እየቀዠ ፤ አላርፍ ብሎ እየተንቀዠቀዠ ይቆያል ። በአገራችን ደንብ መሠረት ሠርግ ቤት አዝማሪ ቁጭ ይዘፈናል ፤ ይገጠማል ። ደስ ያለው ሁሉ እየተነሣ ወዳጁን ያመሰግናል ፤ ቂመኛውን በአሽሙር ይሳደባል ። ያ አዝማሪም ተገንዝቦ እያ እሱ ምንተዳው የነገሩትን እያሳመረ ይዘፍናል ። አዳላችሁ… ያ ባለጌ ሰውየ በእሱ ቤት አማርኛ ዐዋቂ መሆኑ ነው ይነሣና ለአዝማሪው ማጥም ይሰጣል ።

'ዐይኑ የሚመስለው የፈረጠ ገብስ ፤
ጥርሱ የሚመስለው የሞተ ፈረስ ፤
እታች ቤት ያደገ መሶብ ሲዳብስ ፤
ጣሉለት ተገብሱ እንድትጸድቅ ነፍስ
ለሱም አትገባ የያዛት በለስ' ይልና እየገለፈጠ ጠላውን ይጠጣላችሁአል ። ዘውዱ ብድግ ብሎ ወደ ቤቱ መሰስ ይልና የተወለወለ ምንሽሩን ይዞ ይመጣል ። ያን ባለጌ በግንባሩ ይከትበታል ፤ እየደጋገመ ፤ እየደጋገመ ይከትበታል ። ወለቅ አለ ተዘያማ ። ማንም አልያዘው ሁለት ዓመት ሆነው መሰል ። በቃ የውሀ ሽታ ሆኖ ቀረ ።”

መንዜው ወሬውን እንደ ጨረሰ በኩራት ስሜት ተጀንኖ ቁጭ አለ ። እንዲህ ያለ ወሬ ሲያወራ የሚፈራ መስሎ ስለሚታየው ይኮራል ፤ ሌሎቹን ያኮርፍና እንደ አንበሳ ተኮፍሶ ቁጭ ይላል ፤ ዐይኖቹን እያጉረጠረጠ ።

ሲሳይ የመንዜውን ወሬ አዳመጠና ወደ ዓለማየሁ ዞር አለ ። በእጁ ትከሻውን ነቅነቅ አደረገው ።

“ዐሌ ስማሽ አይደል… አየሽ ሰው መብቱን ሲደፍሩበት ምን እንደሚያደርግ በምንሽር …ሰማሽ አይደል በአደባባይ አድርጐት የሔደውን?…የመብት ጉዳይ ነው… ታዲያ አንቺ ፤ ሲሳይ በዐክስ

ተማታ ብለሽ ትጮኺያለሽ… ወንዶቹማ እንዲህ ያደርጋሉ" አለ ራሱን እያወዛወዘ።

ዓለማየሁ ፈገግ አለ ። መንዜው ያወራው ታሪክ ቢያስገርመውም ሲሳይን የእንትት ይሻላል ብሎ የሠራውን ሊያጸድቅለት አልፈለገም ።

"ስማ ሲሳይ" አለ ራሱን እያከከ "እየሀ የእንትትና የእሱ ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲያ ነው ።"

"የት የት ታራርቂዋለሽ ?" አቋረጠው ሲሳይ ።

"የለም እዳምጠኝ ። መቸስ የእንትትና የእሱ የተራራቀ ጉዳይ ነው፡ ሰውዬው የደረሰበት ሁኔታ ያበሽቀኛል ፤ ሚስቱን በማንም ይሁን ማን ሊቀማ አይገባም ፤ ለመብቱ መቆሙን እደግፋለሁ ። ግን ይቅርታ አድርግልኝ ቤቱ ሔዶ ምንሽር ይዞ መጥቶ ሰውን ያህል ፍጡር በዐይንህ ሚስቱን እየህብኝ… በአሽሙር ሰደብከኝ ብሎ መግደል ትክክል ነው አልልም ። እርግጥ አበሻ 'በሀገርና በሚስት የለም ዋዛ' ሲል በሁለቱ ለሚመጡበት ቅጣቱም የዋዛ እንደ ማይሆን ቢገባኝም ፤ አፌን ሞልቼ ደግ አደረገ የምልበት ጨካኝ እንጀት የለኝም ሲሳይ ። ያንተ ደሞ ከዚህ ፈጽሞ የተለየ ነው ። በትዕግስት ሊታለፍ ፤ በውይይት ሊፈታ የሚችል ነበር… አይደለም እንዴ ሲሳይ? መማር እኮ ፤ ማወቅ እኮ ሌላ ትርጉም የለውም…መማር ቡጢ ከመሰንዘር በፊት ለማሳመን የሚረዳ አይደለም እንዴ?"

"በቃ በቃ ተይኝ"… ሲሳይ በውይይቱ ለመግፋት አልፈለገም።

ሐረገወይን ዓለማየሁ ቤት ስትደርስ ስንታየሁ ከሁለት ጓደኞቹ ጋር ሆኖ ምሳ ሲበላ አገኘችው ። ከበሩ ላይ ተቀበለና እቅፍ አድርጎ ሳማት ። ነገሩ ባይገባትም እሷም እቅፍ አደረገችና ሳመችው ።

"አዲስ አበባ… አዲስ አበባ ደረሰኝ ፤ ደስ ብሎኛል ደስ ብሎኛል" አላት ፤ የደስታ ሲቃ በሚተናነቀው ድምፅ ሐረገወይን

ይኸ ነው ብላ ልትገልጸው የሚያዳግት የደስታ ስሜት ወረራት ። ትክ ብላ እየተመለከተች እቅፍ አድርጋ ዳግመኛ ሳመችው ። ከጣቢያ ጀምሮ ስንጋተራ ድረስ ስታስብበት የቆየችው ጉዳይ የሚያረካ ሆኖ አገኘችው ።የስንታየሁ ሁለት ጓደኞችም አዲስ አበባ የተመደቡ በመሆናቸው ቤቷ ፌንጠዝያ በዛባት ። ተበላ ተጠጣ ።

"ሐረዬ ከሰዓት በኋላ መሥሪያ ቤት እንድትመጡ ተብለናል ፣ እስከ ስንት ሰዓት እንደምንቆይ አላውቅም ። ዞሮ ዞሮ ወደ ማታም ቢሆን ፖሊሶቹን ለምኜ ዓለማየሁን መጠየቁ አይቀርም ፣ በጣም ነው የጓጓው ፣ የተመደብኩበትን ለማወቅ ። እንቺ እዚሁ ቆይና ሐጂ እኛ ወደ መሥሪያ ቤት መሔዳችን ነው" አለና ስንታየሁ ከመቀመጫው ተነሣ ፣ ጓደኞቹም አብረውት ተነሡ ።

"ምንም አታስብ ለዓለማየሁ እኔ ሐጂ እነግራለሁ ። አንተ ከጓደኞችህ ጋር ስትጫወት አምሽ ። ዛሬ ያንተ ደስታ ነው ፣ እኔ ሐጂ እነግረዋለሁ ፣ እንደውም በምደባው ቅር ካለው አፅናኚው ፣ ደስ ካለው የደስታው ተካፋይ ሁኚ ብሎ ነው የላከኝ ።"

ተሰነባበቱና ሦስቱ ጓደኞች ወጡ ። ሐረገወይን ዓለማየሁ አልጋ ላይ ጋደም ብላ ቆየችና አሥር ሰዓት ሲሆን ወጣች ፣ ለዓለማየሁ የወንድሙን የምሥራች ልትነግር ።

በእግሯ ጥቂት ተጓዘችና ንግድ ሥራ ትምህርት ቤት ፊት ለፊት ቆማ ታክሲ መጠበቅ ጀመረች ። ወደ ፒያሳ የሚወጡት ብዙዎች ታክሲዎች እየሞሉ ስለሚመጡ እንደ ችኮላዋ ቶሎ ማግኘት አቃታት ። በእግሯ ጉዞ ጀመረች ። ብሔራዊ ቴያትር ፊት ለፊት ቆማ ታክሲ መጠየቅ ጀመረች ። አንድ ቶዮታ ዴ ሉክስ ክላክስ እያሰማች መጣችና ከጐኗ ቆመች ።

"ሐረገወይን… ሐረገወይን የት እንቸገርልሽ?"

ድንግጥ አለች ሐረገወይን ። ከፊት ለፊት የተቀመጠው ሰው የመኪናዋን የኋላ በር ከፈተና "ግቢ" አላት ። የምታደርገው ጨነቃት ። መልኳ በቁጣ ሲለዋወጥ ያስማታል ፣ ግራና ቀኝ

ተገላመጠችና ፈንጠር ብላ ወደ ፊት መጓዝ ጀመረች ። መኪናዋ ተከተለቻት ።

"እንቺን ለመርዳት እኮ ነው ... ሐረገወይን ግቢ እንጂ !" የኋላውን በር ከፈተና ጋበዛት ። ገልመጥ ብላ ተመለከተችውና ወደ ኋላዋ ዞራ በፈጣን እርምጃ መራመድ ጀመረች ። መኪናዋ ወደ ኋላ መጥታ ልትደርስባት ስትል ታክሲ እስቁማ ገባች ። ያቆመላትን ታክሲ ነጂ ታላቅ ውለታ እንደዋለላት አድርጋ ቆጠረችው ። ታክሲዋ ውስጥ ሦስት ወጣት ሴቶች ተቀምጠዋል ፤ ሞቅ ያለ ጨዋታ ይዘዋል ። ከፊት የተቀመጠችዋ ወጣት ፊቷን እዞራ ከኋላ የተቀመጡትን ሁለት ጓደኞቿን ታጫውታለች ። ይሥቃሉ ። ከፊት የተቀመጠችዋ ወጣት የአምባር ቅርፅና መጠን ያለው ክብ ነገር ጆሮዎቿ ላይ አንጠልጥላለች ። ክቡ ነገር እየተወዛወዘ ግራና ቀኝ አንገቷን ይደበድባል ። ጸጉሯን ዳርና ዳሩን ሹርባ ተሠርታ መኻሉ ላይ የተጐነጐነ ጸጉር ተጠቅልሎ ትንሽ ኮረብታ መስሎ ጉብ ብሏል። በግራ ክንዷ ያነገተችው ቦርሳ መለስተኛ ሻንጣ ያህላል ። የለበሰችው እጅጌ የሌለው ጃኬት የአዲስ አበባን ክረምት የማያውቅ አዲስ መጥ የበረሀ ሰው አስመስሎአታል ። ጓደኞቿን ታስቃቸዋለች። ትለፈልፋለች ፤ እነሱ ይስቃሉ ። ሐረገወይን በታክሲዋ የኋላ መስተዋት አሻግራ ተመለከተች ። ያች ቶዮታ ተከትላቸዋለች ።

ሚልኪያስ መኪናዋን ያሽከረክራል ፤ ወሰንየለህ ከጐኑ ቁጭ ብሎ እጁን እያወናጨፈ ያወራል ። ሐረገ ወይን ለቋት የነበረው የፍራቻና የድንጋጤ ስሜት ወዲያውኑ ሰፈረባት ። ከታክሲዋ ወርዳ ምን ማድረግ እንዳለባት ማሰላሰል ጀመረች ። ገንዘብ ጨምራ ወደ አራት ኪሎ ለማለት ቆረጠችና መልሳ ተደላድላ ቁጭ አለች ። ቶዮታዋ ፍጥነቷን ጨመረችና ከታክሲዋ ፊት ለፊት መጥታ መንገዱን ዘጋች ። ታክሲዋ ሲጢጢጥ የሚል ድምፅ አሰምታ ቶዮታዋን አለፈችና ሔደች ። እንደገና ተቀድማ መንገድ ተዘጋባት ፤ ፈጠን ዝግ ፤ ቆም እያለች የምትሔደው ቶዮታ ሆን ብላ መንገዱን ልትዘጋበት ያሰበች መሆኑን የተረዳው ታክሲ ነጂ እየተበሳጨ ዝግ

ብሎ ይከተላል ። ያሳፈራቸው ሴቶች በመሆናቸውም እነሱን ፈላጊዎች ይሆናሉ የሚል ጥርጣሬም አድሮበታል ። "ታዲያ ሲወርዱለት ያሳድ እንጂ የእኔን መኪና ሊገጭ ይፈልጋል እንዴ?… ሺይት" አለ በልቡ ። ዐልፎ ለመሔድ ከኋላ የሚመጡ መኪናዎችን ሲቆጣጠር ድንገት ቶዮታዋ ቀጥ አለችና ቆመች ። ሊገጫት ትንሽ ሲቀረው ጡሩንባውን እጅግ አጮኸና እጥፍ ብሎ አለፋቸው ።

"ምን መሆኑ ነው ደደብ !" አለ ወደኋላ ዘወር ብሎ እየተመለከተ ።

"አንተ ዝም ብለህ ሒድ" አለች ከጐኑ የተቀመጠችው ወጣት፡ ቀጠለች "ሰው ሲዘገት እንዴት አያውቅም ፡ እናቴ ትሙት በጣም ነው የሚያበሽቀው ፡ ሲዘገት አያውቅም እንዴ! ግግም ሲሉ አያበሽቅም ? በቃ አንተ ዝም ብለኸው ሒድ! ቆይ ደሞ እሠራለታለሁ ፡ እናቴ ትሙት እሠራለታለሁ" ከቦርሳዋ መሐረብ አውጥታ ፊቷን መጠራረግ ጀመረች ።

"አስቴር ታውቂዋለሽ እንዴ?" ጠየቀቻት ከኋላ ከተቀመጡት ጓደኞቿ አንዷ ።

"ማወቅ ነው! አውቀዋለሁ ። እምልሽ ሲዘገት ግን እንዴት ሰው አያውቅም ። ደርሶ ግግም ይባላል እንዴ ! ይገርምሻል መውጪያ መግቢያ እኮ ነው ያሳጣኝ ፡ ዝም ብሎ ያሳድደኛል ፡ እናቴ ትሙት ቆይ ልኩን ነው የማሠራለት ።"

ሐረገወይን ትክ ብላ በመገረም ተመለከተቻት ። ድብልቅልቅ ያለ ሐሳብ መጥቶ አዕምሮዋን ረበሻት ። የደስታም ፡ የመብሸቅም ፡ የመናደድም ፡ የመገረምም፡ ምስቅልቅል ሐሳብ ተፈራረቀባት ።

"እጨምራለሁ ወደ አራት ኪሎ ትሔዳለህ" አለች ድንገት ።

ሐረገወይን ሁለተኛ ጣቢያ ስትደርስ ከታክሲዋ ወረደችና ዙሪያዋን ቃኘች ። የሚያስደነግጣት አንዳችም ነገር አላጋጠማትም። በፍራቻ ዙሪያዋን እየገላመጠች ወደ ጣቢያው ገባችና ፖሊሱን መለማመጥ ጀመረች ።

ለዓለማየሁ የደስ ደሱን አውርታ ስለ ሌሎች ነገሮችም ተጨዋውታ ስኞ እንደሚገናኙ ተነጋግረው ፡ ተሰናብታው ወጣች ። ከጣቢያው ጕን ካለችው የከተማ አውቶቡስ ማቆሚያ ጥቂት እንደ ቆየች ወዲያው አሥር ቁጥር አውቶቡስ መጣችና ተሳፈረች ። አውቶቡሷ በየጣቢያው የጫነችውን እያራገፈችና አዳዲስ ሰዎችም እየጨመረች ወደ ላምበረት ገሰገሰች ።

የካ ሚካኤል ካለው የአውቶቡስ ማቆሚያ ብዙ ሰው ወረደ ፡ ያንኑ ያህልም ተሳፈረ ። ወደ ሚካኤል ቤተክርስቲያን በምታስወጣው ቀጭን አስፋልት መንገድ ላይ ብዙ ሰው ተሰብስቧል ። ሁለት የፖሊስ መኪናዎችና አንድ የሬሳ መኪና ቆመዋል ። ከተሰበሰቡት ሰዎች መካከል ደረታቸውን እየደለቁ የሚያለቅሱም አሉ ። የመንደሩ ሰውና ወሬ ለማዳነት የሚሮጠው ተላላፊው መንገደኛ ሁሉ ተሰባስቦ መንገዱን አጣቧታል ። በአውቶቡሷ ውስጥ የነበሩት ሁሉ በመስኮት ዐይናቸውን ወርውረው ይመለከታሉ ። “ምንድን ነው? ምንድን ነው ?” የሚል ድምፅ ይሰማል ።

ሐረገወይን ከጕኗ ለቆሙትና ዕቃ ለተሸከሙት ሽማግሌ መቀመጫዋን ለቀቀችና እሷም በአውቶቡሱ መስኮት አሻግራ መመልከት ጀመረች ። የሰዎች ግርግር ይታያታል ። ነገሩን ለይታ በውል ልታውቀው ግን አልቻለችም ።

“ምን ሆነው ነው አባቴ?” ወንበር የለቀቀችላቸውን ሽማግሌ ጠየቀቻቸው ። አልመለሱላትም ። አውቶቡሷ መንቀሳቀስ ስትጀምር ሁሉም የየግሉን ጨዋታ ያዘና ጫጫታ በረከተባት ። ሽማግሌው የያዙትን ዕቃ አስተካከሉና ከጀርባ ቆመው የነበሩትን ሴት ጠርተው ወንበሩን አጋሩአቸው ። ሐረገወይን አሁንም ጕንበስ አለችና ፡

“አባባ… አባባ… ሚካኤል የተሰበሰበው ሰው ምን ሆኖ ነው ፡ የደረሰ አደጋ አለ እንዴ?” ጠየቀቻቸው ።

“እዬ ልጄ … አንድ ሰው ተሰቅሎ ነው”

“ውይ ራሱን ነው የሰቀለው ወይስ ሰው ሰቀለው?”

"ምን ይታወቃል ብለሽ ነው? ቦሊሶችም ነበሩ ያው መጣራቱ አይቀር ።"

"መቼ ነው የተሰቀለው?"

"ሰውማ 'ትናንት ነው የተሰቀለው' እያለ ነው የሚያወራ" አሉ ቀና ብለው እየተመለከቷት ። ክፉኛ ይመታ የነበረው የሐረገወይን ልብ "ትናንት" የሚለውን ቃል ስትሰማ በረድ አለ ። በመላ ሰውነቷ ችፍ ብሎ የነበረው የድንጋጤ ላብ የከረረ የጧት ፀሐይ እንደገጠመው ጤዛ ከላዩአ ላይ ተነሣ ። ግን ለተሰቀለው ሰው አንጀቷ ተንሰፈሰፈ ።

"የሚታወቅ ሰው ነው? የዚሁ ሰፈር ሰው ነው? " ጠየቀች መለሰችና ።

"ኧረ የለም ፡ አልመሰለኝም የዚህ ሰፈርስ ሰው አይደለም ፡ ዘመዶቹ ጠፍተው ገና አሁን ነው አሉ የተገኙት ። እንደሚባለውማ ሰውዬው እቤቱም አላደረ ። ዘመዶቹ ሲፈልጉ አድረው ሲያጡት በየቦሊሱ ጣቢያ ሲያመለክቱ ነው አሉ የዋሉት ። ያው መጨረሻው እንዲህ ሆኖ አገኙት ፡ ሚካኤል ጓሮ ተሰቅሎ አገኙት ።"

"ውይ ውይ ! አቤት ሚስቱን ያየ እርር ነው ያለችው" አሉ ከሽማግሌው ጐን የተቀመጡት ሴት ።

"ይገርማል እኮ! አንዱ ሰው ቅድም ሲያወራን ትናንት አራት ኪሎ ትክዝ ብሎ ብቻውን እያወራ ፡ እየተበሳጨ እመብርሃን በቃህ በይኝ እያለ እያዘነ አይቸዋለሁ···· ገርሞኝ ተከትዬ እመለከተው ነበር ብሎ አወራን" አለ ወሬያቸውን ሲከታተል የቆየ አንድ ተሳፋሪ ።

"እኔን አፈር ይብላኝ " አሉ ሴትዮዋ ደረታቸውን እየደለቁ ።

ሐረገወይን ከአውቶቡሷ ወረደችና ወደ ቤቷ የሚወስደውን ዳገታማ ቀጭን ኮረኮንች መንገድ ተያያዘችው ። ቤት ደርሳ የዋናውን አጥር በር ስታንኳኳ ወዲያውኑ አቶ ገበየሁ ከፈቱላት ። ሰላምታ ሰጠቻቸው ፡ አቀርቅረው የግልምጫ ተመለከቷት ።

ለሰላምታዋ ምላሽም አልሰጡአት ። እሷ ግን ሰላም ይበሏትም አይበሏትም ልብ አላለችም። ቀጥታ ወደ መኝታ ክፍሏ ሔደች ። ልብሷን ለውጣ ወደ ዛማኑኤል መኝታ ቤት ሔደች ።

በሩን ገፋ አድርጋ ስትገባ ዛማኑኤል አቀርቅሮ ተመስጦ ይጽፋል ። የሁልጊዜ ሥራው ነው ። ያነባል ፣ ይጽፋል ፣ ያነባል ይጽፋል ፣ ዐልፎ ዐልፎ ከጥንት ጓደኞቹ ቢሮ ይሔድና ገንዘብ ሲሰበስብ ይውላል ። ከሚያገኛት ገንዘብ ውስጥ በግማሹ መጽሐፍ ገዝቶ ይመለሳል ። አንዳንድ ጊዜ ጓደኞቹ የሰጡትን ገንዘብ በሙሉ መጽሐፍ ይገዛበትና ባዶ እጁን ይቀራል ። ጠባዩን በግልጽ የሚያውቁት ጥቂት ጓደኞቹ መጽሐፍ ይገዙለታል ፣ የኪስ ገንዘብ ይሰጡታል ፣ መጠጥ እየጋበዙም ያጫውቱታል ።

ዛማኑኤል ረታ የአቶ ወንዲራድ ባለቤት የወይዘሮ ተዋበች የእኅት ልጅ ነው ። አንድ እኅትና ሁለት ወንድሞች አሉት ። የአሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪ በነበረበት ወቅት እጅግ ይወዳቸው የነበሩት እናቱ በሕመም ሞቱበት ።

የአሥራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ዐልፎ ዩኒቨርሲቲ ለመግባት ከደብረብርሃን አዲስ አበባ ሲመጣ ያረፈው አክስቱ ቤት ነው ። ዩኒቨርስቲ ሁለት ዓመት ሲማር በየሳምንቱ ላምበረት እየሔደ አክስቱን ይጠይቃል ፣ ለተማሪ የምትሆን ጥቂት የኪስ ገንዘብ ተቀብሎ ይመለሳል ። አቶ ወንዲራድ ከጐፋ በየዓመት በዓሉ ወደ አዲስ አበባ በመጡ ቁጥር ለልጆቻቸው ልብስ ሲገዙ ለእርሱም አንድ ነገር ጣል ያደርጉለታል ። የሁለተኛ ዓመት የዩኒቨርስቲ ትምህርቱን ለማጠናቀቅ ጥቂት ወራት እንደቀሩት ሕመምተኛ ሆነ ። ከፍተኛ የራስ ሕመም ገጠመው ። ያልደረሰበት ሆስፒታል አልነበረም ። በመጨረሻ አማኑኤል ሆስፒታል ታክሞ ጥቂት ሻል አለው ። ሐኪሙ “ራስህን አታስጨንቅ ፣ ብዙ ማሰብ አይኖርብህም እንዳውም ሙሉ በሙሉ ከበሽታህ እስከምትድን ድረስ ትምህርትህን ብታቋርጥ መልካም ነው” ብሎ ቢመክረውም ዛማኑኤል የሚወደ

ውን የቋንቋ ትምህርት ለማቋረጥ አልፈቀደም ።

መልሶ ትምህርት ቤት ገባና የሁለተኛ ዓመት ትምህርቱን በጥሩ ውጤት አጠናቀቀ ። ግን በሽታው ጠናበት ። ሁለት ወር ክረምት አክስቱ ቤት ተቀምጦ አማኑኤል ሆስፒታል እየተመላለሰ ሲታከም ቆየ ። ተሻለው ። ዘመድ ወዳጅ ተሰባስቦ ትምህርቱን ለጥቂት ጊዜም ቢሆን እንዲያቋርጥ ተመከረና በአስተማሪነት ተቀጥሮ ደብረታቦር ሔደ ።

ለአክስቱ፡ ለሐረገወይንና ለወንዲራድ በየጊዜው ደብዳቤ ሲጽፍ ቆየና በሦስተኛው ዓመት ድምፁ ጠፋ ። አክስቱና ሐረገወይን እጅግ ተጨነቁ ፡ የሚጠይቁት ሰው አጡ ። ሐረገወይን ልክ እንደ እናቷ ልጅ የምትመለከተው መካሪ ወንድሟ ስለነበር ፡ የሞተባትን ያህል አለቀሰች ። ወይዘሮ ተዋበች የሚያደርጉት ሲጨንቃቸው ጉረቤቶች ትምህርት ሚኒስቴር ሔደው ይጠይቁ ይሏቸዋል ። ሔደው ጠየቁ ። ታስሯል ይባላሉ ። ደብረ ታቦር ድረስ ሔደው ጠየቁት ። ዛማኑኤል “ፖለቲካ ተናግሯል” በሚል ክስ ተፈርዶበት አንድ ዓመት ከአሥራ አራት ቀን ታስሮ ተፈታ ። በተፈታ ማግሥት ደብረታቦርን ለቆ ወደ አዲስ አበባ መጣና አክስቱ ቤት አንድ ዓመት ቁጭ አለ ።

“ሥራ ፈልገህ ግባ” ሲሉት አይሰማም ፡ “ትምህርት ሚኒስቴር ሒድና ሌላ ቦታ ቀይሩኝ በል” ሲሉት አይሰማም ። በየጓደኞቹ ቢሮ ውሎ ይመለስና መኝታ ክፍሉን ዘግቶ ያነባል ፡ ይጽፋል ። ቤታ ሥራው ይኸ ሆነ ። ደስ የሚለውን መጽሐፍ ሁሉ ሐረገወይንን በግድ ያስነብባታል ። ቀስ በቀስ እሷም ወደደችው ። ማንበብን ሕይወቷ አደረገችው ።

“ደኅና ዋልክ ዛሚ” አለችና አስደነገጠችው ። ዞር ብሎ ተመለከታት ፡ ቆየና የእሱን ወንበር ለእሷ ሰጥቶ እርሱ አልጋው ጠርዝ ላይ ቁጭ አለ ።

“ዛሬ ደስ ብሎሃል ፡ ያገኘኸው ነገር አለ?” አለችው ፈገግ ብላ።

"ምንም ፡ ምንም ሐረዬ… ያገኘሁት አንድም ነገር የለም ፡ ግ
ሐሬ እያንዳንዱ ቀን ለዐዋቂ ሰው አዲስ ናት ። ልትደሰችበ
ይገባል። ሲከፋሽም እምቢ ብለሽ ተደሰችበት ፡ ምን አባ
ትሆናለች ፡ ለዚህ ነው እንጂ ያገኘሁትስ ነገር የለም ሐረዬ !" አለ
እንደ መቀለድ እየቃጣው ።

"እሽ ምን አዲስ ነገር አለ? ያየኸው የሰማኸው?…" ማቶ
አለች ።

"ራሷ ቀኗ አዲስ መሆኗ ለእኔ ለውጥ ነው …አንድ በይ ። ትናንት ስለተባባልነው ጉዳይ አሲቃን እንድታነጋግር እነ?ባን ቤት አማክሬያት 'እሽ' ብላኛለች ። ሁለት በይ ፡ ቀጠሮ አለኝ አሳልፌ
ሽም ? የደብረብርሃን ልጆች አገኘሁና ከእነሱ ጋር በማውራት ውዬ ወደዚህ ስመጣ እቶ ገበየሁ ፎገሩኝ እልሻለሁ ሦስት በይ…"

"እንዴ ደሞ ምን ብለው ነው የሚፎግሩህ" አቋረጠችው ሐረገወይን ።

"እኔ እንጃ ሐረዬ ምናልባት ከጓደኞቼ ጋር ተጫውቼ ጠጥቼ በመምጣቴ ተናደው እንደሆን አላውቅም ። ያገርምሻል እኔ እልባ ባኝ ብለው እንጂ እሳቸውማ ብዙ ጊዜያቸው ነው ፡ የሚገርመው ሽማግሌ" አለ ወገቡን ይዞ ቀጥ ብሎ ቆመና ።

"ቆይ ቆይ ምናለህ ንገረኝ ?"

"በር እንዳኳሁ ፡ ከፈቱልኝ ። 'ምን ይኸን ያህል ተደበድባለህ' አሉኝ እየተቆጡ ። እኔ ደግሞ ሀገር ያጉና ብዬ ልቀልዳቸው ብሞክር ኧረ ተይኝ የማይባለውን ሁሉ አሉኝ ። 'ልክ ልኩን ነገሩኝ ነው' የሚባለው ። ውሻ ፡ ውሻ ናቸው ። ውሻ ጌታው ቤት እንግዳ ሲሔድ እንዴት እንደሚጮህ ታውቂያለሽ ? ልክ እንደዛ ። የጌታውን ዘመድ ፡ ጌታው በክብር ሲጋብዘው የጠራውን ዘመድ እንኳ ውሻ አላስገባም ብሎ እንደሚጮኸ…ልክ እንደዚያ ዓይነት ።"

"እኮ ምን አሉህ ንገረኝ… ንገረኝ እኮ ነው የምልህ ?"

"በቃ ስለእሳቸው ይብቃን ፡ ይኸን ያህልም ጊዜያችንን ከመሰዳብን ይበቃል ። ሐረዬ…እስኪ ውሎሽን አውሪኝ ይልቅስ"

ቁጭ አለ ። እጇን አገጩ ላይ አስደገፈና አፍጦ ይመለከታት ገባ ።

ሐረገወይን ከቤት ከወጣችበት ጊዜ አንሥቶ እስከምትመለስ ድረስ ያየችውን ያደረገችውን ሁሉ በዝርዝር አጫወተችው ። በጽሞና ሲያዳምጣት ቆየ ። ስንታየሁ አዲስ አበባ መመደቡን ስትነግረው ደስ አለው ። ስለ እነ ሚልኪያስ ያወራችው አስከፋው ። ግን ደስታውንም ፡ ቁጣውንም አልገለጸላትም ። ሲያዳምጣት እያፈራረቀ የቁጣና የደስታ ስሜት የሚያስነብበውን ፊቷን ሲመለከት ቆየና ከመቀመጫው ብድግ አለ ። ወደ ጠረጴዛው ሔደና ሲጽፍበት የነበረውን ወረቀት አነሣ ።

"ሐረዩ ሁለት ደቂቃ ፍቀጅልኝና ስጽፈው የነበረውን ላንብብ ልሽ ።"

ለጥቂት ጊዜ ግራ ተጋባችና "እሺ አንብብልኝ...ፈቅጄልሃለሁ" አለችው ።

"ሁለቱን ደቂቃ ብቻ ሳይሆን ጆሮሽንና ልብሽንም አብረሽ ፍቀጅልኝ"

"እንግዲህ አትቀልድ" አለችና ሣቅ አለች ። ወረቀቱን ይዞ አልጋው ጠርዝ ላይ ቁጭ አለ ። ማንበብ ጀመረ ።

"እንቆቅልህ ? ምን አውቅልህ ። ስትጣፍጥ የምትመር ፡ ግን ጣዕሟ ይህ ነው የማይባል ፡ ቀይ ናት ሲሏት ጥቁር ፡ ጥቁር ናት ሲሏት ነጭ ፡ ምንድን ናት ? እ…እስስትም አይደለች ፡ እትቀመስ ምንስ መልኳ ቢቀያየር ፡ አዎ ፡ አዎ ይች ነገር ሕይወት ናት ። አዎ ሕይወት። ከደስታ ፡ ከሐዘን ፡ ከብሶት ፡ ከርካታ ፡ ከሐዘን ፡ ከፈንጠዝያ ፡ ከማጣት ፡ ከማግኘት ፡ ከቅንጦት ፡ ከእጦት ከሌሎችም ቅመሞች ተከክታ ፡ ተቦክታ የተጋገረች ሥጋወደሙ ናት ። ግን ሲቀምሷት የቅመሞቹ ሁሉ ጣዕም አንድ ላይ አይሰማም ፡ አንድ ላይ አይታወቅም ። ሌሎቹ ቅመሞች ሁሉ ይደበቁና አንዱ ቅመም ብቻውን ጎልቶ ይሰማል ። የደስታው ወይ የሐዘኑ ፡ የቅንጦት ወይ የእጦቱ ፡ የፈንጠዝያ ወይ የሐዘኑ ። እና የሕይወትን ምንነት ለማወቅ ደግመው ደጋግመው ሲቀምሷት ይገባል ። የሕይወትን

ጣዕም ሊያውቁ የሚችሉት የተሠራችባቸውን ቅመሞች ሁሉ ሳይሰለቹ ለመቅመስና ለማጣጣም ፣ ሩጫዋን ሁሉ ሳይሰለቹ ለመሮጥ የተዘጋጁት ብቻ ናቸው ። ሕይወት ጉደኛ ነች ። ስትመርም ስትጣፍጥም ታረካለች ። ጉደኛ ነች ፣ ሁልጊዜ ስትጣፍጥ ደግሞ ትመራለች ። ተኛን ስንል የምንባንንባት ፣ ነቃን ስንል የምናሸልብባት የሌትና ቀን ሕልም ናት ። አጭር ናት ፣ ግን ግሳንግሷ ብዙ ነው ። በጥበብ በብልሃት ልትያዝ ይገባል ። ግድርድር ነች ፣ ቀናተኛ ነች ፣ ቂመኛ ነች ፣ ተፈታታኝ ነች ። በትዕግሥት ተቀበሉኝ ትላለች ። 'የጠለቀች ፀሐይ መልሳ ትወጣለች ፣ የረገፈች ጽጌሬዳ መልሳ ታብባለች ፣ እኔ ሕይወት ግን ቀናተኛ ነኝ ። አልጨልምም ፣ ከጨለምኩ ግን ዳግም ብርሃኔ አይታይም' ብላ ታስፈራራለች ። ግን ሞኝ ናት ፣ ሩኅሩኅ ናት ። በሯን ሲያንኳኩ ቶሎ አትከፍትም ፣ ታስጠብቃለች ። ታናድዳለች ። እልህ ታስጨርሳለች ። 'ደግማችሁ በር ምቱ በሩም ይከፈትላችሁአል' ትላለች ። አቤት ከከፈተች መስተንግዶዋ ! አቤት ርኅራኄዋ ! አቤት ጭንቀቷ ። አዎ የሕይወት ፊዚክሷ ይኸ ነው የሕይወት ጆግራፊ ፣ ታሪክ ሂሣቧ ይኸ ነው ። ሌላም ፈተና የላት ።

"ሰውም ቢሆን እንዲሁ ነው ፣ ባሕሪው የሕይወት ትክክለኛ ግልባጭ ነው ። ቶልስቶይ ይህን ደርሶበታል ። እንዲህም ሲል ተናግሮታል…'እጅግ ተጋንነው ከሚነገሩት አጉል እምነቶች አንዱ እያንዳንዱ ሰው የሚታወቅበት የራሱ ባሕርይ አለው የሚለው ነው። አንዱ ደግ ፣ አንዱ ክፉ ፣ አንዱ ዐዋቂ ፣ አንዱ ጅል ፣ አንዱ ትጉህ ሌላው ዳተኛ ። ሰዎችማ እንዲህ አይደሉም ። እርግጥ ነው አንዱ ሰው ከክፉ ይልቅ ብዙውን ጊዜ ደግ ፣ ከጅል ይልቅ ብዙውን ጊዜ ዐዋቂ፣ ከዳተኝነት ይልቅ ብዙውን ጊዜ ትጉሕ ወይም የዚሁ ተገላቢጦሽ ሊሆን ይችላል ። ግናግና አንዱን ሰው ደግና ዐዋቂ ሌላውን ጅልና መጥፎ ማለቱ አግባብ አይሆንም ። ሰዎች እንደ ወራጅ ወንዝ ናቸው። የወንዙ ውሃ እዚህም ፈሰሰ እዚያ ያው ነው ፣ ግን አንዱ ቦታ ጠበብ ፣ ሌላውጋ ሰፋ ፣ እዚህ ዝግ ፣ እዚያ ፈጠን ፣

እዚህ ኩልል እዚያ ደፍረስ ፡ እዚህ ቀዝቀዝ ከዚያ ሞቅ እንደሚል ሁሉ ሰዎችም እንደዚሁ ናቸው ። እያንዳንዱ ሰው እያንዳንዱን የሰው ልጅ ባሕርይ ጀርም እውስጡ አዝሏል ። ታዲያ ሰውየው ያው አንድ ሰው ሆኖ አንድ ወቅት አንድ ባሕሪው ሌላ ወቅት ሌላው ባሕርይ ጐልቶ እየወጣ ፡ ራሱን የማይመስል ሆኖ ይቀርባል ። እዎ ውነቱን ይሆናል...ቶልስቶይ ።

“ዓለምም እንዲሁ ናት ፡ ሲያዝኑ አብራ እምታዝን ፡ ሲደሰቱ አብራ እምትደሰት ። ዓለማችን የብዙ ምስቅልቅል ሁኔታዎች ቅርጫት ናት ። የሥልጣኔ ፡ የድህነት ፡ የክፋት ፡ የቅንነት ፡ የእምባገነንነት ፡ የጉልበት ፡ የርኅራኄ ፡ የዕውቀት ፡ የጥበብ ፡ የሞኝነት ፡ የጅላጅልነት ፡ የፍርሃት ፡ የጀግንነት ማጠራቀሚያ ቅርጫት ነች ። እና እኒህ ሁሉ አንድ ጊዜ እርስ በርስ እየተጋፉ ሌላ ጊዜ እርስበርስ እየተስማሙ ይኖሩባታል ። ሲፋቀሩ ጸጥ ትላለች ፡ ሲጋፉ ማዕበል ያናውጣታል ።

“እና የሕይወትን ምሥጢር ዕወቁ ፡ የሕይወትን ምንነት አጥኑ። እሷ ደሞ ትምህርት ቤት ግቡም አትል ። ራሷ ትምህርት ቤት ናት ። እየ ሕይወት ! ።

“ቅሪ ከቶውንም ቅሪ፡
መድረክ ላይ ወጥቶ እንደሚፈራ እንደሚርበተበት፡
ጥበቡ እንዳልዘለቀው፡
ለአፍታ ታይቶ ድርግም እንደሚል አጉል ተዋናይ፡
ብቅ ብለሽ ፡ ጥልቅ ለማለት ፡
ቅሪ ከቶውንም ቅሪ፡
ቧልት ነሽ ጅል ያወጋሽ ትርኪምርኪ፡

ቁምነገር የሌለብሽ ፍሬከርስኪ ብሎ ሸክስፒር የተሳለቀብሽ ፡ የዳር ድንበርሽን ስፋት ለይቶ የምንነትሽን ጥልቀት ተረድቶ ሊመራመርሽ ያልፈለገው ዑመር ከያም ፡

“ሕይወት ሒደት እንጂ ሎጂክ ማን አረገው ፡ ጭቅጭቁን ትተህ መለኪያህን አንሣው”

ብሎ ፊቱን ያዞረብሽ ለእኔ ደግሞ ጸዳሉ ነሽ ። ምድር እምብርት ላይ ተንጠልጥለሽ ለሁሉም ብርሃንሽን እምትሰጪ ጮራሽ ሁሉም ጋር የሚደርስ ጸዳሉ ነሽ ። አውላላ ሜዳ ላይ ቆመሽ ነፋስ የሚያወዛውዝሽ ፣ ጠፋች ሲሉሽ ቦግ ፣ ደመቀች ሲሉሽ ጭልጭል የምትይ ጸዳሉ ነሽ” ቀና ብሎ ሐረገወይንን ተመለከታት ።

“እንዴት ነው ? ሕይወት እንዲህ ሆና ነው የታየችኝ ወደድሽልኝ?” አለ ከመቀመጫው እየተነሣ ። ሐረገወይን አቀርቅራ ቆየችና ፈገግ እያለች ቀና አለች ። ምን ብላ እንደምትመልስለት ግራ ገባት ። ትከሻዋን ያዝ አደረገና ወደ ጆሮዋ ተጠጋ ።

“ኩ … ርር ወደድሽው ወይ ?” አላት ።

“ምዕራፍና ቁጥር ብትሰጠው ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ይወጣዋል ። ከዚህ ውጭ ወድጀዋለሁ” አለች ፊቷን ጭምድድ አድርጋ ።

“ግዴለም…ግዴለም ምዕራፍና ቁጥር ካስፈለገ ይሰጠዋል ። ግን ወደድሽው ?”

“ይገባኛል እኔን ለማፅናናት ስትታክት መቆየትህ ይገባኛል፣ ልክነኝ አይደል ?” ትክ ብላ ተመለከተችው ። እንደመሣቅ ቃጣውና ሣቁን እፍን አደረገ ።

“ግን አፅናንቶሻል ? እውነት አፅናንቶሻል?”

ሣቅ እያለች “አዎ አፅናንቶኛል” አለችው በልቧ እንዳይቀየመኝ የሚል ፍራቻ እያደረባት ። ዛማኑኤል በረዥሙ ተነፈሰና ተንጠራራ ። ሲተነፍስ የሆነ ሽታ አወዳት ። ዛማኑኤል ጠጅና ካቲካላ ይወዳል ።

“ይኸውልሽ አየሽ ከእውነት የበለጠ የሚያፅናና ነገር የለም እኮ ! ታላቁ እንግሊዛዊ ገጣሚ ጆን ኪትስ ‘ውበት እውነት ናት እውነትም ውበት ናት ። በምድር የምናውቀውም የምንፈልገውም ይኸንኑ ብቻ ነው’ ብሏል ። አየሽ ተፈጥሮ የለገሰችሽን ውበት ከእውነት ጋር ስትቀላቅይው ደስተኛ ትሆኛለሽ ። ሁልጊዜም እውነትን ካሰብሽ ደስተኛ ትሆኛለሽ ። አየሽ የዛሬው አዳርሽ የግዴታ ከትናንትናው የተሻለ መሆን አለበት ። ምንታደርጊያለሽ

መስለሽ ! አሁን ቀጥታ ወደ መኝታ ክፍልሽ ትሔጃለሽ ። መታጠቢያ ቤት ገብተሽ ገላሽን ትታጠቢያለሽ ፣ ራትሽን ትበያለሽ፡ ከዚያ አልጋሽ ላይ ጋደም ብለሽ የጀመርሻትን መጽሐፍ ጥቂት አንብበሽ ለጥ ትያለሽ ። የሚያስጨንቅ ሐሳብ ቢመጣብሽ እምቢ ብለሽ ተኚ ። 'አሻፈረኝ' በይው ። እይው ፣ እዚህ እዚህ ላይ የዴል ካርኔጂ ምክር ይጠቅማል ። ዴል ካርኔጂ ምን ይላል መሰለሽ? 'ችግር ደርሶብህ ስትጨነቅ ችግሩ ሊያደርስብህ የሚችለውን የመጨረሻውን ክፉ ነገር አስብና ቢደርስብኝስ ምን እሆናለሁ ብለህ አቃለህ እየው' ይላል ። እና አንቺም አቃለሽ እይው ። እሺ የእኔ እመቤት እንዳልኩሽ አድርጊ ፣ መልካም ዕንቅልፍ ።" ጠጋ አለና ግንባሯን ሳም አደረጋት ።

"ካልክስ እኔም አስቤበት የዕንቅልፍ ኪኒን ገዝቼ መጥቻለሁ"

"ኖ ፣ ኖ ልክ አይደለሽም ፣ እየሽ የቆሰለን አዕምሮ አደንዝዘሽ ናተኛ ብትይው እኮ በጄ ብሎ አይተኛልሽም ፣ አትሳሳች ፣ ሞኝ አትሁኝ ። ትርፉ የበለጠ ሕመምና ቁስል ነው ። በቅድሚያ ልታባብይው ይገባል ። አባብለሽ አባብለሽ ልክ እንደ ሕፃን ልጅ ብታስተኚው ዕንቅልፍሽ የጤና ዕንቅልፍ ይሆናል ። ስለዚህ የመከርኩሽን አድርጊና ተኚ ። መልካም ዕንቅልፍ" አሁንም ጠጋ አለና ግንባሯን ሳማት ።

ሐረገወይን ተሰናብታው ልትወጣ በሩን ስትከፍት ፣ ከእናቷ ጋር ግጥምጥም አሉ ።

"ውይ እማዬ ነሽ ? እንደምን ዋልሽ ?" አለቻቸው ። ክፉ ነገር የሠራች ያህል ድንግጥ ብላ ። ተያይዘው ወደ ዛማኑኤል መኝታ ክፍል ገቡ።

የሐረገወይን እናት ወይዘሮ ተዋበች ሲበዛ ዝምተኛ ሴት ናቸው ። በትንሽ በትልቁ ጭንቅ ይላቸዋል ። ለችግሮች መፍትሔ ከማሰብ ይልቅ ቁጭ ብሎ ማልቀስ ይቀናቸዋል ። በዛ ላይ በሽተኛ ናቸው ። ከልጅነት ጀምሮ አብሮአቸው ያደገ ሕመም አለባቸው ። ሐረገወይንን በጭንቅ ከወለዱ በኋላ ሐኪም በጥብቅ አስጠንቀቃቸው ። "በቃ ሁለተኛ እንዳይወልዱ ፣ ለሕይወትዎ ያሰጋዎታል"

አለና አሰጋቸው ። ሐረገወይን የመጀመሪያም የመጨረሻም ልጃቸው ናት ። ወይዘሮ ተዋበች ሰው የሚመክራቸውን አይሰሙም ፣ ያስባሉ ፣ ይጨነቃሉ ፣ ለሰው አይገልፁትም ። ውስጥ ውስጡን ይቃጠላሉ ። ቤታቸው እንግዳ መጥቶ በልቶ ጠጥቶ ከሔደ "ውይ ጉዴ እንደው እንዴት ይታዘበኝ ? ምንኛ ይወቅሰኝ...ባዶ ቤት አስገብቸ ሰለቀው ምንኛ ይወቅሰኝ..." ብለው ሦስትና አራት ቀን ይጨነቃሉ ።

አንድ ጊዜ ጐረቤታቸው የሆነ ሰው ሞቶና አምስት ቀን መደዳውን የእዝን ይዘው ሐዘኑ ቤት እየዋሉ አመሹ ። ባለቤታቸው ከሞቱባቸው ሴት ጐን ፍራሽ ላይ ቁጭ ብለው እኩል ሐዘንተኛ ሆነው ከረሙ ። በስድስተኛው ቀን ራሳቸውን አመማቸውና ቤታቸው ተኙ ። ወደማታ ላይ ሐረገወይን ከሥራ ስትመለስ መታመማቸውን ሰምታ ልትጠይቃቸው ወደ መኝታ ክፍላቸው ስትሔድ "ጉድ ጉድ...የጉድ ጉድ እንደው ምን ይባላል ?" እያሉ ብቻቸውን ሲያወሩ አገኘቻቸውና ድንግጥ ብላ ፣

"አባዬ አባዬ አመመሽ ? አመመሽ?" ድምጿ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ጠየቀቻቸው ።

"እየ ልጄ የራስ ሕመሜ እማ ምናለው እንደው ሐዘኑ ቤት የውሃ ሽታ ሆኜ ስቀር ምን ይሉኝ ብዬ ሰግቼ ነው ፣ ጉድ ነው እንዳው ጉድ ነው" ብለው መለሱላት ። ይሉኝታ አለቅጥ ያጠቃቸዋል ። ሐረገወይን ቅይም ብላ ተቆናጥራ ጥላቸው ወጣች ።

"ደኅና ዋልክ ? እንደምን ዋልክ" አሉ ቅዝቅዝ ባለ ድምፅ ። ዓማኑኤል ከመቀመጫው ተነሥቶ ተቀበላቸው ። ወንበሩን ለቀቀላቸውና አልጋው ጫፍ ላይ ቁጭ አለ ።

"እኔማ ጧት ያልከኝን ነገር ለአለቃ መንገሬን ልንገርህ ብዬ ነው ። 'ጥሩ ነው ፣ እንግራቸውና እሚሉትን እንስማለን' ብለውኛል። ይህንን ልንገርህ ብዬ ነው ።"

"ጥሩ ነው ቆይ...ሐሬ ይከሞእታል ። እፏ ሔዳ ዐረፍ ትበል ።

አንቺ እና እኔ ብናወራ ይሻላል ። አይመስልሽም ? ሐረዩ ሐጂ ሀረና በዩ ደጎና አደሬ" ሐረገወይንን እጇን ይዞ ከክፍሉ አስወጣትና ሸኝቷት ተመለሰ ። ለሐረገወይን ያነበበላትን ወረቀት እንግና አዟዙሮ ተመለከተው ። ቀዳደደና ጭብጥብጥ አድርጎ በመስኮቱ አውጥቶ ጣለው ።

ሐረገወይን መኝታ ክፍሏ እንደገባች ፡ ልብሷን አወላለቀችና የሌሊት ልብሷን አጠለቀች ። በላዩ ላይ ጋቢ ጨመረችበት ። በመስኮቱ ባሻገር ስትመለከት ወይዘሮ ድርቤና ዘነበች ይጨቃጨቃሉ ። ድርቤ እየተወራጩ ይናገራሉ ። ዘነበች በሁለት እጆቿ ወገቧን ጥፍር አድርጋ ይዛ እየተወዛወዘች ትለፈልፋለች ።

"አንቺ ዘነበች ፡ ዘነበች" ተጣራች ሐረገወይን ። ዘነበች ዞር ብላ ተመለከተቻትና ጭቅጭቋን ቀጠለች ። የሁለቱ ጭቅጭቅ እየከረረ ፡ እየከረረ ሔደና እጅ እስከመሰናዘር ደረሱ ።

"ወደል አጋሰስ...አንቺም ሰው ሆንሽና እኔን ልትሳደቢ ነው ? ክፉና ደግን ባየሁበት ቤት ስንት ዘመን በኖርኩበት ቤት...ባለቤቶቹ ያልተናገሩኝን አንቺ የማን ባላባት ነሽ እባክሽ ? ብጠጣ ባንቺ ገንዘብ የጠጣሁ መሰለሽ ? ታለኝ ጋኑንስ ብገለብጠው ምን ቁርጥ አረገሽ ፡ ወደል ወደላ" ድርቤ እየተሳደቡ ተጠጉት ።

"ልብ አርጉ ልብ አርጉ ኋላ ፡ በገዛ እጅሁ እንዳትዋረዱ ፡ እንዳትዋረዱ ብየዎታለሁ ። እኔ ዘነበች የማንም እምቡላ መትፊያ አይደለሁም ። ሔዱና ከቲካላሁን ተጋቱ ፡ እኔን ለቀቅ አድርጉኝ ።" ትወዛወዛለች ዘነበች ።

"እጠናብርሻለሁ ፡ ማንንም የምፈራ አይምሰልሽ ። ቂጥሽ ሲወፍር ጊዜ እኮ ፡ ሰው ናቅሽ ··· ወደል ወደላ ፡ ምን አገባሽ አልኩሽ እኮ! ብጠጣ ምን አገባሽ ! ገንዘብ አዋጪ አላልኩሽ ። ወይ ደግፊኝ አላልኩሽ ! ውርድ ከራሴ ! ሁለተኛ ብትናገሪኝ ደንደስሽን ብዬ ነው እምደፋሽ ! ልብ አርጊ ብየሻለሁ ። ደሞ ጠጣሽ ፡ ተፉሽ ? ብተፉስ ምን ቤት ነሽ አንቺ ? ክፍሉን እንደሁ አታድሪበት ።"

"ደጋ እንተያያለን ፡ እርስዎ ደንደሴን ሲሉኝ የእኔ እጅ በሶ

ጨብጦ እንደሁ እንተያያለን ።"

"በሶ አባሽ ይጥፋ ፡ እኔ ድርቤ እንኳን አንቺን ያን ጉረምሳንም ይዘሽ ነይ ። ጥሪው…አሁኑኑ ሒጅና ጥሪው ። እምፈራው እንዳይመስልሽ ። ምናባቱ ይቀርብኝ መሰለሽ? 'እትዬ ድርቤ ሆዱን አሞኛል ትንሽ ካቲካላ እንዳለሁ' እያለ አደል እሚለምነኝ ! ሒጅና ጥሪው ወደል…ወደላ ።"

"አንቺ አንቺ ዘነበች አንቺን እኮ ነው አትሰሚም እንዴ ?" ተቆጣች ሐረገወይን ። ሁለቱም ድንግጥ አሉና ጭቅጭቃቸውን አቆሙ ። ድርቤ እየተንገዳገዱ ወደ ማሰድ ቤታቸው ተጓዙ ። ዘነበች ነጠላዋን እያስተካከለች ወደ ሐረገወይን ሔደች ።

"ምንድን ነው የሚያጨቃጭቃችሁ ? ትንሽ ሰው አትፈሩም ። ትንሽ አታፍሩም"

"ምን ላርግ ብለሽ ነው እትዬ ። እንደው እኮ የአባታቸው ገዳይ አርገው ነው የቆጠሩኝ ። ባለፉ ባገደሙ ቁጥር ያሽሟጥጡኛል ፡ ካቲካላቸውን ይገለብጡና ቃልደበደብኩሽ ይሉኛል ። ምን ላርግ እትዬ ! ግራ ተጋባሁ እኮ ። ምነው ከዚህ ቤት እህል ውሃዬን የሚቆርጥልኝ ባገኘሁ?"

ዘነበች ነጠላውን ተሽፋፈነችና ማልቀስ ጀመረች ። ምርር ያላት ትመስላለች ። ሐረገወይን እቅፍ አደረገቻት። አንገቷን ቀና አደረገችና በነጠላዋ እንባዋን ጠራረገችላት ። ወደ እርሷ አልጋ እጇን ስባ ወሰደችና አስቀመጠቻት ። ተቆጣቻት ፡ መከረቻት ፡ አጽናናቻት ። ገራገሯ ዘነበች ወዲያው ምልስ አለች ። ነገሩ ሁሉ ያስቃት ጀመረ ።

"ሆቸ ጉድ ምነው እንደሳቸው ያለ ኃይለኛ ቢገጥምልኝ ፡ እንደው እሚያረጋቸውን ብታዩ እኮ ትስቂያለሽ ። ሙች ። እኔ ደሞ ለእሳቸው ክፉ አይደለሁ ። እንደ ገረድ ያዙኛል ። 'ራሴን አሞኛል ይኽን ይኽን ሥራ ይሉኛል ። 'በጀ' ብየ እሠራለሁ ፡ 'ልብሴን እጠቢ' ይሉኛል ፡ አጥባለሁ ፡ እትዬ ሙች እማያረጉኝ እኮ የለም ።

እኔ ደሞ ልክ እንደእናት እኮ ነው የማያቸው ፣ በይነጥላቸው እኔን ለምን እንዳስጠላቸው አላቅም ። የትልቅ ሰው ወራዳ ፣ በስማም መጠጣታቸው ሳያንስ ሰክረው ቡራ ከረዩ ማለታቸው አይገርምም.. .ወራዳ...አሁን እንግዲህ ያንንም...እንደውለታ መቁጠራቸው ነው!...ድንቄም።”

“አሁን ዝም በይ ብየሻለሁ ፣ ከእኔ ጋር ነው የምትጣይው አሁንስ ነግሬሻለሁ ዝም በይ...”

“እሽ ፣ እሽ ፣ እትዬ” ነጠላዋን አስተካክለችና ለበሰች ።

“ዘንዬ ፣ ሰማሽ ··· ምን ሥራ አለሽ አሁን ?”

“እሚሠራማ መች ይጠፋል ፣ ምነው ምን ፈለግሽ ?”

“ቡና እንድታፈይልኝ እፈልጋለሁ ። ቶሎ በይና ከሰል አቀጣጥለሽ ነይ ። እዚሁ ነው የምታፈይልኝ ። ቶሎ በይ እሺ” ከኋላዋ እየገፋች ወደ ውጭ አስወጣቻት ።

ሐረገወይን መኝታ ክፍሏ እንደገባች ራሷን በልታ የዕንቅልፍ ኪኒን ውጣ ለመተኛት ነበር ሐሳቧ ። እንዲህ ማድረጉን አልወደደችውም ፣ በዛማኑኤል ምክር መጽሐፍ ለማንበብም ፈለገችና መልሳ ተወችው ። ከዘነበች ጋር ጥቂት ተጫውታ አዕምሮዋን እንደ ሕፃን ልጅ እያባበለች ማስተኛቷን መረጠች ። ተመልሳ ወደ ዛማኑኤል መኝታ ክፍል ለመሔድና የእናቷንና የእሱን ምክር የመስማት ሐሳብም መጥቶባት ነበር ። ግን እሷ እንድትወጣ ማድረጉ የምክሩ ተሳታፊ እንዳትሆን ፈልጎ መሆኑ ተሰማትና ተወችው ።

ዘነበች ከሰል እያያዘ አመጣችና አስቀምጣ መልሳ ወጣች ። የጋመው ከሰል የሐረገወይንን ክፍል የበለጠ አደመቀው ። ቅዝቅዝ ብላ የነበረችው ክፍል ለብ እያለች ሔደችና ለአፍታ ሞቀች ። ሐረገወይን ወንበር አስጠግታ ቁጭ አለች ። ዘነበች ቅራቅንቦዋን ተሸክማ መጣችና ወለሉ ላይ ዝርፍጥ ብላ ቡናዋን መቁላት ጀመረች። ሐረገወይን ፡

“ተብየም አላውቅ ! እኚህ ሴትዮ ኋላ ሰበብ እንዳይሆኑብሽ ብትጠነቀቂ ይሻልሻል ?” አለች ። ቀልድ ለመጀመር አስባ ።

"ውነትሽን ። እትዬ ሙች ውነትሽን ነው ። ለራሳቸው በካቲካላ ያለቁ ሴት ኧረ ተይኝ እቴ ። የቢስን ጆሮ ይዞ ፣ ተዪ ሌላ ጨዋታ አምጪ ፣ ቡና ላይ እንዲህ አይወራም" ዘነበች ነገሩ እንገሸገሻት ።

"እሽ ታዲያ ስለምን ላውራልሽ ? ስለ እቶ ገበየሁ ላውራልሽ" ሐረገወይን አፏን በጋቢዋ አፍና መሳቅ ጀመረች ። ዘነበች ቀና ብላ ተመለከተቻትና ፈገግ እያለች ፣ "መቸስ መቀለጃ አግኝተሻል ፣ ገብቶኛል እኮ ልታጃጂዪኝ እንጂ ውነት ቡና አምሮሽ ነው አሁን..."

"ሙች ሙች በጣም ነው ያሰኘኝ ። ቡናው ብቻም ሳይሆን አንቺም ናፍቀሽኛል"

"ድንቄም ከመቼው ናፈቅሁሽ እቴ"

"አንቺ ሳትሆኝ ጨዋታሽ ይናፍቀኛል ማለቴ ነው ።"

"እንደሱ በያ...እንደሱ በያ ፣ አውቄዋለሁ አባክሽ ልታጃጅይኝ መሆኑ መቸ ጠፋኝ..." አለች "ጠፋኝ" የሚለውን ቃል እየጐተተች ።

"ኤጭ አንቺ ደሞ ዝም ብለሽ ነው እምትቆጪ ። አሁን እኔ አንቺን አጃጅላለሁ ? ሙች በእንትንት አሟውችኝ ብልሽ ማጃጃል ነው እንዴ"...ሐረገወይን ከልቧ ነበር ።

"እትዬ ሙች መቆጣቱ አይለም ሳቧልትሽ ነው"

"እሽ ተአገርሽ እንዴት እንደመጣሽ አዲስ አበባ እንዴት እንደመጣሽ እስቲ አውሪኝ ዘነብዬ ።"

"እይ እትዬ ውነት እየረሳሽው ነው ፣ ወይስ የእኔ ወሬ እየጣፈጠሽ ? ስንት ጊዜ ነው የነገርኩሽ ? ሙች አሟውቼሻለሁ እኮ ያውም ስንት ጊዜ"

"እሽ ደሴ የሥራሽባቸው ሴትዮ ቡና ቤት ማቢና ሥራ አላሉሽም"

"ወገኛ ናቸው...ወገኛ ። እሳቸውማ ስንቴን መሰለሽ የተባጠሩልኝ ። መቸስ እኮ ያላረጉኝ የለም ። እንዴ ሲጋራ ማኸ ይሉና

ይጠሩኛል ። አንዴ ብርጭቆ እጠቢ ይሉኛል ፤ አንዴ አምቦ ውሃ አምጪ ይሉኛል ። ሽራቸውን እኮ ነው ። እጠጪው መኻል እንድገባላቸው እኮ ነው ። ኧረ እንኳን ልገባ የገቡትም ያሳዝኑኛል..."

"ለምን ለምን ያሳዝኑሻል ዘንዬ ?"

"እኔ ንንጇ ዝም ብለው ያሳዝኑኛል ።ተኳኩለው ስታያቸው ጊዜ የደላቸው መስሎሻል ፤ በስማብ የስንቱን ግልምጫ የስንቱን እርግጫ ችለው ይኖሩታል ፤ አበስኩ ገበርኩ ።...እልቅስ ያልነገርኩሽ አንድ ነገር ላውጋሽ...እስተዛሬ የሚያስቀኝ ነገር አለ ። የመጃጃሌን ነገር ነው እምነግርሽ..."

"እሽ ንገሪኝ" አለችና ተደላድላ ተቀመጠች ሐረገወይን ።

"ይኸውልሽ...ተደሴ ስንነግ እትዬ...ያች እመቤታችን የነበሩት፣ ለዚያች አብራኝ ለመጣችው ጓደኛዬ ዘመድ አዲስ አበባ ይደውሉልሽና አሳፍረው ይልኩናል ። መጥተን መጥተን አቶቡሱ መቋሚያ ደረስንልሽና ወረድን ። እሷም እኔም አገሩን አናቀው ፤ አየ የቡልሃ ነገር ። ሁለት ቡልሆች ተገናኝተን መውጫውን አናቅ መግቢያውን ፤ ወደሰማይ ብናይ ወደ ምድር...ማን ቁብ ይበለን ። ሁሉም እየትካሩ ዘው ዘው ይላል ። አንዲት የሸራ ሻንጣ ነበረችኝ እሷን አዝዬ ቁሜልሻለሁ ። እሚያልፈው እሚያገድመው ሁሉ እየታከከኝ ሻንጣዬን ሲነካካ ጊዜ ልዘረፍ ነው እልልሽና አዙሬ እቅፍ አደረኳት። ደሞ መሬት ላይ አስቀመጥኩና ቁጭ አልኩባት ። ያች ጓደኛዬ ሰማይ ምድሩ ዞሮባት በዐይኗ ወዲያ ወዲህ እየዋተተች ያንን ዘመዷን ትፈልጋለች ። እንደው እናቴ በምን ቀን እረግመሽኝ ነው እዚህ ፈተና ውስጥ የዶልሽኝ ? እልኩና እለቀስኩኝ ።

"ታዲያልሽ አንድ ቀጠን ያለ ሰው መጥቶ 'አንቺ መሬማ መጥተሻል እንዴ' አለና ጓደኛዬ ላይ ጥምጥም አለባት ። ኧዲያ... ያንዬ አቅሉ መለስ አለልኝ ። ከዘመዷ ጋር አስተዋወቀችኝና ይዞን ወጣ ። እሱ ተፊት ተፊት እኛ ተኋላ ተኋላ እንሔዳለን ። እሁን ቤታው የቱ ነው ቢሉኝ አላውቀውም፣ እንደው በየጉራንጉሩ

እየመራ ወሰደን። እኛ ደሞ ሁሉንገር ዐይኑ አዋጅ ሆናብን እንድየ ሰውን ፡ እንድየ ፎቁን ፡ እንድየ መኪናውን እየተመለከትን እንከተለዋለን ።

“አስፋልቱን ጨርሰን ግሙ መንገድ ውስጥ ገባንልሽና ትንሽ ቆልቆል እንዳልን ፡ ግራና ቀኙን ስመለከት ስጡ ጨረቃ መስሎ አለ። ወደ ቀኝ ስመለከት ብቅል ፡ ወደ ግራ ስመለከት ጌሾ… እንሔዳለን ፡ እንሔዳለን ሊያልቅልሽ ነው ። እንደው ሜዳው ሁሉ ብቅልና ጌሾ ሆኗል ። ደሞ የጠባቂዎቹ አበዛዝ። ተዚህ እስተሾላ እሚደርሰው አገር ላይ እንጣለው አስጥተውታል ። ግርም' አለኝና ‘አጀብ አዱኛ ! መቸስ ራስ ደጃማች ታልሆኑ ይኸን ያህል ብቅልና ጌሾ አያሰጡም ። የታደለች ናት በዚህ ድግስ እምታገባ’ እያልኩ ሳደንቅ ቆየሁና ‘መሬም መሬም’ አልኳት ጓደኛዬን ‘ይኸን ጉድ አየሽልኝ ወይ አቦ’ ስላት እሷም ለካ እንደ እኔ ገርሞአት ኖሮ ‘አቦ ደግ አርገዋል ፡ ተደገሱ አይቀር እንዲህ አርጎ አገሩን ማብላት ነው’ አለችኝ ። ‘ኧረ እኔስ የገረመኝ ይህን ሁሉ ድግስ ምን ውስጥ ሊያበሉት ነው ፡ ምን ዓይነት ዳስ ሊጥሉ ነው እንቺዬ’ አልኳት ‘አይ እንቺ ደሞ ድግሱ ይሳካ እንጂ ዳሱ ይጠፋ ብለሽ? እንደፎጤ ሜዳ አለው አገር ላይ ያንጣልሉታል’ አለችኝ ። አይ መጃጃል ። አዲያልሽ ያ የጓደኛዬ ዘመድ ‘ቶሎ ቶሎ ኑ ! ምን እያላችሁ ነው’ አለና ቀረት አለ ። ‘አዬ እኛማ ይህን ሁሉ ብቅልና ጌሾ ስናይ ጊዜ እንዴት ያለ ሀብታም ሰው ቢሆኑ ነው ይህን ሁሉ ለድግስ እሚያዘጋጁ ብለን እየተገረምን ነው’ አልነው ። መቸስ ሰው እንደዚያ ሚሥቅ አይቼ አላውቅም ። አገር ጉድ እስቲለው ድረስ ሳቀብን ። ‘ለድግስ እኮ አይደለም ሊሸጥ ነው’ ሲለን ጊዜ ከው እንልልሽም…ይኸውልሽ እኔ መጃጃል የጀመርኩት ገና የአዲስ አበባን ምድር ስረግጥ ነው እልሻለሁ” አለች ስኒውን ለሐረገወይን እያቀበለች ።

ሐረገወይን ስትሥቅ ስለነበር ፡ ስኒውን ስትቀበላት እጇ እየተንቀጠቀጠ ቡናው እጇ ላይ ፈሰሰባት ። “አሁንስ እንቺም

ተጃጃልሽ" አለችና ዘነበች ስኒውን ነጠቀቻት ። ሁለቱም ብዙ ሳቁ ዘነበች ቡና ሞላችና ስኒውን መልሳ ሰጠቻት ።

"አይ ተብየም አላት ፣ ምነው እስተዛሬ ይችን ሳትነግሪኝ ደበቅሽኝ ሙች ታዝቤሻለሁ — " አለች ሐረገወይን ስትስቅ ዐይኗ ላይ ያቀረረውን እንባ በእጇ እየጠራረገች ።

"እህ እስተ ዛሬ ብነግርሽማ ዛሬ ምን እንጫወት ነበር እትዬ ፣ እስቲ አውሪኝ ስትይኝ ፣ አውርቼ ጨርሻለሁ ብልሽ ፣ ይህን ጊዜ ተፋጠን አልነበር እምንቀመጥ ...ጨዋታና ስንቅን እየቆጠቡ ነው ልጇ ።"

"ዘነብ አሁን መቸም ሰልጥንሻል ፣ በዚያ ላይ ቆንጆ ነሽ ፣ አሁን ደመወዝ ይውጣልኝና ቆንጆ ቆንጆ ልብሶች እገዛልሽና ቆንጅዬ ሜማ ታደርጊና ምን የመሰለ ባል ነው የምድርሽ... እሽ ።"

ዘነበች በሽርደዳ ዓይነት አመለካከት ሐረገወይንን አየቻት ። ከውስጧ ያልወጣ ሣቅ ሣቀች ።

"ምነው እባክሽ እኔ መምረጥ አቅቶኝ ነው እንዴ አንቺ ባል እምታመጭልኝ ፣ ታገሬ ያስወጣኝ ምን ሆነና ። እየው አራጋውን ሳላየው ሳላውቀው ዘመዶቼ ዳሩኝ ፣ አልስማማኝ ብሎ ኮበለልኩ ፣ አስገድደው መለሱኝ ። ያንኑ ሰውዬ ያለውዴታዬ መልሰው ዳሩኝ ፣ ኮበለልኩ ። ተዚያ ወዲህም ባል ተንጋጋ ፣ አሻፈረኝ አልኩ ። ተእንግዲህ እትዬ ሙች ለዚህ እንደ አሸን ለፈላ ወንድ ሰው ባል አይመርጥልኝም ። ዕድልሽ ይመር ታለ እምወደውን እሚወደኝን አገባለሁ ፣ ታልሆነ ጥንቅር ብሎ ይቅር ። ...እንዴ ታላገቡ አይኖርም ያለ ማነው?"

ሐረገወይን ማንሣት የሌለባትን ጉዳይ አንሥታ ሳታስበው በሐሳብ ማጥ ውስጥ ተነከረች ። ለስሙ ዘነበች ስትናገር ዓይን ዓይኗን ስትመለከታት ቆየችና ድንገት ከእራሷ ጋር ወግ ያዘች ። ከራሷ ጋር ክርክር ገጠመች ። ጭንቀቱን ያስረሳኛል ብላ የጀመረችው ጨዋታ እንደ መዘንጋት ብላው የነበረውን ሐሳብ ድንገት

ጫረባት ። ከራሷ ጋር ሙግት ገጠመች ፤ ድንገት ተወሽቆ የረበሻትን ጉዳይ ለመዘንጋትና ዛማኑኤል እንደ መከራት ጭንቀቷን ወጊድ ብላ ለመደሰት ሐሳቧን ገሸሽ አድርጋ ምንም እንደልሆነች ሰው ለመሆን ከራሷ ጋር ሙግት ገጠመች ።

“እትዬ እኛ አገር መቸም እስከ ቶና ድረስ ነው እሚጠጣ ፤ ብቻ ዕንቅልፍሽን ይከለክልሻል ፤ ይችን ጠጭና አከትመን ወደ የቤታችን እንግባ” ስኒውን ዘረጋችላት ። ሐረገወይን ከነበረችበት የሐሳብ ሰመመን ብንን ብላ ተቀበለቻት ። ለጥቂት ደቂቃዎች ነፍሷን ጸጥታ ዋጣት ።

“ግን እትዬ ባሉን ተይውና ለደመወዝ እገዛልሻለሁ ያልሽውን ቀሚስና ጫማ እንዳትረሺ መቸስ እንደዜ ታፍሽ ወጥቷል አትክጅኝ” አለች እያሳቀች ።

“እኔ ደሞ ቃል ገብቼ ክጀሽ አውቃለሁ ፤ እስከ ዛሬ አልገዛሁልሽም?” አፈጠጠችባት ።

“ውይ ውይ ስቧልት ነው ። እትዬ ሙች ስቧልት ነው ··· ኸረ ገዝተሽልኛል ።”

“ግን አንድ ነገር አንቺም ቃል ግቢልኝ ...ምን መሰለሽ ራስሽን አትጣይ ፤ እይው እስቲ አሁን ጸጉርሽ ታጥቦ ተበጥሮ ያውቃል? እውነቱን ተናገሪ ።”

“እሱስ ውነትሽን ነው ፤ እዬ እትዬ ፤ እየየም ሲዳላ ነው አሉ ፤ መቼ ላበጥረው ብለሽ ...ተይው እባክሽ እኔ ሲያልፍልኝ እሱም ያልፍለታል ። ተበጥሮ ብቻውን ቢያምርበት ምን ያረጋል ብለሽ? ግንጥል ጌጥ አያደምቅ አይደል እሚባለው ። ቢበጠርማ እንደሚያምርበት አውቃለሁ እትዬ ። አገሬ ተነበርኩ ...እንግዲህ ድግስ ሲኖር አዝማሪ ቆሞ ይዘፈን የለም?... አብሮ አደጌ አገባችልሽና ሽርጉድ እላለሁ ። ያን አራጋውን ፈትቼ ወንዱ ሁሉ ያስቸግረኝ ነበር ። ኢዲያልሽ ያም አዝማሪ ለካስ ዐይኑን ጣል አርጐብኛል መሰል ፤ እየዞረ ሲዘፍን ሲሸልም ቆየና ወደ እኔ ጠጋ ብሎ ይዘፍን ገባ ።

‘ዘንዬ ዘነበች ዘንዬ ዘውድ ዓለም
ጠጉርሽን በመቶ ገምቼልሻለሁ ፡
ዓይንሽን በመቶ ገምቼልሻለሁ ፡
ጥርስሽን በመቶ ገምቼልሻለሁ ፡
አንገትሽን በመቶ ገምቼልሻለሁ ፡
ጡትሽን በመቶ ገምቼልሻለሁ ፡
ግማሽ አከላትሽን አልገመትኩልሽም
ሰው ያላየው ገላ እምብዛ አያስዋሽም’ ሲል ጊዜ ፡ ያ ሁሉ ሰው እንዴ እያወካም መሰለሽ ። እፍር አልኩና አንገቴን ድፍት አደረግሁ። ሰው እየሣቀ ሲያስቸግረኝ ጊዜ ውልቅ አልኩና ጠፋሁ ። ምን ያረጋል እንዲህ ተብሎ ተዘፍኖልን ነበር ።” አንገቷን ሰበቀችና እስክስታ እንደሚወርድ ሰው ሰውነቷን አርገፈገፈችው ። ከውስጥ የፈነቀላት የኩራት ስሜት ፊቷን አደመቀው ።

ሐረገወይን ሣቀች ሣቀችና ስትጨርስ ድገሚ ብላ ግጥሙን አስደገመቻት ። ስትደግምላትም ከበፊቱ የበለጠ ሣቀች ።

“ዘንዬ ይኸንን ለዛማኑኤል ንገሪው ፡ አንድ ነገር ይጽፍበታል እንድትነግሪው” አለቻት በትዕዛዛዊ አንጋገር ።

“እይ ያውቀዋል ፡ ነግሬዋለሁ ጽፎታል ።”

ዘነበች የተናገረችው ቃል መልሶ ራሷን አስደነገጣት ። እፍር አለችና ቀና ብላ ሐረገወይንን አየቻት ። ደም እንደ መሸኮርመም አደረጋትና ከተቀመጠችበት ተነሣች ። ፊቷ በላብ የተጠመቀ መስሎ ተሰማት ። ጕንበስ አለችና ዕቃዎቿን መሰብሰብ ያዘች ።

“ውይ እትዬ ውድቅት ሌሊት ሆን እኮ ፡ በይ ልሒድ ተኚ እንቺም” ወደበሩ አመራች ።

“ቆይ ገና ነው ፡ ቆይ ገና ነው እባክሽ” ተከተለቻት ሐረገወይን። ዘነበች አልተመለሰችም ። ወጥታ ጠፋች ።

ሐረገወይን በሯን ቆለፈችና አልጋዋ ውስጥ ገብታ ጥቅልል

አለች ፡ ዛማኑኤል የመከራትን ሁሉ ለማድረግ ሞከረች ። እንዳለፈው ሌሊት አልሆነባትም ፡ ቶሎ ሰንቅልፍ ወሰዳት ።

ሁለት ሰዓት ያህል ከተኛች በኋላ ፡ የመባንን ያህል ብርግግ ብላ ተነሣች ። አንድ የረሳችው ነገር ትዝ አላት ። የመኝታ ክፍሏን በር ከፍታ ውጭ ወጣችና ወደ ዛማኑኤል መኝታ ክፍል ሔደች ። የመኝታ ቤቱ መብራት ጠፍቶ ጨልሟል ፡ ቀስ ብላ በሩን አንኳኳች፡ መልስ አላገኘችም ። ደገመችና አንኳኳች ፡ ኃይሏን ጨመር አድርጋ።

“ማነው ማነው” የሚል ድምጽ ከውስጥ ተሰማ ።

“እኔ ነኝ...ሐረገወይን ነኝ ፡ ከፈትልኝ”

ዛማኔኤል ደንግጦ ተነሥቶ በሩን ገርበብ አድርጐ ከፈተና መኻል ላይ ቆሞ “ምን ሆንሽ?” ምን ሆንሽ?” አለ ድንጋጤ በተመላበት ቁርጥ ቁርጥ ባለ ድምፅ ። ሐረገወይን ወደ ውስጥ ለመግባት ስትሞክር ፡ በሩን ዘጋና አላሳልፍ አላት ።

“አስገባኝና መብራቱን አብራው ፡ ሳልነግርህ የረሳሁት አለ”

“እዚሁ ንገሪኝ ምናለ ፡ እዚሁ ንገሪኝ”

“ምን እውጭ አስቆመን በሌሊት...አስገባኝ” ወደ ውስጥ ልትገፋው ሞከረች ። አልሆነላትም ።

በሩን ጥብቅ አድርጐ ያዘና እንደ ግድግዳ ቆመባት ፡ ቀስ ብሎ በሩን ሲዘጋው ሁለቱም ከውጭ ቀሩ ። እጇን ይዞ ከመኝታ ክፍሉ አርቆ ወሰዳት ።

“አየሽ የሚያነብና የሚጽፍ ሰው በሚተኛበት ክፍል ውስጥ በሌሊት መግባት አደገኛ ነው ። በጣም አደገኛ ነው ። ምን መሰለሽ ጻፍ ፡ በርታ አይዞህ የምትል የሥነ ጽሑፍ ውቃቢ የምትባል አለች ፡ ልክ እንዳንቺ ቆንጆ የሆነች ። የደራሲያን ጋሻና መከታ ናት ። አይዞህ ባያቸው አጽናኛቸው ፡ ጉልበትና ብርታት የምትሰጣቸው ፡ ብዕራቸው ራስ ላይ ቁጭ ብላ በርታ የምትላቸው ናት ። ደሞ ለምን ትናንት ሳታነብ አደርክ? ለምን ትናንት ሳትጽፍ አደርክ? ብለው

የሚያስፈራሩ ፣ የሚያባያቡ ፣ የሥነጽሑፍ ዱካኮች የሚባሉ አሉ ። እንደ ሰው እጅ እግር ራስ ሆድ ያላቸው ጉንዳን የሚያካክሉ ነገሮች ናቸው ። በትልቅ የጭነት መኪና ይሳፈሩና ይመጡብሻል ። ሌሎቹ ቆመጣቸውን ይዘው ዙሪያሽን ሲከቡሽ የዱካኮቹ አለቃ በራስጌሽ በኩል ይወጣና አንድ እግሩን ከትራስሽ ላይ አንድ እግሩን ራስሽ ላይ አድርጎ ዝንጥ ይልና ይቆማል ። አቤት እግሩ አከባበዱ ፣ የብረት አጥር የተሣኪንሽ ነው የሚመስልሽ ። 'አንተ ለምን አባክ ነው ትናንት ያልጻፍከው ። ለምን አባክ ነው ትናንት ሳታነብ የተኛሽ ው?' ይልና ይጮህብሻል ፣ አንቺ የዚህ ጊዜ ያለብሽ መለማመጥ ብቻ ነው ። ክፉ ክፉ ነገር እናገራለሁ ብትይ ዙሪያውን የከበቡትን ዱካኮች 'በሏት' ይልና ትጥቅጥ አድርገው ነው የሚገድሉሽ ። ታዲያ ምን ጥሩ ነገር አለ መሰለሽ ፣ የሥነ ጽሑፍ ውቃቢ የእነሱ መኪና አቧራውን እያቦነነ ፣ ወንዙን እንደ አሞራ ክንፍ አውጥቶ እየተሻገረ ሲመጣ ትመለከትና እሷ ቀድማ ቤትሽ ውስጥ ገብታ ትጠብቃቸዋለች ። 'እንዳትነኩት ወዮ እንዳትነኩት' እያለች ትከለክልልሻለች ። ታዲያ አሁን እኔ ክፍል ሁለቱ ተፋጠው ቆመዋል ፣ እየሽ ላንቺው ብዬ ነው ያላስገባሁሽ ።"

"እባክህ ዱካክ የምትለውን ወደዚያ በልና ቁም ነገሩን ላውራህ"

"እሺ እኮ ንገረኝ ምንድን ነው ንገረኝ?"

"ይኸውልህ ድንገት ነው ትዝ ያለኝ ። በሌሊት ተነሥተህ ከወጣህ ነገሩ እንዳይበላሽ ብዬ ነው አሁን የመጣሁት ። እንደ ነገርኩህ ሰኞ ወይ ማክሰኞ ፍርድ ቤት ይቀርባል ብለውኛል ፖሊሱ ። ፍርድ ቤት ደሞ አንድ ነገር እንዳይጉነጉንበት ከወዲሁ አንድ ነገር ብናደርግ ብዬ ነው ። ፖሊሱ እኮ በግልፅ ነው የነገረኝ ። ከአቅሚ በላይ ነው ብለውኛል ። አሁን ደሞ ተሯሩጠው በጭቦ ያስፈርዱበታል ብዬ ሰግቻለሁ ። እየው ዓለማየሁ ቤት ሆኜ ለአጐቴ ኃይለማርያም ደውየለት እፈልግሀለሁ ጉዳይ አለኝ ብየው ሰሞኑን ዕረፍት ስለሆንኩ ፣ በማናቸውም ሰዓት እቤት ብትመጪ ታገኝኛለሽ

ብሎኛል ። ግን አሁን ሳስበው ከእኔ አንተ ትሻላለህ ፡ ሁሉንም ነገር አስረዳው ፡ እኔ አለቃ እምትሏቸውን ሰው ብዙም አላምናቸውም ። እንግዲህ አደራህን ነገ ጧት ሔደህ ይህንኑ ንገረው በቃ ይህንኑ ልነግርህ ነው ፡ በረደኝ ልግባ" አለች ጋቢዋን እያስተካከለች። ዛማኑኤል ለጥቂት ጊዜ ዝም ብሎ ቆየ ። ሐሳቡን አወጣ አወረደና ተነፈሰ ።

"በጣም ጥሩ ሐሳብ ነው ሐጂ እነግራቸዋለሁ ፡ መቼስ ሰው አያደርጉኝም ። ጠይቂአቸው አላውቅም ፡ ስንት ጊዜ ሆነኝ መሰለሽ! ቢሆንም ላንቺ ስል የፈለጉትን ይበሉኝ እሔዳለሁ ። ግን ሐሬ ነገ አይመቸኝም ። ዛሬ ያገኘሁአቸው ጓደኞቼ ጋር ጧት ተቀጣጥረናል እርግጠኛ ነን አብረን እናምሽ ሳይሉኝ አይቀሩም ። እና ሰኞ በጧት... በጧት እሔዳለሁ እሺ" ትከሻዋን ያዝ አደረገና ወዘወዛት።

"ምን ማለትህ ነው ሰኞ ቢያቀርቡትስ ፡ ነገሩ ተበላሸ አይደለም እንዴ !"

"ነገና ሰኞ ምንም ለውጥ አያመጣም ፡ አታስቢ አይዞሽ ሰኞ በጧት ··· በጧት እሔዳለሁ ··· ቻው ደኅና እደሪ" ወገቧን ደገፍ አድርጐ ከዋናው ቤት የኋላ በር ድረስ ሸኛትና ተመለሰ ።

ሐረገወይን ገብታ ጥቅልል ብላ ተኛች ። ዕንቅልፍ ቶሎ አልወሰዳትም ። ለሚያስብ ሰው አንድ ሰዓትም በዋዛ አትገፋም ። እንደዘበት እምታልፈው ደቂቃ ዳገት መስላ ትታያለች ። የእሷንና የዓለማየሁን የአምስት ዓመት የታሪክ ማኅደር ማገላበጥ ጀመረች ።

ዓለማየሁና ሐረገወይን መጀመሪያ የተያዩት እሱ የሦስተኛ ዓመት የዩኒቨርስቲ ተማሪ እሷ የአሥረኛ ክፍል ተማሪ ሆነው ነው ፡ ትምህርት ቤት እንደተከፈተ በመስከረም ወር ልክ የዛሬ አምስት ዓመት ።

ዓለማየሁ የሦስተኛ ዓመት የመጀመሪያ ሴሚስተር ትምህርቶቹን ተመዘግቦና ከዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ ወጥቶ ብቻውን ቁልቁል

ወደ ስድስት ኪሎ ሐውልት ወረደ ። አባቱ ከደሴ አውቶቡስ ተራ ወደ አዲስ አበባ ሲሸኙት "በዚህ ልብስህን ግዛ ፡ በል እንግዲህ በርታ ደብዳቤም ጻፍልን እኛም የሚመጣ ሰው ባገኘን ቁጥር ለሻይ እሚሆን እንልክልሃለን" ብለው ግንባሩን ሳም ካደረጉ በኋላ ጭብጥብጥ አድርገው ኪሱ ውስጥ ባስቀመጡለት አንድ መቶ ሃምሳ ብር አንድ ነጣ ያለ ሱሪ ፡ አንድ ሰማያዊ ጃኬት ፡ ጫማና ሸሚዝ ገዝቶአል ። አዲሱን ልብሱን ለብሶ ብቻውን ወደ ስድስት ኪሎ ሲወርድ ድንገት አንድ ነገር አየና ድንግጥ ብሎ ቆመ ።

ሐረገወይን ያን ጊዜ የአሥራ ስድስት ዓመት ልጅ ናት ። እሷም ለዘመን መለወጫ ተብሎ የተገዛላትን ቀሚስ ለብሳ ቆንጆዬ ጫማ አድርጋለች ። ጸጉሯን ጠቅልላ ለሁለት ከፍላው አንዱን በስተቀኝ በኩል እስከ ጆሮዋ ድረስ ፡ አንዱን በስተግራዋ በኩል ዘና አድርጋ አስቀምጣዋለች ። በስተቀኝ በኩል ባለው ጥቅልል ጸጉሯ ላይ ሮዝ ቀለም ያላት ሪባን አንጠልጥላለች ። የቀይ ዳማ ናት ። ጉንጮቿ የሚፈርጡ ይመስላሉ ። ዐይኗ ከሩቅ የሚንቦገቦግ የደረሰች ልጃገረድ ። ዓለማየሁ ከላይ ወደ ታች ሲመጣ እሷ ወደ ላይ ወደ እቴጌ መነን ትምህርት ቤት ረጋ ብላ ስትራመድ ዐይኖቿ እንደ ጦር ወጉት። ቋንጃ ቋንጃውን በዱላ እንደ ተደበደበ ሰው እግሩ ተሽመደመደ ፡ እንደበቱ ተያያዘ ፡ እቆመበት ተገተረና ቀረ ። በቃ ያን ጊዜ ተለከፈ ።

ሐረገወይን ዐይኗ ሰው መምታቱን አላወቀችም ። ለዛ ባለው አረማመድ ረጋ አለችና አለፈችው ። ተመለሰና ተከተላት ። ቀረብ ይላትና ቀረት ይላል ። ጠደፍ ጠደፍ ብሎ ያልፋትና ቀስ ብሎ ይራመዳል ፡ ዝግ ይላል ። እሷ ደሞ ተራዋን ታልፈዋለች ። ከጀርባ ሆኖ እስኪጠግብ ይመለከታትና ፈጠን ብሎ ያልፋታል ። ለተመለከተው ቲያትር የሚሠራ ይመስላል ። በቃ ወደዳት ። እንዳይናገራት ፈራት ። ሐረገወይን ሲቀድማት ፡ ሲጠብቃት ግራ ተጋባችና ጠረጠረችው ። እሷም ሰረቅ አድርጋ ተመለከተችው ። አመለካከቷ ግን የግልምጫና የጥላቻ ነበር ። ትምህርት ቤቷ ልትደርስ ጥቂት

ሲቀሩት ከኋላዋ በኩል ቀረብ ብሎ "አንቺ… አንቺን ነው" አለ ።

ዝም ብላው ሔደች ዞርም አላለች ። ልቡ የበለጠ መምታት ጀመረ ። ዝም ብሎ ተከተላት ፣ ትምህርት ቤቱ በር ደረሰ ፣ ልትገባ ስትል ከንዷን ያዘና ጐተት አደረጋት ። ዐይኗን እያጉረጠረጠች መንጨቀችውና ገባች ። በሩ ላይ ሆኖ በዐይኑ ተከተላት ። ብዙ ተማሪዎች መኻል ገብታ ጠፋችው ።

ረዥም ጉዞ የሚጀመረው በአንድ እርምጃ ነው ። ረዥሙን ጉዞውን እሱም በዚህ ሁኔታ ጀመረው ። ዓለማየሁ ከዚህ በፊት የሴት ጓደኛ ኖሮት አያውቅም ። ሴቶችን አይቀርብም ። አብረውት የሚማሩትን ሴቶችም ከሩቅ ይሸሻቸዋል ። ሲያናግሩት ይደነግጣል ፣ እጁ ይንቀጠቀጣል ። መንቀጥቀጡ እንዳይታወቅበት አንዱን እጁን በሌላው እጁ ግጥም ያደርግና ይይዛል ። በትምህርቱ ግን ጉበዝ ነው ሁሉም ይቀኑበታል ።

ትምህርት ቤቱ በር ላይ ለጥቂት ደቂቃዎች ቆሞ ቆየና ተመልሶ ወደ ስድስት ኪሎ አመራ ። ሐሳቡ ዝብርቅርቅ አለበት ። የተመለከታት ልጅ ከፊቱ እየመጣች ግትር ትልበት ጀመር ። ተጨነቀ ። አሰበ … አሰበ ። ለሰው ለማማከርም ፈለገ ፣ ፈራና ተወው ። ሊረሳት ፈለገ ፣ አቃተው ።

እንደ አንዳንድ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በፍቅር ተነድፎ ትምህርቱን እንዳይዘነጋ ፣ እንዳይወድቅና የሰው መሳቂያ እንዳይሆን ፈራ ። ልጅቱን ስከታተል ወንድሞቿ ወይ ዘመዶቿ አንድ ነገር ቢያደርጉኝስ? ብሎ ፈራ ። ምንም ምንም ሳያደርግ የፍራቻ ክምር ተቆለለበት ። የፈለገው ይሁን ብሎ ቆረጠ ።

ዩኒቨርስቲ በር ደረሰና ተመልሶ ወደ ትምህርት ቤቷ ሔደ ። አካባቢው ጭር ብሏል ። ተመልሶ ወደ ዩኒቨርስቲ ሔደ ። በዚህ ዓይነት ብዙ ሲመላለስ ቆየ ፣ ጥቂት ተማሪዎች እየወጡ ወደ ቤታቸው ሲሔዱ ተመለከተና የደስታ ስሜት ተሰማው ። ያ ደስታው ከመቅጽበት ጠፋና መልሶ ድንጋጤ ወረረው ። የፍራቻ

ሸክም ተሜነው ። ሐረገወይን ከሁለት ጓደኞቿ ጋር እያወራች ስትመጣ ከሩቅ አያት ። የሚያደርገው ሲጨንቀው ፊቱን አዞረና እሷን ቀድሞ ቁልቁል ወደ ስድስት ኪሎ ወረደ ። ራመድ ራመድ ይልና እየተገላመጠ ይመለከታል ። ራመድ ራመድ ይልና ዞር ይመለከታል ።

ሦስቱ ጓደኛሞች እየወሩ እየተጫወቱ ዝግ እያሉ ይራመዳሉ ። ዓለማየሁ እነሱን ከሩቅ እያየ ይሔዳል ። ይሸሻቸዋል ። የዩኒቨርስቲውን ዋና በር እልፍ እንዳለ የሚያደርገው ገረመውና ቆመ ። ሦስቱ ጓደኛሞች እየቀረቡት መጡ ። የመንገዱን ጠርዝ ይዞ እጆቹን ከጃኬቱ ኪስ ውስጥ አስገብቶ በኩራት አቋቋም ቆመና ጠበቃቸው ። ሐረገወይን ከሩቅ ተመለከተችውና ድንግጥ አለች ። ለጓደኞቿ የሆነ ነገር ነገረቻቸውና ሁሉም ዓለማየሁን እየሰረቁ ተመለከቱት ። እሱም ደነገጠ ። ብቻ ትኩር ብሎ ተመለከታት ። እልፍ እንዳለች ወደ ኋላ ዞር ብላ ተመለከተችው ፡ ደነገጠና ማትር ብሎ ቀረ ። ጥቂት ራቅ ብለው እንደሔዱ ተከተላቸው ።

እንበሳ ቤት ፊት ለፊት ሲደርሱ ሁለቱ ጓደኞቿ ስላምታ ሰጧትና ጥለዋት ሔዱ ። እሷ ብቻዋን አውቶቡስ መጠበቂያው ላይ ቆመች ። ዓለማየሁ እጆቹን ከጃኬቱ ኪስ እንደ ከተተ ከጐኗ ሔደና ቆመ ። በቁመት ጥቂት ይበልጣታል ። የእሷ ሰውነት ከእርሱ ይልቅ ደልደል ይላል ። ሐረገወይን ሰረቅ አድርጋ ተመለከተችውና ቦታዋን ቀየረች ። ጥቂት ቆየና እሱም ተከተላት ። ከጐኗ ቆመ ። አውቶቡስ የሚጠብቅ ሰው መስሎ ተገተረ ። አልፎ አልፎ ሰረቅ ያደርግና ይመለከታታል። የሚናገረው ነገር አልነበረውም ። ሁሉም ነገር ጠፋው ። አውቶቡስ ለመጠበቅ የተሰበሰበው ሁሉ የሚያውቁት ቡት መስለውና ፈራ ። ግማሽ ሰዓት ቆመ ። አውቶቡስ መጥታ ስትቆም ሰው ሁሉ እየተጋፋ ሲወጣ እሱ ብቻ ቀረ ። ዞር ብሎ ሲመለከት ሐረገወይን የለችም ። ክው አለና ደነገጠ ። ዐይኑን አውቶቡሱ ውስጥ ልኮ ሰውን ሁሉ መመልከት ጀመረ ። ድንገት ዐይን ለዐይን ተገጣጠሙ ። ደነገጠና ዐይኑን ምልስ አድርጐ

አቀረቀረ ። አውቶቡሷ መንቀሳቀስ ጀመረች። እጇን አርገበገበላት ፣ ሥቃቧት ዘወር አለች ።

ሣቋ የማሸነፍ መሆኑ አልገባውም ፣ ከንፈሮቿን ቀስ በቀስ እየከፈተች መሐንዲስ አስተካክሎ የተከላቸው የሚመስሉ ጥርሶቿን ስታሳየው የሱም ልብ አብሮ ሣቀ ። የዕለቱ ልፋቱ አንድ ውጤት ያስገኘለት መስሎ ተሰማው ። እፎይ አለ ።

ዩኒቨርስቲ ገብቶ ራቱን በልቶ ከጓደኞቹ ጋር ተገናኝቶ መኝታው ላይ ጋደም እስኪል ድረስ ያ ፈገግታዋ ከራሱ ድቅን እያለ አስቸገረው ። ለጓደኞቹ አወራቸው ።ስለቁንጅናዋ ፣ አረማመዷ ፣ እጅግ እጅግ እያጋነነ አወራቸው ። ሁሉም አናናቁበት ፣ በሸቀ ። እሱን ሆኖ የሚያደንቅለት አንድም ጓደኛ አጣ።

የመኝታ ቤት ጓደኛው አለባቸው አምሽቶና ጠጥቶ ሲመጣም አወራው ። እሱም የባሰውን አናናቀበት ። ምክርም ቢጠይቀው “ስድስት ኪሎ ሐውልቱ ሥር ጃኬትህን አንጥፈህ ተንበርክክና በዚያ ስታልፍ ስለ ሰማዕታት ብለሽ በፍቅር አትጨክኚ ብለህ ለምናት ። እምቢ ካለችህ ክፍት አፍ ፣ ኮባ ሰፈር ምን ምን የመሳሰሉ ሴቶች አሉ በልና አቧራ የቃመውን ጃኬትህን አራግፍበት ፣ በቃ ። ይኸን አርገህ እምቢ ካለችህ ትምህርትህን አቁመህ አገርህ ውረድና የላሊበላን ደብተራ መስተፋቅር አስተብትበህ ተብትብባት ። በቃ ይኸው ነው በቃ” … እያለ እየተንተባተበ አሾፈበት ።

ዓለማየሁ ሳምንት ያህል በዚሁ ዓይነት ተመላለሰ ፣ ባከነ ። በመጨረሻ ግን ተሳካለት ። ሐረገወይንን ወጥመዱ ውስጥ ገባችለት ። ቀስ በቀስ እሷም እንደሱ ተረታች ።

በየቀኑ ይገናኛሉ ። ትምህርት ቤት በር ላይ ይጠብቃታል ። አውቶቡስ አሳፍሯት ይመለሳል ፣ አንዳንድ ጊዜም አብሮአት ሒዶ ሰፈሯ ድረስ ሸኝቷት ይመለሳል ። አንዳንድ ጊዜ በአውቶቡስ መጠበቂያው መጠለያ ቁጭ ብለው አንድ ሰዓት ፣ ሁለት ሰዓት አውርተው ይለያያሉ ። ቅዳሜ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ በትምህርት

የሚከብዳትን ሁሉ ያስረዳታል ።

ከትምህርቱ ሁሉ ሒሳብ አትወድም ። ፈጽሞ አይሆናትም ። የግድ ሆኖባት እንጂ ጭራሽ ባትማረውም ደስ ይላታል ። ዓለማየሁ በሒሣብ ጉበዝ እንድትሆን ያላደረገው ጥረት የለውም ። ትዳሚ በመጣ ቁጥር የሚያስረዳት ሒሣብ ነው ። ግን እያደር ጥሬ ትሆንበታለች ። ተስፋ አይቆርጥም ። እንደውም አንድ ጊዜ ፡ "ሒሣብን ካላለፉ ዩኒቨርስቲ አይገባም ብዬ እንጂ ሒሣብ ከደረሰበት አልደርስም ነበር ። አንድ ጊዜ ማትሪክን ልውሰድ እንጂ ሒሣብ የሚባል ነገር ባይኔም አላይ ፡ እንደውም እሱት ሰቃ ገዝቸም መልሱን ላልተሳሰብ እምለላሁ" ብላ አሥቃው ነበር ።

ዓለማየሁ እንደ እኅት ይመለከታታል ፡ እንደ አባት ይጠብቃታል ፡ እንደ እናት ይንከባከባታል ፡ በትምህርቷ እንድትጐብዝ ያበረታታታል ፡ ይመክራታል ። ወደደችው ። ከመጥፎ ጓደኞች ጋር እንዳትገጥም ያስጠንቅቃታል ፡ ወደደችው ። በዕረፍት ጊዜዋ መጻሕፍት እንድታነብ እየወሰደ ይሰጣታል ፡ አንብባ ስትመልስለት "እንዴት ነው" ብሎ ይጠይቃታል ። ከመጽሐፉ ታሪክ አንዳንድ ጉዳዮችን እያነሣ ይተርክላታል ። የእሷንም አስተያየት ይጠይቃል። ወደደችው ።

አንዳንድ ጊዜ ውሃ ቀጠነ ብላ ታኮርፈዋለች ። ተለማምጦ ፡ ለምኖ ይታረቃታል ። አንድ ሁለት ቀን ተኮራርፈው በእሱ ልመና ሲታረቁ ዐይን ለዐይን ይፋጠጡና ሁለቱም ያለቅሳሉ ። ዳግመኛ ላለመኮራረፍ ይማማላሉ ። ሦስት ጊዜ ከጐረምሶች ጋር ተደባድቧል ፡ ለእሷ ብሎ ። ከዚያ ወዲህ የትኛውም ጐረምሳ ቢያስቸግራት እንዲህ ሆንኩ ብላ አትነግረውም ፡ ታዝንለታለች ፡ ትወደዋለች ። ፍቅራቸው እንደ ሰደድ እሳት እየተቀጣጠለ ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ ሔደ ። አብሮአቸው አደገ ።

ዓለማየሁ ከሐረገወይን ጋር ሲወጣ ሲገባ አንድ እጅግ የሚሳቀቅበት ጉዳይ ነበር ፡ ሁልጊዜም የሚለብሳት አንድ ሰማያዊ ጃኬትና አንድ ነጭ ሱሪ ብቻ ። ሁለት ሸሚዞች አሉት ። እነሱን

ይቀያይራል ። እንደ ዘመኑ ባለ ገርል ፍሬንዶች ለመሽቀርቀር አልቻለም ። ያችን ጃኬትና ሱሪ ማታ ያጥባል ፤ ጠዋት ደርቀው ያገኛቸዋል ። ለብሶ ይወጣል ። ሌሎች ልብሶችም አሉት ፤ ግን አደባባይ የሚያወጡ አልነበሩም ። ያፍርባቸዋል ።

ሐረገወይንን ከትምህርት ቤቷ በር ላይ ጠብቆ ወደ ቤቷ ሲሸኛት በየዕለቱ የእርሷ የቅርብ ጓደኞች ሲመለከቱት ይሳቀቃል ፤ ይፈራል ። ሐረገወይንም ነገሩን ግልፅ አድርጋ አትንገረው እንጂ እሷም በእሱ ትሳቀቃለች ። ጓደኞቿን ታፍራለች ። የጓደኞቿን የሚሽቀረቀሩ ቦይፍሬንዶች እየተመለከተች ትማቀቃለች ። ደስ ቡኛል እያለች ትሠጋለች ።

አንድ ቀን ከትምህርት ቤት ወጥታ አንበሳ ቤት መስኮ ላይ ቁጭ ብለው ሻይ እየጋበዛት ሲጫወቱ ቆየና ወደ ቤቷ ለመሔድ ስትነሣ የጃኬቱን ኮሌታ ያዝ አደረገችና "አለማየሁ ይኸ ዩኒፎርማችሁ ነው እንዴ?" ያለችው ዛሬም ድረስ እየታወሰው ይሳቀቃል ። ያን ጊዜ ግን ሽምቅቅ እፍር ነው ያለው ። ምንም መልስ አልሰጣትም። ተኳርፈው ከአንበሳ ቤት ወጡ ። ሸኝቷት ወደ ዩኒቨርስቲ ሲመለስ እያዘነ ነበር ። ድህነቱ ፤ የቤተሰቡ ማጣት ያን ጊዜ ነው የታሰበው ። ድህነትን ማጣትን ክፉኛ ያማረረው ያን ጊዜ ነው ። ግን ድህነት እንደ ገላ እድፍ በሳሙና ታጥበውት በአፍታ የሚገላገሉት ጉዳይ ሆኖ አላገኘውም ። ለሁለት ቀን በተከታታይ ተደበቃት ። በዚህ አኩረፈችው ፤ በገዛ እጁ ጠፍቶ ተለማምጦ ተለማምጦ ታረቀ ።

ሐረገወይን ፤ ዓለማየሁ ልብስ እየለዋወጠ ባይሽቀረቀርም ትወደዋለች ። የእሷ ፍራቻ ጓደኞቼ ይንቁኛል የሚል የልጅነት ፍራቻ እንጂ የዓለማየሁን ፍቅር በምንም አትለውጠውም ።

ለጥምቀት በዓል አባቷ ከጎሬ ሲመጡ "ከጓደኞችሽ እንዳታንሽ የፈለግሽውን ግዢበት" ብለው ሦስት መቶ ብር ሰጧት ። ደስ አላት ። አንድ አርብ ቀን ዓለማየሁ ወደ ቤቷ ሸኝቷት "ባይ ደኅና እደሪ" ብሎ ሲሰናበታት "ነገ ትምህርት አለህ እንዴ?" አለችው ፤

ትምህርት ነበረው ፡ ግን የለኝም አለና ዋሸ ። "እንግዲያውስ አንድ የእናቱ እህት ልጅ አለ ከአባቱ ጋር ጎፋ ነው የሚኖረው ፡ እዚያ ነው የሚማረው ። ልክ አንተን ነው የሚያህለው ፡ አባቱ ልብስ ግዛለት ብሎ ገንዘብ ስለ ሰጠኝ በአንተ ልክ እገዛለታለሁ ፡ አንተ ታገዛኛለህ ነገ ጧት አራት ኪሎ እንገናኝ" ብላ ቀጠረችው ።

በማግሥቱ ጧት ተገናኙ ፡ መርካቶ ሔደው ሁለት ሱሪ ፡ ሁለት ጃኬት ፡ ሁለት ሸሚዝ ፡ አንድ ሹራብ ፡ አንድ ጫማ ፡ ሦስት ካልሲ ገዙ ።

"የወንድ ልብስ መምረጥ አልችልም ፡ እስኪ ደስ የሚል ጃኬት ምረጥልኝ" ትለዋለች ። ዓለማየሁ ለእሱ ደስ የሚለውን ይመርጣል ። "ይበቃው ይሆን? እስኪ ለካልኝ" ትለዋለች ። ይለካል፡ ይስማማዋል ። ገንዘቡን ትከፍልና የገዛችውን ጠቅልላ ትይዛለች ። ወደ ሌላ ሱቅ ይሔዳሉ ። "ጥሩ ሱሪ ምረጥልኝ የአገር ቤት ልጅ ነው ብለህ እንዳትንቀው ቆንጆውን ምረጥለት" ትለዋለች። በሱቁ የተደረደሩትን ሱሪዎች ሁሉ በዐይኑ ይማትርና አንዱን ይመርጣል። "እስኪ ለካው" ትለዋለች ፡ ይስማማዋል ። ሐረገወይን፡ ዓለማየሁ ልብሱን ለክቶ ሲስማማው ውስጧን ደስ ይለዋል ። ዓለማየሁ በየሱቁ የመረጣቸውን ልብሶች ሁሉ ወዷቸዋል ። ሊገዛ የማይችል በመሆኑ ግን ከመጐምዠት በቀር ሌላ ምርጫ አልነበረውም ።

የገዙአቸውን ልብሶች ለሁለት ተከፋፍለው ይዘው በታክሲ ወደ አራት ኪሎ ሔዱ።

"ዓሌ ዛሬ ቆንጆ ምሳ እጋብዝሃለሁ ፡ ስትለፋ ስለ ዋልክ ቆንጆ ምሳ ምብላት አለብህ እሺ" አለችው ሣቅ እያለች ።

"እሺ ደስ ይለኛል" አላት ።

ተያይዘው ወደ አንድ ስናክ ባር ገቡ ። ምሳቸውን በልተው እንደጨረሱ ፡

"ዓሌ በል እንግዲህ አባቱ ቤት ስላለ የት ጠፋች ይላልና ቶሎ

መሔድ አለብኝ ። ከመሔዴ በፊት ግን አንድ ነገር እለምንሀለሁ ። እሺ ትለኛለህ አይደል ዓሌ?” አለችው ዐይኗን ፍጥጥ አድርጋ ። ዓለማየሁ የምትለምነው ነገር ምን እንደሆነ ባያውቅም ፡

“ምነው ሐረጌ የምን ልመና ነው እዘዢኝ እንጂ ፡ ስትለምኝ ኀማ ደስ አይለኝም ። እዘዢኝ እታዘዛለሁ” አለ ሁለት እጆቹን ወደ እርሷ ዘርግቶ ።

“እንግዲያውስ ዛሬ የገዛነው ሁሉ የአንተ ነው ፡ እንደ ወደድካቸው እገምታለሁ” ይዛው የነበረውን ጥቅል ነገር አንሥታ ዘረጋችለት ። ቀዝቀዝ ባለ ሁኔታ ተቀበላት ። ፈዘዘ ፡ ደነገጠ ፡ የሚያውቃት ሐረገወይን ሳትሆን ሌላ መስላ ታየችው ፡ በዕድሜ የሚበልጣት የሴት ጓደኛው ሳትሆን ውስጡን የምታውቀበት ወላጅ እናቱ መስላ ታየችው ። ዐይኖቹ ዕንባ አረገዙ ።

“ትዕዛዝ ነው ተቀበል” አለችና ሣቅ አለች ።

ከአቀረቀረበት ቀና አለና ፡

“ሐረጌ በጣም ነው የምመሰግንሽ ፡ ግን እኮ ልክ አይደለ ሽም ...”

“ትዕዛዝ ነው ብየሀለሁ ዝም በል” አለች አቋረጠችውና ። የሚናገረው አልነበረውም ። ጠረጴዛውን በሁለት እጆቹ ክርን ተጭኖ ጥቂት አሰበና ፡ ከፊት ለፊቱ ያለውን ኮካኮላ የተቀዳበት ብርጭቆ አንሥቶ ተጐነጨ ። ሐረገወይን ሂሣቡን ከፈለችና ተያይዘው ወጡ ።

እስከ ላምበረት አውቶቡስ ማቆሚያ ድረስ ቀስ እያሉ ሔዱ ። አብዛኛውን መንገድ አልተነጋገሩም ፡ ተኮራርፈው ሔዱ ። አሥር ቁጥር አውቶቡስ መጥታ “በል ... ሰላም” አለችና እጁን ጐትታ በሁለት እጆቿ ጠበቅ አድርጋ ጨበጠችው ። ሮጣ አውቶቡሷ ውስጥ ገባች ። ዓለማየሁ ፡ ሐረገወይን በሁለት እጆቿ ፈልቅቃ ጭብጥ አድርጋ የለቀቀችውን የቀኝ እጁን መዳፍ ዘረጋና ተመለከተው ። ድንግጥ አለ ። አራት የአሥር ብር ኖቶች ተጣጥፈው ቁጭ ብለዋል ።

ፈጠን አለና ወደ አውቶቡሱ መስኮት ተጠጋ ፡ ከሐረገወይን ጋር ዐይን ለዐይን ተገጣጠሙ ። እጆቿን አውለበለበችለት ። ወደ መስኮቱ ጠጋ አለና ፡

“ምን መሆንሽ ነው ሐረ ፡ ልክ አይደለሽም” አለ ።

“ጓደኞችህ እኮ ማስመረቂያ ይሉሀል ...” አለች ፈገግ ብላ ። ፈገግ ስትል የእሱም ልብ ወከክ አለ ። ፈገግታዋ ደስ ይለዋል ። ያረካዋል ። ሁልጊዜ ፈገግ እያለች ስታስደስተው ብትውል ደስ ይለዋል ። ፈገግ ስትልለት ውበቷ ጉልህ ሆኖ ደምቆ ይታየዋል ። እንዳች ነገር ከእግር እስከራሱ ይወረዋል ። ያን ቀን በዚሁ ተለያዩ ።

የሐረገወይን የዚያን ዕለት ድርጊት ሕይወቱን ሙሉ አይረሳውም ። ውለታ ለመመለስ ያላሰበው አልነበረም ። ብዙ አውጥቷል ፡ አውርዷል ። ለሐረገወይን የሚያሳያት እውነተኛ ፍቅር ብቻውን በቂ ሆኖ አላገኘውም ፤ ከአሥረኛ ክፍል ወደ አሥራ አንደኛ ክፍል ከአርባ ተማሪዎች ስምንተኛ ሆና ስታልፍ ስልሳ አምስት ብር አውጥቶ የአንገት ሐብል አሠርቶ ሰጣት ። ውለታ በመመለሱ ልቡ ረካ ።

አንድ ጊዜ አባቱ ሠላሳ ብር ይልኩለታል ፡ አላጠፋትም ፡ ሳጥኑ ውስጥ ቆልፎ አስቀመጣት ፡ ከሁለት ወር በኋላም ሠላሳ ብር ላኩለት፡ እሷንም አስቀመጣት ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መልቀቂያ ፈተና ጽሕፈት ቤት ለተማሪዎች በሚሰጠው የትርፍ ጊዜ ሥራ አንድ ሳምንት ሠርቶ ካገኛት ሐያ አምስት ብር ውስጥ አምስቷን ጨምሮ በስልሳ አምስት ብር የአንገት ሐብል ገዛላት ። በስጦታ ወረቀት ጠቅልሎ ኪሱ ውስጥ አስቀመጠ ። በሰኔ ወር መጨረሻ የፈተና ውጤቷን ተቀብላ ስትወጣ ትምህርት ቤቱ በር ላይ ጠበቃት ፡ እየተጫወቱ በእግራቸው እስከ አራት ኪሎ ድረስ ሔዱ ፡ ወደ አንድ ቲ ሩም ይዞአት ገባና ኮካ ኮላ ጋበዛት ። ከኪሱ ውስጥ ያስቀመጠውን የተጠቀለለ ስጦታ አወጣና ሰጣት ።

“ምንድን ነው?” አለችው ።

"ስትከፍችው ታውቂዋለሽ" ፈገግ አለ ፡ የኮካ ኮላውን ብርጭቆ ከፊቱ እያነሣ ።

ሐረገወይን የተጠቀለለውን ፈታችና አየችው። የአንገት ሐብሉን በጣቷ አንጠልጥላ ደስ በሚለው ፈገግታዋ ትኩር ብላ ተመለከተችው ። ፈገግ እያለ ተመለከታት ። ከመቀመጫዋ እየተነሣች "በል እንካ አንገቴ ላይ አጥልቅልኝ" ብላ ጉንበስ አለች። አጠለቀላት ። ጉንጮቹን አገላብጣ ሳመችው ። ሁለቱም ምክንያቱን ሊገልፁት ባይችሉም ፡ ተቃቅፈው አለቀሱ ። ዛሬ ድረስ ይህንን እያስታወሱ ይሥቃሉ ።

ዓለማየሁ ለአንድ ዓመት የዩኒቨርስቲ ሰርቪስ ጉመጎሩ ፡ አርባምንጭ በመምህርነት ተመድቦ ሲሔድ መርካቶ አውቶቡስ ተራ ሲሸኛት የተላቀሱት ሰው ጉድ እስኪላቸው ድረስ ነበር ። ሁለት ጊዜ ወደ አዲስ አበባ መጥቶ አይቷታል ። የአርባ ምንጭን ውብ ተፈጥሮ እንድታይ ደጋግሞ በደብዳቤ ጠይቋት ነበር ፡ ግን አልቻለችም ። ዓለማየሁ ወደ አርባ ምንጭ ሲሔድ አባቷ ከጎፋ ተቀይረው ወደ ጊምቢ ተዛወሩ ። አባቷን ለመጠየቅ ብላ መሔድ ትችል ነበር ፡ አልሆነላትም ። ዓለማየሁ አርባምንጭ በቆየባቸው አሥር ወራት የጻፈላትን ደብዳቤዎች ሁሉ አስቀምጣቸዋለች ።

ዓለማየሁ ከአርባ ምንጭ ሲመለስ ያገኝት ከነበረው አንስተኛ ደመወዝ ባጠራቀመው ገንዘብ ለዓመቱ የሚሆነውን ልብስ ገዛ ። ለሐረገወይን ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ሰጠ ። ፍቅራቸውን በአዲስ መልክ ጀመሩት ። ዓለማየሁ የዩኒቨርስቲ ትምህርቱን የሚያጠናቅቅበትና ብዙ ሥራ የሚሠራበት እሷም የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የምትወስድበት ዓመት ስለነበር ፡ እንደ መጀመሪያቸው በየዕለቱ ለመገናኘት አልቻሉም ። በአምስት ቀን አንድ ጊዜ ይገናኛሉ ። ቁጭ ብለው ተጫውተው ተሳሥቀው ይለያያሉ ። ሐረገወይን ፈተናውን ዐልፋ ዩኒቨርስቲ እንድትገባ ዓለማየሁ ከፍተኛ ፍላጎት ስለነበረው ፡ እንድታጠና ይመክራታል ። ያበረታታታል ። ይጠፋባታል ። ሲጠፋባት መኝታ ቤቱ ድረስ ፍለጋ ትሔዳለች ። ሲጠፋባት

ትታመማለች። ዓመቷ ለሁለቱም የጭንቅ ዓመት ነበረች ።

ከዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ ውጭ ቤት ተከራይተው ይኖሩ የነበሩ ጓደኞቹን አስፈቅዶ ሦስት ጊዜ ወስዷታል ። ሦስቱንም ጊዜ ተሳስመው ተለያዩ ። ሁለቱም ስሜታቸውን ገተው ለረዥሙ እቅዳቸው አሰቡ ። ሁለቱም ነፍስ አወቁ ። ከዓለማየሁ ፍቅር የእሷ ባሰ ። ከዩኒቨርስቲ ተመርቆ እንደወጣ ሥራ ይዞ አስፈላጊዎቹን የቤት ዕቃዎች እንዲያሟላ እሷ ዩኒቨርስቲ ገብታ ትምህርቷን እንድትቀጥል ፡ ስትጨርስም ለመጋባት ወሰኑ ። የረዥም ጊዜ ዕቅድ አወጡ ።

እንዳሰቡት ግን አልሆነላቸውም ። ሐረገወይን በዚያ አጥብቃ በምትፈራው ሂሳብና በታሪክ ወደቀች ። ዓለማየሁ ቀድሞውንም በሂሳብ እንደማታልፍ ቢያውቅም ፡ በውል መውደቋን ሲያውቅ ተናደደ ። ከእርሷ ይበልጥ በሸቀ ። ሐረገወይንን ይበልጥ ላለማናደድ ሲል ግን ብስጭቱን እፍን አርጎ ያዘው ።

ከዩኒቨርስቲ ተመርቆ እንደወጣ በአዋሽ ሸለቆ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት በረዳት ኤክስፐርትነት ተቀጠረ ። ሠንጋ ተራ ሦስት ክፍል ቤት አግኝቶ ተከራየ ። ኑሮ ጀመረ ። ትምህርት ቤት በነበሩበት ወቅት የነደፉት የረዥም ጊዜ ዕቅድ በእሷ መውደቅ ሳንካ ቢያገኘውም ፡ ሌላ ስልት ቀየሱ ። ሐረገወይን ማታ ማታ እየተማረች የወደቀችባቸውን ትምህርቶች ውጤት እንድታሻሽል፡ ሥራ የሚገኝም ከሆነ እንድትይዝ ተስማሙ ። ትምህርት ቤት ሲያማርጡ ቆይተው የካቴድራልን የማታ ትምህርት ቤት መርጠው ሁለቱም ሔደው አስመዘገባት ። ሁለት ወር እንደ ተማረች አባቷ "ሥራ አግኝቼልሻለሁ ትገቢያለሽ ተዘጋጂ" ይሉአታል ። ደስ አላት ፡ ለዓለማየሁ ስትነግረውም ደስ አለው ።

የሐረገወይን አባት ወንዲራድ በብዙ ቦታዎች በአውራጃ ገዥነት ሲሠሩ ቆይተው አዲስ አበባ ከተዛወሩ ስድስት ወራቸው ነበር ። የልጃቸው በፈተና መውደቅ ውስጥ ውስጡን ቢያበስላቸ

ውም ፡ አውጥተው ግን አልተነፈሱትም ። ፈተና መውደቅ ከሌሎቹ ማነስ መስሎ ታይቷቸው እንጂ ፡ ፈተናውን ሀልፋ ዩኒቨርስቲ ብትገባም ባትገባም ለእርሳቸው ያው ነው ። እንደውም ሥራ ይዛ "ሥራ የያዘች የደረሰች ልጅ አለቻቸው እኮ" መባልን ይመርጣሉ ። በዘመድ መሥራትን ያውቁበታል ፡ እንዲያውም ያመልኩበታል ። "ያስቀመጡት ዕቃና የሰሩት ውለታ ለክፉ ቀን ይደርሳል" እያሉም ለሰው ብዙ ያደርጋሉ ። የልጃቸውን ሥራ ጉዳይ ብዙ አሰቡበትና አንድ ቀን አንድ ሐሳብ ውልብ አለባቸው ።

ወሰንየለህን ማሳደድ ጀመሩ ። የሰው ጉዳይ አስፈጻሚ ዘና መጥቀባቸው ከአንዴም ሁለት ሦስት ጊዜ አስደስተው ልከውታል ። በአውራጃ ገዥነታቸው መደረግ የማይገባውን አድርገውለት ትልቅ ውለታ ጥለውበታል ። አሳደው አገኙት ። "ልጄ አሥራ ሁለተኛ ጨርሳ ይኸው እቤት ተቀምጣለች ። አንተ እያለህ እንዴት ሥራ ፈታ ትቀመጣለች ?" ሲሉት ፡

"ምነው ምነው ወንዲራድ የእኔ እጅና እግር ቆሞ እየሔደ የእርስዎ ልጅ ሥራ ፈታ ትቀመጣለች ፡ በውነት በውነት ዝምድናውን ትተውታል ማለት ነው ፡ ነገ ··· ነገ ጧት ግዴለዎትም ፡ አማርጣ ትገባለች ። እኔ እያለሁ" ነበር ያላቸው ። ወንዲራድ የቀዘ ሰው አይደሉም ፡ ቃል አስገብተው የእሱን ስልክ ጽፈው የእርሳቸውንም ሰጥተው ተለያዩ።

ወሰንየለህ በሦስተኛው ቀን ደወለላቸው ። "ነገ ጧት ልጅነቷን ይዘው ሜክሲኮ አደባባይ እንዲጠብቁኝ ፡ ልክ ሦስት ሰዓት ። ነገውኑ ትጀምራለች" አላቸው ከራት በተጫላበት አነጋገር ። "እስይ የእኔ ከተፎ ውለታ ለመመለስ ያብቃኝ" አሉት ውስጣቸው በደስታ ተሞልቶ ።

በማግሥቱ ልክ ሦስት ሰዓት ሜክሲኮ አደባባይ ተገናኝተው ወደ ስፌሬያን ኩባንያ ይዞአቸው ሔደ ። ወንዲራድን እንግዳ ማረፊያ ክፍል አስቀምጦ ሐረገወይንን ወደ አንድ ቢሮ ይዞአት ገባ ። ጥቂት ቆይተው ወጡ ። በሁለቱም ፊት ላይ የድል ምልክት ይታያል ።

ወንዲራድ ከመቀመጫቸው ተንሥተው ተቀበሉአቸው ።

“ጥቶ በቃ ። ነገ ቤት ትጀምራለች ፤ እንግዲህ በርትታ መሥራት ነው” አለ ወሰንየለህ የሐረገወይንን እጅ ጨብጦ ዐይን ዐይኗን ትኩር ብሎ እየተመለከተ ።

ወንዲራድ “ብድር መላሽ ያርገኝ ውለታ መላሽ ያርገኝ” እያሉ የወሰንየለህን እጅ ጨብጠው ክንዱ እስኪዝል ድረስ ወዘወዙት ። ያንዕለት በዚሁ ተለያዩ ።

ወሰንየለህ የሐረገወይንን ውበትና የሚማርክ አቋም ሲመለከት አንዳች ነገር ወረረው ። “ቆይ አንድ ቀን ደግሞ አንቺን ሥራ እይዝብሻለሁ” ብሎ ፎከረ ።

ሐረገወይን ሥራ መያዟን ለዓለማየሁ ስታበስረው ከልቡ ደስ አለው ። የደስ ደስ ጋበዛት ። ያን ዕለት ለረዥሙ እቅዳቸው አንድ አዲስ ምዕራፍ የተከፈተበት አድርገው ቆጠሩት ። ሁለቱም ደስ አላቸው ። ወይዘሮ ተዋበችና ዘነበች ቡና አፍልተው ሲመርቋት አመሹ ።

ሐረገወይንና ዓለማየሁ በሰባት ሰዓት ከቢሮአቸው ወጥተው ዓለማሁ ቤት ይገናኛሉ ፤ ምሳ በልተው አብረው ይወጣሉ ። ማታ ከትምህርት ቤት ስትወጣ ይጠብቅና ሸኝቷት ይመለሳል ። በማግሥቱ በምሳ ሰዓት ይገናኛሉ ። የበለጠ እየተቀራረቡ ፤ እየተሳሳቡና ፍቅራቸውን እያጠናከሩ ሔዱ ። ሐረገወይን ቤተሰቦቿን ስለምትፈራ ከዓለማየሁ ጋር ባታስተዋውቀውም ዓለማየሁ ከትንሽ ወንድሙ ከስንታየሁና ከአክስቱ ከወይዘሮ ባፈና ጋር አስተዋወቃት ። ቤተሰብ ሆነች ፤ እነሱም ወደዷት ። የዓለማየሁ አክስት ወይዘሮ ባፈና “በል እንግዲህ አባትህ አንድ ነገር ሳይሆን ደስ አሰኘው ፤ ቶሎ በሉና ተጋቡ ። ለድግሱ እንደሁ አታስብ ፤ እኔ እያለሁ ምንም አይቸግር” እያሉ ብዙ ጊዜ ይጨቀጭቁታል ። ችኮላውን አልወደደውም ። በየወሩ ከሚያገኙት ደመወዝ የቤት ዕቃ ይገዛል ። ሐረገወይን የጐደለውን ሁሉ በማስታወሻዋ እየያዘች በየወሩ ዕቃ

ትገባለች ። ቤታቸው የተሟላ ሆነ ።

በዓመቱ መጨረሻ የሚያሳዝን ሁኔታ ገጠማቸው ። ሐረገወይን ዳግመኛ በሂሣብ ትምህርት ወደቀች ። እጅግ አዘነች ፤ ታመመች ። ያን ዕለት ሥራም አልገባች ። ስትናደድ ዋለች ፤ ለትምህርት ቤት የከፈለችው ገንዘብ ፤ ልፋቷ ከሁሉም በላይ ዓለማየሁ ዓመት ሙሉ ሲንከለት የቆየው ፤ ከትምህርት ቤት እስክትወጣ ድረስ እሷን ቆሞ በመጠበቅ ያሳለፈው ጊዜ ሁሉ ከንቱ መሆን እየታሰባት ስታለቅስ ዋለች ።

ዓለማየሁ ከሥራ ወጥቶ ቤቱ ሲገባ ሠራተኛው በር ላይ ጠብቃ ነገረችው ። ሐዘኑን ድብቅ አድርጎ ፈጥኖ ወደ መኝታ ቤቱ ሲገባ ጋቢ ደርባ ጥቅልል ብላ ተኝታ አገኛት ። በርከክ አለና ራሷን ደባበሳት ። የትኩሳት ምልክት አላየበትም ። የሚናገረው ጠፍቶት ፍዝዝ ብሎ ቆየ ። እሷን ማጽናናት አለበት ፤ ግን ምን ብሎ እንደሚያጽናናት ግራ ገባው ።

"ሐረ ሐረዬ" ተጣራ በእጁ ራሷን እንደያዘ ። ጋቢዋን ገለጥ አድርጋ ተመለከተችው ። ዐይኖቿ በዕንባ ርሰዋል ። ፊቷ አብጧል ፤ ጸጉሯ ጭብርር ብሎአል ። ደነገጠ ፤ አንገቷን እቅፍ አደረገና ቀና አደረጋት ።

"ምንም አታስቢ ሐሪ ፤ ትምህርትና ዳገት ቀስ እየተባለ ነው ይባል የለ !"

ቀልዱን አልወደደችለትም ። ገልመጥ ብላ ተመለከተችውና ተነሥታ ወደ መታጠቢያ ቤት ሔደች ። አልተከተላትም ። ምን ማድረግ እንዳለበት ፤ ምን ቢናገር እሷን ማፅናናት እንደሚችል ማሰብ ጀመረ ፤ የረባ ነገር ሊያገኝ ግን አልቻለም ። ሐረገወይን ከመታጠቢያ ቤት ስትመለስ ፊቷን ታጥባ ጸጉሯን አበጥራ አምራና ደምቃ ታየችው ። በሩን ገባ እንዳለች እቅፍ አደረገና ያዛት ። ቀና ብላ ዓይን ዓይኑን ተመለከተችው ፤ አስተያየቷ አሳዛኝ ነው ፤ ዓይኖቿ ዕንባ አቀረሩበት ። አንገት ለአንገት ተጠማጥመው ለጥቂት ጊዜ

ቆየ። በእቅፉ እንደያዛት አልጋው ላይ አስቀመጣትና ወጥቶ ወደ ሳሎን ሔደ ። አንድ ወንበር ይዞ ተመለሰና ቁጭ አለበት ።

“ሐረ ይህ እኮ ሕይወትሽን ሊያጨልም የሚችል ጉዳይ አይደለም ። በእንቺ በኩል ማድረግ የሚገባሽን ሁሉ አድርገሻል ። በቃ ፡ አልሆነም ፡ ወይቅሽ ፡ ደግሞ ልንገርሽ አንቺ ብቻ ሳትሆኚ ብዙ ሰው ነው የሚወድቀው ። እና መፍትሔው ማልቀስ አይደለም ፡ ማልቀስ መሆንም የለበትም ። ስታለቅሽ ራስሽን ከመጉዳት በቀር የሚተርፍ አንድም ነገር የለም ። የዕንባ ጎርፍ ፊትን ያጨማድድ ካልሆነ በቀር ፡ ችግርን ጠርጎ ሊወስድ አይችልም ። መፍትሔውም ምን እናድርግ? ብሎ ማሰቡና ያንን ለመፈጸም መዘጋጀቱ ብቻ ነው ። አየሽ አንድ ዓመት ተምረሽ ከንቱ እኮ አልቀረሽም ፡ በሂሳብ ብትወድቂ የታሪክ ውጤትሽን አሻሽለሻል ። ሂሳብም የማይወጡት ተራራ ሆኖ ሊኖር አይችልም ። ሞክሪ ፡ ሞክሪ አንድ ቀን ታልፊዋለሽ ። ሐረዬ ምንም አይደል ፡ ለመጭው ዓመትም ደግመሽ ትማሪያለሽ…”

“ሁለተኛ ሂሳብ ልማር ፡ በቃ በቃ” አቋረጠችው ፡ ከአልጋው ላይ ተነሣችና ቆመች ። እቅፍ አድርጎ መልሶ አስቀመጣት ።

“በመጭው ዓመት የምትማሪው ሂሳብ ብቻ ስለሆነ ፡ ጊዜሽን በእሱ ላይ ብቻ ታጠፊያለሽ ፡ በትምህርት ቤትም ብቻ ሳይሆን አንድ ጐበዝ ልጅ ቀጥረን እንዲያስጠናሽ እናደርጋለን… በቃ ።”

“ወደቤቴ ፡ ወደቤቴ ሸኘኝ” አለች ከአልጋው ላይ እየተነሣች። ዓለማየሁ ሰዓቱን ተመለከተ ፡ ለአንድ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ይላል። ተያይዘው ወጡ ።

ታክሲ ተኮናትረው ላምበረት ድረስ ሔዱ። ከታክሲዋ ውስጥ ብዙ ብዙ ነገር ተጫወቱ ፡ ተፈቃቀፉ ፡ ሳይስማሙ ተለያዩ ። ከታክሲዋ ወርደው ቀጭኗን ኮረኮንች መንገድ መውጣት ስትጀምር ፡ “በል ተመለስ ቶሎ ቤት ግባ” አለችው እጇን እየጨበጠች ። ተሰነባብተው ጥቂት እርምጃዎች እንደተራመደ ከኋላው እየተከተ

ለች ጠራችውና ወደ ጆሮው ጠጋ ብላ ፡

"ነገ ምሳ በልቼ ተመልሼ መሥሪያ ቤት አልሔድም ፡ አንተም ከሰዓት በኋላ ጉዳይ አለኝ ብለህ አስፈቅደህ እንድትመጣ እሺ !" አለችው ቁርጥ ቁርጥ በሚል ትንፋሽ "ምነው ? ምነው ?" አላት እሱም እየተርበተበተ ። "ብርቱ ጉዳይ አለኝ" ተሰነባብተው በየቢሯቸው ገቡ ።

በማግሥቱ ምሳ በልተው እንደጨረሱ ሐረገወይን እጁን ተጣጠበችና ዓለማየሁን ሳሎን ትታ ወደ መኝታ ቤት ገብታ ተኛች። ዓላማየሁ ሳሎን ቁጭ ብሎ መጽሐፍ ያነባል ። ግማሽ ሰዓት ያህል ከተኛች በኋላ ዓለማየሁን ጠራችው ። ዓለማየሁ የሚያነበውን መጽሐፍ እንደ ያዘ ወደ መኝታ ክፍሉ ሲገባ ተኝታ አገኛት ።

"ስሚ ዛሬ እዚህ ቤት ማን ይመጣል ?" ጠየቀችው ። ጥቂት አሰበና "ማን ይመጣል ብለሽ ነው እንጃ ማንም አይመጣም"

"ስንታየሁ ወይም አትዬ ባፈና አይመጡም?"

"አይመጡም ፡ ምን መሰለሽ ሥራ ስላለ እኔን አገኛለሁ ብለው አይመጡም"

"እሽ እንግዲያውስ የመኝታ ቤቱን በር ዝጋውና ና"

ዓለማየሁ በሩን ዘጋና ወደ አልጋው ጠጋ አለ ።

"ና ተኛ" አለችው የለበሰችውን ብርድልብስ እየገለጠች ። መጽሐፉን በእጁ እንደ ያዘ እግሮቹን አንጠልጥሎ ጋደም አለ ከጐኗ።

"የለም የለም ልብስህን አውልቅ ፡ ትዕዛዝ ነው አውልቅ ።"

ዓለማየሁ ልብሶቹን በእርጋታ አወለቀና ተኛ እንደሷው ።

"ቴፑን ክፈተው ድምፁን ከፍ አድርግና ክፈተው" አለች ከሹክሹክታ ባላነሰ ድምፅ ። ከፈተና መልሶ ተኛ ። የተቀባችው ሽቶ ከማፋጯ የተፈጥሮ ጠረኗ ጋር ተዋህዶ አወደው ። ገላዋ ከዚህ ቀደም የሚያውቀው ሳይሆን አዲስ ሆነበት ። ጠጋ ብሎ ሲያቅፋት ሰውነቷ

ሁሉ ቀለለው ። ችቦ አይሞላም ወገቧ ።

ተሸፋፍነው ምስጢር ጀመሩ፡ ሌላው ሰው የማያውቀው ረቂቅ ምስጢር ። ከተዋወቁ አራተኛው ዓመት መሆኑ ነው ። ሲከባበሩ ሲተፋፈሩ ኖረዋል ። ለረዥም ጊዜ ዕቅዳቸው ብቻቸውን ሳይሆን ብዙ አጃቢ በሞላበት ፡ በሥራ ሰዓት ሳይሆን ከሥራ ሰዓት ውጭ — ቀን ሳይሆን ሌሊት ፡ እየተዘፈነ ፡ እየተቦረቀ ፡ እየተበላ ፡ እየተጠጣ። በዋልድባም ይዘፈናል ። ዘፈንም እኮ ውስጡን ደስ ሲል ካልሆነ በቀር እስክስታ አያስወርድ ።

ያ ምስጢራቸውን ሸፍኖ የነበረው ብርድልብስ መሬት ላይ ወርዶ ዘፍ ሲል የማቃሰትና የእፎይታ ቅልቅል ድምፅ ተሰማ ። ሁለቱም ሰማዕታትን እንደሚማፀኑ ምዕመናን አንጋጠው ጣራ ጣራውን ይመለከታሉ ፡ የድካም ፡ የደስታ የቁጭት ብዙ ብዙ ዓይነት ስሜት በአዕምሮአቸው እየተመላለሰባቸው ። ዓለማየሁ ፈንጠር ብሎ ተነሣና የእሱን ትራስ ጨምሮ አንተራሳት ፡ አለበሳት። የሚያደርገውን አጣና ዝም ብሎ ቆመ ። ቴፑ ይዘፍናል ።

እሷስ እንኮይ ናት የአባይ ዳር ፡ እንኮይ ናት የአባይ ዳር
የማትሰለች ጣፋጭ ማር
እንኮይ ናት የአባይ ዳር
ጮማ ሞልቶላት ከእናቷ ቤት ሞልቶላት ከአባቷ ቤት
እንጀት በላች ወይ የእኛ እመቤት
በላች ወይ የእኛ እመቤት
ሆ…ሆ… የአባይ ዳር እንኮይ

“ዓለማየሁ ዓለማየሁ…” ተጣራች ሐረገወይን በገመምተኛ ሰው ድምፅ ዓይነት ። አንገቷን ቀና አድርጎ ተመለከታት ። “ውሃ ውሃ” አለችው እየቃሰተች ።

ያመጣላትን የብርጭቆ ውሃ ግጥም አድርጋ ጠጣችና ትኩር ብላ ተመለከተችው ፈገግ እያለች ።

“አልዩ አትቀየመኝም አይደል?”

“እንዴ… ለምን?”

“ዞሮ ዞሮ ያንተው ነው ብዬ ነው ፣ ማትሪክ ስለወደቅሁ ለአንተ ያዘጋጀሁልህ ሽልማት ነው ፣ በል ብቻህን ብር አምባር ሰበረልዎ እያልክ ጨፍር ...” ከትከት ብላ ሣቀች ። የሐረገወይን ከፍተኛ ስጦታ ፣ የዓለማየሁ ከፍተኛ ሽልማት ።

ሐረገወይን በዓለማየሁ ከፍተኛ ትትኮሳ ለሦስተኛ ጊዜ ሂሳብ ለመፈተን ካቴድራል ትምህርት ቤት ተመልሳ ገባች ። አዲሱ ዓመት ግን ለእርሷ የሚስማማ አልሆነላትም ። በሂሣብ ከመውደቋ ይበልጥ የሚያበሳጫት ፣ የሚያናድዳት ጉዳይ ገጠማት ። አንድ ቀን ቢሮዋ ቁጭ ብላ ስትሠራ ስልክ ይደወልላታል ። ወሰንየለህ ነበር ። ደውሎላት አያውቅም ፣ ሥራ ካስገባት ጊዜ ጀምሮም ያገኘችው ከሁለት ጊዜ አይበልጥም ፣ ያውም በመንገድ ላይ ። “አይዞሽ በርቺ” ብሎኣት ነበር ሁለት ጊዜም የተለያዩት ። ባለውለታዋ ነው ። ታከብረዋለች ።

ለብርቱ ጉዳይ እንደሚፈልጋት ከነገራት በኋላ ፣ በሰባት ሰዓት ቢሮዋ እንደሚመጣ ምሳ አብረው እንደሚበሉ አስታውቋት ስልኩን ዘጋ ። ብርቱው ጉዳይ ምን እንደሆነ ለመገመት ባትችልም ፣ መጠበቅና ከሰውዬው ጋር ምሳ መብላት እንዳለባት ወሰነች ። ወዲያውኑ ለዓለማየሁ ደውላ ምሳ እንዳይጠብቃት ሥራ ያስገባት ሰው ለብርቱ ጉዳይ እፈልግሻለሁ እንዳላትና በሰባት ሰዓትም እንደሚገናኙ ነገረችው ። ይተማመናሉ ፣ ያለችውን ሁሉ ተቀበላት ፣ ማታ ትምህርት ቤት እንደሚጠብቃት ተነጋግረው ስልኩን ዘጉ ።

ሰባት ሰዓት ላይ ወሰንየለህ ከሚልኪያስ ጋር ሆነው ወደ ሐረገወይን ቢሮ ሔዱ ። ሚልኪያስ መኪናው ውስጥ ቁጭ ብሎ ወሰንየለህ ከቢሮዋ ድረስ ሔዶ አመጣት ። የመኪናዋን የኋላ በር ከፈተና አስገባት ፣ ከሚልኪያስ ጋር አስተዋወቃት ።

ሚልኪያስ ብዙ ሴቶች ያውቃል ። እንዳውም “ፍቅር የማያውቅ ደነዝ ነው” እያሉ ነው የሚሰድቡት ። ሴትን ማድነቅ

አይወድም ፡ ግን ቶሎ በፍቅር ይወድቃል ፡ ቶሎም ይረሳዋል ። ኩራተኛ ነው ፡ በተለይ በሴቶች ላይ መኩራት ደስ ይለዋል ። ሐረገወይንን ሲመለከት ግን ያ ሁሉ ወኔው ከዳው ። እጇን ጨብጦ "ሚልኪያስ እባላለሁ" ሲላት መልኩ ሁሉ ልውጥውጥ ሲል ታወቃት ። እጇን ሲጨብጥ የኤሌክትሪክ ገመድ የጨበጠ ያህል ሰውነቱን ነዘረው ። ተቅበጠበጠ ።

ወሰንየለህ ይመለከታቸዋል በኩራት አቀማመጥ ተቀምጦ ። ሚልኪያስ ወዲያውኑ ስሟን ማቅላመጥ ጀመረ ። ሐረገወይን ሚልኪያስ እጇን ሲጨብጠው ፡ የአጨባበጡን ሁኔታና የመልኩን መለዋወጥ ስትመለከት "ማን ልበል" ብሏት ስሟን ስትነግረው እንዳልሰማ ሰው ሆኖ እጇን እንደጨበጠ "ማን…? ማን…?" እያለ እጇን ጠበቅ ያደረጋት ሁሉ ደስ አላላትም ። ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ባትሆንም ፡ እንዳች የጥርጣሬ ስሜት አደረባት ።

ሚልኪያስ መኪናውን እያከነፈ ሸቅብ ወጣና ዋቢሸበሌ ሆቴል ፊት ለፊት አቆመ ። ከመኪናው ወረደና የኋላበር ከፍቶ ሐረገወይን እንድትወርድ ጋበዛት ። ስትወርድ ትከሻዋን ያዝ አደረገና "ምሳ እኮ እዚህ ይሻላል ብዬ ነው" አላት ከውስጡ ያልወጣ ሣቅ እየሣቀ ።

ዋቢሸበሌ ሆቴል ገብተው ምሳ በሉ ። ሐረገወይን ምሳው አልጣማትም ። ሚልኪያስ ያሳያት የማያስፈልግ እንክብካቤ ሁሉ ቀፈፋት ። ኮካኮላ ይቀዳላታል ፡ ብርጭቆውን አንሥቶ ይሰጣታል ፡ የምግብ ሳህኗን ከፊቷ ቀረብ ራቅ ያደርግላታል ፡ መቀመጫ ወንበሯን አሥር ጊዜ ያስተካክልላታል ፡ በጐረሰች ቁጥር "እንዴት ነው ወደድሽው?" እያለ ይጠይቃታል ። ይህ ሁሉ አስጠላት ። ምሳ በልተው እንደጨረሱ ወሰንየለህ ሁለቱን በስፋት አስተዋወቃቸው ። ሚልኪያስን ውስጡንና ላዩን ሁሉ ያውቀዋል ። ሐረገወይንን ግን አያውቃትም ። ብዙ እንደሚያውቃት ሆኖ ሲናገር ታዘበችው ። ግን አልተቀየመችውም፡ ለእርሷ በማሰብ ሆኖ ተሰማት ።

"ሐረገወይን እንግዲህ ሚልኪያስን በደንብ ተዋወቂው ፡

የሚጠቅምሽ ሰው ነው ። የተስፉ የወንድና ሴት ልብሶች ከውጭ ሀገር እያስመጣ የሚያከፋፍል ኩባንያ ባለቤት ነው ። የኩባንያው ሥራ አስኪያጅም እሱ ራሱ ነው ። ስለ አንቺም ጉዳይ አንሥቼበት ደኅና ደመወዝ ያለው ቦታ ሲለቀቅ ከእኔው ጋር መጥታ ትሥራለች ብሎኛል ። አሁን ካለሽበት ቦታ በጣም የሚሻል ነው ፡ ትጠቀሚያ ለሽ ። አየሽ የአባትሽ ውለታ ስላለብኝ የእሳቸውን ውለታ በአንቺ በኩል መክፈል አለብኝ ሐረገወይን ፡ እና ከሚልኪያስ ጋር በደንብ ተዋወቂ ። ያንቺን ስልክ ስጭው ፡ የእሱንም አድራሻ ይሰጥሻል" አለና ወደ ሚልኪያስ ዞር አለ ።

"ስማ ቀላል ልጅ አትምሰልህ፡ ጌታ የጌታ ልጅ ናት ። በትምህርቷ በጣም ጎበዝ ፡ ሰው ቀና ብላ የማታይ ጠባይዋ ከመልኳ የበለጠ ሸጋ ነው ። እንግዲህ እኔን ሆነህ እርዳልኝ ፡ እንዳልኩህ አንተ ጋ ቦታ ሲገኝ ብታስገባት መልካም ነው ።" ሲናገር ከአፉ ፈጠን ፈጠን ይላል ፡ እጆቹን ያወራጫል ። ለሁለት ሰዎች ሳይሆን ብዙ ሰዎች በተሰበሰቡበት አዳራሽ ውስጥ መድረክ ላይ ወጥቶ የሚደሰኩር ይመስላል ።

ሐረገወይን ሐሳቧ ተምታታባት ። በአንድ በኩል ተጠራጠረች ፡ በአንድ በኩል የተሻለ ሥራ ላገኝ ይሆን? የሚል ተስፋ አደረባት ።

በመጡበት አኳኋን ተመልሰው ወደ ሐረገወይን መሥሪያ ቤት አመሩ ፡ ሚልኪያስ ከኪሱ አውጥቶ የአድራሻ ካርድ ሰጣትና ተሰነባብተው ተለያዩ ። ሐረገወይን ወደ ቢሮዋ ገባች ። ሚልኪያስና ወሰንየለህ ወደ ውጭ ወጡ ።

"ወሰንየለህ በእውነት ዛሬ ወንድ ወጥቶሃል ። አሪፍ ልጅ አይደለችም እንዴ እባክህ ። ሙት ሙት ዛሬ አስደስተኸኛል ። ከሥራህ ሁሉ ያረካኝ የዛሬው ሥራህ ነው ፡ ብራቮ... ብራቮ ወሰንየለህ" አለ ሚልኪያስ የደስታ ሲቃ እየተናነቀውና የጉሥኘት ከራ እየተፈተፈው ። ወሰንየለህ ልቡ ረካ ፡ ትልቅ ውለታ እንደዋለና ብዙም እንደሚጠቀምበት ገመተ ።

"ሚኪ… ስማ ልንገርህ" አለው ቶኝ እጁን ከመኪናዋ መቀመጫ መደገፊያ ላይ በረዥሙ ዘርግቶ ተዝናንቶ እየተቀመጠ ። "አንተ መቸስ ውሎህ ቢስ ነህ ፤ ደሞ አንተን ሳላስደስትህ የሞርኩበት ጊዜ አለ? ሙት ውሎህ ቢስ አትሁን ፤ ለማንኛውም ምርጥ ልጅ አስተዋውቄሀለሁ ፤ ከእንግዲህ እወቅበት ፤ መቸስ ለእኔ ይኸን አድርግልኝ አልልህም ፤ የልፋቴን ፤ አለ እያደል የወጣሁበት የወረድኩበት …" ከትከት ብሎ ሣቀ ፤ የውሸት ሣቅ ። ደሞ ቀጠለ ። "ስማ አባቶች ምን እንደሚሉ ታውቃለህ?…ፈረስ ያደርሳል እንጂ አያዋጋም…"

"ተው እባክህ እሱ የዱሮ ፈረስ ነው ፤ የዛሬው ፈረስ ያዋጋል" አቋረጠው ሚልኪያስ ። እየተገለፋፈጡ ሽቅብ ወደ ፒያሳ ከነፉ ።

ቀኖች እየተቆጠሩ አንዱ ሳምንት በሌላው እየተተካ ሲሔድ የሐረገወይን ጥርጣሬ እውን እየሆን መጣ ። ያም 'ብርቱ ጉዳይ' የተባለችበት ነገር እውነትም ብርቱ ሆነባት ።

ሌላ ቀን እንደዚሁ ምሳ አብሬቸው በላች ፤ ሦስተኛም ደገመች። አራተኛ አልሔደችም ፤ ሽሽት ጀመረች ። ወሰንየለህ በየጊዜው እየመጣ ይጨቀጭቃታል ፤ ሚልኪያስ በስልክ ይነዘንዛታል ። አስረዳቻቸው ፤ እሬሎኛ አለኝ አለቻቸው ፤ ግን ሊገባቸው አልቻለም ። ከዚያ ወዲህ ፈራቻቸው መሸሽ ጀመረች ። ግን ምሳ ተጋበዥ ትባላለች ፤ ሽርሽር እንውጣ ትባላለች ፤ እምቢ አለች ። ሸሸቻቸው ። መውጫ መግቢያ አጣች ። እቢት የምትልበት ቦታ አጣች ። ችግሯን ብቻዋን ለመቋቋም ወሰነች ። ለጓለማየሁም ደበቀችው ። ሐረገወይን የቢሮዋ ስልክ አስጠላት ። ስልኳ በጮኸች ቁጥር ልቧ አለቅጥ መምታት ይጀምራል ፤ ትሸበራለች ፤ አእምሮዋ ሰረናት ያጣል ። አንድ ጊዜ ከፊት ለፊቷ ያለችው ስልክ ጮኸች ፤ እየተጠራጠረች አነሣች ።

"ሀሎ ሐረገወይን እንደምን አለሽ?"

"ደኅና … ደኅና … ደኅና ነኝ" ማንነቱን አወቀችው ።

"ስሚ ዛሬ ምሳ አብረን ነን ፤ ቢሮሽ ድረስ እመጣለሁ ።"

"የለም አይመቸኝም ፤ ከጓደኞቼ ጋር ቀጠሮ ስላለኝ አይመቸኝም"

"ምን ዓይነት ቀጠሮ? ማለቴ ፤ ከወንድ ጓደኛ ወይስ ከሴት…"

ማቾ ። እሷ ተናደደች ። ማቹ የልብ ሳይሆን የጉራ ፤ የመኩፈስ የመብለጭለጭ ማቾ መሆኑ ገባት ። ሚፖቅ በጆሮዋ የሰማችው ድምፅ ጆሮዋን አሳመመው ። "ወራዳ" ብላ ስልኩን ብትዘጋው ደስ ባላት ፤ ግን ቻለችው ።

"እሱ እኮ የግል ጉዳይ ነው ፤ ምን ያደርግልዎታል" አለች ለጥቂት ጊዜ ዝም ካለች በኋላ ።

"ደሞ አንቱ ነው እንዴ የምባለው" አላት አሁንም እየማቀ ።

"ምን ክፋት አለው ፤ ባክብሮዎ እኮ ነው" አለች ነገሩ ገርሞአት። ሚልኪያስ ተናደደ ። ራሱን በዱላ የተመታ ያህል ተሰማው ።

"ግዴለም መከባበር በአንቱታ ብቻ አይደለም ፤ ከዛሬ ጀምሮ አንተ እንድትይኝ ፈቅጄልሻለሁ ፤ አንተ በይኝ" አለ በጐረነነ ትዕዛዛዊ ድምፅ ።

"እእ እንጃ…" ድምፁ ደክሞ አለ ።

"እንዴት እኔ እንጃ?"

"ሕሊናዬ የሚፈቅድልኝ አይመስለኝም" አለች በተሰላቸ ድምፅ ።

"ለማናቸውም በሰባት ሰዓት እንድትጠብቂኝ ።" ስልኩን ዘጋው ። ሐረገወይን በስድስት ሰዓት ወጥታ ጠፋች ። ከሰዓት በኋላም አልተመለሰችም ።

በማግሥቱ ሻሂ ጠጥታ ስትመለስ ስልኳ እየጮኸ አገኘችው ።

"ሀሎ ሀሎ" አለች ማን መሆኑን ለማወቅ እየጓጓች ።

"ሐሬ ታዲያስ ፤ ሽፈትሽ አይደለም ?"

"ማን ልበል ?" አለች የመቆጣት ያህል ሮሙኝ ። ማንነቱን አውቃለች ፡ ልታናንቀው ፈለገች ። ግን ልቧ ፈራ ።

"እንዴ ድምጼ ወፈረብሽ ወይስ ቀጠነብሽ ?"

"ዶክተሯ ስልኩን ልዘጋው ነው ማን ልበል" የበለጠ ተቆጣች።

"ሚልኪያስ ነኝ አሁንስ አወቅሽኝ ..." የምትሰጠው መልስ ቸገራት ።

"ዶክተሯ እርስዎ ነዎት ? ዝም ብለው እየደወሉ የሚያስቸግሩ ሰዎች አሉ ። ሥራ የሚያስፈቱ ፡ እነሱ መስለውኝ ነው ዶክተሯ" አለች በጣቶቿ ጸጉሯን እየነጨች ፡ በእግሯ የቆመችበትን ወለል እየደበደበች ።

"የቆንጆ ልጅ ጣጣ ነው አይዞሽ ። ምን ያደርጉኛል ብለሽ ነው አይዞሽ ። ስሚ ከሳምሶን ጋር ትናንት አብረን ነው ያመሸነው ፡ ጥሩ ሠራተኛ ነች ጐበዝ ነች ብሎኛል ። አድንቆሻል ። በእውነት እንዲህ ሲለኝ ኮራሁኝ ። 'የእኔ እኅት ሰነፍ ልትሆን አትችልም' ብዬ ዘነጥኩበት ። ስሚ ... የደመወዟንም ጉዳይ አስብበት ብየው ግዴለም ብሎኛል ፡ አይዞሽ" አለ ልጥጥ ባለ አነጋገር ።

ሐረገወይን ድምፁ አስጠላት ። ቶሎ ጨርሶ በተገላገለች ደስ ባላት ነበር ። በጆሮው ላይ ልትዘጋበት ፈለገች ። "ባለጌ" መባሉ ደሞ አስጠላት ።

"ዶክተሯ አንድ ጊዜ" ብላ ስልኩን አስቀመጠችና ዘላ ከቢሮዋ ወጣች ።

"ምን ቀን ነው ከዚህ ነዝናዛ ጋር ያገጣጠመኝ ። ምነው ሥራ ባልይዝ ቢቀርብኝ" ምርር ብላ አዘነች ። ወሰንየለህን በልቧ ረገመችው ። "አቀጣሪ ፡ ሴታሴት ርካሽ" ሰደበችው በልቧ ። ተመልሳ ወደቢሮዋ ገባችና ስልኩን አነሣች ።

"ዶክተሯ ለሥራ ተፈልጌ ...ነው" አለች በተሰላቸ ድምፅ።

"ይኸውልሽ...የደወልኩልሽ እንኳ ለቁምነገር ነው ። ከፈረን

ሳይ ጥሩ ጥሩ ሬዲሜድ የሴት ልብሶችና ጫማዎች አስመጥቻለሁ ። መጥተሽ መርጠሽ እንድትወስጂ ነው ። አየሽ የአንቺን ምርጫ ስለማላውቅ ነው ። አሁኑኑ መኪና እልክልሻለሁ ። የት ሔደች እንዳይሉሽም ለሥራ አስኪያጁ ለሳምሶን እደውልለታለሁ እሺ…” ስልኩን ዘጋው ።

ከሩብ ሰዓት በኋላ ተላላኪው አንድ ሰው አስከትሎ ቢሮዋ ገባና “እርስዎን የሚፈልግ እንግዳ ነው” አላት ። የተላከውን ሹፌር “ይቅርታ አይመቸኝም በላቸው” ብላ መለሰችው ።

ሌላ ጊዜ ደወለላት ፡ “ወደእኔ ኩባንያ በትልቅ ደመወዝ ላመጣሽ አስቤአለሁ ፡ ቃላት የምሥራች ፡ ምን ይስማሻል ?…” አነጋገሩ የዝንጣ ነበር ።

“በጣም አመሰግናለሁ ፡ በሚቀጥለው ዓመት ትምህርት ቤት ስለምገባ ፡ የያዝኩትንም ሥራ ለመልቀቅ እያሰብኩ ነው ፡ በጣም አመሰግናለሁ” አለችው ። ሚልኪያስ ያላሰበው ነገር ስለነበር ፡ ክው ብሎ ደነገጠ ። ተስፋው ሁሉ እየመነመነ የሔደ መስሎ ታየው። ተቆጣ ፡ ሰውነቱ ሁሉ ልውጥውጥ አለ ። “መለማመጥ በቃ” አለ በልቡ ። ሌላ ዘዴ ማውጠንጠን ጀመረ ፡ ፍቅርን በጉልበትና በገንዘብ የሚገባበትን ዘዴ ።

ሚልኪያስ ወሰንየለህን ጮኸበት ። ጩኸቱ የጤና አልነበረም። ዘዴ አያጣም ብሎ ስለሚያምንበት ስልት እንዲቀይስለት ነበር ። ፈረስ ሆኖ ጦር ሜዳ ማድረስ ብቻ ሳይሆን እንዲዋጋለት ። ወሰንየለህ ብዙ ጊዜም አልፈጀበት ፡ ስልት የሚለውን ስልት ለመቀየስ ። በአንድ በኩል እውነቱን ነበር ። “ይህች ልጅ ዕድል በሯን እንኳኩታ ስትገባ እንቢ ያለችበት ምክንያት አለ ፡ እጮኛ አለኝ ያለችው እውነቷን መሆን አለበት ፡ ካላትም ትወደዋለች ማለት ነው። ይህንን ለእኔ ተወው አጣራዋለሁ ፡ በሦስትና በአራት ቀን መርምሬ እደርስበታለሁ ኩሬ” አለው በኩራት ።

ሦስትና አራት ቀንም አልፈጀበት በሁለተኛው ቀን ጉዳዩን ደረሰበት ። ካቴድራል ትምህርት ቤት ሔደ ። መኪናውን ከሩቅ

አቁሞ ሲጠብቅ ቆየ ። ሐረገወይንን ዓለማየሁና ዛማኑኤል ተያይዘው ሲሔዱ አያቸው ። "ከሁለቱ አንዱ ጓደኛዋ ነው" ብሎ ጠረጠረ ።

ሐረገወይን ፍራቻ ስላደረባት እንደ ቀድሞው ዓለማየሁ ብቻ ሳይሆን ዛማኑኤልም ጠብቆ እቤቷ እንዲያደርሳት ካደረገች ቆይታለች ። ዓለማየሁንና ዛማኑኤልን ካስተዋወቀቻቸው በኋላ እጅግ የሚቀራረቡ ጓደኞች ሆነዋል ። ችግሯን በዝርዝር ለዛማኑኤል አስረድታዋለች ፤ ዓለማየሁ ለነገሩ ሁሉ ባዕድ ነው ። ምንም ዓይነት የሚጠራጠርበት ነገርም አላየም ። ወሰንየለህ በዐይኑ ሸኛቸውና ተመለሰ ። በማግሥቱ ሐረገወይን ከሥራ ስትወጣ በሩቅ ሆኖ ተከተላት ። ሠንጋ ተራ ገብታ ጠፋችበት ። ጠብቋት ፤ ስምንት ሰዓት ተኩል ላይ ከዓለማየሁ ጋር ተያይዘው ሲመጡ አያቸው ። ዓለማየሁና ሐረገወይን ተሰነባብተው ሲለያዩ ወሰንየለህ ዓለማየሁን ተከትሎ ሔደ ። ዓለማየሁ በታክሲ ፤ ወሰንየለህ በራሱ መኪና ። ዓለማየሁ ፒያሳ ወርዶ ቁልቁል ወደመሥሪያ ቤቱ በእግሩ ሲሔድ ተከተለው ። ወሰንየለህ የሚያውቀው መሥሪያ ቤት ነው ። ብዙ ወዳጆች አሉት ። የሚወዱት የሚፈሩት ብዙ ወዳጆች አሉት ። በየቢሮው ሲገባ ቆየና ወጥቶ ሔደ ። ለሚልኪያስ የምሥራቹን ነገረው ።

ሌላ ስልት መቀየስ ነበረባቸው ። ሚልኪያስ ሐረገወይንን አጥብቆ እንዳፈቀራት ፤ እልህ እንደያዘው ፤ እልኸኛ ሴትም እንደሚወድ ፤ ደስ እንደሚለው በቀድሞው ትዕዛዛዊ አነጋገር ሳይሆን በሚያሳዝንና በመለማመጥ መልክ ወሰንየለህ ተአምር እንዲፈጥር ለመነው ። ወሰንየለህ እንዲህ እንዲህ ዓይነት ነገር ደስ ይለዋል ። ሲለመን ይኮራል ። ተለምኖም ይሁን ፤ ታዞ አንድ ነገር ባደረገ ቁጥርም ይጠቀማል ። "የልፋቴን ዋጋ" የሚለው ፈሊጥ አለው ። ቀድሞም ሐረገወይንን ሥራ ሲያስገባ ውበቷን አድንቆ "ቆይ አንድ ቀን ሥራ እያገባብሻለሁ ብሎ" ፎክሮ ነበር ። ወሰንየለህ የሚልኪያስን ሁኔታ ሲመለከት በአንድ በኩል ፍራቻ በሌላ በኩል ደስታ ተሰማው ። ብዙ አወጣ አወረደ ። አባቷን ለመጠየቅ ወሰነ ።

"ስማ ሚኪ." አለው ቁጭ ብለው ሚልኪያስ ቢራ ሲጠጡ ።

"እየሀ ልጅቷ እምቢ ብትልም ፤ ተስፋ ሳይቆርጡ ማባበል ያስፈልጋል ። ያንን ማስከዳት ያስፈልጋል ። አለ አይደለም ማማላት ማፋረስ...እሱን ዘዴ መጠቀም ። ይኸ አንዱ ዘዴ ነው ። ግን እንደነገርኩህ እሷ እንደ ዘመኑ ልጅ አይደለችም ፤ የቤት ልጅ ናት ። ቤተሰቦቿን በጣም ትፈራለች ። እና በምንም በምንም እሷን እየተለማመጡ በሌላ በኩል አባቷን መጠየቅ ያስፈልጋል ። እሱን ለእኔ ተወው ። እሳት የላሱ ሰዎች አሉ እነሱን ይዤ እሔዳለሁ ። አባቷን ውሃ ነው የማደርጋቸው ። እሱን ለእኔ ተወው" አለው ።

ወሰንየለህ የሐረገወይንን አባት ፈልጎ አገኛቸው ። ለብርቱ ጉዳይ ቤታቸው ድረስ እንደሚመጣ ነግሮአቸው ተቀጣጥረው ተለያዩ ። ወንዲራድ ሐረገወይንን ሊጠይቀኝ ነው የሚል ጥርጣሬ አልነበራቸውም። ወሰንየለህን የሚያውቁት በጉዳይ አስፈጻሚነት ፤ በነገር አማላጅነት ነው ፤ "ደሞ ምን ፍጠር ሊለኝ ነው" ሲሉ ዋሉ አደሩ ።

ወሰንየለህ በቀጠራቸው ዕለት ከሁለት ሌሎች ሰዎች ጋር ሆኖ ወደ ወንዲራድ ቤት ሔደ ። በመልካም መስተንግዶ ተቀበሉአቸው። ወንዲራድ የጠበቁት ነገር ባይሆንም ፤ አልገረማቸውም ። እንዲሁም ደስ አላቸው ። መክሬ መልሱን እሰጣለሁ ብለው የአሥራ አምስት ቀን ቀጠሮ ሰጡና እንግዶቹን ሸኙ ።

በሳምንቱ ወንዲራድ ባለቤታቸውን ወይዘሮ ተዋበችን ፤ ነፍስ አባታቸውን አለቃ መዘምርን ከግራና ከቀኝ አስቀምጠው ሐረገወይንን አስጠሯት ። በዝርዝር ጉዳዩን ካስረዷት በኋላ ፤ የእነሱን ፈቃድ እንድትፈጽም ጠየቋት ፤ እምቢ አለች ። አለቃ ብዙ ምሳሌና ጥቅስ እያወረዱ ተቆጧት ፤ "እምቢ" አለች ። አባቷ ለእርሷ ሲሉ ያደረጉትን ሁሉ እያስታወሱ አታዋርጂኝ ብለው ለመኗት ፤ ተቆጧት ፤ እምቢ አለች ። ያን ዕለት አስተያየት ያልሰጡ ዝም ብለው ሁሉንም ሲታዘቡ የቆዩ ወይዘሮ ተዋበች ብቻ ነበሩ ። ሐረገወይን ምርር ብላ እያለቀሰች ተናገረች ፤ የሚሰማት አላገኘ

ትም። ተቆጥታ በሩን በርግዳ ወጣች ።

ሳምንት እንግዶቹ በአንድ ወገን ፡ ወንዲራድ አሊቃና ተቀበች በሌላ ወገን ሆነው ሲደራደሩ ቆዩና ተለያዩ ።

“በእኛ በኩል ፈቅደናል ፡ ትንሽ እቢ ናት ያንገራገረችብን እንቆጣለን ግዴለም” አሉ አሊቃ የሚወዱትን ጠጅ እየተጐነጩ ። ወንዲራድ የአሊቃ አነጋገር ደስ አላላቸውም ። የልጅቷ ፈቃድ ባይኖሣ ፈቃዳቸው ነበር።

“አሊቃ ደሞ ዝምብለው ነው ፡ የልጅ ቁጣና የጀበና ቱማታ አንድ ነው ቶሎ ብርድ እሚል ። ደሞ የእሷን ቁምነገር ብለው ያወራሉ” አሉ እየተቆጡ ።

ወሰንየለህና ሁለቱ እንግዶች ከወንዲራድ ቤት ሲወጡ እየፈነደቁ ነበር ። ማታ ሚልኪያስ ቤት ግማሽ ሠርግ ያህል ተደግሶ ሲበላ ሲጠጣ ተመሸ ።

የወንዲራድ ቤተሰብ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ተረበሸ ። ወንዲራድ ትንሽ ትልቁን አኩረፉ ። ሐረገወይንን በየዕለቱ ይጨቀጭቁአታል ። የምትበገር ሆና አላገኙአትም ። እሷን ትተው ልጂን ያበላሽ ዛማኑኤል ነው ብለው እገላለሁ አሉ ። ጠሉት ፡ የባለቤታቸውን እኅት ልጅ ። ማታ ማታ ሳሎን ቁጭ ብለው አብረኸኝ ብላ አጫውተኝ የሚሉትን ዛማኑኤልን በዐይናቸው ለማየት አስጠላቸው ። በልጃቸው በሐረገወይን ቂም ያዙ ፡ ከራሳቸው ልጅ ጋር እልህ ተያያዙ ።

ወሰንየለህ የዋዛ ሰው አይደለም ፡ እያሳደደ ስለሚልኪያስ ጌትነት ፡ ስለጠባዩ ፡ ስለ ገንዘቡ ብዛት ይተርክላቸዋል ። አንድ ቀንም አብሮ ምሳ ጋብዟቸዋል ። ሚልኪያስ የሚልክላቸውን ስጦታ ያደርስላቸዋል ።ወንዲራድ ደግሞ የእንግሊዝ ካፖርት ፡ የእንግሊዝ ባርኔጣ ይወዳሉ ። ይሉኝታ ጥፍር አድርጐ ያዛቸው ፡ በገዛ ቤታቸው አመፁ ፡ በገዛ ቤተሰባቸው ላይ ሸፈቱ ። ሐረገወይንን በዐይነ ቁራኛ ይከታተሉ ጀመር ፡ የት ዋልሽ የት አመሸሽ አበዙ ንዝንዝ ። የሚወዱት ሳሎናቸው አስጠላቸው ፡ ሐኪም የከለከላቸውን መጠጥ

ጀመሩ ፡ ሥራ ውለው የትም አምሽተው ይመጡና ቀጥታ መኝታ ቤታቸው ይገባሉ ፡ አልጋቸው ላይ ሆነው ራት ያዛሉ ።

ሐረገወይን ጭንቀቷ እየበረታ ሲሔድ ብቻዋን ልትጨነቅ አልፈለገችም ። ከአክስቷ ልጅ ከዛማኑኤል ጋር ሆነው ዝርዝር አድርገው አወሩት ለዓለማየሁ ። ዓለማየሁ የመጨነቅ ምልክት አላሳየም ። ነገሩን አናናቀና ተወው ። "ምን ይሆናል ብለሽ" ይላል ጉዳዩ በተነሣ ቁጥር ። ወሰንየለህንና ሚልኪያስን አሳየችው ፡ አወቃቸው ። የድብብቆሽ ጨዋታ ተጀመረ ። እየሁህ ፡ አላየሁህ የትልልቅ ሰዎች ድብብቆሽ ጨዋታ…ሲያስጠላ ።

ሐረገወይን መለስ ብላ ዛሬ 1963ትን እንደሴት እንዳሳለፈችው ስታስታውስ ዝብርቅርቅ ይልባታል ። መልኩ ዥጉርጉር ይልባታል።

አዲሱ ዓመት እንኳ አላስከፋትም ። ያን የማይወጡት ተራራ ወጣችው ፡ ያን የማይፈነቀሉት ጋሬጣ ፈነቀለችው ። ሂሣብ ተንበረከከላት ፡ አለፈች ። ግን ደስታዋ ሙሉ ደስታ አልነበረም ። እንዳዘነችበት እንዳለቀሰችበት በሣቅ በደስታ በፌሽታ መልሳ ብትቀልድበት ፡ ብታፌዝበት ደስ ባላት ፡ ግን አልሆነላትም ። ዛማኑኤል እሷና ዓለማየሁ ተማክረው ትምህርቷን ማታ ማታ እንድትቀጥል ተስማምተው ዩኒቨርስቲ ተመዝግባለች ። የድብብቆሹን ጨዋታም ተያይዛዋለች ። በየዕለቱ እየተጨነቀች ፡ ሰውንም እያስጨነቀች ፡ ገላጋይ አጥታ ። ከወር ወር ያሻለዋል እያለች በጋውን ዘልቃ ክረምቱን አልፋ መስከረም ደረሰች ፡

ሐምሌ ድንጋይ ይዟል ሰው ሊገድልላችሁ
ናሴ ሰይፍ መዟል ሰው ሊገድልላችሁ
መስከረም ጦር ይዟል ሰው ሊገድልላችሁ
አትገላግሉም ወይ ያላችሁ ያላችሁ ።

*

ምዕራፍ አራት

የወንዲራድ ታናሽ ወንድም ኃይለማርያም በሻህ ቀጠንና ረዘም ያሉ ሰው ናቸው ። ከወደ ጀርባቸው በዛ ብሎ የበቀለው ሽበታቸው ዐልፎ ዐልፎ ከሚታየው ጥቁር ጸጉራቸው ጋር ተቀላቅሎ ደማቅ ውበት ሰጥቶአቸዋል። አፍንጫቸውን ከበ አገጫቸው ሲደርስ ፡ ወደታች የሚንዠረገገው ገብስማ ጺማቸው በየሁለት ቀኑ እየተስተካከለ ፡ በእንክብካቤ የተያዘ ችግኝ ይመስላል ። ከአፍንጫቸው ሥር ያለውን ሪዛቸውን ዳርና ዳሩን እስረዝመውት በየደቂቃው ያፍተለትሉታል ። ግራ እጃቸው ከእሱ ላይ አይነቀልም። ያፍተለትሉ ያፍተለትሉና አሹለው ይለቁታል ። አንድ ጊዜ በግራ ፡ አንድ ጊዜ በቀኝ በኩል ያለውን ሪዛቸውን ያፍተለትላሉ ፡ ግራ እጃቸውን እያመላለሱ ።

ኃይለማርያም በብዙ መሥሪያ ቤቶች ሠርተዋል። በፈረንሳይ የኢትዮጵያ የትምህርት አታሼ ሆነውም አገልግለዋል ። ከቤተሰባቸው ውስጥ ተማሩ የሚባሉት እሳቸው ናቸው ። የፍልስፍናና የታሪክ መጻሕፍትን ማንበብ ይወዳሉ ። በእግራቸው መሔድ ይወዳሉ ፡ ከሥራ ወጥተው ቤታቸው ይሔዳሉ ። ጥቂት አርፈው ከቤታቸው ይነሡና ጃንሜዳን ይዞራሉ ፡ በስድስት ኪሎ ታጥፈው ቁልቁል ወደ አፍንጮ በር ይወርዳሉ ፡ አቀበቱን ወጥተው ጊዮርጊስ ይደርሱና ይመለሳሉ ። ታዲያ በእግራቸው ሲዞሩ የሚያውቃቸው ሰው እንዲያገኛቸው ፡ ካገኛቸውም አቁሞ እንዲያወራቸው አይፈልጉም ። አይወዱም ፡ የእግር ጉዞአቸውን የሚያሰናክልባቸው ። ስለ አነበቡት መጽሐፍ መጽሔትና ጋዜጣ ከሰው ጋር መወያየት ይወዳሉ ። አንዳንድ ሰው በዚህ ባሕሪያቸው ይወዳቸዋል ። አንዳንዱ ይሸሻቸዋል ። ማታ ማታ ቁጭ ብለው መጻፍ ይወዳሉ ። የሚጽፏቸው ነገሮች አንድም ጊዜ ታትመው አያውቁም ። ይጽፉ ይጽፉና

ለራሳቸው እንብበሙት ይተኛሉ ። ጧት ወደ መሥሪያ ቤታቸው ሲሔዱ ላገኙት ሰው ሁሉ ያንን ማታ የጻፉትን ላንብብ ይላሉ ።

አንዳንዱ ይደሰትበታል ፤ አንዳንዱ እንዳይቀየሙኝ ብሎ የይስሙላ ጆሮውን ጣል አድርጎ ያዳምጣቸዋል ። አንዳንዶች "የአራዳው ሸክስፒር" እያሉ ያሾሟጥጧቸዋል ። ኃይለማርያም ሚስት አግብተው አያውቁም ፤ ልጅም የላቸው ። ዕድሜ ልካቸውን የኖሩት በሠራተኛ ነው ። ወንድማቸው ወንዲራድ ብዙ ጊዜ ጨቅጭቀዋቸዋል ፤ አግባ እያሉ ። ኃይለማርያም ግን ሞገደኛ ሰው ናቸው።

ኃይለማርያም በሻህ የዓመት እረፍት ወስደው ቤታቸው መዋል ከጀመሩ ጥቂት ቀናት አልፈዋል ። የብዙ ዓመታት ጓደኛቸው ዘረያዕቆብ ቤት ድረስ እየመጡ ያጫውቷቸዋል ። የኃይለማርያም ቤት ሳሎን ፈረስ ያስጋልባል የሚባለው ዓይነት ነው። የሳሎኑ ግድግዳ በልዩ ልዩ ፎቶግራፎች ጥቅሶችና ሥዕሎች አጊጧል ። ከዋናው በር በላይ ባለው ግድግዳ ጋሻና ጦር ተሰቅሏል ። በልዩ ጌጥ ከተሠራ ሸክላ ውስጥ በቅሎ በአራቱም ማዕዘን የሳሎኑን ግድግዳ የከበበው ሐረግ ለቤቱ ግርማ ሞገስ ሰጥቶታል ። ኃይለማርያም አበባ መትከል ፤ መኮትኮት ውሃ ማጠጣት ይወዳሉ ። እንደ ልጅ አድርገው ይንከባከቡታል ።

ኃይለማርያምና ዘረያዕቆብ ሳሎን ውስጥ ተቀምጠው ይጫወታሉ ። በመኻላቸው ባለችው አነስተኛ ጠረጴዛ ሁለት ብርጭቆዎችና አንድ ወይን የተሞላበት ጠርሙስ አለ ። አንድ ጠርሙስ ጨርሰው ሁለተኛውን አቅርባ ሠራተኛቸው መመለሷ ነበር ። ሁለቱ ጓደኞች ቀደም ሲል በጀመሩት ውይይት ከመግባባት ይልቅ ወደ መጣላቱ በማዘንበላቸው ዘረያዕቆብ ፤

"ተወው በቃ የማይናገረውን ወይናችንን እንጠጣ 'ወይን ያስተፌስህ ልበሰብ …' ተብሎ የለም" ብለው ብርጭቆአቸውን አንሥተው ከተጉነጩ ወዲህ፥ ሁለቱም የመከራከሪያ ያህል ተፋጠው ተቀምጠዋል ። ኃይለማርያም ከአዲሱ ጠርሙስ በሁለቱም ብርጭቆ

ዎች ተዳና ጺማቸውን ማሾል ጀመሩ ። ዘረያዕቆብ ትክ ብለው ይመለከቱአቸዋል ።

“እየው ዘረያዕቆብ አልሰማኸኝም ነው እኮ እምልህ ፤ ከሁሉም መደማመጥ አይበልጥም ? ለአባባሉ ትክክለኛነት ይኸው አንተው ራስህ እኮ ምስክር ሆንክ ። አመል ሆኖብህ ትዕግሥት ትዕግሥት ትላለህ እንጂ ውሸትህ እኮ ነው ! ራስህ መቼ ታውቀውና፣ ሳታጣጥም ቱግ ትላለህ...ክፉ አመል ። ይኸው እኮ ነው መብለጭለጭ እንወዳለን ፤ ከሥራ ለአቃቂር እንቸኩላለን ፤ ሰውን በሠራው ሥራ ከማድነቅ ይልቅ ባጠፋው ለመኮነን እንጣደፋለን ··· ክፉ አመል ። ታዲያስ ምን ላይ ነው ስሕተቱ ፤ አንተ እኮ ዝም ብለህ ነው ቱግ ያልከው...እንደማመጥ አልኩህ” አሉ ከረር አድርገው ጺማቸውን እያፍተለተሉ ።

“ልክ ነው ኃይሉ ፤ ይኸን እኮ አልካድኩህም ፤ እኔ የተቃወምኩህ ሁሉንም በጅምላ አትኮንን ፤ ሁሉንም በጅምላ ጥፋተኛ አታድርግ ብዬ ነው ። እርግጥ ነው አንተ የምትላቸው ሰዎች ዓይነት ሞልተዋል ፤ እንዴ መቸስ ከስንዴ ውስጥ እንክርዳድ አይጠፋ ። የዚያን ያህል እኮ ነው ። ይኸ ደሞ በእኛ ማኅበረሰብ ብቻ ሳይሆን በማናቸውም ስልጡን በሚባል ሕዝብ ዘንድም ያለ ነው ። ይኸን ነው የጠላሁብህ ፤ ሁሉንም በጅምላ ጥፋተኛ አታድርግ ፤ በጥቂቶች ጥፋት ሁሉንም አትጥላ አትወንጅል ነው ያልኩህ ። እየው ‘መጥፎ ሰው እንዳላይ ብለህ ዐይንህን አትጨፍን ፤ ጥሩው ሰው ሲያልፍ ሳታይ ያመልጥሀል’ ይባላል...”

“ጥሩ ብለሃል ፤ ጥሩ ብለሀል” አቋረጧቸው ኃይለማርያም ፤ በግራ እጃቸው ጣቶች ጢማቸውን ጉንጉኑና ብርጭቆአቸውን አነሡ ። ለሀመል ያህል ቀመስ አድርገው መልሰው አስቀመጡት ። ቀና አሉና ጉሮሮአቸውን ጠራረጉ ።

“እየው ጥሩ ብለሀል ያልኩህ አጥቦ ጭቃ ስለሆነብኝ ነው ። ቅድምም ያልከው እኮ ይኸንኑ ነው ። ያልተስማማነውም በዚህ ነው። በዚህ ሁሉንም በጅምላ በምትለው ነገር እኮ ነው የማልስማ

ማው ። እየው ነገሩ እኮ የሥልጣኔ ፡ የትምህርት ፡ የመመራመር ፡ የማወቅ ፡ ጉዳይ ነው ። እሱን እኮ ነው የምልህ ተማርን የምንለው ፡ ተሌላው ትንሽ ሻል አልን የምንለው ፡ አወቅን የምንለው እኮ ነን ጥፋተኞቹ ። ያማ ምኑን ያውቀዋል፡ ለመተቸት ፡ ለመንቀፍ ለመቃወምም እኮ ቢያንስ ጥራዝ ነጠቅ መሆን ያስፈልጋል ። እንግዲህ የተማረውንም ያልተማረውንም ወገን አንድ ላይ አድርጌ በመኻል በዳር ያለውን ሕዝብ ሁሉ አካትቼ በጅምላ ከተናገርኩ እንዳልከው ስህተት ነው ፡ ግን ይህን ያልኩ አይመስለኝም ። ለዚህ ነው ተሳስተሀል የምልህ ። እርግጥ አወቅን ተምንለው መኻል ውስጥም ዐልፎ ዐልፎ ለመድኃኒት ያህል የምትለው ዓይነት ሰው አይጠፋም ። ታዲያ እሱ እንክርዳድ ውስጥ እንደተገኘ ስንዴ ይቆጠራል...ይኸው ነው እኮ ! ስንዴ ውስጥ የተገኘ እንክርዳድ እየተለቀመ እንደሚጣል ሁሉ እሱም ከሌላው መኻል ተለቅሞ ይጣላል ፡ ይኸው ነው..."

"ጥሩ…ጥሩ አሁን ራስህ አመጣኸው ፡ እንዳልከው ይለቀምም ይጣልም የሚመሰገን ፡ ከሌላው የሚሻል እንደሌላው ለትችት ለአቃቂር የማይቸኩል የበሰለ ሰው አለ ማለት ነው ። ይኸውልህ ራስህ እኮ አመጣኸው ። ታዲያስ እሱንስ አብረህ ለምን ትወቅሰዋለህ? ነው የምልህ ፡ ለይ! በጅምላ ሁሉንም አትወንጅል ማለቴ ለይህ ነው ። አሁን የተግባባን መሰለኝ ። መቸኮል ምን ያረጋል ፡ ትዕግሥት ይኑርህ ነው እምልህ ።"

"የለም ፡ የለም ፡ አልተግባባንም ፡ ወዴት ወዴት? አየህ እንዲህ ዓይነቶቹ አንድ ሁለት ብለህ በጣት የምትቆጥራቸው ሰዎች እኮ በጠባቡ አንዱን ከአንዱ ጋር ለማነጣጠር እነሱ ከነሱ ይሻላል ፡ እንቶኔ ከእንቶኔ ይበልጣል ለማለት ካልሆነ በቀር ፡ ስለሀገር ፡ ስለ ሕዝብ በሰፊው ስናወራ እኮ መለኪያ ሊሆን አይችልም ። ስንዴ በቁና ሰፍረህ አፊትህ አስቀምጠህ እውስጡ እንክርዳድ መኖሩን ብታውቅም እኮ ፡ ያው ስንዴ ነው እንጂ ሌላ አትለው ። እንክርዳዱንም ዐልፎ ዐልፎ ስንዴ ብታይበትም እምትጠራው ያው

እንክርዳድ ብለህ ነው ፡ ይኸው ነው።"

"ይኸውልህ ጓዴ… እኔ መቸም የዚህ ሁሉ ዋንኛ ምክንያት አስተዳደጋችን ይመስለኛል ፡ ባህልና ወጋችን ይመስለኛል ። እኛ እኮ ታሪክን ፡ ፍልስፍናን ፡ ኪነጥበባትንና ሊትሬቱርን እየተማርን አይደለም ያደግነው ። አብዛኞቻችን ከብት ስናግድ ፡ ማዕረግ ያለውም ቢባል ጉግሥ መግጠም ፡ ጦር እንጣጥር መወርወር ፡ ገበጣና ሰንጠረዥ መጫወትን ነው… እየተማርን ያደግነው ። ታዲያ ተፈረንጁ ሥልጣኔ ጋር አለመስተካከላችን ፡ እዚሁ እኛም ውስጥ ብስል ተቀሊል ሆነን ለመገኘታችን ምክንያቱ ይኸው ይመስለኛል ። እንጣደፋለን ፡ እንቸኩላለን ፡ ትዕግሥት የለንም ። ስንቸኩል ደሞ እናጠፋለን"

"አዎ ልክ ነህ ። ግን የዘነጋኸውም አንድ ነገር አለ ። መቸስ እንደ ፈረንጁ ሆነን ለምን አላደግን አንልም ። እንለያያለን…እንለያያለን ። እኛ እኮ ያቃተን መሆን የሌለብንን ፈረንጆችን መሆን ሳይሆን በእውነቱ ራሳችንን መሆን እኮ ነው ያቃተን ። የራሳችንን ባህል ፡ የራሳችንን ወግ አሳድገን የሥልጣኔ ወግና ባህል ማድረግ እኮ ነው ያቃተን ። ክፉ ዐመል ። እየው ረሳኸው ያልኩህ ፡ ተረቱን ነው ፡ ተረትና ምሳሌውን ። አባቶቻችን 'ተረት ተረት የላም በረት' ብለው ብልጠትን በጦጣ ፡ ተንኮልን በቀበሮ ፡ የዋህነትን በበግ ፡ ጅላጅልነትን በአህያ ፡ ጀግንነትን በአንበሳ ፡ ቁጡነትን በነብር ፡ እየመሰሉ ሲተርቱልን ኖረናል ፡ ሲያስተምሩን ፡ ታዲያ የተረቶቹን ምሳሌነት ዐውቀን መርምረን ከእኛ ሕይወት ፡ ከዘመኑ ሥልጣኔ ጋር እያጣጣምን ትምህርት እንድንቀስምበት ፡ የጥንቱን ከዛሬው ጋር አዋህደን አዲስ ነገር እንድንፈጥርበት ፡ እኛም ለልጆቻችን የእኛን ዘመን ተረት እንድናበጅ እንጂ ዝንተዓለም እነሱ የነገሩንን እንድንደግም አይደለም ። ይህ ተሆነ ሥልጣኔ የለም ፡ ሕይወት አንድ ቦታ ትረጋለች ። እንደ ኩሬ ውሃ አንድ ቦታ ተቋጥራ ትቀራለች ። የእኛ ጥፋት ይኸ ነው… ራሳችንን መሆን አለመቻል ፡ ክፉ ዐመል ።"

"ልክ ነህ ልክ ነህ" አሉ ዘረያዕቆብ በማድነቅ ራሳቸውን

እየነቀነቁ ፡

"እየሀ ዘረያዕቆብ የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ራስን ማወቅ ነው ። ራስህን ካላወቅህ አካባቢህንና ሌሎችንም ማወቅ አትችልም ። ራስህን ካላወቅህ ከሰዎች ጋር ትጋጫለህ ፡ ከዓለም ጋር ትጋጫለህ ፡ ከራስህ ጋር ትጋጫለህ ። ከሁሉም የከፋው ግጭት ደግሞ ከራስ ጋር መጋጨት ነው ። እኛን እኮ የሚገድለን መብለጭለጭ ነው ። ከሌሎች በታች የሚያደርገን እኮ ራስን ባለማወቅ ነው ። መኮፈስ ፡ መብለጭለጭ እንወዳለን ። ባዶ ምድር ላይ እንውረገረጋለን ፡ ምን ተይዞ ጉዞ ። ሌሎች ሚሠሩ ቁጭ ብለን ተመልክተን ሲጨርሱ እንተቻቻቸዋለን ፡ ተስፋ እናስቆርጣቸዋለን ። ክፉ በመል ። መኮፈስ ምን ይጠቅማል ፡ ማጥላላትስ ምን ያደርጋል ። ውስጡን ለቁስ ሆነን ብንብለጨለጭ የት ያደርሰናል ። ተብለጭልጨን አምረን በመታ የት ብቻ ሥልጡን መባልን እንወዳለን ። አዳፋ ልብሳችንን አውጥተን ጥለን እንብለጨለጫለን ። ልብስ ቢዐዳ የጭንቅላት እድፍ አይጠራ ። ጅል ልማድ ። ላይ ላዩን አምሮ ውስጡን ማደፍ ። ክፉ በመል" ብድግ አሉ ከመቀመጫቸው ወደ መስኮቱ ጠጋ አሉና ወደ ውጭ ማዳመጥ ያዙ ።

"እንቺ… ማነሽ ብርቱካን! ብርቱካን! የውጭ በር ይንኳኳል ክፈቺ" ተጣሩ ሠራተኛቸውን ፡ መልሰው ወደ መቀመጫቸው ሔዱና ብርጭቆአቸውን አነሡ ።

ወዲያው የሳሎኑ በር ተከፈተ ። ዛማኑኤል የሳሎኑን በር ፀለፈና አንገቱን ዝቅ አድርጎ ሰላምታ ሰጠ። ራመድ ራመድ እያለ ኃይለማርያምን ተጠጋና ጨበጣቸው ፡ ዘረያዕቆብንም ጨበጠና ቆመ እጁን እያሸ ። ፊቱ ላይ ከእፍረት የመነጨ ፈገግታ/ጉልህ ሆኖ ይነበባል ።

"ቁጭ በል ፡ ቁጭ በል እንጂ" አሉ ፡ ኃይለማርያም ወደ ሶፋው በእጃቸው እያመለከቱት ። "እኔ እምልህ ለመሆኑ ቤቱን ማን አሳየህ ልጄ ፡ እኔማ ተመልሰህ እዚያው ጎንደር የገባህ መስሎኝ ነበር ።"

"የለም እዚሁ ነኝ" አለ ዛማኑኤል አሁንም ፈገግ እያለ ።

"የለም የለም ታዲያ አዲስ አበባ ውስጥ የተቀመጠ ሰው ዘመድ እንዳይጠይቅ ዐዋጅ ወጣ እንዴ ፤ አንተው ትሻል ነበር ፤ አንተንም አበላሹህ?… ዘረያዕቆብ በል ተዋወቀው ፤ የወንድሜ ባለቤት እኅት ልጅ ነው ።"

ዛማኑኤል ከመቀመጫው ተነሥቶ ዘረያዕቆብን ጨበጠና ተመልሶ ቁጭ አለ ።

"መቸም ዛሬ የመጣኸው ብርቱ ጉዳይ ብትይዝ ነው ፤ ምነው ወንድሜ ደኅና አይደለም እንዴ?… የጠና ሰው ብቅ ሲል እኮ ያስደነግጣል ፤ መርዶ ይዘህብኝ እንዳትመጣ ብዬ ነው"… ኃይለማርያም የራሳቸው አባባል አሣቃቸው ። ሳቃቸውን ሲጨርሱ ቀጠሉ ወጋቸውን ።

"ይኸውላችሁ መቸስ ጨዋታን ጨዋታ አይደለም የሚያመጣው ? ታላቁ እስክንድር ሆሜርን አጥብቆ ይወደው ፤ ያደንቀው ነበር ይባላል ። አንድ ቀን ከጄኔራሎቹ ጋር ቁጭ ብሎ ሲጫወት አሽከሩ እየሮጠ እያለከለከ ወደ እሱ ሲመጣ ይመለከተዋል ። ታላቁ እስክንድር ግርም ብሎት ፤ ከጐኑ የተሰበሰቡትን ጄኔራሎች የሰውየውን አኳኋን ፤ አሯሯጥ አሳያቸውና 'ይኸ ሰው ሆሜር ከመቃብር ተነሣ ብሎ ሊነግረኝ ካልሆነ በቀር እንዲህ የሚያስሮጠው በዓለም ላይ ምንም ምክንያት የለም' አለ ይባላል ። ታዲያ እሱም እኮ ጠፍቶ ከርሞ ድንገት ብቅ ሲል ጊዜ አስደንግጦኝ ነው ።" ሣቁ ፤ በአሣሣቃቸው አይዞህ ስቀልድ ነው የሚሉ ይመስላል ።

"የለም እኔ ልጠይቅዎ ነው የመጣሁት ፤ የጠና ሰው መቸስ በሕይወት እስካለ ብቅ ማለቱ አይቀር ። ሐረገወይን እረፍት ላይ ነው፤ ቤት ነው የሚውለው ብላኝ እንግዲህ ቢቆጡኝም ይቆጡኝ ዛሬ ወንድ ይውጣኝ ሒጂ ልጠይቃቸው ብዬ ነው የመጣሁት" አለ ዛማኑኤል እግሩን በእግሩ ላይ እያነባበረና ከቀድሞው ይበልጥ ፈገግ እያለ ። ሠራተኛዋ ብርጭቆ አምጥታ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠችና ወጣች።

"የዛሬ ልጆች እኮ የእኛን መጠጥ ታናንቁታላችሁ ። ምን እያላችሁ ነው የምትጠሩት? ባለ ኪሻ ፡ ግንበኛ ፡ ምን እያላችሁ ታሬክሱታላችሁ የተከበረ መጠጣችንን ፡ ትወይ የለም እንዴ? ነው ወይን ጥሩ ነው ቅመሰው"... ኃይለማርያም ጠርሙሱን አንሥተው ቀዱ ። ብርጭቆቸውን ወደ ዓማኑኤል ጠጋ አደረጉ ።

"ይኸውልህ የሽማግሌ ነገር የሚሔድበት የለው አይደለም ቁጭ ብለን እንሚጠጣለን ። የባጥ የቆጡን እያነሳን እንተቻለን ። ዘረያዕቆብ አንተና እኔም እኮ ከምንወቅሳቸው ሰዎች አንሻልም ። ይኸው ሰውን በመተቸት ፡ ሌላውን በመውቀስ ላይ አይደለንም? ታዲያስ ምን እምንሻልበት ጉዳይ አለ? " አሉ ወደ ዘረያዕቆብ እየተመለከቱ ።

"አየ ኃይሌ ደሞ ይኸን አመጣህ ? ትችት ይቅር ያለ የለ ! እኛ እኮ የወቀስን ሥራን ጠልተው የሌላውን ሥራ የሚያናንቁትን ፡ ከመሥራት ይልቅ ቁጭ ብለው ማውራትን የሚመርጡትን ፡ ሳያውቁ እንዳወቁ ፡ ሳይሆኑ እንደሆኑ ፡ ሳይሰለጥኑ እንደ ሰለጠኑ አድርገው ራሳቸውን የሚቆጥሩትን ነው ። አይደለም እንዴ? አንተ እና እኔ ደግሞ ሠርተን ሠርተን በማረፊያችን ቁጭ ብለን ብንጫወት፡ የማኅበረሰባችንን ክፉና ደግ ብናነሣ ምን ያስከፋል? ያስከፋል እንዴ ወዳጄ" አሉ ዘረያዕቆብ ፊታቸውን ወደ ዓማኑኤል አዙረው እሱንም በውይይቱ ለመጋበዝ እየፈለጉ ።

ዓማኑኤል የመጣበትን ጉዳይ ለኃይለማርያም ለመንገር ፈራ። ኃይለማርያም ከጓደኞቻቸው ጋር የያዙትን ጨዋታ ላለማቋረጥ ቢያቋርጥም ሁለቱ ብቻ ሊነጋገሩበት የሚገባውን ምስጢር ከኃይለማርያም ጓደኛ ለመደበቅ ኃይለማርያም ብቻቸውን እስኪሆኑለት ድረስ ማቆየት ፈለገ ። በሌላ በኩል ሐረገወይን የላከችው ጉዳይ አጣዳፊ በመሆኑ ዝም ብሎ መቆየቱ አሳሰበው ። የእሱ ፍላጎት እንደገባ ጉዳዩን አስረድቶ ለመውጣት ነበር ፡ አልሆነለትም ። በውይይቱ ለመሳተፍና መጨረሻውን ለማየት ወሰነ ።

"የለም አያስከፋም" አለ ዛማኑኤል በእጁ ይዞት የነበረውን ብርጭቆ እያስቀመጠ ። "አያስከፋም ፡ ውይይት እኮ አንዱ የዕውቀት ማግኛ ዘዴ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊ የአዕምሮ ምግብም ነው። ትችት እኮ እናንተ እንደምትሉት የሌላውን ሥራ ለማራከስ ፡ ሌላውን ለማጣጣል ካልሆነ በቀር አንዱ የሥልጣኔ መወጣጫ ነው ። ትችት ትክክለኛ ከሆነ ለዕድገት ጠቃሚ ብቻ ሳይሆን የግድ የሚያስፈልግ ነው ። ውይይታችሁ ጥሩ ነው ። የሰው ልጅ እኮ አእምሮውን አሳርሮ እያዝናና ስለ ሐዘን ፡ ስለ ፍቅር ፡ ስለ ጀግንነት ፡ ስለ ስህተቱና ስለውጤቱ በአጠቃላይ ስለ ሕይወት ካልተወያየ ፡ ካልተመራመረ ደስታ እኮ ሊኖረው አይችልም ።"

"ልክ ነህ ዛማኑኤል ፡ ሙሉ በሙሉ እደግፈሃለሁ ፤ ዛሬ ያለንበት ዘመን እኮ ሰው በልቶና ጠጥቶ በማደሩ ብቻ እፎይ የሚልበት ዘመን አይደለም ። ዘመኑ የሥልጣኔና የማወቅ ፡ የመመራመር ዘመን ነው ። የቀድሞውን ጅላጅል ዘመን ብዙ ብዙ ትተነው መጥተናል ። ዛሬ የሰው ልጅ የሚወደውን የማግኘት ፡ የጠላውን የማጥፋት ፡ ሲደክም የዋለ አእምሮውን የማዝናናት ፡ ፍላጎቱ ከመቸውም ጊዜ የበለጠ ነው ። ለሆዱ የሚሆነውን ለመፍጠር የሚደክመውን ያህል ለአዕምሮው ምግብ የሚሆነውን ለማግኘት እኮ ይደክማል ። ዛሬ በቀን ውስጥ ያሉትን ሐያ አራት ሰዓቶች ለሦስት እኩል ከፍለን ስምንት የሥራ ሰዓት ፡ ስምንት የመዝናናት ፡ ስምንት የዕንቅልፍ ሰዓት የምንለው እኮ እኛ ስለጠንን የምንለው ነው ። የዋሻው ሰው እማ መች ይሆን አውቆት ! እኛ ለሦስት እኩል ከፍለነዋል ፡ የእኛ ልጆችና የልጅ ልጆች ደግሞ አሥራ ሁለት የመዝናናት ፡ ስድስት የሥራ ፡ ስድስት የዕንቅልፍ ሳይሉ ይቀራሉ? አይመስልህም ዛማኑኤል" አሉ ኃይለማርያም የቀኝ በኩል ሹል ጢማቸውን ጥብቅ አድርገው እያፍተለተሉ ።

ዛማኑኤል ያሰበው ነገር ራሱን አማተው ።

"ልክ ነዎት ትናንት እጅግ ጠባብ የነበረው የሰው ልጅ አዕምሮ፡ ከቆመበት ምድር እጅግም ርቆ የማይሔድ የነበረው

አስተሳሰቡ ዓለምንና በጥቅሉ ሕይወትን መመርመር ሲጀምር እንደ ውቅያኖስ ሰፍቷል ። ማን የሚያሳዝነው ፡ ዛሬም በዚህ በሰለጠነው ዓለም ከአፍንጫቸው አርቀው የማያስቡ መሰሎቻቸው ነው ። ነጩን ነጭ ማለት የሚያቅታቸው ፡ ጥቁሩን ጥቁር ማለት የሚጠሉ ሞልተዋል እኮ ! ታዲያ እነዚህን ምን እንላቸዋለን ...”

“እነሱንማ ምን እንላቸዋለን ፡ በሐያኛው ምዕተ ዓመት የሚኖሩ የዘመኑ ዋሻ ሰዎች ናቸዋ ! ያለ ስማቸው ስም እንሰጣቸው” አቋረጡት ኃይለማርያም ።

ዓማኑኤል ሐሳቡን ተናግሮ ባይጨርስም፣ ኃይለማርያም ስላቋረጡት ሊጨምር ያሰበውን ተወና ትኩር ብሎ ይመለከታቸው ጀመር ፡ ቀጠሉ ኃይለማርያም ።

“ይገርማል ዓማኑኤል··· ይኸውልህ ወደ ዋናው ጨዋታችን መጣህ ፡ ይህንኑ ነበር እኛም እምንጫወተው ። ‘አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ’ አይደለም እንዴ ከነተረቱ ። ይኸው እኮ ነው መብለጭለጭ እንወዳለን ማንነታችንን ዘንግተን የማናውቀውን ለመሆን እንጥራለን ። እራሳችንን ለመሆን እንፈራለን ። ይኸ እኮ ነው የእኛ ችግር ፡ በዘር ፡ በጎሳ ፡ በትውልድ ፡ በአምቻ በጋብቻ ተቆላልፈን ሌላውን እያራከስን ፡ ሌላውን እየወነጀልን እንኮፈሳለን። ክፉ ዐመል ። ታዲያ እንደግ ስንል በየት አርገን ፡ እንራመድ ስንል በየት አርገን ፡ ዙሪያው ገደል ይሆንብናል ። በገዛ እጃችን ማሰሪያ ገመዳችንን እናሳጥራለን ። ይኸውልህ በዚህ ላይ ነበር ውይይታችን ። አጠቃላይ ማኅበረሰባችንን እየገመገምን ነበር የመጣኸው ። እስቲ እንግዲህ አንተም ሐሳብህን አክል አድርግበት ፡ የእኔ አባባል ምን ነበር መሰለህ ከሥራ ይልቅ ለአጥፊ ትችት እንሽቀዳደማለን ፡ ከማመስገን ይልቅ መውቀስን እናዘወትራለን ፡ ምንም ሳናውቅ ብዙ ያወቅን እየመሰለን እናጠፋለን ፡ ከእኔ ወዲያ ለአሳር ስለምንል ሌላውን እንንቃለን ፡ ታዲያ ዋናው በሽታችን ይኸ ነው ፡ ራስን ያለማወቅ ወረርሽኝ ፡ ራስን ለመሆን ያለመፈለግ ፡ ያለመቻል ፡ መድኃኒት የሌለው ወረርሽኝ ። ክፉ ዐመል ። እንግዲህ

ነበር የተባባልነው ። እርግጥ ነው ፤ ሁሉም መቸስ አንድ ነው ሊባል አይገባም ፤ ከእንከርዳድ መኻል አንዳንድ ስንዴ እንደማይጠፋ ሁሉ በዋቄ ፤ ተመራማሪ ፤ አሳቢ አርቆ ተመልካች ይኖራል ። ታዲያ ይኸም ቢሆን በሽንብራ ማሳ ውስጥ ብቻውን እንደ በቀለ ዛፍ ከየትም ሆኖ ይታያል ፤ ዐይን ያርፍበታል ፤ እንደ ሰርዶ ተመሆም ይጣላል ። በላ እስቲ ያንተስ ሐሳብ ምንድ ነው ?'' ዛማኑኤል ላይ አፈጠጡበት ፤ ሲናገሩ ብድግ ቁጭ ይላሉ ። ይቁነጠንጣሉ ። አስተያየታቸውና ቃላት አጠራረታቸው ዛማኑኤልን ለውይይት ለመጋበዝ ሳይሆን ንዴቻቸውን "ይኸውልህ ተረታህ" በማለት ክስ የሚያቀርቡ ያስመስላቸዋል ። ብርጭቆአቸውን አንሥተው በረዥሙ ተጎነጩለት ። እግራቸውን አነባበሩና ዛማኑኤልን አፈጠጡበት ። "ልክ ነህ በሉኝ እንጂ" የሚል መስሎ ታየው ።

"ትክክል ናችሁ ፤ ይህ አንዱ አራሽ አንዱ አሳራሽ ፤ አንዱ ጌታ ሌላው ሎሌ ፤ በሆነበት ጥቂቶች ማይሠሩ ቂጥ ብለው በሚበሉበት አብዛኛው ግን ደጋግ አሳላፊና የበይ ተመልካች በሆነበት ማኅበረ ሰብ ሊደርስ የሚችል ጉዳይ ነው ። እንዲህ ባለውና ማባት ማግኘት ሳይሠሩ መክበር ፤ ማስነው ከንቱ መቅረት ጉልተው በሚታይበት ማኅበረሰብ ጥቂቶች መብለጥለጣቸው ያለ ነው ፤ የሚሆን የሚደርስ ጉዳይ ነው ፤ አዲስ አይደለም ። እንዲህ ዓይነቱ ማኅበረሰብ አዲስና አሮጌ አስተሳሰብ በየደቂቃው በየሰዓቱና በየቀኑ የሚናቆሩበት ፤ የሚፋጩበትና ጦር የሚማዘዙበት ነው ። በዚህ ግብግብ አዲሱ ለማሸነፍ ፤ አሮጌም ላለመሸነፍ በሚያደርጉት መፋጨርጨር ብዙዎቻችን ልንጎዳ እንችላለን ።

"በአጠቃላይ ከእንዲህ ዓይነቱ የእኩልነት ጭላንጭል ከማይታይበት ከጥቂት ጌቶች ቀንበር ለመላቀቅ ተማርን የሚሉት ፤ እኩልነትን የሚናፍቁ ወገኖች ሁሉ መንቀሳቀስ አለባቸው ። ቀድሞም ትችት መሰንዘር ጠቃሚ ነው ያልኩት በዚህ ምክንያት ነው ። ይህ ካልሆነ ላለው ይጨመርለታል እንደሚባለው አንጋር የዘር ሐረግ እየቆጠሩ ፤ ሥጋና አጥንት እየመረጡ ሌላውን የሚንቁት ፤

ሌላውን የሚያንቋሽሹት መብለጭለጫቸው ፣ ሳያውቁ በወትን ማለታቸው ፣ ትክክል እየመሰላቸው ይሔዱና የበለጠ ችግር ውስጥ ይከቱናል ። ታዲያ እናንተ እኮ አታውቁትም ፣ እናንተም እኮ እንደኛው ናችሁ! ሀገራችን እኮ የሁላችን ናት! እኛ ባረስን ፣ እኛ በደከምን ለምን እናንተ ትደልባላችሁ ፣ አርሥን ሠርተን ባበላን ባጠግን ባጐረስን ምነውሳ ጣታችን መንከሱ ? ብሎ የሚቀጣቸው የሚገስፃቸው ያስፈልጋል ። ሥራ የሚሠራው እንዳሉት በዘር ፣ በጐሳ ፣ በዘመድ ፣ በአምቻ በጋብቻ ከሆነ ነገር ተበላሸ ማለት ነው ። እማኞቹ የማይመሰክሩ ፣ ዳኞቹ የማይፈርዱ ፣ ጠበቆቹ የማይሞግቱ ፣ ጸሐፊቱ የማይጽፉ ከሆነ ማኅበረሰቡ ሊያድግ አይችልም ። ይኸው ነው ።

“ሕዝቡን ንቀውና ረግጠው እንደ አልቅት የተጣበቁበትን መሳፍንትና መኳንንት ከራሱ ላይ ማውረድ አለበት ። ይህን ካላደረገ ስለ እኩልነት ፣ ስለ ፍትህ ፣ ስለ ዕድገት ሊያወራም አይችል። ይህን ካላደረገ ፍርድ ተጓደለብኝ ፣ ጠማኝ ፣ ራበኝ ፣ በገዛ ሀገሬ እንደ ባዕድ ታየሁ ብሎ ሊያማርር አይገባም … ብቻ ዝርዝር ውስጥ ከገባን ብዙ ነው… እንዘልቀውም… ልሳሳትም እችላለሁ …”

ዛማኑኤል ራሱ በተናገረው ቃል ያፈረ መሰለ ። ከኃይለማርያም ጋር የሚቀራረብ ቢሆንም ፣ እንዲህ ደፍሮ መናገሩ መልሶ አስደነገጠው። ኃይለማርያም እንደ ወንድማቸው እንደ ወንዲራድ ማትር ፣ ወግ አጥባቂ በዘመድ በሥጋ ፣ በአጥንትና ደም አጥብቀው የማያምኑ መሆኑን ቢረዳም ፣ መሳፍንቱና መኳንንቱ ከሕዝቡ ራስ ላይ ይውረዱ ብሎ የተናገረው ስቅጥጥ አደረገው ። ፈራ ፣ ብዙም ሊቀጥል አልፈለገም። ምላሱ ተሳሰረበት ፣ የሚናገራቸው ቃላት አልጥም አሉት ፣ ተጠራጠረና ብርጭቆውን እንሥቶ በግራ እጁ መዳፍ ላይ አስቀመጠና በቀኝ እጁ ያሽከረክረው ጀመረ ። ካቀረቀረበት ቀና ሲል ከኃይለማርያም ጋር ዐይን ለዐይን ተገጣጠሙ ። እንደ ሕፃን ልጅ ተሽኮረመመ ። ስጋቱ ከአክብሮት የመነጨ ሆኖ አጉል ጭንቀት ለቀቀበት እንጂ ኃይለማርያም በአነጋገሩ አልተከፉም ። እንዳውም ደገፉት ።

ዘረያዕቆብ ግን ፡ አነጋገሩ የድፍረት ሆኖ አስቆጣቸው ። ከወዳጃቸው ከኃይለማርያም ጋር ጥሩ ጨዋታ ይዘው በመኻል መጥቶ ስላደፈረሰባቸው ተቆጡ ። ሰውነታቸው ሁሉ ተለዋወጠ ። ጅማታቸው ፡ ፊታቸው ላይ አፍጥጦ ቁጣቸውን ገለጠባቸው ፡ ተቆጡ ። ሰውነታቸው ሁሉ ተለዋወጠ ። ማጅራታቸውን አሳባቸው ። “ወጠጤ ፡ አትራዘለል ፡ የእርጉም ዝንብ… የዛሬ ዘመን ልጆች ትልልቅ ሰው ሲጫወት ደርሳችሁ ጥልቅ ትላላችሁ ። ስድ ፡ ስድ አደግ… ውጣ” ብለው ከጎናቸው ባስቀመጡት ከዘራ ራሱን በበጠረቁት ደስ ባላቸው ነበር ። ግን “እሰው ቤት አልዋረድም” ብለው ተውት ። በአንድ በኩል ኃይለማርያምን ፈሩ ። ቁጣቸው ከፊታቸው ላይ እየተነበበባቸው አኩርፈው ተቀመጡ ። ኃይለማርያም ግን የዛማኑኤል አነጋገር ጥሞአቸው ራሳቸውን በድጋፍ ሲያወዛውዙ ቆዩና፡-

“ልክ ነህ ሪቮሊሲዮን ያስፈልጋል ። የቄሳርን ለቄሳር እንዲሉ ሰውን አበላልጦ የማያይ ጥሩውን ጥሩ ፡ መጥፎውን መጥፎ ለማለት የሚችል በሰው ልጅ እኩልነት የሚያምን አድሚኒስትራሲዮን ያስፈልጋል ። አየህ ፈረንሳዮች አንድ የተለመደ አባባል አላቸው ። ‘ትልልቆቹ ትልልቅ የሚመስሉን ቁጭ ብለን ስለምናያቸው ነው… እንነሣ’ ይላሉ ። በእውነቱ ጥሩ አባባል ነው ። እኒህ እንደ ሐምሌ ደመና ተቆልለው ከሩቅ ትልቅ የሚመስሉን ቀረብ ብለን ስላላየናቸው ነው። ጉም ናችሁ የምትተኑ ልንላቸው ይገባል ። እንዳልከው የሚቆጣቸው የሚያርማቸው ያስፈልጋል ። በእውነቱ ሪቮሊሲዮን ያስፈልጋል ። የአስተሳሰብ የአተያይ ሪቮሊሲዮን ያስፈልጋል ። በአሮጌ ሰውነት አዲስ ልብስ ላጥልቅህ ቢሉት እኮ ያስቸግራል ። በእውነቱ መሆን ያለበት ይኸው ነው ። የአስተሳሰብ የአተያይ ሪቮሊሲዮን ያሻናል ። እንደ ካሮት ወደ መሬት የሚያድግ አስተሳሰባችንን ልንለውጥ ይገባል ። ጥሩ ብለሃል ዛማኑኤል ። ግን አንድ ያልተረዳኸው ጉዳይ አለ ። ምን መሰለህ ልንቆጣቸው ፡ ልንመክራቸው ፡ ልክ አይደላችሁም ልንላቸው ይገባል ብለሃል ፡ ጥሩ አባባል

ነው ። ግን ማን ነው የሚላቸው ፡ የእኛ ሰው ይቅርታ አድርጉልኝና ግልፅ እኮ አይደለም ፡ በእውነት ግልፅ እኮ አይደለም ፡ የራሱን ደናግ በሰው ቂጥ ለመፍሳት የሚፈልገው እኮ ብዙ ነው…” ኃይለማርያም የራሳቸው አባባል አሣቃቸው ። ሲሥቁ ሳላቸው ተነሣባቸውና ክፉኛ አርገፈገፋቸው ። ዘረያዕቆብ ሲመለከቷቸው ቆዩና ሳሉ በቀላሉ የማይለቃቸው መሆኑን ሲያውቁ እየሮጡ ወደ ወጥ ቤት ሔዱ ። በብርጭቆ ውሃ ይዘው ተመለሱ ።

“ግጥም አርግና ጠጣበት ፡ ግጥም አርገው” አሉ ።

ኃይለማርያም ውሃውን ከተጐነጩ በኋላ የእፎይታ ምልክት ታየባቸው ። ወደ ኋላቸው ልጥጥ ብለው ቆዩና ቀና አሉ ። ዛማኑኤል ሰዓቱን ይመለከታል ። በእሱ ቤት ‘ቸኩያለሁ መሔዴ ነው’ የሚል መልእክት ማስተላለፉ ነበር ። ኃይለማርያም አልተመለከቱትም ። በቤቱ ውስጥ ለጥቂት ጊዜ ጸጥታ ሰፈነ ። ኃይለማርያም ከተቀመጡበት ተንሥተው በሰፊው ሳሎናቸው ጥቂት ተንጎራደዱና ተመልሰው ቁጭ አሉ ። የእፎይታ ስሜት ከፊታቸው ይነበባል ። በቤቱ ውስጥ መልሶ ጸጥታ ሰፈነና ቆየ ።

“አቶ ኃይለማርያም የመጣሁበት አንድ ጉዳይ ነበር ። ጨዋታ ይዘን እንዳልረሳው ብዬ ነው“ አለ ዛማኑኤል ሲፈራ ሲቸር ቆየና ።

“ታዲያ ንገረና ምናለ ፡ ምንድነው ጉዳይህ”

ዛማኑኤል አቀርቅሮ ቆየና ሁለቱን ጓደኞች በየተራ ተመለከታቸው ። “ምስጢር ነው እንዴት ይሻላል?” ለማለት ነበር ። ግን ሁለቱም አልተረዱለትም ።

“ምንድነው? ምን ችግር አለ ንገረን” ኃይለማርያም ጮህ ብለው ተናገሩ ።

“የለም ትንሽ የቤተሰብ ጉዳይ ነበር” አለና ዘረያዕቆብን ተመለከታቸው ። ዘረያዕቆብ ከአሁን አሁን ይናገራል ብለው ትኩር ብለው ይመለከቱታል ። የሚናገረውን ለመስማት የጓጉ ይመስላሉ ። ያበሳጫቸውና ያልጣማቸው ውይይት ተቋርጦ የቤተ

ስብ ጉዳይ በማንሣቱ ተደስተዋል ።

ኃይለማርያም ለአፍታ ብዙ ሐሳብ ተመላለሰባቸው ። ወንድማቸውን አሰቡ ፡ “ከባለቤቱ ጋር ተጣልቶ ይሆን? መቸስ የእኔ ወንድም ጉደኛ ነው ፡ ደሞ ተእንዷ የደቀላትን አምጥቶ አሳድጊ ብሏት ተጋጭተው ይሆን”… ብዙ ብዙ ነገር በሐሳባቸው አወጡ አወረዱ ።

“ንገረና ፡ ‘ኢ ፕሮብሌም ዌል ስቴትድ ኢዝ ኢ ፕሮብሌም ሀፍ ሶልቭድ’ አይደለም እንዴ የምትሉት ። ምንድነው ችግሩ እስኪ አስረዳኝ”… ኃይለማርያም እጃቸውን አጣጥፉና የዛማኑኤልን ዐይን ይመለከቱ ጀመር ።

ዛማኑኤል ያሰበው ሊሳካለትና ለኃይለማርያም ብቻ ለመናገር አልቻለም ። ለሁለቱም ለመናገር ወሰነ ፡ ግን ከየት ጀምሮ የት እንደሚጨርስ ተምታታበት ። አንድ ዐረፍተ ነገር ይናገርና ‘የለም የለም ከሥሩ ብጀምርላችሁ ይሻላል’ ብሎ ያቋርጠዋል ። ከሥር ከሚለው ይጀምርና ድብልቅልቅ ይልበታል ። ከመኻል ይጀምርና ያቋርጣል ። በሚገባ ማስረዳት አቃተው ። ኃይለማርያም ነገሩ ቶሎ ገባቸው ። ብዙ ጥያቄዎች ጠየቁት ፡ ለጥያቄዎቹ ትክክለኛና ተገቢ መልስ ሰጠ ። ማወቅ ያሰቡትን ሁሉ እያከታተሉ ጠየቁት ፡ መለሰላቸው ። ታሪኩን ከዳር እስከዳር ተረዱት ። ዛማኑኤል ካስረዳና ለተጠየቀው መልስ ከሰጠ በኋላ ፡

“እና ይኸውልዎ ፡ ግሬ ሲገባት ጊዜ እስኪ ሒድና ለአጎቴ አማክረው ስትለኝ ጊዜ ነው አመጣጤ ። ልጁን እየተጋገዙ እንዳያጠቁት ፡ በፍርድ ቤትም እንዳያስወስኑበት ስለፈራች ነው ። ደሞ ይገርምዎታል ፡ እንዴት ዓይነት ጨዋ ፡ ሰው አክባሪ ልጅ መሰለዎት!” ብሎ በሐዘን ፊቱን ኩምትር አድርጎ አቀረቀረ ።

ኃይለማርያም የሚናገሩት አልነበራቸውም ። ከፊት ለፊታቸው የተቀመጡትን ዘረያዕቆብንና ዛማኑኤልን በየተራ ሲመለከቱ ቆዩና በረዥሙ ተንፍሰው ወደ ኋላቸው ለጠጥ አሉ ። የሐሳብ ገመድ ይገምዱ ጀመር ።

“አቤት! አቤት! እንዴት ዓይነቱ ዘመን ላይ ደረስን? ልጅ አባቱን የማይቀበልበት ዘመን ፡ ልጅ አባቱን የሚከስበት የሚያዋርድበት ዘመን! አቤት… አቤት”… አሉ ዘረያዕቆብ ። እጃቸውን እያወራጩና ወደ ጣራው እያንጋጠጡ ።

“የለም… የለም ዘረያዕቆብ እንደእሱ አትበል ፡ እስከአሁን እኮ ስንፈጨው የቆየነው ጉዳይ ነው ። በእውነቱ እኛ እኮ በልጆቻችን ዘመን የምንኖር ፍጡሮች ነን ። የሚያስገርመው ግን በእነሱ ዘመን እየኖርን እነርሱን መምሰል አለመቻላችን ነው ። ክፉ ሀመል ። እኛ የሆንነውን ሁሉ ሁኑ ፡ እኛ ያደረግነውን ሁሉ አድርጉ ካልናቸውማ ምኑን ከእኛ ተሻሉት ፡ ምኑን ሰለጠኑት”… ኃይለማርያም ተቆጡ ።

“ተው ኃይለማርያም ፡ ሥልጣኔ እንዲህ ከሆነ በአፍንጫችን ይውጣ ፡ መቸስ አባት እኮ ዞሮ ዞሮ አባት ነው ። ለልጁ የሚጠቅመውን እንጂ የሚጎዳውን አያደርግም ። ይኸን መቸስ አሌ አትለኝም ። ያምራል ብለው ከተናገሩት ይከፋል ብለው የተውት ይሻላል ፡ ይኸን ሥልጣኔ ብለህ አታውራው ። አባት ልጁን ለፈለገው ቢሰጥ ሰው መርጦ ቢድር ምን ክፋት አለው? አያት ቅድመአያቶቻችን ሲያደርጉት የኖረ እንጂ አዲስ ነገር አይደል ። ተው ይኸን ሥልጣኔ አትበለው ።” ዘረያዕቆብም ተቆጡ ።

ዛማኑኤል ‘የጭቅጭቁ አቅጣጫ ደስ አላለውም ። መጀመሪያውንም የፈራው ነገር በመሆኑ ነገሩ የተበላሸበት ያህል ቆጠረው ። ዘረያዕቆብ ጉዳዩን የተሳሳተ አቅጣጫ ስላሲያዙበት ተቆጣ ፡ መልኩ ሁሉ ልውጥውጥ ሲል ታወቀው ።

“ዛማኑኤል ፡ አይዞህ በእኔ ወንድም ልጅ የተነሣ ዳግመኛ የትሮይ ጦርነት አይቀሰቀስም ፡ እሚሆን እሚሆነውን እናያደርጋለን ፡ የሚመክረውን እንመክራለን ፡ የምንቆጣውን እንቆጣለን ። ካስ ምርጫጥማ ምን በወጣት ። እይ የእኔ ወንድም! ጭገዶኛ ሰው እኮ ነው፡ እንዳልከው ገታራ ሰው ነው ፡ በዚህ የሚመለስ አይመስለኝም፡ የለም የለም ልጁን ያጠፋዋል…” ድንገት ብድግ አሉ ኃይለማር

ያም። እንደቆሙ ቀበቶአቸውን አስተካክለው ታጠቁና መልሰው ቁጭ አሉ ። ዛማኑኤል ቁጣው እየበረደ የፈለገው እየደረሰ ሲሔድ ተሰማው ።

"ምን መሰለዎ አቶ ኃይለማርያም እኔን እጅግ ያሳሰበኝ የሐረገወይን ጭንቀት ነው ። በእውነት ቢያዩአት እጅግ ያዝኑላታል። 'ምንም ያላጠፋ ልጅ ምክንያት ሆኜ አሳሰርኩ' እያለች የአእምሮ ዕረፍት አጥታለች ። ይኸም ብቻ አይደለም ፣ መቸም ያባቷን ጠባይ ስለምታውቅ ነገ ከነገ ወዲያ የሚሆነው ሁሉ ያሳስባታል ፣ ቶሎ ብሎ አንድ ነገር ማድረግ..."

"ባባትና በልጅ መኻል መግባትም አያስፈልግ በእውነት" ዘረያዕቆብ አቋረጡት "የባዕድ ጠብ አይል ። ያውስ ይህ መች ጠብ ይባላል ። ትዕግሥት አድርጉ...ዋናው ትዕግሥት ነው ። መኻል መግባት ያካርረዋል እንጂ ምንም አይጠቅምም ። እኔ ልምከራችሁ... አባትም ሲበቃቸው ይመለሳሉ ፣ ልጅም ትጸጸታለች ፣ ያንን በትዕግሥት መጠበቅ ነው" ከዘራቸውን አነሡና አገጫቸውን እጀታው ላይ አስመርኩዘው ዛማኑኤልን ትክ ብለው ተመለከቱት ።

"የለም ምን መሰለዎት ፣ ትዕግሥት የሚሉት ጥሩ ነው ፣ ግን ጊዜ ጊዜ አለው ፣ ችግር ላይ ወድቆ ትዕግሥት ትዕግሥት ማለት ሞትን ከመጋበዝ ውጭ ሊሆን አይችልም ። ችግሩን ሊፈታው ቢችል ደስ ባለን ነበር ፣ ግን አይፈታውም ፣ እሷንም ከጭንቀት ልጁንም ከእስር ቤት ሊገላግል አይችልም ። እንዲህ አይደለም እንዴ አቶ ኃይለማርያም ?" ዛማኑኤል ለጥያቄው የአዎንታ መልስ በመፈለግ ዐይኑን በማስተዛዘን እያቁለጨለጨ ወደ ኃይለማርያም ተመለከተ ።

"አዎ ! ለምኑ ነው ትዕግሥቱ ? እኔ ወንድሜን ዐውቀው የለም፣ በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ አሉ ! እሱ መች ይኸን ይወድና ገና ሰው አፈጃለሁ ነው የሚለው ፣ እኔ ወንድሜን መቼ አጣሁት ! ታዋርዱኛላችሁ ይላል እንጂ ራሱን የሚያዋርድ እኮ ራሱ ነው ! ያልተገነዘበው ነገር ቢኖር ይህንኑ ነው..." ኃይለማርያም ብስጭታ

ቸው አልለቀቃቸውም ።

“መቸም አንድ ነገር ማድረግ እንዳለብን ይታየኛል” አለ ዛማኑኤል ድምፁን ለስለስ አድርጎ ። “እኔ በእውነቱ ይች ልጅ ፍላጐቷ መማር ነው ፡ የትዳር ሐሳብም አላየሁባት ። በመጀመሪያ ያለ ፍላጐቷ አግቢ ልትባል አይገባም ፡ ብታገባም እሷ የመረጠችውን እንጂ ሌላ ሰው የመረጠላትን እሷ የማትፈልገውን መሆን የለበትም ። ቅድም እንደ ተናገርኩት እኔ ከሁሉም ይበልጥ የሚያሳስበኝ እሷ ይህንን ወይንም ሌላውን ማግባቷ ሳይሆን በዚህ የተነሣ የአዕምሮ ዕረፍት ማጣቷና ጭንቀቷ ነው ። ይህ ደግሞ ክፉ ችግር ላይ፡ በሽታ ላይ ሊጥላት ይችላል ። ያን ጊዜ አባቷም ሆኑ ሁላችንም ከፍተኛ ጸጸት ያድርብናል ። ከወዲሁ አንድ ነገር ማድረግ አለብን ፡ ትዕግሥት ብለን ቁጭ የምንል ከሆነ ያን የምንፈራውን ጸጸት መጋበዝ ይሆንብናል ።

“ጭንቀት ቀስ በቀስ እያመነመነ በቁመና የሚገድል ትልቅ ደዌ ነው ። በየሰኮንዱ ፡ በየደቂቃው አዕምሮን የሚያቆስል ከባድ በትር ነው ። አንድ ያነበብኩት መጽሐፍ ትዝ ይለኛል ። በጥንታዊ ቻይና የጦር አበጋዞች የጦር ምርኮኞቻቸውን የሚያሰቃዩበት አንድ ዘዴ ነበራቸው ። መጀመሪያ እግርና እጃቸውን ጥፍር አድርገው ያስሯቸውና ያስቀምጧቸዋል ፡ በአናታቸው ትክክል ውሃ በማሰሮ ያንጠለጥሉና ውሃው ቀስ በቀስ ጠብ ጠብ እንዲል ያደርጋሉ ፡ ጭንቅላታቸው ላይ ያ ውሃ ቀን ተሌሊት ጠብ ጠብ ይልባቸዋል ። የውሃው ጠብታ እያደር በፋስ ራሳቸውን የሚመቱ ያህል ያማቸዋል፡ ይዘገንናቸዋል ፡ ቀስ በቀስም አዕምሮአቸውን ያስታቸዋል ። ጭንቀትም እንዲሁ ነው ። ዕንቅልፍን እየነሣ የአዕምሮ እረፍትን እያሳጣ እራስ ላይ ቀስ በቀስ እንደሚንጠባጠብ ውሃ አዕምሮን የሚያስት ትልቅ ደዌ ነው ። ይኸ ነው እኔን ያሳሰበኝ ። ይህችን ልጅ ከዚህ ደዌ መከላከል አለብን”...ዛማኑኤል ሁለቱንም እየተዟዟረ ተመለከታቸው ።

ፈዘው ያዳምጡታል ። ኃይለማርያም በወንድማቸው ድርጊት

በመናደዳቸው የዛማኑኤልን አነጋገር ሙሉ በሙሉ ተቀበሉት ። ቀደም ባለው ውይይት የዛማኑኤል አነጋገር 'ድፍረት' ያስቆጣቸው ዘረያዕቆብ ግን አልወደዱለትም ። አባባሉ ሁሉ አልጣማቸውም።

"እና አሁን ምን ይሻላል ነው የምትለው ዛማኑኤል" ጠየቁት ኃይለማርያም ።

"እንግዲህ ከእኔ እርስዎ ይሻላሉ ፡ የሚሆነውን የማይሆነውን ከእኔ የበለጠ ያውቁታል ። እውነተኛ ፍትህ እስኪኖር ድረስ መቻስ ሰው የሚያደርገውን ማድረጉ ጥሩ ነው ። ማለቴ በምንም በምንም ብሎ ራስን መከላከሉ ጥሩ ነው ። ልጅቷ ከአባቷ ጋር ተቀያይማ እንዳትቀር በሕይወቷ ፡ በግል ሕይወቷ ጣልቃ እንዳይገቡ ማድረግ ነው ፡ ምርጫውን ለእርሷ እንዲተዉ ማድረግ ነው ። እሳቸውን መቆጣትና የበለጠ ችግር ውስጥ እንዳንገባ መምከር ነው ። እኔ ያልኩት ካልሆነ ብለው በሰው ላይ የማይገባ ድርጊት ለመፈጸም ሰውን ለመበደል እንዲህ መሯሯጣቸውን እንዲያቆሙ ፡ ክሳቸውን እንዲሰርዙ መምከር ነው ፡ በእኔ በኩል ለጊዜው የሚታየኝ ይኸው ነው" ዛማኑኤል አነጋገሩ የጥርጣሬ ይመስላል ። እያንዳንዷ ቃል ከአፉ ስትወጣ ይጠነቀቃል ።

"ሆቸ ጉድ አሁን እንዳው የምትናገሩት አስባችሁ ነው ? 'ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃም' የሚባለው እኮ እውነት ነው ፡ እኔ እምለው ሰው ልጅ ወልዶ ፡ አስተምሮ ፡ አሳድጎ ፡ ልዳር ፡ ለቁም ነገር ላብቃ ቢል በራሱ ልጅ ሕይወት ጣልቃ ገባ ይባላል ? ይኸ የጉድ ጉድ ነው...እውነት እሚደንቅ ነው ። የዘመኑ ትምህርት ችኮላ፡ ዝርጠጣ ነው እንዴ ! ስማ አንድ ታሪክ ላውራህ አዳምጠኝ" ዘረያዕቆብ እንደ ግሥላ ተቆጥተው ዐይናቸውን አፍጥጠው ዛማኑኤልን ተመለከቱት ።

የፊታቸው ሁኔታና የእጃቸው አሰነዛዘር ለማውራት ሳይሆን ለመደባደብ የተነሡ አስመስሏቸዋል ። "ስማ የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል እንዳይሆንባችሁ ። አባቶች ሲተርቱ 'ልጅ እየመከሩት ያጠፋል ፡ እጅ እየታጠቡት ያድፋል !' ይላሉ ። ታዲያ ይች ልጅ ዛሬ

ብትናደድ ነገ ትበርዳለች ፡ እንዴ ! ደሞ እኮ ጭንቀት እምትሉት ነው የማይገባኝ ፡ እንዴ ! ልጨነቅ ካሉ እኮ ትንሽ ትልቁ ያስጨንቃል ፡ እናቱ የሞተችበትና ገበያ የሔደችበት እኩል ያለቅሳሉ አሉ ! ይኸ እስኪ ምን ነው የሚያስጨንቅ ? እውነትም እምትጨነቁበት እምትጠበቡበት አታችኋል ማለት ነው…"

"ቆይ ቆይ እንደሱ አይደለም" አቋረጧቸው ኃይለማርያም ፡

"ሐሳብህ እኮ አልገባኝም ፡ ምን አርጉ ነው እምትለው ፡ 'ቢወራ ገብረየስ ቢንተከተኩ ሽሮ' አሉ አንተ ሌላም ፈሊጥ የለህ እንዴ ምንድነው ታገሱ ብሎ ነገር ?"

"እንዴ ! እኔማ የልጅ ጨዋታ አታድርጉት ነዋ የምለው ፡ የቤተሰብ ጉዳይ ነው አላላችሁም እንዴ ? የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል፡ እንዳታበላሹት አትጣደፉ ፡ አትቸኩሉ ነው የምለው ። ታገሱ ረጋ በሉ ነው የምለው ። ይኸው እኮ ነው ቅድም ስንከራከር በት የቆየነው ጉዳይ ፡ ለመተቸት ፡ ሌላውን ለመቆጣት ፡ ለማንኳሰስ እንቸኩላለን አይደለም የተባባልነው ? ታዲያስ አሁን እናንተ ምንድነው የምታደርጉት ፡ ቅድም የጠላችሁትን እኮ ነው አሁን የምታደርጉት፡ ወይስ 'የእኔን አልኩሽ እንዴ?' ብለው እንደተቆጡት ቄስ ልትሆኑ ነው ። አድምጡኝ አንድ ተረት ልንገራችሁ ፡ ዘመኑን አላስታውሰውም አንድ ያነበብኩት ተረትና ምሳሌ ትዝ ይለኛል" ዘረያዕቆብ ጉሮሮአቸውን ጠራረጉና ተስተካክለው ተቀመጡ ። ቀጠሉ ወጋቸውን ። "ትዕግሥት ካለ መቸስ ሁሉም ነገር አለ ። ልብ በሉና አድምጡኝ ። በአንድ ሀገር እጅግ በጣም የደኸየ ፡ ከሚለብሰው ቡትቶ በቀር ቤሳ ቢስቲን የሌለው ሰው ነበር ። እሱም ሆነ ሚስቱ ልጅ አልነበራቸውም ። በየዱሩ እየዋለ እንጨት እየለቀመ የዕለት ጉርሱን ያገኛል ። ሲያጣም ጦሙን ያድራል ። ምናለፋችሁ ኑሮው ካሉት በታች ከሞቱት በላይ ነበር ። ታዲያ ይህ ሰው ኑሮ መረረኝ ሰለቸኝ ብሎ አንድም ቀን ፈጣሪውን አማሮት ፡ አስቀይሞት አያውቅም ። አንድ ቀን ቀን ይወጣልኛል ብሎ ያስብ ነበር ። ያሰበው አልቀረም ። አንድ ቀን ሕልም ታየው 'ከሰማያት

ወርደው የሚጎበኙህ ሦስት እንግዶች ይመጣሉ ። ተቀብለህ አስተናግዳቸው ። የሚሉህን ፈጽመህ እንድትሸኛቸው' ይልና መልአክ ያናግረዋል ። ያ ሰው ሲጨነቅ ዋለ ። 'ምን የመሰሉ እንግዶች ይሆኑ ፣ እኛ ጎጆ፡ በባዶ ቤት መጥተው ምን ላረጋቸው ነው' እያለ ይጨነቃል ።

“ገንዘብ ፣ ልጅና ትዕግሥት ከሰማያት ወርደው ወደ እሱ ቤት ጉዞአቸውን ጀመሩ ። ብዙውን መንገድ አቋረጡና አንድ ትልቅ ወንዝ ላይ ደረሱ ። ወንዙ ጢም ብሎ ሞልቶ መሻገሪያ ጠፍቷል ። ሦስቱም የወንዙን ሙላት ሲመለከቱ፥ ቆዩና ትዕግሥት ቀስ ብሎ ተሻገረ ። ሁለቱ ቀሩ ። ልጁ ገንዘብን ይጣራና 'በል እንግዲህ ይኸን ወንዝ ለመሻገር እኔ አቅም ያንሰኛል ። አንተ ትልቅና ብርቱ ስለሆንክ ተሸከምና አሻግረኝ' ይለዋል ። የዚህን ጊዜ ገንዘብ ቱግ ይልና ይቆጣል ። 'አንተ ባለጌ ፣ እንዴትስ ዐፍረት የለህም ታላቅህን ወደ ላይ እንጋጠህ ስታዝ አታፍርም ? በል ና ፣ ናና ተሸከመህ አሻግረኝ እራስህ ና ወዲህ ኋላ አሳር ይገጥምሃል' ብሎ ይጮህበታል። ሁለቱም እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ሲባባሉ ጠብ ይጀምሩና ከፉኛ ይደባደባሉ ። ትዕግሥት ነገሩን በጽሞና ሲመለከት ቆየና ሁለቱንም ዐቅፎ አሻገራቸው ። ሰላም ወረደ ።

“ኋላ ወደ ሰውየው ቤት ይሔዱና የመጡበትን ጉዳይ አስረድተው ከሦስት አንደኛችን ያንተ አገልጋይ ለመሆን ነው የተላክነው ፣ ከሦስታችን አንዱን መርጠህ ታስቀራለህ ፣ የቀረነው ተመልሰን ወደ መጣንበት እንሔዳለን ። በል እንግዲህ ፈረሱም ይኸው ፣ ሜዳውም ይኸው ይሉና ተፊት ለፊቱ ይገተራሉ ። ያ ድሀ ሰው ማናቸውን እንደሚመርጥ ግራ ይገባዋል ፣ ይጨነቃል ፣ ይጠበባል ። ይሔድና ሚስቱን ያማክራታል ። 'አንተ ሞኝ እንዴትስ ግራ ይገባሃል ፣ ልጅን መርጠህ ምን ልታበላው ? ምን ልታጠጣው ? ምን ልታለብሰው ? የትስ ልታስተኛው ነው ? ትዕግሥትንስ ማሰብህ ምን ሊፈይድልን ነው? አትጃጃል ቤትህ የገባን ሲሳይ አትመልስ ገንዘብን ምረጥ' ትለዋለች።

“የሚስቱን ምክር ይሰማና ወደ ጐረቤቱ ይሮጣል ። ያ ጐረቤቱ ምቀኛው ነበር ፡ ማጣቱን እንጂ ማግኘቱን እማይፈልግ ሰው ነበር ። ሦስቱ እንግዶችም ድሀው ሰው ቤት በመምጣታቸው ቀንቶ ኗሯል ። ያ ድሀ ሔዶ ‘አባክህ አማክረኝ እስቲ ማናቸውን ልምረጥ’ ይለዋል ። ያ ምቀኛ በእሱ ቤት ተንኮል መሥራቱ ነው ‘ልጅ ብትመርጥ ገንዘብ ስለሌለህ በረሃብ ትገለዋለህ ፡ ገንዘብን ብትመርጥ የምታወርሰው ልጅ ስለሌለህ ሀብትህ ሁሉ የትም ባክኖ ይቀራል ፡ የማንም መጫወቻ ይሆናል ፡ ስለዚህ አርፈህ ትዕግሥትን ምረጥ’ ይልና ይመክረዋል ። ልብ አድርጉ እንግዲህ ። ያ ድሀ የጐረቤቱ ምክር ይበልጣል ይልና ሔዶ ‘ትዕግሥትን መርጫለሁ’ ይላቸዋል ። ገንዘብና ልጅ ተሰናብተው ሲሔዱ ትዕግሥት ከሰውየው ይቀራል ። እቶ ሚስት በተለይ ገንዘብ በመሔዱ ተናደደች ።

“ታዲያ ምን ይሆንላችሁአል ፡ ገንዘብና ልጅ ይሔዱ ይሔዱና እዚያ ወንዝ ይደርሳሉ። ማ ይሻገረው ። የቀድሞ ንትርካቸውን ጀመሩ ፡ እኔን አሻግረኝ ፡ የለም እኔን አሻግረኝ ሲባባሉ ቆዩና ተካረው ተደባደቡ ። ድክም ሲላቸው ቁጭ አሉና መከሩ ። የለም ብቻችንን ሊሆንልን ስለማይችል ከድሀው ሰው ቤት ተመልሰን ከወንድማችን ከትዕግሥት ጋር አብረን እንኑር ይባባሉና ይመለሳሉ። አብረው መኖር ጀመሩ ። ከዚያ ወዲህ የዚያ ድሀ ቤት የደስታና ፈንጠዝያ ቤት ሆነ እላችሁአለሁ ። እና ታገሱ አትቸኩሉ ‘የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል’...”

“የለም የለም ተረቱ ጥሩ ነው” አቋረጣቸው ዛማኑኤል። “ይኸን ያወጉንን ተረት እኔም አንብቤዋለሁ ፡ ግን አንድ የረሱት ነገር አለ ፡ ሲጨርስ እኮ ‘ግን ግን እንሮህ ቁጭ ብለህ እባብ ሊነክስህ ወዳንተ ሲመጣ እያየህ ትዕግሥት ብለህ ዝም ብትል እኔ የለሁበትም’ ይላል እኮ ። አዩ ሕይወት የብዙ...”

“በቃ ! በቃ !” ዘረያዕቆብ እንደ ብራቅ ጮሁና ቱግ ብለው ተነሡ ። በሰውነታቸው ውስጥ ያሉት ጅማቶች ሁሉ ፊታቸው ላይ የተሰበሰቡ ይመስል መልካቸው ሁሉ ተለወጠ ። ዛማኑኤል ከው

ብሎ ደነገጠ ። ዘረያዕቆብ ደማቸው ፈላ ፡ አቅበጠበጣቸው ። ወዲያ ወዲህ ተመለከቱ ። ከዘራቸውን ከመሬት አነሡና ወደበሩ ሮጡ ። በሩ አጠገብ የተሰቀለውን ካፖርትና ባርኔጣቸውን አውርደው በሩን በረገዱና ወጡ ። ኃይለማርያም ተከተሉአቸው ።

“ዘረያዕቆብ ትሔድና ኋላ እንጣላለን...እንጣላለን ብየሀለሁ...” ጮሁ ። ዘረያዕቆብ አልተመለሱም ። ቤቱ ውስጥ ጸጥታ ሰፈነ ። የሞቀ ውይይት ሲደረግበት የቆየው የኃይለማርያም ሳሎን ሬሳ የወጣበት ክፍል መስሎ ቁጭ አለ ። ሁለቱም አንገታቸውን ደፍተው እንዳቀረቀሩ ብዙ ቆዩ ።

“ይኸውልህ የእኔ ጓደኛ እንዲህ ዓይነት ሰው ነው” ኃይለማርያም በረዥሙ ተነፈሱና ተነስተው ወደ መኝታ ክፍላቸው አመሩ ።

ዛማኑኤል ብቻውን እንደ ተከዘ ቀረ። የመጣበትን ፡የተላከበትን ጉዳይ ሳይፈጽም አጉል ንዝንዝ ውስጥ ገብቶ ጊዜውን እንዳጠፋ ቆጠረው ። እንዲህ አድርግ የተባለውን ዘንግቶ አሻው ውሎ አሻው አምሽቶ ማታ ወደ ቤት ሲገባ “ዛማኑኤል ያንን እንዴት አደረክልኝ?” ሲሉት “ውይውይ” ብሎ ራሱን ሲጨመድድ “ተወው እኔው ነኝ ጥፋተኛዋ እንዳው በዋል ፈሰስ ነህ” ብለው አክስቱ የሚቀልዱበት ትውስ አለውና ራሱን መታው ። የሰመመን ዓይነት ዕንቅልፍ እንደ ማሸለብ ሲለው የአቶ ኃይለማርያም ስልክ ጩኸት ቀሰቀሰው። እንደ መባነን አለና ተነሣ ። ሁለት ልብ ሆነ ፡ ስልኩን ማንሣት ፡ አቶ ኃይለማርያምን መጥራት ። እንደ መበርገግ አለና የስልኩን እጀታ አነሣ ።

“ሀሎ...ሀሎ”

“አዎ አዎ”

“ነኝ ዛማኑኤል ነኝ ...እንዴ ሐሪ ነሽ እንዴ እንደ ምን ዋልሽ?”

“ኧረ አባክሽ...በጣም ጥሩ ፡ በጣም ጥሩ”

“እዛው እመጣለሁ ፡ እዛው ጠብቁኝ እመጣለሁ”

“አዎ ነግሬያቸውአለሁ ፡ ወደ መኝታ ቤት ገብተው ነው !”

"እሽ እሽ ግዴለም ለእኔ ተይው ቻው" ስልኩን ዘጋ ። ተጨማዶ የነበረው ፊቱ ፈካ አለ ። ብስጭቱና ቁጭቱ ከላዩ ላይ እየለቀቁት እፎይታ እየተሰማው ሔደ ። ተመልሶ ወደ ስራው ሔደና የመውደቅ ያህል ዘፍ ብሎ የእርካታ ትንፋሽ ተነፈሰ ። እጆቹን ራሱ ላይ አነባበረና እንጋጦ ተቀመጠ ።

አቶ ኃይለማርያም ከመኝታ ክፍላቸው ወጥተው ወደ ሳሎን ሲገቡ ሌላ ኃይለማርያም መሰሉ ። አደባባይ የሚወጡበትን ኮት ጥቁር ሱፋቸውን ለብሰዋል ። በነጭ ሸሚዛቸው ላይ ያሰሩት ወደ ቡናማ ቀለም የሚያደላ ክረባታቸው ከልብሳቸውና ከቁመናቸው ጋር ተስማምቶአል ። ላመል ታክል ሸሚዛቸው ላይ ጠብ ያደረጉት ሽቶ ከሩቅ ታውዳለች ።

"ስልክ ሲጮህ የሰማሁ መሰለኝ?" አሉ ክረባታቸውን እያስተካከሉ ።

"ሐረገወይን ናት ። እንዳጋጣሚ እኔን ነበር የፈለገችው"

"ምን አለች ? ደኅና አይደለችም እንዴ ?"

"የለም ደኅና ናት ፣ ጉዳዩ ለአቃቤ ሕግ ቀርቦ ነበር ፣ አቃቤ ሕግ በቂ ማስረጃ ስላልቀረበ ፣ ልጁ ሊከሰስ አይገባውም በማለት በነጻ አሰናበተው ነው የምትለኝ"

"ታዲያ ትልቅ የመሥራች ነዋ!"

እጃቸውን ለሰላምታ ዘረጉለት ። በሁለቱ እጆቹ ይዞ ጨበጣቸው ። ባደረጉት ሰፊ ውይይት ችግሩን የፈቱት መስሎ ታያቸው ። ሞቅ ፣ ቀዝቀዝ ስትል የቆየችው የኃይለማርያም ሳሎን መልሳ ደመቀች ።

ምዕራፍ አምስት

ክረምት የልቡን ሠርቶ "እንዲህ ነኝ እኔ ወንዱ!" እያለ እየተጐማለለ ፡ እየፎከረ ፡ "ቆይ ደሞ እንገናኛለን" እያለ እየዛተ፡ እያስፈራራ ሥፍራውን ለጥቢ ፀሐይ እየለቀቀ ጓዙን ጠቅልሎ መሔድ ጀምሯል ።

ተንፋፍቀው የሰነበቱት መሬትና ፀሐይ ቶሎ የሚግባቡም አይመስሉ ። ጨረሯን ሙሉ በሙሉ መሬት እንዳታደርስ ከልክሎ አት ከመሬት ጋር አኩራርቷት የከረመው ዳመና ሲገፍ ፀሐይ በብቸኝነት የምትኩራራ ትመስላለች ። እሷም በተራዋ ትፎክራለች። ማለዳ በምሥራቅ በኩል ብቅ ትልና እንደ ሞቅ እንደ ቀዝቀዝ እያለች ትውላለች ። እንደ ክረምቱ ዝናብ ሌትም ቀንም ሙዝዝ አትልም ፡ ለመናፈቅ ትፈልጋለች ። ደምቃ እንደ ወጣች ሁሉ በንብረቀለም ታጅባ ማታ ትጠልቃለች ፡ ትጠፋለች ። ማን በሰው አትጨክንም ፡ ሰዓቷን ቆጥራ ብቅ ትላለች ። ብርሃኗን ትዘራለች ፡ ሙቀቷን ትለግሳለች ። "በሉ እስቲ እውነት ተናገሩ ፡ ከእኔና ከዝናብ ማን ይሻላችሁአል?" ብላ የምትጠይቅ ትመስላለች ።

አዲስ አበባን የከበቡት ተራሮች በአደይ አበባ አሸብርቀው ጀንበር ስታዘቀዝቅ በሚሸኟት ደማቅ ቀለማት ተውበው ፡ ከተማችውን ዙሪያዋን ከበው የሚደለቁ ይመስላሉ ። መስከረም ሲያልቅም "መስከረም ጠባ" እያሉ ይዘፍናሉ ። ወፎች ስልልታውን ያስንኩታል ።

ከዱሮው አይሮፕላን ማረፊያ ባሻገር በጆሮባው የረጲንና የመናገሻን ተራራ ተገን አድርጎ ችምችም ብሎ የበቀለው ደን እሱም የአደይ አበባውን የከበሮ ድልቂያና ጭብጨባ የሚከተል ይመስል የራሱን እስክስታ ጀምሮአል ። ወደ አንድ ወገን ጋደል ይልና ... ቀና ... እንደ ገና ወደ ሌላ ወገን ጋደም... አንድ ላይ።

እንጋጠው ሲመለከቱት በተለይ ብሶት ያለበትን ሰው ያባብሳል "ኧረ ጥራኝ ዱሩ" በሚሉት ዓይነት ።

የአዲስ አበባ ግርግር መሸትም ሲል አያባራ ፡ እንዳውም ይብስበታል ። እግረኛውም መኪናውም ይርመሰመሳል ። የመንገድ ዳር መብራቶች አዲስ አበባን ማድመቅ ጀምረዋል ፡ ልጆች 'የሰማይ አምፑል' እያሉ የሚጠሯት ጨረቃ ግዙፍ ሉል መስላ ከአዲስ አበባ በስተ ምሥራቅ አድማሱ ጥግ ልጥፍ ብላ ትታያለች ። ገና ሞተሯን እያጋለች ነው ፡ ድምቅ አላለችም ። ጨለማና ብርሃን ፡ የሚረካከቡባትን ሰዓት ብዙ ሰዎች ይወዱአታል ። ነፋሱም አየሩም ጤና ነው ብለው ለሽርሽር ይወጡበታል ።

ሚልኪያስ ፍኖት የሳሎኑን ስስ መጋረጃ ገለጠና ወደ ውጭ ተመለከተ ። ከግንቡ አጥር ውጭ ሊታየው አልቻለም ። አረንጓዴ ቀለም የተቀባው የአጥሩ የብረት በር እንደ ተዘጋ ነው ። የግቢው ልዩ ልዩ አበቦች የጀንበሯን ማሽቆልቆል የሚቃወም ሰልፈኛ መስለው ተርታውን ተሰልፈው ግራ ቀኝ ይወዛወዛሉ ። ሚልኪያስ ዐይኑ ሊደርስበት የቻለውን ሁሉ እስኪበቃው ቃኘና ሰዓቱን ተመለከተ ። አሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል ።

የለበሰው ጉርድ ነጭ ሸሚዝ ፡ ጥቁር ሱሪና ጫማ ሠርገኛ ለማጀብ የሚዘጋጅ እድምተኛ አስመስለውታል። ሥርዓት ሳይጠብቁ በጸጉሩ ዙሪያ የበቀሉት ነጫጭ ጸጉሮች የውበትም የዕድሜም ምልክት ከመሆን ዐልፈው መልኩን ስለሚያጠፉት እሱም ሁልጊዜ ያጠፋቸዋል ። አጠርና ደንደን ያለ ቁመና ያለው በሀብቱ የሚኮራ እጅግ እልከኛ ሰው ነው ።

አግብቶ አያውቅም ፡ ግን በከተማው ያሉ ብዙ ሴቶችን ያውቃል ፡ እሱንም ብዙ ሴቶች ያውቁታል ። አይቼ ዐልለፍ ይላል ። ዕድሜው ከአርባ ያለፈ ቢሆንም ፡ አሁንም ጉርምስና ይሰማዋል ። ገንዘቡ ማናቸውንም ነገር ሊገዛ የሚችል መስሎ ስለሚታየው ሁሉንም ይንቃል ። ያራክሳል ። ጉራና እልክ ስለሚጠናወቱት

ሊታይ ሊታይ እያለ ገንዘቡን ይረጫል ። ሴት ካየ የማያደርገው ነገር የለውም ።

የዕውቀቱን ማነስ በገንዘቡ መብዛት ለማካካስ ይሞክራል ። ሞኛ ሞኝ ነው ቶሎ በፍቅር ይሸነፋል ። ፍቅሩ ግን እንደ እንቧይ ካብ ነው ፣ ቶሎ የሚናድ ። ከእናቱ ጋር ሱቅ ወጥቶ ኳስ ሲያይ "እማዬ ኳስ ግዥልኝ" ፣ ጫማ ሲያይ "እማዬ ጫማ ግዥልኝ" አሻንጉሊት ሲያይ "እማዬ አሻንጉሊት ግዥልኝ" ፣ በሰማይ የሚበር አይሮፕላን ሲያይ "እማዬ አይሮፕላን ግዢልኝ" እያለ እንደሚያስቸግር ሕፃን ልጅ ፣ እሱም ለብሳና ተኳኩላ ያያትን ሁሉ ለእኔ ይላል ። ታዲያ ብዙ ጊዜ ይቀናዋል ። ካልቀናው ግን ሰው ልግደል ይላል ። ብዙዎቹ ሴቶች ጠባዩን ስለሚያውቁበት ቶሎ ቶሎ ከገንዘቡ ያነሡለትና ዘወር ይላሉ ። እሱም ይኸን ይወዳል ። ሙጭጭ የሚልበትን አይወድም ።

ጓደኞቹ ብዙ ጊዜ ይመክሩታል ። 'አግባ ፣ አግባ ፣ አግባ' ይሉታል ። የሰው ልጅ ሲያይ ስለሚቀና ልጅ መውለድ አጥብቆ ይፈልጋል ። ዕድሜው አርባ ዓመት ከሞላ ወዲህ መሯሯጡን ትቶ ለማግባት ወሰነ። ያላማከረው ጓደኛ የለም ፣ ያማከራቸው ጓደኞቹ ሁሉ "አሁን ልብ ገዛህ ማለት ነው...በል ቶሎ ደሞ ሐሳብህን ሳትቀይር...ቶሎ አግባ" ይሉታል ። ብዙ ያማረጠ ሰው ስለነበር ግን ሐረገወይንን እስከሚተዋወቅ ድረስ በዐይኑ ሙሉ የሚያያት ፣ ለትዳር የሚያስባት ሴት አላጋጠመውም ። ከሐረገወይን ጋር ሲተዋወቅ ልቡ ደነገጠ ። አንዳች ነገር ከእግር ጥፍሩ እስከ ጸጉሩ ድረስ ሲወረው ተሰማው ። ተለከፈ ። ያ የለመደው መንቀዥቀዥና ሴት ሲያይ ረጋ አለማለቱ እንጂ ፣ ሐረገወይንን ያየበት ዐይን ሌሎቹን ካየበት ሁሉ የተለየ ነበር ።

በተዋወቁበት ዕለት ሌሊቱን ስለትዳር ሲያስብ አደረ ። የሚጠራቸውን ሰዎች ብዛት ፣ የድግሱን ዓይነትና ስፋት ፣ በሠርጉ ዕለት የሚለብሰውን ልብስ ጥራት ሚዜዎቹን ሲያወጣ ሲያወርድ አደረ ። ያን ሌሊት ሚልኪያስ የዘወትሩ ሚልኪያስ አልነበረም ።

አዱስ ሚልኪያስ ሆኖ አደረ ።

የሚልኪያስ አጐት አቶ አያናዓለም ሚልኪያስን እንደ ልጃቸው አድርገው ይመለከቱታል ። ሚልኪያስ አባቱ በመኪና ተገልብጠው እንደ ሞቱ ሀብታቸውን ሁሉ ወርሶ በንግዱ ዓለም ሲሠማራ አቶ ዐያናዓለም ገንዘቡ እንዳይባክን የወንድማቸው ስም በክፉ እንዳይነሣ ብዙ ብዙ መክረውታል ። መጀመሪያ ላይ ሚልኪያስ የአጐቱን ምክር ይሰማ ነበር ። ሰው እያወቀ ፡ ገንዘብ እየያዘ ሲመጣ ምክራቸውን ናቀና የራሱ ሐሳብ ተገዥ ሆነ ። የትም የመብረር ፡ የመክንፍ የማጥፋት ፡ የማውጣት ፡ የማውረድ ሐሳብ ተገዥ ሆነ ። አጐቱ ይህ ድርጊቱ ደስ አላላቸውም ። የእሱ ዕድሜ እኩያ የሆኑትን ልጆቻቸውን ይዘው መከሩት ፡ ተቆጡት ፡ አንድ ጊዜ፡

"ሚልኪያስ መቸስ አንተ ልጅ አይደለህም ፡ እኛንም መምከር የምትችል ትልቅ ሰው ነህ ። አባትህ አንተን በመውለዱ ሀብቱ ባክኖ አልቀረም ፡ ስሙ አብሮት አልተቀበረም ። ስሙን የሚያስነሣ ልጅ ያለው ሰው ቢሞትም አያስቆጭም ። አንተም ልጅ እንድትወልድ ስምህን የሚያስጠራ ትልቅ ሐውልት እንድትተክል እንፈልጋለን። ምክራችንን ተቀበለን ፡ አንዷን ደስ ያለችህን ምረጥና እንዳርህ ፡ ሌላ የመጣንበት ነገር የለም ለዚሁ ነው እሺ በለን" ብለውት ከመቀመጫቸው ብድግ ሲሉ ሚልኪያስ እንባ ተናነቀው ። ያሳለፈው ዕድሜ ሁሉ በከንቱ እንደላፈ ቆጠረው ። የዕለት ተዕለት ደስታው ፡ እያማረጠ የሚበላው ፡ የሚጠጣው ፡ የሚያየው ሁሉ ከንቱ ሆኖ ተሰማው ።

"ግዴለም ፡ ግዴለም ጥቂት ቀን ስጡኝ" ብቻ ነበር መልሱ ። በእርግጥም ሚልኪያስ መለወጥ ጀመረ ። ትኩረቱ ወደ ትዳር ሆነ ። ዘሎ ዘሎ ወጣለትና ልብ ገዛ ፡ እንደ አጐቱ ምክር ሚስት ለማግባት ቆርጦ ተነሣ ። እስከ ዛሬ የሚያውቃቸውን ሴቶች ሁሉ አሰባቸው ። ከቁጥራቸው መብዛት ሁሉንም ሊያስታውሳቸው ባይችልም ፡ ጐላ ጐላ ብለው ምስላቸው ፊቱ ላይ ድቅን ያሉበትን ሁሉ አሰባቸው ። አንዳንዶቹን መልካቸውን ፡ ውበታቸውን ባይጠላውም ጠባያቸው

ለትዳር የሚሆን መስሎ አልታየውም ። በሚገባ ያውቃቸዋል ፡ የወንድ ጓደኞቻቸው እንደ ዘመዶቻቸው ብዙ የሆኑ ሴቶች ለትዳር አይሆኑትም ። "ጧት ከአንዱ ፡ በሰባት ሰዓት ከአንዱ ፡ በዐሥራ ሁለት ሰዓት ከሌላው ጋር የምትዘለል ሴት እንደ ውሻ እንገቷ ላይ ሰንሰለት ካላሠሩበት በቀር ለትዳር አትሆንኝም በርፉ አትተመጥልኝም" ብሎ አሰበ ። በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ጊዜ እንጐቴ ያወጉት ነገር ትዝ አለው ።

የእንጐቴ የቅርብ ጓደኛ ለልጃቸው ሚስት ሲያፈላልጉ ይቆዩና ሁለት አማራጮች ይቀርቡላቸዋል ። አንዷ በጠባዩአ እጅግ የተመሰገነች ፡ ከቤት የማትወጣ ፡ ከትምህርት ቤት ወደ መኖሪያዋ ፡ ከመኖሪያዋ ወደ ትምህርት ቤቷ እንጂ ሌላ የማታውቅ ፡ ቀና ብላ ሰው የማታይ ናት ። ሌላዋ የዚችኛዋ ተቃራኒ ናት ። ውሎዋ በየዳንስ ቤት ነው ። ትዞራለች ፡ ያማራትን ሁሉ ታማርጣለች ። ቤተሰቦቿን ያስቸገረች ወንዳወንድ ነች ። በውበት ሁለቱም አይተናነሱም ። በትምህርት ደረጃቸው የተለያየ ትምህርት ቤት ይማሩ እንጂ አንድ ናቸው ። የሁለቱም ቤተሰቦች የታወቁ ናቸው ።

ታዲያ የእንጐቴ ጓደኛ ዘመድ ይሰበስቡና "በሉ እስኪ ምክሩ የትኛዋን እንዳርለት" ብለው ሲጠይቁ የተሰበሰበ ዘመድ ሁሉ "እንዴ ምን ጥያቄ አለው ያችኛዋን ነዋ ፡ ጨዋዋን ፡ ከቤት የማትወጣዋን ፡ የቤተሰቧን ስም በመጥፎ የማታስነሣዋን" ይላሉ። ሰውየው ሁሉንም ሲመለከቱ ቆዩና "እሷን መረጣችሁ ?" ብለው ጠየቁ በመገረም አነጋገር ። ሁሉም በእርግጠኝነት "እንዴታ! እንዴታ" ይላቸዋል ። ሣቅ ይሉና "እንግዲያውስ ተሳስታችሁአል ፡ እጅግ ተሳስታችሁአል ። ያች ከቤቷ የማትወጣውን ልጅ ታስራ እንደ ኖረች ጥጃ ቁጠሯት ። ስትለቀቅ የምትፈነጭበት ሜዳው ሁሉ አይበቃትም ፡ ይችኛዋ ግን በወጣትነት ዘመኗ የሚያሻትን ሁሉ አድርጋ ዘላ ዘላ ፡ ጨፍራ ጨፍራ፡ ወጥቶላታል ፡ ከእንግዲህ አትሞክረውም ። ጥሩ የትዳር ሰው እምትሆነው ይች ናት...ዘላ የጠገበችው ። እንዴ...ታፍና ታስራ የኖረችን ልጅ ለልጄ

ድሬ አላስበጠብጠውም ፣ ትዳሩን አላበላሸበትም” ብለው ያችን ስትዘል የኖረች ልጅ ዳሩት ። እውነትም ትዳራቸው የሞቀ ፣ ሰው የሚቀናበት ሆነ ።

አጎቱ ይህችን ወጣ አንድ ጊዜ ያወሩለት ትዝ አለው ። በወሬ ወሬ ተነሥቶ ያወሩት እንጂ እንዲህ ዓይነት ሴት መርጠህ አግባ ብለው ለመምከር አልነበረም ። ሚልኪያስም ይህንኑ ያውቃል ። ብቻ እንዲህ ዓይነቶቹንም ሴቶች አሰባቸው ፣ ግን ፈጽሞ ሊጥጥለት አልቻለም ።

አንድ ቀን ቢሮው ቁጭ ብሎ የትዳሩን ጉዳይ ሲያወጣና ሲያወርድ ድንገት አንድ ሐሳብ ውልብ አለበት ። ወሰንየለህ ። ወሰንየለህ ጉዳይ ፈጻሚው ነው ፣ አድርግ ያለውን ሁሉ ያደርግለታል ፣ የማይገፋት ተራራ መስሎ የሚታየውን ሁሉ በቀላሉ ይንድለታል ፣ ፈጽሞ የማይቻል ነው ብሎ የፈራውን ጉዳይ ሁሉ ሳይውል ሳያድር ያስፈጽምለታል ። ግን አይምረውም “እንግዲህ የክንዴን ፣ የልፋቴን… ይህን አድርግልኝ አልልህም…እንተው አስብበት” ብሎ ሣቅ ይላል ። ምልኪያስም ንፉግ አይደለም ፣ ዘገን አድርጎ ይሰጠዋል ።

ሚልኪያስ ወሰንየለህን “ለብርቱ ጉዳይ እፈልግሃለሁ ከተመቸህ ቢሮ ድረስ እንድትመጣ” ብሎ ደወለለት ፣ በማግሥቱ ቢሮው ድረስ መጣ ።

“ወሰንየለህ ዛሬ የፈለግሁህ ለብርቱ ጉዳይ ነው እጅግ ብርቱ ጉዳይ አለኝ” አለው ።

“ታዲያ ምሳ ልጋብዝህ ፣ ልብስ ላልብስህ ብለህ አትጠራኝ ሁልጊዜም ቢሆን የምትፈልገኝ ለራስህ ጉዳይ ነው! ደሞ ምን ገጠመህ?” አለና ሣቅ አለ ።

“ሙት የዛሬውስ የምር ነው ፣ እትሣቅ ለብርቱ ጉዳይ ነው የፈለግሁህ” ሚልኪያስ ከመቀመጫው ተነሣና በቢሮው መስኮት አሻግሮ ተመለከተ ። ከሩቅ የሲሚንቶ ፋብሪካ አቧራ እየተጥመለ

መለ ወደ ላይ ሲወጣ ታየው ፡ ዐይኑን መለስ አደረገና ከበሮው ጐን ባለችው ጠባብ መንገድ ኳስ የሚጫወቱትን ልጆች ተመለከተ ። ከኪሱ ሲጃራ አወጣና አቀጣጠለ ። መልሶ ወደ መቀመጫው ሔዶና ዘና ብሎ ተቀመጠ ። ወሰንየለህን ትክ ብሎ ተመለከተው ።

“ምነው ኩባንያህ ይዘጋ ተባለ እንዴ? ጨንቀህሳ” አለ ወሰንየለህ ።

“የለም ፡ ምን መሰለህ ፡ በቃኝ …ሰለቸኝ የብቸኝነት ኑሮ ። ሙት ሙት የመንዘላዘል ኑሮ ሰለቸኝ ፡ የዘመዶቼ ቁጣና ምክርም ሰለቸኝ ፡ የማማርጣቸው ሴቶችም ሰለቹኝ ። ሙት ሙት ሁሉም ነገር ሰለቸኝ ። እንግዲህ በምርኩዝ ሳልሔድ በፊት ላገባ እፈልጋለሁ ። ለዚህ ነው የፈለግሁህ …” ሲጋራውን በረዥሙ ሳበና እንጋጦ “እ…ፍ” አለው ። ጢሱ እየተጥመለመለ ወደ ላይ ወጣ ።

“አሳብህ ጥሩ ነው፡ ታዲያ እኔ ሚዜ እንድሆንህ ነው? አጋፋሪ? የፈለግኸኝ” ወሰንየለህ የሽርደዳ ሣቅ ሣቀና እጁን ሰደደ ወደ ሚልኪያስ ሲጋራ ባኮ ።

“የለም ጥሩ ሚስት እንድትፈልግልኝ ነው ፡ የትዳር ሴት እንድትፈልግልኝ ነው”

ወሰንየለህ የመደንገጥ ያህል ብርግግ አለ ። አንድ ሐሳብ ጭንቅላቱን መታው ።

“ምነው መምረጥ አቃተህ እንዴ? ሲበዛ እኮ ዐይን ዐዋጅ ይሆናል?”

“ወሰንየለህ አትቀልድ ፡ ሙት ሙት ጥሩ ሚስት የምትሆን ፈልግልኝ”

ወሰንየለህ ለጥቂት ጊዜ ከሲጋራው ጋር አቀርቅሮ ሲጫወት ቆየና ቀና አለ ።

“እውነትህን ከሆነ እኔ ምንቸገረኝ”

“እውነቴን ነው ሙት ። እውነቴን ነው ፡ እኔ እምልህ ፡ ልክ ነህ

እኮ መምረጥ አቅቶኛል ። እኔ የማውቃቸው ደግሞ ለትዳር የሚሆኑ አልመሰለኝም ።”

“ልክ ነህ ፡ ልክ ነህ ፡ ይኸ እንደ ሙጃ የትም የሚያበቅለውና አላፊ አግዳሚው የሚነቅለው እኮ ለትዳር አይሆንም” ወሰንየለህ ውስጡን ደስ እያለው የአንገት በላይ ሣቅ ሣቀና ስሜቱን እየተመለከተ ተነሣ ። ሚልኪያስ ከልቡ መሆኑ አለመሆኑን ለማወቅ ሲል ሆን ብሎ ያደረገው ነበር ። ውጭ ሥራ እንደ ሚጠብቀው እንደ ችኩል ሰው እየተንቆራጠጠ ፡ “በል እንግዲህ እስኪ በደንብ አስብበትና ደውልልኝ” አለው ። ቆዳውን ለማዋደድ እየተግደረደረ ።

“አስቤበታለሁ እኮ ነው የምልህ ፡ ብዙ ጊዜ አስቤበታለሁ ፡ አንተ ያሰብህ ጥሩ ሚስት መፈለግ ብቻ ነው” ሚልኪያስም ተነሣ ።

“እስኪ አንድ ነገር ልጠይቅህ”

“ጠይቀኝ ጠይቀኝ” ሚልኪያስ እጆቹን ዘረጋና የወሰንየለህን አፍ ይጠባበቅ ገባ ።

“መቸስ ሚስት ፈልግልኝ ስትለኝ በወንድምነት እንጂ በሌላ እንዳልሆነ ይገባኛል” የማልፈጣ ዓይነት ሣቅ ሣቀ ። ሚልኪያስ የጥያቄው ምንነት ባይገባውም ፡

“ ውይ ውይ በወንድምነት ነው” አለ ።

ወሰንየለህ ያስቀመጠውን ዕቃ አዋዶ በውድ ለመሸጥ እንደተዘጋጀና “የለም የለም በዚህ አያዋጣም” እያለ ከገዥው ለመራቅ እንደሚግደረደር ቀርቃሪ ነጋዴ የውስጡን ለማውጣት አልፈለገም ።

“እሺ እንግዲያውስ እኔም ሳስብበት ልቆይ ፡ መቸስ ለአንተ የምትሆንዋን ሚስት አሁን አስቤ ልነግርህ አይቻለኝም ፡ ጊዜ ስጠኝ፡ ጊዜ ስጠኝ” አለ ልክ ከልቡ እንደሚናገር ሰው እጆቹን እያወራጨ ።

“እሺ እስጥሀለሁ ፡ አንድ ሳምንት! አንድ ሳምንት ! አንድ ሳምንት አይበቃህም?” ወሰንየለህ የሚልኪያስ ትጋት ገባው ፡ ሣቅ

እያለ "ማይልስ ማይልስ አራት ቀን ይበቃኛል" አለ ።

በዚሁ ተሰነባብተው ተለያዩ ።

ከአራት ቀን በኋላ ወሰንየለህ ሚልኪያስ ቢሮ እየተንደረደረ ገባና "ምስር ብላ በለኝ ምስር ብላ በለኝ" ብሎ ፎኸ ። ሚልኪያስ አልገባውም ። የሚቀመጥበትን ወንበር በእጁ እያሳየው ሲጋራውን አቀጣጠለና ቁጭ አለ ። በዝርዝር ሲጫወቱ ቆዩ ።

ወሰንየለህ ሐረገወይንን ሥራ ሲያስገባ "ቆይ አንድ ቀን እኔም ሥራ እያዝብሻለሁ" ብሎ እንደዛተ ሁሉ ከሚልኪያስ ጋር ሊያስተዋውቃቸው ቀጠሮ ያዘ ። አስተዋወቃቸው ።

ሚልኪያስ ወሰንየለህን ለብዙ ጊዜ ያውቀዋል ፣ ያመሰግነዋል፣ ይወደዋል ። እንደዚያን ዕለት ግን ወዶት አያውቅም ። የልቡን በውቆ መርምሮ ብዙ ወጥቶ ወርዶ ቆንጆ ጠባይ ቆንጆ መልክ ያላት ልጅ አስተዋወቀኝ ብሎ ደስ አለው ። ከአስተዋወቃቸው በኋላ ሦስቱ ምሳ በልተው ሐረገወይንን ቢሮዋ አድርሰው ሲመለሱ ሚልኪያስ ለወሰንየለህ አንድ ሙሉ ሱፍ ሸለመው ።

"ገና የሚዜንቱ ይቀራል" እያለ ነበር የተቀበለው ።

ብዙ ያየው ሚልኪያስ ሐረገወይን ጋ ሲደርስ አዲስ ሆነ ። ገና ሲመለከታት የነደፈው ፍቅሯ ብዙ አሯሯጠው ። ብዙ አስወጣው ፣ የብዙ ሰው ፊት አስመታው ። ጓደኞቹ ግን ብዙም አላመኑትም ፣ የእሱ ጭንቀት ሊስማቸው አልቻለም ። የቀድሞው ሚልኪያስ በሴት የሚቀልደው ሚልኪያስ እንዲህ ይሆናል ብሎ ማንም አልገመተውም ፣ የሐረገወይን ፍቅር ተከብሮ ተፈርቶ ተደንቆ በኖረበት ከተማ የተዋረደ መስሎ እንዲታይ አደረገው ። ፍቅር ብቻ ሳይሆን ፣ ትዳር ፍለጋ ብቻ ሳይሆን እልህና እንዴት ተደፍሬ? የሚለው የማን አለብኝነት ጅል ወኔ ተናነቀው ። ሐረገወይንን በእጁ ለማስገባት ብዙ ብዙ ሞከረ ። በልዩ ልዩ ዘዴ ተፈታተናት ። የምትበገር አልሆነችለትም ። በመልእክተኛው በወሰንየለህ አስሞከረ ፣ ከተስፋ በቀር ያገኘው ውጤት አልነበረም ። ሽማግሌ ቤተሰቧ

ዘንድ ልኮ "በእኛ በኩል ፈቅደናል" አሉት እንጂ ሐረገወይንን በእጁ ሊያስገቡለት አልቻሉም ። የተረፈው ነገር ቢኖር በየምክንያቱ ለእባቷ የሚልከው ስጦታ ብቻ ነበር ።

ስለዚህም አዲስ ስልት መቀየስ ነበረበት ። ሐረገወይንን በእጁ ለማስገባት የሚያስችለው ስልት ፡ እልሁን የሚወጣበት ስልት መቀየስ ነበረበት ። ግን ራሱ ስልት መቀየስ አያውቅም ። ሁሉን ነገር ይገዛልኛል ከሚለው ገንዘቡ በቀር ምንም አልነበረውም። እና በገንዘቡ ፍቅርን መግዛት አሰበ ። መለማመጥን ማሳመንን በጉልበት መተካት ነበረበት ። ለተጠየቁት ጥያቄ ምላሽ መስጠት ሲያቅታቸው ፡ አለማወቅ ውርደት መስሎ የሚታያቸው ሰዎች ማጣፊያው ሲያጥርባቸው ተናግሮ ከማሳመን ይልቅ ፡ በክርን ማንበርከክን እንደሚመርጡ ሁሉ እሱም ትዕግሥቱ አለቀበት ። እልሁ ተፈታተነው ። ብስጭቱ እንደ እሳተ ገሞራ ገንፍሎ ወጣበት ፡ እንደ መብረቅ ብልጭታ ራሱ ላይ ተንቦገቦገበት ።

መንገዱ ምንም ይሁን ምን ለችግሩ መፍትሔ የማይሻ ደካማ ነው ። ደሞ ደፋርና ጢስ መውጫ አያጣ ፡ ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ እየተባለ በሚተረትበት ኅብረተሰብ ውስጥ ጭፍን ድፍረትና ገንዘብ የማይሠሩት የለም ።

እጅግ የሚተማመንበት ወሰንየለህ ጉዳዩን ቁርጥ ሊያደርግለት አልቻለም ። በተገናኙ ቁጥር "እሱን ለእኔ ተወው" እያለ ይፎክርለታል ። ግን ጠብ የሚል ነገር አልሆነለትም ። 'ላም አለኝ በሰማይ' እያለ ብዙ ጊዜ ለመቆየት አልፈለገም ። እሱም ምክሩ ፡ ወሰን የለህም ምክሩ አልሆኑላቸውም ። ሌላ ስልት መቀየስ ነበረበት ።

ስለ ጉዳዩ በዝርዝር ሊያወጋቸውና "ምን ይሻላል?" ብሎ ሊያማክራቸው ቤቱ ድረስ እንዲመጡ የቀጠራቸው ጓደኞቹ ይመጣሉ በተባሉበት ሰዓት አልደረሱም ። ሚልኪያስ ሰዓቱን እየተመለከተ ወዲያ ወዲህ ይንጐራደድ ጀመር ። አከታትሎ ብዙ ሲጃራ አጨሰ ። ድንገት ብድግ አለና ወደ ስልኩ ሮጦ ቁጥሮቹን ማዞር ጀመረ ። ስልኩን ሲያውል ባለ ጋራዥ ጓደኛው ክሊሉ ጆርጅ በሩ

ተከፍቶለት ሲገባ ተመለከተ ። ንዴቱ ትንሽ በረድ አለለት ።

“ሀሎ ምን ነካህ እየጠበቅሁህ… አሁንም ቤት ነህ እንዴ? ስማ ተስፋዬንም አስቤው ነበር ፡ ግን እሱ ከመጣ ደግሞ ያበጠብጠናል ። ጥሩ ጥሩ ሐሳብ ይሰጥን ነበር ፡ ግን ያበጠብጠናል ብዬ ፈራሁ ። ይምጣ የምትል ከሆነ ይዘኸው ና ። አይጠቅምም የምትል ከሆነ ተወው ። ይኸንን ውሳኔ ለአንተ ትቼለሁ ። ጆርጅ መጥቶአል ። አንተም ቶሎ…ና” ስልኩን ዘጋና ወደ ጆርጅ ዘወር አለ ።

“ስማ በባዶ ቤት ልታደርቀኝ ነው የጠራኸኝ ምንድንነው የሚባለው አስተናጋጅ ሲጠፋ እንግዳ የቤት ባለቤት ይሆናል ፡ ራቡንም ያስተናግዳል ነው የሚባለው? ቦርኮ” ጆርጅ ሣቅ እያለ ተናገረ ።

ሲናገር ምላሱን ያዝ ያደርገዋል ። ኮልተፍ ይላል ። ቀዥቃዣ ነው ። እንደ ቦታ አርፎ መቀመጥ አይሆንለትም ፡ ያቅበጠብጠዋል ። እጁ አያርፍም ፡ የለበሰውን ጃኬት እጅጌ ወደ ላይ ይሰበስባል ፡ ቶሎ ቶሎ በቀኝ እጁ የግራ እጅ እጅጌውን ሰብስቦ መለስ ሲል የቀኙ ይተረተርና ይወርድበታል ፡ እንደገና ይሰበስባል ፡ ፋታ የለውም ። ጓደኞቹ “አንተ ይኸን ያህል ከምትለፋ ለምን እጅጌ ጉርድ አትለብስም” ይሉታል ።

“እጄ ሥራ ይፈታል እ ፡ እጅ ከቆመ ደሞ ሞተሬ አቆመ ማለት ነው” ይላል እየቀለደ ።

“ዝም ብለህ ተቀመጥ ፡ እንዲህ ዓይነት አማርኛ ሰምቼም አላውቅ ፡ አንተን ብሎ ተራች ፡ አርፈህ ተቀመጥ” ሚልኪያስ የቀልድ ቁጣ እየተቆጣ በእጅ ሰላምታ ካቀረበለት በኋላ ፡ ከፊት ለፊቱ ሔዶ ቁጭ አለ ። የሚልኪያስ ሠራተኛ መጠጦችና ብርጭቆዎች የተደረደሩበት ጋሪ እየገፋች መጣች ። ጋሪውን ከመኻላቸው አቁማው ተመልሳ ወጣች ። ሁለቱም እንደ ፍላጐታቸው እንዳንድ ጠርሙስ አንሡና በብርጭቆ ቀድተው ከፊት ለፊታቸው አስቀመጡ።

"እሺ ጆርጅ ደኅና ነህ ወይ እባክህ ፡ ሥራስ?" አለ ሚልኪያስ

"ሥራ በጣም ይበዛል ፡ በጣም ይበዛል ፡ አሁንማ የመኪና ጥገና ብቻ ሳይሆን ፡ የባልና ሚስት ጥገና ሥራም ስለ ጀመርኩ በጣም ይበዛል?"

"ደሞ የባልና ሚስት ጥገና ምንድን ነው?"

"እንዴ የጠራኸኝ ለዚህ አይደለም እንዴ አንተ?" ጆርጅ ብርጭቆውን እንደያዘ ተነሣ ። እጅጌውን እየሰበሰበ ወደ መስኮቱ ሔደ ።

"ስማ ጆርጅ" አለ ሚልኪያስ "ጥፋተኛው አንተ አይደለህም፡ ዱሮውንም አንተን ሰው ነህ ብዬ ስጠራ ነው የተሳሳትኩት"

"እንዴ ደሞ ምን ልታደርገኝ አስበሀል ፡ መኪና አደረግኸኝ እንዴ ታዲያ…ቦርኮ" ጆርጅ እየተንጐራደደ የግድ ማቅ መማቅ ጀመረ ።

"እባክህ ሚልኪያስ የምትለውን በለኝና ልሒድ… ሙት በጣም በጣም እቸኩላለሁ ።"

"ለዚህ ነው በቁምህ የምትጠጣው ፡ ቆመህ ስትጠጣ ብዙ ስለምትወስድና መጠጡን ስለምትጨርስብኝ እባክህ ቁጭ በል"

"ኋላ ስወጣ ሂሣቡን ተሳስበህ ልትቀበለኝ ትችላለህ"

"የእኔ ቤት እኮ እንደ ማንኛውም ቤት ቀላል ሂሣብ የሚያስከፍል እንዳይመስልህ"

"ግዴለም ግዴለህም ። ሚስት የምትሆን ሴት ክፈል አትበለኝ እንጂ ገንዘብ እከፍላለሁ" ሁለቱም ተሣሣቁ ። ጆርጅ ቀልድ ይወዳል ፡ ግን መቀለድ አያውቅበትም ።

አበበና ተስፋዬ ተያይዘው ገቡ ። ሚልኪያስ የሞቀ አቀባበል አደረገላቸው ። ቁጭ እንዲሉ የሚፈልጉትን ጠየቀና መጠጥ ቀዳላቸው ። ጆርጅ በክፍሏ እየተንጐራደደ ያወራል ፡ ሌሎቹ እየሣቁ ያዳምጡታል ። ሚልኪያስ ሰዓቱን ተመለከተና ፡

“በሉ እስኪ ወደ ጉዳያችን እንሒድ” አለ እያጨበጨበ ። ጫቱና ጨዋታው ኢቆመና ክፍሏ ውስጥ ጸጥታ ሰፈነ ። ጆርጅና አበበ የመጡበትን ጉዳይ ያውቁታል ። ተስፋዬ ለነገሩ እንግዳ ነው ። የሚልኪያስ አብሮ አደግ ጓደኛው ቢሆንም ፡ ብዙ ጊዜ አይጥመውም ። ኩራቱ ፡ መንቀባረሩ ፡ ከእኔ ወዲያ ላሳር ማለቱ ያናድደዋል ። ‘ኢባክህ ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ’ እያለ ሁልጊዜ የሚተርትለት ሁሉ ያበግነዋል ። ግን ሲቸግረው የሚደርስለት ሚልኪያስ ነው። እሱም ከቸገረው በቅድሚያ የሚያማክረው ሚልኪያስን ነው። አበበ ጅላጅል ነው ። እንደነዷት የሚነዳ ። ጓደኞቹን ይወዳል፡ ለጓደኛው ሟች እሚሉት ዓይነት ሰው ነው ።

“እንግዲህ ሌሎቻችሁ እንኳ ታውቁታላችሁ ፡ ምናልባት ተስፋዬ ነው የመጣበትን ጉዳይ የማያውቅ ። እና በወንድምነታችሁ አንድ ምክር እንድትሰጡ ነው የጠራኋችሁ ። በቅድሚያ ግን አንድ ጊዜ ልቅዳላችሁ መሰል” ሚልኪያስ ተነሣ ።

“ግዴለም ግዴለም እሱን ለእኛ ተውልን ፡ እንተ ዝም ብለህ አውራ… በርኮ” ጆርጅ ተነሣና መቅዳት ጀመረ ።

ሚልኪያስ ከየት እንደሚጀምር ግራ ገባው ፡ ነገሩ እንዳይንዛዛበት ፈለገ ፡ ግን እንዴት ብሎ አሳጥሮ ያውራው ። ለጥቂት ጊዜ ከራሱ ጋር አቀርቅሮ ሲማከር ቆየና ቀና አለ ።

“ይኸውላችሁ ፡ መቸስ ሰው አትውደድ አይባልም ። ወደድኩ። በጨዋ ደንብ ቢተሰቦቿን አስጠየቅሁ ፡ እሺ ተባልኩ ። በእውነት እዚህ ለመድረስ ያወጣሁትን ገንዘብ ብነግራችሁ ትናደዳላችሁ ። ግዴለም እሱ አይቆጨኝም ። ልጅቷ እምትገርማችሁ ናት ። ደረቅ የደረቅ ደረቅ ናት ፡ እንዲህ ስላችሁ ግን መልኳን ማለቴ አይደለም”

አቋረጠና ሣቀ ። ብቻውን ነበር የሣቀው ፡ የሚያጅበው አላገኘም ። የቀኝ እጁን መዳፍ አጥፎ አፉ ላይ ለጠፈና “እ. ሁ ” ብሎ ቀጠለ ።

“እጅግ ኩሩ ናት ። በእውነቱ ብትኮራም አይፈረድባትም ።

ቆንጆ ልጅ ካልተግደረደረ ምን ያረጋል ። በቀላሉ የምትቀመስ አልሆነችም ። እኔ ደግሞ ገንዘብ ባወጣሁ ፡ በለፋሁ እና እሷም በኩራት ቁጥር እየወደድኳት ሔድሁ ። እውነቱን ነው ምን እንዳስነካችኝ ላውቅ አልቻልኩም ፡ ራሴንም ይገርመኛል ። ብቻ ወሰንየለህ ማደለህም በእኔ ተወው ይለኛል ።

"ዛሬ እንዲህ አድርጊ ፡ ነገ እንዲህ ሥርቺ ፡ ከነገ ወዲያ ለአባቴ እንዲህ አድርጊ ፡ ትናንት አግኝቻት እንዲህ ብላኝ… የማይለኝ የለም፡ ታዲያ መጨረሻው 'ባል ይኸን ያህል አምጣ' ነው ። እሰማለሁ እሰማለሁ ፡ እና ይኸን ሁሉ ያፈሰስኩባትን ልጅ ማግኘት አይገባኝም?"

"እንዴ ለመሆኑ ትጠራጠራለህ እንዴ ? የዩት ቀብራራ ናት እሷ ፡ ይገርማችሁአል የአህያ ሥጋ አልጋ ሲሉት ምድር የሚሉት ለካ እውነት ነው" አበበ እየተቆጣ ተናገረ ።

"እንዴ አበበ ለካ ሞኝ ነህ ፡ ሰውዬው የወደዳትን ቀብራራ እያልክ ትሳደባለህ እንዴ ጉድ ፈላ እንዴት ያህያ ሥጋ ትላታለህ… ቦርኮ"

"እባክህ ጆርጅ ተው ሚልኪያስ ጨርስልን" አለ ተስፋዬ በጽሞና የሚያዳምጠው ጉዳይ ስለተቋረጠበት ። ሚልኪያስ ቀጠለ ወጉን ፤

"ምን መሰላችሁ ፡ ያው አባቷ ፈቅደዋል ፡ ወሰንየለህ እንደነገረኝም በጣም በጣም ተናደዋል አሉ ፡ ልጁንም ያሳሰሩት እሳቸው ነበሩ ።"

"የቱን ልጅ የቱን ልጅ" ተስፋዬ ይዞት የነበረውን ብርጭቆ ቁጭ አደረገው ።

"የእሷ ጓደኛ ነበር ፡ የልጅቱ ጓደኛ" ሚልኪያስ መለሰለት ።

"እንዴ ታዲያ ምን ብለው ነው የሚያሳስሩት?"

"ተስፋዬ እባክህ ተው ጥያቄ አታብዛብን" ጆርጅ ተቆጣ ።

ሚልኪያስ መልኩ ልውጥ አለ ። መጀመሪያውንም የተስፋዬን

መምጣት አልወደደውም ። የአሁኑ ጥያቄውም ለነገር መሆኑ ገባው። ወጉን አቆመና ከቀዳው ውስኪ አከታትሎ ፉት አለለት ።

"ቀጥል ቀጥል" አለው ጆርጅ ።

"ምን እቀጥላለሁ ጨረስኩ እኮ ፡ እና ምን ላድርግ ነው የምላችሁ፡ ቁም ነገረኞች ከሆናችሁ አንድ ነገር አድርጉ"

ሚልኪያስ እግሮቹን አነባብሮ ወደ ኋላው ተለጠጠና ተቀመጠ። ጆርጅ እጅጌውን እየሰበሰበ ቦክስ የሚገጥም ጉረምሳ መስሎ ይንጐራደዳል ። መጠጥ ሲቀማምስ ያ ክልስ መልኩ በርበሬ ይመስልና ቁጭ ይላል ።

"እየው ስሙ ስሙ" አለ ብርጭቆውን በቀኝ እጁ ወደ ላይ ሰቅሎ ፡

"አንድ የሚባል አባባል አለ ፡ በደንብ አላውቀውም ብቻ ምን መሰላችሁ ያለፋ ያደከመ ነገር ደስ ይላል ፡ ያላደከመ ነገር እርካሽ ይሆናል ይባላል ። አንድ ቆንጆ ቁምነገር አትሉም ። ሁለተኛ ቆንጆ ቁምነገር ደግሞ ሚሊኪያስ ወሰንየለህን የሚያህል ሰው ገጣጥሞ መሥራት ብቻ የቀረው ሰው ይዞ ይኸን ማድረግ እንዴት አቃተው ።··· ስማ ስማ ልክ የዛሬ ወር ወሰንየለህ ምን እንዳደረገ ታውቃለህ ። እሳት ነው እሳት ። የመለዋወጫ ዕቃዎች ከጣሊያን አስመጥቼ ግምሩክ ቀረጥ አበዛብኝ ፡ ከዐቅሜ በላይ ጠየቀኝ አልኩት። ስንት ? ስንት ? አለህ አለኝ 'ሰማንያ ሺህ ብር' አልኩት ። ሣቅ አለና 'አምስት ትከፍላለህ' አለኝ ፡ 'ምን አምስት' አልኩት ፡ 'አምስት ሺህ ብር' አለኝ ። 'እከፍላለሁ እከፍላለሁ' አልኩት ። ይዞኝ ሔደ ። ምንም ጊዜ አልፈጀበትም ። ዕቃየን እቤቴ አስገባልኝ ።

"ደግሞ ደግሞ ሌላ ጊዜ ዕቃ ላስመጣ የውጭ ምንዛሬ ጠየቅሁና ይኸን ያህል በአንድ ጊዜ አይፈቀድም ብለው ከለከሉኝ አልኩት ። መጣና ወረቀቱን ከእጄ መንጠቀና ወሰደው ፡ ከሰዓት በኋላ ደወለልኝ ፡ ሔድኩ አስፈቅዶ ጠበቀኝ ። ማን ምን ያደርጋል ለፈቃጅ ለአስፈቃጅ እያለ ሙልጭ አድርጐ ነው የበላኝ ። እሳት እሳት ነው

እሳት ፣ ስማ ስማ ምን እንደሚሉት ታውቃለህ 'ሚሚ' እኮ ነው ቅጽል ስሙ ። ግን ግን ውሸታም ነው ፣ እልም ያለ ውሸታም ፣ ሲዋሽ ደግሞ ለሌላው ብቻ ሳይሆን ለራሱም እውነት እስኪመስለው ነው የሚዋሸው ። ጉ-ጉ-ጉ- ሚሚ በጣም ኃያል ሰው ነው ። እና እሱን የሚያህል ሰው ይዞ እኛን አማክሩኝ ብሎ ሲጠራ አያፍርም እንዴ እባካችሁ.... በርኩ።"

ጆርጅ ወጉን ጨረሰና መንኮራደዱን ጀመረ ። እየተንኮራደደ ብርጭቆውን የቄንጥ አያያዝ ይዞ የቄንጥ አጠጣጥ ይጠጣል ። ተስፋዬ ከጨዋታው ይልቅ መጠጡ የጣመው ይመስላል ። ይጠጣል ተነሥቶ ለራሱ ይቀዳል ይጠጣል ፣ ደግሞ ይንግል ፣ ይቀዳል ። ያጨሳል።

"ይኸውላችሁ የወሰንየለህን ጉድ ካነሣችሁ እኔም አንድ ነገር ልጨምር" አለ አበበ ብርጭቆውን ወደ ጠረጴዛው እየመለሰ ። "የእናቴን ጉዳይ ለማስፈጸም በየመሥሪያ ቤቱ ስንቀዋለል ከረምኩና ነገሩን ልጨርስ ትንሽ ሲቀረኝ አንድ ሰው ጋር ተጣላሁ ። ምን ይሆንላችሁአል! ወረቀቱን እንጠልጥዬ አንዱ ቢሮ እገባለሁ ፣ ሰውየው የሚያደርግልኝ አንድ ነገር ብቻ ነው ። ጉዳዩን ተመልክቶ ፊርማውን መፈረም ብቻ ። ያለቀ ጉዳይ ነዋ ። ያለቀ እኮ ነው ፣ አለቃው ፈርመዋል ፣ ሊቃወምም ሊያንገራግርም አይችልም ፣ ያለበት ፈርሞ እኔን ማሰናበት ብቻ ነው ። ቢሮውን እንኳኩቼ ስገባ ልጥጥ ብሎ ተቀምጦ ጋዜጣ ሲያነብ አገኘሁት ። ጋዜጣውን አጣጠፈና 'ምን ነበር?' አለኝ ። 'እዚህ ላይ እንዲፈርሙልኝ ነበር ጌታዬ' አልኩና ወረቀቱን እፊቱ አስቀመጥኩለት ። አንድ ጊዜ ወረቀቱን ፣ አንድ ጊዜ እኔን ደግሞ ወረቀቱን ደግሞ እኔን ሲገላምጠን ቆየና 'ዛሬ ቀኑ ስንት ነው' አለኝ '21 ነው' አልኩት ። 'በ30 ተመለስ' አለና መልሶ ልጥጥ አለ ። 'እንዴ ምነው ፊርማ ብቻ አይደለም እንዴ አሁኑኑ ይጨርሱልኝ ላስቸግርዎ እባክዎ' አልኩት። 'የለም የለም በ30 ተመለስ ምናላት ስምንት ቀን ናት' አለኝ ። ሲናገር መቸስ ያበሽቃችሁአል ። ቅብርር ይላል ።

“ነገሩ ግርም አለኝና ‘በስምንት ቀን ስንት ሥራ ይሠራል ፡ እዚህ ላይ መፈረም ምን ጊዜ ይፈጃል ፡ እስከ አሁን ሄጄ እኮ ነበር ፡ ጨርሰን ነበር’ አልኩት ። ቅብርር እያለ የጎሪጥ ተመለከተኝና ‘ልክነህ መፈረም ጊዜ አይፈጅም ፡ ግን እየህ አሁን ፈርሜ ብሰጥህ በአንድ ቀን የጨረሰለት ጉቦ ተቀብሎ ነው ይሉኛል ፡ ገባህ አሁን’ አለና ወረቀቱን ወረወረው ። ልነግራችሁ አልችልም አንዳች ነገር ብልጭ አለብኝ ። በለው በለው አለኝ ።

“ወዲያው አጅሬ ወሰንየለህ በሩን በርገድ አድርጎና ‘ቶሎ ቶሎ ፈርማ ፈርማ’ እያለ ከበስተ ጀርባው ዞረና ዐቀፈው ። እኔን ሲያየኝ ድንግጥ አለና ‘ምን ጉዳይ አለህ? ደሞ አንተ’ አለና ጠየቀኝ ። ነገርኩት ፡ እባክህ ላስፈርም መጥቼ እሳቸው ለሳምንት ቀጥረውኝ እየለመንኩ ነው’ አልኩት ። ‘የእሱ ወረቀት የቱ ነው’ አለና ጠየቀው ሰውየውን። በጣቱ አመለከተው ። የእሱንም የእኔንም ወረቀት ከፊቱ አቀረበለትና ‘ቶሎ ቶሎ’ እያለ አጣደፈው ። የሁለታችንንም ፈረመልን ። ወሰንየለህ ‘እባክህ ጉዳይ ስላለኝ አንድ ጊዜ ውጣልኝ’ አለኝ ። ነገሩ ችግር አለኝና ወጣሁላቸው ። በሩ ላይ ቆሜ ጠበቅሁት። ወዲያው መጣና ‘ቶሎ ቶሎ ሐያ ብር ሐያ ብር ድርሻህን ትፋ ትፋ’ አለኝ ወረቀቱን እየሰጠኝ ። ‘የምን ሐያ ?’ አልኩት ተቆጥቼ ። ‘የሰውዬው’ አለኝ ። መችስ ተጣድኗል ። ሳልወድ በግዴ አፍንጫዬን ይዞ አስከፈለኝ ። ጉደኛ ሰው ነው ። ውነትም ወሰንየለህ የሚታገድበት ድንበር የለውም እኮ እሱ…”

“አሁን እኮ ነገሩን ሁሉ ተዋችሁትና ጨዋታችሁ ሁሉ ስለ ወሰንየለህ ሆነ? የመጣችሁበትን ጉዳይ ረሳችሁት መሰል” አለ ሚልኪያስ በጓደኞቹ የተቀየመ በሚመስል አነጋገር ።

“ምን እናርግህ ፡ እኮ እኛ ምን እንጥበስልህ ?” ጆርጅ አፋጠጠው ።

“መጥበሱን ተወውና ቁም ነገር ካላችሁ ተናገሩ”

“ይኸውልህ ፡ ቁም ነገር ፡ እውነት ቁም ነገር” አለ ጆርጅ

እየተቀመጠ ፡ "ምን ታደርጋለህ መሰለህ ፡ አባቷ ከፈቀዱ እሷ እምቢ ካለች ዋንኛው ምቀኛ ያ የእሷ ቦይፍሬንድ ነው ፡ ታስሮ ተፈታ ያልከው ፡ በቃ እሱ ነው ጠላትህ ። እየህ እሷ እሱን ወይ ትወደዋለች ወይ ትፈራዋለች ። ስለዚህ አስቀጥቅጠው ፡ በደንብ አስቀጥቅጠው"

"እዩ ጆርጅ በአንተ ቤት አማርኛ መናገርህ ነው ! ቅኔ መናገርህ ነው" አቋረጠው አበበ ፡ ሲሥቅ ትን ሊለው ነበር ።

"የምን አማርኛ አበበ ፡ ችግር አለው ፡ ቆንጆ አይደለም አማርኛው…ቦርኬ"

"የለም የለም ማስቀጥቀጥ ስትል ምን ማለት እንደሆነ ታውቃለህ?"

"እህ…ገባኝ ገባኝ አንተ የቡጡን ዓይነት ነው የምትለው ? ታዲያ ጎበዝ ነኝ በአማርኛ ! ብራቮ እኔ ጆርጅ ጎበዝ ነኝ" ጆርጅ እየሣቀ ተነሣ ።

"እኔ የምለው የመጣችሁበትን ጉዳይ ለምን አትወያዩበትም ። ሰውዬው እኮ የተናደደ ይመስለኛል" ተስፋዬ አነጋገሩ ብዙም የጠጣ አላስመሰለው ። የትዝብት ዓይነት አነጋገር ረጋ ብሎ ጀመረ ። "በቃ እምላችሁ እንነጋገርበት ። ሚልኪያስ አንዳንድ ጥያቄዎች ልጠይቅህና እኔም ሐሳቤን እገልጻለሁ ። አበበ በጥቂቱ አጫውቶኛል ። ዛሬ ሳይሆን ቀደም ሲልም አጫውቶኛል ፡ ግን የረባ አስተያየት ለመስጠት አንዳንድ ጥያቄዎች ልጠይቅህ"

"እኮ ጠይቀኝ ጥሩ ነው ጠይቀኝ"

"ይኽ የምትሉት ታሰረ ያላችሁት ሰው የልጅቷ ምኗ ነው?"

"እረ ባየኸው አሽከሯም መሆን የማይችል ሽባ ቢጤ እኮ ነው"

"የለም የለም የጠየቅሁህን መልስልኝ ምኗ ነው?"

"ቦይፍሬንዷ ነው ፡ ምን የሚደበቅ አለ ፡ ቦይፍሬንዷ ነው" ጆርጅ ፎኸ ። ተስፋዬ "እኪ" አለና የማቃሰት ያህል ተንፍሶ ቀና

አለ ሚልኪያስን ትኩር ብሎ እየተመለከተ ።

"ልጅቷን አንተ አነጋግረሀት ምን አለችህ?"

"ቀድሞ መች ታነጋግርሀለች ። እንደ ያደረጋት ነገር አለ ማለት ነው?"

"አነጋግረሀትም አታውቅ?"

"እሱማ አነጋግሬአትአለሁ ፡ ቃል የገባሁለት ጓደኛ አለኝ ይቅርታ አለችኝ"

"ታዲያ እንዲህ ካለችህ ምን ትፈልጋለህ ፡ ነገሩ እኮ እዚህ ላይ ያበቃል"

"አንተ ደሞ ሁልጊዜ ጠማማ ነህ ። እንዴት ያበቃል" ተናደደ ሚልኪያስ ።

"ተስፋዬ ውነትም ጠማማ ነህ አንተ ። እሷ እሺ ብትለውማ እኛንም አይጠራን ነበር ። ለሠርጉ ብቻ ነበር የሚጠራን ። ወንድማችንን ታውቀዋለህ እልከኛ ነው ፡ ወንድ ነው ፡ እንዴት ተደፈርኩ ፡ እንዴት ተናቅሁ ብሎ ነዋ ! እልህ እልህ ታቃለህ ? በቃ በቃ እሱ ነው አየህ" ጆርጅ የጨለጠውን ብርጭቆ አስቀመጠና የሁለቱንም እጆቹን እጅጌዎች ሰበሰበና ቁጭ አለ ።

"የለም የለም ጆርጅ ምን መሰለህ አልቋል ፡ ያልኩበት ምክንያት ነበረኝ ። አበበ እንደነገረኝ ሚልኪያስ ብዙ ብዙ ሞክሮአል ፡ ያም ሚግ የምትሉት ሰው ብዙ ሞክሮአል ። ግን አልሆንላቸውም ፡ በቃ ፈቃደኛ አይደለችም አለቀ ። አየህ ለጨረታ የቀረበች ዕቃ ብትሆን ኖሮ እሱ ወንድሜ አሸንፎ እንደሚወስዳት እርግጠኛ ነበርኩ ። ግን ክፋቱ ዕቃ አይደለችም ። ሰው ናት ። እና የእኔ ምክር ወላድ በድባብ ትሒድ… ሌላ ሌላ ምረጥ የምትስማማህ የምትወድህ እሺ የምትልህ… በሉ ደኅና እደሩ…" ተስፋዬ ተነሣና ውልቅ አለ ። አበበ እየተከተለ ጠራው ። በጀም አላለው ሒደ ብቻውን ። ክፍሏ ውስጥ ለጥቂት ጊዜ የመደናገጥ ጸጥታ ሰፈነ ።

"አበበ ነህ እንዲህ የምትሠራኝ ቀድሞውንም ነግሬሀለሁ ፡

ዶክን ወፈፌ አታምጣብኝም ብየሀለሁ ፡ ጉረኛ ደደብ ፡ በእሱ ቤት ማወቁ ነው ፡ መመራመሩ ፡ መናገሩ ነው ደደብ ፡” ሚልኪያስ ብስጭቱ ቱግ አለበት ። በተስፋዬ መውጣት የተቀሰቀሰው ንዴቱ ብቻውን ያናግረው ጀመር ። አበበ ድንግጥ ብሎ ቀረ ። የጠጣው ሁሉ እንደ ጤዛ ተኖ ከላዩ ላይ ሲነሣ ተሰማው ። የፍራቻና የድንጋጤ ስሜት እንደ ብርድ ያንቀጠቀጠው ገባ ። ጆርጅ ግን ምንም አልመሰለው ። ብርጭቆውን የቁንጥ ያዘ የቁንጥ ተጎነጨለትና እጅጌውን እየሰበሰበ ተነሣ ።

“ቦርኮ ፡ ዝምብላችሁ ነው የምትለፋለፉት ። ስማ…ስማ ተስፋዬ እኮ እውነቱን ነው የተናገረው ። በቃ አይሆንም ላላችሁ ፡ አይሆንም ፡ እሽ ካላለች ምን ይጠበስ ፡ ተስፋዬ እውነቱን ነው ። ዝም ብላችሁ ነው የምትሰድቡት ፡ እውነቱን ነው ። ስማ…ስማ ጣሊያን ምን ይላል መሰለህ ‘ኪ ጆካ ኩን ቼቾ ትሮቫ ኡን ካልቾ’ ይላል ። ምን መሰለህ ‘ከአህያ ጋር የተላፋ መጨረሻ ካልቾ አይቀርለትም’ ማለት ነው ። እና ዝም ብላችሁ ነው የሰደባችሁት”

“ተው እንጂ ጆርጅ አህያ አልከን እኮ” አበበ ተናደደና ተነሣ ።

“ቦርኮ …ዝም ብለህ ቁጭ በል” ጆርጅ አባረቀበት ። አበበ ቀልቡ የተገፈፈ ያህል ደንግጦና መልሶ ቁጭ አለ ።

ሚልኪያስ! ሦስት ጥያቄዎች እጠይቅሃለሁ ለሦስቱም ቆንጆ ቆንጆ መልስ ትመልስልኛለህ ፡ ከዚያ በኋላ እኔ ደግሞ ቆንጆ ሐሳብ አቀርባለሁ ፡ በዚህ ትስማማለህ?” ጆርጅ ሚልኪያስ ላይ አፈጠጠበት ። ሚልኪያስ ካቀረቀረበት ቀና አላለም ።

“በቁምነገር ከሆነ ጠይቀኝ እመልስልሀለሁ?”

“ብራቮ ሚልኪያስ… አዳምጠኝ እንግዲህ” ጆርጅ እጅጌውን እያጠፈ ቁጭአለ ።

“ስማ ጥያቄ አንድ ፡ ወሰንየለህ እንዴት ዝም አለ ፡ ነገሩ ከበደው ወይስ አንተ ገንዘብ አሳነስከው? ሁለተኛ ልጅቷን ስታነጋግራት ምን እንዳለች ፡ ምን ብለህስ እንደጠየቅሀት እሷ ምን ምን

እንደመለሰ ንገረኝ ሦስተኛ ልጅቷን በእውነት ትወዳታለህ ወይ … በቃ … ለእነዚህ ጥያቄዎች ቀንጆ ቀንጆ መልስ መልስልኝ” ጆርጅ ጥያቄዎቹን አቀረበና እጆቹን አጣጥፎ ወደ ኋላው ልጥጥ ብሎ ተቀመጠ ።

“እሺ በቁም ነገር ከሆነ ልመልስልህ ፤ አበበም ልብ ብለህ አዳምጠኝ” ሚልኪያስ ትንሽ ተቁነጠነጠና ወደ ሶፋው ጫፍ ተጠግቶ ቁጥጥ አለና ሲጋራ አውጥቶ አቀጣጠለ ፤ ሁለቱንም በየተራ ተመለከተና መልሶ አቀረቀረ ።

“በቁም ነገር የምንጫወት ከሆነ ሦስቱንም ጥያቄዎች ልመልስልህ ፤ ለመጀመሪያው ጥያቄህ ወስንየለህ በእውነቱ ያልሞከረው ነገር የለም ፤ ከእሱ ጕደለበት የምለው ነገር የለም ። እውነቱን ልንገራችሁ ራሱን አዋርዶ ለእኔ ያላደረገው ነገር የለም ። ልጅቷን ያስተዋወቀኝ እሱ ነው ። ለብቻዋ እየጠበቀ ስለ እኔ ብዙ ብዙ አውርቷታል ፤ እምቢ ስትልም እሷን እየተከታተለ ምስጢሯን ሁሉ ለማወቅ ሞክሯል ፤ የምትገባበትን የምትወጣበትን ሁሉ አጥንቷል። ልጁንም ያሳሰረ እሱ ነው ። አባቷ ይከሰሱ እንጂ ውስጥ ውስጡን የሠራ እሱ ነው ። ፍርድ ቤት ሲደርስ ሊሆንለት አልቻለም ። ግን አሁንም ተስፋ አልቆረጠም ። አባቷን ሽማግሌ ይዞ የጠየቀ እሱ ነው። በሚገባ አሳምኖአቸዋል ። እሳቸው በእኛ በኩል ናቸው ። ለሁለተኛው ጥያቄህም…ሁለት ጊዜ ከወስንየለህ ጋር ምሳ ጋብዣት አለሁ ፤ ሌላ ጊዜ ብቻዬን ምሳ ጋብዣት ዕቅዴን ነግሬያትአለሁ ።”

“ምን ብለህ… እኮ ምን ብለህ?” አቋረጠው ጆርጅ ።

“ቆይ ልነግርህ አይደለም ። ‘ወስንየለህ ስለ አንቺ ብዙ አጫውቶኛል ፤ እስከ አሁን እንዳየሁሽም ከነገረኝ ብትበልጪ እንጂ አታንሺም ፤ እና እኔ እውነቱን ልንገርሽ ለትዳር እስቤሻለሁ ፤ ብንጋባ መልካም ኑሮ እንደምንኖር እገምታለሁ ፤ ከእኔ ጋር ሆነሽ ምንም የምታስቢው ነገር አይኖርም’ አልኳት ። ‘የለም እጮኛ አለኝ’ አለችኝ ፤ ብለምናት ብለምናት ድርቅ አለች ። እኔ መጀመሪያ

የመሰለኝ አለ አይደለም የመግደርደር ዓይነት… እንደእሱ መስሎኝ ነበር ። እምቢ ስላለች አልከፋኝም ፡ ልክ ናት ፡ እንዴት ባንዴ እሺ ትላለች ብዬ በስልክም በወሰንየለህም በኩል ደጋግሜ ሞከርኳት ። እንዳውም መሸሽ ጀመረች ፡ እኔን ብቻ ሳይሆን ወሰንየለህንም መሸሽ ጀመረች ። እንደሚመስለኝ በእግሯ መኳተንና ከማንም እዚህ ግባ የማይሉት ጋር መሔድ አምሯት አይደለም ። ልጅ አንድ ነገር አድርጓታል ። ትፈራዋለች ማለት ነው ። ታስሮ በነበረበት ጊዜም እየተመላለሰች ትጠይቀው ነበር ፡ እንዳውም ከአባቷ ጋር ሁሉ ተጣልታ ነበር አሉ ። አሁን ቀን ቀን እየሠራች ማታ ማታ ለመማር ዩኒቨርሲቲ ተመዝግባ ትምህርቱን እየተጠባበቀች ነው ብሎ ወሰንየለህ ነግሮኛል ። አንድ ሁለት ቀንም ማታ እሱ እና እኔ በዚያ በኩል እንገፐበን ነበር ፡ አላገኘናትም ። ለሦስተኛው ጥያቄህ …እኔ ምን ልበልህ ግልጽ እኮ ነው ። ራሴንም ይገርመኛል ፡ እውነቱን ነው ይገርመኛል ፡ እና ግልጽ ነው ለማለት ነው…”

“የለም የለም ግልጽ አይደለም በደንብ መልስልኝ” ጆርጅ ጮኸ ።

“አንተ ደሞ ድርቅ ትላለህ በቃ ይወዳታል እንዴት አይገባህም፡ ታዲያ ይኸን ሁሉ ምን ያለፋው ነበር…” አበበም ጮኸ ።

“ልክ ነው በቃ መልሶልሀል ፡ እንግዲህ ሐሳብ አለኝ ያልከውን አምጣ” ሚልኪያስ ተደላደለና ተቀመጠ ።

“አይ ሚልኪያስ ታሥቀኛለህ ፡ ደሞ ታሳዝነኛለህ ። ምን መሰለህ ስላላገኘሁት እንጂ እሺ ብላ ሁለት ቀን ከአንተ ጋር ብትቀመጥ እኮ በካልቾ መተህ ቦርኮ ብለህ ነበር እኮ የምታባርራት ። የምታሳዝን ሰው ነህ ሙት የምታሳዝን ፍጡር ነህ” ጆርጅ እየተቁነጠነጠ ብርጭቆውን ዐቅፎ ተነሣ ።

“እሺ በል ምንድን ነው ሐሳብህ ?” ጠየቀው ሚልኪያስ የያዛትን ቁራጭ ሲጋራ መተርኮሻው ላይ እየደፈጠጠ ።

“የእኔ ሐሳብ ምን መሰለህ ሁለት አማራጭ አለ ። አንደኛው

በቤተሰቧ በኩል ግፊት አድርገው እንዲያስረክቡህ ማድረግ?"

"ተው እንጂ ተው እየነገሩህ አትሰማም እንዴ" ሚልኪያስ አቋረጠው በንዴት ።

"ምን ዓይነት ጉድ ነው እየነገርኩህ አትሰማም እንዴ ዕቅዱን ልንገርህ ፡አባቷ የበኩላቸውን እያደረጉ ነው ፡ እናንተም አግዙኝ ብለው ግልጽ አድርገው ለወሰንየለህ ነግረውታል" ሌላ ሲጋራ አቀጣጠለና ተለጥጠ ተቀመጠ ።

"እንግዲያውስ እሱን ተወውና ሁለተኛውን ሐሳቤን ልንገርህ፡ ምን መሰለህ በሆነ ዘዴ ሁለቱን ማጣላት ያስፈልጋል ።"

"ማንና ማንን?" አለ አበበ ብርጭቆውን እየሞላ

"ልጅቱንና የምትሉትን ልጅ ነዋ ፡ በቃ ሁለቱን በሆነ ዘዴ ማጣላት ቦርኮ··· እንደ ዘዴ ፈልጎ ሁለቱን ማለያየት··· ይኸ ካላዋጣ ወደ ሌላ ዘዴ ፡ በቃ በቃ ምንድንነው የምትሉት? ያልተገላበጠ በቆሎ ነው ስንዴ የምትሉት እንደ እሱ መገለባበጥ ነው በቃ···"

"እንዴት ብለን ነው የምናጣላቸው?" ሚልኪያስ የመገረም ጥያቄ ጠየቀው ። የቀኝ እጁን ጣቶች እጥፍ አድርጎ አገጩ ላይ አስመረኮዘና ፍዝዝ ብሎ ይመለከተው ጀመር ።

"የምታጣሉአቸው እማ ፡ እንዴት መሰለህ ስክረን ስናድር እንዳይደብረን ስንጠጣ ምንድነው የሚባለው? እሾህን በሾህ አይደለም? በቃ እናንተም ፍቅርን በፍቅር አጣልታችሁ እንደገና ሌላ ፍቅር መመስረት"

"አልገባኝም ፡ ጆርጅ ጣሊያንኛ ሆነብኝ ግልጽ አድርገህ ንገረኝ"

"የሞትክ ፡ እንዴት አይገባህም ፡ እየው እሱ ሌላ ያፈቀረ አስመስሎ ለእሷ መንገር ፡ እሷም ሌላ የምታፈቅር አስመስሎ ለእሱ መንገር በቃ ። ግን አሪፍ ሰው ያስፈልጋል ። በጣም አሪፍ ሰው

ያስፈልጋል ። ልክ እንደዚያ ዘፋኝ ። እሱ እንዳለው '…ያንቺን አምጡና ለእኔ ንገሩና ፤ የእኔን ወሰዱና ለአንቺ ንገሩና አርሬው ተኙ አለያዩንና' አይደለም? ልክ እንደ እሱ ሁለቱን አለያይቶ ዝንጥ ብሎ መጥቶ ለአንተ የሚያስረክብህ አራዳ ሰው ያስፈልጋል ።”

“እንዴ እንዴት ይሆናል ጆርጅ” አበበ ግርም ብሎት ጠየቀ ። ሚልኪያስ ያነከሞት ፍዝዝ ብሎአል ። ሶፋው ላይ የመተኛት ያህል ተንጋሎ ያዳምጣል ።

“ለምን አይሆንም ይሆናል እንጂ” ጆርጅ ያቀረበው ሐሳብ ያስደሰተው ይመስል ብርጭቆውን በቅፎ ያንኮራደዳል ። አረማመዱ የጠጣ ሰው ሳይሆን ገና ሊቀምስ ወደ መሸታ ቤት ሹክክ ብሎ እንደሚሔድ ዓይነት ነው ።

“ለምን አይሆንም ፤ በቃ ይሆናል… ቦርኮ ለምን አይሆንም ። እሱ ሌላ ሴት ያፈቀረ ማስመሰል ። እሷ ሌላ ሴት ያፈቀረ ከመሰላት እሱን ለማብሸቅ ስትል ከሚልኪያስ ጋር መጥታ ልጥፍ ነው የምትለው ፤ ጆርጅ ምን አለ በለኝ ። ሚልኪያስ ደግሞ ሁለት ቀን ያስቀምጥና ባፋንኩሎ ብሎ በካልቾ ሲያጉናት ሌላ ተረኛ ደግሞ ይቀልባል ፤ አዲዮ ።”

“ጆርጅ ደሞ ዝብርቅርቅ ታደርገዋለህ” ሚልኪያስ ከተንጋለለበት ብድግ አለ ። “አሁን ይኼን ምን አመጣው ደኅና ትጀምርና መልሰህ ዝብርቅ ታደርገዋለህ ።” አፈጠጠበት ጆርጅ ላይ ።

“ስማ ሚልኪያስ በእውነቱ የውስኪህን ሒሣብ የከፈልኩ መሰለኝ ፤ ቆንጆ ሐሳብ አይደለም ። ግን ምን መሰለህ አራዳ ሰው ያስፈልጋል ፤ ከነመረጃው አቅርቦ የሚያሳምን አራዳ ሰው አለ አይደለም በሆነ ዘዴ ሁለቱን የሚያጣላ የሚያደባድብ ዘዴ በቃ ። አራዳ ቴክኒክ መቀየስ በቃ… ስማ በዚህ ዘዴ ትስማማለህ?”

ሚልኪያስ አቀርቅሮ ከቆመበት ቀና አለ ። ፊቱ ያስፈራል ። ፍም መስሏል ።

“እስማማለሁ” አለ እጅግ በደከመ ድምፅ ። አነጋገሩ ለእሱ ጉዳይ መፍትሔ ለመፈለግ ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ የሚሰጥ

ሳይሆን ፍርድ ቤት ቀርቦ "በል በጥፋትህ ታምናለህ አታምንም?" የሚል ድምፅ ሲጮህበት እየፈራራና እየተንቀጠቀጠ ፡ "አዎ አምናለሁ" የሚል ሰው ይመስላል ። ጆርጅ የሰነዘረው ሐሳብ አብሰለሰለው ፡ በሐሳቡ ብዙ ብዙ ብዙ ቦታ ዞረ ። የሰመመን ዕንቅልፍ መሳይ ሽለብ አደረገውና መልሶ አባነነው ፡ "እስማማለሁ" አለ ደገመና ።

"ብራቮ ሚልኪያስ ከተስማማህ ለዚህ ጉዳይ የምትረዳህ እሳት የላሰች ልጅ ነገ ይዤልህ እመጣለሁ ። የውስኪህ ውለታ ነው መሰል ድንገት ነው ትዝ ያለችኝ ። በቃ በቃ…እጺዮ…ነገ ይዤልህ እመጣለሁ ፡ ግን ስማ ስማ ደሞ አንተ ስላመጣሀት ሂሣቡን ራስህ ክፈል እንዳትለኝ ደግሞ "… ጆርጅ ከት ከት ብሎ ሣቀ ። ሲሥቅ ብርጭቆው ውስጥ የነበረው እየተንጠባጠበ ሱሪውን አረጠበበት ። አጎንብሶ ከት ከት ብሎ ሣቀ የሣቀበት ነገር ገርሞአቸው ሁለቱ ይመለከቱታል ። ጉዳዩ ባይገባቸውም ሣቁ ፈገግ አሰኛቸው ።

"በምን መሰላችሁ የሣቅሁት" አለ ጆርጅ አሁንም ሣቁን ሳያቆም ፡ "እየው ያሰብኩአት ልጅ ዋናው አራዳ ናት ፡ እሳት እሳት ናት ። ልክ እንደ ወሰንየለህ ሚሚ ናት ሚሚ ። እና ምን መሰላችሁ እሷን ሳመጣለት እሷን ወዶ በቃ ያችን አልፈልግም ይች ትሻለኛለች እንዳይለን ፈርቼ ነው"… ክትክት ብሎ ሣቀ አሁንም ፡ ሁለቱም አጀቡት ።

"ጆርጅ አትቀልድ አባክህ ፡ ሙት እውነቱን ነው የቁም ነገር ከሆነ ነገ እጠብቅሃለሁ ፡ ቢሮዬ እጠብቅሃለሁ ፡ የምትለውንም ሂሳብ ግዴለህም የፈለገችውን አደርግላታለሁ ።"

ሚልኪያስ ከተቀመጠበት ተነሣና ጆርጅን ዐቀፈው ፡ ሐሳቡ ልቡን አርክቶታል። ሐረገወይን በዚህ ዘዴ ከዓለማየሁ ጋር ተጣልታ በንዴት መጥታ ጥምጥም ስትልበት ታየው ። "እስከዛሬ ስላጠፋሁ ይቅርታ አድርግልኝ" ብላ እግሮቹ ላይ ስትወድቅ ወለል ብሎ ታየው ። ልቡ ፈካ ። ጆርጅን እንዳቀፈ ወገቡን መታ መታ አደረገና መልሶ ተቀመጠ ።

"በቃ ነገ ከአምስት እስከ ስድስት ሰዓት ።" ጆርጅ የያዘውን

ብርጭቆ በማማሽ ትንፋሽ ጭልጥ አደረገና ወረወረው ። “አሬ በደርች” እጅጌውን እየሰበሰበ “ቻው… ቻው” አለ ወደ በሩ እያመራ ።

“እንዳትረሳ እንግዲህ” አለ ሚልኪያስ ሲሸኘው አብሮት እየወጣ ።

ሚልኪያስ የትዳር ስሜቱ የበለጠ ተቀሰቀሰ ። የጨለመ የመሰለው ተስፋው እንደገና ጋት ውጋጋን ከፋች ሲንቦገቦግ ታየው ። 'ፍቅር ያልገዛትን ሴት እልህ ፣ ጉልበትና ገንዘብ ሊገዛት ይገባል ፣ ደፋርና ጢስ መውጫ አያጣም' እያለ ተፅናና ። ቀማምሶ መተኛት የዘወትር ልምዱ ቢሆንም ፣ ዛሬ ያለወትሮው የጠጣው ሁሉ ተጫጫነው ። እንግዶቹን ሸኝና ወደ መኝታ ክፍሉ አመራ ። ልብሱን አወላልቆ የሌሊት ልብሱን ለውጦ ጋደም አለ ። ብዙም አልቆየ ተነሥቶ የመኝታ ክፍሉን አነስተኛ ቴሌቪዥን ከፈተ ። የፍቅር ፊልም ይታያል ። ጋደም ብሎ መመልከት ጀመረ ፣ በዚያው አሸለበው ። ጠጥቶ ብቻውን ሲተኛ ብዙ ጊዜ ያቃዠዋል ። ሐሳብ አዕምሮውን ከናወጠው ቅዠት ይጨመርና ያንገላታዋል ። ዝብርቅርቅ ያለ ሕልም አይሉት ቅዠት ተፈራረቀበት ። አንዱን ጀምሮ ሳይጨርስ ሌላ ይተካበታል ። አንዱን ተገላገልኩ ሲል ሌላው ከተፍ ይልበታል ።

በመጀመሪያ አንድ ትልቅ አዳራሽ ውስጥ ተቀምጦ ተመለከተ። በአዳራሹ ሰዎች ግጥም ብለው ሞልተውበታል ። በአዳራሹ መኻል እንደ መድረክ በተዘጋጀ ክብ ነገር ውስጥ ሁለት ሰዎች ጉራዴ ይዘው ቆመዋል ። ከክቡ ነገር ግርጌ ሌላ ሰው ቆሞ የሆነ ምክር ይመክራቸዋል ። መከረ መከረና ፊንጠር ብሎ ቆመ “ጀምር” ብሎ ፉ'ሽ ። ሁለቱ ሰዎች በያዙት ጉራዴ መፋለጥ ጀመሩ ። የተሰበሰበው ሕዝብ በለው ፣ በለው አይዞህ…ይጮሀል ። አንዱ ባለ ጉራዴ ሌላውን ተንጠራርቶ ተንደርድሮ አናቱን ሲፈልጠው ራሱ ግምስ ይላል ፣ ሌላውም ይንጠራራና ሲሰነዝር የዚያኛው ጭንቅላት ለሁለት ይገመስና እስከ አፍንጫው ድረስ ይከፈታል ። ሕዝቡ

እያዞሀ…እያዞሀ…በለው…በለው ይጮኻል ። የመጀመሪያው ሰው ተንጠራርቶ ፡ ተንጠራርቶ ፡ ተንደርድሮ ፡ ተንደርድሮ እፊቱ የቆመውን ጠላቱን የተከፈለ ጭንቅላት ባለ በሌለ ጉልበቱ በጐራዴው ሲያሳርፍበት እስከ ሆዱ ድረስ ይሰነጠቃል ። ሁለቱም ወተት ይፈሳቸዋል ። ወተቱ ጐርፍ ሠርቶ ከሁለቱም ጭንቅላት ይፈልቃል።

ሕዝቡ በለው… በለው ይላል ። እስከ ሆዱ የተሰነጠቀው ሰው ወተቱን እያዘራ ተገትሮ ይቀራል ፡ ጐራዴው ከእጁ አምልጦ ይወድቃል ። በለው በለው ይላል ሰዉ ። ያ ሰውዬ አሁንም ተንጠራራና እንዴ ሲያቀምሰው ያ የፈዘዘ ሰው ለሁለት ይሰነጠቅና ግራና ቀኝ ዘፍ ብሎ ይወድቃል ። ትልቅ ዛፍ የወደቀ ያህል ጮኸ ። ሰው አጨበጨበ ። ሚልኪያስ 'እኔ ይኸን ጭካኔ አላይም ብሎ' ዐይኑን ጭፍን አደረገና ጉልበቱ ላይ ተደፋ ። ትርዒቱ ተቀየረና ሌላ መጣበት ።

ሽንጣም መኪና ይዞ እየከነፈ በቸርችል ጐዳና ሽቅብ ይወጣል። ሔዶ ሔዶ ሊደርስ ሲል መንገዱ ጥብብ ይልበታል ። ወፍራም ሰው ሊያሳልፍ የማይችል ዙሪያውን በሰንሰል የታጠረ ቀጭን መንገድ ይሆንበታል ። መኪናውን ሲጢ ጢ ጥ ያደርግና ያቆማል ። ወርዶ በእግሩ መሔድ ይጀምራል ። ጥቂት እንደ ተራመደ መትረየስ የታጠቁ ከወገባቸው በታች ሰው ፡ ከወገባቸው በላይ ተኩላ የሆኑ ነገሮች ከሰንሰሉ ውስጥ እየወጡ "እጅ ወደ ላይ ፡ እጅ ወደ ላይ እንዳትበላሽ" ይሉታል ። ክው ይልና ይደነግጣል ። እንደ ደነገጠ እጆቹን ወደላይ አንቀርፍፎ ያለቅሳል ። "በናታችሁ ምን አደረግሁ አችሁ መንገዱ እኮ ጠበበኝ ነው ፡ ምን ላርግ…እባካችሁ ማሩኝ" ለመናቸው ። ሳንጃቸውን ወድረው ቀስ እያሉ ዐይናቸውን እያጉረጠረጡ ሲጠጉት አንዲት አሞራ ትመጣና ጸጉሩን እንቃ አንጠልጥላ ወደ ሰማይ ትወስደዋለች ። "እሪይ" ብሎ አሞራዋን ለማመስገን ቀና ሲል ትርዒቱ ይቋረጥና ሌላ ትርዒት ይጀመርበታል ።

ትልቅ ስታዲየም ይመስለዋል ። ሰዉ ተጨናንቆ ተቀምጧል ።

ጠጠር ብትወረወር መሬት አታርፍም ፡ ከአፍ እስከ ገደፉ ጥቅጥቅ ብሎ ሞልቷል ። ይዘፈናል ፡ ይጨፈራል ። “ወንድምዬ ሆ ወንድም አበባ ይዞህ በቶሎ ግባ … ያሆ… ያሆ…ያሆ…” ይዘፈናል ፡ ይጨፈራል ። እሱና ሐረገወይን እትልቁ ስታዲዮም ዋና በር ላይ ከሄሊኮፕተር ወርደው የሙሽራ ልብስ ለብሰው ወደ ስታዲየሙ ይገባሉ ። ብዙ ሕፃናትና ሴቶች አጅበዋቸዋል ። ወደ ውስጥ ዘልቀው ሲገቡ ሕዝቡ ተንሥቶ ያጨበጭብላቸዋል ። ዕልልታው ይቀልጣል። እርግቦች ይለቀቃሉ ፡ ርችት ይተኮሳል ።

ሚልኪያስ የሐረገወይንን ክንድ እንደ ጨበጠ በኩራት እየተራመደ ወደ ስታዲየሙ መኻል ሜዳ ይሔዳል ። ጭብጨባውና ዕልልታው እጅግ ደምቆ ይሰማል ። ወዲያው ስድስት ጉሬዛዎች በሰማይ እየበረሩ ይመጡና እዛው ሰማይ ላይ ሆነው ክብ ይሠራሉ ። ሙሽሮቹን ይዞሩአቸዋል ። ዞረው ዞረው ሁለቱንም ዕቅፍ አድርገው ከመሬት ያነሡና ወደ ሰማይ አርቀው ይወስዷቸዋል ። ሚልኪያስ የሐገረወይንን እጅ ጥብቅ አድርጐ ያዘ ። ቁልቁል ወደ መሬት ሲመለከት ልቡ ፈራ ። ሕዝቡ አንጋጦ እየተመለከታቸው ገዝም ብሎ ያጨበጭባል ፡ ይዘፍናል ፡ ዕልል ይላል ። “ሰማ ሚልኪያስ” አለችው ሐረገወይን ። “እያረግን ነው ፡ ወደ ሰማየሰማያት ። እነዚህን ጉሬዛዎች ያስመጣሁ እኔ ነኝ ። አየህ እንድናርግ ያደረግሁት ስለምወድህ ነው ። ስለምቀናብህ ነው ። መሬት ላይ ሆነን አንተን ማንም እንዲያይብኝ አልፈልግም ፡ ሴቶች አንተን ሲያዩ እያየሁ በቅናት እንድቃጠል አልፈልግም ። ስጠግብህ ፡ ፍቅርህ ሲሰለቸኝ ተያይዘን ወደ መሬት እንወርዳለን” አለችው ። ወዲያው ጉሬዛዎቹ ጉዞአቸውን ጨርሰው ሙሽሮቹን ደመና ፍራሽ ላይ አስተኙአቸውና በየተራ እጅ ነሥተው ተሰናብተዋቸው ተሰወሩ ። “ሐሬዬ ምናለ መሬት …መሬት አይሻለንም ነበር? እኔ እምልሽ ልማልልሽ ሙች ልማልልሽ ፡ ማንንም ማንንም አላይም ፡ ከአንቺ በቀር ማንንም አላይም ሙች…ሙች ልማልልሽ” ለመናት ። “አይሆንም…አይሆንም ስልህ እኔ እኮ አምንሀለሁ ፡ አንተማ ሌላ

አታይም ፡ ሌሎች ያዩብኛል ነው የምልህ… ገባህ ፡ ቢቃ እዚሁ እንከርማለን ፡ ሁለታችን ብቻ እንደ ልባችን እየተንፈላሰስን ፡ እንደ ልባችን ሚዳውን ሁሉ እየሮጥን ፡ እንደ ልባችን እየጠጣን እየበላን ። ገባህ? ፀሐይ ቅርባችን ናት ጨረቃ ጐረቤታችን ናት ፡ ከሰው ዐይን ፡ ከምቀኝነት ፡ ከፍርሃት፡ ከተንኮል ፡ ከዛቻ እርቀን እንደ ልባችን … እንሽሞንሞናለን … እንደ ልባችን እንዘላለን ። ገባህ ታዛቢ የለብን ገልማጭ ። ተቆጭ የለን ተመልካች እንደ ልባችን እንዘንጣለን ገባህ? ደሞ ጐሬዛዎቹ እየመጡ ያጫውቱናል ፡ የጉሬዛ ዳንስ እየደነሱ ያስደስቱናል ፡ አየር ላይ እየተንሳፈፉ ቲያትር ይሠሩልናል ገባህ ? ደሞ ፍቅራችንን ስንጨርስ ስንጣገብ ይመጡና አጅበው መሬት ያደርሱናል ፡ እሺ የእኔ ድምቡሽቡሽ” ግንባሩ ላይ ሳም አደረገችው ፡ ከንፈሩ ላይ ደገመችው ፡ ትክ ብላ ተመለከተችው ፡ የከንፈሯ ላይ ማር እየጣፈጠው ከንፈሩን በምላሱ እያሟሸ አጣጣመው ፡ አጣጥሞ አጣጥሞ የደመናው ፍራሽ ጐረበጠውና ነቅነቅ ሲል “ማነው ? ሌባ የሌባ ውላጅ ምንድን ነው የምትፈጥሩት” የሚል ድምፅ ከኋላቸው አባረቀባቸው ። ሁለቱም ድንግጥ ብለው ዘወር አሉ ።

ረገኸርም ቀንድ ያለው በአፉ እሳት የሚተፋ አፍንጫው መሬት ወርዶ የሚጐተት ግንባሩ ላይ ዐይን የተለጠፈበት ፍጡር አፍጠባቸዋል ። “ዲያብሎስ ነው ዲያብሎስ” አለች ሐረገወይን ድምጿን ስልል አድርጋ ። “አቤት መሐረው ዲያብሎስ የምድር የሰማያት ጌታ ያልከንን እንታዘዛለን ቁጣህን አብርድልን ፡ ትዕግሥትህን ምረጥልን” ሚልኪያስ በግንባሩ ተደፍቶ ተለማመነው ። ያ ፍጡር የበለጠ ተቆጣና “ውርጋጥ ፡ ውርጋጥ ፡” ብሎ ሐረገወይንን በአንድ እጁ እፍስ አደረገና አነሣት ። ግንባሩ ላይ ወደ አለው ዐይኑ አስጠጋና ተመለከታት ። “አንቺ እዚህ ትቆያለሽ” አኪሉ ከተታት። “ተነሥ አንተ ውርጋጥ” በእርግጫ አቀመሰው ።

ሚልኪያስ ከሰማየ ሰማያት እየተሽቀነጠረ ፡ እየተሽቀነጠረ ወረደና መሬት ሲደርስ ዷ…አ ብሎ ወደቀ ። ብንን አለ ።

ብርድልብሱን አሽቀንጥሮ ጣለና ተነሣ ። “በስማብ በስማብ” ተንሥቶ አልጋው ጠርዝ ላይ ቁጭ አለ ። ያቺ ቴሌቪዥኑ ብቻዋን እሽሽ …ሽ… ሽ ትላለች ። ተነሣና ዘጋት ። ወደ መታጠቢያ ክፍሉ ገብቶ ፊቱን ታጥቦ ወጣ ። መልሶ አልጋው ውስጥ ገባ ፡ ያ ሌሊት የጭንቅ ሌሊት ሆኖበት ነጋ ። እየፈራ ፡ እየባነነ እየበረገገ ፡ እየቃዠ የጭንቀት አዳር አደረ ። ጠጥቶ ብቻውን ሲተኛ ያቃዠዋል ፡ የዛሬው ግን ለብቻው ነው ። ሌሊቱን ረገመ ፡ ብቸኝነቱን ረገመ ፡ የቅዠትን አምላክ ረገመ ። የቅዠትን ዓለም ረገመ ፡ እርግማን ።

በማግስቱ አምስት ሰዓት ተኩል ላይ የሚልኪያስ ቢሮ ብርግድ አለና ተከፈተ ። ሚልኪያስ አቀርቅሮ ይጽፋል ። ቀና ብሎ ተመለከተ ወደ በሩ ። ጆርጅ ከኋላው አንዲት ልጅ አስከትሎ በሩ ላይ ተገትሮአል ። ፊቱ ላይ የሚነበበው ፈገግታ የክልስ መልኩን አጥፍቶ ቴባ ጣሊያን አስመስሎታል ። ሁለቱን የበሩን ማዕዘኖች በእጆቹ ግጥም አድርጎ ይዞ በረዥሙ ተንፈሰና ፡

“ቦርኮ …ግቡ አትልም? ቤት ለእንቦሳ አትልም?” ተቆጣ ።

ሚልኪያስ ወደ ቢሮው እንዲገቡ ጋበዛቸው ። ሁለቱንም ወንበሮች እየሳበ አስቀመጣቸውና ፡

“ምን…ምን ይምጣላችሁ?” አለ እጆቹን እያፋተገ ።

“የማታው ዓይነት ፡ ለእኔም ለእሷም” ጆርጅ አነጋገሩ የምር ይመስላል ። ተነሣና አሻግሮ በመስኮት ይመለከት ጀመር ። የአዲስ አበባን ሰማይ አጣቦ የከረመው ደመና ቀስ ቀስ እያለ ጓዙን እየጠቀለለ በመልቀቅ ላይ ነው ። የፀሐዩአ ብርሃን ድምቅ ብሎአል ። በቢሮው ዙሪያ ባሉት መደርደሪያዎች የተለያዩ የሴትና የወንድ ልብሶች ተደርድረዋል ። በቢሮው አንድ ማዕዘን ጥግ በቆመው የመጻሕፍት መደርደሪያ አናት ላይ በተጌጠ ሞልሚላ ብርጭቆ ውስጥ የተለያዩ መልክ ያላቸው አበባዎች ተሰክተው ተቀምጠዋል ። የተደረደሩት የተለያዩ ልብሶችና የአበቦቹ ቀለማት ለክፍሏ ውበት

እጉናፅፊው የቀለም መምረጫ ቢሮ አስመስለዋታል ።

እንግዳዋ ልጅ ፡ እግሮቿን አነባብራ በቢሮዋ ውስጥ ያሉትን ሁሉ በዐይኗ ትማትራለች ። የሚልኪያስ ተላላኪ ሦስት ማኪያቶ አቅርቦ እንደ ወጣ ጆርጅ ተመልሶ ቁጭ አለ ።

“ዶክተር አላስተዋወቅሁአችሁም እኮ ፡ ተዋወቁ” አለ እጆቹን ሁለቱም ወደ አሉበት እየዘረጋ ። ሚልኪያስ ከመቀመጫው ተነሣና

“ሚልኪያስ እባላለሁ” አለ እንግዳዋን እየጨበጠ።”

“አስቴር እባላለሁ” አለች እሷም ከመቀመጫዋ እየተነሣችና ሣቅ አከል ፈገግታ እያሳየች ። ጆርጅ እጅጌውን እየሰበሰበ ይሥቃል፡ ይንከተከታል ብቻውን። ሚልኪያስ ሣቁን አልወደደለትም ።

“ምን ሆንኩ ልትል ነው ደግሞ እኛም እንሣቅ አብረንህ ምንድን ነው የሚያሥቅህ?”

“የለም የለም ለሰው አይነገርም ፡ ምስጢር ነው ምስጢር ፡ ትናንት የተናገርኩት ትዝ ብሎኝ ነው የምሥቀው” ሣቁን ሊያቆም አልቻለም ። ሣቀ ሣቀና ከኪሱ መሐረብ አውጥቶ ዕንባውን ጠራረገ።

“በጣም ዶክተር ፡ ሣቅ አልችልም እኔ እኮ! ሙት አልችልም ፡ ቦርኮ ። ስማ ቁም ነገረኛ አይደለም? በቀጠሮ ክተፍ ነው አየህ ። እንግዲህ ያልኩህ ልጅ እሷ ናት ። እንዲህ ስታያት ዓይን አፋር እንዳትመስልህ ጂሉት … ጂሉት ናት ። ዋና ዋና አራዳ! አይደለም እንዴ አስቴር” አስቴር ላይ አፈጠጠባት ።

አስቴር ቀና ብላ አየችውና ፈገግ አለች ። ፈገግ ስትል ግራና ቀኝ ጉንጮቿ መኻል ጉድጉድ ይላል ። ፈገግታዋ የተደበቀ ውበቷን ያወጣዋል ። እሷ ይህንን ጥሩ አድርጋ ታውቃለች ። ሌሊት ተኝታ ካልሆነ በቀር ቀኑን ሙሉ ከፊቷ ፈገግታ አይጠፋም ።

ጆርጅ ቀጠለ “ሁሉንም ነገር ነግሬያትአለሁ ። ቀላል ነው

ብላኛለች ። እንግዲህ በደንብ ተነጋገሩና ሁለታችሁ ጨርሱ ።"

"እኮ አንተ … ምን … ይመስልሀል … ማለቴ… አንተው ጨርሰዋ…" ሚልኪያስ የሚናገረው እንደጠፋበት ተሚጋጋች ምላሱ ተሳሰረበት ። ባለጉዳዩ እሱ ቢሆንም ፣ የንግሩ ውል ጠፍቶበትና ተደነጋገረው ። እጆቹን እያፋተገ አፍጦ ጆርጅን ተመለከተው ።

"እንዴ ምን እኔ አጨርስልሀለሁ ራስሀ ጨርስ እንጂ ቦርኮ ። በቃ ለምን እንደፈለግናት ነግሬያትአለሁ ። ሂሣቡን ተነጋገሩ አይደለም እንዴ አስቴር?"

"ልክ ነው" አለች አስቴር ። "ነው" ስትል ዐይኗን ጨፈን አደረገችና ረጋ አለች ። "እኔ እምልህ ጆርጅ … ያው ዋናውን ነገር ነግረኸኛል ። በሂሣቡ ከተስማማን በኋላ ደግሞ አንዳንድ የሚሟሉ ነገሮችን እጠይቃለሁ ፣ አይመስልህም ጆርጅ?"

አስቴር ቦርሳዋን ከፈተችና አንስተኛ መስተዋት አወጣች ። መስተዋቷን በግራ እጇ ይዛ ከፍ ዝቅ እያደረገችና ዐይኗን እያሎለቀች በትንሺ መስተዋት ውስጥ ያለችውን አስቴርን አየቻት ። መልሳ ቦርሳዋን ከፈተችና የከንፈር ቀለም አወጣች ። ከንፈሯን በስሱ ቀባችና ቀለሙን መለሰችው ፣ ለስላሳ ወረቀት አወጣች ። በወረቀቱ ከንፈሯን አበስ አበስ አድርጋ ጠቅልላ መልሳ ቦርሳው ውስጥ ወረወረችው ። እርሳስ ቢጤ አወጣችና ዐይኗን እየጨፈነች የዐይኗን ዙሪያ ጸጉር አጠቆረች ። እንደ እስክስታ መውረድ አንገቷን አሹላ አወዛወዘችና ብትን ጸጉሯን ወደ ኋላዋ በተነችው የምታደርገውን ያጣች ይመስል አቁነጠነጣት ።

"ታዲያ እሱስ ምናለ ጆርጅ ሐሳብህ ምንድን ነው? እኔ እምልህ አንተው ብትጨርሰው… ምናለ ይኸ ነው ይኸ ነው በልና አስማማን እ" አለ ሚልኪያስ ጆርጅ ሚልኪያስ እንደቸገረው ገባው ። ነገሩን እንደጀመረ መጨረስ ያለበት መሆኑ ተሰማው ።

"በል ስንት ታስብላትአለህ ፣ እምልህ ጉዳዩን ከፈጸመች ማለቴ ነው?" ጆርጅ ጠየቀ ። ሚልኪያስ ሲጋራውን አከታትሎ

ሳበና ቀና አለ ።

"እኔ ልንገርህ ውነት የምትፈጽመው ከሆነ የፈለገችውን እሰጣታለሁ"

አስቴር ሁለቱንም ስታዳምጥ ቆየችና ከቦርሳዋ ኬንት ሲጋራ አውጥታ አቀጣጠለች ። የሲጋራ አያያዟ ፡ አሟሟጧና ጢስ አወጣጧ ከሌሎቹ ሁሉ ለየት ያለ ነው ። በቁንጥ ነው የምትይዘው ፡ በቁንጥ አሳሳብ ትስብለትና በቁንጥ "ኢፍ" ትለዋለች ።

"ቁርጥ ያለ ቢሆን አይሻልም ፡ አይደለም እንዴ ጋሽ ጆርጅ" ደረቅ ፈገግታ ፈገግ አለች ።

"ውነቷን ነው" አለ ጆርጅ ራሱን በድጋፍ እያወዛወዘ። "ስማ… ሚልኪያስ ይች ልጅ መቸም እንደምታስደስትህ አውቃለሁ ፡ አየህ መቸስ አለ አይደለም… እሷም እኮ ብትሆን ደፍራ ነው ይኸን ነገር የምትሠራው። ያውም በሰማይ ቤት የሚደርስባት ሳይቆጠር ። ምንድን ነው የሚባለው አሥርቱ ማዘዣዎች ናቸው የሚባሉት? አትስረቅ ፡ አትግደል ፡ አታጣላ ምናምን የሚሉትን እነሱን በመጣሷም ትጠየቅበታለች ፡ ስለዚህ አየህ በደንብ አስብላት አይደለም እንዴ አስቴር" አስቴር ላይ አፈጠጠባት ። አስቴር በፈገግታዋ ላይ ሌላ ፈገግታ ጨመረችበት ፡ ወደ ሰማይ አንጋጣ አፏን አሞጠሞጠች ፡ አፏ ውስጥ ያለውን ጢስ በቀጭኑ ወደ ላይ ለቀቀችው ፡ መለስ አለች እየፈገገች ።

"ልክ ነህ ጋሽ ጆርጅ እምልህ እኔ እንኳ አሥሩን ትዕዛዞች ግዴለኝም ፡ ኬር የለሽ ነኝ ለእነሱ ። ግን አየህ አሥራ አንደኛውን አጥብቄ አከብራለሁ" እንደ መሽኮርመምም ፡ እንደ እስክስታም እያደረጋት ሰውነቷን አርገፈገፈችና ግማሽ ሣቅ ሣቀች ።

"አይ አስቴር ደሞ አሥራ አንደኛ ጨመራችሁበት! እናንተ አራዶች የማታመጡት የለ ደሞ ምንድን ነው አሥራ አንደኛው? ብዙ ብር ተቀበሉ ነው ትንሽ ብር ተቀበሉ የሚለው" ጆርጅ ክንዱን ጠረጴዛው ላይ አስመርኩዞ ትክ ብሎ ተመለከታት ።

"አይ! አይደለም ጋሽ ጆርጅ ፡ ስረቅም ፡ አመንዝርም ፡ ግደልም ግን አትያዝ ነው የሚለው" ቦርሳዋን እንዳንጠለጠለች ተነሣች ። ጆርጅ ትከሻዋን ይዞ ወደ ታች እየጨመቀ መልሶ አስቀመጣት ። አስቴር የሚልኪያስን ልብ ማንበብ ተሳናት ። ጆርጅ እንደነገራት ሆኖ አላገኘችውም ። የእሷ ሐሳብ ገና እንዳየት "በይ ያኸን ያህል አስጥሻለሁ ፡ ለዛሬውም ይኸን ያህል እንቺ" ብሎ የሚያፍስላት መስሏት ነበር ። ቀዘቀዘባት ። የነበራትን ታላቅ ጉጉት አበረደባት ። በፊቷ ገፅታ አትግለጠው እንጂ ተናደደች ፡ እንዳች የብስጭት ስሜት ኩርኩር አስነሣት ። ግን ንዴቷ አይታይም ፡ ፈገግታዋ ሸፈነው ። መልሳ ቁጭ አለችና እየተቁለጨለጨች ጆርጅንና ሚልኪያስን ተመለከተቻቸው ። ጆርጅ የአስቴር መቀነኛ ነጥ ገብቶታል ።

"በቃ በቃ እዚሁ እኮ ማደራችን ነው ፡ ይኸውልህ እሷ እንደተባለው ነገሩን ትጨርስ ፡ በዘዴ በብልሀት ትጨርስ ። አንተ አምስት መቶ ብር ስጣት ፡ አሁን ለጊዜው ምንድን ነው የሚባለው የሥራ ማስኬጃ" ጆርጅ መናገሩን አቋረጠና ከት ከት ብሎ ሣቀ "አለ አይደለም የሥራ ማስኬጃ መቶ ብር ስጣት ፡ ቀሪውን ስትጨርስ ፡ አይሻልም አስቴር" ተነሥቶ እጅጌውን እየሰበሰበ አፈጠጠባት ። አስቴር ቶሎ መልስ አልሰጠችም ፡ አቀርቅራ ቆየችና ቀና አለች ። እንደ እስክስታ ወረደችና አንገቷን ስብታ አወዛውዛ ወደ ፊቷ የመጣውን ጸጉሯን ወደ ኋላዋ ሰበሰበችው ። ሁሉም የምትናገረውን ይጠብቃሉ ።

"ግዴለም ፡ ይሁን ግን በመጀመሪያ አንድ መቶ ሀምሳ እፈልጋለሁ"

"ግዴለም ግዴለም እሰጣለሁ" አለ ሚልኪያስ እጁን ወደ ሲጋራው ባኮ እየላከ ።

"እኪ" አለች አስቴር ፈገግታዋን ደመቅ አድርጋ ። "እንግዲህ አንዳንድ የሚሚሉ ነገሮች አሉ ። ማለቴ የልጁንና የልጅቷን አድርሻ ስማቸውን ፡ የሚወጡና የሚገቡበትን ፡ አለ አይደለም

ታሪካቸውን ፡ ጓደኞቻቸውን ሁሉ ማወቅ አለብኝ ። በቅድሚያ ይኸን ልታደርጊልኝ ይገባል ።”

“ልክ ነው ልክ ነው” ጆርጅ ደገፋት ።

ሚልኪያስ ከያዘው ሲጋራ በረዥሙ ሳበና ጢሱን አፉ ውስጥ እንዳፈነ ጉንጮቹን አሳበጠና አርቆ አሰበ ።

“ልክ ነሽ እሱንማ እናደርጋለን ። ምን መሰለህ ጆርጅ ወሰንየለህ ዛሬ ጧት ከአባቷ ጋር ይገናኛል ። የሚሉትን ነገር መጥቼ እነግርሀለሁ ብሎኛል ። ከሰዓት በኋላ ይመጣል” ሰዓቱን ተመለከተ ። “አዎ በስምንት ወይ በዘጠኝ ሰዓት ይመጣል ፡ እሱ የሚለውን እንሰማና ከአስቴር ጋር አስተዋውቀዋለሁ ። ያው እንግዲህ እሱ በሆን ዘዴ ያለችውን ሁሉ ያደርግላታል ። ቀላል ነው። ከሰዓት በኋላ ብትመለሽ ይመችሻል አስቴር?” የአስቴርን ዐይን ዐይኗን አየ ።

“ግዴለም እሺ በስምንት ሰዓት ተኩል እመጣለሁ…” በዚሁ ተስማሙ ። ሚልኪያስ ከመሳቢያው ውስጥ ብር አውጥቶ አንድ መቶ ሃምሳ ብር ቆጥሮ ሰጣት ። ጆርጅና አስቴር ተያይዘው ወጡ ። ሚልኪያስ ቢሮው በር ላይ ቆሞ በዐይኑ ሸኛቸው ። የጆርጅ አልፋሮ ሚዮ መኪና ጢሷን ከኋላዋ እያንቧለቀች ፡ እየሮኸች ፡ እየተንደቀደቀች ከነፈች ። ከሚልኪያስ ዐይን ተሰወረች ። ሚልኪያስ “ይቅናሽ” አለ የቢሮውን በር በርግዶ ከመግባቱ በፊት ። “ባለቤት ካልሮኸ ጐረቤት አይረዳም የሚባለው እውነት ነው ፡ በሰው ተማምኜ እጄን አጣጥፌ ብቀመጥ ምን ሊገኝ?… በቃ በቃ ትክክል ነኝ” አለ የወንበሩን ጠርዝ ይዞ ለመቀመጥ እያጐነበሰ ።

ምዕራፍ ስድስት

ሐረገወይን አብሮአት ያደገው ፍራቻ ፡ መሽቆጥቆጥና አንገት መድፋት ሙጥጥ ብሎ ባይለቃትም ፡ ቀስ በቀስ ከላዩዋ ላይ ገሸሽ እያለላት እንደ ልጅ ሳይሆን እንደ ሙሉ ሰው ማሰብ ጀማምሮአታል። እንደ ልጅነቷ ያለማሰቧና ያለመጨነቋ ምስጢር ቢገባትም ፡ በሕይወቷ አፍላ ወቅት በገጠማት የሒሳብ ውጣ ውረድ ምርጫዋ ከወለደቿት ፡ ካሳደጉአት ፡ እንደ ዐይን ብሌናቸው ከሚጨነቁላት አባቷ ይልቅ ወደ አለማየሁ የማድላቱ ጉዳይ አሁንም እንቆቅልሽ ሆኖባታል ። ደጋግማ ራሷን ትጠይቀዋለች ፡ የሚሰጣት መልስ "ዓለማየሁ" የሚል ነው ። ግን ረቂቁን ምስጢር "ፍቅር" ከሚለው አልፋ ውስጡን ገልባ ልትተነትነው አልቻለችም ።

ቢሆንም የአባቷን ጉዳይ ቸል ብላ ረግጣ ልታልፈው አልፈለገችም ። አባቷን ስትወድ ኖራለች ፡ ዛሬም ትወዳቸዋለች ። እንዲቀየሙባት ፡ እንዲከፋባት እንዲታመሙባት አትፈልግም ። ነፍስ እያወቀች ክፉና ደጉን እየለየች በመጣች ቁጥር ፡ ለአባቷ ያላት አክብሮትና ፍቅርም እየጨመረ መጥቷል ። ቀን በተቆጠረ ፡ ዓመት በታጠፈ ቁጥር በልጅነቷ የምታውቀው የአባቷ ፊት እየተለወጠና ወደ እርጅናው ዓለም እየጠለቁ መምጣታቸው ያሳስባታል ፡ ሁልጊዜ ያስጨንቃታል ። መለኮታዊ ኃይል አግኝታ አባቷን ከእርጅናና ከሞት ነፃ ማድረግን ትመኛለች ። ለአባቷ ያላት ፍቅር ይኸን ያህል ያጃጅላታል ። ተፈጥሮን መጋፋትን ያህል ሕልም ያሳልማታል ። ትሳሳላቸዋለች ። ግን ምን ታድርግ ሌላው እንዲያስከፋባት የማትፈልገውን አባቷን ራሷ አስከፋቻቸው ። ይኸ የሕሊና ረፍት ነሣት ።

ማለዳ ተነሥታ ትጣደፋለች ። ቀኑን ሙሉ ትጣደፋለች ።

ነፍሷ ትባክናለች ። ከአቅሟ በላይ የሆነ የሕይወት እንቆቅልሽ አልፈታ ብሎ ያንገላታታል ፤ የሕይወት ምርጫ ከፊቷ ተደቅኖ ያወዛውዛታል ። “ገና አልጋዬ ውስጥ እንደገባሁ ዕንቅልፍ ድው አድርጐ ይወስደኛል ያለሁበትን ሳላውቅ ይነጋል” የሚላት ሰው ያስቀናታል ። ዕንቅልፍ የሰው ልጅ የተፈጥሮ ግዴታ ሳይሆን ለጥቂት ሰዎች ብቻ የታደለ የተፈጥሮ በረከት መስሎ ይታያታል ።

ሐረገወይን ዛሬ ከወትሮው ይበልጥ ማልዳ ነው የተነሣችው ። ቁምሳጥኗን ከፍታ እጇ እንደፈቀደ አውጥታ የለበሰችው ልብስ ሁሉም ተስማምቶአታል ። ትናንሽ ፈርጦች ዙሪያዋን የፈሰሱባት ወደ ቅጠልማ የምታደላው ጉርድ ቀሚሷ ፤ በሮዝ ሸሚዟ ላይ ጣል ያደረገችው ነጭ ሹራብ ሁሉም ተስማምተዋታል ። ረዥም ተረከዝ ያለውን ጥቁር ጫማዋን እግሮቿ ላይ ሰካችና ወደመስተዋቱ ጠጋ ብላ ጸጉሯን ማበጃጀት ያዘች ። ጸጉሯን በማበጠሪያው አከታትላ ላገችው ። የጸጉሯን ጫፍ ይዛ ጐነጐነች ፤ ያንን ረዥም ጉንጉን ቀስ እያለች እየጠቀለለች መኻል አናቷ ላይ አድርሳ ከመረችው ። ከቦርሳዋ የጸጉር ማስያዣዎች አውጥታ ዙሪያውን አሰረችው ። እንደ ጨረሰች እየተዟዟረች ራሷን መስተዋቱ ውስጥ ተመለከተች። ውብ ሐረገወይን የልብሶቿ ምርጫ አስደስቶአታል። ተጨንቃና አማርጣ ስትለብስ ለምን እንደዚህ እንደማያምርባት ገረማት ። ነገሩን ሁሉ ተወችና ቀላል የምርጫ ፍልስፍና ውስጥ ገባች ፤ ሕይወት ሁሉንም ትለግሳለች ፤ ሁሉንም ታቀርባለች ። እና ሁሉም እንደ የምርጫውና አቅሙ ሕይወት ከለገሰችውና ሕይወት ካቀረበችው ይቋደሳል ። ማን ጊዜ ፈጅተው ፤ ገንዘብ አውጥተው አዕምሮን አስጨንቀው ዘመድ አዝማድ አማክረው የመረጡት ጉፉያ ሆኖ የሚገኝበት ጊዜ አለ ። እርር ያደርጋል ። ደሞ ሳይጨነቁ ፤ ሳይጠበቡ እጅ እንዳመጣ ያገኙት ሲጥም ፤ ሁሉን ሲያስንቅ ይገኛል ። ከማስደሰት ያልፍና ያስገርማል። ይህ የሕይወት እንቆቅልሽ ሐረገወይንን ሊገባት አልቻለም ። ሕይወት ተጨንቂ ተጠብቢ ያቀረብኩላቸውን እንዴት ይመርጣሉ? እኔ ላልታመን? እኔ ላልመስገን? እያለች ቂም እየያዘች ይሆን?

ያ ጐረቤት የሚፈራው ፡ ጐረቤት የሚያከብረውና የሚተናበት የወንጂራድ ቤት በየሰለቱ ደምቆ ይታይ ነበር ። ጀምበር ዘቅዘቅ ስትል ጀምሮ እስከ መንፈቀ ሌሊት ድረስ ሲበላበት ፡ ሲጠጣበት ፡ ሲወጋበት ነበር ··· ዘመድ አዝማዱ ተሰባስቦ ። ይህን ሁሉ ሲያስተናግድ የኖረው ፡ የወንጂራድ ሳሎን ዛሬ ውታቢ ራቀው ። የሚጐበኘው አጣ ። ማታ ማታ ያን የለመደውን ድምቀት ተንፍጐ ብቻውን ፈዞ ያመሻል ፡ ብቻውን ፈዞ ያድራል ። ወንጂራድ የቤቱ ምሰሶ የቤተሰቡ አድባር የትም ይዋሉ የት ቤታቸው እንደ ገቡ ወደ መኝታ ክፍላቸው ያመራሉ ። አልጋ ላይ ሆነው ራት ያዛሉ ፡ እዚያው ይበላሉ ።

ወይዘሮ ተዋበች ቀድሞውንም ቁጥብና ዝግ ናቸው ፡ ዛሬ ደግሞ የባሰውን ተዘግተው የመኝታ ክፍላቸውን የሙጥኝ ብለዋል ። ሐረገወይን ማታ ቤቷ እንደ ደረሰች ቀጥታ ወደ መኝታ ክፍሏ ትገባለች ፡ ከዘነበች ጋር ጥቂት ትጨዋወትና ትተኛለች ። አባቷን አኮረፈች ፡ አባቷም አኮረፏት ። ቤቱ ሁሉ ተኳረፈ ፡ በዚህ ራሷን እንደ ትልቅ ወንጀለኛ አድርጋ ማየት ጀመረች ። ረፍት ነሣት ። ሁልጊዜ ራሷን ለመደለል ትሞክራለች ፡ ግን አይሆንላትም ። በሰው ላይ የምትጠላውን ብቻ መንጋገር እሷም ዐይኗ እያየ ገባችበት ።

የምርጫን ፍልስፍና እንዶታ ለጥቂት ጊዜ አዕምሮዋን አስጨንቃ ቆየችና መልሳ ወደ መስተዋቱ ተመለከተች ። አለባበሷ ያማረ ፡ መልኳ የተዋበ ግን አዕምሮዋ የተረበሸ ሴት መስተዋቱ ውስጥ ታየቻት ። አዘነችላት ። እየተዟዟረች ራሷን መስተዋቱ ውስጥ ተመለከተች ። ቀጥ ብላ ቆማ ፈገግ አለች ። መስተዋቱ ውስጥ ያለችው ሐረገወይንም ፈገግ አለች ። አፈረች ፡ አንገቷን መለስ አደረገችው የድንጋጤ ያህል ብርግግ ብላ ፡ ሌላ ሰው አልነበረም ራሷን አፈረች ። ደሞ ራስን ማፈርን ያህል የሚያስፈራ የለም ። የቁምሳጥኗን በር በኃይል ወርውራ ዘጋችና ወደአልጋዋ ሔዳ በግርጌ በኩል ጠርዙ ላይ ተቀመጠች ። ለጥቂት ጊዜ አቀርቅራ ቆይታ ቀና ስትልና የመኝታ ቤቷ በር ሲንኳኳ አንድ ሆነ ። “ማነው?” ም

አላለችም ተነሣችና ከፈተች ።

ዛማኑኤል ጸጉሩን እንዳንጨባረረ ዐይኑን በእጁ እያፈተገ በሩ ላይ ቆሟል ። ምንም አላለችውም ። ተመልሳ አልጋዋ ጠርዝ ላይ ተቀመጠች ። ዛማኑኤል እንደ ገባ በሩን ዘጋ ። ከተቀመጠችበት ኰትኳ አስነሣት ፤ እየተንሟነጨች ተነሣችለት ። ከፊት ለፊቱ አቁሞ ከግር እስከራሷ ደጋግሞ ተመለከታት ። ሐረገወይን ሥራው ገርሞአት ዝም ብላ ትመለከተዋለች ፡ "ሐርዩ" አለ የተንጨባረረ ጸጉሩን በእጁ እየዳሰ ። "ምን ሆንክ ፤ ደሞ ምንልትል ነው?" አልጋዋ ጠርዝ ላይ ተመልሳ ቁጭ አለች ።

"ምን መሰለሽ ፡ ሙች ነስ ብለሻል ። እንደ ጧት ፀሐይ እንዳዘ ደምቀሽ ስመለከትሽ መንፈሴ ደስ ይላታል ። እያየሽ ቀኑን ሁሉ ደስ ብሎኝ ይውላል ሙች ። ሕይወት አብባ እንደ አደይ አበባ ፈክታ ትታየኛለች ። መዓዛዋ አዲስና እንግዳ ይሆንብኛል ። ጨለማውን ገፎ ብርሃንን እንደሚያነግሰው የማለዳ ጮራ ትንቦገቦግልኛለች ። እያየሽ ሐረዬ! ሕይወት ከፋት ተንኮልና ምቀኝነት የማይታወቅባት ፍንፍን ቡቡ ትሆንልኛለች ።" ተንደረደረና ግንባሯ ላይ ሳም አደረጋት ።

"የአንተ ሕይወት ደሞ ቅጧ የጠፋ ናት" ገላመጠችውና ከተቀመጠችበት ተነሣች ። ወደ መስኮቱ ሔደች ። መስኮቱን ብርግድ አድርጋ ከፈተች ።

"ምነው ሐረዬ የእኔ ሕይወት ቅጥ የላትም?" አጠያየቁ ቅያሜ አዘል መሰሎ ተሰማት ።

"እይ ስቀልድህ ነው ፤ ቀልድ አታውቅም እንዴ?"

"እንዴ በደንብ እንጂ ዝንጥ አድርጌ ነው ቀልድ የማውቀው! ምን መሰለሽ ዛሬ ድል ድል ይሸተኛል?"

"የምን ድል?"

"ዛሬ እኮ ነው የቤተሰብ ስብሰባችን ፤ እያየሽ ድል ድል ይሸተኛል የአንቺና የእኔ ድል ገባሽ" እንደ መሽከርከር አለና ወደ

መስኮቱ ተጠግቶ ቆመ ። ሐረገወይን ቶሎ ምላሽ አልሰጠችውም ፤ የተለያዩ ሐሳቦችን ማውጣት ማውረድ ጀመረች ። ቁርጥ ያለ ውሳኔ ቶሎ ልትሰጥበት ባልቻለችው ሐሳብ ከራሷ ጋር ሙግት ገጠመች ። ጭልጥ ብላ ሐሳብ ውስጥ ገባች ።

“ስሚ ሐረ” አስደንግጦና ከሐሳቧ መለሳት ።

“ይኸውልሽ ትናንት ቤት እነግርሻለሁ ብዬ ሳልነግርሽ በቤት ወጣሽብኝ ማታ እነግርሻለሁ ብዬ ነበር አልተሳካልኝም ። አምሽቼ ገባሁ። በጣም አምሽቼ ነው የመጣሁት ፤ ተኝተሻል ። ታዲያ አሁን ማልጄ መነሳቴ እንደ ትናንቱ በቤት ወጥተሽ ጉድ እንዳትሰሪኝ ብዬ ነው። ዛሬ ደሞ ሰንበት ነው ። እዚሁ ነው የምትውይው አይደለም?” ዝም አለችው ። ጠበቃት ፤ ዝምታ ።

“እዚህ አይደለም እንዴ የምትውይው?” ድምፁን ከፍ አደረገና ጠየቃት ።

“የለም የምሔድበት አለኝ ዛማኑኤል” ዛማኑኤል ድንግጥ አለ ። ያንን የተንጨፈረረ ጸጉሩን አሻሸና ፤

“አይሆንም ሐረ ፤ ፈጽሞ አይሆንም ፤ ምን መለስሽ! ምነው ተመካከረን በአለፉ በኩል ወንዲራይን እናነግራቸው ተባብለን ። ምነው? ምን መሰለሽ? እትዬ ከትናንት ወዲያ ነው የነገረችን ፤ አንተው ንገራት ብላ ቱምንገረኝ ሰው አጣንታ ።” አቋረጠና ራሱን አከከ ። በልመና አስተያየት ዐይኑን እያቁለጨለጨ ። “እየሽ የዕለት ተዕለት የሕይወት ጥሪ አለ አይደለም ፤ ሁለቱንም ቀን አልሆነልኝም። አለ አይደለም በጣም አመሸሁ።”

“ምን አለ አንተ ማምሸቱ ቢቀርብህ?” ተቆጣች ። አጠያየቋ ለምን ሳትነግረኝ ቀረህ ለማለት አልነበረም ፤ እያመሸ መምጣቱን አትወድለትም ። በዚህ አጋጣሚ ልትቆጣው ፈለገች ።

“እውነቱን ነው የምልህ ፤ ምን አለ ቢቀርብህ?” ደገመችና አፋጠጠችው ፤ የሚሰጠው መልስ አልነበረውም ። ጥያቄዋ ፈጽሞ ያልጠበቀው በመሆኑ ግራ ተጋባ ። ለምን እንደ ጠየቀችው

ይገባዋል። ለእሱ በመቆርቆርና በማዘን መሆኑን ስለሚያውቅ ጨነቀው ፤ ግን የሚመልሰው ነገር አጣ ። መልስ አጥቶ ሲጨነቀው አጭበርብሮ የሚያልፍበትን ዘዴ አሰበና ሣቅ አለ ።

"ይገርምሻል ሐሪ በዚህች ዓለም ላይ ብዙ የማላውቃቸው ነገሮች ስላሉ ፤ በቀን ሰውን ማየት እፈራለሁ ። በጠራራ ፀሐይ በሰው መኻል መጓዝን እፈራለሁ ። 'እየው እየው ይኸ ጅል በዚህች ጠባብ ዓለም ውስጥ ስንት የማያውቀው ነገር እያለ ለዐዋቂዎች ፤ ለፈላስፎች የምትፈነጠቀውን የፀሐይ ብርሃን ሊጋራ ቀን ሲጓዝ ታዩታላችሁ?' እያሉ ሰዎች የሚጠቃቀሱብኝ ይመስለኛል ። ታዲያ የሰውን ይሉኝታ ፈርቼ ለእኔ ቢጤ አላዋቂ የዋሆች ተፈጥሮ የለገሰችን ጨረቃ ካለች በእሷ እየተመራሁ ፤ እሷ ከሌለችም ዐዋቂዎች በሠሩልን የኤሌክትሪክ ብርሃን እየታገዝሁ ቤቴ እደርሳለሁ ። ይገርምሻል ምሽቱ ለእኔ ቢጤዎች የተፈቀደልን በመሆኑ ፤ እንደ ልቤ እዝናናለሁ…" ራሱን ክፉኛ አከከው ። በልቶት አልነበረም ፤ በአፉ የሚያወጣው ውሸት ስላልጣመው ራሱን በማከክ በሚሰማው ድምፅ ጆሮውን ለማታለል አስቦ ያደረገው ነበር ። ለእሱ ያልጣመው ለሐረገወይንም አይጥማት ። በዚሁ እስታኮ የወሬውን አቅጣጫ ሊለውጥ ፈለገ ።

"እኔ የሚገርመኝ ይልቅ የጋሽ ገበየሁ ንዝንዝ ነው ። አቤት! አምሽቼ ስመጣ ደስ ሲላቸው! የዓለም ስድብ ያወርዱብኛል ፤ መቸስ ብንማረር እንደማልለቃቸው እያወቁ እንጂ ቢደበድቡኝም ደስታቸው ነው ። አቤት ትናንትማ ሌላ አድርጐአቸው ነበር ። ይሰድቡኛል ፤ ይገላምጡኛል መቸስ አባት ናቸው ብዬ ዝም እላቸዋለሁ ። ይገርምሻል እኮ ሐረዬ! ሲሰድቡኝ መናደድ ያለብኝ እኔ አይደለሁም እንዴ? ለምን መልስ አልሰጠኝም ብለው ነው መሰል ክፉኛ ይናደዱብኛል ። አቤት ያን ጊዜ እኔ ደስ ሲለኝ ። አየሽ ምቀኛ ነኝ ማለት ነው እኮ! ሌላው ሲከፋና ሲናደድ ከተደሰትኩ ምቀኛ እንጂ ሌላ ምን ልሆን እችላለሁ።"

"ምቀኝነቱን ተወውና ፤ እሳቸውና አንተን የሚያጣላ ነገር

ምን አለ? ሁልጊዜ ነው ሰደቡኝ ገላመጡኝ የምትለኝ ። እኮ ምንድን ነው የሚያጣላችሁ?”

ማምለጫ ብሎ ያመጣው የባሰውን የከበደና ምላሽ የማይሰጥበት ሆነበት ። ዐይኑን ፍጥጥ አደረገ ። ሲጨንቀው ማቁ ይመጣበታል ።

“የሚገርም እኮ ነው ፤ ትናንት ምን ሆነ መሰለሽ ። ስድስት ሰዓት ይሆናል እንኳኳሁ ፤ እንኳኳሁ ዝም አሉኝ ። ተኝተው ይሆናል አልኩና በመኝታ ቤታቸው ጥግ ቀረብኩና ቀስ ብዬ ‘ጋሼ ገበየሁ ጋሼ ገበየሁ” አልኳቸው ‘ማነው’ አሉና ጮሁ ። “እኔ ነኝ እኔ ነኝ” አልኩአቸው ። ብጠብቅ ፤ ብጠብቅ ሊከፍቱልኝ ነው ። መልሼ ተጣራሁ ። እየተነጫነጩ ከፈቱልኝ ፤ መቸስ ተይኝ ውሃ የማያስኝ ዱላቸውን ቀስረው አፈጠጡብኝ ። ዝም አልኩ ፤ ‘እኔ የምልህ በጊዜ አትገባም እንዴ? ስታርስ ወይ ስትነግድ ውለህ ጥሪት ይዘህ የመጣህ አትመስልም? አውደልዳይ ፤ አሳዳሪዎችህ በጊዜ ሲገቡ አንተ የማጌታ ነህ? ተናገሩኝ ባይ ፤ ወጠጤ ፤ ምነው የስመኝ ውሾች ሰውን ሁሉ ሲበሉ አንተን አይበሉህ ፤ ለካ ውሻ ውሻን መች ይበላል..?’ አያልሉሽም ። በጣም አዘንኩባቸው ። እኔ ደግሞ ጓደኞቼ ትንሽ ብር ሰጥተውኝ ስለነበር ፤ አስቤ እስቲ እሳቸውም እኮ ወጣ ማለት ያምራቸዋል ሻይ ጠጡ ብዬ እሰጣቸዋለሁ ብዬ አምስት ብር አስቀምጬላቸው ነበር ፤ እንዲያውም ይኸውልሽ” … ኪሱን ደባበሰና ከሱሪው የኋላ ኪስ የተጨባበጠች አምስት ብር አውጥቶ አሳያት ፤ “ይህችን ብር ለእሳቸው ብዬ ነው ያስቀመጥኳት ። ጠጋ ብዬ ልሰጣቸው አሰብኩና ሲሰድቡኝ ጊዜ በሸቅሁ ፤ ብሬን መልሼ ኪሴ አስገባሁና ወደ መኝታዬ ። … ትናንት ያነበብኩአቸው የፍቅር ታሪኮች ይገርሙሻል ፤ በጣም በጣም …”

“የለም የለም” አቋረጠችው “የፍቅሩን ታሪክ ተወውና የጀመርከውን ጨርስልኝ”
“ጨረስኩ እኮ ሐረ ።”

"እንዲያውም አልጀመርክልኝም ። የጠየቅሁህን እኮ አልመለስክልኝም ። ዓማኑኤል ሙት አልመለስክልኝም ። እቀየምሀለሁ ከእኔ የምትደብቀው ነገር አለህ እንዴ ዓማኑኤል? ንገረኝ እንጂ እኔ እምልህ ምንድን ነው የሚያንታርካችሁ? ያከብሩህ ነበር ፣ ይወዱህ ነበር ፣ አሁን ምን ተፈጠረና ጠብ ይረሳችሁ ፣ ሙት እቀየምሀለሁ ንገረኝ" አልጋዋ ጠርዝ ላይ ቁጭ አለችና አንጋጣ ትመለከተው ጀመር ።

ሐረገወይን ራሷን ወንጀለኛ አድርጋ ትቆጥራለች ። ቤቱ ውስጥ አለመግባባት ካለ ምክንያቱ እኔ እሆናለሁ ብላ መስጋት ከጀመረች ውላ አድራለች ። አሁንም የምትጠብቀው መልስ "በአንቺ ምክንያት" የሚል መስሏት ተጨንቃለች ። ዓማኑኤል ግን ይህን ጭንቀቷን አልተረዳላትም ። እሱም በበኩሉ ተጨንቋል ። የሐረገወይን መኝታ ክፍል ወለል መልስ ያቀብለው ይመስል አቀርቅሮ አፈጠጠበት ። ቀና አለ ካቀረቀረበት ። ፊቱ ሁሉ ፈገግ ብሏል ፣ መደናገጥ የፈጠረው ፈገግታ ። ውስጥን ዘልቆ የማይገባ ፈገግታ ፣ ፊትም ላይ ብዙ የማይቆይ አርቴፊሻል ፈገግታ ። ከሐረገወይን ጐን ቁጭ አለና እጇን ትከሻዋ ላይ ጣል አደረገ ።

"ምን መሰለሽ ሐረዬ ፣ ሕይወት እንደምታውቂያት ዥንጉርጉር ናት ። እኒህ ሰው የሕይወትን ምንነት መለየት ተስኗቸው ግራ የተጋቡና የራሳቸው ሕሊና የሸፈተባቸው ይመስለኛል ። ሕሊና ሲሸፍትብሽ ደግሞ አይጣል ነው ።" ቆም አለና አሰበ ። "እየሽ ሕሊና ያለራሱ የሚፈራው ዳኛ ስለሌለ ያስቸግራል ከሸፈተ ። እና እኒህ ሰው የዕድሜያቸውን ትልቅነት ከክብራቸው ኢምንትነት ጋር ያስተያዩትና ሐቁን ለመቀበል ሕሊናቸው ይጠምባቸዋል ። ለማዘዝ ፣ ለመቆጣት ፣ ለመገልመጥ ፣ ለመደባደብ ይፈልጋሉ ። የዚህ ጊዜ በእርሳቸው ግምት ከእኔ ያነሰ ሰው ነው ብለው ፣ አሸንፌዋለሁ ብለው የሚያስቡትን ሰው ይፈልጉና እሱን ላንገላታህ ይሉታል ። እየሽ ሕይወት የጣለችባቸውን ዕዳ ። ታዲያ የሚበልጡትና የሚያሸንፉት ሰው ሲፈልጉ እኔን አገኙ ። እኔም ለሸፈተ ሕሊና እርዳታ

ለመስጠት በመታደሌ አያከፋኝም ። ደስ ይለኛል ። ተቆጡኝ ፡ ሰደቡኝ ፡ ገላመጡኝ ብዬ አልቀየማቸውም ፡ የሕይወት ዕዳ ነዋ··· የሕይወት ··· ”

“ተው እባክህ ምነው ሕፃን ልጅ አደረግኸኝ እንዴ” ሐረገወይን ተቆጥታ ተነሣች ። ስትነሣ ትከሻዋን ተመርኩዞ የነበረውን የዛማኑኤልን እጅ ገፍትራ ወረወረችው ። ዛማኑኤልም ተከትሏት ተነሣ ። ተንሥተው ተፋጠጡ ።

“እሺ ይሁንልህ ፡ እሳቸው የሚጣሉት መች አንተን ብቻ ሆነና፡ ዘንበችም አይወዱኝም ፡ ይሰድቡኛል ብላኛለች”

“ልክ ነሽ ሐረ...እሷንም አሸንፋታለሁ ፡ ሠራተኛ ነች ፡ የበታች ነች ብለው ያስቧታል”

“እህ ታዲያ ለምን ከእትዬ ድርቤ ጋር አይጣሉም ፡ ከሠራተኛ ጋር የመጣላት ዐመል ካለባቸው ? ድርቤ ጋር ግን ሸርክ ናቸው ፡ የለም የደበቅኸኝ ነገር አለ እውነቱን ንገረኝ”

ዛማኑኤል ጥያቄው ወሰብሰብ አለበት ። ከዚህ የሚወጣበትን ዘዴ አሰበና አንድ ነገር ትውስ አለው ።

“የለም ሐረ ምን መሰለሽ ! እትዬ ድርቤ ሠራተኛም ቢሆኑ እኮ በዕድሜ እኩያ ስለሆኑ እሳቸውን ለማዋረድ ሕሊናቸው አይደፍርም... እባክሽ ለምን በጥቃቅን ነገር ራሳችንን እናስቸግራለን ? በቃ ተይው...ተይው በቃ” እየጐተተ አልጋዋ ላይ አስቀመጣት ።

“አንተው እኮ ስላመጣኸው ነው ፡ አንድ ጊዜ ገላመጡኝ ፡ አንድ ጊዜ ሰደቡኝ ትላለህ ፡ ሲጠይቁህ ደግሞ ሕይወት ሕይወት ትላለህ ፡ ምን ላድርግ እኔ...”

“ተይው አልኩሽ ተይው” ከጐኗ ተቀመጠና ኪሱን መደባበስ ጀመረ ፡ ከሸሚዙ ኪስ የተጣጣፈ ወረቀት አወጣና መገላለጥ ያዘ። “ሐረ ትናንት ሳነብ አንድ ደባሪ የፍቅር ታሪክ ገጠመኝና ወደ አማርኛ መልሼ ከኪሴ አስቀመጥኩት ። ላንብብልሽ” አንገቷን ቀና አደረገና አፍጥጦ አያት ፡ “ላንብብልሽ ሐሬዬ ? ግን የምልሽ

ከእንትን በኋላ የጻፍኩት ስለሆነ ፣ አማርኛው ቢወላገድብሽ እንዳትቀየሚ ፣ እሺ.... ላንብብልሽ ?” ፈገግ አለ ።

“እና... እሺ አንብብልኝ”... እንዲቀየምባት አልፈለገችም ። የጻፈውን ላንብብልሽ ብሏት እንቢ ካለች ያኮርፋታል ። ‘አንብብልኝ’ ስትለው ደስ አለው ፣ ወረቀቱን እየገላለጠ ከተቀመጠበት ተነሣ ።

“ከጥንታዊ የግሪክ አፈ ታሪክ ያገኘሁት ደባሪ የፍቅር ታሪክ ነው አድምጭኝ ።” ድምፁን ለስለስ አድርጎ ማንበብ ጀመረ ።

“የንግሥት ሴሚራሚስ ከተማ በነበረችው ባቢሎን ውስጥ ፒራሙስና ቲስቤ የተባሉ በውበታቸው አገር ያደነቃቸው ወንድና ሴት ወጣቶች ነበሩ ። አንድ ላይ አደጉና በመጨረሻ ሁለቱም በፍቅር ወደቁ ፣ ፒራሙስ ቲስቤን ወደደ ። ቲስቤም ፒራሙስን አፈቀረች ። ፍቅራቸው ጠና ። ለመጋባትም ቆረጡ...ግን ወላጆቻቸው እንዴት ተደርጎ ብለው ከለከሉ ። አይ ጣጣ! ግን ፍቅር እኮ ይቅር ቢሉት የሚቀር አይደለም ፣ እሳት በተዳፈነ መጠን ግለቱ እንደሚጨምር ሁሉ ፍቅርም መኻል ጣልቃ ከገቡበት የባሰውን ይጠነክራል ። ደፋርና ጢስ መውጫ አያጣም የሚባለው ዓይነት ፍቅርም [illegible] መንገዱ ብዙ ነው ። እኒህን በልባቸው ውስጥ የፍቅር ነዲድ የሚንቦገቦግባቸውን ወጣቶች መለያየት የማይሞከር ነበር ።

“ሁለቱ ወጣቶች ጐረቤት ናቸው ፣ የሚለያቸው አንድ ግድግዳ ነው ፣ ታዲያ ይኸ ግድግዳ አንድ ቀዳዳ አለው ። ቀዳዳውን ከዚህ ቀደም ማንም አይቶት አያውቅም ። የፍቅር ዐይን ግን የማያየው የለውምና እኒህ ወጣቶች ይህንን ቀዳዳ ደረሱበት ። በቀዳዳው እየተገናኙ የፍቅር ወግ ማውጋት ጀመሩ ። ያሻቸውን ሁሉ እያወጉ ፍቅራቸውን ተገላለጡ ። ግድግዳው ግን ድምፅን ከማሳለፍ ውጭ መልክ ለመልክ እንኳ ተጠጋግተው ለመተያየት የሚያስችል አልነበረም ። ቢሆንም ወደዱት ። የፍቅር ወጋቸውን ሲያወጉ ይቆዩና ‘ደኅና እደር ፣ ደኅና እደሪ’ ተባብለው ሲለያዩ ፣ ወንዱም እፊቱ ያለውን ሴቷም እፊቷ ያለውን ግድግዳ ይስማሉ ። ‘እፍ ለእፍ

ተገጣጥመን እሷ ከእኔ፡ እኔ ከእሷ ከንፈር የማር ወለላ እንድንቀምስ ባታስችለንም ፡ በሁለታችንም ጆሮዎች የፍቅር ሐረጐች እንዲደርሱ አድርገሀልና ለአንተ ታላቅ ከበሬታ አለን' እያሉ ያንን ግዑዝ ግድግዳ ያመሰግኑታል ። ቀኑን ሙሉ በዚያች ቀዳዳ ሲያወሩ ይውላሉ ፡ ጆምበር ዘቅዘቅ ስትል ይሰነባበታሉ ።

''ማለዳ ጐሕ ሲቀድና የፀሐዩዋ ብርሃን ጤዛውን እያሟሸሸ ሲሔድ ወደዚያች ቀዳዳ ይጠጋሉ ። ስለ ፍቅራቸው ፡ ስለ ወደፊቱ ሕይወታቸው ፡ አሁን ስላሉበት ሁኔታ ሲያወሩ ይውላሉ ፡ ሲያሳዝኑ። አንድ ቀን አንድ ታላቅ ውሳኔ ላይ ደረሱ ። ያንኑ ዕለት ማታ ተያይዘው ለመጥፋት ። ሁለቱም በነጻነት ፍቅራቸውን ለመወጣት ። ከከተማዋ ርቀው ወደ አንድ ገጠር ለመሔድ ተስማሙ። ከሥሩ የጠራ ምንጭ ካለበት ነጫጭ ፍሬዎች ከሚያበቅለው ዛፍ ሥር ከታላቁ የኒኑስ መቃብር ለመገናኘት አቀዱ ። እቅዳቸው ሁለቱንም አስደሰታቸው ። ግን እንዴት ቀኑ ይመሽላቸው ። ያ አንድ ቀን ዓመት መስሎ ታያቸው ፡ ግን መሸ ። የደመቀች ፀሐይ እንዳማረባት አትቆይ ፡ ፀሐዩዋ ጠለቀችና መሸላቸው ። ቲስቤ ሰው አየኝ አላየኝ እያለች እየሰጋች ሹልክ ብላ ከቤቷ ወጣች ቀድማ። እየበረረች ሔደች ፡ ወደዚያ ወደ ተቀጣጠሩበት ወደ ታላቁ መቃብር፡ ስትደርስ ግን ፒራሙስ አልነበረም ፡ ዘገየባት ።

"የፍቅር ረመጥ እያቃጠላት ቁጭ አለች ልትጠብቀው ፡ ግን ያልጠበቀችው ነገር መጣባት ። አንዲት እጅግ የምታስፈራ አንበሳ ከፊት ለፊቷ መጣችባት ። አንበሳዋ ያደነችውን በልታ አፏ በደም ተለውሶአል ። አመጣጧ ከምንጩ ውሃ ለመጐንጨትና የበላችውን ለማወራረድ ነበር ። ቲስቤ አንበሳዋን ስታይ ሽሽቷን ተያያዘችው ። ስትሸሽ የለበሰችው ነጠላ ወደቀና ቀረባት ። አንበሳዋ ውሃዋን ጠጥታ ወደ ጫካዋ ለመግባት ስታመራ የቲስቤን ነጠላ አገኘች ፡ ብጥትጥቅ አደረገችና ረጋገጠችው ።

"ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ፒራሙስ የተቃጠሩበት ቦታ ደረሰ። የተመለከተው ቲስቤን ሳይሆን የነጠላዋን ቅዳጅና የአንበሳ

ኮቱ ነበር ፤ ዘገንነው ። 'ቲስቤ ሞታለች…በቃ ሞታለች' አለ ። ያችን ውብ ፍቅረኛውን በዚህ አደገኛ ቦታ አላንድ ጠባቂ ብቻዋን ጥሎ በመዘግየቱ ተቃጠለ ። 'እኔ ነኝ ፤ እኔ ነኝ የገደልኩሽ ፤ እኔ ነኝ ጠላትሽ' አለ ። ጉንበስ ብሎ የነጠላውን ቅዳጅ አነሣና እየሳመውና እያለቀሰ ወደዚያች ዛፍ አመራ ። 'እያ አሁን ደግሞ የእኔን ደም ትጠጪያለሽ' ሰይፉን መዘዘ ፤ ሽንጡ ላይ ሳገው ፤ ደሙ ቲንን እያለ ተረጨ ። ያቺን ዛፍ አቀላት ፤ ነጩ ፍሬ ሁሉ ቀላ ።

“ቲስቤ እንበሳዋን ፈርታ ብትሸሽም ፤ አጥብቃ የሰጋችው ፍቅረኛዋን እንዳታጣ ነበር ። ወደዚያች ነጫጭ ፍሬዎች ወዳሉአት ዛፍ ለመመለስ ወሰነችና ከተደበቀችበት ወጣች ። ቦታው ደረሰች ፤ ግን ዛፏን ልታገኛት አልቻለችም ፤ እርግጥ ዛፍ አለ ። ግን አንድም ነጭ ፍሬ የለበትም ፤ ደነገጠች ። ትኩር ብላ ስትመለከት አንድ የሚላወስ ነገር ታያት ። ተንቀጠቀጠች ። የራሷን ዐይን ልታምነው አልቻለችም ። ፒራሙስ በደም ተለውሶ ወድቋል ። ያጣጥራል ። ላዩ ላይ ወደቀችና ተጠመጠመችበት ። የቀዘቀዙትን ከንፈሮቹን በከንፈሮቿ ዳሰሰቻቸው ። 'ስማኝ የእኔ ጌታ አንድ ጊዜ አድምጠኝ' ለመነችው ። 'እኔ ነኝ ቲስቤ ነኝ ፤ ቲስቤ ፍቅረኛህ' አነባች ። ፒራሙስ 'ቲስቤ' የሚለውን ቃል ሲሰማ ዐይኖቹን ገለጥ አደረገ ። ግን አፍታም አልቆዩ… ሞት መልሶ ከደናቸው ።

“ቲስቤ ፒራሙስ ጐን የወደቀውን ሰይፍና የነጠላዋን ብጥስጣሽ ትኩር ብላ ተመለከተቻቸው…ነገሩ ገባት ። 'ለእኔ ባለህ ፍቅር ራስህን በእጅህ አጠፋህ ? እኔም ወንድ ይውጣኝ ሞት እንኳ ሊለየን አይችልም? ፒራሙስ ጐን የወደቀውን ሰይፍ እንሥታ ደረቷ ላይ ሰካችው ።

“እማልክት አዘኑላቸው ፤ ወላጆቻቸው አዘኑላቸው ። ያች በደም የቀላች ዛፍም ለእነዚህ እውነተኛ ፍቅረኞች ዘላለማዊ መታሰቢያ ሆና ትኖራለች”

እንብቦ እንደጨረሰ ወረቀቱን አጣጠፈና ሸሚዙ ኪስ ውስጥ ከተተ ። ሐረገወይንን የግልምጫ እየተመለከታት ከጐኗ ቀና አለ ።

“ደባሪ የፍቅር ታሪክ ነው ። ይኸውልሽ ሳነበው ድብር እያረገኝ ፡ አንብቤ ስጨርስ አዘንኩ ። እና የዘመናችን ፍቅረኞች እንዲህ ዓይነት ክፉ ዕጣ እንዳይደርስባቸው ሌት ማታ እጸልይላቸዋለሁ አልኩና ገለበጥኩት ፡ እኪሴ ውስጥ አስቀመጥኩት እልሻለሁ ። ደባሪ ታሪክ አይደለም ሐረዬ ?”

ሐረገወይን ከነበረችበት የሐሳብ ባሕር ውስጥ ተንቦጫርቃ ስትወጣ ፊንጠር ብላ ከተቀመጠችበት ተነሣች ። ዛማኑኤል ላይ አፈጠጠችበት ።

“ደሞ ደባሪ ይላል ! ደባሪ አንተ ነህ እርኩስ ?”

“ምነው ሐረዬ ምን አደረግሁሽ”

“ለምን ታነብልኛለህ ፡ የማልፈልገውን ታሪክ ?”

“ይኸ እኮ የጸሎቱ ክፍል ነው ፡ ለዘመናችን ፍቅረኞች ሁሉ የምጸልይበት ዳዊቴ ነው ፡ ለአንቺም ለእኅቴ እጸልይልሻለሁ አይዞሽ” ጐተተና አስቀመጣት ።

“እየህ ዛማኑኤል ፡ ቤተሰቦቻቸው ኋላ ከማዘን መጀመሪያ እንጋባ ሲሏቸው እሺ ቢሉ እኮ ይኸ አሳዛኝ እጣ አይወድቅባቸውም ነበር ። እና ራስህ ደባሪ ነህ ደባሪ ታሪክ የምታነብልኝ” እቀርቅራ ዝም አለች ።

ሁለቱም አቀርቅረው ተኮራርፈው ለጥቂት ጊዜ ቆዩ ። ዛማኑኤል ከእቶ ገበየሁ ጣጣ ለመውጣት ብሎ ፈጠርኩ ያለው ብልሀት መልሶ ራሱን አሳዘነው ። ካቀረቀረበት ቀና አለና ሐረገወይንን ተመለከታት ። እንዳቀረቀረች ናት ። በግድ ቀና አደረጋት ። እንደ ታላቅ ወንድም ተቆጣት ። ዐይኖቿ ላይ ተቋጥረው የነበሩትን የዕንባ ዘለላዎች ጠረገላትና ተነሣ ።

“ሐርዬ በቃ ተነሽ ፡ ምነው ሕፃን ልጅ ሆንሽብኝሳ ! ስሚ እንግዲህ ተሰናጅና አብረን እንገባለን ፡ አሲቃ መምጫቸው ደርሶአል ። ጋሽ ወንዲራድ ፡ እትዬ ፡ አሲቃ ፡ አንቺና እኔ ነን የምንገኘው። ጋሽ ኃይለማርያምም ከተሻለኝ እመጣለሁ ብለዋል ። የምልሽ ሐሳብሽን ሳትደብቂ መናገር አለብሽ በቃ ፡ የዛሬው ቁርጥ

ቀን ነው ። እየሽ ካስረዳሻቸው እኮ…እኔ እርግጠኛ ነኝ ፡ እንቺን ልጆቻቸውን የሚቀጥሙ የሚያስቀይሙ አይመስለኝም ። በቃ ። ሳትፈሪ ሳትደብቂ ተናገሪ ፡ እኔም የበኩሌን እናገራለሁ ፡ እሺ በቃ ። እኔም ፊቴን ልተጣጠብ" ለመውጣት መንገድ ጀመረ ።

"ቆይ እንጂ ፡ ምን አስቸኮለህ" አለችው ለስለስ ባለ የሚያሳዝን ድምፅ ። አለበት ቦታ እንደደረቀ ቀረ ።

"እኔ የምልህ ምን ይሻላል ነው የምትለው ፡ እንደምታውቀው ዓለማየሁ ታሞአል ፡ ሆስፒታል እንሔዳለን ያልነው ደግሞ ዛሬ ነው፡ አሁን ይጠብቀኛል ቤት ሆኖ ፡ ምን አድርጊ ነው የምትለኝ ዛማኑኤል"

"የለም ሐሩ ስልክ ደውይለትና ግልጽ አድርገሽ ንገሪው ወይ ሐኪም ቤትም መቶ አለቃ ስንታየሁ ይውሰደው ፡ አይመስለሽም ሐሩዬ ። ይኸ እኮ ፈጽሞ ልትቀርበት የማትችይው ጉዳይ ነው። እኛው ፈልገነው እኛው ልናፈርሰው አይገባም ።"

"ቆይ እስቲ አሁን ምን አዲስ ነገር ይፈጠራል ብለህ ነው አለቃ አለቃ የምትለኝ? ምን ፍርድ ይፈርዱ ምን አዲስ ነገር ያመጡ ብለህ ነው ? አሁንስ አንተም እንደ እነሱው ሆንክብኝ" ብድግ አለች።

"የለም አልሆንኩም ። እየሽ አለቃ አዲስ ነገር ባያመጡ እንቺና እኔ በግድ አዲስ ነገር ማምጣት አለብን ። እኔ ምርጫሽ ምርጫዬ ነው ። ይህን ታምኚያለሽ ፡ የሚቀረን ትልቅ ነገር ጋሼ ወንዴራድ ምርጫሽን እንዲወዱልሽ በምርጫሽ እንዲስማሙልሽ ማድረግ ነው ። መተማመን ይኖርብናል ። ከተማመንን ደግሞ ጋሼ ወንዴራድን ማሳመን አያቅተንም ፡ በግድ ማሳመን አለብን ። እየሽ ምንም ቢሆን አባትሽ ናቸው ፡ ዛሬ ቢቀየሙ ነገ ይቅር ይላሉ ፡ ትናንት ባያምኑ ዛሬ ፡ ዛሬ ባያምኑ ነገ ያምናሉ ፡ ይለወጣሉ ። እኔ የምፈልገው ይህንን ነው ። አምነውልሽ ምርጫሽን ወደውልሽ መርቀው የፈለግሽውን እንዲድሩሽ ። ሕይወት እንደችሁ ይመራ

እንድትደምቅልሽ ፡ ሕይወት ሰቃ እንደረሳ መንገደኛ ቅርቅር እንዳትልሽ ፡ ጠመዝማዛ የሌለበት ቀጥ ያለች ጐዳና እንድትሆን ልሽ” ጠጋ አለና ግንባሯ ላይ ሳም አደረጋት ።

“በቃ ተስማማን አይደለም ሐረዬ”…ከጥቂት ዝምታ በኋላ “እሺ እንዳልክ” አለችውና በረዥሙ ተንፈሰች ። የእፎይታ ትንፋሽ ።

ዛማኑኤል የሐረገወይንን መኝታ ክፍል በር ከፍቶ ሲወጣ ፡ ዘነበች ከሩቅ ስትመጣ አየ ። በሩን ቀስ አድርጎ እየዘጋ ጠበቃት ። አመጣጧ ወደ ሐረገወይን ክፍል ነበር ። እግሩን አንፈራጦ በሩን ዘጋባት ። ቀና ብላ ዐይን ዐይኑን አየችው ሣቅ እየተናነቃት ። እጁን ይዛ ልትጎትተው ሞከረችና አቃታት ። አንድ እግሩን አነሣና ሰጣት እሱንም ጎተተችው አልነቃነቅ አላት ። ንድድ ሲላት እግሩን ወረወረችው ። ሰው አየኝ አላየኝ የሚል ፍራቻ ተናነቃት ።

“ኧረ እፈር…ሰው ቢያየንስ” አለችው ጠጋ ብላ ፡ ጠጋ ስትል አገጯን ያዝ አድርጎ የበለጠ ወደ እሱ አስጠጋት ፡ ቀና አደረገው አገጯን ። አንገቷ ላይ ያለውን በአራት ረድፍ የተሠራ ንቅሳት ትክ ብሎ ተመለከተው ።

“ኧረ እፈር…ሰው ቢያየንስ” ድምጿ እየሰለለ ሔደ ።

“በወረቀት ነበር ተጽፎ እምናይ ፡

ቀለም በሰው አንገት እንዲህ ያምራል ወይ ?” አገጯን ለቀቀና ትኩር ብሎ ተመለከታት ።

“ጉረኛ ዛሬ ነው የታየህ” አፈጠጠችበት ።

“በዐይንሽ ጦር አትውጊኝ”

“አበጀሁ” ገፈተረችው ። ሣቀና መንገዱን ለቀቀላት ። እየፈራች በሩን ከፈተችና ገባች ። ሐረገወይን ቁምሳጥኗን ከፍታ ልብሷን ትቀያይራለች ። ስታያት ደነገጠች ። “እንቺ ምን እየተባባላችሁ ነበር” የምትላት መስሎአት ድንግጥ አለች ፡ ፈዛ ቆመች ።

"እንቺ ፡ ተብየም አላት ፡ ዛሬስ ደኅና አደራችሁም እትዬ እንዴ..!"

"አቦ ጨርሽ ብዬ ነው" ጎንበስ አለችና ምራቋን ጢቅ አደረገች ። ድንግጥ ብላ በእግሯ ጠራረገችው ።

"እኔ እምልሽ ደሞ ማታ ከእትዬ ድርቤ ጋር ምንድን ነበር የምትጨቃጨቁት ። አሁንስ አበዛችሁት ፡ እንዳው አያስለቻችሁም እንዴ ልጄ ። ሌት ማታ ጭቅጭቅ ምንድን ነው?"

ዘነበች የድርቤ ወሬ እንዲነሣባትም አትፈልግ ። ሌት ማታ ይጨቃጨቃሉ፡ ይሰድቡአታል ፡ ይገላምጧታል ፡ ያስፈራሩአታል ብቻ ። እዚያው ተጨቃጭቀው ያለገላጋይ ይገላገላሉ ብቻ ። ከዚያ ውጭ ሌላ ሰው እንዲያነሣባት አትፈልግም ፡ ሰልችቶአታል ። መጀመሪያው ላይ ለምን ሰደቡኝ አዋረዱኝ ብላ ትናደድ ነበር ፡ የኋላ ኋላ ግን ውስጣቸው ክፋት የሌለበት የደረቅ ስካር ንዝንዝ መሆኑን ስትረዳ ችላ አለቻቸው ። አንድ ሰሞንም ጥርጣሬ ነበራት ። ገበየሁ ናቸው የሚያሰድቡኝ ብላ ትጠረጥር ነበር ። ግን ድርቤ ሞቅ ሲላቸው ገበየሁንም አብረው ስለሚሰድቡ ጥርጣሬዋ ተዋት ። ሐረገወይን ለባበሰችና ወደ ዘነበች ተጠግታ ለሰላምታ እጇን ሰነዘረችላት ። ዘነበች በሁለት እጆቿ ጨበጠቻት ፡ የአክብሮት አንገቷን ዝቅ አድርጋ ።

"መልሽልኝ እንጂ ምንድን ነው የሚያጨቃጭቃችሁ?"

ዘነበች ወደ በሩ ዘወር አለችና ምራቋን ጢቅ አደረገች ።

"ምንድን ነው ደሞ በየሥፍራው የምትተፊው ። ትናንትም ዝምብዬ አየሁሽ ፡ በየሥፍራው ስትተፊ ። በይ ቶሎ ጥረጊ ። እያደር ባላገር ትሆኛለሽ እንዴ?" ተቆጣቻት ሐረገወይን ። ምራቋ አስነውሯት አልነበረም ። ልታስተምራት ትፈልጋለች ።

"ኧረ እንቺ እትዬ ይኸን ወራት የሆንኩትን አላቀውም። እንዳው ተምድር ተነሥቶ ያቅለሸልሸኛል ፡ እኒህ ሴት ምኑን አብልተውኝ ይሆን እትዬ..." እትዬ ድርቤን በማማቷ መልሳ

ድንግጥ አለች ። ለቀልድ ብላ የተናገረችው ያስገምተኛል ብላ ሰጋች። ቢያስቀይሙአትም ክፉ ይሆኑኛል የሚል ጥርጣሬ የላትም።

"እኔ እምልሽ ተብየም አላቅ ምንድን ነው ግን የሚያጣላችሁ?"

"አቦ ተያቸው እሳቸውን ፡ ወይኔ ሀለት ሁኖባቸው ነው ። ቢቃ መሳደብና መነታረክ ይወዳሉ ። አቦ እሳቸውን ተያቸው እልቅስ እትዩ...እንደው ዛሬ ነገ እያልኩ ፈራ ተባ ስል እኮ ነው የከረምኩት" ዝም አለችና ለጥቂት ጊዜ ቆየች ። ልትናገር የፈለገችውን ነገር የፈራችው መሰለች ።

"ምኑን ነው ዛሬ ነገ ያልሽው?"

"እንደው ልጠይቅሽ ብየ" አቀረቀረችና በእግሯ ወለሉን አሰሰች ።

"ምኑን ነው የምትጠይቂኝ"

"ሰሞኑን እንደወትሮሽ አይደለሽም ፡ ጨዋታሽ ሁሉ ጥፍት ብሎብኛል ፡ ያ ቀልድሽ ሁሉ ርቆኛል ።" አቋረጠችና አጉንብሳ ምራቋን ጢቅ አደረገች ። ግን ማድረጓ አልታወቃትም ፡ "ታዲያ እንደ ምን ሁና ይሆን እያልኩ ሳስብ ነው የከረምኩት ። እትየ ሙች እንዳው ምን ሁነሽ ነው ?" ተሽከረመመች ፡ ነገሩን ቀደም ብላ ያወቀችው መሆኑን ሐረገወይን የምታውቅባት መስሎአት ሰጋች ። የሐረገወይንን ባሕርይ ለውጥ በሚገባ ደርሳበታለች ፡ ለምን እንደሆነም አውቃለች ፡ ግን ከራሷ ለመስማት ፈለገች ። ሐረገወይን ለምን ሳትጠይቂኝ የምትላት እየመሰላትም ቆይታለች ። ነገሩን ቀደም ብላ ባትሰማ ኖሮ አጠያየቋ እንዲህ አይሆንባትም ፡ አይሰባበርባትም ነበር ። ታዲያ ሐረገ ወይን የምታውቅባት መስሏት ሰጋች ።

"እንዴ ምን ሆንኩብሽ ተለወጥኩብሽ እንዴ ?"

"ምነው እትየ መቸስ የወትሮዋ እትየ አይደለሽም ። አንድ የሆንሽው ነገር አለ ፡ እንዴ አትሽ የለ እንዴ ! የገጠመሽ ነገር አለ"

"በምን ዐወቅሽ?" ሐረገወይን የመገረም ሣቅ ሣቀች ።

“ከራማዬ ይነግረኛል”

ዛማኑኤል በሩን ብርግድ አድርጎ ገባ ። ጸጉሩን አበጣጥሮ የክት ልብሱን ለብሶ እንደአትመ ሽክ ብሎአል ፣ ሁለቱም ገላመጡት ። በመምጣቱና ወሬያቸውን ስላቋረጠላቸው ሁለቱም ኀስ አላቸው ።

“ዘነበች ቁርስ ትሰጭናለሽ” ጠየቃት ።

ዘነበች ወጣች ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ለሁለቱም የሚሆን ቁርስና ሻይ ይዛ መጣች ። አስቀምጣ ተመልሳ ወደማዕድ ቤቷ አመራች ። ጥቂት ቆይተው ጠሯት ።

“ዘነብ እስኪ ሳሉን ሒጂና ማን ማን እንዳለ ተመልከችና ንይ”

“አለቃ ሲገቡ አይቻቸዋለሁ ፣ ጭዛዛውም ጠጅ ይዘውላቸው ሔደዋል”

‘ጭዛዛ’ የሚለው ቃል ከአፏ ሲወጣ ድንግጥ አለች ፣ አመለጣት ። እንደመሸከርመም አደረጋትና የግራ እጇን ትንሽ ጣት አፏ ውስጥ አስገብታ ነከሰቻት ።

“ደሞ ጭዛዛው ማነው?” ሐረገወይን ተገርማ ጠየቀች ።

“ተያት እባክሽ ጋሼ ገበየሁን ነው ፣ በቃ ሒጂ ማን ማን እንዳለ ተመልከችና ንይ ፣ እቃ የምታወጪ መስለሽ ያሉትን ሁሉ ተመልከችና ንይ?”

“ቆይ...ቆይ” ሐረገወይን ጮኸች ።

“ምነው ምን ፈለግሽ”

“የለም ስልኩን ትንቀልና ታምጣልኝ ፣ መጀመሪያ ዓለማየሁ እንዳይጠብቀኝ ልደውልለት...አይመስልህም ?”

“ግዴለም እኔ እደውልለታለሁ” ዛማኑኤል እጆቹን እያፍተገ ወጣ ።

ዘነበች እንደታዘዘች ወደ ሳሎን አመራች ፣ ልቧ ምቱን ጨመረባት ። ሰው የተሰበሰበበት ክፍል መግባት ትፈራለች ። ቀሚሷንና ነጠላዋን አስተካክላ የሳሎኑን በር ቀስ ብላ ከፈተች ። ዕቃ የምታወጣ ይመስል ወደቡፌው ተጠግታ ቆመች ። ደሞ

ተንበረከከችና የቢፌውን በር ከፈተች ። ጆሮዋን ከኋላዋ ወደምትሰማው ድምፅ ጣል አድርጋ አንድ ብርጭቆ አወጣች ። ጥቂት ቆየት ብላ መልሳ አስቀመጠችው ። ማንካ አወጣች ፣ መልሳ አስቀመጠችው ። የዳቦ ቢላዋ አነሣች ፣ መልሳ አስቀመጠችው ፣ ስታስቀምጠው የብርጭቆ እናት ነክቶ ጮኸባት ። ደነገጠችና ወደተሰበሰቡት ሰዎች ዘወር አለች ። በእሷ ላይ ትኩረት ያደረገ አልነበረም ።

ወንዲራድ መኻል ላይ ጉብ ብለዋል ። ወይዘሮ ተዋበች ነጠላቸውን አፍንጫቸው ላይ ጣል አድርገው ተቀምጠዋል ፣ ፈገግ እያሉ የአለቃንና የኃይለማርያምን ጨዋታ ያዳምጣሉ ። አቶ ገበየሁ ወዲያ ወዲህ ይላሉ ። አለቃ ፊት ጠጅ የተሞላበት ብርጭቆና ጠርሙስ አለ። ኃይለማርያም ይሥቃሉ ፣ የአለቃን ወግ እያዳመጡ ። ወንዲራድ አይናገሩም ፣ መኻል ላይ እንደአንበሳ ጉብ ብለው ዐይናቸውን ያጉረጠርጣሉ ። አንበሳ ባያገሳም ያስፈራል ።

ዘነበች ሁሉንም ነገር ማተረች ፣ ከእንብርክኳ ተነሣችና ጠደፍ ጠደፍ እያለች ወጣች ። ያየችውን ሁሉ ለሐረገወይንና ለዘማኑኤል ነገረች ።

ዘማኑኤልና ሐረገወይን ሳሎን ሲደርሱ ኃይለማርያም ተነሥተው የእጅ ሰላምታ ሰጡአቸው ፣ ሰላምታቸው ሞቅ ያለ ነበር ። ሐረገወይን ከእናቷ ጐን ተቀመጠች ። ዘማኑኤል ወንበር ሳበና አለቃ ጐን ተቀመጠ ። ወንዲራድ ያንን ዐይናቸውን እያጉረጠረጡ ሐረገወይንንና ዘማኑኤልን በየተራ ገላመጡአቸው ። አለቃ የሞቀ ወሬያቸውን አቋረጡና ዝም አሉ ። ሁሉም ተኳረፉና ጸጥታ ሰፈነ ፣ ማ ምን ብሎ ይጀምር ፣ ዝምታ ። አለቃ ብርጭቆአቸውን አንሥተው ጭልጥ አድርገው አስቀመጡት ፣ ጠርሙስም አንስተው ቀዱ ።

“ወይን ያስተፌሥህ ልበ ሰብ ተብሏል እኮ ፣ አይደለም እንዴ ልጅ ኃይለማርያም” አሉ የግልፈጣ ሣቅ እየሣቁ ።

“እሱስ ተብሏል ፣ ግን እኮ እርስዎ የሚጠጡት ጠጅ ነው ፣ ስለ ጠጅስ የተባለ ነገር የለም ?” ኃይለማርያም ራሳቸው ያቀረቡት ጥያቄ አሣቃቸው ። ከወንዲራድ በቀር ሁሉም ሣቁ ። ወንዲራድ

በመሐረባቸው አፍንጫቸውን ጠራረጉና ፤

“አለቃ እንግዲህ የሚባለውን በሉኝ” አሉ የተሰላቸ በሚመስል ድምፅ ።

“ጌታዬ በእርስዎ ይሻላል ብየ እኮ ነው ፤ ይባርኩልን እንጂ ፤ ከትልቅ ሰው ቀድሜ እንዳልናገር ብየ እኮ ነው ። ይጀምሩት ፤ እርስዎ”

“እኔማ ምኑን እጀምረዋለሁ ፤ ቀድሞ ብየ እኮ ጨርሻለሁ” ድምፃቸው እየሰለለ ሔደ ። የተሰላቸና ተስፋ የቆረጠ ድምፅ ይመስላል ። ሐረገወይኑን አገጩን በእጇ መዳፍ አስመርኩዛ አቀርቅራ ታዳምጣለች ። ዘሚካኤል አለቃ ጎን ሆኖ ይቁነጠነጣል ።

“ምን ትጨርሳለህ ፤ ገና ሳንጀምር ! ያለህን ሐሳብ ግለጥልንና እኛም የሚሰማንን እንናገራለን ።” ኃይለማርያም ቆጣ አሉ ። ፍራቻ ነግሦበት የነበረው ክፍል ጭቂት ነቃ አለ ።

“እሺ ይሁና ብላችሁአል” አቋረጡና አፍንጫቸውን አሚሹ ። “ጨርሻለሁ ያልኩትማ ፤ በአባትነቴ ፤ በትልቅነቴ ፤ ልጄን በወግ በማዕረግ ለጠየቀኝ ሰው ሰጥቻለሁ ፤ አክብረው ጠይቀውኝ በክብር መልስ ሰጥቻለሁ ፤ በአባትነት በሀገር ወግና ልማድ መሠረት ። ይህ አይሆንም ፤ ከአባቴ ፈቃድ ወጥቻለሁ የምትል ከሆነ እኔም ልጅነቷን ነጃለሁ ፤ በቃኝ ብያለሁ ፤ ታዲያ ምን ይደረጋል ፤ ልጅ አባቱን የሚያዋርድበት ፤ በአጎረሰ እጁን የሚነክስበት ዘመን ሲመጣ ምን አደርጋለሁ ! በቃ ይኸው ነው ቃሉ ፤ ከቃሉ ከፈቃዴ ከወጣች እኔም ልጅነቷን ነጃለሁ ! አደለም እንዴ አለቃ?”

“የለም የለም እንደሱ አይደለም ፤ ቆይ ጌታዬ ለመከድ አይቻኩሉ ፤ ፈጣሪ አይወደውም ፤ የኢዮብን ትዕግሥት ይስጥዎ! አይቻኩሉ ፤ ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃም ይላሉ እኮ አበው ። ልጅ ሲያጠፉ አባት መምከር መቆጣት ያለ ነገር ነው ። ዛሬም አመጣጣችን ለዚህ ነው ። የለም አባትሽን አስቀይመሻል ፤ አስቆጥተሻል ፤ ፈቃዳቸውን ፈጽሚ ፤ ይቅር በሉኝ በይ ብለን እንገስጻለን ፤

እንመልሳለን...የለም የለም አይቻኩሉ ጌታዬ..." አሉት አነጋገራቸው ጠደፍ ጠደፍ ያለ ነው ። እንደጨረሱ እጃቸውን ወደ ብርጭቆአቸው ላኩ ። ጉሮሮው የደረቀበት ሰው ያህል በረዥሙ ተጐንጩና "እ…ህ" አሉ ። ሐረገወይን ከሩቅ ትገላምጣቸዋለች ። የሚናገሩት ሁሉ አይጥማትም ፤ ዘማኑኤል ይቁነጠነጣል ።

"ቆይ አለቃም እኮ ልክ አይደሉ ፤ እርስዎም እኮ ቸኩሉ ። ገና የምንቆጣውን ፤ የምንመልሰውንና የምንመክረውን ሳናውቅ ዘለው ለምን ፍርድ ይሰጣሉ ? እሱ በአባትነቱ ለሰው ልዳራት ብሎ አሻፈረኝ አለች ነው የሚለው ። የእሷንም እንስማ እንጂ ፤ አለያማ ብያኔያችን የአድልዎ ይሆናል ። አለቃ ዘመኑ እኮ የተለወጠ ነው ። እንደ ዘመኑ እንለወጥ እንጂ ። ጊዜ እኮ ባለህበት እርገጥ ብንለው በጀ አይለንም ፤ እረግጦን ነው የሚያልፈው...እንደ ዘመኑ እንሁን ። የሐረገወይን አባት ወንዴራድ ነው በቃ ። ካድኩ ቢል ላፉ አባትነቱ እንደሁ አይፋቅ ። እሷስ ተነሥታ አባቴ አይደለም ብላ ብትክድ ለአፏ ትበለው እንጂ የእሱ አባትነት አይፋቅ..."

"የለም የለም ኃይለማርያም አታዘባርቀው ወጋችንን" ወንዴራድ ተቆጡ ፤ "ነገርኩህ እኮ ፤ ይኽ እኮ ምርምር ውስጥ የሚያስገባ አይደለም። ግልጽ እኮ ነው ጉዳዩ ፤ አባት ያለው አይከበር ፤ አባት ልጁን አይዘዝ፡ ወላጅ ልጁን አይዘዝ ፤ ወላጅ ልጁን አይቆጣ ፤ ልጅ አባቱ ያለውን አይስማ ነው የምትለው?"

"የለም የለም እንደ እሱ አላልኩም ፤ አባት ልጁ የሚለውንም ይስማ ነው ያልኩህ ፤" ኃይለማርያምም ተቆጡ ።

ወይዘሮ ተዋበች ሁኔታው አልጣማቸውም ፤ የነጠላቸውን ጫፍ አፍንጫቸው ላይ ጣል አድርገው ሁሉንም ይታዘባሉ ። ወንዴራድና ኃይለማርያም ምን ጊዜም ተግባብተው ተጫውተው አያውቁም ። በትንሽ በትልቁ ይነታረካሉ ፤ ይኳረፋሉ ።

"እንዲህ ብናደርግ አይሻልም" አለ ዘማኑኤል እጆቹን እያፋተገ ። አለቃ ቁና ብለው ተመለከቱት ፤ ወንዴራድ መልካቸው ለውጥ አለ ። ግንባራቸውን ቋጥረው አፈጠጡበት ። ሐረገወይን

ካቀረቀረችበት ቀና ብላ የዛማኑኤልን አፍ ትጠብቅ ጀመር ፡ ትኩር ብላ ትመለከተዋለች ።

“በላ ምን ይሻላል ነው የምትለው?” አሉ ኃይለማርያም።

“መቸስ ፡ የቤተሰብ ጉዳይ ስለሆነ ግልጽ አድርገን መነጋገራችን ይጠቅማል ። ጋሽ ወንዲራድ በአባትነታቸው መቸስ ትክክል ናቸው ፡ እኔ የምልሽን አግቢ ማለታቸው በአባትነት ወጋቸው ፤ በሚያውቁት ልማድ ትክክል ናቸው…”

ሐረገወይን ገርሞአት ትቁነጠነጣለች ። የወትሮው የምታውቀው ዛማኑኤል አልመሰላትም ። ጠረጠረችው ፡ ‘አሀ ለካ እሱም ከድቶኛል’ ብላ አሰበች ። በማለዳው መኝታ ክፍሏ ድረስ መጥቶ ‘ድል ድል’ ይሸተኛል ያላት ትውስ አላትና ብሽቅ አለች ፡ ተነሥታ ለመውጣት ፈለገች ። እልህ ክፉኛ ተናንቃት ። ‘ደሞ የአንቺ ምርጫ የእኔ ምርጫ ነው ብሎ ያታለለኝ’ ብላ ጠላችው ።

“በሌላ በኩል ደግሞ” ቀጠለ ዛማኑኤል ፡ “ሐረገወይን ትንሽ ልጅ ስላልሆነች ፡ ትንሽም ብቻ ሳይሆን የዘመኑ ትውልድ ፡ የአዲስ ባህልና ወግ አባል ስለሆነች ፡ ባልን የሚያህል ፡ የሕይወትን ውጣ ውረድ አብሮ የሚጋራን ፡ የሕይወት ጓደኛ የመምረጥ መብት አላት፡ ዘመኑ የፈቀደላት ፡ ሕይወት የፈቀደችላት ። ለእሷ የትዳር ጓደኛ የሚሆነውን ሌላ ሰው ሲመርጥላት ላይጥማት ይችላል ። ትዳሯ ትዳር ላይሆን ይችላል ። ሕይወት ፊቷን ልታዞርባት ትችላለች ። ስለዚህም ‘የለም የራሴን እማውቅ እኔ ብቻ ነኝ’ ብትል ትክክል ናት። ልብ አድርጉ እንግዲህ ሁለቱም በየበኩላቸው ትክክል ናቸው። ነገሩ አስቸጋሪ መስሎ የሚታየንም ለዚህ ነው ። ሁለቱም ትክክል ስለሚመስሉን ። ግን የምናስታርቅበት ዘዴ አለ ። የሁለቱ ትክክለኛነት የሁለት ዘመን ፡ የሁለት ሕይወት እውነት ነው ። አንዱ እውነት ዘመኑ እያለፈበት የመጣ ፡ ሌላው ሕይወት እያበበ ፡ እያፈራ ያለ እውነት ነው ።”

“በሕግ ብየሃለሁ ፡ በሕግ ብየሃለሁ” ተቆጥተው ተነሡ።

ወንዲራድ ፡ አራስ ነብር ሆኑ ። የግንባራቸው ላይ ደምስሮች ፍጥጥ ብለው ግትርትር አሉ ። የንዴታቸው ብዛት ያንቀጠቅጣቸዋል ። ሁሉም ደንግጠው ይመለከቱአቸው ጀመር ።

‘‘ቢወራ ገብረየስ ቢንተከተከ ሽሮ አሉ ። በሕግ ብየሀለሁ ፡ ይኸን ስበካህን የምትሔድበት ሔድና ስበክ ብየሀለሁ ፡ ቤቴን አትበጥብጥ ብየሀለሁ ፡ ሔድና እኩዮችህ ፡ ወዳጆችህ ፡ ቢጤዎችህ ጋር ተፈላሰፍ ፡ ወራዳ! ቤቴን አትበጥብጥ’’ ከግንባራቸው ጀመሩና የጓሊት አናታቸውን በመሐረባቸው ጠረጉ ።

ኃይለማርያም ሪዛቸውን ያፍተለትላሉ ። አፍተልትለው አፍተልትለው ጫፉን አሾለው ይተዉታል ።ሐሳብና ንዴት ሲገባቸው ቁጭታቸውን የሚወጡት በሪዛቸው ነው ። አለቅጥ ያፍተለትሉታል።

‘‘እንዴ ምን አርጐ ነው ቤትህን የበጠበጠው ፡ ምንአረገ ፡ ደግ በተናገረ ደርሰህ ቤቴን በጠበጠ ትላለህ እንዴ?’’ መልሰው ሪዛቸውን ያፍተለትሉ ገባ ። ወንዲራድ የቁንጥ አዟዟር ሆነው ወንድማቸው ላይ አፈጠጡ ፡ በዐይናቸው ከሚያፈጡባቸው ተንፖሥተው በጥፊ ቢመቱዋቸው በወደዱ ነበር ፡ ግን ዋጥ አደረጉት ንዴታቸውን።

‘‘ዝም በል እማታቀው ነገር ውስጥ ጥልቅ አትበል ። በገዛ እጄ የፈጠርኩትን ችግር እኔ ነኝ የማውቀው’’ ከንዴታቸው መለስ አሉና አነጋገራቸው ለሰለሰ ።‘‘ቤቴን ትዳሬን የማውቀው እኔ ነኝ፡ነገርኩህ እኮ! እሱ ከመጣ ወዲህ ነው ቤቴ የተበላሸው ። ክብር ያጣው ፡ የተዋረደው፡ እሱ ከመጣ ወዲህ ነው ። ቤቴ በውድቅት ሌሊት መቆርቆር የጀመረው እሱ ከመጣ ወዲህ ነው ። እሱ ነው ። እሱ ነው ያበላሻት ልጄን ፡ ከአባቷ ፈቃድ እንድትወጣ ያበላሻት ፡ ሰይጣናዊ ምክር የሚመክራት እሱ ነው ።’’

‘‘እንዴ ምን ብሎ ነው የሚመክረኝ? እኔ ልጅ ነኝ? ወደእሱ አትሒድ እኔን ልትቆጣ ትችላለህ ፡ እሱ ምን አደረገ ፡ እሱ ምን ፈጠረ?’’ ሐረገወይን ተውረገረገች ።

ወይዘሮ ተዋበች ነቃ አሉ ። የነጠላቸውን ጫፍ ከአፍንጫቸው ላይ አውርደው ትከሻቸው ላይ ጣል አደረጉት ። አለቃ በጭራቸው አየሩን አተራመሱና ጉሮሮአቸውን ጠራረጉ ።

“አበው መጀመሪያ ልጆቻችሁን ዳዊት ፡ መጽሐፈ ሲራክ ፡ መጽሐፈ ሰለሞን ፡ አስተምሯቸው ። ‘መቅድመ መሀርዎሙ ለወልድክሙ መጽሐፈ ሲራክ ወመጽሐፈ ሰለሞን ፡ ወመዝሙረ ዳዊት ፡ መሀርዎሙ ኪናተ ዘይደልዎሙ’ ነው ያሉት ። ታዲያ ይህንን ምናምኑን እያነበቡ ቢባልጉ ምን ይጠቅማል ፡ መጥፎ ምክርስ የት ያደርሳል ፡ ቻል ያደርጉት ጌታዬ ፡ በገረገራው ይገዙዎታለሁ ፡ ባለጌ ያሳደገውና ከባለጌ ጋር የዋለ ልጅ ምን ሊማር ብለው...” አለቃ ራሳቸው በተናገሩት ቃል ድንግጥ አሉ ። በልበሙሉነት ሲናገሩ ቆዩና ‘ባለጌ ያሳደገው’ የሚለው ቃል ከአፋቸው ሲያመልጥ ብርግግ አሉና ደነገጡ ፡ በራሳቸው ጥፋት ተሸበሩ ። በውስጣቸው አማተቡና ጭጭ አሉ ። ባለጌ ያሳደገው ሲሉ ወንዲራድን የሰደቡ መስሎአቸው ቢደነግጡም ፡ ወንዲራድ ነገሩን በዚያ መልክ አልወሰዱትም ። አልተናደዱም ። ዛማኑኤል ግን ተናደደ ። የአለቃ ፍልስፍና ውስጡን አሳረረው ፡ ወደ አለቃ ጆሮ ጠጋ አለ ።

“አንተ ቀላዋጭ ቄስ ሳትለፈልፍ ዝም ብለህ ጠጅህን አትጠጣም ።” ሹክ አላቸው ።

አለቃ የሚያደርጉት ጨነቃቸው ፡ ተቁነጠነጡ ፡ ሁሉንም ገልመጥ ገልመጥ አደረጉ ። ዛማኑኤል ምንም እንዳላደረገ ሰው እግሮቹን አነባብሮ ተቀምጦ ጣራ ጣራውን ይመለከታል ። ኃይለማርያም ራሳቸውን እያፍተለተሉ የሚናገሩትን ያስባሉ ። አለቃ የዛማኑኤል ስድቡ ቆጠቆጣቸው ። ከመቀመጫቸው ተነሡ ጭራቸውን ይዘው ።

“በአባትነቴ አንድ ነገር ልናገር ፡ ፍቀዱልኝ ። መቼስ ጌታዬ ቻይ በመሆናቸው ነው እይ ይህንን ልጅ እስከዛሬ ከቤት አስወጥተውት ነበር ። እኔ ነኝ ተው ቻሉ እያልኩ ያበረድኩዎ! የኢዮብን

ትዕግሥት ይስጥዎ እያልኩ ያከላከልኩዎ! እንዴትስ አባት አይከበር ፡ እንዴትሳ የአባት ምርጫ ለልጅ አይጥም ፡ የቀድሞ ንግግሩ በውነቱ እትልቅ ሰው ፊት የሚነገር አልነበረም ፡ ድፍረት ነው ፡ የድፍረት ድፍረት ። ልጅን ተአባት ተናት ፈቃድ አውጥቶ ለሌላ መስጠት የመሸጥ ያህል ነው ፡ ክህደት ነው ። ነገሩንማ ደርሰንበታል እኮ ፡ እሱ ነው የመከራት ፡ እሱ ነው ያሳሳታት ፡ ታባቷ ፈቃድ አውጥቶ ለሌላ የሸጣት እሱ ነው ። የደባ ገበያ ሥጋው አሥር ቆዳው ሐያ ይባላል ።'' አቆሙና ትከሻቸው ላይ ያለውን ነጠላቸውን አስተካከሉ ። ሲናገሩ እጃቸው ክፉኛ ይወናጨፋል ። ሌሎቹ አፍጥጠው ይመለከቱአቸዋል ። ከወንዲራድ በቀር ሌሎቹ የንቀትና የጥላቻ አስተያየት ነው የሚያዩአቸው ። ''ትልቁ መጽሐፍ ከወንድሞቹ ወገን ሰው ሰርቆ የሸጠ ሰው ቢኖር 'ወቅንያ አው ሲጣ ቅተሉ ለሠራቂ' ይላል ። ቢገዛው ወይ ቢሸጠው ግደለው ነው የሚለው ። ይኸ እኮ የራስን እኅት አሳልፎ የመሸጥ ያህል ነው…'' ልባቸው በእርካታ ተሞልቶ ቁጭ አሉ ።

''የለም መምሩ ተሳስተዋል ፡ እንደ አባት ሳይሆን እንደ ልጅ ነው የሆኑብኝ ፡ በቁም ነገር እንጫወት እንጂ ። 'ያምራል ብለው ከተናገሩት ይከፋል ብለው የተውት' ይመረጣል ። ለምን ጋል ጋል እንላለን ። 'መናደድን የማያውቅ ሰው ሞኝ ነው ፡ በቀላሉ የማይናደድ ግን ብልህ ነው' ይባላል ። ብልህ እንሁን እንጂ ፡ ቱግ ቱግ የምንል ከሆነማ ምኑን ተግባባነው ፡ ምኑን እልባት ላይ ደረስነው ። እስኪ አሁንም ልጅቷ ምን እንደምትል እንስማ ፡ እናዳምጣት ፡ የእሷ ጉዳይ ሆኖ እሷን መርሳታችን እኮ ልክ አይመስለኝም…'' ኃይለማርያም ተናግረው ሲጨርሱ ወደ ሐረገወይን ዞር አሉ ። ሁሉም እሷን እሷን ይመለከት ጀመር ።

''እኔ እኮ ጨርሻለሁ አጐቴ ፡ አንደኛ ነገር ፍላጐቴ መማር ነው፡ ለማግባትም ብፈልግ የእራሴ ምርጫ አለኝ ። እንደውም እውነቱን ልንገራችሁ እጮኛ አለኝ ፡ ከእሱ ውጭ ማንንም ይምጣ ማን አላገባም ፡ ዕቅዴ ይኸ ነው…'' ወደ ኋላዋ ጋደም ብላ

ቁቀመጡኝ ።

“ታዲያ ምን እድርጉ ነው የምትሏት?” አሉ ኀይለማርያም ሁለት እጆቻቸውን ዘርግተው ። ዛማኑኤል ኀይለማርያምን በመደገፍ አንገቱን ወዘወዘ ። ቀና አለ ።

“ጋሼ ኀይለማርያም ጥሩ ብለዋል ፡ መቸስ አለመግባባቱ አለ ። እኛ የምንፈልገው ጋሼ ወንዲራድ የእፁን ምርጫ ፡ የእፁን ፈቃድ እንዲቀበሏት ነው ። ትክክል ነሽ ብለው በአባትነት መርቀው እንደ ፈቃድሽ እንዲሏት ነው ። እኔ ይህን ስናገር እፁን እንደ እናት ፡ እሳቸውንም እንደ አባት በመመልከት ነው ። ቤቱም ቤቴ ነው ። በእውነቱ እኔ የራሴን ቤት አላፈርስም ። በድፍረት የምናገረው ቤቱ ቤቴ ፡ ጉዳዩ ጉዳዬ ነው ብዬ ነው … እንዴ ዘመኑን መሆን መቻል አለብን እኮ ጋሼ ወንዲራድ ፡ ያለንበት ዘመን እኮ ራሳቸውን ከእውነተኛ ፍቅር በቀር ለሌላ ነገር ሲሉ ለወንድ አሳልፈው መስጠትን የማያውቁ ሴቶች ወይንም በገንዘብ ወይ በሥልጣን መማረያ ሴትን መግዛትን የማያውቁ ወንዶች ትውልድ የሞላበት ዘመን ነው ። ይህንን መቀበል አለብን ። ችግሩ እኮ የወንዲራድና የሐረገወይን ሳይሆን የሁለት ዘመን ጠብ ነው ፡ የሁለት ሕይወት ግብግብ ነው ፡ አዲሱ ያሸንፋል ፡ አሮጌው ይወድቃል ፡ ይህንን እንቀበል ።”

“በቃ በቃ ፡ ውጣልኝ ከቤቴ ፡ ውጣ ብየሀለሁ” ወንዲራድ ዐይናቸውን እያጉረጠረጡ ተነሡ ። “ውጣልኝ ማነህ ማነህ ገብየሁ ና አስወጣልኝ ! ባጐረሰኩ አልነከስም ውጣልኝ ውጣ…”

“የለም ዘበኛም አያስፈልግም እኔው እወጣለሁ”

“እዎ ውጣልኝ… በገዛ ቤቴ አትበጥብጠኝ”

ክፍሉን መልሶ ፍራቻና ዝምታ ዋጠው ። ዛማኑኤል ዝግ እያለ እየተራመደ የሳሎኑን በር ከፍቶ ወጣ ፡ ሁሉም የድንጋጤ ዝምታ ወረረው። ወይዘሮ ተዋበች ዐይናቸው ዕንባ ቋጠረ ። ሐረገወይን ከንፈሯን ነክሳ ቆየችና ዞር ብላ እናቷን ስትመለከት ፡ የዕንባ

ዘለላዎች በጉንጮቻቸው አቋርጠው ይወርዳሉ ። የእሷም ዐይኖች ዕንባ አረገዙ ።

“ምነው እሌታ ዝም ትላላችሁ እንዴ” ተነሡ ተዋበች እንባቸውን እየጠረጉ ። “የሙት ልጅ እንዲህ ይባላል ፡ አባቴ ባይሆን ከቤት አስወጡኝ ብሎ ያዝንብን የለም እንዴ! ሆድ የሚብሰው የሙት ልጅ ከቤቱ ውጣልኝ ይባላል ።” እያለቀሱ ወደ ሳሎኑ በር አመሩ ፡ ሐረገወይን ተከተለቻቸው ።

ዛማኑኤል ዋናውን የግቢውን በር ወጥቶ ሔዶአል ። አቶ ገበየሁ በሁለት እጆቻቸው ወገባቸውን ይዘው ቆመው ቁልቁል ሲወርድ ይመለከቱታል ። ፊታቸው ላይ የአሸናፊነት ምልክት ይነበብባቸዋል ። ተዋበችና ሐረገወይን የግቢውን በር ወጥተው ቁልቁል ሲመለከቱ ፡ ዛማኑኤል ኮረኮንቹን መንገድ ጨርሶ አስፋልቱ መንገድ ሊገባ ትንሽ ቀርቶታል ።

“ዛማኑኤል ዛማኑኤል” ተጣራች ሐረገወይን ። ዞር ብሎ ተመለከታት ፡ “ቆየኝ ቆየኝ” ቆሞ ጠበቃት ። የወይዘሮ ተዋበች ዕንባ አላቋረጠም ።

ሐረገወይን መኝታ ክፍሏ ገብታ ጥቂት ልብሶች በአንስተኛ ሻንጣ ቋጥራ ወጣች ። ዛማኑኤል እዚያው በታ ላይ ቆሞ ጠበቃት ፡ ተያይዘው ሔዱ ።

ምዕራፍ፡ ሰባት

ዓለማየሁ ቢሮው እንደደረሰ ኮቱን አወልቆና ወንበሩ መደገፊያ ላይ አስተካክሎ ሰቀለው ። በነጭ ሸሚዙ ላይ ያደረገውን ከረባት እስር አላላና ቁጭ አለ ። ታሞ ስንብቶ ቢሮ ከገባ ገና ሁለተኛ ቀኑ ነው ። ከኮቱ ኪስ ሲጃራ አወጣና አቀጣጠለ ፣ ቶሎ ቶሎ ሳበለት። ከአፉ የሚወጣውን የሲጃራ ጢስ በዐይኑ እየተከተለ ይዞራል ። ሐሳብ አዕምሮው ውስጥ ተሸንቅሮ አልወጣ ብሎ ያንገላታዋል ። ሐረገወይንና ዛማኑኤል የእሱ እንግዶች ሆነዋል ። ቤታቸው እንዲመለሱ ጎትጉቶ ነበር ፣ ግን አልሆንለትም ። በዚያች በእሱ ቤት ውስጥ እሱ ፣ ወንድሙ ፣ ሠራተኛው ፣ ሐረገወይንና ዛማኑኤል መኖር ጀምረዋል ። ዓለማየሁ መኝታ ክፍል ውስጥ እሱና ወንድሙ ምክትል መቶ አለቃ በንታየሁ ፣ በሁለተኛው መኝታ ክፍል ሐረገወይን ይተኛሉ ። ዛማኑኤል ዓለማየሁ ሲታሰር የተገዛችውን አነስተኛ ፍራሽ እያነጠፈ ሳሎን ይተኛል ፣ ለሁሉም አዲስ ሕይወት።

ቤቷ ሁሉንም ለማስተናገድ ትበቃለች ። የሚበሉትም ሆነ የሚጠጡት አይቸግራቸውም ፣ ግን ዓለማየሁ ያስባል ፣ ይሰጋል ። ምን እንደሚያሳስበውና እንደሚያሰጋው ቢጠየቅ ደግሞ ይኸ ነው ብሎ በውል የሚናገረው ነገር የለውም ፣ ግን ይሰጋል ። መልሶ እዚያች እስር ቤት መግባትን አይፈልግም ፣ ስሙ በክፉ መነሣቱን አይሻም ፣ ጠላቶቹ ጥቃት ሲያደርሱበት ለማየት አይፈልግም ፣ በእሱ የተነሣ ትንሽ ወንድሙ በንታየሁ ከሰው ጋር እንዲጋጭ ፣ ችግር እንዲደርስበት አይመኝም ፣ ይፈራል ። ሐረገወይን እሱ ቤት መኖሯ ቢሰማ ሰማይና መሬት የሚገለባበጡ መስሎ ይታየዋል ፣ ይሰጋል ። የሚሰጋበትን ጉዳይ አስቦ አስቦ ይኸ ነው ብሎ ለመለየት ይፈልግና ግራ ግብት ሲለው "ለሐረገወይን ሲባል የፈለገው

ይምጣ!'' ብሎ ራሱን ለማጽናናት ይፈልጋል ፡ ግን አይጽናናም ፡ ልቡ ደረቱ ውስጥ ሲደልቅ ይሰማዋል ፡ እያወቀ ያለማወቅ በሽታ ።

ከሲጃራው ጋር ሲጫወት ቆየና ተነሣ ። ቀስ ብሎ እየተራመደ ወደ መስኮቱ ሔደ ፡ አሻግሮ ተመለከተ ። ብዙ ብዙ የሚታይ አለ ፡ አሻግሮ የጠራውን ሰማይ በዐይኑ ዳሰሰው ፡ የጠራው ሰማይ እንጋጠው ሲመለከቱት ቢውሉ አይሰለችም ። ሰማያዊም ሰማይ ጥርት ብሎ ተዘርግቷል ፡ ለዐይን የሚጎረብጥ እንዳችም ነገር የለበትም ። ተፈጥሮን አደነቀ ፡ ውስብስብ የተፈጥሮ ምርምር ውስጥ ገብቶ ራሱን ለጥቂት አስጨነቀ ። ተፈጥሮ አያሌ አስደናቂ ቁጥር ሥፍር የሌላቸው ውብ ነገሮችን ለሰው ልጅ መደሰቻ ባታቀርብ ኖሮ፡ የሰው ልጅ የተፈጥሮን ረቂቅነትና ውስብስብ ባሕሪ ለማወቅ ሌት ተቀን ባይማስን ኖሮ··· አይ··· አይ እርስበርሱ ተፋጅቶ ያልቅ ነበር ፡ ገረመው ። ስለዚህ ተፈጥሮ ለሰው ልጅ ምንድን ነው? እሺ ሰው ተመራምሮ ተመራምሮ የተፈጥሮን ምንነት ቢደርስበትስ? አይ ተፈጥሮ ረቂቅነትሽ ፡ የማይደረስበት ምስጢርሽ ተደረሰበት ብሎ ሊንቃት ገሸሽ ሊያደርጋት ፡ ፈጽሞ ሊሆንም ሊታሰብም የሚችል አይደለም ። ምርምሩ ራሱ ረቀቀበት ፡ ብዙም ሊገፋበት አልፈለገም።

የጠራው ሰማይ ላይ የተተከለ ዐይኑን መለስ አደረገና ቁልቁል ተመለከተ ። ቀፈፈው ። ''አይ የሰው ልጅ ሥራ'' አለ በልቡ ። የዱሮው ቄራ፡ የእሪ በከንቱ ደሳሳ ጐጆዎች ያረጁ ቆርቆሮዎች አሳዘኑት ። ሰውማ ምናለበት ሲያረጅም ያምርበታል ፡ የሰው ልጅ የሠራው ቆርቆሮ ዕድሜ ሲጫጫነው አቤት ሲያስጠላ ። ገረመው ። የብዙዎቹ ቤቶች የቆርቆሮ ክዳን ምስማር ስለወላለቀ በምስማሩ ምትክ ትላልቅ ድንጋይ ተጭኖአቸዋል ። ቤቶቹን ደግፎ የያዘው ያረጀ የባሕርዛፍ ግድግዳ ፡ ቅንቅን የበላው ምሰሶ ራሱን ችሎ መቆም አቅቶት በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኖበት ድንጋይ ተሸክሞ በመባሉ ምርር ብሎ የሚያለቅስ ይመስላል ።

ደግነቱ አዲስ አበባ ክፉም ደጉም የሚታይባት ናት ። ዐይን

አንድ ነገር ላይ አርፎ ቢከፋው ፤ መለስ ብሎ ሌላ የሚያስደስት ነገር ያያል ፤ መኖርም እኮ ደስ የሚለው ለዚህ ነው ። እዩ እንዲህ ካልሆነማ ሌትም ቀንም ክፉ ፤ ሌትም ቀንም ደግ ብቻ ከሆነማ ያስጠላል ። ዓለማየሁ አንዱን ሐሳብ ጥሎ ሌላውን እያነሣ መቋጠሪያ የሌለው ምርምር ውስጥ ገብቶ ሲወዛወዝ ፤ የቢሮ ባልደረባው ታፈሰ በሩን በርግዶ ገባ ፤ ዓለማየሁ ድንግጥ አለ ። ያነሣ የጣለውን ምስቅልቅል ሐሳብ የነበረበትን ጭንቀት በተአምር ያወቀበት መሰለውና ተርበተበተ ።

“ምነው ጋሼ ታፈሰ… ዘገየህሳ” አለ በተደናገጠ ድምፅ፡

“ምን አባክህ ጐረቤቴ አንድ ሴት ምጥ ይዟት እሷን ላደርስ ሆስፒታል ሔድኩ ። መቼስ ይች የሽማኔ ጉድጓድ መኪናዬ እኮ በሰፈሩ ትልቅ ሰው አድርጋኛለች ። ብቻ የምበሽቀው ለሠርግ አጃቢነት አይመርጧትም” አለ ታፈሰ እየሣቀ ።

ታፈሰ በዚህ መሥሪያ ቤት ውስጥ መሥራት ከጀመረ አራት ዓመቱ ነው ። በዕድሜም በሥራ ልምድም የበሰለ ሰው ነው ። ዕድሜው ሃምሳ ይጠጋል ። በብዙ መሥሪያ ቤቶች ሠርቷል ። ጥቃት አይወድም ፤ በእሱ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ላይ ጥቃት ሲደርስ ይከፋዋል ። ቀጭን ረጅም ነው ። ጢሙን ማሳደግ ይወዳል ፤ ንዴቱ አፍንጫው ዳር ናት ፤ ቶሎ ቱግ ይላል ። ይሳደባል ፤ ልግጥ ይላል ፤ ወዲያው ደሞ ይበርዳል ፤ ቱግ ብሎ ዝም እንደሚል የቡና ጀበና ። ብዙ ጊዜ ከአለቆቹ ጋር ይጋጫል ፤ ማስጠንቀቂያ ይጻፍበታል ፤ ደመወዙን ይቀጣል ፤ ከሥራ ይባረራል ። ለሐያ ስድስት ዓመታት በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ሠርቷል ፤ ግን በደመወዝም በዕድገትም ዝቅተኛ ነው ። ግን አይከፋውም ። “ደመወዝ ለማስጨመር ፤ ዕድገት ለማግኘት ላለፈ ላገደመ አለቃ ሁሉ ማጐብደዱን የእግር ምንጣፍ ሁን ቢሉኝ እኔ ታፈሰ በጄ አልል ። እንዲሁ እንዳማረብኝ እሞታለሁ እንጂ ፤ እኔ ታፈሰ አልንበረከክም” ይላል ፤ ታዲያ አልጠቀመውም ። ከሥራ ይባረራል ፤ ወር ሁለት ወር ሥራ ፈቶ ልጆቹን ያስርባል ። ሥራ ሲያገኝም ያው ነው ይጋጫል ፤ ይናደዳል ፤

ይበርዳል ። "ተናዳጅ እንጂ አናዳጅ አይሞትም" የሚሉ ጥሩ ፈሊጥ አለው ። ይናደድና ቶሎ ይረሳዋል ።

ታፈሰ ገብቶ እንደተቀመጠ ፡ የመሥሪያ ቤቱ ተላላኪ በፖስታ የታሸገ ወረቀት ይዞ መጥቶ ለዓለማየሁ ሰጠውና ተመለሰ ። ዓለማየሁ ፖስታውን ከፍቶ አነበበው ፡ ሲያነብ ፊቱ ልውጥውጥ አለ። አንብቦ እንደጨረሰ "ጋዶም ኢት! ምን ማለቱ ነው?" አለና ጮኸ ።

"ምነው ዓሌ ፡ ምን ተፈጠረ"

"ይገርምሃል ጋሼ ታፈሰ! የሚሠራው ሥራ"

"እኮ ምን ተሠራ?"

ዓለማየሁ ወረቀቱን ለታፈሰ ሰጠው ፡ ታፈሰ ማንበብ ጀመረ ።

"ለአቶ ዓለማየሁ ድንበሩ ፡ መሥሪያ ቤቱን ሳያስፈቅዱ ለአሥር ቀናት በሥራ ገበታዎ ላይ ባለመገኘትዎ ፡ የአሥር ቀን ደመወዝዎን የተቀጡ ሲሆን ፡ ዳግም የዚህ ዓይነት ጥፋት ቢፈጽሙ በቀጥታ ከሥራ የሚባረሩ መሆኑን እናስታውቃለን ።

የኤክስፖርቶች ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ "

ታፈሰ አንብቦ እንደ ጨረሰ ለጥቂት ጊዜ አቀረቀረና ቀና አለ ።

"ትናንት የሐኪም ፈቃድ አለኝ አላልከኝም እንዴ?"

"እሱ እኮ ነው የገረመኝ ፡ የሐኪም ፈቃዱን እኮ ለእሱው ሰጥቼዋለሁ"

"ታዲያ እንዴት ይጽፍብሃል?"

"ግራ የገባ ነገር ነው ጋሼ ታፈሰ"

"የለም የለም ሒድና አስረዳው ፡ እንቢ ካለ ለሥራ አስኪያጁ ንገራቸው ። ይኸው ነው የእኛ አገር ቢሮክራሲ ፡ እኛን ሲጠብስ የኖረው አነሰውና ደሞ ወጣቶቹን ሊጀምራችሁ አይደለም" ታፈሰ ንዴቱ መጣበት "ሒድና አስረዳው ፡ አፍንጫው ላይ ጣልለትና ሒድ ..."

“እንዴት ይሳሳታል ፧” ዓለማየሁ ጉረመመ ።

“ጠብ አላችሁ ከዚህ ቀደም”

“ኧረ የለንም ጋሽ ታፈሰ”

“ብቻ ሒድና አስረዳው ፣ ሰውዬው ግን የሚገባው ሰው አይደለም ። ግን ታውቀዋለህ ማንነቱን”

“የት አውቀዋለሁ ጋሽ ታፈሰ ፣ እዚሁ ነው ያወቅሁት ፣ አንድ ዓመት ሆነው አይደለም እንዴ እኛ ጋ ከመጣ”

“አዎ የእኛ አለቃ ከሆነ አንድ ዓመቱ ነው ። ከዚያ በፊት ግን ብዙ መሥሪያ ቤት ሠርቷል ። እንደ እኔ እየተባረረ እንዳይመስልህ ። ከዝና አራቱቶ ሲያልቅበት ሌላ ከዝና ፍለጋ ነው የሚዞረው ። ቀላል ሰው እንዳይመስልህ ፣ የዚህችን ሀገር ገንዘብ እንክት አድርጎ የበላ አጋሰስ ነው። የበላትን ሁሉ የግድ እስቲተፋ ድረስ ጌታ ነው ፣ ባለ ጊዜ ነው ። ድንጋይ የሚሰብር ቅል ነው ። የደጃዝማች እርገጣቸው የእኅት ልጅ መሆኑን ታውቃለህ?”

“ኖ—ኖ— አላውቅም ጋሽ ታፈሰ”

“እንግዲያውስ እወቅ ፣ እዚህ ያመጣው ምክትል ሥራ አስኪያጁ ነው ። የእሱ ቢጤ ቅል ሲፈልግ እሱን አገኘና አስመጣው ይገርምሀል… ቅል ነው ሰባራ ቅል ። ግን እኔ አንድ ድንቅ የሚለኝ ነገር አለ ፣ ዓለማየሁ ቅል ለምን ከእሱ የባሰ ቅል እንደሚፈልግ” የመገረም አስተያየት እያየ ራሱን በእጁ አስመረከዘና ትክዝ ብሎ ቆየ ።

“እይ ጋሼ ታፈሰ ‘ሰው ከዘመዱ አህያ ከአመዱ’ አይደል የሚባለው” ዓለማየሁ ነገሩን አናንቆ ተወት አደረገበት ፣ እሱን ያሳሰበው ሌላ ። እሱን ያስገረመው የሐኪም መረጃ አቅርቦ መቀጣቱና በማስጠንቀቂያ መስፈራራቱ እንጂ የአለቃው ቅልነት አልነበረም ። ታፈሰ ግን አሁንም እንደደነቀው ነው ፣ ቀጠለ ወጉን ።

“ዓሌ መቸም አንተ ገና ልጅ ነህ ። ምንጊዜም የማልረሳው አንድ ነገር አለ ልንገርህ ።” አቆመና ዓለማየሁን የማሳዘን ዓይነት

ሲስተያየት አየው ። 'እባክህ ፍቀድልኝ ልንገርህ' የሚል ይመስላል። ዓለማየሁ ታፈስን ማስቀየም አልፈለገም ፤ በውስጡ የራሱን ሐሳብ እያብሰለሰለ ላይ ላዩን ሊያዳምጠው ፈለገ ።

"እሺ ንገረኝ ጋሼ ታፈሰ" አለ ጥርሶቹን ብልጭ አድርጎ ።

"ይኸውልህ እዚህ ወወክማ ቅዳሜ ቅዳሜ ክርክር ይደረግ ነበር ። ታዋቂ ታዋቂ ሰዎች እየተሰበሰቡ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ይተቹ ይወያዩ ይከራከሩ ነበር ፤ ታዲያ እኔ አልቀርም ። ክርክራቸው ሁሉ ስለሚጥመኝ የወወክማ ደንበኛ ነኝ ። ሦስት ወይም አራት ዓመት ይሆነዋል ፤ እንዳጠውም ሳይበልጠው ብለህ ነው" አንጋጠጠና ዓይኖቹን ጨፍኖ ጥቂት ፈሰበና መለስ አለ ።

"ብቻ ተወው ዘመኑን ረሳሁት ። ክርክሩ ስለ ከተማዋ ጽዳት ነበር ፤ ስለ አዲስ አበባችን ፤ ሁሉም እየተነሣ የተሰማውን ይናገራል። አንዱ አንዱን ይቃወማል ፤ ሌላው ይደግፋል ፤ ምናለፋህ ክርክሩ ጦፈ ። ብዙ ጋዜጠኞች ነበሩ ፤ ታዋቂ ታዋቂዎቹም ነበሩ ። እየተነሡ ማዘጋጃ ቤቱን ወረዱበት ፤ ለጽዳቱ ተጠያቂ እሱ ነው ። ምንም አልሠራም ፤ አላሰበበት ፤ ምንትስ ምንትስ እያሉ ሲኮንኑት የማዘጋጃ ቤቱ የሕዝብ ግንኙነት ሹም ፊቱን ፍም አስመስሎ ብድግ ይልልሀል ። አይወርድባቸውም በእነዚያ ጋዜጠኞች ላይ ። እንደ ውም ምን ይልልሀል 'ለከተማችን ጽዳት አለመጠበቅ አንዱ ተጠያቂዎች ጋዜጠኞች ናቸው ። ሲጠጡ ውለው ሲጠጡ አምሽተው እዚያው እማዘጋጃ ቤቱ ፊት ለፊት ሲሸኑ ብዙ ጊዜ በዱዳ ዘበኞቻችን ይያዛሉ ። ለዚህም በቂ ማስረጃ አለኝ' አለና ቁጭ አለ ። ቁጭ ሲል ያ ፍም መስሎ የነበረ ፊቱ መለስ አለለት ። አዳራሹ ውስጥ የተሰበሰበው ሁሉ አንድ ጊዜ አወካ ፤ ሣቅ በሣቅ ሆነ ። ታዲያልህ አንዱ ታዋቂ ጋዜጠኛ ብድግ አለና እጁን ሲያጨበጭብ ያ ያወካ የነበረ ሰው ሁሉ ጭጭ አለና አፍ አፉን ይመለከተው ጀመር ። አይ አነጋገር! አይ ቁመና! አይ አማርኛ! ሌላ ነው ሲናገር ። ስለ ከተሞች አጠቃላይ ገለፃ አደረገልህና ፤ 'እንደ አዲስ አበባ ባሉት ትልልቅ ከተሞች አንድ የሕዝብ ግንኙነት ሹም ቢያንስ ሦስትና አራት

ዓለምአቀፍ ቋንቋዎችን ማወቅ አለበት ፤ የኛዎቹ ግን የሚያውቁት አንድ ቋንቋ ብቻ በመሆኑ ከሥራቸው ዱዳ መቅጠራቸው አያገርመንም' አለና ቁጭ አለ ፡፡ ይች አባባል ዕድሜ ልኬን አትረሳኝም ፡፡ ...እና ይኸውልህ ዓለማየሁ የማንም ዱዳ እኮ ነው የሚጫወትብን...በቃ ፡፡ ሒድና አስረዳው እምቢ ካለ ልክ ልኩን ንገረው... ለሥራ አስኪያጁ ሔደህ አስረዳ በቃ” አለና መጻፊያውን አንሥቶ አጎነበሰ ፡፡

ዓለማየሁ ፈገግ አለና ሲጋራ አውጥቶ አቀጣጠለ ፡ ወዲያው ከፊት ለፊቱ ያለችው ስልክ ጮኸች ፡፡ ሲጋራውን የለኮሰበትን ክብሪት እንፉት ከሲጋራ መተርኮሻው ላይ ወረወረና ስልኩን አነሣ፡፡

“ሀሎ...ሀሎ”

“ነኝ አዎ”

“አዎ ነኝ”

መልኩ እየተለዋወጠ ሔደ ፡ ይኸ ነው ብሎ ሊገልጸው የማይችለው አንዳች ነገር ከእግር ጥፍሩ ጀምሮ ወደ ላይ ወረረው ፡ አናቱ ይደርስና መልሶ ወደ ታች ይመለሳል ፡፡ አላበው ፡ ሳያውቀው ከመቀመጫው ተነሣና ቆመ ፡

“በፍጹም ሊሆን አይችልም ፡ ሌላ ሐረገወይን እንዳትሆን”

“አዎ ሐረገወይን ወንዲራድ”

“ቢሆንም ፈጽሞ ሊሆን አይችልም”

ታፈሰ ምን ነገር ተፈጠረ ብሎ ትኩር ብሎ ይመለከተዋል ፡፡ ስልኩን ዘግቶ ጉዳዩን እስከሚያወራው የቸኮለ ይመስላል ፡፡

“ፈጽሞ ላምን አልችልም እያልኩዎ”

ስልኩ ጆሮው ላይ ተዘጋበት ፤ የራሱን ጆሮ ተጠራጠረው ፡፡ የስልኩን እጀታ ግጥም አድርጐ ይዞ ወደፊቱ ቀረብ አድርጐ አፈጠጠበት ፡፡ ግዑዙ የስልክ እጀታ “ጡ—ኡኡ” የሚል ረዥም ድምፅ ከማሰማት በቀር ሌላ የሚናገረው አልነበረውም ፡፡ በንዴትና በኃይል መልሶ አስቀመጠው ፡፡

"እ··· ና" አለና በረጅሙ ተነፈሰ ።

"ምንነው ችግር አለ እንዴ ? የምን ጭራ ነው" ጠየቀው ታፈሰ ። እሱም የድንጋጤ ትኩስ አየር እየተነፈሰ ። ዓለማየሁ መልስ አልሰጠውም ፤ "ፈጽሞ የማላምነው ነገር ነው" አለ በልቡ ። "ፈጽሞ ሊደረግ አይችልም ፤ ነገር አለው ፤ ነገር ነገር አለው ፤ በፍጹም ላምነው አልችልም ። ሔረገወይን የሰው ባል ልትቀማ ? ያውም የልጆች አባት ? ፈጽሞ አይደረግም ፤ 'እጅ ከፍንጅ ባሌ ላይ ይዣታለሁ ?' ፈጽሞ አይደረግም እ ··· ና ··· 'የልጆቼን አባት ፤ የምወደውን ባሌን ልታቅራርጠኝ ነው ፤ በዱርዬ አስደብድቤ ነፍሷን ነው የማወጣው ?" እ ··· ና ሊሆን አይችልም ፤ ፈጽሞ ሊሆን አይችልም ።" ዝርፍጥ ብሎ ተቀመጠ ፤ የመውደቅ ያህል ።

"ምንነው ዓለማየሁ ችግሩ ምንድነው ንገረኝ እንጂ" ታፈሰ መቀመጫውን ለቆ መጥቶ ከዓለማየሁ ፊት ለፊት ቆመ ። ጉንበስ አለና እጁን ለዳበሰው ፤ ጭንቅላቱን ዳሰሰው ፤ ያተኩሳል ፤ "ወባው የተነሣበት" ሰው መሰለው ፤

"ምንነው አንተ ልጅ ንገረኝ እንጂ ምን ሆነሃል ?"

"ምን ··· ም · አይደል ··· ጋሽ ታፈሰ ··· የግ ··· ል ··· ጉዳይ ነው ··· ነ ው"

"ንገረኛ ምንድነው ጉዳዩ"

"ቀ ··· ላል ነው ··· ቀላ ···ል"

"እረ እባክህ ንገረኝ" ···

ዓለማየሁ ቀና አለና በረዥሙ ተንፍሶ ከቅምጡ ተነሣ ። ታፈሰ ሊነግረኝ ነው ብሎ ዐይኑን ዐይኑን ይመለከታል ።

ጋሼ ታፈሰ በቃ ቁጭ በል ··· የቤተሰብ ጉዳይ ነው አያሳስብም ሒድ ቁጭ በል ቀላል ··· ጉዳይ ነው ···" ድምፁ ቁርጥ ቁርጥ አለ ። ከአነጋገሩና ከሰውነቱ ሁኔታ ግን ነገሩ ቀላል እንዳልሆነ ለመገመት አያስቸግርም ። ታፈሰ ብዙ ሊያስቸግረው

አልፈለገም ። ጉዳዩ እሱንም ቢያሳስበውም ብዙ ሊያስጨንቀው አልፈለገም ። ትክዝ ብሎ ወደ መቀመጫው ተመለሰ ።

“እ …ፍ” ይላል ዓለማየሁ ። የተለያዩ ሐሳቦችን በአዕምሮው ይመላልሳሉ ። አንዱን ያነሣል ፡ እሱን ይጥልና ሌላ ያነሣል ፡ የሐሳብ ቅብብሎሽ ። ራስን ለማሳመን ከራስ ጋር የሚደረግ ግብግብ ። ‘ማንነሽ ለምን አላልኳትም ፡ ፈጽሞ ላምነው አልችልም ፡ ሐረገወይንን የሰው ባል ልትቀማ ? እጅ ከፍንጅ በሰው ባል ላይ ልትያዝ ? ፈጽሞ አታደርገውም … ግን ግን እኮ ማ … ን … ያውቃል ? ልትባሳት … ፈጽሞ አላምንም ። ታዲያ እንዴት ስሟን ከነአባቷ አወቀቻት … እኔንስ እንዴት ብላ አወቀችኝ … ደሞስ … በደንብ ነው እኮ የገለጸቻት እሷው ናት … እሷው … ግን … አታደርገውም ፡ ፈጽሞ ላምነው የማልችለው ጉዳይ ነው ።” ሰውነቱ ሁሉ ተርገፈገፈ ፡ ፊቱን ላብ አሰመጠው ። ሐሳብ እንደ ክፉ ባላጋራ ታገለው ፡ ሊያሸንፈው ተፍጨረጨረ አልቻለውም ። “ጋሽ ታፈስ በል በል ልሒድ ትንሽ ራሴን ስላመመኝ እቤቴ ሔጄ ልተኛ ።”

“የለም የለም የቅጣቱን ጉዳይ በቅድሚያ አስረዳ እንጂ ፡ ዝም ካልካቸው እኮ ከደመወዝህ ተቀናሽ ያደርጉብሃል … ”

“የለም … ነገ አመለክታለሁ … አሁን ልሒድ” ግንባሩን እየጠራረገ ወጣ ፡ ታፈሰ በዐይኑ ሸኘው ።

ዓለማየሁ ወዴት እንደሚሔድ አያውቀውም ፡ ግን ይራመዳል። የታፈሰን ጥያቄ ለመሸሽ ሲል ከቢሮው ወጣ ፡ እግሩ እንደረገጠ ወደ ፊት አዘገመ ። ቆም ሔደት ይላል ። የመሥሪያ ቤቱን በር ወጥቶ ሔደ ፡ ከራሱ ጋር ሙግት እየገጠመ “በፍጹም አላምንም፡ አይ በፍጹም … እኔ ምን ዓይነት ሰው ነኝ ? እንዴት … ግን ልበል … ስምዎን ማን ልበል ፡ የስልክ ቁጥርዎ … የባለቤትዎ ስም … የት ቦታ መቼ … በስንት ሰዓት አይባልም … ፈጽሞ የማልረባ ሰው ነኝ … ግን እንዴት ላምን እችላለሁ ፡ ምንስ ቢሆን ሐሬን ልጠርጥር ? ማን ያውቃል … ያ እርኩስ በገንዘቡ አታሎአት … ወይ የሆነ

መድኃኒት … ሊሆን ይችላል ። እንዴት … ደሞ እሱ ሚስት የለውም ፡ እሷን ካላገባው እያለ? ቢሆንም ገረዱ ልትሆን ትችላለች ። … ሐረገወይን የሰው ባል ደፍራ፡ ልትቀማ እያደረገም አላምንም ፈጽሞ አላምንም”

“አላምንም” ሲል አረማመዱን ፈጠን አደረገና መልሶ ቀዝቀዝ አለ ፡ የኤሊ ዓይነት ጉዞ ። ከአዕምሮው ጋር እየታገለ የሚራመድ ሰው መሆኑ በግልጽ ያስታውቃል ። እሪ በከንቱንና ቸርችል ጐዳናን የሚያገናኘውን አቀበት ተያያዘው ። የሐረገወይንንና የእሱን የትውውቅ ታሪክ፡ አብረው ያሳለፏቸውን የፍቅርና የደስታ ጊዜዎች ብዙ ብዙ አስታወሰ ። አባቷን ፡ ሚልኪያስን ፡ ወስን የለሀን በልቡ ረገመ ። መልሶ ከራሱ ጋር ሙግቱን ጀመረ ። “አሁን ምን ማድረግ አለብኝ ?” ብዙ ያንገላታው ቶሎም ምላሽ ያላገኘለት መጨረሻ አስፈርቶት የሸሸው ጥያቄ ነበር ። “ልጠይቃት፡ ምን ምን ብዬ እጠይቃታለሁ ፡ ‘አንቺ የሰው ባል ቀማሽ ፡ እንዴት ሴት ባሌን ቀማችኝ አስጠንቅቅልኝ ፡ ብላ ደወለችልኝ’ ብዬ ልናገራት … ፈጽሞ አላደርገውም … ‘አመንካቸው ፡ ተቀበልካቸው ? እኮ እኔ ሐረገወይን የሰው ባል ልቀማ’ ብላ ብትሞነብኝስ ፡ ብታዝንብኝስ … ፈጽሞ አላደርገውም … እኮ ታዲያ ምን ላድርግ … የለም የለም የፈለጋትን ትበል … ኋላ ሌላ ክፉ ነገር ከሚመጣ እሷ ብትቆጣ ይሻላል ልንገራት በቃ በቀጥታ ቢሮዋ ድረስ ሔጄ መንገር … ግን ምን አስቸኮለኝ ቤት ይደርስ የለ …” እፎይታ እንዳገኘ ሰው በረዥሙ ተነፈሰና ቆም አለ ። ግንባሩ ላይ ችፍ ብሎ የነበረውን ላብ በመሐረቡ ጠራረገና ሲጃራ አውጥቶ አቀጣጠለ ። ሲጃራ አጢሶ የማያውቅ ሰው እፏፏስ ማጨስ ጀመረ ። ሳብ እ … ፍ ፡ ሳብ … እፍ አደረገው አከታተሎ ። “ይኸ ፈጽሞ ሊሆን አይችልም … ደሞ ነግሬያት በንዴት ላይ ንዴት ልጨምርባት ፡ ከቤት ወጥታ እኔን ብላ እኔን ተጠግታ ሳስቀይማት ፈጽሞ አላደርገውም … ኤጭ”

ታፈሰ ቢሮው ቁጭ ብሎ በተረጋጋ አዕምሮ መሥራት

አልቻለም ። ዓለማየሁን በዐይኑ ሸንቆት የቢሮውን በር ዘግቶ ቁጭ ሲል እንዳች ነገር አዕምሮውን ጠቅ አደረገው ። መሥራት አልቻለም ። ዓለማየሁን እንደዚያ ሆኖ አይቶት ብቻውን እንዲሔድ መልቀቁ አስገረመው ። "ጨካኝ ፡ ጨካኝ ነኝ" አለ በልቡ ። ወዲያው በሩን ከፍቶ ወጣና እየሮጠ ዓለማየሁን ተከተለው ። ብዙም አልራቀበት ፡ ከኋላው ደረሰና እጁን ያዝ አደረገው ።

"እንዴ ጋሼ ታፈሰ ምነው" አለ ዓለማየሁ በደከመ ድምፅ ።

"እረ አንተ ልጅ አላማርከኝም ፡ ምን ሆነሀል ንገረኝ እንጂ" ለመነው ።

"ምንም አልሆንኩ ጋሽ ታፈሰ ፡ ሙት ምንም አልሆንኩ" የግድ ፈገግ አለ ።

"እንዴት ምንም አልሆንኩ ትለኛለህ ፡ ሁኔታህ ሁሉ ልውጥ ውጥ እያለብኝ ራሱ ሰውነትህ እየነገረኝ"

"ምንም አልሆንኩም"

"ዘመድ ሞተ ወይስ ታመመብህ"

"እረ ደህና ነኝ"

"ታዲያ ከሥራ አባረሩህ"

"እይ ጋሼ ታፈሰ… አላባረሩኝም" አሁንም ፈገግ አለ ።

"ምነው ዓለማየሁ ፡ ሰው እኮ ለሰው መድኃኒቱ ነው ንገረኝ እንጅ ።"

ዓለማየሁ ቆም አለና የታፈሰን ሁለት እጆች ጨብጦ ቀና ብሎ ተመለከተው ፡ አስተያየቱ የልመና አስተያየት ነበር ። "በቃ ተወኝ ጋሽ ታፈሰ ፡ ሌላ ጊዜ እነግርሃለሁ ፡ አሁን ተወኝ ፡ ብቻዬን ተወኝ በቃ ሒድ ተመለስ "

"እሺ እስቲ አረፍ ብለን ሻይ እንጠጣ"

"አንጠጣም አልኩህ ፡ በቃ በቃ ተወኝ … ራሴን አሞኛል ቤቴ ሔጄ እተኛለሁ"

ቃፌስ ቸርችል ጐዳና አቀበት ላይ ካለው የአውቶቡስ ማቆሚያ ድረስ ሸኝቶት ተመለሰ ። ዓለማየሁ በአውቶቡስ ወይ በታክሲ መሔድ አልፈለገም ፣ ቃፌስ ከዐይኑ መሰወሩን ካረጋገጠ በኋላ ቁልቁለቱን ተያያዘው ። አካሔዱ ግን አቀበት የሚወጣ እንጂ ቁልቁለት የሚወርድ አይመስልም ። ቴዎድሮስ አደባባይ ሲደርስ "የእኔ ዓለም ፣ አንተ የእኔ ዓለም" የሚል የሴት ድምፅ ከኋላው ተሰማው ። "ዓለማየሁ" ብላ የምትጣራ ሴት መስላው ድንግጥ ብሎ ዘወር አለ ። እጃቸውን ወደ እሱ የዘረጉ ሴት ተመለከተ ። "በፍጹም እኚህ ሴት ሊሆኑ አይችሉም … የእኚህን ባል … ፈጽሞ …" ብሎ አሰበ ።

"ምን ነበር ምን ፈለጉ ?" አላቸው ድፍረትና ፍርሀት በተቀላቀለበት ድምፅ ።

"የእኔ ዓለም ሳሪስ … ሳሪስ ነው ቤቴ ደካማ ነኝ ለጽድቅ እሆንሀለሁ … የአቶቡስ መሳፈሪያ ጽድቅብኝ"

ኪሱን ደጋግሞ ፈተሸ ። ዝርዝር ሳንቲም አልነበረውም ። ከቦርሳው ውስጥ አንድ ብር መዞ ሰጣቸውና ዞር አለ ። እየተከተሉ መረቁት ፣ ሰልችቶት "በቃ ተመለሱ" እስኪላቸው ድረስ ።

ዓለማየሁ በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ጠጥቶ ሰክሮ አደረ ።

ምዕራፍ ስምንት

ቀን ቀን ጭንቀት የሚያሳድዳቸው ሰዎች እንሱም በተራቸው ተደብቀው ሊያሳድዱት ሲፎክሩበት ይውላሉ ። ፎክረው አያቀፉም፡ ማታ መጠጥ ቤት ይገቡና ይሸሸጉታል ። ጭንቀትም ደንበኛውን ፈልጎ ማግኘት ያዳግተዋል ። ግን መፈለጉን አያቋርጥም ፤ ፈልጎ ቢያገኛቸው ደሞ ብርጭቆአቸውን ያነሡና ያስፈራሩታል ። ደጋግመው ብርጭቆ ያነሡበታል ፤ ያንየ እሱም ይፈራና በቀጠሮ ብቅ ሊል ይደበቃል ፤ ራስን የመደበቅ ጨዋታ ።

ዓለማየሁ ስክር ቤት የመግባቱ ነገር አሳሰቦት ዋለ ፤ አሳሰቦት አደረ ። ስካር ለእሱም ሆነ አብረውት ላሉ ሁሉ እንግዳ ነበር ። እሱን ግን አለቅጥ አስጨነቀው ። ጠባዩ ተለወጠ ብለው ይታዘቡኛል ብሎ እጅግ ፈራ ። ግን የታዘበው አልነበረም ። "በዋልድባስ ይዘፈን የለ!" ብለው አልፈውታል ።

ያን ዕለት ጧት ከቢሮው ወጥቶ ያልተንከራተተበት ቦታ አልነበረም ። ወደ ቢሮው አልተመለሰም ። ሐሳብ ሲያወዛውዘው ውሎ ሲያወዛውዘው አመሸና መጨረሻ በብርጭቆ ተገላገለው ። በምሳ ቤቱ ባለመሔዱ ሐረገወይን ስትጨነቅ ዋለች ፤ ቢሮው ደወለች ፤ ስልኩን የሚያነሣ አልነበረም ፤ ከምሳ በኋላም ደወለች ፤ አሁንም የሚያነሣ አልነበረም ። ከቢሯ ተመልሳ እቤም ስትጨነቅ አመሸች ። ሁሉም ሲጨነቁ አመሹ ፤ አንድ ነገር ቢሆን ነው እያሉ ። አምሽቶ ቤቱ ሲገባ አንድም ነገር አልተነፈሰም ፤ እየተንገዳገደ ገብቶ ተኛ ። ሌሎችም መደካከሙን ተመልክተው ዝም አሉት ፤ አላስቸገሩትም ። ማልዶ ከቤቱ ወጣ ፤ ቀጥታ ወደ ቢሮው ሔደ ።

ለምን እንደሰከረ አልተናገረም ፤ የጠየቀውም አልነበረም ፤ ውለው አደሩ ። ያሳሰበው ነገር በጭንቅላቱ መመላለሱን ባይተውም፡ ዓለማየሁ ራሱን ለማፅናናትና ነገሩን ለመርሳት ያላደረገው

ጥረት አልነበረም ። ጠባዩ ከወትሮው የተለየ እንዳይሆን ያጠነቀቃል ፣ በሐረገወይን ላይ የሚያየው የተለየ ባሕርይ የለም ፤ ያቺው የሚያውቃት የምትወደው ሐረገወይን ናት ። "እንቺ የሰው ባል ቀማሽ እንዴ ?" ብሎ ሊያስቀይማት አልፈለገም ። እስኪ … የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል ብሎ አሰበ ። ወንድሙን ስንታየሁን ፖሊሳዊ ክትትል እንዲያደርግና በወንድምነት እንዲረዳው ፈልጎ ነበር ። ኋላ ተወው ። ዝም ብሎ የሚመጣውን ለመጠበቅ ወሰነ ።

ሐረገወይን እንዳችም ለውጥ አይታይባትም ። ጧት ትወጣለች ፣ ማታ ታጅባ ወደ ትምህርት ቤት ትሔዳለች ፣ ታጅባ ወደ ቤቷ ትመለሳለች ። ራት በልተው ተሰብስበው ሲጫወቱ ያመሻሉ ። ዛማኑኤል እንደ ወትሮው አምሽቶ መግባትን ትቷል ፤ ጧት ይወጣል በአሥራ ሁለት ሰዓት ተመልሶ ይመጣል ። ሐረገወይንን አጅቦ ትምህርት ቤት ለማድረስ ተረኛ ከሆነ እሷን ጠብቆ ትምህርት ቤት ያደርሳል ፤ ከትምህርት ቤት ይመልሳል ። ተረኛ ካልሆነ ከአብዩ ደጉ ጋር ሲጫወት ያመሻል ።

አብዩ ደጉ ዓለማየሁ ቤት መግቢያ ላይ በምትገኝ አንድ ደሳሳ ቤት ውስጥ በደባልነት የሚኖሩ ሽማግሌ ናቸው ። አብዩ ደጉ በደባልነት የሚኖሩባት አንዲት ክፍል ቤት በአፍጢሟ ለመደፋት ቀን የምትቆጥር አስቂኝ ጎጆ ናት ። ወይዘሮ ስመኝ ሁለት ወፍራም የጥድ ግንድ ገዝተው ከፊት ለፊቷ በግራና በቀኝ አስመርኩዘዋታል። በመግቢያው በር ላይ ትልቅ ጠፍጣፋ ድንጋይ አለ ። አብዩ ደጉ ከሥራቸው እንደተመለሱ እዚያ ጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ ቁጭ ይላሉ ። ወይዘሮ ስመኝ የደሳሳዋ ጎጆ ባለቤት በወር ሦስት ብር ያስከፍሉአቸዋል ። አብዩ ደጉ የቤት ኪራይ አሳልፈው አያውቁም ፤ በወቅቱ ይከፍላሉ ፤ ወይዘሮ ስመኝ ሙሾ አውራጅ ናቸው ። ሰው ሲሞት ገንዘብ እየተከፈላቸው ያለቅሳሉ ። እሳቸው ግን ዘፈን አለብኝ ብለው ነው ወደ ተጠሩበት የሚሔዱት ። አረቂያቸውን ይጠጣሉና ሲያስለቅሱ ይውላሉ ። ማታ እቤታቸው ሲመለሱ አብዩ ደጉን ይሰድቡአቸዋል ። "ሁለት ብር አምጣ አለዚያ አስወጣሀ

ለሁ" ይሏቸዋል ፣ ደጉ ይሰማሉ ። ወይዘሮ ስመኝ ሌሊቱን ሙሉ ግጥም ሲደረድሩ ያድራሉ በዕንቅልፍ ልባቸው ። ቀን ሲያስለቅሱ ለት የዋሉትን ሟች ስም እየጠሩ አንገቴ ፣ ጣቴ ፣ ሀብቴ ፣ ጸጉሬ ፣ እያሉ ሲያሞግሱ ዋይዋይ ሲሉ ያድራሉ ። አብዬ ደጉ መተኛት ያቅታቸውና "እመት ስመኝ እመት ስመኝ ንቂ ንቂ" ብለው ይቀሰቅሱአቸዋል ። ስመኝ ይነቁና ከት ብለው ይሥቃሉ ፣ ምን ላርግ ብለህ ነው ደጉ እንጀራዬን እንዲህ ሲያደርገው ፣ እንደው እኮ በአንድ ፊቴ ያንተው ይሻላል በሙቴ ። እስቲ እየው ሰው አባት ሲሞትበት ፣ እናቱ ስትሞትበት ልጁ ሲሞትበት ውነት ማዘን አቅቶት ፣ ማልቀስ ዕንባ ማፍሰስ አቅቶት ነው እኔን የሚጠራ ፣ አይ ይኸ ሞኝ ሕዝብ … እኔማ ምንቸገረኝ ሲነፋረቅ ቢውል ገንዘቤን ከሰጠኝ" ይላሉ ።

አብዬ ደጉ ለማኝ ናቸው ። ግን ሠንጋ ተራ ሰፈራቸው ውስጥ አይለምኑም ። ሌሊት ይነሡና ይወጣሉ ወደ አራት ኪሎ ። የአራት ኪሎን መሸታ ቤቶች ፣ ሱቆች ፣ የአውቶቡስ መጠበቂያ ፌርማታዎች ሲያስሱ ይውላሉ ። የአራት ኪሎ ውሪዎች "የዶሮ ሌባ ፣ የዶሮ ሌባ" እያሉ ያበሽቁአቸዋል ። እሳቸው ግን እንኳ ዶሮ ሊሰርቁ ፣ የወደቀ ሳንቲምም አንሥተው አያውቁም ። በተገላቢጦሽ የሠንጋ ተራ ልጆች ይወዱአቸዋል ፣ ገና የሰፈራቸውን ኮረኮንች መንገድ እንደተያያዙ ብዙ ልጆች ይከቡአቸዋል ። 'አብዬ ደጉ አብዬ ደጉ' እያሉ ፣ ከበዋቸው ይጨፍራሉ ። አብዬ ደጉ 'ትፍ ትፍ' እያሉ ልጆቹን ከኋላቸው አስከትለው አጐንብሰው ወደዚያች ልትወድቅ ወደ ተዘጋጀች ጐጆ ያመሩና ጠፍጣፋው ድንጋይ ላይ ዘፍ ይላሉ ። ልጆቹ ፣ 'አብየ ደጉ አብዬ ደጉ' ይላሉ እያጨበጨቡ ።

"ያሳድጋችሁ ፣ ያሳድጋችሁ ቁጭ በሉ ቁጭ በሉ" ልጆቹ እየተጋፉ ቁጭ ይላሉ ።

"ማነው አለቃ አለቃችሁ ማን ነው ? ሁሉም 'እኔ እኔ' እያሉ ይነሣሉ ። "የለም የለም ቁጭ በሉ አንተኛው ና አንተ ከፍ ያልከው ና" አብዬ ደጉ አንዱን ይመርጣሉ ። "በል እስኪ ስንት ናቸው

ቋጠሯቸው" የልጆቹ አለቃ ይቆጥራል ። አብዬ ደጉ "በል እንግዲህ በየተራ አቅርብልኝ" ይላሉ የደረት ካፖርታቸውን ኪስ እየዳበሱ ። ከኪሳቸው የተጠቀለለ ወረቀት ያወጣሉ ። የተጠቀለለውን ወረቀት ይገልጣሉ ። አንዲት ነጭ ከረሜላ ይመዙና የተጠጋቸውን ልጅ "ስምህ ማን ነው" ይሉታል ። ልጁ ስሙን ይናገራል "ትና ትና ያሳድግህ" ከረሜላዋን ይሰጡትና ይቀመጣል ። ሌላው ይመጣል "ስምህ ማነው ?" ይናገራል ፡ ግንባሩን ሳም ያደርጉና "እስይ እስይ ያሳድግህ" ፡ ሌላው ይመጣል "ጐበዝ ጐበዝ" ፡ ለሁሉም ያዳርሳሉ። አንዳንዶቹ ልጆች ሎሌዎች ናቸው ፡ ሁለት ጊዜ ይቀበላሉ ። ሌሎቹ በአብዬ ደጉ ይከሱአቸዋል ። "አብዬ ደጉ ሁለት ከረሜላ ነው የወሰደው ቀጣፊው" አብዬ ደጉ አይቆጡም "ጐበዝ ጐበዝ ቁጭ በሉ ቁጭ በሉ" ይላሉ ። ተረት ማውራት ይጀምራሉ ። ልጆቹ ፈዘው ይሰሙአቸዋል ። ሲያወሩ ይቆዩና ጀንበር ስታዘቀዝቅ "በሉ ደህና እደሩ" ብለው ጸሎት መሳይ ነገር እያጉመተመቱ አጉንብሰው ደሳሳ ጐጆአቸው ውስጥ ይገባሉ ።

አብዬ ደጉ በሌሊት ይነሣሉ ፡ አንድ ለማኝ አይቀድማቸውም። አሥር ሰዓት ሲሆን ልመና ያቆማሉ ፡ ድንጋይ ባገኙ ቁጥር ቁጭ ብለው እያረፉ ወደ ሠንጋ ተራቸው ይመለሳሉ ። የድሮው ቴራ ሲደርሱ ከአንድ ትልቅ ድንጋይ ላይ አረፍ ይሉና ያንን ድሪቶ ካፖርታቸውን ይሸፋፍናሉ ። ለምነው ያገኙትን ገንዘብ ይቆጥራሉ። ቆጥረው ሲጨርሱ ሀምሳ ሳንቲም ያስቀሩና ሌላውን ከጉያቸው ስበው በሚያወጧት የጨርቅ ከረጢት ውስጥ ከተው አጥብቀው ይቋጥሯታል ። ከዚያ ካፖርታቸውን ለብሰው ወደ ደንበኛቸው አንድ ኪዮስክ ይሔዳሉ ። "አንተ ልጅ ያንን ለማደኝ ስጠኝ" ይሉታል ። የሃምሳ ሳንቲም ነጭ ከረሜላ በጋዜጣ ቅዳጅ ጠቅልሎ ይሰጣቸዋል ። ሀምሳ ሳንቲማቸውን ከፍለው ወደ ሠንጋ ተራ ያዘግማሉ ።

የአብዬ ደጉ ሕይወት ይኸው ነው ፡ ቀን ቀን ልጆች የዶሮ ሌባ እያሉ ሲያበሽቋቸው ይውላሉ ፡ ሲመሽ የሠንጋ ተራ ልጆች

ይመርቁአቸዋል ፣ ዛማኑኤል እንደ ልጆቹ ተሰልፎ ከረሜላ እየታደለው እንጂ ፣ እሱም ቁጭ ብሎ የአብዬ ደጉን ተረት ሲሰማ ያመሻል ፣ ሽርክ አድርጎአቸዋል ። ጥቂቶቹ ገንዘብ ካገኙም ሸጉጥ ያደርጉባቸዋል ። ሐረገወይን ይህንን እያየች “አየ ዘማኑኤል” እያለች ትያቅበጠለች ፣ ዓለማየሁ በጎጆዋ ባለፈ ባገደመ ቁጥር “የዘማኑኤል ጓደኛ ቤት” እያለ ያበሽቀዋል ።

ሐረገወይን ፀጉሯን በረዥሙ ተሠርታ ፣ የምትወደውን ሰስ አረንጓዴ ቀሚስ ለብሳ ስትወጣ ስትገባ የሠንጋ ተራ ጐረምሶች ይመለከቱአትና ምራቃቸውን ይውጣሉ ። እንዳንዶቹ በነገር ወጋ ያደርጉአታል ። እንዳንዶቹ ባሽበረቁ ቃላት አድናቆታቸውን ይገልጣሉ ። ለሁሉቱም ዓይነት ሰዎች ምንም መልስ አትሰጣቸውም። በተለይ የሚያደንቋትን ሰዎች እንዳልሰማ ሁና ዝም ብላቸው ስታልፍ ብሽቅ ይላሉ ። ከሁሉም አብልጦ የሚወዳት ዘርጋው ነው ። ዘርጋው ሠንጋ ተራ ትልቅ የብረታብረት ሱቅ አለው ። ወጣትና ሴት አውል የሚሉት ቢጤ ነው ፣ መዘንጥ ይወዳል ። ሐረገወይንን ካየበት ጊዜ አንስቶ ልቡ ተረበሸ ። መውጫ መግቢያዋን አጠናና አንድ ቀን ወደ ዓለማየሁ ቤት መታጠፊያ ጠባብ መንገድ ላይ ጠብቆ ፣

“ጤና ይስጥልኝ የእኔ እመቤት ፣ ዘርጋው እባላለሁ” አላት ።

“ጤና ይስጥልኝ” አለችና ዐይን ዐይኑን ተመለከተችው ። ፈገግ ብሎ በጥርሱ ሊጥላት ፈለገ ። የመኪናውን ቁልፍ ከቀኝ እጁ ወደ ግራ እጁ አዛወረና አሽከረከረው ።

“ይቅርታ ልተዋወቅሽ ፈልጌ ነበር ፣ ቁጭ ብለን ብንጫወት ይመችሻል? ”

እንዳች ነገር ሰውነቷን ሲወራት ተሰማት ። የያዘችውን ቦርሳ ወርውራ ልትመታው ፈለገች ፣ የቦርሳው ምት የሚያረካትም መስሎ አልታያት ። ተዟዟረችና ድንጋይ ፈለገች ፣ የልቧን የሚያደርስላት ትልቅ ድንጋይ ለማግኘት አልቻለችም ።

“ከፊቴ ዞር በል ፣ ዞር በል ብየሃለሁ ግንባርክን ሳልልህ”

ዘርጋው ፈጽሞ የጠበቀው አልነበረም ፣ ድንግጥ አለ ፣ የሚያደርገው ግራ ገባው ፣ ይቅርታ ብሎ ሊሰወር ፈለገ ፣ ሊሰድባትም አሰበ ።

“ካስቀየምኩሽ ይቅርታ አድርጊልኝ”

ገፈተረችውና አለፈች። ወደ ኋላ ዞር ብሎ ራሱን እየነቀነቀ ተመለከታት ። ‘አዕምሮዋን ሳት ሳታደርግ አትቀርም’ ብሎ አሰበና ሥራው እየገረመው ወደ ብረታ ብረት ሱቁ አመራ ።

ዘርጋው በዚሁ አከተመለት ፣ ብቻ በአዕምሮው ውስጥ የተሳለው የሐረገወይን ምስል ሊጠፋለት አልቻለም ። ጧት ከቤት ስትወጣ ፣ በሰባት ሰዓት ለምሳ ስትመለስ ፣ በሩቅ ሆኖ ያያታል ። ከዐይኑ ስትሰወርበት እያዘነ ይሔዳል ፣ ደግመኛ ማነጋገሩን ግን ፈራው ።

አንድ ቀን ሐረገወይን ከሥራ ወደ ቤቷ ስትመለስ ዘርጋው ከአንድ ሰው ጋር ቆሞ ሲያወራ ከፊት ለፊቷ ተመለከተችው ፣ ገልመጥ አድርጋ አይታው አለፈች ። ዞር አላለችም ፣ ወደ ቤቷ ገሰገሰች ። ዘርጋው ከሰውዬው ጋር የጀመረውን ወሬ አቁሞ ከዐይኑ እስከምትሰወር ድረስ እስኪጠግብ ተመለከታትና መልሶ ወደ ሰውየው ዞር አለ ። ሰውየውም ምንም አላለው ፣ ትዝብቱን ታዝቦ ወሬያቸውን ቀጠሉ ።

ሐረገወይን የዓለማየሁን ቤት ሳሎን በር ብርግድ አድርጋ ስትገባ ዛማኑኤል ሳሎን ውስጥ ይንደፋደፋል ። ሸሚዙን ጠቅልሎ ተንበርክኮ በአንዲት አነስተኛ የመጽሐፍ መደርደሪያ ላይ መጻሕፍት ይደረድራል ፣ እያንጐራጐረ ። ሐረገወይን መግባቷንም አላስተዋለ ፣ ብቻውን እያወራ ይደረድራል ። በሩ ላይ ቆማ ዝም ብላ ታስተውለው ጀመር ። ይጣደፋል ፣ አንዱን መጽሐፍ ያነሣል ፣ ሌላውን ይጥላል ፣ ያወራል ፣ ይዘፍናል ፣ ይሥቃል ፣ ግራ ገባት ።

“ስማ አሁንስ አበድክ መሰለኝ··· ደሞ ብቻህን ማውራት ጀመርክ?”

የኩራት አዚዚር ዞር ብሎ ተመለከታት ። ግንባሩ ላይ ላብ ችፍ ብሎበታል ። እናቱ ገበያ ውላ የተመለሰችለት ሕፃን ልጅ እናቱን በሚያይበት ዓይነት ተመለከታትና ፈገግ ብሎ ተንብርኩ ቀንማ ።

"ምን አልሽኝ ሐረዬ" አለ እጆቹን እያፋተገና ወደ እርሷ እየቀረበ ።

"ብቻህን ማውራት ጀመርክ ወይ ነው ያልኩህ"

"ብቻየን እኮ አይደለሁም ሐርዬ"

"ደሞ ማን አለ ልትለኝ ነው ? ወይስ መጽሐፎቹ ሰው መሰሉህ?"

ፈገግ አለና ትከሻዋን መታ አደረጋት ።

"ሰማሽ ሐረ"

"አቤት"

"ብቻየን የማዋራ መሰለሽ? አየሽ ሐረ" አለና እጆቹን ወደ ወንበሮቹ አመለከተ ፡ "እይው እንዚህን ወንበሮች እያንዳንዳቸውን በአምስት መቶ ሰው ወከልኩአቸው ፡ ይህችን ክፍል እንደ ትልቅ መሰብሰቢያ አዳራሽ ቆጠርኳት ፡ እና ተናግሬ ሰውን ለማሳመን እችላለሁ ወይ ብየ መናገር ጀመርኩ ፡ ኮስተር ብዬ ንግግር አደረግሁ፡ ታዲያ ምን ያደርጋል አፌ ደረቀ እንጂ የሚያጨበጭብ ሰው አልነበረም ። እኔ ምን አገባኝ አሁን ስናገር ብውል ሩብ ዴሞስቴን አይወጣኝ ብየ ተውኩት ፡ እውነት ሐርዬ ንግግር ሳደርግ እዚህ ቆመሽ ነበር እንዴ? ወይ ጉዴ ስጃጃል ተመልክተሽኛል? ሙች እስኪ ንገሪኝ" አለና እጆቹን ከጀርባው ላይ አስተሳስሮ አፈጠጠባት። ሐረገወይን እንደመደናገጥ አለችና ፡

"ውይ ቆመህ ስትናገርስ አላየሁም ፡ እኔ እኮ አሁን ነው የመጣሁት ። በሩን ገፋ አድርጌ ስገባ ተንበርክከህ ታንጎራጉራለህ። ምን እያረገ ነው ጉዱን እያለሁ ብየ ዝም ብየ ስጠብቅ አንድ ጊዜ ትሥቃለህ ፡ አንድ ጊዜ ትዘፍናለህ ፡ ግራ ሲገባኝ እኮ ነው ደሞ

ብቻህን ማውራት ጀመርክ እንዴ ያልኩህ" አለችው ቦርሳዋን ሶፋው ላይ ጣል አድርጋ ወደ መጻሕፍት መደርደሪያው እየሄደች ። መጽሐፎቹን ትኩር ብላ ተመለከተቻቸው ። አንዳንዶቹን እያነሳች ተመለከተችና ወደ ዐማኑኤል ዞር አለች ። አንድ ነገር ልትጠይቀው መሆኑ ገብቶታል ።

ሐርዬ ቆይ መጀመሪያ የጠየቅሽኝን ልመልስና ያሰብሺውን ትጠይቂኛለሽ እሺ ሐርዬ"

"እሺ ደስ ይበልህ" አለችው ።

ለመናገር የፈገው ነገር ቀድሞ ኢማቀው ። "ምን መሰለሽ ሐርዬ" አቋረጠና ማቀ ።

"እባክህ አትቀልድ" ብላ ጮኸችበት ፡ እጇንም ማቅ እያፈናት።

"ምን መሰለሽ ብቻየን ሥሥቅ የነበረው የአንቺና የእኔ ነገር ገርሞኝ ነው"

"ምን የሚገርም ነገር አለና ይገርምሀል?"

"አለ እንጂ ሐሪ!""

"እኮ ምን?"

"እንዴ ሰው እኮ ሲሸፍት ራቅ ብሎ ጫካ ነው የሚገባው ፡ አንቺና እኔ ግን ከላምበረት ወጥተን ሠንጋ ተራ መሸፈታችን ነው ያማቀኝ"…የግልምጫ ተመለከተችውና ቁጭ አለች ።

"መቸም የማታመጣው የለህም ፡ ደሞ እንዲህ የሚል ቧልት አመጣህ"

"ቧልት አይደለም ሐርዬ ይኽ እኮ ለሚመራመር ሰው ብዙ የሚጻፍበት ነው"

"በቃ ተወኝ" ብላ ተነሣች ። መልሳ ወደ መጻሕፍት መደርደሪያው ሔደችና "ስማ ቤት ሔደህ ነበር ማለት ነው" አለችው መጽሐፎቹን እያስተዋለች ።

“እይደለም ሐረ ልነግርሽ እኮ ነበር ቀደምሽኝ እንጂ ፡ ቅድም ልትጠይቂኝ የነበረው ይህንኑ ነው አይደል?”

“አዎ ይህንኑ ነበር ፡ ማንን አገኘህ ቤት”

“የለም እኔ አልሔድኩም ፡ ይኸውልሽ ጧት አንቺ ወደ ሥራ እንደ ሔድሽ ቤት ደወልኩና ያ ሞዛዛ ሽማግሌ አነሣ ፡ ድምፄን ቀየርኩና ዘነበችን ነበር አልኩት ፡ ጠራልኝ ።”

“ታዲያ ምን አለችህ ፡ ማለቴ ምን አወራችህ”

“ቆይ ልነገርሽ አይደል ፡ እኔ መሆኔን ስታውቅ አለቀሰችና ‘ከእትዬ ጋር አንድ ላይ ናችሁ ወይ?’ ብላ ጠየቀችኝ ፡ ‘አዎ አንድ ላይ ነን፡ ደኅና ናት አታስቢ’ አልኳት ። ‘መጽሐፎቼን ፈልጊ ነበር እንዴት ይሻላል’ ስላት፦ ‘አንድ ቦታ ጠብቀኝና ላምጣልህ’ አለችኝ፡ ባቡር ጣቢያ ተቀጣጠርን ይዛልኝ መጣች ። እኔም ለማናቸውም ቤቱን ብታየው ይሻላል አልኩና አምጥቼ ቤቱን አይታ ሸኘኋት እልሻለሁ። እትዬም… ይታይሻል” አለና ወደ ቢፌው አመለከታት።

“ምኑ”

“የታሰረ ሳህን አይታይሽም”

“ይታየኛል ምንድን ነው?”

“እትዬ ናት የላከችው ፡ ለልጆቼ ስንቅ ብላ ሠርታ የላከችልሽ ነው ፡ ዛሬ ምሳሽን እሱን ነው የምትበይው”

ሐረገወይን ሮጥ አለችና ወደ ሳህኑ ሔደች ። የተሸፈነበትን ነጭ ጨርቅ ገለጥ አድርጋ የሳህኑን ክዳን አነሣች ። ጣጥም ብሎ ሞልቷል ፡ ነጭ እንጀራ ፡ ሥጋ ወጥ ። ከላዩ ላይ ቆንጠር አድርጋ ጕረሰችለት ። ወዲያው ዐይኖቿ ዕንባ አዘሉ ። እያለቀሰች ወደ መቀመጫዋ ተመለሰች ። ዛማኑኤል ተቆጣና ለቅሶዋን አስቆማት ።

“ቆይ ሌላስ ምን አለችህ” ጠየቀችህ ፡ ዕንባዋን እየጠራረገች ።

“አይ ቸኩላ ነበር ፡ ምንም አላወራችኝ” አላት ውሸቱን ። ዘነበች “እትዬና ጌቶች ተጣልተዋል ‘ልጇን አባረህ ያገር መሣቂያ

አደረግኸን’ ብለዋቸው ተቀያይመዋል ፡ እትየ ሲያለቅሱ ይውላሉ ፡ ሲያለቅሱ ያመሻሉ” ያለችውን ሊነግራት አልፈለገም ። መዋሸቱ ትክክል መሆኑ ቢገባውም ቅር አለው ። ወዲያው የሳሎኑ በር ተከፈተና ዓለማየሁና ስንታየሁ ተከታትለው ገቡ ።

የወይዘሮ ተዋበች የሳህን እንጀራ ጣፍጦአቸው በሉ ።

ምዕራፍ ዘጠኝ

በማግሥቱ ልክ በሰባት ሰዓት ተኩል ዓለማየሁ ፡ ስንታየሁና ዛማኑኤል በምግብ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው ይጫወታሉ ። ዛማኑኤል ልዩ ልዩ ተረቶች እያወራ ያሥቃቸዋል ። ዓለማየሁ ሸሚዙን ወደ ላይ ጠቅለል አደረገና ሰዓቱን ተመለከተ ። የዛማኑኤልን የሚያሥቁ ተረቶች ማድመጥ ቢፈልግም ፡ አንድ ነገር ጭንቅላቱን ወጋ አደረገው ። በምሳ ሰዓት ሁልጊዜም ቀድማ የምትገባው ሐረገወይን ናት ። ዛሬ ግን ዘገየች ፡ ለምን? ዓለማየሁን አስጨነቀው ። በሐሳቡ ብዙ ቦታ ረገጠ ፡ የተለያዩ ጥሩና መጥፎ ግምቶች አዕምሮው ውስጥ አቃጨሉበት ፡ ቁጭ ብሎ ተረት እያደመጠ መሣቁን አልወደደውም ፡ የመበርገግ ያህል ከመቀመጫው ተነሣና ስልክ ወዳለበት ትንሽ ጠረጴዛ ሮጠ ። ስንታየሁና ዛማኑኤል ተገርመው በዐይናቸው ተከተሉት ። ያ ሲሥቅ ሲያወራ የነበረ ዓለማየሁ ለአፍታ ተለወጠና ፊቱ ሁሉ ግርጥት አለ ። “ምን ሆንክ ዓለማየሁ” አለው ስንታየሁ ።

“እንዴ አንድ ነገር ካልሆነች እንዴት እስካሁን ትቀራለች ፡ ምናልባት ቢሮዋ ልደውል ብየ እኮ ነው”

ሐረገወይን ቢሮ ደወለ ፡ የሚያነሣ አልነበረም ። ስልኩ ጮሆ ጮሆ የመያዝ ምልክት አሳየ ። የመወርወር ያህል ዘጋውና ቁጭ አለ። ሁሉም ተኮራርፈው እንደተቀመጡ ሠራተኛዋ መጣች ፡

“እንዴት ይሻላል ላቅርብ እንዴ ምሳ”

“የለም እሷን እንጠብቃለን” ይቆይ አለ ስንታየሁ ።

ዛማኑኤል ከተቀመጠበት ተነሥቶ በዚያች ጠባብ ክፍል መንጐራደድ ጀመረ ። መልስ የማያገኝለት ችግር ሲገጥመው መንጐራደድ ይወዳል ፡ እየተንጐራደደ ለችግሩ ምላሽ ለማግኘት

ይሞክራል ፡ ግን አያገኝም ፡ የሚያገኝለት ከሆነ ቀድሞውንም ተነሥቶ አይንጐራደድም ። እሱንም ሐሳቡ ዘልቆ ገባውና ግንባሩን ያልበው ጀመር ።

"ዓለማየሁ ወይ ሔደን እንፈልጋት እንጂ"

"እሱ ይሻላል" ዓለማየሁ ኮቱን እንደገና መልበስ ጀመረ ። ሚስቱም ተያይዘው ሊወጡ ሲሉ ሐረገወይን በሩን ብርግድ አድርጋ ገባች ፡ ሁሉም ድንግጥ ብለው መንገዱን ለቀቁላት "እ… ና" ብላ በረዥሙ ተነፈሰች ። ቦርሳዋን አሽቀንጥራ ጣለችና የመውደቅ ያህል ዘፍ አለች ሶፋው ላይ ፡ አሁንም "ኡፍ" አለችና ራሷን በሁለት እጆቿ ጥምም አድርጋ ይዛ አቀርቅራ ዝም አለች ።

"ሐረ ምን ሆንሽ ፡ ምን ሆንሽ" አለ ዓለማየሁ ከፊት ለፊቷ ተንበርክኮ ራሷን እየደባበሰ ፡ ቀናም አላለች ። "ምን ሆንሽ ንገሪኝ እንጂ" ከጎኗ ተቀመጠና እቅፍ አድርጎ ከቀረቀረችበት የግድ አስነሣት ።

ትኩር ብላ ተመለከተችው ። ዐይኗን የጋረደው ቀጭን የዕንባ ሻሽ ተጠቀለለና ወረደ ። ያች ክፍል ለአፍታ የሐዘን ደመና አንዣበበባት ። ምን እንደሆነች ሊገባቸው ባይችልም ፡ ስሜቷን አብረው አዘኑ ፡ የእነሱንም ዐይን የዕንባ ጭጋግ ሸፈነው ። "ምን ሆንሽ" በሚለው ጥያቄ ሊያዋክቡአት አልፈለጉም ። ተቀመጡና ዐይን ዐይኗን ይመለከቷት ገባ ።

የዓለማየሁ ሠራተኛ ምሳ ይዛ መጥታ ምግብ ጠረጴዛው ላይ ትደረድራለች ። ቤቱ ውስጥ ያልለመደችው ጉዳይ ያለ መሆኑ ቢገባትም ፡ ምንድን ነው ብላ ለመጠየቅ አልደፈረችም ። እንጀራውን ፡ ወጡን እያስቀመጠች ጆሮዋን ጣል አድርጋ ለማዳመጥ ሞከረች ፡ ከውጭ ከሚሰማው የሁንጋ ተራ ግርግር ፊሽሽት በቀር ቤቱ ውስጥ የሚናገር የለም ። ሁሉም ተኮራርፈው ቁጭ ብለዋል ። ደርድራ ስትጨርስ ወደ ዓለማየሁ ጠጋ አለችና ፡

"ምሳ ቀርቧል ጋሼ" አለች ። ምንም ምላሽ አላገኘችም ።

ለጥቂት ጊዜ ቆም ብላ አስተዋለችና ወደ ጓዳዋ ገባች ። ሐረገወይን ከቀረቀረችበት ቀና አለች ፡ ሁሉንም ተመለከተቻቸው ፡ ዓለማየሁ አቀርቅሮአል ፡ ዛማንኤል እሷን ይመለከታል ፡ ሰንታየሁ ከመስኮቱ ባሻገር ውጭ ውጪውን ይመለከታል ። ሐረገወይን "ተነሡ ምሳ እንብላ" ብላ ቀድማ ወደ መታጠቢያ ገባች ። ታጥባ ተመለሰችና ወደ ምግብ ጠረጴዛው ሔዳ ቁጭ አለች ፡ ሌሎቹም ተከተሏት ። ሁሉም ተኮራርፈው ቁጭ አሉ ። ሁሉም አቀርቅረው መብላት ጀመሩ ። ዓለማየሁ ብዙም ጊዜ አልቆየ ጥቂት ጉርሻዎች ጎራረሰና ተነሥቶ ሲጋራውን አቀጣጠለ ።

"ምነው አትበላም እንዴ ፡ ቁጭ በል እንጂ" አለው ዛማንኤል።

"እይ በቃኝ ጠገብኩ"

"ምን በላህና ነው የምትጠግበው"

"የለም በቃኝ" ረዥሙ ሶፋ ላይ ሔዶ ቁጭ አለ ።

ሐረገወይን በዐይኗ ተከተለችው ፡ "ረበሽኳችሁ አይደለ? በጣም ይቅርታ አድርጉልኝ ። ዓለማየሁ ምን መሆንህ ነው ፡ ምሳ አይደለም እንዴ ና እንጂ" አለችና ተነሣች ። "ሙት ና ና ብላ ፡ ካልበላህ እኔም ልተወው ነው ። ሙት! ልተወው ነው ፡ እየራበኝ ልተወው ነው"

ዓለማየሁ ተመልሶ መጣና ቁጭ አለ ። ሐረገወይን ትክ ብላ ስትመለከተው ሲጋራውን ወረወረና መልሶ መብላት ጀመረ ። ሐረገወይን የጥፋተኝነት ስሜት ተሰማት ። በውስጧ የሚንቀለቀለው የንዴት እሳት በገፅታዋ ላይ በሚያሳየው ምስቅልቅል ምስል አሁንም እንዳች ነገር መሆኗን የሚጠቁም ቢሆንም ፡ ቤት ስትገባ የነበረችበት ሁኔታ ተለውጦአል ። ራሷን መቆጣጠር ችላለች ። ግን ፊቷን ትኩር ብለው ሲመለከቱት የዘወትሩ ድንቡሽቡሽ የሐረገወይን መልክ አይደለም ። እንደ አዲስ አበባ ከሩቅ ይንቦገቦግ የነበረው እነሁላይ ውበቷ ውርጭ እንደመታው ቡቃያ ኩምሽሽ አለ ።

ችግርን ችሎ መከራን ታግሶ ብሶትና በደልን "ግዴለም" ብሎ የሚያልፈውን ሆድ ፡ ብዙ ይችላል የሚባለውን ሆድ የገዛ አካሉ ፊት ያጋልጠዋል ። ሆድ ውስጥ የተደበቀን ምስጢር እት ፊት አደባባይ ያወጣዋል ። ሐረገወይን ጥቂት ተክዛ ቆየችና ፡

"ይኸውላችሁ" አለች ። አድምጡኝ የምትል ያህል ተሰማቸው ፡ ሁሉም መብላታቸውን ትተው ፈዘው ተመለከቷት ። "ይቅርታ አድርጉልኝ ምን ላድርግ ዕድሌ ሆኖ ችግር በየቦታው ይከተለኛል ..." ቁራሽ እንጀራ እንጣችና ጣቷን ጠርጋ ወረወረችው።

"ንገሪና ምንድን ነው የሆንሽው?" ዓማኑኤል ሳያስበው ጮኸ።

"እንዴት ለክፉ ለከፈችኝ"

"ምን ብላ ነው የምትለክፍሽ" ዓማኑኤል የበለጠ ተቆጣ ። ዓለማየሁና ስንታየሁ ፊታቸውን አኮሳትረው ዝም ብለው ያዳምጣሉ ።

"በሰባት ሰዓት ከሥራ ወጥቼ ወደዚህ ስመጣ በሩ ላይ ጠበቀችኝና 'አንቺ ስሚ ብትታገሺ ይሻልሻል ፡ የጀመርሽው ሥራ እንደማያዋጣሽ እወቂ ፡ አንገትሽን አንቄ ነው የምገልሽ' አለችኝ ፡ ድንግጥ አልኩና 'ምነው የእኔ እናት ወደ እኔ ነሽ እንዴ' አልኳት ። 'አዎ አንቺን ነው ፡ አንቺን' አለችኝ ለመማታት እየተጋበዘች ፡ 'እንዴ የት ታውቂኛለሽ' አልኳት ፡ 'ድንቄም እንዴት አላውቅሽ" አለችኝና ተነሣች ። ቦርሳዋን ወደ አስቀመጠችበት ሶፋ ሔደች ፡ ቦርሳዋን ከፍታ ነጭ መሐረብ አወጣችና ተመልሳ ተቀመጠች ። መሐረቧን በግራ እጇ ይዛ አፍንጫዋንና ግንባሯን ጠረገች ። ሌሎቹ የተለያየ ስሜት በውስጣቸው እየተብላላና በጉጉት እየተቁለጨለጩ ይመለከቱአታል ። ግንባሯን ጠራረገችና ከቆመችበት ቀጠለች ።

"እና ምን አደረግሁሽ አልኳት ፡ 'እጮኛየን መልሽልኝ ነው የምልሽ ዓለማየሁ እጮኛዬ ነው ፡ እረፊው አርግዤለታለሁ ፡ እና

ልብ ካለሽ አደጋ ሳያደርስብሽ ተዪልኝ ነው የምልሽ' አለችኝ ። ይገርማችሁአል መቸስ ስትለፈልፍ ፍጥነቷ ልነግራችሁ አልችልም፡ ተውረገረገችብኝ ። ደሞ ያበሸቀኝ ምን መሰላችሁ ብዙ ሰው ተስብስቦ እያየን ፡ በጣም በጣም በሸቅሁ ። ዘግቻት ለመምጣት መንገድ ስጀምር እየተከተለች 'ነግሬሻለሁ ፡ አስረግዞኛል ፡ የእኔ ዕድል ተበላሽቶ አንቺ በሕይወት የምትኖሪ አይምሰልሽ' ትለኛለች። እኔ ብዙ ነገር ስለምጠረጥር ልጨቃጨቃት አልፈለግሁም ፡ እንዳልሰማ ሁኜ ለመምጣት ሞከርኩ ፡ እስከ ሜክሲኮ አደባባይ ድረስ እየጨቀጨቀችኝ መጣችና ወደ ኋላ ተመለሰች ፡ እሰይ ተገላገልኩ ስል ሁለት ዱርዬዎች አስከትላ እየሮጠች መጣችና 'ይች ናት ይች ናት' ብላ ወደ እኔ አመለከተቻቸው ፡ ከዱርዬዎቹ አንዱ ሸሚዙን እየጠቀለለ ወደ እኔ መጣና 'ንብር አየኝ በይ ፡ ቆይ ጉሮሮሽ ላይ ነው የምቆምብሽ' ብሎኝ ሔደ ...” ዕንባዋ ሳይታሰብ ዱብ ዱብ ማለት ጀመረ ። ጉንጮቿ ለአፍታ መልካቸውን ቀይረው ሲዳፈን የተዘጋጀ እረመጥ መስለው ቂጭ አሉ ። ከዚህ በኋላ መቀጠል አልቻለችም ድምጿ ተስረቀረቀ ። ለጥቂት ደቂቃዎች በክፍሏ ውስጥ ጸጥታ ሰፈነ ።

ዓለማየሁ ሲጋራውን አቀጣጠለና የመጀመሪያውን የሲጋራ ጢስ በረዥሙ ተንፍሶ አስወገደው። ከአፉ የሲጋራው ጢስ ብቻ ሳይሆን አንጀቱን ሲቦረቡረው የቆየው ውስብስብ ሐሳብ አብሮ የወጣ ያህል እፎይታ ተሰማው ።

ሠራተኛዋ ምሳ ያቀረበችባቸውን ዕቃዎች አንሥታ እስከምትጨርስ ጠበቀና ፡ “ጉበዝ አንድ የተሸረበ ነገር አለ” አሁንም ሲጋራውን የብስጭት ዓይነት እየሳበ ። “እመኑኝ አንድ ነገር አለ ፡ እኔ አፍኜ ሳልነግራችሁ ቀረሁ እንጂ እኔንም ተፈታትነውኛል ። ከአምስት ቀን በፊት መሰለኝ ቢሮ እንደገባሁ ስልክ ይደወላል ፡ አንዲት ሴት 'ሐረገወይን ባሉን የልጆቼን አባት ቀምታኛለች ግንባሯን ብየ ሳልፈጠፍጣት አስታግስልኝ' አለችኝ ። ፈጽሞ ማመን አልቻልኩም ፡ 'እረ እባክዎ ሌላ ሐረገወይን እንዳትሆን'

አልኳት ፡ 'ሐረገወይን ወንዷራድ አይደለችም እዚህ ቦታ አያደለም የምትሠራው' አለችኝ ። የነበርኩበትን ሳትኩኝ ፡ ብዙም ሳልጠይቃት አስፈራርቻ ስልኩን ዘጋችብኝ ..." ከሲጋራው እኩሌታችሉ ሳበለት ። "ነገሩ አሁን ነው የገባኝ ... እውነቱን ልንገራችሁ ፡ ያን ቀን ጠጥቼ የገባሁት ለዚህ ነው ..."

ስንታየሁ "ተወው ተወው ገባኝ ገባኝ" አለና አቋረጠው ። ዳግመኛ ለጥቂት ሰከንዶች ጸጥታ ሰፈነ ።

ስንታየሁ ዘሎ ተነሣና ከሶፋው ላይ ያስቀመጠውን መለዮውን አንሥቶ አስተካክሎ ራሱ ላይ ሰካው ። ከፊቱ ላይ የሚነበበው የቁጭት ስሜት ብርር ብሎ ወጥቶ በጠላቱ ላይ የሞት ብያኔ ለመስጠት የተዘጋጀ እልከኛ ሰው አስመሰለው ። አየር ሳይሆን እሳት የሚተነፍስ ይመስላል ። ንዴት ለካ መላ ያሳጣል ፡ በዚያች ጠባብ ክፍል ውስጥ ጥርሱን ነክሶ ሽንጡን መዞ ተውረገረገና ለመውጣት ወደ ሳሎኑ በር አመራ ።

"ቆይ እንጂ አንተ ደሞ የት ነው የምትሔደው" ሬሖቦት ዓለማየሁ ። ስንታየሁ በሩ ላይ እንደተገተረ ቀረ ። ሐሳብ ውስጡን ያተራምሰው ጀመር ። ለመሔድ ተነሣ እንጂ የት ነው የምትሔደው ቢሉት በእርግጠኝነት የሚናገረው አልነበረውም ። ለወትሮውም ወደ ሥራው የሚሔደው በዚህ ሰዓት አይደለም ። ተመልሶ ቁጭ አለ። መለዮውን ከራሱ ላይ አውርዶ ሶፋው ላይ ወረወረና ግንባሩን በሁለት እጆቹ አስመርኩዞ አቀረቀረና ቀና አለ ።

"ይኸውላችሁ ይኸ ሁሉ ደባ በእነዚያ ሰዎች የተጐነጐነ ነው። ምን አለፋችሁ ሊሳካላቸው ባለመቻሉ በዚህ መልክ ሁለታችሁን ለማጣላት የጐነጐኑት ሴራ ነው ። በቃ አንተም አንቺም በየግላችሁ ጥላቻ እንድትይዙና ጠብ ውስጥ እንድትገቡ ፡ እንድትቆራረጡ የተሸበረ ነው ። እይ ... እይ ....ይች ትጥፋን ። በዚህም ብቻ የሚመለሱ አይመስለኝም ። ገና ከዚህ የከፋ ነገር ያደርጋሉ ፡ ከእንግዲህ ክፉ ጠላት እንደገጠመን አውቀን መጠንቀቅ ይኖርብናል ። ሌላ ምንም የምናደርገው ነገር አይኖርም ። በቃ በቃ ።

ሐረገወይን ወደ ትምህርት ቤት ስትሔድና ስትመጣም ከእንግዲህ የምናደርሳት ሁለት ሁለት ሆነን መሆን አለበት ። ዓለማየሁና ዛማኑኤል በተራ ትሔዳላችሁ ፣ እኔ ግን መቅረት የለብኝም ፣ በየዕለቱ አብሬ መሔድ አለብኝ ።" ሰዓቱን ተመለከተና ተነሣ ። "እሺ እኔ ልሒድ ጠቅላይ ግምጃ ቤት የምሔድበት አስቸኳይ ሥራ አለኝ በሉ" ብሎ እየተቻኮለ ወጣ ።

ዓለማየሁ ፣ ዛማኑኤልና ሐረገወይን ሲጫወቱ ቆዩ ። ሐረገወይን ከሰዓት በኋላ ሥራ መግባት አልፈለገችም ፣ ዓለማየሁ ዛማኑኤል ከቤት ሳይወጣ እንዲያጫውቷት አደራ ብሎ ወደ ሥራው ሔደ ። ማታ ዓለማየሁና ስንታየሁ ትምህርት ቤት አደረሷት ፣ መልሰውም አመጧት ። የገጠማቸው አንድም ነገር አልነበረም ። ዓለማየሁ ቤት ውስጥ ቁጭ ብሎ ጠበቃቸው ። ከሥራ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ሐሳቦችን ሲያወጠንጥን ቆየ ። ወደ ኋላ መለስ ብሎ የእሱንና የሐረገወይንን የፍቅር ታሪክ አስታወሰ ። እንከን ያልነበረበት ገና ያላፈራ እንቡጥ የፍቅር ጊዜ ማሳለፋቸው ደስ አለው ። አሁን ችግር ተፈጠረ ፣ ችግሩ ደግሞ እነሱ የፈጠሩት ሳይሆን ሌላ ባዕድ የፈጠረባቸው ነው ። ስለዚህም እንዳልፈነዳ ጽጌረዳ የሚቆጥረውን የሁለቱንም ፍቅር ተንከባክቦ ለፍሬ ለማብቃት ቁርጥ ሐሳብ ላይ ደረሰ ። ብቻውን እዚያች ትንሽ ሳሎኑ ውስጥ ቁጭ ብሎ ብዙ ብዙ ተፈላሰፈ ።

የሰዎች ባሕርይ አስገረመው ። ተንኮል ፣ ሸር ፣ ጥቂት ለማግኘት ሰውን ያህል ክቡር ነገር ማጥፋት ፣ የሌላውን ለመንጠቅ ፣ የሌላውን ለመውሰድ በገንዘብ ፣ በጉልበት ፣ በዘመድ በአዝማድ መጣር ። "ሥልጣኔ ያመጣው የማኅበረሰብ ዕዳ" አለ በልቡ ። ደግሞም ደጋጎቹ ትውስ አሉት ። የሌላውን ችግር የራሳቸው አድርገው የሚቆጥሩ ፣ ለሰው ልጅ ደኅንነት ሲሉ ገንዘብና ጉልበታቸውን ብቻ ሳይሆን ሕይወታቸውን ለመስጠት የተዘጋጁ ብዙ ብዙ ሰዎች ታወሱት ። አይ ይህች ዓለም ፣ የክፋትን ያህል ደግነትም የጥላቻን ያህል ፍቅርም ባይታይባት ፣ የሚያስጠላ ብቻ ሳይሆን የሚያስደስ

ትም ፡ የሚዘገንን ብቻ ሳይሆን የሚጥምም ባይሰማበት አርኩሶች ብቻ ሳይሆኑ ጻድቃንም ባይኖሩባት ሊኖሩባት ቀርቶ ለአንድ ቀንም አይታደርባት ነበር ። ውይ ውይ እንዴት ተንገሸገሸ ነበር! ብሎ ይመይጠ ። ግን አለ በሐሳቡ ፡ የትኛው ይበልጣል? በዚህች ስራ ግን ጠባብ ምድር ላይ አይሎ የሚታየው ክፋት ወይስ ደግነት ፡ ብዙ ብዙ አሰበበት ፡ ተመራመረ ። ደመረ ። ቀነሰ ይኸኛው ብሎ ቁርጥ ያለ ምላሽ ሊሰጠው አልቻለም ። ይኸኛውን ባለና ወይ ሌላ ሐሳብ ተሸጋገረ ።

ግን ግን ክፋት ፡ አብረት ፡ ማንአህሎኝነት ፡ ተንኮል ይኸን ይኸን የመሳሰለው እኩይ ምግባር ሁሉ የማ ባሕርይ ነው ፡ የተማሩ ወይስ ያልተማሩ ሰዎች ፡ ብዙ አውጥቶ አውርዶ አሰበው ። እንዲሁ ቀላል መልስ ሊያገኝለት አልቻለም ። የተማሩ የሚላቸውን አሰባቸው ክፋትም ደግነትም አገኝባቸው ፡ ያልተማሩትንም አሰበ — እነሱም አለባቸው ። ብዙ አመራመረው ፡ እንግዲህ መማር ማለት ሀሁ ከመቁጠር የሚጀመር ከሆነ ፡ እም የተማሩ ሰዎች ባሕርይ ነው ፡ ግን መማር ሀሁን ከመለየት በላይ ከሆነ የማይማን ጠባይ ነው ። በመማርና ባለመማር መኻል ያሉት ፡ ትንሽ ዕውቀት ያላቸው ሳያውቁ ያወቁ የሚመስላቸው ፡ ገንዘብ በትዕቢት ባና ዐይናቸውን የሸፈናቸው ፡ ሥልጣን ልባቸውን ያሳበጠባቸው ባሕርይ ነው ። በቃ በቃ ። ይስ አለው ።

እና በዚህ ምስቅልቅል ዓለም ውስጥ የእሱና የሐረገወይን ፍቅር ፡ የሁለቱ ግንኙነት ፡ የሁለቱ አንድነት ኢምንት አይደል እንዴ? ምቀኝነት ፡ ክፋት ፡ ተንኮል ካልሆነ በቀር ወላድ በድባብ ትሂድ እንጂ ሴቱም ወንዱም እንደአሸን አይደለ እንዴ ፡ ለምን የኔን? ቅናት መሰል ነገር ኮርኮር አደረገው ። ሳይታወቀው የሶፋውን መደገፊያ በኃይል በቡጢ መታው ።

ሠራተኛው “ጋሼ ሻይ ላፍላ እንዴ?” አለችው ድንገት ከኋላው ደርሳ ። እዕምሮው ውስጥ ገብቶ የሚያስበውን ሁሉ ያወቀችበት ይመስል ድንግጥ አለ ።

"ተይው ተይው አልፈልግም" ቶሎ አለና ሒሳቡን ለወጠ ፡ "እሺ ትንሽ አፍሊ ።"

ሠራተኛው ትዕዛዙን ተቀብላ ወጣች ፡ መልሶ በሐሳብ ክሩ ውስጥ ገብቶ መንቦጫረቅ ጀመረ ። የተለያየ ኅብር ያለው ሐሳብ እንደ ዝንብ ወረረው ። አንዱን ጥሎ አንዱን ማንሣት ። 'የእሷና የእኔ ጉዳይ እንዲህ ሆኖ እስከ መቼ ይዘልቃል ። አንድ ነገር መደረግ አለበት ። መቋጠሪያ ያስፈልገዋል ፡ መቋጠሪያ ገመድ …' ሲጋራ አወጣና አቀጣጠለ ። እዎ ያስፈልገዋል ። ቀለበት ፡ ቀስ ብሎ ደግሞ ሠርግ ። አዎ በቃ ። መምሬ ቸሬ ሚስትንና ዳዊትን በብብት ነው ይሉ ነበር ። አዎ በዋስትና መያዙ ። ቀለበት በሚለው ቆረጠ ። እኒያ ግትር የሐረገወይን አባት ትዝ አሉት ። ረጋገመና ተዋቸው ። ታማሚዋ ርኅሩኅ እናቷ ድቅን አሉበት ። ወንድሟ ብሎ ተስዶ እሱ ቤት የገባው ዛማኑኤል ባሕርይ ግርም አለው ። ዐይኖቹ የደስታ ይሁን የምን ሊገባው ባልቻለ ሁኔታ ዕንባ አዘሉ ። ደስታም እኮ ያስለቅሳል ። ግን ለደስታና ለሐዘን የሚፈሰው ዕንባ ኍተሬው አንድ ይሆን? እንጃ ። ይህን ሁሉ ተወና ስለ መሥሪያ ቤቱ ማሰብ ጀመረ ። በበጐ የሚነካ ብዙ ሰው አጣ ፡ የጋሼ ታፈሰን ባሕርይ መመርመር ጀመረ ። የሕይወትን ውጣ ውረድ ያየ ፡ ለችግርና ለብሶት ያልተበገረ፡ ሕይወት የጣለችበትን ዕዳ ሁሉ የከፈለ ። እይ የሕይወት ፈተና! ግራ የተጋባ ፈተና! አሁን እስኪ ማን ይሙት አቀበቱን ሽምጥ ጋልቡ ፡ ዳገቱን ተንደርድራችሁ ውጡ ፡ ቁልቁለቱን እያቀስታችሁ ውረዱ ብሎ ፈተና አለ? የሕይወት ፈተና ፡ የማይታለፍ ፈተና ።

በሩ ሲንኳኳ ብርግግ አለና ተነሣ ። ተቀምጦ ሳይሆን ተኝቶ እንደባነነ ሰው ተንጠራራ አፋሸገ ፡ እጆቹን ግራና ቀኝ ዘርግቶ ወገቡን ሽምድምድ አድርጎ "አ… ፍ" አለና በሩን ከፈተ ። ሐረገወይን ዛማኑኤልና ስንታየሁ ተከታትለው ገቡ ። ብቸኝነት ተጫጭኖአት የነበረችው ቤት በአንዴ ደራች ።

ራት በልተው ሲጨዋወቱ ዓለማየሁ ብቻውን ሲያብሰለስለው

የቆየውን ሐሳብ ለሌሎቹ ለማካፈል ወሰነ ።

"እስኪ አንዳንድ ነገሮች … ብንመካከር ይሻላል ብየ ያሰብኩት አለ" ሁሉም "ምንድን ነው? ምንድን ነው" አሉት የሚለውን ለመስማት መጓጓታቸውን በሚገልጽ ስሜት ፡ ፊዘው ዐይን ዐይኑን ይመለከቱት ጀመር ።

"አዲስ ነገር እንኳ አይደለም … ያው የሐረገወይንና የእኔ ጉዳይ ነው … እንደምታውቁት ችግር እያንዣበበ ነው ፡ ችግሩ ደግሞ ምን ሊያስከትል እንደሚችል መተንበይ ቢያስቸግረኝም ፡ ጥሩ ውጤት እንደማይኖረው ግን አውቃለሁ … "

"ማብራሪያውን ተውና ወደ ቁም ነገሩ ና" አቋረጠው ዛማኑኤል።

"አንተ ደግሞ የአብዬ ደጉ ተረት ካልሆነ ሌላው አይጥምህም?"

ስንታየሁ እንደቀልድ አድርጎ በነገር ጎሸም አደረገው።

"የለም ይኸም ቁም ነገር ነው አዳምጠኝ" ዓለማየሁ ዛማኑኤልን የልመና አመለካከት መልክት አለውና ቀጠለ ፡ "ምን መሰላችሁ ነገሩን አወጣሁት አወረድኩት፡ በእውነት ብዙ አሰብኩበት ፡ ሰዎች ሊነጣጥሉን ይፈልጋሉ ፡ ያለ ፍላጎታችን ፡ ሊለያዩን ይጥራሉ። እነሱ የቻሉትን ሁሉ እያደረጉ ይፈታተኑናል ፡ እኛ ዝም ብለን የምንጠብቅ መስሎ ነው የታየኝ ። ጠላትን ዝም ብሎ መጠበቅ ደግሞ ድክመት ይመስለኛል ። ሽንፈትን አሜን ብሎ መቀበል ይመስለኛል ። ስለዚህም አንድ ነገር ማድረግ አለብን ።"

"ይኸ ደግሞ ፡ ምን እናርግ ፡ የምናረገው ጠፍቶን አይደል እንዴ እንዲህ የምንሰቃየው ?" ሐረገወይን በስጨት አለች ።

"ቆይ እንጂ አስጨርሺው ሐረዬ" አላት ዛማኑኤል። ዓለማየሁ ሦስቱንም በየተራ ተመለከታቸውና ሲጋራ አውጥቶ አቀጣጠለ ። ሁለት ጊዜ አከታትሎ ማገለት ።

"ልንወያይበት እንችላለን…የቤተሰብ ፈቃድ ባይኖርበትም…

ግንኙነታችንን ሕጋዊ አድርገን መቀመጡ ግን ለማናቸውም የሚጠቅም ይመስለኛል…እና እኔ ያሰብኩት ማዘጋጃ ቤት ሔደን ቀለበት ብናደርግስ ? …” ቀለበት የሚለው ቃል ከአፉ ሲወጣ በውስጡ የነበረውን የፍቅር ስሜት ቀስቅሶበት ወጣ ። ሁሉም ዝም አሉ ፤ ሐረገወይንን ስረቅ አደረገና ተመለከታት ፡ የእሷም ዐይን እሱ ላይ ተተክሏል ። ዐይን ለዐይን ተገናኙ። ዐይኗ ለአምስት ዓመት የማያውቀው ዐይን አልመስለው አለው ። ከአምስት ዓመት በፊት መጀመሪያ ሲያያት የወጋው ዐይን መስሎ ታየው ። ለአፍታ ብዙ ቦታ ደርሶ ተመለሰ ። ዐይኑን በዐይኗ ላይ ተክሎ ለማቆየት አልቻለም፡ እንደተቆጡት ሰው ዐይኑን መለስ አደረገው ።

“በጣም ጥሩ ሐሳብ ነው ፡ በእውነት የምንደግፈው ሐሳብ ነው” ዛማኑኤል የሚናገረው ነገር ጠፋው ። ከተቀመጠበት “ግሩም ነው ድንቅ ነው” እያለ ተነሣና ወደ ዓለማየሁ ሔዶ ጉንጩን ሳመው፡ ሐረገወይንን መለስ ብሎ ተመለከታት ፡ አፍራ ስታቀረቅር እቅፍ አድርጎ ሳማትና መልሶ ተቀመጠ ።

“በእውነት ማድረግ የሚኖርብን ነገር ይኸ ብቻ ነው ፡ የቤተሰብ ፈቃድ ያልከው ነገር ግዴለም ፡ ሌላ ጊዜ ይደርሳል ፡ መጀመሪያ መቀመጫዬን ብላለች ዝንጀሮ ። በቃ ፡ በቃ… መቼስ ቀለበት ማድረግ ማለት ያው የመጋባት ያህል ነው ፡ እንዴ ሕጉም እኮ ያግዘናል…መቼስ ማንም ይሁን የሰው ሚስት ሲቀማ ዝም ብሎ አይታይ…አይደለም እንዴ…” የሚያደርገውን አሳጣው ፡ የደስታውን ስሜት በቃላት መግለጽ ያዳገተው ይመስል አለቅጥ ተቁነጠነጠ ። የሰውነቱ እንቅስቃሴ የደስታ ፡ የድጋፍ መሆኑ ግን ያስታውቃል ።

“ቆይ እስኪ ምን ማድረግ ነው የሚኖርብን” አለ ስንታየሁ ። ሐረገወይን ምን ምን መደረግ እንዳለበት ብታውቅም ፡ ለጥያቄው መልስ መስጠትም አልፈለገች ። ዝም አለች ። ዓለማየሁ የእሱን ሐሳብ ለመስማት ፈለገና።

“ሐሬ ምን ይሻላል ትያለሽ?” ብሎ ጠየቃት ።

"እንጃ" አለችና የኮረኮሩአትን ያህል ሣቀች ።

"ስሙ ስሙ" አለ ዛማኑኤል "እንዴ ሐረዬ እኮ አበዛሽው እንዴ ! ሙች የስንታየሁን አልጋም ልቀቂለት፣ እስከ መቼ እሱ አልጋ ላይ ትተኛለሽ ?"

"ሒድ ደረቅ" አለችው ።

"ምን ምን እንደሚደረግ እንጠይቃለን...ጧት አንድኛችን ማዘጋጃ...ቤት ሔደን እንጠይቃለን ፤ እኔ ብዙ ጣጣ ያለበት አይመስለኝም... ለማንኛውም እንጠይቃለን" አለ ዓለማየሁ ቁርጥ ቁርጥ በሚል ድምፅ ። የሐረገወይንን ሐሳብ ማዳመጥ ቢፈልግም ፤ ዝምታዋም ተቃውሞ አለመሆኑን ተረድቶአል ።

"የለም እኔ እንኳ ለማለት የፈለግሁት" አለ ስንታየሁ ጸጉሩን ወደኋላው እየዳጠ ፤ "የማዘጋጃ ቤቱን ጣጣ ሳይሆን እዚሁ እቤታችን ውስጥ ማለቴ ነው ። መቼስ ዝም ብለን አናደርገው ። ባናበዛም ትንሽ ድግስ ቢጤ ማዘጋጀት አለብን ። በቃ ። እና እንዲህ የሚሻል መሰለኝ" አለ ለጉዳዩ ከልቡ የተጨነቀበት በሚመስል አነጋገር ።

"ጥሩ ምን ይመስልሻል ሐረ" አለ ዓለማየሁ ወደ ሐረገወይን እያመለከተ ፤ ሐረገወይን አንገቷን ደፍታለች "እሺ ይሁን" ብላ መለሰች ። አነጋገሯ ከአንገት በላይ የምንቸገረኝነት ስለመሰላቸው ሌሎቹ ደስ አላላቸውም። ስንታየሁ በጉዳዩ ላይ ቀደም ሲልም ብቻውን ሲያስብበት የቆየ በመሆኑ በስፋት እንዲወያዩበት ፈለገ ። እንዲህ በአጭር መቋጨን አልፈለገውም ። የሌሎቹን ስሜት ለመሳብ ለመሞከር የሌለበትን ሳል እንደ መሳል አለና ፤

"እንግዲያውስ እንዲህ እናድርግ...ዛሬ ሐሙስ አይደ ለም ?..."ጠየቃቸው ። ራሳቸውን ደፋ ቀና በማድረግ የአዎንታ መልስ ሰጡት ፤ "እንግዲያውስ ነገ ዓለማየሁ ማዘጋጃ ቤት ሔደህ ሁኔታውን ጠይቅ ። ለሳምንት ቅዳሜ ቢሆን ደስ ይለኛል ። ቅዳሚ ጧት ቀለበት ታደርጋላችሁ ፤ ከሰዓት በኋላ የተወሰኑ ጓደኞቻችንን ጠርተን እንጋብዝ ፤ ነገ አክስቴን ጠርተን ሁኔታውን እናስረዳትና

ድግሱን ትጀምር…እኔ በበኩሌ ሁለት መቶ ሀምሳ ብር ወጪ አደርጋለሁ ። ለድግሱ በቂ ከሆነ ሆነ ፡ ካልሆነ ትጨምራላችሁ በቃ በቅድሚ ትስማማላችሁ።”

“ጥሩ አሥር ቀን አለን ማለት ነው” አለ ዓለማየሁ ወደ ሐረገወይን ዞር ብሎ ። ሐረገወይን ሐሳብ ባሕር ውስጥ ገብታ ትዋኛለች ። አባቷን ፡ እናቷን ሌሎቹንም ዘመዶቿን አስታወሰች ። ፈቃዷን አልፈጽም ብለው ብትቀየማቸውም ፡ እስከ መጨረሻው ልትቆራረጣቸው አትፈልግም ። ዛሬ ብታኮርፍ ነገ ትታረቃለች ፡ ነገ ተመልሳ እናት አባቷ ቤት ትገባለች ፡ ግን የቀለበቱ ጉዳይ እጅግ ከበዳት ። ዓለማየሁን ጠልታ አይደለም ፡ ቀለበት ማድረጓንም ጠልታ አይደለም ፡ ዞሮ ዞሮ ከዓለማየሁ አትርቅም ፡ ቀለበቷም ሠርጓም ከእርሱ ጋር ነው ። ግን ከአባቷ ከእናቷ ፈቃድ ውጭ ፡ እነሱ የሌሉበት ፡ እነሱ ያልመረቁት ፡ እነሱ ያልደገሱት የሚያዛልቅ መስሎ አልታያት አለ ።

የላም በረት ጐረቤቶቻቸው የአንድ ሰሞን ቡና ማጣጫ እንደምትሆን ጠረጠረች ። ይኸ እሷን ብዙም አላስጨነቃት ፡ ግን እንዴት ብላ የአባቷን ዐይን ታያለች። እንዴትስ ብላ ከእናቷ ጋር ትገናኛለች… “ውይ ምነው ልጄ ለፍቼ አሳድጌ ፡ ስመካብሽ እንደ ልጄ ስልሽ ? እንደ ባለጌ ውልቅ ብለሽ ወጥተሽ ወግሽን ማዕረግሽን ሳላይ የሰው መሣቂያ ታደርጊኝ ፡ በስተርጅና በመጦሪያዬ እንዲህ ታዋርጅኝ” ብለው ከፊቷ ሲያነቡ ታያት ። አባቷ እየፎከሩ እየዛቱ “ከጃለሁ ፡ ከጃለሁ ልጅም አይደለች ጅባት ብያለሁ” ብለው ሲምሉ ሲገዘቱ ታሰባት ፡ እንገሸገሻት ።

ደሞ የእንሚልኪያስ ነገር ትውስ አላት ። ራሷን ለማፅናናት ሞከረች ፡ ምንም ቢሆን እኔ የፈለግሁትን እንጂ ሌላ ሰው የፈቀደውን ሊድረኝ አይገባም ፡ አባቴን እናቴን እወዳለሁ ፡ በወላጅነታቸው አከብራለሁ ፡ እፈራቸዋለሁ ፡ ግን የማልፈቅደውን የማልወደውን አድርጊ ሲሉኝ የለም አላደርግም በማለቴ ሊከፉ አይገባም ፡ ባለማድረጌም ተወቃሽ ልሆን አልችልም ። እየየም ሲዳላ

ሆነና እንጂ መች በድብብቆሽ እናደርገው ነበር ፡ በወግ በማዕረግ መዳር ከፈለጉ የምለውን አይሰሙኝም ፡ ድብልቅልቅ አለባት ።

ዓለማየሁ ደሞ ሌላ የሚቀየማት ሰው ነው ። ይወዳታል ፡ ያለ እሷ ሰው የለውም ፡ አስቦ ተጠቦ ማምለጫ ብሎ ያመጣው ዘዴ ነው ቀለበቱ…ደሞም ዛሬ ቢቀር ነገ ፡ ነገ ቢቀር ከነገወዲያ አይቀር ፡ ታዲያ ለማይቀር ነገር ምን ብላ ታስቀይመው…ትይዘው ትጨብጠው ጠፋት ።

ዛማኑኤል አቀርቅራ የምታስብ መሆኗን ተረዳና "ሐርዬ ምንድን ነው የምታስቢው" ብሎ ጮኸና አስደነገጣት ። ከመቀመጫዋ ጀርባ ቆሞ ጉንጮቿን እየደባበሰ ከሐሳቧ ሊያነቃት ፈለገ ። ውስጧን ያውቃል ፡ ጭንቀቷን ይረዳል ፡ እሷም ይህንን ትገነዘባለች። ቀና ብላ ተመለከተችውና ፈገግ አለች ። ከውስጧ የመነጨ ፈገግታ ነበር ፡ ዛማኑኤል ደስ አለው ። በቁንጥ አረማመድ እየተራመደ ተመልሶ ቁጭ አለ ። እንዲህ ዓይነቱን አረማመድ የሚራመደው ትኩረት ለመሳብ ሲፈልግ ብቻ ነው ። ቁጭ እንዳለ በረዥሙ ተነፈሰ ።

"የዛሬዋ ዕለት የማትረሳ ዕለት ነች ። በወረቀት ሳይሆን በልባችን ማስታወሻ እንድንመዘግባት አደራ እላለሁ ። መቼስ በቅዳሚው የተስማማን መሰለኝ ፡ አይደለም እንዴ ዓለማየሁ?" ዓለማየሁ ላይ አፈጠጠበት ።

"ልክ ነው ዛማኑኤል"

"ሐርዬስ ተስማምተሽ የለም "

ሐረገወይን ሣቅ የሚቃጣው ፈገግታ አሳየችና "ተስማምቻለሁ" አለች ።

"ስንታየሁ ?"

እህ እኔማ ባቀረብኩት ሐሳብ እንዴት አልስማማ!"

"ጥሩ እንግዲያ ቀለበቱም ድግሱም ቅዳሜ ይሆናል፡ ስንታየሁ ድግሱን እችላለሁ ብሎአል ። እኔም ለዚህ ቀለበት የማደርገው ነገር

አለኝ" ሁሉም ፈገግ እያሉ ይመለከቱት ጀመር ። "በዓለም ላይ የማልችለውን ነገር አደርግላችሁአለሁ ። ከራሷ ከሕይወት እኩል ለምወዳቸው ሰዎች ማድረግ ያለብኝን አደርግላችሁአለሁ። የማልችለውን ፡ ሞክሬው የማላውቀውን ቅኔ እቀኝላችሁአለሁ ፡ ቅዳሜ በቀለበታችሁ ዕለት ፡ ከዋክብትና ጨረቃ ደምቀው እንደሚታዩበት ልብ እንደሚበላው እንደሚያምረው ምሽት ከሩቅ እየተንቦገቦጋችሁ ስመለከታችሁ ያንየ ድንቅ የሚባል ቅኔ እቀኝላችሁአለሁ ።" ጠረጴዛውን በሁለት እጆቹ መዳፍ ተመርኩዞ ተነሣ ። አንገቱን አስገግና ወደ ፊት ተጠጋ ወደ ሐረገወይን "እህ ትስማማላችሁ?" አለ በሹክሹክታ ድምፅ ።

የሞቀው የሐረገወይን ስሜት ቅዝቅዝ አለ ። በሐሳብ ስትናውዝ ቆይታ ብዙ ከራሷ ጋር ተሟግታ ምናባቱ ፡ "የፈለገው የፈለገውን ይበል" ከሚል መደምደሚያ ላይ እንደደረሰች ፡ ውይይቱን በጋለ ስሜት ስትከታተል ቆየችና ድንገት ቅዝቅዝ አለች። ዐይኖቿ ዕንባ አረገዙ ። ለዛማኑኤል በውስጧ አለቀሰች ። "ወንድሜ ገንዘብ ባይኖረው አይደለም ቅኔ ያለኝ ፡ ገንዘብ ቢኖረው ስንቱን ባደረገ ፡ ድህነቱን ለመሸፈን ብሎ ቅኔ አለ ፡ ማድረግ የሚችለው ባይኖር አቅም ባይኖረው አይደል… ዕንባዋ ማንፍል ብሎ ፈሰሰባት ። ቶሎ ብላ በመሐረቧ ጠረገችው ። ለምን እንዳለቀሰች ግን የተረዳ አልነበረም ።

ጧት ዓለማየሁ ማዘጋጃ ቤት ሔዶ እንዲጠይቅ ስንታየሁ አክስታቸውን ጠርቶ ነገሩን ሊያስረዳ ተስማምተው ሁሉም ወደ መኝታ ክፍላቸው ገቡ ።

ዛማኑኤል ሁሉንም ደኅና እደሩ ብሎ በሩን ከፍቶ ወጣ ። የልማዱን ሊያደርስ ፡ ቤታቸው መግቢያ ላይ ካለች አንዲት አነስተኛ ኪዮስክ የአንድ ብር ጧፍ ገዝቶ ተመለሰ ። መጽሐፉንና ጧፉን ይዞ ተቀመጠ ። ሌሊቱ ለሁሉም መልካም ሌሊት ሆኖ አደረ።

ሐረገወይን በዐሥራ ሁለት ሰዓት ከሥራ እንደተመለሰች ወደ ቤት ትመጣለች ። ቤት እንደደረሰች ጥቂት መቆያ ትጐርስና

እንደተራቸው ዛማኑኤልን ወይም ስንታየሁን አስከትላ ወደ ትምህርት ቤቷ ትሔዳለች ። ዓለማየሁ ተረኛ ከሆነ ፒያሳ ይጠብቃታል ። ከፒያሳ ወደ አራት ኪሎ ፡ ከአራት ኪሎ ወደ ስድስት ኪሎ ይሔዳሉ። እሷ ስትማር ተረኛው እጃቢ በአካባቢው ቆይቶ ዩኒቨርሲቲ በር ላይ ይጠብቃታል ። ከስድስት ኪሎ አራት ኪሎ ፡ ከአራት ኪሎ ፒያሳ ፡ ከፒያሳ ሠንጋተራ ። ታክሲ መጠበቁ ከአንዱ ታክሲ ወደሌላው መገላበጡ ቢሰለችም ሐረገወይንን አጅቦ ማመላለሱን አንዳቸውም አልጠሉት ።

ዐርብ ዕለት ተረኞቹ ዓለማየሁና ስንታየሁ ነበሩ ። ሐረገወይንና ስንታየሁ ቤት ተገናኝተው ጥቂት መቆያ ቀማምሰው ወጡ ። ብዙም አልጠበቁ ፡ ቶሎ ታክሲ አገኙና የፒያሳን አቀበት ተያያዙት። ፒያሳ ከወትሮው ይበልጥ ግርግር በዝቶበታል ። ቁጥር ስፍር የሌለው ሕዝብ ይርመሰመሳል ፡ ከየአቅጣጫው መጥቶ ፒያሳ ደርሶ በተለያየ አቅጣጫ የሚበተነው ሕዝብ ፒያሳን ሰፍሮበት መፈናፈኛ አሳጥቶታል ። ከመሥሪያ ቤት ወደ ትምህርት ቤት ፡ ከትምህርት ቤት ወደ ቤት ፡ ወደ መጠጥ ቤት የሚሔደው ሁሉ ይጋፋል ። ሁሉም እየተጋፋ በመሔድ ከዚያ ግርግር ለመውጣት ይጣደፋል። ህግ እያለ፡ ቸኩሎ እየተጣደፈ ሐሳብ ገብቶት እየተጐተተ ፡ ቀጠሮው አልፎበት እየገሰገሰ ፡ የት ልሒድ ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ያላገኘው እያሰላሰለ ይርመሰመሳል ። ተርታውን ተሰልፈው የቆሙት የፒያሳ ሊስትሮዎች ሰውም አይለዩ ፡ የሁሉንም ጫማ ልጥረግ እያሉ ያስቸግራሉ ። ከረሜላስ ፡ ማስቲካስ ፡ ሲጋራ ያለቀበት ፡ ብለው ከፊት ለፊት የሚጋረጡት ሱቅ በደረቴዎች የፒያሳውን ግርግር ይወዱታል ። ከሰው ኪስ ዘሎ በመግባት የተካኑት ጩልሌዎችማ ሠርግና ምላሻቸው ነው ።

ወዲያ ወዲህ የሚሯሯጡት መኪናዎች ድምፅና ጡሩምባ ፡ ታክሲ ባየ ቁጥር የየሰፈሩን ስም እየጮኸ የሚጠራው ታክሲ ጠባቂ የሱቅ በደረቴው የዕቃ ዝርዝር ፡ የሊስትሮው ጋሽ ልጥረግ ተደማምረው ፒያሳን አብዶች ተሰባስበው ከበሮ የሚደልቁበት የሙዚቃ

መድረክ አስመስለዋታል ።

ሐረገወይንና ስንታየሁ ከታክሲ እንደወረዱ የፒያሳው ግርግር ጠበቃቸው ። ስንታየሁ የታክሲውን ከፈለና የሐረገወይንን እጅ ጭብጥ አድርጎ ይዞ ወደዳር እየጐተተ አወጣት። ከዳር ቆመው ዓለማየሁን በዐይናቸው መማተር ጀመሩ ። ሐረገወይን ጊዜ አልፈጀባትም ፡ ሁልጊዜ ከሚጠብቅበት ቦታ ሲኒማ ኢትዮጵያ ፊት ለፊት ቆሞ አየችው ። "ያው" አለችና በጣቷ አመለከተችው ። ስንታየሁ በዚያ ግርግር መኻል እጇን እንደያዘ ወደ ዓለማየሁ ሔዱ ። ከሩቅ አያቸውና ዓለማየሁም ወደ እነሱ መጣ። ዓለማየሁና ሐረገወይን ከሁለት ሰዓት ለበለጠ ጊዜ ሳይተያዩ ከቆዩ ይነፋፈቃሉ ፡ እንደ አዲስ ተዋዋቂ ፍቅረኛ እንሁን ይላሉ። ግን ይህንን አውጥተው አይገልጡትም ፡ እሱም እሷም በውስጣቸው ያፍኑትና በዓይናቸው ብቻ ይገልጡታል ።

"እንዴ ልቀቃት እንጂ የላምበረት ሰዎች ካዩአችሁ የአቶ ወንዲራድ ልጅ ፒያሳ ላይ በፖሊስ ተይዛ ስትሔድ አየናት ብለው ነው የሚያወሩባት" አለ ዓለማየሁ ገና እንደተገናኙ ፡ ሐረገወይን ፡

"ውይ ውይ ምን ባልኩህ" አለች በዐይኗ እየገላመጠችውና የአጭር ጊዜ ናፍቆቷን እየተወጣች ።

የፒያሳ አራት ኪሎ ታክሲ እልህ ያስጨርሳል ፡ ብዙ አስጠበቃቸው ። ሽምግል ያሉ ሰው ተሳፋሪዎቻቸውን ሁሉ እያስደሰቱ፥ እያሣቁ የሚሔዱ ክርክስ ያለች ታክሲ ይዘው መጡ ። ስንታየሁ ተጋፍቶ የኋላ በሩን ያዘና ዓለማየሁንና ሐረገወይንን አስገባቸው። "ለወጣቶች የምትገባ ታክሲ ናት ፡ አይደለችም እንዴ ልጆቼ !" አሉ ባለታክሲው እነ ዓለማየሁ ገብተው በሩን እንደዘጉ። ሁሉም በልባቸው ሣቁባቸው ። ታክሲዋ ስትሔድ ስትንቋቋ እያደረሰ ፡ በርበሬ በርበሬ ትሸታለች ። መርካቶ የሚሸጡ ቅመማ ቅመሞች ለዓይነት የተነሰነሰባት ትመስላለች ፡ ቁሽሽ ያለች ናት ። አሽከርካሪው ሽማግሌ ከፊት ለፊቱ ወንበር የተቀመጡትን ዘመናዊ ባልቴት በወሬ ይዘዋቸዋል ። ባልቴቷ በመነፅራቸው ውስጥ አሾልቀው

እየተመለከቱ ፈገግ ይላሉ ። ጥርሳቸውን ሙሉ በሙሉ አያሳዩም ። የጨዋ ጣት የሚባለው ዓይነት ሁለት ምስት ጥርሶቻቸውን ብልጭ ያደርጉና አሻግረው ወደ ውጭ ይመለከታሉ ።

ዓለማየሁ ጧት ማዘጋጃ ቤት ሔዶ ቀጠሮ ማስያዙን በምሳ ሰዓት የነገራቸው ቢሆንም ፡ አሁንም ጉዳዩን በዝርዝር ያጫውታቸዋል ። በምሳ ሰዓት ቤት ውስጥ ካልተገኘው ከህማንኤል በቀር ስንታየሁም ፡ ሐረገወይንም ዓለማየሁ ቀለበቱን ትዳሚ ልክ በአምስት ሰዓት አስቀጥሮ መምጣቱን አውቀዋል ። አሁን ደግሞ አዲስ ሆኖባቸው ያዳምጡታል። ያች ከርካሳ ታክሲ [illegible] እግዳሚውን ጆሮ እያደነቆረች ፡ እየተንኳኳች በአሳር አራት ኪሎ ደረሰች። አራት ኪሎ ባንክ ፊት ለፊት ወረዱ ።

"ወንዴ ፡ የሳቱ ላንቃ ፡ እም...የሳቱ ላንቃ ፡ ግራ አሳይቶ ቀኝ እሚማታ ፡ አንድ ብቻውን ለሺ እሚበቃ ፡ ወንዴ የሳቱ ላንቃ ፡ እም..." ቀብራራው እንደ አንበሳ እያገሳ ፡ እየነጠረ ዐይኑን እያጉረጠረጠ አላፊ አግዳሚውን ያስፈራራል ።

ሐረገወይን ወደ እሷ እየነጠረ ሲመጣባት ዘለለችና የስንታየሁን ወገብ ያዘች ። ቀብራራው ፖሊስ ይፈራል ። ስንታየሁን ከእግር እስከ ራሱ የጎሪጥ ተመለከተና ወደ ሌላ ዞር አለ ።

"ወንዴ የእሳቱ ላንቃ ጉሮሮ ላይ ቆም አፈር የሚያስበላ ሀ. ሀ. ሀ." እያጉረጠረጠ መንገዱን ተሻገረ ። አረማመዱ ያስፈራል ። አንገቱን መዞ ወደ ኋላው ለጠጥ ብሎ እጆቹን ለቀቅ አዘጋጅቶ ይንጥራል ። የሚያውቁት "ደግሞ ተነሣበት ይኸ ቀውስ" ይሉታል ፡ አይፈሩትም ። የማያውቁት ከሩቅ ይሸሹታል ። መንገዱን ተሻገረና አውቶቡስ ማቆሚያው ፊት ለፊት ቆሞ አውቶቡስና ታክሲ በሚጠብቁት ላይ አፈጠጠባቸው ። "እም ---እም ---የሳቱ ላንቃ" ብዙዎቹ ሸሹት ። አንድ ድሪቶ የለበሰ እግሩን እስከ ጉልበቱ ድረስ በአሮጌ ጨርቅ የጠመጠመ ሰካራም ከኋላው ደረሰና ፡

"ባሻዬ ቤት ምን ብለህ ነው የሰደብከኝ አሁን ላንጉንህ" አለው ። እሱም ዐይኑን እያጉረጠረጠና የጠጅ ትንፋሹን በኃይል እየተነፈሰ።

ቀብራራው ደረቱን ንፍት አድርጎ ፣ አንገቱን ወደ ላይ መዘዘና በሁለት እጁ ሰካራሙ አንገት ላይ ተጠመጠመበት ።

ግብግብ ተጀመረ ። የአራት ኪሎ ውሪዎች ከበው "እይዞህ በለው...ወፈፌው አይዞህ ፣ ይህን ጥጋበኛ በለው" ይጮሀሉ ። ቀብራራው በኃይል ተንጠራራና በዚያ መጅ እጁ የወፈፌውን ጭንቅላት አቀመሰው ። ወፈፌው ተንገዳገደ ። ቀብራራው መልሶ ተንጠራራና ደገመው ። ወፈፌው እንደ ዛፍ ተገንደስና ተዘረረ ።

"የት አባክ እኔ ቀብራራው...እም" ወፈፌው ያለከልካል ፣ ዐይኖቹን ስልምልም እያደረገ አላፊ አግዳሚውን ይማፀናል ። ቀብራራው የሚንጥርበትን እግሩን አንሣና ወፈፌው ሆድ ላይ ጫነበት "እ...እ" አለ ወፈፌው ። ደሞ ጫን አለው ። ሌላውንም እግሩን አንሣና በሁለት እግሩ ቆመበት ። ወፈፌው መቆጣጠር አቃተው ። የበላውም የጠጣውም ሁሉ ወጣበት ። የተሰበሰበው ወሬ አዳናቂ ሁሉ "እፍ እፍ" እያለ አፍንጫውን እየያዘ ሸሸ ።

ወዲያው አረጋሽ እብዲቱ ብቅ አለች ። ራሷ ላይ የተሸከመችው ኮተት ብዙ ነው ፣ ብዙ ቀለም ያላቸው የተቆራረጡ ጨርቆች ፣ የሲጃራ መጠቅለያ ወረቀት ፣ የጋዜጣ ቁርጥራጭ ፣ የዶሮ ላባዎች ፣ የተሸነቋቆረና ብል የበላው ሳህን ። ይህን ሁሉ በአንድ ሰፊ ሻሽ ጠቅልላ ራሷ ላይ አስረዋለች ። በእጇ ማሳና አጭር ዱላ ይዛለች ። ዙሪያዋን አምስት ውሾች ከበዋታል ። ውሾቹ ከእርሷ ጋር ሲዞሩ ውለው ማታ አብረዋት ቤታቸው ይገባሉ ። ቤታቸው እሪ በከንቱ ድልድይ ጐን ነው ። ድንጋይ ተከምሮ የተሠራ ቤት ። ድንጋዩ ክምር እናት ላይ የላውንደሪ ላስቲክ ተዘርግቷል ፣ በየሦስት ቀኑ ይቀደዳል፣ አረጋሽ ወዲያ ወዲህ ሩጣ ትለውጠዋለች ። የቤቱ ክዳን ቆርቆሮ መሆኑ ነው ። ውሾቹ ከፊት ከኋላዋና ከጐኗ አጅበዋት ይጓዛሉ ። ማንም ሰው ደፍሮ አይጠጋትም ። በያዘችው አጭር ዱላ ያንን ማሳ ትደበድበዋለች ፣ ያን ጊዜ ውሾቹ መሯሯጥ ያበዛሉ ። ማታ ማታ ወደ

ቤታቸው ሲሄዱ በየልኳንዳ ቤቱ እየገባች ለውሾቹ ራት ትለምንላቸዋለች ። ሰው አያፌክንባትም ፡ ሁሉም ይሰጡአታል። ውሾቹ ጠግበው ያድራሉ ። በጣም ይወዱአታል ፡ ይንከባከቡአታል። የሚያውቃት ሰው ሁሉ "አረጋሽ እብዲቱ እንኳ ከሰው ልጅ የውሻ ልጅ ማሳደግ ይበልጣል ብላለች" እያለ ይተርትባታል ። እሷ ግን ውሻ አስከትላ ብትውል ፡ ብታድርም ከሰው ልጅ ውሻን አታስበልጥም ።

በውሾቹ ታጅባ ከባሻ ወልዴ ችሎት በኩል ብቅ አለችና ዋናው መንገድ ስትደርስ ቆም አለች ። ጣሳዋን እየደበደበች የሰፈሩን ጸጥታ አደፈረሰችና መንገዱን ተሻገረች ። ተሻግራ የዋናውን መንገድ ጠርዝ ይዛ ቆመች ፡ መለፍለፍ ጀመረች ፡ ጣሳዋን እየደበደበች ። እሷ ስትቆም ውሾቹ ዙሪያዋን ከበው በርከክ በርከክ ብለው እያለከለኩ አንጋጠው ይመለከቱአታል ። "እስቲ አባክ ፡ እስቲ አባክ ...አንተ ወለወልዳ..." አለች ጣሳዋን መደብደቧን አቋረጠችና ። ባጠገቡዋ ያልፉ የነበሩ የማያውቋት ሽማግሌ ነገሩ ግራ ቢገባቸው የለበሱትን ጋቢ ጠቅለል አደረጉና ውሃ የሚያስኝ ዱላቸውን ለመሰንዘር አዘጋጅተው ፈንጠር ብለው ተራመዱ ፡ ወደ ኋላ ገልመጥ አድርገው ተመለከቱአት ። "እስቲ አባክ አንት ወለወልዳ...የቅራሪ ልጅ ባይሹሉብሽ ነው እምላኝህ..." ሽማግሌው ቆም አሉና ፡

"ጤና የለሽም እንዴ...በመንግሥት አገር ምን አርግ ነው እምትይኝ?" አፈጠጡባት ጠጋ አሉና ። በርከክ ብለው የቆዩት ውሾች ተነሡና በሽማግሌው ላይ ጮሁባቸው ፡ ዙሪያውን አዋከቡአቸው ። ጉዳዩ የገባው አንድ የአራት ኪሎ ዱርየ ልቡ እስኪፈርስ ሣቀና ሽማግሌውን እየጐተተ ወሰዳቸው ። አረጋሽ ቀጠለች ንዝንዟን ።

"አንት ወለወልዳ ···በል በል እስኪ ንክች አድርገኝ ···ያን ጊዜ ሆዴ ውስጥ ገብስ ዘርተህ ግማሹን በቆሎ ዘርተህ እኔ ደሞ ሽንቴን እያጠጣሁ አሳድጌልህ ፡ ሲደርስልህ እንዲትም በቆሎ ሳታቀምሰኝ አልሄድክም···ወለወልዳ ፡ ባይበሉብሽ ነው እምላኝህ

…ሌባ የሌባ ልጅ… ያውም ሆዴ ውስጥ ገብስህን ስታጭድ ኩላሊቴንና ወተት እንጀቴን አብረህ አጭደህ አልወሰድክብኝም… ወለወልዴ …ኪኪኪኪ…ኪኪኪኪ…ቶይ ቶይ ባልሠራልህ …ቶይ እኔ እያደለሁም የምትሳፈርበትን መኪና ገደል ባልጨምረው…እይ ዋኝ …ዋኝ እኔ ነኝ ?… አባይ ይመስክር! አባይ ይመስክር! አንተ ወለወልዴ" ድንገት ብርግግ አለችና ጣሳዋን እየደበደበች መንገዱን ተሻግራ ቁልቁለቱን ተንደረደረች ። ክፋቱ የጣሳዋ ጩኸት እየተሰማ ተሰወረች ።

ሐረገወይን የቀብራራውንና የአረጋሽ እብዴቱን ሁኔታ ስትከታተል ቆየችና መለስ ስትል ያልጠበቀችውን ነገር ተመለከተች ። ግርም አላት ። ዐይኗን ማመን አልቻለችም ። የተዘበራረቀ ሐሳብ ለአፍታ አዕምሮዋን ረበሸው ፣ እግሯን ብርክ ያዘው ። ለጥቂት ጊዜ ፈዛ ቆየችና "…አዎ…አዎ" ብላ ጮኸች ። ስንታየሁና ዓለማየሁ አጠገብዋ ቢኖሩም አላዳመጡአትም ። የእነሱም ዐይንና አዕምሮ በአራት ኪሎው ትዕይንት ተመስጦአል ። ሐረገወይን የስንታየሁንና የዓለማየሁን እጆች ያዘችና ጐተተቻቸው ። እጆቿ ይንቀጠቀጣሉ ፣ አንዳች ነገር የገጠማት መስሎ ታያቸው ።

"ምነው ምንሆንሽ?" አለ ዓለማየሁ እሱም ግራ ተጋብቶ ።

"ያ…ቻት…ያ…ቻት…ያቺ ሌ…ባ ያቻት"

"ማ…ማናት" ዓለማየሁ የሚያደርገው ጠፋው ። ስንታየሁ የሚይዘውንና የሚጨብጠውን እንዳጣ ሰው ዙሪያውን ይቃኛል ። ከሐረገወይን ገጽታ የሚያነበው የድንጋጤ ፣ የፍራቻና የድረሱልኝ ምልክት ግራ አጋባው ።

"እኮ ማን ናት ንገሪኝ እንጂ" ጮኸ ። ሐረገወይን ቶሎ መልስ አልሰጠችውም ። ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ ይላል ። የፊቷ ቀለም እየተለወጠ ፍም እየመሰለ ሔደ ፣ በውስጧ የሚቀጣጠለው የንዴትና የበቀል ስሜት ገንፍሎ ብረረ ብረረ እያለ ይገፋታል ።

"ያ…ችው ፣ ያችው ያች ሌባ" አሁንም ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ ይላል ።

"እኮ የቷ ፡ የቷ ናት ንገሪኝ እንጂ!"

ሐረገወይን የወረራትን የድንጋጤ ፡ የቁጣና የበቀል ስሜት ለመቆጣጠር ሞከረች ። በግንባሯና በጸጉሯ መኻል ችፍ ብሎ ቁልቁል ለመወርወር የተዘጋጀውን የላብ ነጠብጣብ በመሐረቧ ጠራረገች ። በረዥሙ ተነፈሰችና ወገቧን በሁለቱም እጆቿ ጥብቅ አድርጋ ያዘች ። ከመንገዱ ባሻገር ከተሰበሰቡት ሰዎች ላይ ዐይኗን እንደተከለች ናት ።

"አዎ ፡ ራሷ… ራሷ ናት ፡ ይች ሌባ ፡ ራሷ… ያች… ያች ራንግለር ሱሪ የለበሰችው ፡ እኛን እያሞጠሞጠች የምታወራው ራሷ ናት ። ይች ሌባ፡ በእሷ ቤትማ የማትገኝ መስሎአት ፡ በእሷ ቤትማ ብልጥ እሷ ብቻ"… መለስ ብሎላት የነበረው የቁጣ ስሜት መልሶ ወረራት ። በውስጧ እየተብላላ የሚደለቀው የበቀል ስሜት መሬትን ፈንቅሎ እንደሚወጣ እሳተ ገሞራ ተናንቃት ። ዓለማየሁና ስንታየሁ የሚያደርጉት ጠፍቶአቸው ተፋጠው ቆመዋል ። "መላ አምጣ እንጂ ምን ዝም ትላለህ" የሚባባሉ ይመስላል ።

ከመንገዱ ባሻገር በአውቶቡስ መጠበቂያው ፊትለፊት ብዙ ሰዎች ተሰባስበዋል ። ጥንድ ጥንድ ሆነው የሚያወሩ ፡ ብቻቸውን ፈዘው የቆሙ ፡ የሚሟሟቁ ፡ የተከዙ ፡ የመደነቅ አስተያየት የሚያዩ አሉባቸው ። አስቴር ራንግለር ሱሪ ታጥቃ ፡ እጀ ጉርድ ጃኬት አጥልቃ ከደረቷ ላይ ልጥፍ ያለች አነስተኛ ቦርሳ አንገቷ ላይ አንጠልጥላ አብራት ካለችው ሹርባ ከተሠራች ኮረዳ ጋር እያወሩ ይሟሟቃሉ ። ከፊት ለፊታቸው አንድ አጭር ሰው በፈጣን እርምጃ ይጓዛል ። እሱን እያዩ ይሥቃሉ ። የሰውዬው አረማመድ እውነትም ያሥቃል። ከልቡ ይገሰግሳል ፡ ሰውዬው አጭር መባልም የሚበዛበት ነው ፡ ክርክም ያለ ድንክ ነው ። ልብ ብሎ ለተመለከተው የሚራመድ ሰው ሳይሆን የሚንከባለል ጉርድ በርሚል ይመስላል ።

"አይገርምሽም በናትሽ ? እስኪ የእሳት አደጋ አልመጣበት እንደ ወፍጮ ቤት በግ እያለከለከ እንደ ኩሽኔታ የሚያሽከረክረው ምንድን ነው? አይገርምሽም በናትሽ ? ኧረ በየሰፈሩ ስንት ጉድ አለ?

ሆዬ ጉድ አይገርምሽም በናትሽ ?" አለች እስቴር ሰውየውን ትኩር ብላ ተመልክታ ሥቃ ሥቃ እንደጨረሰች ።

"የማራቶን ልምምድ ይኖርበታል እባክሽ" አለች ጓደኛዋ የጀመረችውን ሣቅ ስትጨርስ ።

"ኤሜ ደሞ እሱ ብሎ የማራቶን ሯጭ ፣ ከአፍ የወደቀ ጥሬ የሚያህል"

"ተይ እባክሽ እንዲህ አትበይ ፣ የምትወደው ትኖራለች ልጄ"

"ውይ …ድንቄም ኪ…ኪ.ኪ.ኪ." እስቴር ከልቧ ሣቀች ።

"አሁንስ በሰውየው አይመስለኝም የሣቅሽው እስቴር…ሙች ሙች በሰውየው አይመስለኝም ሚኪ ነፍስ ነገር ትዝ ብሎሽ ነው አይደል?"

"አይገርምሽም በናትሽ አሁን ያለፈችው መኪና የእሱ መስላኝ ወይኔ ሲንከራተት አላየሽም ። ውይ ሚኪ…" የጀመረችውን አልጨረሰችም ፣ ከኋላዋ ትከሻዋን ጐተት ያደረገውን ሰው ለማየት ዞር አለች ፣ ድንግጥ አለች ። ሐረገወይን ፊቷ ላይ የሚነበበው ገጽታ ያስፈራል ። እስቴር ዞር ስትል በሁለት እጆቿ አንገቷን ጨመደደቻት ።

"እንቺ ሌባ …እንቺ ሌባ…" ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ ይላል የሐረገወይን ። በአካባቢው የነበረው ሰው ሁሉ ነገሩ ገርሞት ከቦ ይመለከታቸው ጀመር ። ሐረገወይን እየሮጠች መንገዱን ስታቋርጥ ተገርመው ይመለከቷት የነበሩት ዓለማየሁና ስንታየሁ የእስቴርን አንገት ማነቋን ሲመለከቱ እየሮጡ መንገዱን አቋርጠው ደረሱላት።

"ልቀቂኝ ብየሻለሁ ኋላ ጉድ ይፈላል ልቀቂኝ" ትጮኻለች እስቴር ።

"አልለቅሽም ፣ በድለሽኛል ጣቢያ ድረስ እንሒድ"

"ታዲያ ልቀቂኛ ፣ አንገቴን ልቀቂኝ"

"አለትሽም ፡ አልለትሽም ብየሻለሁ"

"የት ታውቂኛለሽ ፡ ልትዘርፊኝ ነው ? በሕግ ልቀቂኝ"

ከተሰበሰቡት ሰዎች መኻል ብዙዎቹ የሁለቱን ጠብ በምንቸገረኝነት ይመለከታሉ ። የአራት ኪሎ ውሪዎች ዙሪያውን ከበው "አስፋ…አስፋ" እያሉ ይቀልዳሉ ። ስንታየሁ እንደደረሰ ሰዉን ሁሉ እየገፈተረ አለፈና ፡

"ምንድነው ምንድን ነው?" ብሎ ጮኸ ፡ የሐረገወይንን ትከሻ እየጨበጠ ። አስቴር ትኩር ብላ ተመለከተችው ። ገጽታው ላይ የግራ መጋባትና የቁጣ ቅልቅል ስሜት የሚነበብበት ነው ። ስታየው ፈራችው ፡ የመሸነፍ ፡ የመጋለጥ ፡ የተስፋ መቁረጥ ሐሳብ ወረራት ። ግን በቀላሉ እጇን ለመስጠት አልፈለገችም ። ስንታየሁ መለዮውን አድርጎ ነገሩ ውስጥ ሲገባ የተሰበሰበው ሰው ገለል ገለል ማለት ጀመረ ። ዓለማየሁ ከጀርባ ቆሞ ግር ብሎት ይመለከታል ።

"እባክህ አስለቅቀኝ ፡ ቦርሳየን ለመቀማት ነው መሰል! የየት አራዳ የቤት ሌባ ናት? አይገርምም ፡ አይቻት አላውቅም ፡ ዘሎ የሰው አንገት ማነቅ አለ እንዴ? እባክህ መቶ አለቃ አስለቅቀኝ" አለች አስቴር አይኖቿን እያቁለጨለጨች ። ልመናዋ የተመልካችን ልብ ይበላል ። የፊቷ ገጽታና ፡ አንገቷን ሰበር አድርጋ በአስጥሉኝ ድምፅ የተናገረችው የተበደለች አስመሰላት ። የሐረገወይን ቁጣ ቀስ በቀስ እየበረደ፡ እራሷን እየተቆጣጠረችና አካባቢዋን እየፈራች ሄደች ። ስንታየሁና ዓለማየሁ ከጐኗ በመቆማቸው አልተደናገጠችም ፡ የአሸናፊነት ልበ ሙሉነት ተሰማት ።

"ያች በዱርየ ልታስደበድበኝ የነበረችው ፤ ከመሥሪያ ቤት በር ላይ ጠብቃ የሰደበችኝና የዛተችብኝ ናት ጣቢያ አድርሺኝ" አለች ዐይኖቿን ስንታየሁ ዐይኖች ላይ ትክል አድርጋ ። ስንታየሁ አስቴርን ትኩር ብሎ ተመለከታት ፡ ወደ ኋላው ዞር አለና ዓለማየሁን ተመለከተው ። ዓለማየሁም እንደ እርሱው ተገርሞ አስቴርን አፍጦ ይመለከታል ። ዙሪያውን ከቦ የቆመው ሰው ፡

"በቃ ወደ ጣቢያ መውሰድ ነው ።"

“እዚሁ ገላግዷቸው”

“ይኸን ጊዜ ተቀማምተው ይሆናል”

“አይ የዘመኑ ልጆች…ዐይናውጣዎች” እንደ መሰለው ይናገራል ።

“እሺ ወደ ማቢያ እንሒዳ” አለ ስንታየሁ ኮስተር ብሎ አስቴርን እየተመለከተ ።

አስቴር የምታደርገው ጠፋት ፤ አዕምሮዋ ተምታታባት ። ወደ ጓደኛዋ ዞር አለች ። ዐይኖቿ በተስፋ መቁረጥ ይቅበዘበዛሉ ። “አይገርምሽም በናትሽ…ወደ ማቢያ ሒጂ ነው እኮ እሚሉኝ” አለች ። ጓደኛዋ መልስ አልሰጠቻትም ። ዙሪያዋን ማተረችና ሹልክ ብላ ጠፋች ።

“ስሚ እንሒድ እኮ ነው የምልሽ” ስንታየሁ ቆጣ አለ አሁንም ።

“እንዴ ወዴት ነው የምሔደው”

“ፖሊስ ማቢያ እንሔዳለን ፤ አፈልግሻለሁ” ሐረገወይንም ቆጣ አለች ።

“ምን አጠፋሁ እና ነው የምሔደው” አስቴር ሐረገወይን ላይ አፈጠጠች ።

“የሠራሽውንማ ታውቂያታለሽ ፤ ልትከጂ ነው”

“እንደውም አልሔድም መጥሪያ አምጭና ነው የምሔደው”

ስንታየሁ ብልጭ አለበት ። የተለያዩ ሐሳቦች ዙሪያውን ከበው አስጨነቁት ። አስቴርን ጉሮሮዋን አንቆ እየጐተተ ወደ ማቢያ የመውሰድ ሐሳብ ለአፍታ ብልጭ አለና ወዲያው ጠፋለት ። ይኸኛውን መንገድ አልወደደውም ። ከበዋቸው የቆሙት ሰዎች የየግል ሥራቸውን ዘንግተው ነገር ያዳንቃሉ ። ግማሾቹ መጨረሻውን እንይ ብለው ዝም ብለው የቆሙ ናቸው ፤ ግማሾቹ የተሰማቸውን ሁሉ ይሰነዝራሉ ።

“ፖሊስ አለ አይደለም እንዴ ፤ እንሒድ ሲልሽ ለምን

አትሒጂም ”

“ዝም ብሎ ከመንገድ ሰው ማነቅ አለ እንዴ… ሆዴ ጉድ”

“ይኸን ጊዜ የሴት ሌባ ትሆናለች”

“እየገፈተረ አይወስዳትም እንዴ ?” ሌላም ሌላም ይነገራል ።

ስንታየሁ የከበቡትን ሰዎች ሐሳብ ሲያዳምጥ ቆየና ፡

“በያ እንሒድ ላድርሳችሁና የምትይውን እዛው ትያለሽ ፡ ጥፋት ከሌለብሽ ትለቀቂያለሽ ፡ አሁን ጊዜያችንን አትፍጂብን እንሒድ” አለ ። አስቴር መከራከሩ የሚያዋጣት መስሎ አልታያትም ። ፖሊስ ጣቢያ ሔዳ ከሚደርስባት ችግር ይልቅ የከበባትን ሰው ዐይን ፈራች ፡ ሰውነቷ ተንቀጠቀጠ ። አዕምሮዋ ተረበሸ ፡ ላብ ላብ አላት ።

“እሺ እስኪ እምሆነውን እያለሁ ፡ እንሒድ”አለች የከበቡአቸውን ሰዎች እየገፋችና ከመኻል ለመውጣት እየታገለች ። ስንታየሁ ክንዷን ያዝ አደረገና ተከተላት ። ዓላማየሁና ሐረገወይን አጀቡአቸው ። ከሳሽና ተከሳሽ ሳይሆን አብሮ አደግ ጓደኞች መስለው ወደ ሁለተኛ ጣቢያ ጉዞ ጀመሩ ። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤትን አልፍ እንዳሉ አስቴር ቀና ብላ ስንታየሁን ተመለከተችው ።

ዐይኖቿ ልመና ያሙቁበታል ፡ ድንገት ሲወነጨፉ ያፈዙና ያነሆልላሉ ። አንድ ጊዜ ወግተው መለስ ሲሉ ወንድ ልብ ውስጥ እሳት ይጭራሉ ፡ ዛሬ ግን አልሆኑላቸውም ። የስንታየሁ ዐይን ጋሻ እየሆን መለሳቸው ። አስቴር ቁርጧን አወቀችና “እሺ ልቀቀኝ እራሴ እሔዳለሁ” አለች እየተመናጨቀች ፡ ለቀቃት ። ሦስቱ አጅበዋት ሁለተኛ ጣቢያ ደረሱ ።

ሁለተኛ ጣቢያ የወትሮው ግርግር ዛሬም አልለቀቀውም ። መጠጥ ቤት የተፈራከሰው ፡ ሲሰርቅ የተያዘው ፡ ገንዘብ ተበድሮ ያልመለሰው ፡ ጠግቦ ሰው የተሳደበው ፡ ወፈፌው ሁሉም ተሰባስቧል ። ይተራመሳል ። ስንታየሁ ዓለማየሁን በዐይኑ ጠቀሰና ወደ ጣቢያው አዛዥ ቢሮ ገባ ። ጥቂት ቆየና ተመልሶ ወጥቶ ሻለቃ ባሻ

አላምረው ቢሮ ገባ ። የሻለቃ ባሻ አላምረው ቢሮ በሰዎች ተጣባለች። ዓለማየሁ እስቴርን አፍጦ ይጠብቃል ። ሐረገወይን ትቁነጠነጣለች ፡ ሦስቴም ተፋጠው ቆመዋል ። እስቴር ከትንሿ ቦርሳዋ መሐረብ አወጣችና ግንባሯን ፡ አፍንጫዋንና ፡ የደረቀውን ከንፈሯን አባበሰችና መልሳ አስገባች ። የጣቢያውን በረንዳ እንጨት ተመረኮዘችና ሐሳብ ውስጥ ገባች ። አሁን ምን ሲሉኝ ምን ብየ ነው የምመልሰው ፡ አላውቅም ብየ ድርቅ ማለት ነው ፡ የፈለገው ይሁን አላውቅም እኔ አይደለሁም ብየ ድርቅ እላለሁ ።… ውይ በምን አባቱ ቀን ነው ከዚህ ሰውየ ጋር ያገናኘኝ ። ወፈፌ አሀያ… እረ ጦሱን እዚያው… የእሱ ብር ቢቀርብኝስ ፡ ስንት ስንት የሚሠራ ሞልቶ እዚህ ጣጣ ውስጥ በምን አባቴንስ ገባሁ… እረ ጦሴን ይውሰድ… ያ ግም ሰላቶ ነው እደል እንዲህ ያደረገኝ….

“እሺ እንት ወደ ውስጥ …ግቢ” አላት አንድ ፖሊስ ። ድንግጥ ብላ ዞር አለች ። “ወደ ውስጥ ግቢ…” በጣቱ የአላምረውን ቢሮ አመለከታት ፡ ቀስ እያለች ገባች ፡ ዓለማየሁና ሐረገወይን ተከተሏት። አላምረው ዓለማየሁንና ሐረገወይንን ትኩር ብሎ ተመለከታቸው ።

“እሺ የት አግኝታሽ ነው የሰበደበችሽ ምን ብላ ነው ያስፈራራችሽ” አለ ወደ ሐረገወይን ዞሮ ።

“መሥሪያ ቤቱ በር ላይ ነው ። በሰባት ሰዓት ወጥቼ ወደ ቤት ስሔድ በሩ ላይ ጠብቃ ሰደበችኝ ፡ ያስረገዘችን ቦይፍሬንዴን ቀምተሽኛል… ባትለቂው ግንባርሽን ነው የምልሽ ብላ አስፈራርታኛለች ፡ ደሞ ሁለት ዱርየዎች አምጥታ ይች ናት ብላ አሳይታቸው እነሱም ሰድበውኛል አስፈራርተውኛል ። አምሳ አለቃ እኔ ያለ ዓለማየሁ የማውቀውም ወንድ የለኝ ፡ የእሷንም አልቀማሁ ፡ የተላከችበት ካለ ትንገረኝ…” ሐረገወይን ዕንባዋ ቀደማት ።

አላምረው ካቀረቀረበት ቀና አለና ፡

“እሽ ምን መልስ ትሰጫለሽ ለምንድነው የተሳደብሽው”

ብሎ አፋጠጣት አስቴርን ። አስቴር አቀረቀረችና ዝም አለች ።

"እንቺን እኮ ነው አትናገርም እንዴ?"

"ውሸት ነው ፡ እኔ ያለዛሬም አይቻት አላውቅ ውሸት ነው"

"ብዙ ምስክር አለኝ ድፍን የመሥሪያ ቤቱ ሰው ይመስክራል" አለች ሐረገወይን ፡ አስቴር መንቀጥቀጥ ጀመረች ። የሚያዋጣትን መልስ ለመስጠት ብዙ አሰበች ፡ ግን ድፍንፍን አለባት ።

"እውነቱን ብትናገሪ ይሻልሻል ፡ ኋላ አሳር ይገጥምሻል"

"እንዴ ምን ይገጥመኛል ውነቱን ተናግሬአለሁ"

"እሺ እሱን ተይው… ስምሽ ማነው?"

"አስቴር"

"አስቴር ማ"

"አስቴር ዳኛቸው"

"ማ"

"አስቴር ዳኛቸው" – አላምረው አንድ ነገር ጭንቅላቱን ጠቅ አደረገው ።

"ሥራሽ ምንድን ነው"

አስቴር አቀርቅራ ቆየችና ቀና አለች ።

"ሥራሽ ምንድን ነው?"

"አይ …ሥራ የለኝም…እምልህ ሥራ እየፈለግሁ ነው"

"እየዞርሽ ሰው ማጣላት አይደል ሥራሽ በገንዘብ እየተገዛሽ" ስንታየሁ አፈጠጠ ።

"ኧረ በናትህ እንደዚህ አትበል ፡ እኔ በሰውም እጠላዋለሁ እንዲህ ዓይነቱን ሥራ ።"

አላምረው ከጀርባው ያለውን መጥሪያ ተጫነና አንድ ፖሊስ ጠራ ።

"እስኪ በግንቦት ወር የደረሰንን የቤት ዘራፊዎች ፋይል አምጣልኝ" ብሎ አዘዘው ። ፖሊሲ እየተጣደፈ ወጣ ፡ አስቴር ግራ ተጋባች ፡ ማልቀስም ፈለገች ፡ ግን አያዋጣትም ። እውነቱን ተናግሬ ይውጣልኝ ብላ አሰበች ፡ ይኸም አስፈራት ። የታዘዘው ፖሊስ አንድ አረንጓዴ ክላሰር ይዞ መጣና ለአላምረው አቀበለው ። አላምረው ክላሰሩን ሲያገላብጥ ቆየና ቀና አለ ፡ የጠፋ ዕቃ ያገኘ ያህል ደስ ብሎታል ።

"እሺ አስቴር ዳኛቸው ሥራ የለኝም ነው ያልሽኝ"

"አዎ ሥራ የልኝም"

"ሉዚ በቀለን ፡ ማርታ ሲራክን ታውቂያቸዋለሽ?"
አስቴር አቀረቀረችና ዝም አለች ።

"ታውቃያቸዋለሽ አታውቂያቸውም" የአላምረው ድምፅ ያስፈራራል ።

"ዱሮ ጓደኞቼ ነበሩ አሁን ግን …"

"አሁን ግን ምን …"

"እምልህ ከእነሱ ጋር አልገጥምም ፡ የት እንዳሉም አላውቅ"

"እሺ እቴጌ ሆቴል አንድ ኢጣሊያዊ ቱሪስት አታላችሁ አራት መቶ ዶላር ሰርቃችሁ ፡ ከሦስት ቀን በኋላ አልተያዛችሁም? አንድ አንድ ወር ታስራችሁ አልተፈታችሁም? መዝገቡ ይኸውልሽ … ታምኛለሽ አታምኝም"

"አዎ ታስረን ነበር"

"አሁን እውነቱን ንገሪኝ ይችን ልጅ ለምን አስፈራራሽ ፡ ለምን ሰደብሽ"

"እናቴ ትሙት እሷን አልሰደብኩም"

"ኋላ ጉድ ይፈላል ብየሻለሁ ፡ እውነቱን ተናገሪ"

"ሙት እውነቱን ነው ።"

አላምረው ንድድ አለው ፡ "ማን ነህ ፖሊስ ና" ተጣራ "ወፌ ይላላ ክፍል ውስድልኝ ያን ጊዜ እውነቱን ታወጣለች ፡ አትናገሪም ማለት ነው" ጐንበስ ብሎ አፈጠጠባት ። እስቴር ድንጋጤዋ እያሳነሳት ሔደ ። ሰውነቷ ሁሉ ቀለላት ። ክፉኛ ጠጥቶ አልጋ ላይ ጋለል እንዳለ ሰው ሰማይና ምድሩ ተገለባበጠባት ። ዓለማየሁና ሐረገወይን በድል አድራጊነት ስሜት ይተያያሉ ።

ስንታየሁ የተቀመጠበት ወንበር ላይ ትንሽ ተንቆራጠጠና "ባሻ ይኸ ብቻ ሳይሆን ሌላም ጉድ አለ ። እሱ ወንድሜንም አንድ ሴት ደውላ 'ስሙን ጠርታ ዓለማየሁ ድንበሩን ነበር የምፈልገው' ብላ 'አዎ እኔ ነኝ' ሲላት 'ገርልፍሬንድህ የልጆቼን አባት ቀምታለችና ግንባሯን ብየ ሳላሳርፋት አስጠንቅቅልኝ' ብላዋለች ፡ የምንጠረጥረው ይችኑ ነው ይህንንም ጠይቅልን" አለ ።

እስቴር ድንግጥ ብላ ዓለማየሁን ትኩር ብላ ተመለከተችው ። ስንታየሁን የጥላቻ ገላመጠችው ።

"እና አትናገሪም ማለት ነው ፡ በይ እንግዲህ ክብር ካልወደደልሽ ተከተይኝ" አላምረው ከመቀመጫው ተነሣና ወደ በሩ አመራ ፡ "ክብር ለማይወድላት እውነቱን ማናገሪያ ዘዴ አለኝ በይ ወጣ በይ" አፈጠጠ ። እስቴር ብርክ ያዛት ፡ ስንታየሁ ከመቀመጫው ተነሣ ። እስቴር ሁሉንም በየተራ ተመለከተቻቸው ፡ ይቅርታ አድርጉልኝ ፡ ማሩኝ አመለካከት ። ከትንሿ በርሳዋ መሐረቧን አወጣችና ከንፈሯን ጠረገች ። መሐረቧን የያዘው እጇ ይንቀጠቀጣል ።

"እሺ እውነቱን እናገራለሁ ፡ ምንም አታድርጉኝም? እውነቱን እናገራለሁ" አለች ።

አላምረው "እውነቱን ከተናገርሽ ምንም አትሆኚ" እያለ ወደ መቀመጫው ተመለሰ ። እስቴር ቁና ቁና እየተነፈሰች ቁርጥ ቁርጥ በሚል ትንፋሽ መናገር ጀመረች ።

"ይኸ እርኩስ ጆርጅ ነው ለዚህ ሁሉ ያበቃኝ ። እሱ አንድ ቀን አገኘኝና እስቴር ለብርቱ ጉዳይ እፈልግሻለሁ ፡ አንቺም ለኪስሽ

ታገኛለሽ ብሎ ሚልኪያስ ጋ ወሰደኝ ። ከሚልኪያስ ጋር አስተዋወቀኝና ጉዳዩን በዝርዝር ነገረኝ ። እኔ… መጀመሪያ እምቢ ብያቸው ነበር ። ግን ኋላ …እምልህ …ቀላል ነው አይዞሽ እያሉ ሰበኩኝ ። እኔ ደሞ ምን ቸገረኝ ገንዘብ ካገኘሁ ብየ እሺ አልኳቸው ። መጀመሪያ ትንሽ ብር ሰጡኝና የሁለቱን ስምና አድራሻ የሚያውቅ ሰው አለ ብሎ አንድ ወሰንየለህ ከተባለ ሰው ጋር አገናኘኝ ። ወሰንየለህ ስማቸውን ስልካቸውን ነገረኝና መጀመሪያ ለዓለማየሁ ደውይለት አለኝ ። ደወልኩለት ፡ ሳነጋግረው የመናደድ ስሜት ሳይበት ስልኩን ጆሮው ላይ ዘጋሁበት ። በቃ የተሳካልኝ መሰለኝ ደስ አለኝ ። ወሰንየለህ ‘ደውለሽለት የተባባላችሁትን ለእኔ ነው የምትነግረው’ ብሎኝ ስለነበር ሔድኩና የሆነውን እየጨማመርኩ ነገርኩት ። ደስ አለው ፡ ‘ዛሬ በቃ ሞቅ ያለ ገንዘብ እናገኛለን ፡ አንቺ ብቻ አይዞህ ዛሬ ማታ ተጣልተው ነው የሚያድሩት እያልሽ ሰበኪው’ ብሎኝ ወደ ሚልኪያስ ቢሮ ሔድን ። ሁሉንም ነገር ነገርነው ። ደስ ብሎት ለእኔ ሁለት መቶ ፡ ለወሰንየለህም የሆነ ብር ሰጠው ። ወሰንየለህ ሥራ አለኝ ብሎ ሔደ ፡ እኔ እሱ ጋር ቆየሁና ራት አበላኝ ። ይኸን ነገር ጨርሽልኝ እንጂ ለገንዘብ ግዴለሽም አለኝ ። ራት በልተን ስንጨርስ ወደ ቤቱ ይዞኝ ሔደ ። ስንጠጣ ለመሸንና ቤቴ አድርሰኝ ብለው እባክሽ መሽቷል ብሎ እዛው እሱ ጋር አሳደረኝ ። ጧት ሲሸኘኝ ‘አሁን ደሞ ልጅቷን በተራዋ አንድ ነገር አድርጊአት’ ብሎ መቶ ብር ጨመረልኝ ። … እኔ ደሞ እሷን … ያው አስፈራራኋት” ሁሉም ፈዘው ያዳምጧታል ። እየተገረሙ ፡ ከንፈራቸውን እየነከሱ ።

“እሺ ሌላስ የምትነግረን ነገር አለ? የቀረሽ አለ” ጠየቃት አላምረው ።

“በቃ ይኸው ነው ፡ እሷን የሰደብኳት ዕለት ወሰንየለህና እኔ ሔደን ለሚልኪያስ ነግረነዋል ። ‘እንግዲህ በእሷ በኩል ያለው አልቋል ፡ የሚቀረው ሥራ የአንተ ነው’ ብሎታል ። እውነቱን ልንገራችሁ … ዛሬ ማታ እንደውም ቤቱ ቀጥሮኛል ። ልክ በአንድ

ሰዓት ተኩል እንድትመጪ ብሎኛል ። አሁን እኮ ጊዜያስ ደርሷል ወደ እሱ ቤት ልሔድ ስል ነው …” ዐይኖቿ ዕንባ አረገዙ ። ሐረገወይን የልቧ ቢደርስም ፡ የእስቴርን ጸጉር ይዛ መጉተት አማራት ።

“ዛሬ ሚልኪያስ ቤት አታድሪም ፡ እዚሁ ነው የምታድሪው፡” አለ አላምረው ።

“እንዴ ምንም አናረግሽ አላልከኝም እንዴ?”

“አሁንስ ምን አደረግንሽ ፡ ሕግ ፊት ትቀርቢያለሽ” ከመቀመጫው ተነሣ ፡ እንደ ፖሊስ ጠራ ። “ያላትን መዝግብና እስር ቤት ከተትልኝ” ትዕዛዙ ፈርጠም ያለ ነበር ። እስቴር እየተንሚነጩች ወጣች ።

ዓለማየሁ የእስር ቤት ትዝታውን አስታወሰና ‘በወንጀል ሳይሆን እንደው ለጉብኝት የሚፈቀድ ቢሆን ለሁለት ሰዓት ያህል ብገባ እንዴት ደስ ባለኝ’ ብሎ አሰበ ። በውስጡ የሚሽከረከረው የድል አድራጊነት ስሜት ፈንቅሎ ወጣና ፊቱ ላይ መንፀባረቅ ጀመረ ፡ ፊቱ አበራ ፡ ዞር ብሎ ሐረገወይንን ተመለከታት ፡ የእሷም ፊት ያበራል ፡ ተቃቀፉ ። የደስታ ዕንባ አወረዱ ።

“እሺ እንግዲህ ክሳችሁን ነገ መቀጠል ትችላላችሁ ፡ እስከዚያው ደኅና እደሩ” አላምረው ተነሥቶ ተሰናበታቸው ። ስንታየሁ ፡ ሐረገወይን ፡ ዓለማየሁ ተከታትለው ወጡ ። ሐረገወይን ደስታ በፈነቀለው ስሜት ስንታየሁን ዘላ አቀፈችው ። ደረቱ ላይ ልጥፍ ብላ ቆየች ። “አይዞሽ አይዞሽ ገና … ገና” አለ ስንታየሁ በእጁ ወገቧን መታ መታ እያደረገ ።

ጣቢያው በር ላይ ሲደርሱ ግርግር ገጠማቸው ።

“ቀስ ብየ ነው የምገባው አትገፍትረኝ… አትንካኝ ብየሀለሁ … ዋ… እምቧ … ወንዱ የወንዶቹ ላንቃ” ይፎክራል ቀብራራው ።

በሩን እንደወጡ ሐረገወይን ሰዓቷን ተመለከተችና “የዛሬው ትምህርት ውሃ ጠጣ አይደል?” አለች ።

"ስለእሱ ታስቢ አሁን ትልቁን ጠላታችንን አስገብተን ድል አድርገን ስለእሱ ታስቢ … አሁን ቀጥታ ወደቤታችን" ዓለማየሁ ወገቧን እቅፍ አድርጎ ያዛት። መንገዱን ተሻገሩና "ታክሲ ፒያሳ" አሉ ።

የሳሎኑን በር ዛማኑኤል ከፈተላቸው ። አብየ ደጉን ጠጅ ጋብዞ ሲያወሩ ቆይተው ወደቤት የተመለሰው ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ነበር ።

"እንዴ" አለ ሰዓቱን እየተመለከተ ፡ "ምነው አባረሯችሁ እንዴ" አላቸው ።

ሶፋው ላይ ዙሪያውን ከበው ቁጭ አሉና ታሪኩን በዝርዝር አወሩት ።

"እና ከቀለበቱ በፊት ፡ በዓላችን ስምንት ቀን ሲቀረው ዛሬ በዋዜማው ድል ተቀዳጅተናል! እንልሀለን" አለ ስንታየሁ ሶፋው ላይ ወደ ኋላው ጋለል እያለ ።

"ለገንዘብ ስትል ነው ይህን ሁሉ ያደረገችው" ጠየቀ ዛማኑኤል ።

"ፍቅርን ያህል ነገር በገንዘብ ተገዝታ ስታፈርስ ፡ እውነት ለገንዘብ ብላ ነው?"

"አዎ ሲነግሩህ አትሰማም እንዴ" ሐረገወይን ቆጣ አለች ።

"እና ለገንዘብ ብላ ሕሊናዋን ሸጣ አንቺንም እሱንም ያቆሸሸች እሷው ነች" ወደ ሐረገወይን ጠጋ ብሎ አፈጠጠባት ። ትንፋሹ ገፈተራትና ቀና አለች ።

"አዎ አልኩህ እኮ ዛማኑኤል"

ዛማኑኤል ከመቀመጫው ተነሣና መንጐራደድ ጀመረ ፡ "አዎ ወንድሞቼ ለእኛ ድል ነው ፡ ትልቅ ድል ። እሷንም እዘኑላት ፡ የሚለቀስላት ፍጡር ነች ። ነገሩንማ ሰፎክለስ ጨርሶታል ። 'በሰው ልጆች ዘንድ የገንዘብን ያህል መጥፎ ሕግጋትና እርኩስ ልማዶችን

ያመጣ የለም ። ክርክርን የሚያስነሣውና ሰዎችን ከቤታቸው የሚያፈናቅላቸው ገንዘብ ነው ። ንጹሐንን ወደ መቃብር ጐዳና የሚመራ ፡ ቅዱስ ጠባያቸውን ገፎ እንዲረክሱ የሚያደርጋቸው እሱ ነው ።" ጨርሶታል ። እና ወንድሞቼ ገንዘብ እሷን አቆሸሸ ፡ አረከሰ ። እሷ ደሞ እናንተን አረከሰች ። ለእኛ ድል ነው ፡ ከፍተኛ ድል ፡ ሕይወት ለቀለበታችሁ ያቀረበችው ስጦታ ነው ፡ ግን እሷም የሚታዘንላት ፍጡር ናት" የመውደቅ ያህል ሶፋው ላይ ዘፍ ብሎ ተቀመጠ ።

ምዕራፍ ዐሥር

ሚልኪያስ የአስቴርን መታሰር እንደሰማ እንደ እብደት ቃጣው። ፒጃማውን እንደለበሰ ከአልጋው ላይ ዘሎ ተነሣና ወደ ሳሎን ሔደ ፡ ከዚያ መልሶ አልጋው ጠርዝ ላይ ትክዝ ብሎ ቁጭ አለ። የአስቴርን መታሰር የሰማባትን ስልክ እጀታ እንሥቶ ጆሮው ላይ አስጠጋና ማሰብ ጀመረ ። ወሰንየለህ "እባክህ ያች ልጅ ትናንት እኮ ታሰረች አሳሰሯት" ብሎ ሲያረዳው ዝርዝሩን ሳይጠይቀው ነበር ደንግጦ ስልኩን የዘጋው ። አሰበ አሰበና ወሰንየለህ ቤት ደወለ። "አሁን ወጣ" የሚል መልስ ሰጠችው የወሰንየለህ ሠራተኛ። ብሽቅ አለና በረዥሙ ተንፍሶ እየተንጠራራ ተነሣ ። ትክዝ ብሎ ቆመ ፡ በዝንጣ ዓይነት አቋቋም ወገቡን በሁለት እጆቹ ጥፍር አድርጎ ይዞ ። መለሰና ዝርፍጥ ብሎ ተቀመጠ ። የስልኩን እጀታ አነሣና ደወለ ፡ ጆርጅ "አቤት" አለው ። እሱም የአስቴርን መታሰር ሰምቶአል ።

ወሰንየለህ ጆርጅ ጋራዥ ድረስ ሔዶ ነግሮታል ። ግን ጆርጅ አልደነገጠም ፡ "አይ …ከሸፈ በለኛ ድሮም ቀልድ ነበር የያዛችሁት" ብሎ ወሰንየለህን አሹፎበታል ።

"ጆርጅ እባክህን ያንን ወሰንየለህን ፈልጌ ነበር ቤቱ ደውዬ አጣሁት" አለ ሚልኪያስ እንደዚያው ትክዝ ብሎ እንደተቀመጠ ።

"እዚህ ፊት ለፊቴ ተቀምጦ በጧቱ ያደርቀኛል"

"አንተ ጋር ነው ያለው?"

"አዎ እኔ ጋር ነው ፡ ታነጋግረዋለህ"

"አዎ በጥብቅ እፈልገዋለሁ"

ጆርጅ ስልኩን ለወሰንየለህ አቀበለው ።

"እህ ሚልኪያስ ምን አሰብክ?"

"እንጃ ምን አስብክ ትለኛለህ እንጃ ፡ እኔ ለሌንቶቹ ቁጭ ብያለሁ"

"እያዘህ አታስብ የሚሆን የሚሆነውን አደርጋለሁ ፡ ለእኔ ተወው ሚኪ ፡ እንኳን ይችን ብዙ እንሠራለን"

"ጎሽ ወሰንየለህ አባክህ ከጭንቀት አውጣኝ እኔ እምልህ"

"አቤት"

"ሌላ ምን ዘዴ ይኖራል ፡ የለፋንበት ሁሉ እኮ ከስረ ማለት ነው። ደሞም እኮ ልጅቷ ያው መለፍለፏ አይቀር ፡ ሁላችንንም እንዳታጋልጠንና የሰው መሣቂያ እንዳታደርገን ነው የፈራሁት"

"ማይለህም አልኩህ ፡ ለእኔ ተወው ፡ እሱን አንተም አትጋለጥ እሷም ታስራ አትቀር ። ብቻ ወጪ ያስከትልብናል ፡ ስማ ገንዘብ ካለ ምንድን ነው የሚባለው …"

"አይ ወሰንየለህ በገንዘብ ከዳንን ለእሱ አታስብ ፡ ግን እኔ እምልህ ሌላ ዘዴ መፈለግ የለብንም እንዴ? ለፍተን ለፍተን እጅ ሰባራ መሆናችን እኮ ነው ፡ ለማንኛውም በጥብቅ እፈልግሀለሁ ፡ መጥተህ ብንመካከር ይሻላል ፡ ዛሬ ከሰዓት በኋላ ይመችሀል?"

"ቅዳሜ አይደለም ቀኑ?"

"አዎ ቅዳሜ"

"በስምንት ሰዓት ቢሮህ ጠብቀኝ"

"እንዳትቀር" ሚልኪያስ ስልኩን ዘግቶ በችኮላ ልብሱን ለባብሶ ወደ ቢሮው በረረ ።

ስንታየሁ አክስቱን ፈልጎ ስለ ድግሱ አውርቶአቸው ዝግጅት እንዲያደርጉ ነገራቸው ። ኋላም ዓለማየሁንና ሐረገወይንን እስከ ትሎ ማቤያ ውሎ በሰባት ሰዓት ወደ ቤታቸው ተመለሱ ። ከቤት ሳይወጡ ሲጫወቱ ዋሉ ፡ አመሹ ።

ዛማኑኤል ከጓደኞቹ ጋር ቀጠሮ አለብኝ ብሎ በጧት የወጣ

አምሽቶ ቤት ሲመለስ ድክምክም ብሎት ነበር ። ስለውሎአቸው ጠየቃቸው ፡ የረባ መልስ የሰጠው አልነበረም። ገፋፍተው አስተኙት ።

ሐረገወይን ማልዳ መነሣት አትወድም ። እሑድ ዕለት ግን ልክ አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ከመኝታዋ ተነሣች ። ሌሊቱን የሚያረካ ዕንቅልፍም አልወሰዳት ። የዛማኑኤል ቅዠትና ጩኸት ሲያባንናት ነው ያደረችው ። የመኝታ ክፍሏን በር ከፈተችና ሳሎን ገባች ። ዛማኑኤል ፍራሹን አንጥሮ መሬት ላይ ተኝቷል ። የሳሎኑን መብራት አበራችና ተመለከተችው ። ዕንቅልፍ አልወሰደውም ፡ ዐይኖቹን ያቁለጨልጫል ። ገርሞአት ትኩር ብላ ተመለከተችው ።

“ምነው ሐሪዬ” አላት ለመነሣት እየታገለ ።

“እኔ እምልህ ምንድን ነው ብቻህን ስትለፈልፍ ያደርከው ፡ እኔ እኮ ብጠራህም አትሰማ ፡ ስታወራ እኮ ነው ያደርከው” ወንበር ሳብ አድርጋ ተቀመጠች ።

“እየ ሐሪዬ” አለ ዛማኑኤል ከመኝታው ተነሥቶ ፍራሹ ላይ ተደላድሎ እየተቀመጠ ፡ “ብቻየን እኮ አይደለም ፡ ከመጽሐፎቼ ጋር ነበር የማወራው ፡ አየሽ በጥሩ ልቦለድ ውስጥ ያሉ ገጸ ባሕርያት ብቸኛ ሰው ሲያገኙ እንደ ልብ ወዳጅ ሆነው ያጫውታሉ ። እና እኔም መጀመሪያ ከጉዱ ካሣ ጋር ስጫወት ቆየሁና እሱ ደኅና እደር ብሎኝ እንደሔደ ሳንቾ ፓንዛ መጣና ሲያሥቀኝ ቆየ ፡ ቀጠለና ኢያጎ እየተቅበጠበጠ መጣብኝ ‘ኢያጐ እባክህ ውጣልኝ’ ብዬ ተማጠንኩት ፡ እምቢ ብሎ ሲሰብከኝ አመሸ ፡ ወዲያው ጃን ቫልዣን ገባና የባጥ የቆጡን ቀባጠረብኝ ፡ ‘ተበደልኩ ተሰቃየሁ ፡ ግን ፈጣሪዬን አላማረርኩትም ፡ የኢዮብን ትዕግሥት ስለሰጠኝ ብበደልም ብከፋም አላዘንኩም ፡ እየህ ዛማኑኤል በሕይወት አትማረር የሕይወትን ምስጢር ለማወቅ ደጉን ብቻ ሳይሆን ክፉውንም ለመቅመስ ዝግጁ ሁን ፡ ‘ቅብጥርስ ፡ ቅብጥርስ’ እያለ ሲለፈልፍብኝ ‘ወንድም ምንም የማውቀው ነገር የለም ውጣልኝ’ አልኩት ፡ አልወጣም ብሎ ብዙ

እንገራገረ ። ገፍቼ አስወጣሁት ። እሱን ገፍትሬ ከአጥር ውጭ አስወጥቼ ስመለስ ይገርምሻል እኮ ሐረገወይን! ራስኮሊንኮቭ ያችን ባልቴት የገደለበትን መጥረቢያ ይዞ እየመጣልሽም መሰለሽ ። ገና ሳየው ደንግጬ አልኩኝ ፡ 'አንተ ጉደኛ ደሞ ምን ታደርጋለህ' አልኩት የመጥረቢያውን ስለት የጉራጌ እየተመለከትኩ ። 'ምን ላርግ ብለህ ነው ዛማኑኤል ይኸው ወንጀሉ ያንከራትተኛል ፡ ፍርድ ቤት ቀርቦ ወይ በስቅላት ወይ በግርፋት ወይ በሌላ መቀጣት እኮ ያባት ነው ፡ የእኔ ፍርድ አዕምሮን ማስቃየት መንከራተት ሆን እየ … እየ … አንተም በእኔ ጨከንነህ ጉደኛ አልከኝ በል ደኅና እደር' ይልልሽና ቀንደኑን እንደተመታች ላም ሹክክ ብሎ ውልቅ አለልኝ ። ጉሽ ተገላገልኩ ብየ ገብቼ ልተኛ ስል …”

“በቃ በቃ አልፈልግም” አቋረጠችው ሐረገወይን ።

“ቆይ እንጂ ልጨርስልሽ … አንቺ ደሞ ክፉ ዐመል አለብሽ ራስሽ ጠይቀሽ መልሰሽ ትሰለቻለሽ ፡ የሌሊት እንግዶቼን ልጨርስ ልሽ”

“እሺ አጠር አድርገው”

“ባትይም አጭር ነው … እየ አንቺ ልጅ አስጠፋሽኝ እኮ እዎ እዎ …” እጁን ግንባሩ ላይ ተክለና ጥቂት አስቦ መለስ አለ ፡ “እዎ ቤት ገባሁልሽና ቁጭ እንዳልኩ በር ተንኳኳ ፡ 'ማነህ' አልኩኝ ። 'እኔ ነኝ' አለ አንድ ድምፅ 'እኮ አንተ ማ'አልኩት ቆጣ ብዬ ። 'ኢቫን ቼርቭያኮቭ ነኝ' አለ ልመና በተቀላቀለበት የሚያሳዝን ድምፅ ። 'ኢቫን ኢቫን ላውቅህ አልቻልኩም' አልኩና ከመቀመጫዬ ተነሣሁ ። 'እረ ያውቁኛል የአንቷን ቸኾቭ ኢቫን ነኝ ጌታው እንደው የማስቸግርዎ ነገር ስላለ ነው ቢቸገሩልኝ' አለ በተስረቀረቀ ተስፋ በቆረጠ ድምፅ ። 'አሀ አንተ ነህ ግባ' አልኩት ። እየሽ አውቀዋለሁ በጣም በጣም የማዝንለት ሰው ነው ፡ ምስኪን ነው ሰውን ማስከፋት የማይፈልግ የዋህ ነው ፡ ግባ አልኩና አስቀመጥኩት ። መሐረቡን ከኪሱ አውጥቶ ዕንባውን ጠራረገና ትኩር ብሎ ተመለከተኝ ። 'ኢቫን ምን ልርዳህ ችግርህ ምንድን ነው ?'

አፈጠጥኩበት ። 'ትግሬማ ያው የሚያውቁት ነው ጌታዬ … መቸስ ሰው ይሳሳታል ፡ እንደሚያውቁት ማንጠስ የሁላችንም የተፈጥሮ ግዴታ ነው ፡ ትንሹም ትልቁም ያነጥሳል ፡ እኔም አነጥሳለሁ ፡ ግን ሰውን ደግሞ አከብራለሁ ። መቸስ የሰብአዊነት አንዱ ሥነ ምግባር መከባበር መሆኑን አውቃለሁ …"

"እባክህ አሳጥረው" አቋረጠችው ሐረገወይን "እንዴ እንዴ ሐርዬ" ለመናትና ቀጠለ ወጉን ። "እዎ እዎ ኢቫን በእውነት ጄኔራል ላይ ያነጠስኩባቸው አውቄ አይደለም ። ይህንኑ ላስረዳቸው ሞከርኩ ፡ ደጋግሜ ይቅር በሉኝ አልኳቸው ፡ ግን 'ጌታዬ ለምን ታሾፍብኛለህ' ከማለት በቀር ይቅር ሊሉኝ አልፈለጉም … እኔ ደሞ በጭንቀት ልሞት ነው … ታዲያ እስኪ ይህንን ጭንቀቴን ላማክርዎት ብዬ መጣሁ' አለና መሐረቡን ከኪሱ አውጥቶ ማልቀስ ጀመረ ። አሳዘነኝ ፡ ሙች አስለቀሰኝ ፡ ንድድ አለኝና 'ስማ ኢቫን' አልኩት ብስጭት ብዬ ፡ 'አቤት ጌታዬ' አለና ከመቀመጫው ተነሣ ፡ 'ስማ እንዳልከው ማንጠስ የተፈጥሮ ግዴታ ነው ፡ አንተም ሆንክ እሳቸው ያነጥሳሉ ፡ ሳታውቅ አነጠስክባቸው ፡ ደጋግመህ ይቅርታ ጠየቅሃቸው ይህን ያህል የማይገባቸው ደደብ ከሆኑ ቢፈልጉ እራት እግራቸውን ይስቀሉ ፡ ምንም አትሆንም አይዞህ እስቲ አነጠስብኝ ብሎ ምን እንደሚያደርግህ እናያለን አይዞህ አትፍራ' አልኩት ።

"ልንግርሽ አልችልም ያ የጭንቀትና የተስፋ መቁረጥ ጥላ ጥሎበት የጠቆረው ፊቱ ቀስ በቀስ ፈገግ እያለ እየቀላ ሔደ ። 'እግዜር ይስጥልኝ ጌታዬ አመሰግናለሁ እንደ እኔው ችግር ያለበት አንድ ልጅ ከበር ቆሞአል፥ ለእርስዎ አቤቱታ አለኝ ብሎ ፡ ግባ ልበለው' አለኝ ። 'ግባ በለው' አልኩት ። ኢቫን ተሰናብቶኝ ወጣ ። ወዲያው የዘጠኝ ዓመቱ ቫንካ ብቅ አለ ። ተንደረደርኩና አገላብጬ ሳምኩት ፡ 'ደህና ነህ ቫንካ? ምን ሆንክ ምን ልርዳህ አልኩት 'ጋሼ ዛማኑኤል መቸስ ችግሬን ያውቁታል ፡ ገና በልጅነቴ የሰው አሽከር ሆኘ እየተሰቃየሁ ይርበኛል ፡ ይጠማኛል ፡ በዛ ላይ ውሃ ቀጠን ብለው ይደበድቡኛል ። የልጅነት ወጉን ሳላውቀው እንዳይጨልም

ብኝ ፈርቻለሁ ። መቼስ የሰቀቀን ኑሮ ለማንስ ደስ ይላል? ጋሼ ዛማኑኤል ፡ ለአያቴ ደብዳቤ ጽፌ ከዚህ ኑሮ ገላግሉኝ አልኳቸው ፡ ግን ምንም መልስ አልሰጡኝም ዝም አሉኝ ። ቢቸግረኝ ለእርስዎ ላማክርዎት ብየ መጣሁ’ አንጋጦ ዐይን ዐይኔን ተመለከተኝ ። ዐይኖቹ ዕንባ አዝለው ፊቱ አበጥ ሲል ታየኝ ፡ በሰው ልጆች ዕጣ አዘንኩ ፡ በሕይወት ውጣ ውረድ ተናደድኩ ፡ ‘አይዞህ ዛንካና እኔ ጋ ትተኛለህ’ አልኩና እቅፍ አድርጌ ጎኔ አስተኛሁት ። ወዲያው ዕንቅልፍ ወሰደው ።”

ሐረገወይን ዛማኑኤልን ትኩር ብላ ተመለከተችና ክትክት ብላ ሣቀች ። ነገሩ እየገረማት ሣቋን ማቆም አቃታት ። ዐይኖቿ የሣቅ ዕንባ እስኪያወርዱ ድረስ ሣቀችና ፡

“እባክህ አትቀልድ” ብላ ከመቀመጫዋ ብድግ አለች ። አሁንም ሣቋን መቆጣጠር አልቻለችም ። ዛማኑኤል ሰረቅ አድርጎ ተመለከታትና እሱም ሣቅ አፈነው ። ብቻውን ሲያወራ ለማደሩ የደረደረው ምክንያት ራሱንም ገረመው ። የሥነ ጽሑፍ ምርምር ኩሬ ውስጥ ገብቶ ጥቂት ተንቦጫረቀና ወጣ ። የገሃዱን ዓለም ሰዎች ከሥነ ጽሑፍ ገጸ ባሕርያት ጋር አነጻጸረ ። በገሃዱ ዓለም የምንጠላውን ፡ የምናወግዘውን ሰው ዓይነት በድርሰት ውስጥ ስናገኘው እንጠላዋለን ? ሰው ክፉ ሲደርስበት ፡ አገር በውሃ ሙላት ሲጥለቀለቅ ፡ የእሳተ ገሞራ ንዳድ ግልብጥ ብሎ ወጥቶ የሰውን ልጅ ሲጠብስ ፡ የሚበላ ፡ የሚጠጣ ጠፍቶ የአዳም ዘር በረሀብ ሲቆላ ፡ እንደ ቅጠል ሲረግፍ ፡ ሰውን ያህል ታላቅ ፍጡር እንደ እንስሳ ሲነዳ፡ እንደ እንስሳ ሲታረድ ፡ ይቀፈናል ፡ ይዘገንነናል … ታዲያ የደራሲ ምናብ በፈጠረው ዓለም ልቦለድ ውስጥ በመልካም ሥነ ጽሑፋዊ ውበት ተከሽነው ሲቀርቡ ሞትም ፡ ረሃብም ፡ ቃጠሎም ስደትም እኒህ በገሀዱ ዓለም የሚያስጠሉን ሁሉ ለምን አያስጠሉንም ? ክፋት መሆኑን የሚዘገንን መሆኑን እያወቅን ፡ እየዘገነነን ‘ኤጭ ቢቃ አላነብም’ ብለን አንወረውረውም … ለምን ? መቼስ ልቦለድ እውነት ቢመስልም ፡ ያው ውሸት ነው ብለን እየተጽናናን ? የሞተውም ውሸት ፡ የተቃጠለው ውሸት ፡ የራበውም ውሸት ብለን

ራሳችንን እየደለልን። እሺ ይሁን ታዲያ ለምን ውሸት እየነባለሽን ዐይኖቹን ወለሉ ላይ ሰክቶ ለጥቂት ጊዜ አዕምሮውን አስጨነቀና ቀና አለ ። ሐረገወይን ምን ሊናገር ነው ብላ ትጠብቀዋለች ።

"ሐረገወይን እሺ ቀልዱን እተዋለሁ ፤ ግን አንድ ጥያቄ ልጠይቅሽ" አለ ለስለስ ባለ ድምፅ ።

"ምንድነው የምትጠይቀኝ?"

"ማታ እንደምን አመሻችሁ ፤ እንዴት ሆናችሁ ብዬ ስጠይቃችሁ ለምን ዘጋችሁኝ ። ይችን እስኪ መልሽልኝ ?"

"ሒድ ጉረኛ እንደዛ ሆነህ መጥተህ ለአንተ ማን መልስ ይሰጣል ፤ ሰው ብትሆንማ ተከትለኸኝ ትሔድ አልነበረም ፤ ሌሊት መጥቶ ከመጠየቅ ተከትለኸኝ አትሔድም ነበር ..." እየተመናጨቀች ጥላው ወደ መኝታ ክፍሏ ሔደች ። ተከትሎአት መኝታ ክፍሏ ገባ ።

"ምነው ሐረ ነግሬሽ"

"ምኑን ነው የነገርከኝ"

"እየሽ ሐረገወይን ነግሬሻለሁ እኮ! ..." አቀረቀረና ዝም ብሎ ጥቂት ቆየ ።

"እንዴ ምኑን ነው የነገርከኝ" ሐረገወይን ቆጣ አለች ።

"የነገርኩሽማ የልጅቷን ፊት ለማየት አለመፈለጌን ነው ። እየሽ ልጅቷ ከገበያ በገንዘብ ገዝተን ለእርድ ከምንነዳቸው እንስሳት የምትሻል አይደለችም ። ገንዘብ ሰብአዊ ሕሊናዋን የጋረደባት ናት ፤ ለገንዘብ ብላ ሰውን ያህል ፍጡር ለማጥፋት መንጋቷ እስፈራ ጥፍሩን አሹሎ ጥርሱን አግጥጦ ሽንጡን ሰብቆ ለመወርወር እንደተዘጋጀ አውሬ ያስቆጥራታል ። እና ሐሪዬ ልጅቱ ታሳዝናለች። ሰውን ያህል ፍጡር ወደ ኋላ ተጉዞ ወደ አውሬነት ሲለወጥ ያሳዝናል አይደል እንዴ ? እና ከሩቅ እንጂ በቅርብ እያየኋት ማዘን አልፈለግሁም ። ተከትየሽ ያልሔድኩት ለዚህ ነው ... ግን እኔ እምልሽ በዚህ ተቀይመሽኛል እንዴ ... እስኪ እውነቱን ንገሪኝ

ሐረ” እጇን ያዘና በመለማመጥ እያታ ትኩር ብሎ ተመለከታት ። ሐረገወይን ቶሎ ልትመልስለት አልቻለችም ። ተከትሎአት አለመሔዱ አናደዳት ፤ በዚህ ተቀይማለች ። ተቀይሜሀለሁ ብላ ልታስከፋው ግን አልፈለገችም ። እውነቱን ተናግራ ልታስቀይመው አልፈቀደችም ፤ መዋሸቱንም አልወደደችም ፤ ግራ ተጋባችና፤

“አላቅም በቃ ተወኝ” አለች እሷም የእሱን እጅ እየጨበጠች። ሊያሳምናት ሞከረ ፤ ብዙ ተለማመጣት ። ቀልዶች እያወጋ አሣቃት ። ሐረገወይን ሥራው ሁሉ እየገረማት ፈገግ አለችና ፤

“በቃ አልተቀየምኩህም ሙት አልተቀየምኩህም ፤ ስቀልድህ ነው” አለች … የተናገረችው እውነት እንዲመስልላት ፊቷን ኮስተር አድርጋ ። “እውነት…እውነት” አለ ዛማኑኤል እጇን ወደ አፏ እየዘረጋ ፤ የዘረጋውን እጅ መዳፍ መታችለት ፤ አመናት ።

“እሺ ደሞ ሌላ ጥያቄ ልጠይቅሽ ?”

“ምን ቸገረኝ ጠይቀኝ”

“ፖሊስ ጣቢያ ሔዳችሁ ምን አደረጋችሁ ማለቴ ምን ተፈጸመ?”

“ያችን ሌባ በዋስ ለቀቁአት”

ዛማኑኤል “ጐሽ ጐሽ” አለና ወደ ጣራው አንጋጠጠ ፤ ደስ አለው ።

“እንዴ … እሷ ስለተፈታች አንተን ምን እንዲህ አደረገህ ፤ ጠላታችን ስለተፈታች ትደሰታለህ እንዴ—አሁንስ አበዛኸው … ሙት ሙት አበዛኸው”

“የለም ሐረ አላበዛሁትም ፤ ሊታዘንላት የሚገባ ፍጡር ናት እኮ ብየሻለሁ ። እየሽ ይህች ልጅ አንቺን አታውቅ ፤ ዓለማየሁን … በቃ ገንዘብ ሰጥተው ወደ ጥፋት መሯት … ይኸው እኮ ነው ። እየሽ ገንዘብ እኮ የማይገዛውና የማይለውጠው ነገር የለውም ። በጥንቱ የአውሮፓ ታሪክ የፈረንሳይ ንጉሥ ሣልሳዊ ሄንሪ የገዳማትን ንብረት ዘርፎ ሸጧል ። ይታይሽ ለገንዘብ ብሎ ከአምላኩ ጋር

ተባልቷል ። ገንዘብ እኮ ማንነትን የሚያስረሳ ሕሊናን የሚገፋ መርዝ ነው ፡ ሼክስፒር እኮ ቲሞንን ያስመልካል ፡ ሌቦችን ማዕረግ አትሞናጅሮ ግርማ ሞገስ ያሰጣቸዋል ፡ ከመሳፍንት አስተካክሎ እጅ እንዲነሡ ያደርጋል ያለው ወዶ አይደለም ። ያች ልጅ በአንቺ ላይ ክፉ ብታስብም ፡ አንቺ ክፉ አልደረሰብሽም ... ሐሬ ግዴለም ትፈታ፡ ይቅር በያት ... ሕይወት ፈቷን የመለሰችባት አሳቧን ፍጡር ናት ግዴለሽም ይቅር በያት ።"

"በቃህ ... በቃህ ተወው"

"በቸስ ፈቷት ስትይ ፡ በሌላ ጊዜ ፖሊስ ጋር ትቀርባለች ማለት ነው?"

"ወጻ ነው ... በግድ ትቀርባለች"

"ቆይ እባክሽ ... በደንብ አስረጂኝ"

"አስረዳሁህ እኮ ፡ በቀጠሮ ልትቀርብ በዋስ ተፈታች ። ላከሷት ለምትላቸው ሰዎችም መጥሪያ ተጽፎላቸዋል ። ቀርበው ቃላቸውን ከሰጡ በኋላ ፍርድ ቤት ትቀርባላችሁ ብለዋል ። በቃ ይኸው ነው ምኑን ነው የማስረዳህ" ሐረገወይን እንደመቆጣት አለችና አልጋዋ ላይ ዘፍ ብላ ተቀመጠች ። ዛማኑኤል አስተያየት መስጠት አልፈለገም ። አቀርቅሮ ዝም አለ ። ሁለቱም በያሉበት በሐሳብ ከነፉ፡ የሐረገወይን የመኝታ ክፍል በዝምታ ተዋጠች ።

የሡንጋ ተራ ሕዝብ በሌሊት ተነሥቶ ሁሉም በየሥራው ይሰማራል ። ቤተክርስቲያን የሚስመው ይርመሰመሳል ፡ የሡንጋ ተራ ልብስ ሰፊዎች መኪና ጩኸት ከሩቅ ይሰማል ፡ የዕለት ጉርስ ፍለጋ ሌሊት የሚወጣው ሥራ አጥ በየጥጉ ይንከላወሳል ። ሴተኛ አዳሪዎች በራቸውን ገርበብ አድርገው ከፍተው ለስንበቱ የሰዓት በኋላ ግርግር ቤታቸውን ያፀዳሉ ፡ ሁሉም በየፈናው የዕለቱን ደፋ ቀና ጀምሯል ።

የሳሎን በር ሲንኳኳ ሐረገወይንና ዛማኑኤል ከሐሳባቸው ባነኑ።

"ማንነው ይሆን በሀገሬ የሚያንኳኳ" አለች ሐረገወይን ። ወደ በሩ እየተጣደፈች ሔደች ፤ ዛማንኤል ተከተላት ። በሩን ከፈተችና እንግዶቹን ወደ ውጭ አውጥቶ ተመለከተ ። ወዲያው ፊቱ ልውጥውጥ አለ ። የመደናገጥ ስሜት ወረረው ፤ በሩን ሰፋ አድርጎ እየከፈተ "ግቡ ግቡ ... " አለ ።

ዘነበችና አሊቃ ተከታትለው ገቡ ። ዘነበች ዐይኖቿ ዕንባ እየተናነቃቸው ሐረገወይንን ተመለከተችና ዘላ ተጠመጠመች ባት። ብዙ ዘመን ተለያይተው የተገናኙ እኅትማማቾችን ያህል ተቃቅፈው ተላቀሱ ፤ አልጠገብ አሉ ። አሊቃ በድንጋጤ ስሜት ተውጠው መስቀላቸውን ደረታቸው ላይ ለጥፈው ፈዘው ቆመዋል ። ከፊት ለፊታቸው እንደሳቸው ፈዞ ቆሞ የሚያያቸው ዛማንኤል በሰው አምሳል የተፈጠረ ሳይሆን ለመተናኮል ጥፍሩን ያሾለና ከአሁን አሁን ልፈንጠር እያለ የሚዘጋጅ ቁጡ ነብር መስሎ ታያቸው ። ከዚህ ቀደም ሁለቱ የተባባሉትን ሁሉ አስታወሱና ፈሩት ፤ ብርክ ያዛቸው ። ዛማንኤል ግን አሊቃ እንደሚያስቡት ዓይነት ሰው አልነበረም ። አልተቆጣም ፤ አያስፈራም ። መምሰልና መሆን የተለያዩ ናቸው ። ብቻ ሁኔታው ገርሞት የሚያደርገውን አጥቶ ፈዞአል ። ሁለቱም ወገን ተፋጠጠና ዝም አለ ።

"ተቀመጡ ... እ ... ተቀመጡ" አለ ዛማንኤል በእጆቹ ወደ ሶፋው እያመለከተ ። አሊቃና ዘነበች በዐይን ጥቅሻ ተነጋገሩ ። ግን አልተግባቡም ። አሊቃ ወደ አንዱ ሶፋ ጠጋ አሉና ከመቀመጣቸው በፊት ዘነበችን አሻግረው ተመለከቱአት ። እሷም ሰረቅ አድርጋ አየቻቸው ። አሁንም አልተግባቡም ። የአሊቃ ዓይን መልዕክት "እንዴት ይሻላል ሳንቀመጥ ቆመን ብንለምናቸው አይሻልም" ለማለት ነበር ። ግን ዘነበች አልገባትም ። እንኳን በዐይን መልእክት ቀርቶ በአፋቸውም ምን ይሻላል ? ቢሏት

"ወይኔ እኔ ምኑን አውቄው ኧረ እንደፍጥርጥርዎ" ብላ ነው የምትሸሽ ። አሊቃ ከመደናገጣቸው የተነሣ የለመዱት ሽምግልናም ጠፋቸው ።

ዘነበች ከወትሮው ወፈር ብላለች ። ፊቷ ሞላ ብሎ አምሮበታል። የአንገቷ ላይ ንቅሳት ጉልቶ ወጥቶ ድምቀት ሰጥቶአታል ። ዘማኑኤል ልብ ብሎ አስተዋላትና "አትተውም" ብለው እንደተቆጡት ልጅ ሽምቅቅ ብሎ ዐይኑን መለስ አደረገ ። ከአለቃ ፊት ለፊት ተቀመጠ ። ሐረገወይንና ዘነበች ጎን ለጎን ቁጭ አሉ ። ለጥቂት ጊዜ ሁሉም ተፋጠጡና ዝም አሉ ።

አለቃ ካባቸውን አስተካክለው መስቀላቸውን በቀኝ እጃቸው ወጣ አድርገው ያዙ ፡ ጉሮሮአቸውን ለመጠራረግ የቀኝ መዳፋቸውን ጨብጠው ወደ አፋቸው አስጠጉና "እእእ … እ" የሚል ድምፅ አሰሙ ። ሌሎቹ ይመለከቱአቸዋል ።

"እንግዲህ ልጆች አዳምጡኝ" አሉ በመስቀላቸው እያማተቡ። "ጌቶችና እሚቴ ልከውኝ ነው የመጣነው … እንደ ልማዳችን … እንደ ባህላችን ቢሆን ቆመን ነበር መለመን የነበረብን ፡ ሳንቀመጥ ቆመን ነበር … መቼስ ባልወልዳችሁም ያው ልጆቼ በመሆናችሁ ብቀመጥም ቅር አይላችሁ …"

"እንዴ እንዴ ምንም አይደል … ቅር አንሰኝም" አለ ዘማኑኤል አቋርጦአቸው ።

"ጉሽ ጉሽ" አሉ አለቃ ተደላድለው እየተቀመጡ ። ጉሮሮአቸውን አሁንም ጠራረጉና ቀጠሉ ፡ "ሐረገወይን እንዲህ ዛሬ ትልቅ ሰው ብትመስይ ገና ጡጦ ስትጠቢ ጀምሮ ያሳደግሁሽ ልጅ ነሽ ። አንተም ዘማኑኤል እንደእሷ ባላውቅህም ያው ልጄ ነህ ። 'እመ ኢወለድኩክሙ አቡክሙ' እንደሚለው ፡ እኔም የሥጋም ባይሆን የነፍስ አባታችሁ ነኝ እና አዳምጡኝ ። … መቼስ አባትሽ የተከበሩ የተፈሩ ሰው ናቸው ። ሁላችንም የምናከብራቸው አዛኝና የድሀ አባት ናቸው ። እግዚአብሐር አምላካችን በቀኝ እጁ የዳሰሳቸው ጻድቅ ናቸው ። ታዲያ በስተርጅና ያውም በተከበሩበት ፡ በጌትነት በኖሩበት አገር እሰው አፍ ውስጥ መግባት የለባቸውም ። ልጆቼ ጌቶች ተጸጽተዋል ። ተሳስቻለሁ ብለዋል ። … ወላዲት አምላክ ምስክሬ ናት ፡ … ልጆቼ ይኸን ሰሞን የምናውቃቸው የወትሮው

ወንዲራድ አያደሉም ፤ በትንሽ በትልቁ ይበሳጫሉ ፤ ሰውነታቸው በየዕለቱ እየሟሸሸ ነው … እና ልጆቼ እናንተም እዘኑላቸው ። 'በአባትነቴ የተሰማኝን ተናግሬአለሁ ፤ የመሰለኝን ለማድረግ ሞክሬአለሁ ፤ ይኸ አይሆንም ካለች የፈቀደችን ታድርግ ፤ ከእንግዲህ እሷ የወደደችውን እወዳለሁ ፤ ይኸ ይሁን ያለችኝን አደርጋለሁ ፤ ወደ ቤቷ ትመለስ' ብለዋል ። እንግዲህ ልጆቼ እሳቸው … አባታችን … አጥፍቻለሁ ማሩኝ ቢሉ እናንተም ሔዳችሁ ጉልበት ስማችሁ ይቅር በሉን ማለት አለባችሁ … እኛም አመጣጣችን ለዚሁ ነው … 'ልጅ እየመከሩት ያጠፋል ፤ እጅ እየታጠቡት ያድፋል' እንዳይሆንባችሁ አሁኑኑ እሺ በሉንና እቤታችሁ … ግቡ" ካባቸውን እያስተካከሉ ተነሥተው ቆሙ ። "እንግዲህ እሺ ካላላችሁኝ አልቀመጥም እሺ በሉኝ ልጆቼ …"

ሐረገወይንና ዛማኑኤል ካቀረቀሩበት ቀና አሉና ተያዩ ። በሁለቱም ፊት ላይ የመኮሳተር ምልክት ይነበባል ። ዛማኑኤል ሐረገወይንን አፍጥጦ ተመለከታት ። በእግሯ ወለሉን እየጠረገች ትክዝ ብላለች ።

ዘነበች የሐረገወይንን መተከዝ ስትመለከት ተቁነጠነጠች ። ካቀረቀረችበት ቀና አደረገችና እቅፍ አደረገቻት ። ዐይን ለዐይን ተገጣጠሙ ።

"እዎ እትዬ" አለች ዘነበች በልምጥምጧ አነጋገር ፤ "ጌቶችስ አላንቺ ማን አላቸው ፤ እትዬስ አላንቺ ማን አላቸው ። ነገር ውስጣቸው ገብቶ በብስጭት እንደ ነገር ቢሆኑብሽ ዞር ዞር ጠጠቱና ነዳማውን አትችይውም ። አንቺም በሽታ ላይ ትወድቂያለሽ ። እትዬ ሙች ጅስምሽን ትጐጂለሽ አልኩሽ ። ጉሚ አትያዥ እትዬ ። ጉሚ ያራርቃል ፤ ጉሚ ያበጣብጣል ፤ ጉሚ ቤተሰብ ያፈርሳል ፤ እትዬ … በቃሽ እምታኘሽበት ቤትሽ ግቢ …" ዕንባዋ ቀደማትና አቀረቀረች ።

ዛማኑኤል ዘነበችን ሰረቅ አደረገና ተመለከታት ። አልጠገበትም ፤ ሰውነቱን ሙሉ በሙሉ ወደ እሷ መልሶ ትኩር ብሎ

ተመለከታት ። ጉንጮቿ ፡ ከንፈሯ ፡ ጸጉሯ ፡ ውፍረቷ አዲስ ሆኑበት። ሆዷን ሰረቅ አድርጎ ተመለከተው ። አንዳች ነገር መላ ሰውነቱን ሲወረው ተሰማው ፡ የወረረው-አንዳች ነገር ቀስ እያለ ውስጡን እየሰረሰረ ራሱ ላይ ወጣና ለአፍታ ድርብርብ ሐሳቦች ተፈራረቁበት ። የሰው ልጅ አፈጣጠር ፡ የሰው ልጅ አመጣጥ ፡ የአባትነት ጣጣ ፡ የአባትና የልጅ ግንኙነት ፡ ወልዶ መሳም ፡ ስሞ ማሳደግ ፡ አሳድጎ መዳር ··· የሕይወት ተከታታይነት ። ሐሳቡ ምስቅልቅል አለበትና ሊረሳው ፈለገ ። ግን እንዲህ በቀላሉ ወጊድ ብሎ የሚያስወግደው አሳብ አልሆነለትም ። ደስታም ሐዘንም ለየብቻው ። ደግሞ የሁለቱ ድብልቅ ተራ በተራ የአእምሮውን ጓዳ አተራመሱበት ። ዐይኑን መለስ አደረገና ከጣራው ላይ ሳገው ። “እውነቷን ነው ዘነበች ··· እውነትም ጉሚ ፡ አዎ ጉሚ ፡ የብጥብጥ እርሾ ነው ፡ ፍቅርን አርቆ ጠብን የሚጋብዝ የሰው ልጅ ባሕርይ ነው ··· የሕይወት እንቅፋት ···ወንዲራድ በሐረገወይን ላይ ጉሚ ሆቺ ጉድ ··· አባት በልጁ ላይ ጉሚ ··· ገበየሁ በእኔና በዘነበች ላይ ጉሚ ··· ወሰን የለሀና ሚልክያስ በሁላችንም ላይ ጉሚ ··· ይህች እርጉም ዓለም ··· ይህች የጉሚ ጉተራ ፡ በራሷ ላይ ጉሚ የምትይዝ እስስት ዓለም ··· ኧረዲያልኝ ።” በትካዜ አቀርቅሮ ቆየና ቀና አለ ። በዙሪያው የተቀመጡትን በየተራ ተመለከታቸው ።

“እሺ አለቃ” አለ ድምፁን ዘለግ አድርጎ ። “የእኛም ፍላጎታችን ይኸው ነው ። ምኞታችን አባት እናቷ ምርጫዋን ደግፈው መርቀው እንዲድሯት ነው ። የእስካሁኑን እንደ ፈሰስ ውሃ እንቁጠረው ፡ የወደፊቱን እናስብ··· በቃ ··· እኔ ዛሬውኑ ይዣት እመጣለሁ ··· ዛሬውኑ ቤቷ ትገባለች” ፡ ሐረገወይንን ተመለከታት፡ እስተያየቱ “እሺ በይ ፡ በዚህ ሐሳብ ተስማሚ” የሚል ይመስላል ፡ ሐረገወይን አልወደደችለትም ፡ ገላመጠችው ። የሐረገወይንን ዐይን ደኅና አድርጎ ያውቀዋል ፡ ዐይኗ ሲሥቅም ፡ ሲቆጣም ሲያዝንም አይቶታል ። የአሁኑ ግን የሐረገወይን ዐይን አልመሰለው አለ ፡ ተጉረጠረጠበት ፡ አስፈራው ።

"የለም … የለም" አለች ሐረገወይን እየተቆጣች "… ዘለን መጥተን ዘለን እንመለስም … እዩ አለቃ … እምልሃት … እኛም መክረንበት መልሱን ይኸን ሁለት ቀን ብንነግርዎ አይሻልም" … ተናግራ እንደጨረሰች እግሮቿን እነባብራ ትክዝ አለች ። ዐይኖቿ ዕንባ ቋጠሩ ፤ አባትና እናቷ ከፊቷ መጥተው ድቅን አሉባት ፤ እንደ ፋንፋን እናቷ "ምነው ልጄ የምን ምክር? እኔ እናትሽ ቤት ለመምጣት ነው እምትመክሪ? ጡቴስ አይወቅስሽም … ብታመም ብሽ … ብሞትብሽ እንቺው አይደለሽ እምትጎጂ … ኧረ ተዪ … ኧረ ተዪ ልጄ" የሚሏት መሰላት ። በግራ እጇ ዐይኖቿ ዙሪያ ያለውን ዕንባ ጠራረገችና በረዥሙ ተነፈሰች ። ዘነበች ጎኗ ቁጭ ብላ በሐዘኔታ ትመለከታታለች ።

ዛማኑኤል "አለቃ በሉእ ምክር አምጡ" አለ ግራ ገብቶት ።

"እንግዲህ ይሁና … የእኛ እንኳ ፍላጐት አሁኑኑ አብረን ብንሔድ ነበር ፤ ግን እንምከር ካላችሁ ምክሩ ፤ … መቸስ ምን ይደረግ …? ታዲያ መልሱን መቼ … መቼ ትነግሩን"

ሐረገወይን ዛማኑኤልን ገላመጠችው ፤ ፍላጐቷ በዚህ ቀን ብሎ መልስ እንዲሰጥ ነበር … ገዝም አላት … ቆጣ አለችና "በቃ ነገና ከነገወዲያ እንነግራችሁአለን" ብላ ከመቀመጫዋ ተነሣች ፤ በዚሁ ተስማሙ ።

አለቃ አመስግነው ወጡ ፤ ዘነበች ወደ ኋላ ቀረት አለችና "አለቃ እኔ ትንሽ እቆያለሁ እርስዎ ይሒዱ" ብላ ጮኸች ። አለቃ ብቻቸውን ተመለሱ ።

ዘነበች ከሐረገወይን ጋር እየተጫወተች ናፍቆቷን ተወጣች ። ሐረገወይንን ለማሳመን ብዙ ጣረች ። ስለ ወንዲራድ ፤ ስለ ወይዘሮ ተዋበች ፤ ስለ ገበየሁ ብዙ ብዙ አወራቻት ። ሐረገወይን ሐሳቧ ቀለል ብሎላት መሣቅ መጫወት ጀመረች ።

"ተብየም አላቅ እስቲ ቡናሽ ናፍቆኛል አፍይልኝ"

"ደሞ ለእሱ ነው" ብላ ተነሣች ዘነበች ።

እሴት እንደወጡ ዓለማየሁና ስንታየሁ ከመኝታቸው ተነሡ ። ዘነበች ቡና አፍልታ ስታመጣ ሁሉም ሳሎን ተሰበሰቡ ፡ ጨዋታቸው ደራ ።

“ተብቨኝ” ኳሳቅ! መቸስ አያልቅብሽም እስቲ የዱሮ ታሪክሽን ለእነ ዓለማየሁ አውሪያቸው” አለች ሐረገወይን ሣቅ እያለች ። ዛማኑኤል በዘነበች ወግ መሣቁን አልወደደውም ፤ ከፋ አለው ።

“አይ እትዬ … ምን ታሪክ አለኝ ብዬ … ይልቅስ ቧልቱን ተይውና ቁምነገር ላውራልሽ ሙች … ታንጂቴ ነው …”

“ምኑ ነው ቁምነገሩ በይ እስቲ ንገሪኝ”

ዘነበች የያዘችውን ስኒ ቡና ጨለጠችና ስኒውን በእጇ ከፍ አድርጋ ይዛ ውስጡን እያዟዟረች ተመለከተችውና አስቀመጠችው።

“እትዬ ታንጂቴ ነው እምነግርሽ … ይኸውልሽ መቸስ በእኔም ላይ የደረሰ ስለሆነ ነው የምነግርሽ”

“እኮ ምንድን ነው… ንገሪኝ”

“አቦ ቆይ አታጃጅይኝ… ምን አጣደፈሽ … እሜቴ ወይዘሮ ተዋቡ የነገሩኝን ነው እምነግርሽ ፡ በሕልማቸው ያዩትን … ልብ በይ … ይኸውልሽ ይኸ ማነው ስሙ እቴ እንቺን ሥራ ያስገባሽ ሰው … ጌቶች ሥራ ፈልግላት ብለውት ሥራ ያስገባሽ”

“እሺ ወሰንየለህ” አለች ሐረገወይን ።

“አዎ እሱ ነው አሉ ፡ በወረቀት የተጠቀለለ ነገር አምጥቶ እሜቴ የገና ስጦታ ነው ተቀበሉኝ ብሎ እጁን ይዘረጋላቸዋል ። እሳቸው ደሞ ልቀበል አልቀበል እያሉ ሲያመነቱ ፡ ‘እንዴ ምነው ስጦታ እኮ ነውር የለበትም ይቀበሉኝ እንጂ’ ይላቸዋል ። እሳቸውም ‘እግዚአብሔር ያክብርልኝ ፡ የነገ ሰው ይበልልኝ’ ብለው መቀበል ። ታዲያ የተጠቀለለውን ዕቃ ይሰጣቸውና ውልቅ ብሎ ይጠፋል ። እሱ እንደሔደላቸው ወረቀቱን ቀስ ብለው ሲፈቱት አንድ ትልቅ ባኮ ነው!! ቀጠሉና ባኮውን ከፈት ሲያደርጉት አንድ ትልቅ እባብ

ዋቅልል ብሎ ተኝቷል ። ኪማያብጃችን ያደነግጥና ድንግጥ ብለው ይባንኑልኛል ። ምን ስለት መቸስ አዳር አይምሰልሽ ያደሩት ። በጧት ያነሙኛና ቡና አፍያልኝ ይሉኛል ። አፍልቼ የአቦሉን ሲሰጧቸው እኔ እንደ ሰጠሁአቸው 'እረ እንቺ ዘነበች' ብለው 'ይሽን ነገር በሕልሜ እየሁ' ብለው ነገሩኝ ።

"ለጊቶችም ቁጭ ብለው አሜወቷቸው ። ጊቶችን ያየ መቸስ … አጅብ የሰሞኑ ክራሞታቸው የጉድ ነው … እህ ሲሉ ሲናደዱ ይኸ ሴባ ጉድ ሲሠራኝ እንዲን ልጄን ሊያስነጥቀኝ ሲሉ ነው የከረሙት"

"ታዲያ የሕልሙ ፍቺ ምንድን ነው አንቺ በምን ፈታሽው?" ጠየቃት ዓለማየሁ ።

"ወይኔ እባብ እባብ ነው መቸስ በደግ ነገር አይፈታ … እባብ መቸስ ያው ሸር ነው … እንዲህ ዓይነቱን በሩቅ ነው እንጂ… ደሞ መቸስ የወለደ ሰው ይታየዋል ፤ አይናቅም ። ይኸውልሽ እትየ የእኔም ታሪክ ተመሳስሎብኝ ነው ። አገሬ እንዳለሁ የመጀመሪያ ባሌ ጋር ተጣልቸ ትቸው ወጣሁ አላልኩሽም ። ምርር ሲለኝ በደል ቢበዛብኝ ትቸው ወጣሁና ወላጆቼ ጋር ገባሁ ። አባቴ 'ስሚን እስነጣሽው በስተርጅና አዋረድሽኝ እያለ ታልተመለስሽ' ብሎ ቁም ስቅል አሳጣኝ ። ታዲያ እናቴ አትናገርም ። እሱ ብቻ ነው ፤ ሌት ተቀን ሴላም ፈሊጥ የለው 'ተመለሽ' ነው ። ምን ይሆንልሻል እንደው እኮ እሚገርም ነው ። ለካ እናቴ እኔ ልጃር ስል ሕልም አይታ ኑሮአል ። ለማንም ሳትነግር እንደው ሆዷን እየበላት ዝም ትልና እኔ አዳራለሁ። አልሰነበትኩም እኮ … ወዲያው ነው ተጣልቼ የተመለስኩ ፤ … ታዲያ እናቴ ዝም ብላ 'እ' ትላለች አባቴ 'ተመለሽ' ብሎ በተቆጣ ቁጥር ዝም ብላ 'እ …' ትላለች ። ውስጥ ውስጡን ዝም ብላ ትነዳለች ። ከአባቴ ንዝንዝ ተመለስኩና መልሸ አራጋው ጋር ገባሁ። አልተኗኗንም ፤ በዓመቱ መልሸ ከበለልኩ ። አዳልሽማ መጨረሻው ምን ይሆንልሻል … ስትነግረን ለካስ ሕልም አይታ ኖራል ። እንደ ነገ ሠርጌ ሊሆን አዳሯን ሕልም አይታ ኖራል ።

በሕልሟ ለእኔ ሠርግ ድግስ እየተዘጋጀ እንጀራው እየተጋገረ ፡ ወጡ እየተሠራ ይታያታል ። እሷም በአንድ ድስት ወጥ ስትሠራ ይታያታል ። ያንን ወጥ ትሠራና ጨርሳ ድስቱን በጉልቻው ላይ አንስታ አስቀምጣለሁ ስትል እማይበጃችን እንክት ይበልና እጇ ላይ ይቀርባታል ። ያ ሸክላ ይሰበርና ወጡ ይፈሳል ፡ እሳቱንም ያጠፋዋል። ድንግጣ ብንን ብላ ትነቃለች ። የሠርጌ ዕለት እንደው ፍዝዝ ብላ ዋለች ፡ ልጇን እምትድር ሴትም አትመስል ነበር ፡ ለካ ነገሩ ሌላ ነው ። አዳልሽ አሯጋው አስከፉቶኝ እንደወጣሁ አባቴ 'ተመለሽ' ሲል ዝም ትላለች ፡ ሲነዘንዘኝም ዝም ትላለች ሲጠናባት ጊዜ 'እኔ ገና ተጧቱም ደስ አላለኝ ፡ እንደማይሆን አውቄዋለሁ' ብላ ሕልሟን ነገረችው ። ይኸው ረከቦት ነው ፡ ተዚያ ወዲህ ሔጂም ተመለሽም ብሎኝ አያውቅ ። ይኸውልሽ ያንቺና የእኔ ታሪክ ማጥምጥም አለልሽና አረፈዋ ። የአንቺ አባት በናትሽ ሕልም ተመለሱ ፡ የእኔም አባት በናቴ ሕልም ተመለሰ … ሕልም አይናቅም ነው እምልሽ …አቦ የኔ ነገር እንደው በወሬ ገተርኳችሁ አይል … ብቻ ቁምነገር ነው …”

ሁሉም ትኩር ብለው ተመለከቱአት ። ፈጥኖ አስተያየት የሰጣት አልነበረም ። ተፋጠው ቆዩና የዓለማየሁ ሠራተኛ ቁርስ ብላ እጅ ለማስታጠብ ስትመጣ ወሬ ጀመሩ ።

ዘነበች ሐረገወይን ጋር ስትጫወት ዋለች ። ማምሻው ላይ ዛማኑኤል ሊሸኛት ይዟት ወጣ ፡ አምሽቶ ተመለሰ ።

ያንኑ ዕለት ምሽት ተሰባስበው በነገሩ መከሩበት ። ብዙም የሚያከራክራቸው አልነበረም ። የቀለበቱ ቀን እንደተጠበቀ ሆኖ ድግሱን ወንዲራድና ተዋበች እንዲያዘጋጁ ፡ ይህንኑ ሐሳብ ዛማኑኤል ማክሰኞ ጧት ሔዶ ለወንዲራድ እንዲያስረዳ ተስማምተው አደሩ ። ሌሊቱ የሰላም እንቅልፍ ሌሊት ነበር ።

ሰኞ በአሥራ ሁለት ሰዓት ስንታየሁ ፡ ሐረገወይንና ዛማኑኤል

ተገናኝተው ወደ ስድስት ኪሎ ጉዞ ጀመሩ ። የዕለቱ አየር ቀዝቀዝ ያለ ስለነበረ ፣ ብዙም ድካም አልተሰማቸውም ። በስሱ የሚነፍሰው ቀዝቃዛ ንፋስ ወበቆት የሞለውን ሁሉ እያረካ ፣ የመንገዱን ዳር ትርዒት ረጋ አድርጎታል ። እነ ሐረገወይን ከአንዱ ታክሲ ወደ ሌላው እየተገላበጡ አራት ኪሎ ደረሱ ።

ከአራት ኪሎ ስድስት ኪሎ ለመድረስም ጊዜ አልፈጀባቸው ። ገና ከሠንጋ ተራ ሲነሡ ጀምሮ አንዲት መኪና ትከተላቸዋለች ። ሠንጋ ተራ ታክሲ ተሳፍረው ፒያሳ እስከሚደርሱ ድረስ መኪናዋ ከኋላቸው ስትከተላቸው ቆየች ፤ ቆመው የአራት ኪሎን ታክሲ እስከሚያገኙ ድረስ ያች መኪና ፊንጠር ብላ ቆማ ጠበቀቻቸው ። በመኪናዋ ውስጥ ሦስት ሰዎች አሉ ከነሾፌሩ ። ፒያሳ እንደቆሙ ከመኪናዋ ፊት በር የተቀመጠው ሰው ከመኪናዋ ወርዶ በዐይኑ ሲከታተላቸው ቆየ ፤ ታክሲ አግኝተው እንደገቡ እሱም ዐይኑን ከታክሲዋ ላይ ሳይነቅል ዝግ ብሎ መኪናዋ ውስጥ ገባና ተከተላቸው ።

ዩኒቨርስቲ በር ደርሰው ከታክሲ እንደወረዱ ዛማኑኤል የሐረገወይንን ትከሻ ያዝ አደረገና ፣

“ደሞ ግቢው ውስጥም አጅቡኝ እንዳትሉና እንዳታስቂኝ” አላት ጥርሱን ብልጭ እያደረገ ። ሦስቱም ተሣሣቁና ሐረገወይን ከሌሎች ተማሪዎች ጋር እየተጋፋች ገባች ።

የዩኒቨርስቲ በር በሚገባውና በሚወጣው የቀንና የማታ ተማሪ ተጨናንቋል ። ሐረገወይን የዩኒቨርስቲውን በር አልፋ ወደ መማሪያ ክፍሏ ስትገሰግስ ፣ ስንታየሁና ዛማኑኤል ከሩቅ ሆነው ተመለከቷት። በዐይን ሸኟት ። መለስ ብለው ሁለቱም ተያዩ ። “እህ እስከምትወጣ ምን እናርግ” የሚባባሉ ይመስላል ።

ስትከተላቸው የቆየችው መኪና ራቅ ብላ ቆማ ቆየችና ሐረገወይን እንደገባች ተመልሳ ወደ አራት ኪሎ አቅጣጫ ከነፈች።

“ታዲያ የት እንቆይ!” አለ ዛማኑኤል ሰዓቱን እየተመለከተ ።

ከአሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል እስከ ሁለት ሰዓት ድረስ ረጅም ጊዜ ነው ፤ የኒቨርስቲ በር ላይ ቆመው ሊቆዩ አይችሉም ። አንዳንድ ጊዜ በአካባቢው ሲዞሩ ይቆያሉ ፤ አንዳንድ ጊዜ ሙዚቃ ትምህርት ቤት ፊት ለፊት ወዳሉት ቡናቤቶች ሔደው ሻይ ፤ ሲያሻቸውም ሌላ ይዘው ሲጫወቱ ይቆዩና ከትምህርት ቤት መውጫ ሰዓት ሲደርስ ይመለሳሉ ።

"እዚያች ቡና ቤት ሔደን ቁጭ እንበል"

"የቷ ቡና ቤት"

"ከእንበሳው ቤት በታች ያለችው"

በዚህ ተስማሙ ። በሸርሸር ጉዞ ዓይነት ቀስ እያሉ ቁልቁለቱን ወረዱ ።

የምሽቱ የአየር ሁኔታ ለምሽት የእግር ጉዞ የሚጋብዝ ነው ። የስድስት ኪሎ ዛፎች የነፋሱን ግፊት እየተጋፈጡ ወዲያ ወዲህ ይወዛወዛሉ ። የአንዱ ዛፍ ቅርንጫፍ ከሌላው ዛፍ ቅርንጫፍ ጋር እየተቃቀፈ ይለያያል ። የነፋሱና የዛፎቹ ውዝዋዜ ድምፅ ተዋህዶ የሚፈጥረው ጣዕመ ዜማ ልብን በደስታ ይኮረኩራል ። ጥግ ጥጉን ይዘው ከላይ ዛፎቹን ከለላ አድርገው የፍቅር ወግ የሚያወጉ አዳዲስ ፍቅረኞች ያሳዝናሉ ፤ ይስ ይላሉ ፤ ያስቀናሉ ፤ ያበሽቃሉ ። የፍቅርን ጥማት መንገድ ዳር አላፊ አግዳሚው እያያቸው እየታዘባቸው የሚወጡትን የሚያይ "አይ ፍቅር መቼ ቦታ ያስመርጥና" ብሎ ያዝንላቸዋል ፤ በየጥጉ ተቃቅፈው አፍ ለአፍ ግጥመው የሚያወሩትን የተመለከተና እሱም ፍቅር የጀመረው ይስ ይሉታል ፤ ፍቅር ጀርባዋን ያሳየችው ይቀናባቸዋል ። ልጅ ወልዶ "ለወግ ለማዕረግ" አደርሳለሁ ብሎ የሚዋትተው "አይ ስምንተኛው ሺህ" ብሎ ያዝንባቸውል ። ይበሽቅባቸዋል ። በተለያዩ ተመልካቾች የተለያየ ስሜትን የሚፈጥር የመንገድ ዳር የምሽት ትርዒት ።

ዛማኑኤልና ስንታየሁ ይህን ሁሉ እየተመለከቱ አልፈው ፤ በጨዋታ ሳይታወቃቸው ብዙ ዞረው ሲደክማቸው ስድስት ኪሎ

ቅጋል ቤንዚን ማደያ ጥግ ካለች አንዲት ቡና ቤት ገብተው ጥግ ይዘው ቁጭ አሉ ። ስንታየሁ የተቀመጠበትን ጠረጴዛ ይበይበና የቡና ቤቱ አስተናጋጅ መጣች ።

“ሁለት ቢራ … ቀዝቃዛ” አላት ፣ ቶሎ አመጣችላቸው ። ቢራቸውን እየተጎነጩ ወግ ጀመሩ ። ዛማኑኤል ፣

“ይኸውልህ ስንታየሁ” አለ በአንድ እጁ የቢራውን ጠርሙስ ይዞ በሌላው እጁ መዳፍ ግንባሩን አስመርኩዞ “እንደው ይገርመኛል … አየህ ያለንበት ኅብረተሰብ አጥንት ፣ ገንዘብና ጉልበት ሳይሆን አዕምሮ የሚገዛውና የሚዳኘው ኅብረተሰብ ቢሆን ኖሮ አንተ እና እኔ እዚህ ባልተገኘን ነበር ። ሐረገወይንን በየቀኑ አጅበን ባልተንከራተትን ነበር ። ግዴለም የእኛን ማጀብ እንተወው ፣ ምናልባት እንደ ሽርሽር ወይ እንደ መዝናናት ልንቆጥረው እንችላለን … ግን … ግን … አየህ የእሷና የዓለማየሁ አዕምሮ ባልተረበሸ ፣ ሌት ከቀን ስጋት ላይ ባልወደቀ ነበር ። ይህ እኔን እጅግ ያበሽቀኛል … ውስጤን ያበግነኛል … እውነቱን ነው የምልህ” ትክዝ አለ ። ለጥቂት ጊዜ አቀርቅሮ ቆየና ቀና አለ ። በግራ እጁ የያዘውን የቢራ ጠርሙስ ወደ አፉ አስጠጋና በረዥሙ ተጎነጨለት ። ስንታየሁ ሁኔታውን ሲከታተለው ቆየና አዳምጠኝ ለማለት ጉሮሮውን ጠራረገ ።

“ዛማኑኤል ምን መሰለህ አንተ ሁልጊዜ የምትለው ነገር አለ እኮ ፣ የሕይወት ዕጣ ነው … እውነትህን ነው ፣ አየህ በዚህ ትውልድ ላይ የተጫነ የሕይወት ዕጣ ነው ፣ ይህንን በግድ መቀበል አለብን ። ደግሞ ግዴለህም እውነትና ንጋት እያደር ነው ይባላል እኮ!”

“እይ እኔ በእሱ አላምንም እባክህ ፣ እውነትና ንጋት እያደር ነው ተብሎ የሚተረተው እኮ ፍትሕና እውነት በዘመድ ፣ በጉልበትና በገንዘብ በሚለወጡበት ኅብረተሰብ ውስጥ ነው ። ታዲያ እውነት ያው እውነት ነው ፣ ቀንና ሌሊት የለው”

“የለም የለም እንደእሱ ማለቴ እኮ አይደለም ዛማኑኤል

እንዲህ ሆኖ አይቀርም ይለወጣል ፡ ጊዜ ይፍጅ እንጂ እውነት ተደብቃ አትቀርም ለማለት ብየ ነው ።”

“እስማ ትክክል ነህ ፡ እየህ አንድ ሊታወቅ የሚገባው ጉዳይ አለ ፡ እውነቱን ውሸት ነው ብለው ሲያቀርቡልህ አዎ ልክ ነው ብለህ የምትቀበል ከሆነ ፡ ተበድለህ በደል ደረሰብኝ ተጐዳሁ ተንገላታሁ ብለህ … ፍትሕ ደጃፍ ሔደህ ፍትሕ ፍትሕ ብለህ ጮኸህ መልሰው በአንተ ላይ ሲፈርዱ ፡ “አረ ልክ አይደለም” ብለህ ከንፈርህን መጠህ የምትመለስ ከሆነ ፡ ያች የተደበቀች እውነት የምትገለጥበት ሰዓት እየራዘመ ይሔዳል ። ይህም ብቻ አይደለም አለቃ እንደሚሉት “የኢዮብን ትዕግሥት ይስጠኝ” ብለህ ሁሉንም ነገር አሜን ብለህ የምትቀበል ከሆነ … በዚህ ብቻ አይተውህም እንደ ሻይሎክ ከቂጥህ ሥጋ ልቁረስ ነው የሚሉት …”

ስንታየሁ በእንዲህ ዓይነቱ ወግ ለመግፋት አልፈለገም ፡ ቢራ ድገሙን ለማለት አጨበጨበ ። ሲያጨበጭብ ዛማኑኤል ጨዋታውን አቋረጠና ስንታየሁ ላይ አፈጠጠ ። አሳላፊዋ ሁለተኛውን ቢራ ከፍታላቸው እንደሔደች ስንታየሁ ከአጠገባቸው የተቀመጡትን ሰዎች ሰርቅ እያደረገ ተመለከተና መለስ አለ ። የጨዋታቸውን አቅጣጫ ለመለወጥ ፈለገ ።

“እኔ እምልህ ዛማኑኤል እንደው እኮ ዛሬ ነገ እጠይቅሀለሁ እያልኩ እየረሳሁት … እምልህ የአንተ ሥራ ጉዳይ … ለምን አትፈልግም … በዚህ አይነት እስከ መቼ … ሙት … ሁልጊዜ እኮ ነው የሚያሳስበኝ”

“እሱን ተወው እባክህ” አቋረጠው ዛማኑኤል ።

“እንዴ ለምን?”

ዛማኑኤል ሣቅ አለ ። አንጋጠጠና የቡና ቤቱን ቆሻሻ ጣሪያ ተመልክቶ መልሶ ጐንበስ አለ ። ፊቱ ላይ አሁንም ፈገግታ ይነበባል፡ “ያች ተደበቀች የተባለችው እውነት ስትገለጥ ነው ሥራ እምይዝ … እሷ ናት ሥራ ፈልጋ የምታስገባኝ ፡ እና እሷን

እጠብቃለሁ ።" ፈገግ አለ ። ስንታየሁ በመልሱ አልረካም ።

"የለም ይኸማ ቀልድ ነው … ሙት ቀልድ ነው"

"ቀልድ አይደለም የምሬን ነው ስንታየሁ"

"አየህ ለአንተ እንኳ ባታስብ ለሀገርህ ማሰብ አለብህ ፡ ሀገሩን የሚወድ ዜጋ በሙያው በሚችለው መስክ ተሰማርቶ እያገለገለ ወገኑን ሀገሩን መርዳት አለበት እኮ ዛማኑኤል"

"አየ ስንታየሁ" ዛማኑኤል ምስቅልቅል ሐሳብ ወረረው ። የደስታ ወይ የሐዘን የማይለይ ፈገግታ ብልጭ አደረገና መልሶ ቁዝም አለ ። "አየ ስንታየሁ ሀገሬንማ እወዳታለሁ … ሙት ሙት እወዳታለሁ እንደውም እውነቱን ልንገርህ" ድምፁን ከፍ አደረገው፡ "በሕይወቴ ብቻ ሳይሆን … በሞትም መቃብሬ ላይ የሚለብሰው አፈር ቀርቶብኝ ለሀገሬ ልማት እንዲውል የምናዘዝ ሰው ነኝ" ትንዝ አለ ።

"ታዲያ ምን ሆነህ ነው … ምን ነካህ ራስህን የማትረዳው"

"እኔ እንጃ"

"እንጃ? እንዴት እኔ እንጃ ትላለህ"

"እኔ እንጃ" … ሁለቱም ሣቁ ።

ስንታየሁ ሰዓቱን ተመለከተና ፡ "ወደዚያው ቀረብ ብንል አይሻልም ሰዓቱ ደርሷል" አለ ። ገንዘብ ከፍለው ከቡና ቤቱ ወጡ ። ቀስ እያሉ ወደ ዩኒቨርስቲ አመሩ ። ዩኒቨርስቲ በር ላይ ቆመው ጥቂት ጠበቁ ። ሐረገወይን ከአንዲት የትምህርት ቤት ጓደኛዋ ጋር መጣች ። ስታገኛቸው ደስ አላት ። ጓደኛዋን ተሰናብታ ሦስቱም ተያይዘው ታክሲ መጠበቅ ጀመሩ ። ግርግሩ የበዛ ነው ፡ ብዙ ጠብቀው አራት ኪሎ የሚያደርስ ታክሲ አግኝተው ተሳፈሩ ።

የአራት ኪሎ ትርምስ በምሽትም ያው ነው ። ከትምህርት ቤት የሚመለሰው ፡ መጠጥ ጠጥቶ ወደ ቤቱ የሚገሰግሰው ፡ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው የሚሮጠው ፡ የምሽቱን ግርግር ለማድነቅ የወጣው ፡

ሁሉም ፤ በየፊናቸው ይርመሰመሳሉ ፣ የአራት ኪሎ ሊስትሮዎች ፣ የቀንን ሥራቸውን ጨርሰው የምሽቱን ድብድባቸውን ጀምረዋል ። በቡድን በቡድን እየሆኑ ይደባደባሉ ። የሰውን መተላለፊያ ዘግተው ይሯሯጣሉ ። መፈራከሻቸው ቀን ቀን ሲሠሩበት የሚውሉት ቡርሹ የቀለም ቆርቆሮው ሳጥኑ ነው ። በቀልድ የጀመሩት የቡድን አርግጫ ቀስ እያለ ወደ ጠብ ይለወጥና ብዙ ሊስትሮ ተፈርክሶ ብዙ የሊስትሮ ሳጥን ተሰብሮ ያድራል ።

አረጋሽ እብዲቱ ኮተቷን ተሸክማ ፣ ውሾቿን አስከትላ ጣሳዋን እየደበደበች አራት ኪሎን ተሰናብታ ወደ ቤቷ ቁልቁል ትወርዳለች እየተሳደበች ። "…ማም…የማም ልጅ…ዋ…በል እስኪ… እስኪ አባክ አንተ ወለወልዳ ፣ ባይበሉብሽ ነው እምላኝህ…እንዳማሩ አይቀሩ አለች አክስቴ … ነፍሷን ያማረው… አሥራ አራት ሽልንጌን በልተህ …የት አባክ…ወለወልዳ…የውሻ አጥንት ከለከልከኝ… ቆይ…ቆይ እኔ አይደለሁም" ጣሳዋን በኃይል እያሎሸች ፣ ዙሪያውን በውሾቿ ታጅባ እየተሳደበች ፣ እየፎከረች ወረደች ፣ ወደ እሪ በከንቱ ።

እነ ሐረገወይን ከታክሲ ወርደው የፒያሳን አቅጣጫ ይዘው ትንሽ ተራመዱና ቆሙ ። ግፊው ብዙ ነው ። ጥግ ይዘው ጥቂት ቆዩና ግፊው በረድ ሲል ወደ መንገዱ ተጠጉ ። አንዲት ታክሲ እየከነፈች መጣችና ከእነሱ ራቅ ብላ ቆመች ። ስንታየሁ እየሮጠ ተከተላት ። ዛማኑኤልና ሐረገወይን እጅ ለእጅ ተያይዘው እየተጓተቱ በኋላ ይሮጣሉ ። ስንታየሁ አልቀናውም ፣ ሌሎች ሰዎች ቀደሙት ። ብሽቅ አለና ቆመ ። ሌላ ባዶ ታክሲ እየተንከራከሰች መጥታ ከእርሱ አለፍ አለችና ቆመች ። እንዳይቀደም እየሮጠ ተከተላት ። ሐረገወይንና ዛማኑኤል እንደተያያዙ ሲከተሉት ድንገት ከፍተኛ የግጭት ድምፅ ተሰማ ። ሐረገወይን ክው ብላ ቀረች ።

ክንዷን አቅፎ የነበረው የዛማኑኤል እጅ የለም ። ዞር አለች የድንጋጤዋን ። ዛማኑኤል መንገዱ ላይ ተዘርሮአል ። 'ኡኡ' ብላ ጮኸች ። ዛማኑኤልን ከገጨችው ፒጆ መኪና ሁለት ሰዎች

እየተቻኮሉ ወረዱና ሐረገወይንን አፋፍሰው ታቅፈው መኪናዋ ውስጥ አስገቧት ። የሙት ሙቷን ትፈራገጣለች ። እፍን ያፈናትን ሰው ፊት በጥፍሯ ቧጨረችና አስለቀቀችው ። ከመኪናዋ የኋላ መቀመጫ ወረወሯት ። እየጮኸች ትታገላለች ። ጠላፊዎቹ የመኪናዋን በር ዘጉና ከፍተኛ የጥሩር ጩኸት አሰምተው ወደ ፒያሳ አቅጣጫ ሲሸመጥጡ ሁለት ጥይት ተከታትሎ ተተኮሰ ። የመኪናዋ ሁለት የኋላ ጎማዎች ለጥ አሉና መኪናዋ ሲጥጥጥ የሚል ድምፅ አሰምታ ወደ ኋላዋ አጉንብሳ ቆመች ።

ስንታየሁ ሽጉጡን በቀኝ እጁ እንደያዘ ወደ መኪናዋ ሮጠ፡ መኪናዋ ውስጥ የነበሩት ሰዎች ከመኪናዋ ወጥተው ሽሽት ጀምረዋል ። ሐረገወይን ተንጋላ ታቃስታለች ። ስንታየሁ የመኪናዋን በር በረገደና ጉትቶ አወጣት ። ትኩር ብላ ተመለከተችው ፡ በድንጋጤ የከሰለው ፊቷ መልኳን ለውጦታል ፡ ስንታየሁ መሆኑን ስታውቅ እንደ ሕፃን ልጅ ተጠመጠመችበት ። ቁና ቁና ትተነፍሳለች ። ዐይኗ ፍጥጥ ብሏል ። ከማቃሰት በቀር መናገር አቃታት ።

ወዲያው ሁለት የፖሊስ መኪናዎች መጡ ። ስንታየሁ የሐረገወይንን እጅ ጨብጦ እየጐተተ ወደ ተሰበሰቡት ሰዎች ይዞአት ሔደ ። ዛማኑኤል በደም ተበክሎአል ። ፖሊሶች የተሰበሰበውን ሰው እያባረሩ አደጋ በደረሰበት አካባቢ ምልክት አደረጉና ዛማኑኤልን አቅፈው መኪና ውስጥ አስገቡት ። ስንታየሁ የሐረገወይንን እጅ እንደያዘ ወደ ፖሊሶቹ አዛዥ ጠጋ አለና የሆነ ነገር ሹክ አለው ። የፖሊሶቹ አለቃ በመገረም ተመለከተውና “እሺ እናንተም ግቡ” አለ። ሐረገወይንና ስንታየሁ ዛማኑኤልን በጫኑበት መኪና ተሳፈሩ። ድንጋጤ ወሮአቸዋል ። ከንፈራቸው ድርቅ ብሎ ፈዘዋል ።

የፖሊሷ መኪና የአራት ኪሎን ሐውልት ተጠምዝዛ የአደጋ ምልክት እያሳየች ወደ ስድስት ኪሎ ተፈተለከች ። የስድስት ኪሎን ሐውልት ዞራ ሆስፒታል ውስጥ ገባች ። ዛማኑኤልን ተሸክመው አውርደው ወደ ድንገተኛ ክፍል ይዘውት ሮጡ ። ሐረገወይን አሁንም እንደደነገጠች ናት ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዛማኑኤልን ከድንገተኛ ክፍል አወጡት ። ሦስት ነርሶች ዙሪያውን አጅበው በተሽከርካሪ አልጋ እንጋለውታል ፣ ዓይኖቹ እንጂ ፊቱ አይታይም ፣ በፋሻ ተጠቅልሎአል ። ተሽከርካሪውን ጋሪ እየገፉ ወሰዱና አንድ ክፍል ውስጥ አስገቡት ። ፖሊሶቹ ይራወጣሉ ። ስንታየሁ የሚያደርገውን አጥቶ ይራወጣል ፣ ወደ ክፍሉ ጠጋ ሲል ፣ ነርሶቹ አንዷ "ይቅርታ መግባት አይፈቀድም …ዶክተሩ እስኪመጡ ቆዩ…" ብላ አስደነገጠችው ።

ዶክተሩ መጥተው ከተመለከቱትና መድኃኒት አዘውለት ከወጡ በኋላ ፣ ስንታየሁና ሐረገወይን ገብተው እንዲያዩት ተፈቀደላቸው ። ዐይኖቹ ቀልተው ያስፈራራሉ ፣ ሐረገወይን ዛማኑኤልን ስትመለከት ድንጋጤዋ ገሸሽ እያለላት ራሷን እያወቀች ሔደች ። ጩኸትና ልቅሶ ማቆም አቃታት ። ስንታየሁ ቢቆጣትም ማቆም አልቻለችም። አዲስ ተረጂ ሆና ቁጭ አለች ። ዛማኑኤል ዙሪያውን ገልመጥ ገልመጥ አደረገና እጆቹን አውጥቶ ሐረገወይንን ያዝ አደረጋት ። ለመናገር እየቃጣ ያዳግተውና ዝም ይላል ። ዐይኖቹ የሚናገሩ ቢሆኑ ብዙ በተናገረ ። አንዴ ሐረገወይንን ፣ አንዴ ስንታየሁን እያፈራረቀ ሲመለከታቸው ቆየ ፣ ለመናገር አቅም አጠረው ። ብዙ ጠበቁት ። አምጦ አምጦ ኃይል ሰበሰበ ፣ የሐረገወይንን እጅ ወደደረቱ ሳብ አደረገና ተመለከታት ።

"ሐሪዬ አይዞሽ …ምንም አልሆን …" ሐረገወይን ዕንባዋን መቆጣጠር አልቻለችም ። ዛማኑኤል ደረት ላይ የተለጠፈውን እጁን አንሣችና መሬቱ ላይ ተዘረረች ። ስንታየሁ የግድ አንሣት ።

"ሐሪዬ … አይዞሽ …አልኩሽ" ቁርጥ ቁርጥ የሚለውን የዛማኑኤልን ድምፅ በግንባሯ ተደፍታ ማዳመጥ ያዘች…"አይዞሽ… ለእኔ አትዘኚ እኛ የአዲስ ትውልድ ተምሳሌቶች ነን … በአሮጌ አስተሳሰብ አረም ተከበን ለማበብ የምንፍጨረጨር እምቡጦች ነን …ለሌላው ብርሃንን እየሰጠች እራሷ እየነደደች…ሟሽሻ እንደምታልቀው ሻማ ያለን ፍጡሮች ነን … እኛ የመጭው አዲስ

በርግደን የምንገባ ፋና ወጊዎች ነን… እያዟችሁ ለእኔ አያታዘንም…ግን ሁለት ነገር አደራ እላችሁአለሁ …ብድንም ብሞትም እጠይቃችሁአለሁ ።”

ሐረገወይን ከተደፋችበት ቀና አለች ፡ ብርግግ ብላ ተነሣችና አልጋው ጠርዝ ላይ እጆቿን አስመርኩዛ ቁልቁል ትኩር ብላ ትመለከተው ገባ …

“አዎ አደራዬ ቀለበቱ እንዳይቀር …አደራ… በሕይወት ካለሁ መጥታችሁ ንገሩኝ…ይኸ አንዱ አደራዬ ነው” ለጥቂት ጊዜ ዝም ብሎ ቆየ ። “አይዞአችሁ እኔ መውደቄን አትዩ ያሸነፍነው እኛ ነን ፡ ግን ቀለበቱን አደራ” ደሞ ዝም አለና ቆየ…“ሐሬዬ ሁለተኛው አደራዬ ዘ… ዘነበች ናት… ድሀ ናት ምስኪን… እርጉዝ ናት ። አዎ ሐሬ… የእኔ ልጅ ነው…”

ሆስፒታል በገባ ልክ በ15 ቀኑ ድኖ ወጣ ።

አበቃ ።

* * *

የጠለቀች ፀሐይ መልሳ ትወጣለች ፤ የረገፈች አበባ መልሳ ታብባለች ፤ እኔ ሕይወት ግን ቀናተኛ ናት ፤ አንዴ ጨልሜም ፣ ከጨለምኩ ግን ዳግም ብርሃኔ አይታይም'' ብላ ታስፈራራለች ። ግን ምን ዋጋ ፤ ሩህሩህ ናት ። በሯን ሲያንኳኩ ቶሎ አትከፍትም ታስጠብቃለች ፤ ታናድዳለች ። እልህ ታስጨርሳለች ''ደግማችሁ በር ምቱ ፤ በሩም ይከፈትላችኋል'' ትላለች ። አቤት ከበሬታዋ መስተንግዶዋ ! አቤት ርህራሔዋ ! አቤት ጭንቀቷ !

* * *

…ዓለምም እንዲሁ ናት ፤ ሲያዝኑ አብራ እምታዝን ፤ ሲደሰቱ አብራ እምትደሰት ። ዓለማችን የብዙ ምስቅልቅል ሁኔታዎች ቅርጫት ናት ። የሥልጣኔ ፤ የድህነት ፤ የክፋት ፤ የቅንነት ፤ የአምባገነንነት ፤ የጉልበት ፤ የርህራሔ ፤ የስሜት ፤ የጥበብ ፤ የሞኝነት ፤ የጅላጅልነት ፤ የፍርሃት የጀግንነት ማጠራቀሚያ ቅርጫት ናት ። እና እነዚሁሉ አንድ ጊዜ እርስ በርስ እየተጋጩ ሌላ ጊዜ እርስ በርስ እየተስማሙ ይኖራሉ ። ሲፋቀሩ ፀጥ ትላለች ፤ ሲጋጩ ማዕበል ያናውጣታል ።

* * *

… እነሆ ፈረንሳዮች አንድ የተለመደ አባባል አላቸው ። ''ትላልቆች ትልልቆ የሚመስሉን ቁጭ ብለን ስለምናያቸው ነው እንነሣ'' ይላሉ ። በእውነት ትክክለኛ አባባል ነው ። እነሆ እንደ ሐምሌ ደመና ተቆልለው ከፍተው ትልቅ የሚመስሉን ቀና ብለን ስላላየናቸው ነው ። ግን ሁላችሁ እምቢታችሁን ልንላቸው ይገባል …

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

[illegible]

ዋጋው ብር 5